# ዐፄ ዮሐንስ

## እና

# የኢትዮጵያ አንድነት

በ

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

፲፱፻፹፪

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
Kuraz Publishing Agency

ስልክ / Tel. 11 27 19
ፖስታ ሣ. ቁ. / P. O. Box 30933

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ADDIS ABABA
Ethiopia

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ።
All Rights Reserved

የሽፋን ሥዕል — በቦሌ ማተሚያ ቤት

በቦሌ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

# ማውጫ

ተራ ቁ. — አርዕስት — ገጽ

1. መቅድም ........ 9
2. ምስጋና ........ 17

ምዕራፍ አንድ
ነዋሪው የአነጋገሥ ወግና ሥርዓት መጥፋት ........ 19

ምዕራፍ ሁለት
የዋግ ሹም ጉበዜ አነጋገሥ — ለእንግሊዝና ለፈረንሣይ መንግሥታት የጻፉዋቸው ደብዳቤዎች ፡ከደጃዝማች በዝብዝ ካሣ ጋር ተዋግተው ስለ መሸነፋቸው ........ 23

ምዕራፍ ሦስት
የደጃች ካሳ ምርጫ ንጉሠ ነገሥትነት — ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር የተለዋወጢቸው የወዳጅነት ደብዳቤዎች ........ 41

ምዕራፍ አራት
የዙፋን ባላንጣዎች ያፄ ዮሐንስና የንጉሥ ምኒልክ ፉክክር በወዳጅ ጠላት ፊት ........ 57

ምዕራፍ አምስት
ንጉሥ ምኒልክ በሸዋና በወሎ የሥልጣናቸው መጠናከር—አሳዛኙ የአቶ በዛብህ አሟሟት ........ 71

ምዕራፍ ስድስት
በመዠመሪያዎቹ የንግሥ ዓመታት በዐፄ ዮሐንስ ፊት የተደቀኑ የማሳመን ችግሮች—የካቶሊኮች አቅዋም ........ 79

ምዕራፍ ሰባት
በከዲቭ እስማኤል የሚመራው የግብጽ መንግሥት በአዲስ መልክ መቋቋም ........ 91

ምዕራፍ ስምንት
የግብጽ ጦር ምጥዋ ከገባ በኋላ ፥ ቦጎስን ስለመውረሩ—የከዲቭ እስማኤል በኢትዮጵያ ላይ የመስፋፋት ምኞት ........ 97

ምዕራፍ ዘጠኝ
የበጎስና ያካባቢው ወረዳ ኢትዮጵያዊነት ........ 103

ምዕራፍ ዐሥር
ከጦርነት በፊት የዐፄ ዮሐንስ ሰላማዊ ስሞታ ለአውሮፓ ኃያላን .. 109

ምዕራፍ ዐሥራ አንድ
ከስሞታ በኋላ የመዠመሪያው ጦርነት—የሙንሲንጀር ፓሻ ፍጻሜ . 131

ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት
ሁለተኛው ጦርነትና የኢትዮጵያ ድል አይቀሬነት 143

ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት
በግብጾችና በዐፄ ዮሐንስ መካከል የምኒልክ አቅዋም .......... 153

ምዕራፍ ዐሥራ አራት
ተንጠልጥሎ የቀረው የሰላም ውል .................. 163

ምዕራፍ ዐሥራ አምስት
ለሥልጣን ጨበጣ የጦር መሣሪያ፦መፍትሔነት—የንጉሥ ምኒልክ ለዐፄ ዮሐንስ መገበር ............................ 171

ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት
የሃይማኖት ክርክር በቦሩ ሜዳ — የመሐመድ ዐሊና የይማም በመጀ ክርስትና መነሣት—እስላሞች ክርስትና እንዲነሡ ስለ መገደዳቸው .. 197

ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት
የንጉሥ ምኒልክና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጠብ ፤ የንጉሠ ነገሥቱ የዳኛ ገላጋይነት ............................ 203

ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት
በእምባቦ የንጉሥ ምኒልክና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጦርነት -- የን ጉሥ ምኒልክ ማሸነፍ ........................... 209

ምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ
የአሸናፊ በኀ አድራጊ — የንጉሥ ምኒልክና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጉዞ ወደ እንጦጦ ፤ ወረይሉ ላይ ከዔ ዮሐንስ ተገናኝተው በሁለቱም ላይ የደረሰው ቅጣት .......................... 219

ምዕራፍ ሐያ
የራስ አርአያና የወይዘሮ ዘውዲቱ የጋብቻ መሣሪያነት — የእምባቦው ጦርነት ያስከተለው ውዝግብ — የወሎ ግዛት ከምኒልክ እጅ ወጥቶ በንጉሠ ነገሥቱ ቁጥጥር ውስጥ መግባት .................. 227

ምዕራፍ ሐያ አንድ
የግብፅ መንግሥት አወዳደቅ—ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀራረብ ያደረገው ሙከራ ................................... 235

ምዕራፍ ሐያ ሁለት
የጐርዶን አሟሟት በሎንደን ስለመሰማቱ—ያፄ ዮሐንስ ተከታታይ ስሞታ ለአውሮፓ ኃያላን—የእንግሊዝ መንግሥት የተጠቃሚነት ችሎታ ... 251

ምዕራፍ ሐያ ሦስት
በሪር አድሚራል ሔዊት አማካይነት የእንግሊዝ ፥የኢትዮጵያና የግብጽ ስምምነት ................................. 267

ምዕራፍ ሐያ አራት
በሔዊት ውል ያፄ ዮሐንስ ጊዜያዊ ደስታና አሳሳች ድል —ራስ አሉላ በኩፊት ከደርቡሾች ተዋግተው ግብጾቹን ስለ ማስለቀቃቸው ..... 275

ምዕራፍ ሐያ አምስት
የሐረርጌ ከኢትዮጵያ ጋር መዋሐድ .................. 285

ምዕራፍ ሐያ ስድስት
የደጃች ኃይሉና የደጃች ወልደ ሚካኤል የዘር አንድነት—የባላባቶቹ የሥልጣን ፍልሚያ ............................ 305

ምዕራፍ ሐያ ሰባት
ደጃች ኃይሉና ራስ ባርያው ከደጃች ወልደ ሚካኤል ጋር በየተራ ተዋግተው እንደ ሞቱ ፥ የሻለቃ አሉላ እንግዳ መሾም ፥ የራስ ወልደ ሚካኤል ከምሕረት በኋላ እስራት ......................... 311

ምዕራፍ ሐያ ስምንት
የዐፄ ዮሐንስና የኢጣልያ መንግሥት የመገናኛው ግንኙነት ... 321

ምዕራፍ ሐያ ዘጠኝ
የኢጣሊያ መንግሥት የመዠመሪያው አገባብ በአሰብ ........ 331

ምዕራፍ ሠላሳ
አፍሪካን በሰላም ለመከፋፈል ቤርሊን ላይ የአውሮፓ ኃያላን ያደረጉት ስምምነት........................... 337

ምዕራፍ ሠላሳ አንድ
ቅኝ ግዛት የማግኘቱ ጉዳይ በኢጣልያ ምክር ቤት ያስከተለው ውዝግብ 343

ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት
ስለ ምጥዋ ወደብ ፥ የኢጣልያ ጦር ምጥዋ መግባትና መስፋፋት .... 347

ምዕራፍ ሠላሳ ሦስት
በምጥዋ መያዝ የኢጣልያና የእንግሊዝ መንግሥት ውስጠ ስምምነት ፥ የቱርክ መንግሥትና የኢትዮጵያ ተቃውሞ ................ 357

ምዕራፍ ሠላሳ አራት
የካፒቴን ሐረሰን ስሚዝ ወደ መቀሌ መምጣት ፥ ከራስ አሉላ ጋር የተመላለሱት ቃል ፥ የንጉሥ ነገሥቱ የስሞታ ደብዳቤ ለንግሥት ቪክቶሪያ ................................. 367

ምዕራፍ ሠላሳ አምስት
በዶጋሊ ጦርነት ዋዜማ የኢጣልያኖች የማታለል ዘዴ ፥ በባላባቶቹ ፍልሚያ መካከል የውስጥ አንድነታችን መላላት ፥ የነባሊምቤኒ ስላይነት ፥ የፈረንሣዮች ኢትዮጵያን ደጋፊነት ............... 375

ምዕራፍ ሠላሳ ስድስት
የዶጋሊ ጦርነትና የራስ አሉላ አሸናፊነት ................. 383

**ምዕራፍ ሠላሳ ሰባት**
ያፄ ዮሐንስ የስምታ ደብዳቤ ለእንግሊዝ መንግሥት—በገርራር ፖርታል አማካይነት የመጣው አሳዛኝ ደብዳቤ ........ 403

**ምዕራፍ ሠላሳ ስምንት**
የምኒልክ ኃይል እየተጠናከረ መሔድ — በምጥዋ መያዝና በዶጋሊ ጦርነት ንጉሡ የነበራቸው አቅዋም ........ 425

**ምዕራፍ ሠላሳ ዘጠኝ**
በኢጣልያና ባፄ ዮሐንስ መካከል ያምኒልክ ያስታራቂነት አሳብ አለ መሳካት — ለፈረንሳይ ፕሬዚዳንት የተላኩት የስምታ ደብዳቤዎች ፍሬቢስነት ........ 433

**ምዕራፍ ዐርባ**
የደርቡሾች አጥቂነት—የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በደርቡሾች መሸነፍ የጐንደር ዘረፋና ቃጠሎ ........ 447

**ምዕራፍ ዐርባ አንድ**
በዮሐንስና በምኒልክ መካከል የተዳፈነው ጠብ — የንጉሥ ምኒልክ ጉዞ ወደ ወሎና ወደ ቤጌምድር—ታላቅ ሰልፍ በአዘዞ ........ 457

**ምዕራፍ ዐርባ ሁለት**
ባፄ ዮሐንስ ውስጥ ያሉ መሳፍንትና መኳንንት — ንጉሡ ነገሥቱ በክተት ዐዋጅ ወደ ሰሐጢ ያደረጉት ጉዞ ፤ የጐንደርን መቃጠል ስለመስማታቸው ........ 469

**ምዕራፍ ዐርባ ሦስት**
ዐፄ ዮሐንስ ስለ ዕርቅ ጉዳይ ከጄኔራል ሳን ማርሳኖ ጋር የተለዋወጡዋቸው ደብዳቤዎች ........ 475

**ምዕራፍ ዐርባ አራት**
የዐፄ ዮሐንስ ከሰሐጢ ወደ መቀሌ መመለስ — የመንግሥታቸው መዳከም—ከደርቡሾች ጋር የሞከሩት መቀራረብ አለመሳካት ...... 485

**ምዕራፍ ዐርባ አምስት**
የንጉሥ ምኒልክ ጉዞ ወደ ጐጃም—የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና የንጉሥ ምኒልክ ዐፄ ዮሐንስን መክዳት — የደጃች ሥዩም ወደሸዋ መምጣት 493

**ምዕራፍ ዐርባ ስድስት**
ዐፄ ዮሐንስ ጐጃምን ስለ መውረራቸው ፤ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንደገና ታምነው በዕርቅ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ስለ መግባታቸው ... 503

**ምዕራፍ ዐርባ ሰባት**
የንጉሥ ምኒልክና የኢጣልያ መንግሥት ወዳጅነት እየጠበቀ መሔድ 509

**ምዕራፍ ዐርባ ስምንት**
በሸዋ የተጠንቀቅ ዐዋጅ — ያፄ ዮሐንስና የንጉሥ ምኒልክ በደብዳቤ መወቃቀስ ........ 517

**ምዕራፍ ዐርባ ዘጠኝ**
በዐፄ ዮሐንስና በሐምዳን አቡ አንጋ መካከል የተደረገ የደብዳቤ ልውውጥ ........ 529

**ምዕራፍ ሃምሳ**
ያፄ ዮሐንስ ጉዞ ወደ መተማ—የጦር ድርጅታቸው ........ 535

**ምዕራፍ ሃምሳ አንድ**
የመተማ ጦርነትና ያመራር ጉድለት—ያፄ ዮሐንስ አሳዛኝ ሞት .... 541

**ምዕራፍ ሃምሳ ሁለት**
የደርቡሾች አሸናፊነትና የዘኪ ቱማል ድንፋታና ውድቀት—የከሊፋ አብዱላሂ ፍጻሜ ........ 553

**ምዕራፍ ሃምሳ ሦስት**
ያፄ ዮሐንስ ሞት ያስከተለው የዙፋን ባላንጣነት—በባላንጣነቱ ፊት የተጠቀሙት ወገኖች ........ 559

# መቅድም

“ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት” በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ለሰባ ዓመታት የበታተናትን የመሳፍንት አገዛዝ በጦር ኃይል ደምስሰው ፣ የኢትዮጵያን ማዕከላዊ መንግሥት የሚያበሥረውን የአንድነት መሠረት ባዲስ መልክ የጣሉበት ሁኔታ ተዘርዝሮ ይገኛል ። እዚህ ላይ በውል ሊጤን የሚገባ አንድ ዓቢይ ነጥብ አለ ። ይኸውም ኢትዮጵያ በሕዝቧ አንድነት ዳር ድንበሯ ታፍሮና ነጻነቷ ተከብሮ ለረጅም ዘመናት የኖረች አገር ፣ ገናና ታሪኳም በዓለም ዙሪያ ሲያስተጋባ የቆየ መሆኑ ነው ። ነገር ግን ከላይ እንደ ተጠቀሰው ፣ የመሳፍንት አገዛዝ በታሪኳ ላይ ጥቁር ነጥብ ጥሎ ስለ ነበር ፣ ያን አስከፊ የታሪክ ገጽታ ለማስወገድ የዐፄ ቴዎድሮስ መነሣት ወሳኝ ድርሻ ነበረው ። ሆኖም ፣ ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት የሚለው ሥያሜ የሚጠቁመው ፣ የኢትዮጵያን አንድነትና የዘመናት እኩሪ ታሪኳን እንደገና የማደስ እንጂ ፣ ፍጹም አዲስ የሆነ ምሥረታ ያለመሆኑን መገንዘብ ያሻል ።

በዚህ በአሁኑ መጽሐፍ ደግሞ ፣ የአንድነት መሥራች ቴዎድሮስ ሕይወታቸውን በፈቃዳቸው በመቅደላ ተራራ ከአሳለፉ ወዲህ ፣ እርሳቸው በጣሉት የአንድነት ሕንፃ መሠረት ላይ ከርሳቸው በኋላ ተነሥተው ከብዙ የፍልሚያ ፍጅት በኋላ ፣ በየተራ የነገሡት ሦስት አውራ መሪዎች ግድግዳውን ለማቆም ፣ ጣራውን ለማዋቀር ከነሕዝባቸው ያደረጉት ተጋድሎ ይገኛል ።

እነዚህም ፣ የላስታው ዋግሹም ጐበዜ ገብረ መድኅን ፣ የተምቤኑ ደጃች ካሣ ምርጫ ፣ የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ኃይለ መለኮት ናቸው ። ሦስቱም በሽፍትነታቸው ሰዓት የሥጋት ዐይናቸው ያተኰረው በኃይለኛው ባባ ታጠቅ የበላይ አጥቂነት ላይ ሳለ ፣ የርሳቸው ሕይወት ማለፉ ሲረጋገጥ ፣ የመንፈስ ዕረፍት አግኝተው ትንሽ ጊዜ ከተጽናኑ በኋላ ወዲያው ሦስቱ የዙፋን ተፋላሚ ሆነው ፣ እርስ በርሳቸው በጠብ እየተያዩ ‘ተከታይ እኔ ነኝ ፣ አንተ አይደለህም’ በሚል ዓላማ ኃይላቸውን ይገማመቱ ዠመር ። ለክፋም ፣ ለደጉም ሦስቱም የየክፍለ ሀገራቸው ሕዝብ ይነስ ይብዛ ተከትሏቸዋል ።

ከሦስቱ ተፋላሚዎች አንዱ ምኒልክ ፣ ከቴዎድሮስ ሞት ቀደም ብለው በ1857 ዓ.ም. ካፄ ቴዎድሮስ ቁጥጥር አምልጠው አቶ በዛብ

ህን በጋዲሎ (ግድም ወረዳ) አሸንፈው ፣ አንኰበር ገብተው እንደ አባቶቻቸው የሸዋ ንጉሥ እየተባሉ ከቆዩ ወዲህ ፣ በ1860 ዓ.ም. ያፄ ቴዎድሮስን ሞት ሲሰሙ ፣ 'ከይሁዳ ነገዶች ከዳዊትና ከሰሎሞን የምወለደው እኔ ነኝ ፣ ለንጉሠ ነገሥታዊው ዙፋን ከኔ የሚቀርብ የለም' በሚል ስሜት ፣ “ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ፣ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት” የሚል ማኅተም አሠርተው ፣ ካገር ውስጥም ከውጭ አገርም መሪዎች ጋር ይጻጻፉ ዠመር ።

ይሁን እንጂ ፣ ከሸዋና ከወሎ በቀር መላ ኢትዮጵያን በቁጥጥራቸው ውስጥ እንዳላገቡ ልባቸው ዕለሚያውቀው ፣ በማኅተማቸው ላይ “ንጉሠ ነገሥት” ከሚለው ጽሑፍ ቀጥሎ “ዘኢትዮጵያ” የሚለውን ደምዳሚ ቃል ለመጨመር አልደፈሩም ። ለውጭ አገር መሪዎችም ሲጽፉ አርእስታቸው ፣ “የተላከ ከንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ዘኢትዮጵያ” የኢትዮጵያው ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት እንጂ ፣ “ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ” ይኸውም ማለት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አላሉም ። የሁለቱ ዐረፍተ ነገሮች አባባል ልዩነት አለው ።

ሁለተኛው የዙፋን ተፋላሚ ፣ ከዛጉዬ ዘር የወረዱት ዋግሹም ጐበዜ የክፍለ ሀገራቸውን የዋግን ፣ የላስታንና የአካባቢውን ሕዝብ ካስተባበሩ በኋላ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ ከመሞታቸው ከዐሥር ቀን በፊት በመጋቢት 22 ቀን 1860 ዓ.ም. በደንቢያ ፣ በወልቃኢት ፣ በጸገዴ የተነሣውን ጣሰው (ጥሶ) ጐበዜን በለሳ ላይ ተዋግተው አሸንፈውት ስለ ነበረና እንግሊዞችም መቅደላን ለቀው ወደ አገራቸው ስለ ተመለሱ ፣ ዋናው መዲና (መናገሻ ከተማ) ጐንደርም በርሳቸው እጅ ስለገባ ቀብቶ የሚያነግሥ ጳጳስ ባጠገባቸው ቢጠፉም ፣ በራሳቸው ፈቃድ በእጨጌ ገብረ ኢየሱስ እጅ ተቀብተው ስማቸውን ተክለ ጊዮርጊስ አሰኝተው በ1860 ዓ./ም. ነገሡ ።

ሦስተኛው የዙፋን ባላንጣ ፣ በእናታቸው በኩል ከስመ ጥሩው የእንደርታ ባላባት ከራስ ወልደ ሥላሴ ፣ ባባታቸው ከተምቤን ባላባት ከሹም ተምቤን ምርጫ የሚወለዱት ደጃዝማች ካሳ ምርጫ (በዝብዝ ካሳ) ናቸው ። እርሳቸውም ባፄ ቴዎድሮስ ጊዜ የባላምባራስነት ማዕረግ ይዘው ለተወሰነ ጊዜ ከቆዩ በኋላ ካፄ ቴዎድሮስ ሸፈቱ ። በመቅደላ ጦርነት ዋዜማ ላይ እንግሊዞችን ላስተናገዱበት ውለታ ዘመናዊ መሣሪያ ከነአሠልጣኙ ስላገኙ ፣ በትግሬም ቀደም ብለው የንጉሠ ነገሥቱን እንደራሴ ራስ ባርያው ገብረ ጻድቅን በደብረሲና አሸነፉ ። ኃይላቸውም ከዕለት ወደ ዕለት እየጠነከረ መጣ ። አዲሱ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ምንም እንኳ የካሳን እህት ወይዘሮ ድንቅነሽ ምርጫን አግብተው ቢነግሡና ካሳም የመዠመሪያውን ዓመት በተክለ ጊዮርጊስ ሥር ቢቆዩ ፣ ኃይላቸው ሲፈቅድላቸው አልታዘዝም በማለት ራሳቸውን



ችለው ተቀመጡ ። ስለዚህ አንዲቷ ኢትዮጵያ በዚህ ጊዜ (1860—63) ዓ ም የሦስት መሪዎች ግዛት ነበረች ለማለት ያስደፍራል ። የኢትዮጵያን ደቡባዊውን ክፍል ብንመለከት ፣ እያንዳንዱ ነገድ ከግራኝ አህመድ ወረራ ፍጻሜ ወዲህ የየራሱን ንጉሥ ወይም ቀንደኛና ትክለኛ ባላባት አበጅቶ እርስ በርሱ እየተዋጋም ፣ እየታረቀም ከማዕከላዊው መንግሥት ተለይቶ ይተዳደር ነበር ።

አገሪቱ መቸም ከራሷ በራሷ የእጅ ጥበበኞች የምታፈራው የጦር መሣሪያ ከጦርና ከጐራዴ ፣ ከጨቤና ከአንካሴ ስለማያልፍ ፣ በዚህ ጊዜ ባላንጣን የማጥቂያውና ሥልጣን የመጨበጫው ዋና መፍትሔ በውጭ አገር የሚሠራው ፣ በባሩድ ጥይት የሚተኮሰው ጠበንጃና መድፍ ነበር ። ዤኔራል ናፒየር ካገሩ ሲመጣና ወዳገሩ ሲመለስ ደጃች ካሳ ላደረጉለት መስተንግዶና አቀባበል 12 መድፍ ፣ 900 ጠበንጃና ብዙ ጥይት ፣ ከእንግሊዛዊው አሠልጣኝ ከኪርክሃም ጋር ሰጥቷቸው ስለነበር በዚህ በዘመናዊ መሣሪያ በ1863 ዓ ም ዐድዋ አጠገብ እርሳቸውን ለማሳመን የዘመቱባቸውን ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስን አሸንፈው ማርከው ካሰሩ በኋላ ከእስክንድርያ ባስመጧቸው ጳጳስ በአቡነ አትናቴዎስ እጅ ተቀብተው ፣ በጥንታዊቷ በአክሱም ከተማ ስማቸውን “ዮሐንስ አራተኛ” አሰኝተው በሥርዐተ መንግሥት በ1864 ዓ. ም. ነገሡ ። አሁን ደግሞ ከሦስቱ የዙፋን ባላንጣዎች ሁለቱ ዮሐንስና ምኒልክ ስለቀሩ ሲዛዛቱ ፣ ሲሰላለሉ ፣ የጦር ሠራዊታቸውን በየቤታቸው ሲያጠናክሩ በመካከል ያሉትን የወሎን ፣ የቤገምድርን ፣ የአማራ ሳይንትን ፣ የጐጃምን ባላባቶችና አስተዳዳሪዎች በማስፈራራትም ፣ በወዳጅነትም ወደ ራሳቸው ለመሳብ ሲጣጣሩ ፣ ከ1860 እስከ 1870 ዓ ም ያለውን ያሥር ዓመት ጊዜ አሳለፉ ።

በዚህ ጊዜ አንደኛ የሁለቱ መከፋፈል ፣ ሁለተኛ የኢትዮጵያ በሥልጣኔ ኋላ ቀርነት ፣ ሦስተኛ የስዊዝ ቦይ መከፈት አደፋፍሮት የግብጽ መሪ ከዲቭ ኢስማኢል ብዛት ያላቸውን የአውሮፓ ተወላጆች በገንዘብ እየቀጠረና የፓሻነት ማዕረግ እየሰጠ ፣ በግብጹ ወታደር ላይ መሪ በማድረግ ራሱ በቱርክ ሡልጣን ከመገዛት ሳይድን ኢትዮጵያን በጦር ኃይል ወሮ ፣ ከሱዳንና ከሱማሊያ ጋር በመደባለቅ ግዛቱን ከሜዲተራኒ ባሕር እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ለማድረስ ሰፋ ያለ ምኞት አደረበት ። ይህ ሰፊ ምኞት አያዋጣህም ፣ በከንቱ አትከሰር የሚለው የዘመድ መካሪም አላገኘም ። ይልቁንም ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ 'ይገባሃል ያስፈልግሃል ፣ ግፋ በርታ' የሚሉት የውጭና ያገር ተወላጆች በረከቱለት ።

ይኸን የወረራ ምኞቱን ወደ ፍጻሜ ለማድረስ በ1866 ዓ.ም. በኅዳር ወር ጉንደት ላይ ፣ በ1868 ዓ.ም. በየካቲት ወር ጉራዕ ላይ ወታደር ልኮ ሁለት ጊዜም ያልሠለጠነ መንጋ ወታደር ነው ብሎ

በናቀው በዐፄ ዮሐንስ ጦር ድል ተመታ ። ስለዚህ ፣ ዐፄ ዮሐንስ ከጄኔራል ናፒየር የተቀበሉትን የጦር መሣሪያ ባገር ውስጥ ጦርነትና የውጭን ጠላት ለመመለስ ተጠቅመውበታል ማለት ነው ። ይህም በግብጾች ላይ የተገኘው ተደጋጋሚ ድል ላፄ ዮሐንስ ባገር ውስጥና በውጭም ከፍ ያለ ዝናን አተረፈላቸው ። የጦር ሠራዊታቸውም አንደኛ ከእንግሊዞች በስጦታ በአገኙት ፣ ሁለተኛ ካፄ ተክለ ጊዮርጊስና ከግብጽ የጦር ሠራዊት በምርኮ በሰበሰቡት የጦር መሣሪያ ኃይላቸው በጣም ስለ ደረጀ ፣ የርሳቸውም ጦር በነገርን ኪርከሃም በጦርነት ቴክኒክ ሠልጥኖ ስለ ታጠቀ ፣ ከዐድዋ ተነሥተው ፊታቸውን ወደሸዋ መልሰው ሰላሌ በደረሱ ጊዜ ፣ ምኒልክ በዚህ ዐይነትና የጊዜ ወቅት ውጊያው እንደማያዋጣ ሁኔታውን ገምግመው በዕርቅና በሰላም ገቡላቸው ። ስለዚህ አቅምን ማመዛዘን ስጦታቸው የሆነው ንጉሥ ምኒልክ ፣ ነገሩ ቢቆጫቸውም በቤተ ክህነት አባቶች የግልግል አማካይነት ‘ንጉሠ ነገሥት’ የሚለውን ሥያሜ ለዮሐንስ ለቀው ፣ በሸዋ ንጉሥነት ሰመርጋት የተስማሙት ከግብጾች ድል መመታት በኋላ ነው ።

በጀግኖቿ ብርታት በሁለት ጊዜ ድል አድራጊነት ኢትዮጵያ ከግብጽ ወረራ መዳኗና የኃይሏ እየተጠናከረ መሔድ ፣ ያለቅጥ በተስፋፋው በግብጽ መንግሥት ላይ ታላቅ የግዛትና የኢኮኖሚ ውድቀት አስከተለ ። ‘በቡሃ ላይ ቆረቆር’ እንደሚባለው ፣ የግብጽ መንግሥት በኢትዮጵያ ግንባር ታላቅ የመሸነፍ በትር ሲገጥመውና ሲዳከም በግዛቱ በሱዳን ደግሞ ፣ በአህመድ መህዲ መሪነት የደርቡሾች መነሣት የባሰ ችግር ፈጠረበት ። በያለበት ላስቀመጠው የበረከተ ጦርና ከውጭ አገር ለቀጠራቸው ምንደኞች የሚከፍለው ገንዘብ አጣ ። የመንግሥቱ ግምጃ ቤት ተሟጠጠ ። ባንኮች ተራገፉ ። በዚህ ዐይነት ችግሩ በግብጽ ላይ በከበደ መጠን ፣ ግብጾች የወሰዱባትን እነቦጎስን ፣ እነሐባብን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመለስ ተስፋው የተቃረበ መስሎታየ ።

እንግሊዝም ሁኔታውን በመገምገም ባንድ ወገን የራሱን የመስፋፋት አሳብ እያደራጀ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ግብጾችና ቱርኮች ከመሕዲስቶች አጥቂነት እንዲድኑ ለማድረግ የዐፄ ዮሐንስ ሕብረት አስፈላጊ በመሆኑ ፣ ኢትዮጵያንና ግብጽን በአድሚራል ሔዊት አማካይነት በተዘጋጀው ውል መሠረት አስታረቀ ። በውሉ ላይ በኢትዮጵያ ዙሪያ የግብጽ ግዛቶች የነበሩት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ ፣ ያፄ ዮሐንስ ዕቃና መሣሪያ በምጥዋ ወደብ ያለቀረጥ እንዲያልፍ ፣ በበኩላቸው ዐፄ ዮሐንስ በከሰላ ፣ በአምዶብና በሰናሂት ደርቡሾች የከበቧቸውን ቱርኮችና ግብጾች በኢትዮጵያ ውስጥ አሳልፈው ወደ ምጥዋ ለመሸኘት እንዲረዱ ተጠቅሷል ።



በዚህ መሠረት ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ውላቸውን አክብረው ፣ እንዲያውም በውሉ ውስጥ ያልተጠቀሰውን በመጨመር ፣ የተከበቡትን ግብጾች በውጊያ ከደርቡሾቹ አድነው ወደ ምጥዋ እንዲያልፉ ካደረጉ በኋላ ከግብጾች ላይ የኢትዮጵያን ግዛቶች ተረከበው ሳይጨርሱ በእንግሊዝ ጠቃሽነት ዐፄ ዮሐንስ በአልጠረጠሩበት ሰዓት በ1877 ዓ. ም. የኢጣልያ ጦር በምስጢር መጥቶ ምጥዋን ያዘ ። በዚህ ምክንያት በሰሜናዊ ምሥራቅ በኩል የኢጣልያ ፣ በሰሜን ምዕራብ በኩል ደግሞ የደርቡሾች ጦር በአንድ የጊዜ ወቅት ሁለት ባላጋራዎች በአገር አፍቃሪው ንጉሠ ነገሥት ፊት ተደቀኑ ።

ዐፄ ዮሐንስ ፣ በእንግሊዝ መንግሥት የቆየ ወዳጅነት ተማምነው በአድሚራል ሔዊት አማካይነት በፈረሙት ውል ምክንያት ከሱዳኖች ጋር እስከ መዋጋት ሲደርሱ ፣ በተለይ ከአዲሱ ባላጋራቸው ከኢጣሊያ ጦር ጋር በሰሐጢ ለጦርነት በተሰለፉበት ጊዜ እንደ ፍጹም ወዳጅ የሚመለከቷቸው የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ፣ ወደፊት ግብጾችና ቱርኮች በሚለቁት በሱዳንና በቀይ ባሕር አካባቢ ከፈረንሣይ መንግሥት ጋር በምናደርገው ፉክክር ፣ ፍልሚያ ካልሠለጠነው ከኢትዮጵያ መንግሥት ይልቅ ፣ የሠለጠነው የኢጣልያ መንግሥት የበለጠ መሣሪያ ይሆነናል በማለት በግልግሉ ጊዜ በይፋም ፣ በምሥጢርም ለኢጣልያ አደሉ ። አዲሱን ወዳጅ ለመጥቀም ፣ የቀድሞ ወዳጃቸውን ዐፄ ዮሐንስን በሰበብ አስባብ እየተጫኑ የኢጣሊያ ኃይል በምጥዋ ወደብና አካባቢ እንዲጠናከር አደረጉ ።

በዚህ ምክንያት ፣ ዐፄ ዮሐንስ ከኢጣልያ ጦር ጋር በሰሜናዊ ምሥራቅ በሰሐጢ ለጦርነት እንደ ተፋጠጡ በሰሜናዊ ምዕራብ በኩል ደግሞ ፣ በመተማ ፣ የደርቡሾቹ አጥቂነት እየገፋ ሔደ ። ደርቡሾቹ ከመተማ አልፈው ፣ ከተማውን ጐንደርን አቃጥለው ፣ ጥር 10 ቀን 1880 ዓ. ም. በሣር ውሃ (ደምቢያ) በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የሚመራውን የጐጃም ጦር አሸነፉ ። በዚያን ወቅት የጦር ድርጅታቸውን ከመቸውም የበለጠ ያጠናከሩት ንጉሥ ምኒልክ በዐፄ ዮሐንስ ትዕዛዝ በኢጣልያ ጦርነት ላይ ለመካፈል ከሸዋ ወደ ወሎ ገሥግሠው አምባጫራ እንደገቡ ፣ ለኢጣልያኑ ራሳቸው እንደሚበቁና ፣ ደርቡሽን መከላከሉ እንደሚሻል የሚገልጽ ትእዛዝ ከንጉሠ ነገሥቱ ደረሳቸው ። በዐፄ ዮሐንስ ሠፈር ኢጣልያንን ያመጡ ምኒልክ ናቸው ፣ አሁንም ከደርቡሾች ጋር ተስማምተዋል የሚለው ወሬ ነፈሰ ። ንጉሠ ነገሥቱም ምኒልክን ጠርተው ፣ “እውነት ነው ወይስ ሐሰት ነው?” ብለው ሳይመረምሩ ወይም በዚህ ጉዳይ ላይ ፊት ለፊት ሳይወያዩ ምኒልክን ወደ ሸዋ እንዲመለሱ አዘዙዋቸው ።

ከ1880--81 ዓ.ም. በደቡብ ኢትዮጵያና በሐረር ሥልጣናቸውን ያጠናከሩት ምኒልክ ፤ ከእንጦጦ አምባጫራ ድረስ ከሔዱ በኋላ ዐፄ ዮሐንስ ሐስተኛ ወሬ በመስማት አቅርበው ሳይጠይቋቸው ወደሸዋ እንዲመለሱ ስላደረጓቸው ፤ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ደግሞ ረዳት ሳይ ጨምሩላቸው በሣር ውሃ ከደርቡሾች ጋር ለጦርነት ብቻቸውን ስላጋ ለጧቸው ፤ ሁለቱ የሸዋና የጐጃም ንጉሦች ለንጉሠ ነገሥቱ ሁለተኛ ላለመታዘዝ ደብረ ማርቆስ ላይ አደሙ ።

በዚህ ምክንያት ፤ ዮሐንስ ከጣልያኖች ጋር ለውጊያ ከተሰለፉበት ከስሐጢ የጦር ግንባር ጦርነትም ሆነ ፤ ደንበኛ ስላምም ሳያደርጉ ወደ ጐጃም ዘልቀው በጦር ኃይል ተክለ ሃይማኖትን አሳምነዋል ። ከምኒ ልክም ጋር በራስ ዳርጌ አማካይነት የልባቸውን በደብዳቤ ተገላል ጠው ከተወቃቀሱ በኋላ፤ ንጉሥ ምኒልክን እንደ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በጦር ኃይል የማሳመኑ ጉዳይ በዚህ ጊዜ አጠራጣሪ ሁኔታ ላይ እንደ ሚጥል ስለ ተገነዘቡት ፤ ለሌላ ጊዜ አቆይተው ጐንደርን በመዝረፍና ቀሳውስቱን በመፍጀት ያስቆጣቸውን የደርቡሽን ጦር ለመበቀል በቀጥታ ወደ መተማ ፊታቸውን አዞሩ ። ወደዚያም ደርሰው ምሽጉን ተገን አድሮጎ የጠበንጃውን ምላጭ በመጨበጥ ፤ አልሞ ከሚጠብ ቃቸው ጠላት ጋር ተጋጥመው እንደ ተራ ወታደር ከፊት ቀድመው በዠግንነት በመዋጋት ላይ እንዳሉና ድል አድራጊነትን ለመጐ ናጸፍ ጥቂት ሲቀራቸው ከጠላት ወገን በተተኮሰች ጥይት ክፉኛ ቆስለው ወደኋላ ተመለሱ ። በጦርነቱ ሰዓት እየተፏከረ በጠበንጃም በጐራዴም በዠግንነት እየተዋጋ ፤ በጠላት ላይ ሽብርና ፍርሃት የነዛው ጦራቸው የንጉሠ ነገሥቱን መቁሰል ወደጐን አቆይቶ አጥቂነቱን በመቀጠልና የተቃረበውን ድል ለራሱ አስቀርቶ በመደምደም ፈንታ የርሳቸውን ቆስሎ ወደኋላ መመለስ ሲሰማ ፤ አዝማቹ ራስ ኃይለ ማር ያምና ዘማቹም ተደናግጠው ከየጦሩ ግንባር አፈገፈጉ ።

ሁኔታውን ሲገመግሙት ፤

ሀ/ ያፄ ዮሐንስ ጦር ጠላት ምሽግ ድረስ ሔዶ መግጠሙ ፤

ለ/ በዚህ የመተማ ጦርነት የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና በተ ለይ የንጉሥ ምኒልክ አለመካፈል ፤

ሐ/ በጦር አመራር ስመጥር የሆኑት የራስ አሉላ አባነጋ ከዋ ናው ጦር ጠቅላይ አዛዥነት መገለል ፤ ለዚህ ለኢትዮጵያ ድል መሆን አስተዋጽኦ እንዳደረገ ይታያል ።

በጉንደትና በጉንዳጉንዲ ፤ በጉራዕና በዶጋሊ በግብጻውያን ላይ ተደጋጋሚ ድል አድራጊነት ያገኘው ፤ በሠለጠነውም የኢጣልያ ጦር ላይ በዶጋሊ አሸናፊነትን የተጐናጸፈው የኢትዮጵያ ጦር ፤ ድርጅታቸ



ውና ሥልጣኔያቸው በዝቅተኛ ደረጃ በሚገኘው በደርቡሽ ጦር ፤ በዚህ ጊዜ መሸነፉ ከማሳዘን ዐልፎ ወገንን የሚያስቆጭ ነው ።

በሕይወታቸው ሙሉ ለአገራቸው ለኢትዮጵያ ዕድገት ሲዳክሙ የኖሩትና የወገናቸውን ጥቃት ለመመለስ ሲሉ ፤ ሕይወታቸውን የሠዉት የእኚህ ንጉሠ ነገሥት ስማቸው ከነዝናቸው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እያበራ የሚኖር መሆኑን እያወሳን ፤ በዚህ መቅድም ባጭሩ የተጠቀሰው ያፄ ዮሐንስና በርሳቸው ዘመነ መንግሥት ክልል ውስጥ የሚገ ኘው የኢትዮጵያ ዝርዝር ታሪክ ፤ በመጽሐፉ አካል ውስጥ በየምዕራፉ በተቻለ መጠን ተተንትኗል ።

መቼም እንደ ኢትዮጵያ ያለ ያንድ አገር ታሪክ ፤ ከዚህ በፊት በየ መልኩ ተዘጋጅቶ ባልተቀመጠበት ሁኔታ በሙሉም ፤ በአጋማሹም ሲጻፍ አንዳንድ ስሕተት በዝንጋዔ ወይም በግድፈት ሊደርስ ይች ላል ። እንኳን ብዙ ገጽ ከያዘ መጽሐፍ ባንድ ገጽ ላይ ከሠፈረ ደብ ዳቤም ስሕተት አይጠፋም ።

ስለዚህ ነው ፤ በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ዓመት ላይ የነበረው ያፄ ሠርፀ ድንግል (1555—1589 ዓ.ም.) ዜና መዋዕል አዘጋጅ ወልደ ሃይማኖት በጽሑፉ መጨረሻ ላይ ፤ “ይቤ በዓለ ዝንቱ መጽሐፍ አኀውየ ማዕምራን አንባብያኒሁ ፤ ወሰማዕያኒሁ ለዝንቱ መጽሐፍ አመ ረከብክሙ ብየ ስሕተት በኀዲገ ዜና እሙንገለ ዝንጋዔ ወአዕ ምሮ ኅድጉ አበሳየ ተዘኪረክሙ ከመ ኅፁዕ አዕምሮቱ ለእጓለ እመ ሕያው ወአኮ ምሉዕ” ብሏል ። ትርጉሙም “ይኸን መጽሐፍ የምታነቡ ዐዋቂዎች ወንድሞቼ ፤ ባለማወቅና በመዘንጋት ያልተጻፈ ቢኖር ፤ የሰው አዕምሮው ሙሉ ሳይሆን ጐደሎ መሆኑን ተገንዝባችሁ ለጥፋቱ ይቅ ርታ አድርጉ . . .” የሚል ነው ። ይኸ አራት መቶ ዓመት ያለፈው የወልደ ሃይማኖት አባባል ፤ እኔም ሌሎችም ጸሐፊዎች ዛሬም ወደፊ ትም መሠረት የምናደርገው አባባል ነው ።

መስከረም 30 ቀን 1976

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ

# ምስጋና

በመዠመሪያ ፣ “ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት” በሚባለው መጽሐፍ ላይ እንዳመለከትሁት በሮማ ፣ በሎንዶን ፣ በፓሪስ የኢትዮጵያ ሰነድ የሚገኝባቸውን የድርጅት አስተናባሪዎች ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ክፍል ኃላፊዎችን እነ አቶ ደግፌ ገብረ ጻድቅን ፣ በባህል ሚኒስቴር የቤተ መጻሕፍት ወመዘክር ሹማምንትና ሠራተኞች የሚያስፈልገኝን መጽሐፍና ሰነድ በማቅረብ የረዱኝን ፣ እነ ወይዘሪት መና ወረደን ፣ የጻፍሁትን በመኪና የመቱልኝን ወይዘሪት ሙናጃ አምዱካን ፣ ወይዘሪት ብርሃኔ ዳባን ፣ በውስጡ ያሉትን ካርታዎች ያዘጋጀልኝን አቶ ዳንኤል ሰይፉን ፣ የኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ኃላፊዎች እትመቱ በተሻለና በተጣራ ሁኔታ እንዲከናወን ባለፈው እንዳደረጉት ፣ ለዚህኛውም ጥረት ያደረጉትን ፣ በመጨረሻም በማንኛውም ወቅት እርዳታዋ ያልተለየኝን ባለቤቴን ወይዘሮ ካሳዬ ደስታን አመሰግናለሁ ።

ተክለ ጻድቅ መኵሪያ

# ምዕራፍ አንድ

## ነዋሪው ያንጋገሥ ወግና ሥርዓት መጥፋት

እስከ ዘመነ መሳፍንት መዠመሪያ (1769) ድረስ ፣ በኢትዮጵያ የአነጋገሥ ባህል ፣ ዙፋን ካባት ወደ መጀመሪያው ወንድ ልጅ ፣ ልጅ የሌለ እንደሆነ ወደ ቅርብ ዘመድ በሚተላለፍበት ጊዜ ፣ ማለትም ንጉሥ ሞቶ ንጉሥ ሲተካ ፣ ዐዋጅ ነጋሪው ወደ አደባባይ ወጥቶ "የሞትንም እኛ ፣ ያለንም እኛ ፣ ወዳጆችን ይደሰት ፣ ጠላታችን ይዘን" በማለት ያሰማል ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ፣ የዚህ አባባል ለወጥወጥ እያለ ፣ "የሞትንም እኛ ፣ የነገሥንም እኛ ፣ ስለ ሞትነው እዘኑ ፣ ስለ ነገሥነው ተደሰቱ" የሚል ዐዋጅ ይናገራል ። ትርጓሜውም ፣ የሞተውም ነጋሚ ወደ ዙፋን የወጣውም መስፍን ካንድ ሰሎሞናዊ ቤተሰብ መሆናቸውን ለማመልከት ነው ።

ይህ ዐዋጅ ፣ ዐፄ ኢዮአስ (1755—1769) በራስ ሚካኤል (ቀታሌ ንጉሥ) ከተገደሉ ወዲህ (1769 ዓ.ም.) እየቀረ ሔደ ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከ 19ነኛው መቶ ዓመት መሐከል ድረስ ነገሥታት ሥልጣናቸውን ባነግሣቸው እንደራሴያቸው ሲቀሙ ፣ እንደራሴዎቹም የራስነትን ማዕረግ ለስሙ ከነገሥታቱ እየተቀበሉ ሥልጣናቸውን በሰይፋቸው ጫፍ (በኃይል) ብቻ ሲያረጋግጡ ፣ ከላይ የተጠቀሰውን የመሰለው ሥርዓታዊ የነጋሚዎች የመለዋወጥ ዐዋጅ እየቀረ ሔደ ። እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ መነሣት ድረስ ከቤገምድር ፣ ከጐጃም ፣ ከስሜንና ከትግራይ ፣ ከላስታ ፣ ከየጁና ከወሎ መሳፍንት እየተነሡ ፣ የፈለጉትን መስፍን እያነገሡ ፣ አንዱ ያነገሡውን ሌላው እየተቃወመ ፣ የራሱን በማንገሥ ባንድ ዘመን ሦስት ነገሥታት የነገሡበት ጊዜ ነበር ። እንዲም ንጉሥ (ተክለ ጊዮርጊስ) 6 ጊዜ ነግሦ 6 ጊዜ የተባረረበት ዘመን ነበር ። ከሁሉ መሳፍንት የየጁና የወሎ ተወላጆች ፣ ከታላቁ ራስ ዐሊ ዠምሮ እስከ ታናሹ ራስ ዐሊ ድረስ ያሉት በርታ ብለው ስለተከታተሉ ፣ ከትግራይም እነ ራስ ወልደ ሥላሴ ፣ እነ ደጃች ሰባጋዲስ ፣ ከጐጃምም እነ ራስ መርድ ፣ ከዳሞት እነ ደጃች ዘውዴ ፣ ከላስታ እነ ራስ አሥራት በየጊዜው ቢነሡም ፣ በጠቅላላው በዘመነ መሳፍንት ያንበኛ የማዕከላዊው የጐንደር መንግሥት ገዥዎች እነዚሁ ወረሼህ የሚባሉት የየጁ ኦሮሞ ባላባቶች እነ ራስ ዐሊ ነበሩ ። እነዚህም

እያንዳንዳቸው ሥልጣን በጨበጡበት ሰዓት ከላይ ከነፋሲል ፣ ከነ ኢያሱ ዘር የመጣውን አንዳንድ ነጋሢ በዙፋን ላይ ያለምንም ሥልጣን ለስሙ ብቻ ያስቀምጣሉ ።

ለምሳሌ ፣ በመጨረሻው መስፍን በታናሹ ራስ ዐሊ ጊዜ የነበሩት ዐፄ ዮሐንስ ሣልሳይ ፣ በራስ ዐሊና በእናታቸው በወይዘሮ መነን ፈቃድ ለስሙ ከነገሡ በኋላ ፣ የእቴጌነት ደረጃ ለማግኘት ሲሉ ወይዘሮ መነን አግብተዋቸው ሳለ ፣ በመካከሉ ቴዎድሮስ መነንንም ፣ ዐሊንም ደምስሰው ከነገሡ በኋላ ፣ ዮሐንስ ሣልሳይን በመቅደላ እንደ እስር አስቀምጠዋቸው ሲኖሩ ፣ ብዙ መከራ አሳልፈው በእንግሊዞቹ ጦርነት ከቴዎድሮስ ሞት በኋላ ነጻነታቸውን አግኝተው ተለቀቁ ። ከተለቀቁ በኋላ ኃይልም ሰበብም ስላጡ ፣ የመንገሥ ፍላጐት አላሳዩም ። ተከታይም አልነበራቸው ። በዚህ ምክንያት በሰላምና በጽሞና ወደ አክሱም ሔደው ተቀመጡ ።

ዐፄ ቴዎድሮስ በሕይወታቸው ሳሉ ፣ ሦስት ወንድና ሦስት ሴት ልጆች እንደ ነበሩአቸው ራሳም ያመለከትና ከነዚህ ሁሉ መካከል በቁርባን ካገቡዋቸው ከእቴጌ ጥሩወርቅ የተወለደው ልጃቸው ዓለማየሁ ብቻ ዋና አልጋ ወራሽ መሆኑን ፣ የቀሩት የተወለዱት ከዕቁባቶች እንጂ ከደንበኛ ጋብቻ አለመሆኑን ፣ ከሁሉም ልጆቻቸው ትልቁ በግምት 23 ዓመት ዕድሜ የነበራቸው ራስ መሸሻ መሆናቸውን ፣ እርሳቸውም ወደ ሸዋ ለመሔድ ካቀዱ በኋላ ፣ አሳባቸውን ለውጠው ወደ ሴት አያታቸው አገር ወደ አማራ ሳይንት መሔዳቸውን ፣ ከሁሉም ታናሽ የሆነው ልጃቸው ኃይሉ ካሳ ከኦሮሞ ተወላጅ ዕቁባታቸው የወለዱት ከናቱ ጋር በትግራይ አገር መቅረቱን ፣ ዕድሜዋ 20 ዓመት የነበረውና ከሴት ልጆቻቸው ውስጥ ታላቅ የነበረችው አልጣሽ ለምኒልክ ተድራ ሳለች ፣ ወጣቱ ደጃዝማች ምኒልክ ትቷት ወዳገሩ አምልጦ ከሔደ ወዲህ ፣ ባሪያው (ራስ) ለሚባል የትግራይ ሹም መዳሯን ፤ የቀሩት ሁለት ሴቶች ልጆች አንዲቱ ያምስት ፣ ሌላይቱ የሦስት ዓመት ዕድሜ ያላቸው በቤጌምድር እናቶቻቸው እንዳስቀሩዋቸው ይገልጽልናል ።[1]

ስለዚህ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ የዙፋንን መብት በኃይላቸውና በትግላቸው እንጂ በሕጋዊ መንገድና በትውልድ እንዳላገኙት ሁሉ ፣ እሁንም ሲሞቱ ታላቁ ልጃቸው ራስ መሸሻም ሆኑ ከደንበኛ ሚስት

1 H. Rassam, Narrative of the British Mission to Theodore, King of Abyssinia, Vol. II, p. 336 (London 1869).



የተወለደውም ደጃች ዓለማየሁ ሊነግሡ አልቻሉም ። እነርሱንም ለማንገሥ የሞከረ አንድም የወታደራዊና የቤተ ክህነት ድርጅት አልተገኘም ። እንኳን ለመንገሥ ብዙዎች የአባታቸው ተቃዋሚዎች ሊበቀሏቸው ይፈልጉ ስለ ነበር ፣ በአባታቸው የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ለመገኘት እና በጐንደር ከተማ መቆየትም እንኳን አቅቷቸው ፣ ዓለማየሁም በጠባቂ ወደ ሎንዶን ሔዶ ለ10 ዓመት ያህል እንደ ተቀመጠ በ1871 ዓ. ም. ታሞ ሞተ ። ራስ መሸሻም ወደ አማራ ሳይንት ሔደው ከሰነበቱ በኋላ ፣ በዚያም ለዘለቄታ መኖር የማያዋጣቸው መሆኑን አመዛዝነው ፣ ወደ አብሮ አደጋቸው ወደ ንጉሥ ምኒልክ ዘንድ ሔደው በሸዋ ተቀመጡ ። ዐፄ ቴዎድሮስ አስረዋቸው የነበሩት ፣ ከዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ የሚወለዱት ደንበኛ ነጋሢው ዮሐንስ ሣልሳይም ፣ በዚህ ጊዜ ምንም ከዓፄ ቴዎድሮስ ነጻ ቢሆኑ ፣ ተከታይና ደጋፊ ስለ አልነበራቸው ፣ እርሳቸውም በዙፋን እንደገና የመቀመጡን ነገር ድምጡንም ሳያነሡ እግራቸውንም ፣ አንደበታቸውንም ሰብስበው በአክሱም ዐርፈው ተቀመጡ ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት ፣ ያፄ ቴዎድሮስ ሞት ባንድ ጊዜ ከቴዎድሮስ ጋር ምንም ዝምድና በሌላቸው ፣ ነገር ግን የጦር ኃይል ባላቸው ፣ በሦስት የዙፋን ባላንጣዎች መካከል የሽሚያ መንገድ ከፈተ ። የሌሎቹን የጥቃቅኖቹን ወደ ጐን ትተን በጣም የታወቁት ላስቴው ዋግሹም ጐበዜ ፣ ሸዌው ንጉሥ ምኒልክ ፣ ትግሬው ደጃች ካሳ ምርጫኗቸው ። የሁለቱን አቆይተን በዋግሹም ጐበዜ እንጋገሥ እንጀምር ።

# ምዕራፍ ሁለት

የዋግሹም ጐበዜ አነጋገሥ — ለእንግሊዝና ለፈረንሳይ መንግሥታት የጻፉ ዋቸው ደብዳቤዎች — ከደጃዝማች በዝብዝ ካሳ ጋር ተዋግተው ስለ መሸነፋቸው

የእንግሊዝ ጦር ፣ የመቅደላን ምሽግ ለወይዘሮ መስተዋት አስረክቦ ወደ አገሩ ከመመለሱ በፊት መስተዋት ስለ ገባችላቸው ፣ ዋግሹም ጐበዜ ዋናውን መናገሻ ከተማ ጐንደርን እጅ አደረጉ ። በስሜን ፣ በወገራ የመጣውን ፣ ጥሶ ጐበዜን በጦር ደምስሰው ያጐታቸውን ልጅ ዋግሹም ተፈሪን ሾሙ ። በጐጃም ደጃች ደስታ ተድላን አባርረው ፣ ለባላምባራስ አዳል ተሰማ እኅታቸውን ወይዘሮ ላቀችን ድረው የራስነት ማዕረግ ጨምረው አደላደሉ ። የቤገምድሩ ራስ ወልደ ማርያምም አሜን ብለው ስለ ተገዙላቸው ፣ ለመንገሥ የሚጐድላቸው ለጊዜው ቀብቶ የሚያነግሥ ጳጳስ አለመገኘት ብቻ ሆነ ።

ባዬ ቴዎድሮስ ዘመን የነበሩት አቡነ ሰላማ ከሞቱ ወዲህ ሌላ ጳጳስ ከግብጽ አልመጣም ። ምቹው የማምጫው በር ምጥዋ በግብጾች እጅ ተይዟል ። ወደዚያ መተላለፊያው የአካለ ጉዛይና የሐማሴን ግዛት በዘፋን ባላንባቸው ፣ በባለቤታቸው በእቴጌ ድንቅነሽ ወንድም ፣ በደጃች ካሳ ምርጫ ተይዟል ። እንደዚሁ ሳይነግሡ በዋግሹምነት ስም ብቻ ጠቅላላውን አገር አስተዳድራለሁ ማለቱ ደግሞ የማያመች ሆነ ። በመሆኑም ጳጳስ ባይኖርም ፣ ይነገሡ ተብሎ በዕጨጌ ገብረየሱስ እጅ ተቀብተው በ1860 ዓ.ም. ነገሡ ። ስመ መንግሥታቸው "ተክለ ጊዮርጊስ" ተባለ ።[1]

ከነገሡ በኋላ ኃይላቸው የበለጠ እየበረታ ስለሔደ ፣ ባዬ ቴዎድሮስ ዘመን በጦርነት የተጻከመው ወሎ በተለይ የወርቂት ወገን ወደ ምኒልክ ቢያደላም ፣ የመስተዋት ወገን እላይ እንዳልነው ገብሯል ።

---

1 የነገሡበት ቀንና ወር በትክክል አይታወቅም ። ዓመቱም ቴዎድሮስ በሞቱበት በ1860 ይሁን ወይም ግዛት ካደላደሉ በኋላ በ1861 መሆኑ አጠራጣሪ ነው ። የሚመስለው 1860 ነው ። ያነገሡዋቸው ዕጨጌ ተክለ አቢብ ናቸው የሚሉ አሉ ። በዚህ ስም በዚህ ዘመን የሚጠራ ዕጨጌ የለም ። ዋዜማ ብ.ጌ.ኀሩይ ገጽ 113 ።

ምኒልክም ፣ "የነጋሢ ልጅ ፣ የቴዎድሮስ ወራሽ እኔ ነኝ" ብለው "ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት" እያሉ ፣ እያተሙ ከውጭ አገር መሪዎች ጋር በሚላላኩበት ሰዓት ግዛታቸውንም እስከ ወሎ አድርሰው ወረይሉን ልክ እንደ ከተማቸው አድርገውታል ። ካሳም በትግራይና በትግሬ * የአውራጃዎቻቸው ባለቤት ሆነው በነጻነት ተቀምጠዋል ። በዚህም ምክንያት ፣ ቴዎድሮስ ላንድነቷ የደከሙላትና የሞቱላት ኢትዮጵያ ፣ በዚህ ጊዜ እንደ ገና ተከፋፍላ የሦስት ነገሥታት (ተክለ ጊዮርጊስ ፣ ምኒልክ ፣ በዝብዝ ካሳ) አገር ትመስላለች ። ሦስቱም በተለያዩ ሦስት አውራጃዎች ቢገኙም ባንድ ባህል ፣ ባንድ ብሔራዊ የአማርኛ ቋንቋ ፣ ባንድ ሃይማኖት የሚጠቀሙ ላንዲቱ ኢትዮጵያ የሚያስቡ ሆነው ሳለ ፣ የከፋፈላቸው ዋናው ምክንያት 'አንዲቷ ኢትዮጵያ በኔ ባንዱ መሪነት ትተዳደር' በሚል ብቻ ነው ። በዚህም መካከል ምኒልክ አገብራለሁ የሚል ስሜት አይኑራቸው እንጂ ፣ ካፄ ተክለ ጊዮርጊስ ጋር ደብዳቤ ተላልከዋል ። ገጸ በረከትም ባቶ (የወደፊት ራስ) ጐበና እጅ ልከዋል ። ይኸም አላላክ በርሳቸው ዘንድ እንደ ወዳጅነት ሲቆጠር ፣ በተክለ ጊዮርጊስ ወገን እንደ መገበር ተቆጥሯል ።

ስለዚህ ይነስ ይብዛ ፣ እነዚህ የተጠቀሱት አገሮች ሲታመኑላቸው አልገዛም ብለው በጣም ያስቸገሩዋቸው ባለፈው ደጋግመን ያነሣናቸው ደጃዝማች በዝብዝ ካሳ ናቸው ። እርሳቸውም ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ፣ ባፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ ላይ ፣ ሁለቱም በየበኩላቸው ባላቸው ቂም የተነሣ ባፄ ቴዎድሮስ ላይ ሸፍተው፣ ካሳም በትውልድ አገራቸው ሹመታቸውን ያጸኑት በመጀመሪያው ወቅት በዋግሹም ጐበዜ ደጋፊነት ነው ። በዚሁ የስምምነት ወቅት ነው ተክለ ጊዮርጊስ የካሳን እህት ወይዘሮ ድንቅነሽን ያገቡት ። ካሳ ግን ፣ ቀድሞውኑ የራሳቸው ኃይል እየበረታ በሔደበትና ጠቡም ከዋግሹም ጐበዜ ጋር እየተባባሰ በሔደበት ሰዓት ፣ የእንግሊዝን ጦር ሲመጣ ተቀብለው እንዳስተናገዱ ሁሉ ፣ ሲመለስም አስደሳች አቀባበልና መስተንግዶ ከማድረግ ጋር 'ከዋግሹም ጐበዜ የምከላከልበት መሣሪያ ይስጡኝ' ብለው ጠይቀው ፣ በጄኔራል ናፒዬር ፈቃድ 12 ዘመናዊ የተራራ መድፍ ፣ 900 የሚሆን የሰናድር ጠበንጃና ሽጉጥ ከብዙ ጥይት ጋር ሰጣቸው ። በኋላም አዳዲሱን የጦር መሣሪያ ከወታደራቸው ጋር

---

* በዚህ ዘመን ትግራይ ከመረብ መለስ ፣ ትግሬ ከመረብ ወዲያ ያሉት ሁለት አውራጃዎች የሚጠሩበት ሥያሜ ነው ።



እያስተማረ የሚያስተዋውቅ አሠልጣኝ ኪርክሃምና ሉዊ ተጨመሩላቸው ። በዚህ አንጻር የተክለ ጊዮርጊስ በአጋጣሚው መጠቀምን ያለማወቅና ቸልተኝነት ፣ የደጃች ካሳ ትጋትና ዝግጅት ያስከተለው ጦርነት በግድ ካሳን አሸናፊ ፣ ተክለ ጊዮርጊስን ተሸናፊ ሲያደርጋቸው ይታያል ። ቢሆንም ፣ ደጃች ካሳ ያፄ ተክለ ጊዮርጊስን ጦር ለመመለስ ኃይላቸውን ስለ ተጠራጠሩት ፣ አቡነ አትናቴዎስን ከግብጽ እየመራ ባመጣላቸው በስምሃር ባላባት በመሐመድ አብደል ራሂም በኩል የግብጹ መሪ (ኢስማኤል) የጦር እርዳታ እንዲያደርግላቸው ጠይቀው፡ት የፈረንሳይ መንግሥት ስለ ተቃወመ ፣ መቅረቱን ዱወ የሚባለው ታሪክ ጸሐፊ ያመለክታል ።[1] እንደዚሁም ተክለ ጊዮርጊስ ፣ ካሳ ያስመጧቸውን ጳጳስ አቡነ አትናቴዎስን እንዲልኩላቸው ማስፈራራትም ፣ ማባበልም ያለበት ደብዳቤ ልከውባቸው ፣ ካሳ እምቢታቸውን ካስታወቁ በኋላ ሁለቱም ለጦርነት ይዘጋጁ ገቡ ጀመር ።[2]

ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ፣ በፊተኛው ጊዜ በቸልታ ወይም በይሉኝታ ያላለፉትን የእንግሊዝን ወዳጅነት አሁን ጊዜው ካለፈና ከነገሡ በኋላ በደብዳቤ ደጅ እየጠኑ ዝምድና ይፈልጉ ገቡ ጀመር ። እንደዚሁም የእንግሊዝ የጦር መሪ ናፒዬር እግዛታቸው በነበረ ጊዜ ፣ ሲፈልጋቸው በወዳጅነት ተገናኝተው ችግራቸውንና ምኞታቸውን ገልጠው ያልፈጸሙትን አሁን ናፒዬር ወደ አገሩ ከተመለሰ ወዲህና ምቹው ጊዜ ካመለጣቸው በኋላ ፣ ከእንግሊዝ ንግሥትም ፣ ከጄኔራል ናፒዬርም በሩቁ በደብዳቤ ለመዛመድ እና ካሳንም ለማስወንጀል በከንቱ እንደ ፈለጉ ከዚህ ቀጥሎ ካለው ደብዳቤያቸው ላይ ይነበባል ።

> "በስመ አብ… መልእክት ዘዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ… ትብጻሕ ኀበ—ንግሥተ እንግሊዝ ኀበ ናጲር (ናፒዬር) እምናም እናንተ ብትመጡ ከሰው በፊት እኔ ተቀብዬ መንገድ መርቼ እህልም ፣ ማርም ፣ በግ ፣ ፍየል ይዘህ ከሠፈራቸው ግባ ብዬ ሀዋጅ ነገርሁ. . ሽፍታ (ጥሶ ጐበዜ) ስለ ተነሣብኝ ወደርሱ ሔድሁኝ ። እኔ ሰሜን እነሱ (የእንግሊዝ ጦር) መቅደላ ሆኑ. . . የደጃች ካሳ ነገር ፊትም ትግራይ ስገባ ከሰው በፊት ሎሌነት (አሽከርነት) ገብቶልኝ ሹሜ ሸልሜ ባኖረው የትግራይ ሎሌዬን አባብሎ ከዳኝ . . ከሰሜን ፣ ከወገራ የሾምሁትን ሎሌዬን ኃይለ ማርያምን አስከድቶ ፣ ዐልፎ ተርፎ

---

1 G. Douin, Histoire du regne du Kedive Ismael — Tome III, 2e partie (1869 — 1873) pp. 308—310.
2 Hairu Tafla (ed.), Chronicle of Emperor Yohannes IV, pp. 127—128.

> እስከ ጐንደር. ሹም ሽልሞ ሰደደው. . . ይኸ ሁሉ
> መደረጉ የናንተን ቃል ጠብቄ ብስነብት ነው እንጂ ፣
> ለርሱ የሚሆን ጉልበት አጥቼ አይደለም. . . ክርስቶስ
> መገፋቴን አይቶ ጉልበት ቢሰጠኝና ባገሩ ብሾምበት አታ
> ድሉብኝ (እንዳትረዱብኝ). .[1]

ይኸኛውም ደብዳቤ ቀን የለውም ፤ ባነጋገራቸው "እምና እናንተ
ስትመጡ" የሚል ቃል ስለ ጠቀሱ ፣ ደብዳቤውን የጻፉት ቴዎድሮስ
በሞቱ ባመቱ በ1861 ዓ.ም. መሆኑ ነው ። ሎንዶን የደረሰውም
በ1861 ዓ. ም. በሰኔ ወር ነው ።[2] "ሎሌዩን ኃይለ ማርያምን አስ
ክድቶ" የሚሉት ፣ ኃይለ ማርያም ጉግሣ የደጃች ካሳ ታላቅ ወንድም
የደጃች ጉግሣ ልጅ ናቸው ። ምናልባት በመጀመሪያው ጊዜ ካሳ ራሳ
ቸው ለጐበዜ ባደሩበት ወቅት ፣ ኃይለ ማርያምም ለጐበዜ ገብተው ሳለ
በኋላ የአጐታቸውን መበርታት ተመልክተው ከጐበዜ ወደ ካሳ ዞረው
ተሾመው ይሆናል ። የሆነ ሆኖ ፣ ለዚህ ደብዳቤ መልስ ከናፒዩር የመ
ጣላቸው ባገሩ ርቀት ፣ በግንኙነት እጦት ፣ ተክለ ጊዮርጊስ በደጃች
ካሳ ተሸንፈው በአባ ሰላማ ተራራ ከታሰሩ በኋላ በጣም ዘግይቶ
ነው ። ደብዳቤውም ባጭሩ በእንግሊዝኛ የሚለው ካሳ በውጭ አገር
መሣሪያ የጠነከሩ ፣ ወታደራቸውም በፈረንጅ አስተማሪዎች የሠለጠነ
ስለሆነ አይችሉምና ትግራይን መውጋት ይቅርብዎ የሚል ነው ።[3]
የእንግሊዝ መንግሥትም አቀዋም ፣ በናፒዩር አማካይነት ለየመሳፍንቱ
እንደ ተገለጠው ፣ "እኛ ባገር ውስጥ ጉዳያችሁ አንገባም" ነው ። ለካ
ሳም መድፉና ጠበንጃው ለመከላከያ ተብሎ ሲሰጣቸው ፣ "ተስማምታ
ችሁ በሰላም ኑሩ" የሚል ምክር እንዳዘለ ይነገራል ። ተክለ ጊዮርጊስ
"ይኸ ሁሉ መደረጉ የናንተን ቃል ጠብቄ ብስነብት ነው" ያሉትም ፣
"ተስማምታችሁ ኑሩ" ተብሎ ፣ አስቀድሞ መቅደላን ሳይለቅ ከናፒ
የር በደጃች መሸሻ አማካይነት የተላከባቸውን የምክር ቃል ሲገልጡ
ይመስላል ።

በዚያን ጊዜ ፣ ብዙ ቅኝ አገር በመያዝ ኃይላቸው የሚሰማው
የእንግሊዞች ብቻ ሳይሆን የፈረንሳዮችም ጭምር ነበር ። በምጥዋም ፣
በካይሮም ፣ በሌላውም ወደብና ከተማ የእንግሊዝና የፈረንሳይ ቆንሲ
ሎች እየተጋጩም ፣ እየተስማሙም አብረው የየግል መንግሥታቸውን
ጥቅም ይጠብቁ ነበር ። በዚህ ምክንያት ፣ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ለእንግሊዝ

1 Public Record Offce, London, Fo. 95-28
2 Chris. P. Rossenfeld, Chronology of Menelek, , p.47.
3 ,,. . . His troops are well armed and taught to fight by Europeans, so that if you make war on him you may not be successful . . ." Letters of Field — Marshal Lord Napier of Magdala . . . It. Col. H.D. Napier, pp. 22—23.



መሪዎች እንደ ጻፉት ሁሉ ፣ ከደጃች ካሳ ጋር ያላቸውን ጠብ ከመ
ግለጽ ጋር የፈረንሳይ መንግሥት ከርሳቸው ጋር በአሳብ እንዲተባበ
ራቸው ፈልገው ፣ ለፈረንሳይ ንጉሠ ነገሥት ለናፖሊዎን ሣልሳይ እንደ
ዚህ ሲሉ ጽፈዋል ።

> "ይድረስ እግዜር መርጦ ካነገሡዎ ንጉሠ ነገሥት ናፖሊ
> ዎን. . .እኔ የእርስዎን ወዳጅነት እጅግ እፈልጋለሁ ። . . .
> ዐፄ ቴዎድሮስ ያከፉትን (ያበላሹትን) ነገር ሁሉ ከምክር
> ዎና ከፍቅርዎ ጋር በእግዚአብሔር ኃይል አቀናዋለሁ. . .
> ደጃች ካሳ እያቴ ላያቴ ፣ እባቴ ላባቴ ተገዝቶ ይኖር ነበር ፤
> እርሱንም እኔ ሾሜ አገር ጠብቅ ብዬ ብተወው አምጦ
> (ሸፍቶ) አልታዘዝም አለ ። አሁን ግን የምጠይቀው (ግባ
> አለዚያ መጣሁብህ ብዬ) ነኝና አይፍረዱብኝ. . ."

ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ደብዳቤውን የጻፉበት ቀን በትክክል
1862 ዓ.ም. ሐምሌ 1 ቀን መሆኑ ተመልክቷል ። ነገር ግን በደብዳቤ
ያቸው ላይ ፣ "እያቴ ላያቴ ፣ እባቴ ላባቴ ተገዝቶ ይኖር ነበር" ያሉት
የዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ አባት ዋግሹም ገብረ መድኅን ሹም ተምቤን
ምርጫን ፣ አያታቸው አቶ አምኃ የምርጫን አባት ወልደ ኪዳንን
ከላስታ ወደ ትግራይ ዐልፈው ለመግዛታቸው ምንም ማስረጃ የለም ።
መቼም የውጭ አገር መሪዎች የኢትዮጵያን ውስጣዊና ዝርዝር ሁኔታ
ስለማያውቁት ፣ ይኸን ብዬ ብጽፍ ጥያቄዬ ክብደት ይኖረዋል ሲሉ
የጨመሩት ይመስላል ።

ይኸ ሁሉ ከሆነ በኋላ ፣ የናፒየር የምክር ደብዳቤ ሳይደርሳቸው
አስቀድሞ ሁለቱም ከ1860 ዓ.ም. ጀምሮ ለጦርነት ሲዘጋጁ ከተክለ
ጊዮርጊስ በኩል ፣ "አምቻውን(ካሳን) ገድሎ ሚስቱን (ድንቅነሽን)
አስለቃሽ" የሚል የፉከራ ቃል ፣ ከደጃች ካሳ በኩል ደግሞ "አማቱን
ገድሎ እህቱን አስለቃሽ" የሚል መልስ እየተወራወሩ ሲዛዛቱ ቆይ
ተው ፣ ተክለ ጊዮርጊስ የሠራዊታቸውን ብዛት ለማስረዳትና ነገሩ
በዛሻ የሚከናወን መስሏቸው አንድ ስልቻ ጤፍ አስሞልተው ፣ "ወታ
ደሬ በዚህ ልክ ነው" ሲሉ ላኩባቸው ይባላል—በአፈ ታሪክ ። ካሳም ፣

> ኩቱርክ ይዋጋል እንኳን ካንካሳ
> ያባ ፊንቅል ልጅ ወሬሳው ካሳ[1]

ብለው ፎክረው ወዲያውም ፣ "ወታደርህ እንደዚህ ቢበዛ በጥይት

1 ተ.ጸ.መ ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ካዔ ቴዎድሮስ እስከ ቀ.ኃ.ሥ. ገጽ 42 ።

ቆልቼ ነው የምሰደው" ሲሉ ጤፉን ቆልተው ላኩላቸው ይባላል ። ይህ አፈ ታሪክ ፣የወታደራዊ ልዩነታቸው በምን በምን እንደሆነ ያሳያል። ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ለናፖሊዎን ሦስተኛ በጾፉትም ደብዳቤ ላይ ፣ "የምጠይቀው ነኝና አይፍረዱብኝ" ሲሉ ፣ ሥጋታቸው ለመሸነፉ ሳይሆን የፈረንሳይም ፣ የእንግሊዝም መሪዎች ካሳን ወግተው ካሸነፉ በኋላ ፣ 'ለምን ወጋኸው' ብለው እንዳይቀየሟቸው ነው ። ቁጥሩ የበረከተ ያልሠለጠነ ጦርም ቁጥሩ ባነሰና በሠለጠነ ጦር እንደሚሸነፍ በደንብ ያጤኑት አይመስልም ።

ነገር ግን ፣ ሁለቱ ባላጋራዎች ሲዘጋጁ ከርመው ፣ በ1863 ዓ. ም. ተክለ ጊዮርጊስ ደጃች ካሳን ለማስገበር ባላቸው ዓላማ ከዘቢጥ ተነሥተው የተከዜን ወንዝ ተሻግረው ወደ ዐድዋ ጉዞ ዠመሩ ። ከስልቻ ጤፍ ጋር ያመሳሰሉት 60 000 የሚሆነው ጅምላ ጦር ጥቂቱ አሮጌ ጠበንጃ ፣ አብዛኛው ጦርና ጋሻ ይዞ ተከትሏቸዋል ።[1] በርሳቸው አንጻር የሚገኙት ደጃች ካሳ ፣ የተከተላቸው ወታደር ቁጥሩ ከ12000 እንደማይበልጥ ጸሐፊው ሁሉ አምኖበታል ። ነገር ግን ፣ ይኸው ቁጥሩ ያነሰው ጦር ፣ አንደኛ ፣ ስድስትና አምስት ኢንች ውፍረት ያለው ሞርታር ፣ 12 መድፍና ብዙ ዘመናዊ የስናድር ጠበንጃ ይዟል ። ሁለተኛ ፣ ከጠባዩ ምሽግነት ያለውን ሥፍራ ይዞ የጦር ልምምድ ባላቸው በነኪርክሃም ፣ በነሉዊ ሠልጥኖ መሣሪያውን ደግኖ በደንብ ይጠባበቃቸዋል ።

ንጉሡ ፣ አስቀድመው ወታደራቸውን በሚከተለው ዐይነት አሰለፉት ። አንደኛ ፣ በቀኝ በኩል የላስታ ፣ የዋግ ፣ ሰባት ቤት ወሎ በዋግሹም ተፈሪ አዝማችነት ፤ ሁለተኛ ፣ በግራ በኩል የጐጃም ጦር በልጃቸው በራስ ብሩ አዝማችነት ፤ ሦስተኛ በመካከል የዋድላ ፣ የደላንታ ፣ የጋይንትና የቤገምድር ጦር በልጃቸው በራስ አበራ አዝማችነት ፤ ግንባር ቀደም የስሜን ፣ የጸለምት ፣ የወልቃኢት ፣ የጸገዴ ጦር በራስ መሸሻ ቴዎድሮስ አዝማችነት አሰልፈው ፣ በሐምሌ 5 ቀን 1863 ዓ.ም. ዐድዋ አጠገብ አሰም ከሚባለው ወንዝ (ፈለገ አሰም) ዳርቻ ከነጦራቸው ደርሰው ተኩስ ሲከፍቱ ፣ የደጃች ካሳ መድፈኞችና ነፍጠኞች ተገን ይዘው በረጋ መንፈስ እያነጣጠሩ እንደ ልብ ጠላቶቻቸውን ያጭዱ ዠመር ።

ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ፣ በፈረስ ላይ ሆነው "ግፋ በለው" እያሉ ወታደራቸውን እያበረታቱ ለማዋጋት ሲሞከሩ ፣ የተቀመጡበት

---

1 የዘመተውን የተክለ ጊዮርጊስን ጦር ቁጥር ቡርዛክ ከ30,000 ላይ አቁሞታል ። Coursac, Le Regne de Yohannes, pp. 71—72.



ፈረሳቸው በመድፍ ጥይት ተመትቶ ሲወድቅ ፣ የጦርነቱን ኃላፊ እንደ ያዛቸው ወደቀ ። ንጉሡም ከፉኛ አወዳደቅ ወድቀው ከጭንቅላታቸው ላይ ቆሰሉ ። ወታደሮቻቸውም ንጉሡ የሞቱ መስሏቸው ተደናግጠው ወዲያና ወዲህ ሲራወጡ ፣ ካሳ ከነጦራቸው ከምሽግ ወጥተው ወታደሩን እያባረሩ ሲወጉ ፣ ተክለ ጊዮርጊስንም ወዲያው ማረኩዋቸው ። በመዠመሪያ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስን ማርኮ ለጌታው ለደጃች ካሳ ያቀረባቸው ልጅ አጽብሐ እንደሚባል ፣ ጦርነቱም ከጧት ዠምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት መፍጀቱ ፣ ምርኮ ስብሰባ እስከ ሦስት ቀን መውሰዱን ፣ ከዚያ አሸናፊው ደጃች ካሳ ያፄ ተክለ ጊዮርጊስን ሰው ከልብ እንደ ማራቸው ገልጸው ፣ "ደም በተፋሰሳችሁበት አገር (በትግራይ) አትደሩ ፤ የተከዜን ወንዝ ተሻግራችሁ በሰላም አገራችሁ ግቡ ፤ እኔም እመጣለሁ" በሚል ዲስኩር ማሰናበታቸውን ዜና መዋዕላቸው ይገልጻል ። ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ግን ፣ ከነልጆቻቸው አምባ ሰላማ* በሚባለው ተራራ ታስረው ጥቂት ዘመን እንደኖሩ ሞቱ ።*

ሌላ መረጃ ደግሞ ፣ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስን የማረኳቸው ራስ አሉላ መሆናቸውን ይጠቅሳል ። ለምሳሌ "አሉላ አባነጋ" በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ ፡—

ንጉሥ ማራኪ ከነዘውዱ

የበዝብዝ አሽከር አሉላ ወንዱ

ከነፋስ የፈጠነ

በወንድነቱ የተማመነ

ከንዱ ብርቱ እንዳንበሳ

በጠላት ሠፈር የሚያገሳ

ተብሎ ተገጥሞላቸዋል ።[1] እንዲሁም ዘውዴ ገ/ሥላሴ ጦርነቱ አራት ሰዓት ብቻ እንደ ፈጀ ገልጸዋል ።

---

* አምባ ሰላም የሚገኘው ገረዓልታ ውስጥ ሲሆን ፣ ገረዓልታ በእንደርታ አውራጃ ውስጥ የሚገኝ ወረዳ ነው ።

1 ስለ ተክለ ጊዮርጊስ አጭር ታሪክ
J. B. Coulbeaux, Histoire Politique et Religeuse d'Abyssinie, Vol. II (Paris) p. 438.
Luca dei Sabelli, Storia di Abyssinia, Vol. III (Roma, 1938), p. 238.




ደጃዝማች ካሣ በራስ ወርቅ ማዕረግ

(ከአርኪቪዮ ኢትዮፒኮ መዝገብ ቤት ፣ ሮማ)



ዐፄ ምኒልክ

(ከሮንጃትና ከሄኖን ፡ ፎቶ)



ዐፄ ተክለጊዮርጊስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት

(ፐብሊክ ሪኮርድ ኦፊስ ለንደን)

በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ። ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ፡ አፄ፡ ተክለ፡ ጊዮርጊስ። ይድረስ፡ አንባሳደር፡ ከሰው መርጦ ከነገሠው ንጉሠ፡ ነገሥት ናፖሊዮን። እንዴት፡ አሉ፡ ደኅና፡ አሉን ልጆቼን


እኔ የርስዎን ወዳጅነት፡ እጅግ እፈልገዋለሁ በረከትዎ፡ ለሰጡለዎ፡ ወዳጅ፡ ነበር፡ ነገር ግን መንገዱ፡ አልተመቸኝም፡ የፍቅር፡ መረጃት ብቻ፡ መስደዴ፡ የመሳሳክ፡ መጀመርያ፡ እንዲሆን፡ የርስዎንም፡ ፍቅር መፈለጌ ምልክት፡ ይሆንም፡ ብየ ነው። አሁ፡ ቱርክ ግን ያክፉትን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ከምክርዎና ከፍቅርዎ፡ ጋራ፡ በግዚአብሔር፡ ኃይል፡ አቀናዋለሁ፡ ብየ አስባለሁ። እኔ፡ በነገሬ፡ ትቸልበዎ፡ እንዲገባ፡ ያገሬም፡ ነጋዴ፡ ንብቶ፡ እንዲገበይ፡ ከጅም የምፈልገው፡ በርስዎ፡ ፈቃድ፡ እንዲሆንልኝ፡ እወዳለሁ። ቆንሲል ካሳ፡ አጼ፡ ሳይቴ፡ አገ ቀ፡ ሰባቴ፡ ተገዝቶ፡ ታዞ፡ ይኖር፡ ነበረ፤ እርሱንም እኔ፡ ሹሜ፡ አገር፡ ጠብቅ፡ ብየ፡ ብተውው፡ ለምጠ፡ አልታዘዝም፡ አለ፡ አሁን፡ ግን፡ የምጠይቀው፡ ነኝና፡ አይፍረዱ፡ ብኝ። ይህን፡ መል ክት፡ በሊሳ፡ እጅ፡ መስደዴ፡ ለውን፡ ዓላማን፡ ነው።

ከተፃፈበት፡ ለደብተ፡ በጎሔ፡ ከከም፡ ገት፡ መቅ፡ ለጽላ፡ የሁለት፡ ዓመት፡ ዘዘመን ማርቆስ ወ ንጌላዊ፡ በሐምሌ፡ መጀመር ያ፡ ቀን።



## ፳፬ ተክለጊዮርጊስ ለፈረንሳይ ንጉሠ ነገሥት ለናፖሊዮን የጻፉት

(ሚኒስቴር ዴዛፌር ኢትራንዤር ሚሟር ኤ ዶክዩማ አፍሪክ • ፓሪስ)



## ምዕራፍ ሦስት

### የደጃች ካሳ ምርጫ ንጉሥ ነገሥትነት - ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር የተለዋወጡ ዋቸው የወዳጅነት ደብዳቤዎች

ከሦስቱ የኢትዮጵያ ኃያላን መሳፍንት ባላንጣዎች መካከል ተከለ ጊዮርጊስ ሲሞቱ ፣ የቀሩት የትግሬው መስፍን ደጃች ካሳና የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ መሆናቸው ነው ። የሁለቱን ትግል እጣምረን ከመመልከታችን በፊት ፣ ብዙ ጊዜ ባለፈው ስሊ እነሣናቸው ስለ ደጃች በዝብዝ ካሳ ባጭሩ እንመልከት ። የሕይወት ታሪካቸውን የሚገልጽ በዘመናቸው የተጻፈና የታተመ ዜና መዋዕል ስለሌላቸው ፣ በቀላሉ የሕይወት ታሪካቸውን በተለይ ከመንገሣቸው በፊት ያለውን ማግኘት ችግር ነው ። ያልታተመ የእጅ ጽሑፍ እንዳለ ለማግኘት አልቻልንም ። በመጨረሻ ባሕሩ ታፍላ ያሳተሙት እንሚለው ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል ።

የደጃች ካሳ አባት ሹም ተምቤን ምርጫ ፣ እናታቸው ወይዘሮ ሥላስ (ወለተሥላሴ) ይባላሉ ። ካሳ የተወለዱት ሐምሌ 5 ቀን በ1829 ዓ. ም. በማይ በሀ (ተምቤን) ነው ።[1] ባባታቸው በኩል በጐንደር መንግሥት ካፄ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ ሞት ወዲህ (1747 ዓ. ም.) መዝ መሪያውና ኃይለኛው የትግራይ መስፍን ከነበሩት ከራስ ስሑል ሚካ ኤል ፣ ከራስ ወልደ ሥላሴና ከደጃች ሰባጋዲስ ይወለዳሉ ።

ካሳ ፣ በጐልማሳነታቸው ጊዜ (1856—7) ላፄ ቴዎድሮስ እሽከር ነት ስለገቡ ለወንድሞቻቸው ፣ ለጉግሣና ለማሩ ፣ የደጃዝማችነት ማዕ ረግ ሲሰጣቸው ፣ ለርሳቸው የባላምባራስነት ደረጃ ተሰጣቸው ። ይኸውም በ33 ዓመት ዕድሜያቸው አካባቢ መሆኑ ነው ። ታላላቆቻቸው ቢሆ ኑም ፣ ወንድሞቻቸው የደጃዝማችነቲ ማዕረግ ሲያገኙ ፣ እርሳቸው በባላ ምባራስነት መወሰናቸው በተለይ ከርሳቸው በዕድሜ 11 ዓመት የሚ ያንሱት የሸዋው መስፍን ምኒልክ በእማችነት ደጃዝማች ሲባሉ ፣ የእር ሳቸው ባላምባራስነት ሳያሳዝናቸው አልቀረም ። ያሸፈታቸውም

1 Zewde G.S., The Process of Reunification, Vo. II, pp. 68—69.

ምክንያት ይኸው ነው ይባላል ። በሸፈቱበት ጊዜ ካሤ ቴዎድሮስ ለትግራይ ግዛት የሚላኩትን ጉልበት ሲሰማቸው እየተዋጉ ፥ ዐቅም ሲያንሳቸው ወደ ደንከል በረሃ እየሸሹ ከባላባቱ ጋር በመተባበር ኑረዋል ። በዚያን ጊዜ ነው ከባላባቱ ልጅ ከደንከሊቱ ተወላጅ ጋር ተጋብተው እርእያን የወለዱ ።

ዋግሹም ጐበዜ ፥ ካሤ ቴዎድሮስ ሸፍተው ሥልጣናቸውን በላስታ፥ በትግራይና በትግሬ ላይ ባስፋፉበት ሰዓት (1857—87) ባላምባራስ ካሳ ከርሳቸው ጋር ተስማሙ ። ጐበዜም እኅታቸውን ወይዘሮ ድንቅ ነሽን ስላገቡ ፥ በዋግሹም ጐበዜ ደጋፊነት ካሳ የተምቤንን ግዛት ተቀብለው ደጃዝማች ተባሉ ። ከዚያም ዐፄ ቴዎድሮስ ደጃች ካሳን ለመደ ምለስ እነ ደጃዝማች ደረሰን ፥ እነ ደጃች ተክለ ጊዮርጊስን ቢልኩ ባንድ ወገን የካሳ ኃይል ፥ በሌላ ወገን በዚያ ዘመን የተነሣው በሽታ ፈጃቸው ። በመጨረሻም በሁሉም ረገድ ኃይላቸው እየበረታ ሲሔድ ላማቻቸው ለዋግሹም ጐበዜ መታዘዙንም ትተው ፥ ራሳቸውን የቻሉ የትግራይና የትግሬ መስፍን ሆኑ ። ኃይላቸውም እየበረታ ስለሔደ ማንም በዚያ አካባቢ ሊቋቋማቸው አልቻለም ። ዐፄ ቴዎድሮስ የሾሚ ቸው ደጃዝማች ባሪያውም ፥ በጦርነት ተሸንፈው በካሳ ተማረኩ ። ባሪያውም የተማረኩ ለት ፥ "አንዱን ዐይኔን ለቴዎድሮስ ስዋጋ አጥቻ ለሁ ፥ ሌላውን ደግሞ ላንተ መንግሥት አጠፋዋለሁ" ብለው ከተማ ረኩበት ጊዜ ዠምሮ ለካሳ ታማኝ አገልጋይ ሆኑ ።

ደጃች ካሳ ፥ ከውጭ መንግሥታት መሪዎች ጋር በቀጥታ እየተ ጻጻፉ ራሳቸውን ማስተዋወቅ ዠመሩ ። በነሐሴ 3 ቀን በ1860 ዓ.ም. ለፈረንሳይ ንጉሠ ነገሥት ለናፖሊዮን ሣልሳይ በጻፉት ደብዳቤ ላይ ፥

> "በስመ አብ. . .መልእክት ዘተፈነወት እምኀበ ደጃዝማች ካሳ ርዕሰ መኳንንት ዘኢትዮጵያ — ትድረስ ለሉዊስ ናፖልዮ ቦናፓርት (ሉዊ ናፖሊዎን) ንጉሠ ፈረንሳይ ፥ እግዚአብሔር የሾመኝ በመስከረም ነው ። በመስከረም ወረቀት እንዳልሰድ እንግሊዞች ከአገሬ በእንግድነት መጥተው ብኝ ነበር ። የበካፋ ፥ የፋሲል የነዚህ የነገሥታቱ ልጅ ነኝ ። ከመሳፍንት የሚካኤል (ራስ ስሑል ሚካኤል) የወልደ ሥላሴ) ራስ ልጅ ነኝ"[1]

1 D. Abbadie, Dessiers d'Antoine D'Abbadie (Bib. Nat. Paris) No. 28-164.



ደጃች ካሳ "እግዚአብሔር የሾመኝ በመስከረም ነው" ያሉት በዚህ ወር 1860 ዓ.ም. በትግራይ ዐፄ ቴዎድሮስ የሾሟቸውን ደጃዝማች ባሪያውን በደብረሲና ላይ ተዋግተው በማሸነፍ ግዛታቸውን ያረጋገጡበትን ጊዜ ለመግለጥ ነው ። በደብዳቤያቸው ላይ ዐፄ ዳዊትን ትተው ዐፄ በካፋን የጠቀሱትም ፥ በካፋ የዳዊት ወንድም ስማቸው በጐንደር ከዳዊት የበለጠ ደመቅ ብሎ ስለሚጠራ ነው ። ዳዊትና በካፋ በኢትዮጵያ ተከታትለው የነገሡበት ዘመን 1708—1713 ዓ.ም. እና 1713—1722 ዓ.ም. ነው ።

እላይ እንዳመለከትነው ፥ ካሳ የተወለዱት በ1825 ዓ.ም. ስለሆነ በ1811 ወይም በ1812 ዓ.ም. ከተወለዱት ካሤ ቴዎድሮስ 14 ወይም 15 ዓመት ያንሳሉ ። በ1836 ዓ.ም. ከተወለዱት ከምኒልክ 11 ዓመት ሲበልጡ ፥ ከተክለ ጊዮርጊስ ጋር እኩዮች ናቸው ። እንግዲህ ባለፈው እንደ ተመለከትነው ፥ እንግሊዞችን ሲመጡ በምልካም ተቀብለው ፥ ሲሔዱም ሸኝተው ባስተናገዱበት ምክንያት በተሰጣቸው ዘመናዊ መሣሪያና በጦር አሠልጣኞቹ በነኪርከሃም እርዳታ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስን ለማሸነፍ ስለቻሉ ፥ በትግራይና በትግሬ ከዚያም ውጭ በቤገምድርም ፥ በጐጃምም ፥ በሸዋና በወሎም ሊቋቋማቸው የቻለ ኃይል ስለ አልነበረ ፥ ወደ ንጉሠ ነገሥትነት የሚያደርሰው መንገድ ለርሳቸው ተከፈተ ።

ግዛታቸው በጠቅላላው የትውልድ አገራቸው ተምቤንና እንደርታ በመሆኑ ፥ ይነስ ይብዛ አካባቢውን ሁሉ ደምስሰው የትግራይና የትግሬ የበላይ ገዥ በመሆናቸው ፥ ባላንጣቸው ተክለ ጊዮርጊስ በምጥዋ በኩል ጳጳስ እንዳያስመጡ እየተከላከሉ ራሳቸው ግን ፥ በ1861 ዓ.ም. በአለቃ ብሩና በመሐመድ አብድራሂም መሪነት ለግብጹ ገዥ ለከዲቭ ኢስማኤልና ለፓትሪያርኩ ፥ ለአባ ድሜጥሮስ 20 000 የማሪያ ትሬዛ ብር ገጸ በረከት ልከው ፥ አቡነ አትናቴዎስን ከግብጽ አስመጥተው በእጠገባቸው እስቀምጠው የንግሣቸውን ቀን ሲጠባበቁ ቆዩ ።[1]

ካሳ ፥ እነ ጄኔራል ናፒዬር ወደ ሎንዶን ከተመለሱ ወዲህ ወዳጅነታቸውን በመልእክት እያጠበቁ ሔደዋል ። እንግሊዞችም ለዓላማቸው ሲሉ ደብዳቤም ፥ ገጸ በረከትም እየላኩ ወዳጅነታቸው እንዲጸና አደረጉ ። ደጃዝማች ካሳም በበኩላቸው ደብዳቤም ፥ ገጸ በረከትም እያዘጋጁ በጊዮርጊስ ርዕሰ መማክርትና በልጅ ወርቄ ምርጫ እጅ ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ወደ ግራንቪል ፥ ወደ ወዳጃቸው

1 ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ፥ ዋዜማ ፥ ገጽ 97-98 ።

ወደ ናፒየርና ወደ ንግሥት ቪክቶርያም እየላኩ ወዳጅነታቸውን በማጥበቅ የራሳቸውን የገዥነት አቅዋም እያጸኑ ሔዱ ።

ካፄ ተክለ ጊዮርጊስ ከመዋጋታቸው ካንድ ዓመት በፊት በነሐሴ 29 ቀን 1862 ዓ.ም. ለግራንቪል በጻፉት ደብዳቤ ላይ፣ "እጅግ ደስ ብሎኛል ፤ እርስዎን ያህል ወኪል በለንደን አድርጌያለሁና. . . የማምና ቸውን ርዕሰ መማክርት ጊዮርጊስንና* ወርቄ ምርጫን ልኬ ሰድጃ ቸውአለሁ ። ገጸ በረከት ለእንግሊዝ ንግሥት ሊሰጡ በመልካም እንዲ ገቡ ቢያደርጉልኝ እጅግ ደስ ይለኛል ። የፍቅር ምልክት ነው ። ደግ ሞም የጥበብ ነገር ሥራ የሚያስተምር በሀበሻ ቢወጣልኝ (ወደ ሀበሻ ቢመጣልኝ) እወዳለሁ. . ." የሚል ይገኝበታል ።

ለንግሥት ቪክቶሪያ የተላከው የገጸ በረከት ዐይነት አንድ የወ ርቅ ድሪ፣24 ጣምራ ጦር፣ አንድ የወርቅ ኮርቻ፣ አንድ የወርቅ ል ባ ልባ፣ አንድ በወርቅ የተከፈፈ በርኖስ፣ አንድ የወርቅ ጫማና ይኸን የመሳሰለ ያለበት መሆኑ መልክተኞቹ በጥር 6 ቀን 1863 ዓ.ም. ከእስክንድርያ ለግራንቪል ቀደም አድርገው በጻፉት ደብዳቤ ላይ ተመልክቷል ።[1]

ከውጭ መንግሥታት መሪዎች ጋር፣ በዚህ ዐይነት እየተጻጻፉ ቆይተው ተክለ ጊዮርጊስን ካሸነፉ ወዲህ ደግሞ፣ ባገር ውስጥ ለታመ ነላቸው የትግራይና የትግሬ፣ እንዲሁም የአማራ መኳንንት ሹመትና ግዛት እያደላደሉ ሥልጣናቸውን አጠበቁ ። ተክለ ጊዮርጊስን ካሸነፉ በኋላ ከመንገሣቸው በፊት ወደ ሸዋ ዘምተው ምኒልክን የማስገበሩን ጉዳይ ለሌላ ጊዜ መድበውታል ። በዚህም ካፄ ቴዎድሮስ እያያዝ ለየት ያለ የመታገሥ፣ በቅድሚያ ኃይልን የማጠናከርና የማመዛዘን ዘዴ እንደ ነበራቸው መገንዘብ ይቻላል ።

ባፄ ተክለ ጊዮርጊስ ላይ ያገኙት ድል አድራጊነት፣ ከእንግሊዞች ባገኙት መሣሪያ መሆኑ ስለሚሰማቸው፣ በዚያው ተክለ ጊዮርጊስን ድል ባደረጉበት ወር በዐሥራ ሰባተኛው ቀን እንደዚህ የሚል የደስ ታና የምሥራች ደብዳቤ ለንግሥት ቪክቶርያ ጻፉ ።

> "በስመ አብ. . .መልእክት ዘሥዩመ እግዚአብሔር ካሳ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ይድረስ ከከበሩት ንግሥት ቪክቶሪያ ዘሀገረ እንግልጣር. . . በርስዎ ምክር፣ በርስዎ ፍቅር ጸንቻለሁ ። እጅግ ደስ ብሎኛል ። አሁንም ጠላቴ ዋግሹም ጐበዜ፣ ዐጤ ተክለ ጊዮርጊስ የተባለው፣ ከዐድዋ ከከተማዬ መጥቶ ተዋጋነ ድል አደረግሁት ፤ ከሠራዊቱ ጋር እርሱንም ያዝሁት ፤ ከጠላቴ ሁሉ አንድ እንኳን ያመለጠ የለም ። ሁሉ ተለቅመው ከጄ ገቡ ፤ ከሸዋው ምኒልክ በቀር። የኢትዮጵያን መንግሥት ሁሉ በእግዚአብሔር ኃይል በእጄ አደረግሁት ። እንደ ጥንት ፍቅራችን አይርሱኝ ይዘኑ ልኝ ። እኔም የእንግሊዝን መንግሥት ፍቅር አረሳሁም ። እንደ ጥንቴ ነኝ ። አባቶቼና አባቶችዎ፣ እኔና እርስዎ እንደ ተፋቀርነ ካሮፒያ (አውሮፓ) ነገሥታት ጋር ሁሉ እንዲያ ፋቅሩኝ እለምነዎአለሁ. . .ተጽሕፈ በ22 ቀን ሐምሌ 1863 ዓ.ም. በዐድዋ ከተማ"[1]

በዚሁ ዐይነት ተመሳሳይ ደብዳቤ እንደ ቅርብ ወዳጅ ለሚመለከቱት ለጄኔራል ናፒየርም ጽፈዋል ።

በነዚህ ደብዳቤዎች ላይ ምንም እንኳን፣ ራሳቸውን ንጉሠ ነገሥት ቢያደርጉም፣ ገና ሥርዓተ ንግሣቸውን ስለ አላከበሩ ስማቸውንም ያው እንደ ተለመደ ካሳ ብለው ንጉሠ ጽዮን የሚለውን አክለውበታል ። ለንግሥቲቱ በጻፉት ላይ፣ "አባቶቼና አባቶችዎ፣ እኔና እርስዎ እንደ ተፋቀርነ. . ." ሲሉ ያወሱት የቅድመ አያታቸው የደብብ ወንድም ራስ ወልደ ሥላሴ በነ ሔንሪ ሶልት አማካይነት ከእንግሊዝ ንጉሥ ከሣልሳይ ጆርጅ ጋር ደብዳቤ እየተጻጻፉ ወዳጅነት ጀምረው የነበረ ውን ሲያወሱ ነው ።[2]

ይኸ ሁሉ ከሆነ በኋላ፣ ደጃች ካሳ በሐምሌ 5 ቀን 1863 ዓ.ም. ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስን ድል ካደረጉ ወዲህ፣ እስከ ጥር ወር ድረስ ባለው የስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለሥርዓተ ንግሥ የሚያስፈልገውን ማናቸውንም ዝግጅት አደረጉ ። ድግሱም ሲሰናዳ ቆይቶ፣ በጥር 13 ቀን 1864 ዓ.ም. በአክሱም ቤተ ክርስቲያን ስመ መንግሥታቸው "ዮሐንስ አራተኛ" ተብሎ፣ በጳጳሱ በአቡነ አትናቴዎስ እጅ ተቀብ ተው በሥርዓተ መንግሥት ነገሡ ። በዚሁ ንግሥ ምክንያት 3 ቀን በዓል ሆኖ፣ ለግብር 4 000 ሠንጋ ታርዶ፣ 50 ጉንዶ ማር የፈጀ 150000 ገንቦ ጠጅ ቀርቦ በደስታ ሲበላ፣ ሲጠጣ እንደ ሰነበተ ሙሴ

---

* ሳሙኤል ጊዮርጊስ የቴዎድሮስን አስተርጓሚ ወይስ ባላምባራስ ጊዮርጊስ የሚባሉትን የግሪክ ተወላጅ? የሚመስለው ግን ሳሙኤል ጊዮርጊስ ነው ።

1 Public Record Offce, ( London( Fol (28) 121133. p. 197



---

1 Ibid.

2 ራስ ወልደ ሥላሴ ለጆርጅ ሣልሳዊ የጻፉትን ደብዳቤና ተመሳሳይ
S. Rubenson, The Survival of Ethiopia Independence (London: Heineman— Association with A.A. U. Press 1978) pp. 48—52

ጂ. ዲወ በዝርዝር ጽፎ አትሞታል።[1] ያገራችንም ጸሐፊ አለቃ ዘዮሐንስ የንግሡን ሁኔታ በመጥቀስ ከነገሡ በኋላ፣ በቤተ መቅደስ ወርቅ መበተናቸውን ሠላሳ ቀን ሙሉ የደስታ በዓል መደረጉን ጠቅሰውታል።

ይኸም ስለሆነ፣ ያው ስለ ርሳቸው ዙፋንና ሥልጣን ከተዋጋው ውስጥ የሞተው ሞቶ በሕይወት የተረፈው ወታደርና መኳንንት በንግሣቸው ጊዜ በመብል፣ በመጠጥ፣ በሽልማት፣ በሹመት ሲደሰት፣ የተሸናፊው የተክለ ጊዮርጊስ ወገን ግን፣ በተለይ የላስታና የሰቆጣው ተወላጅ ሐዘንተኛ ነበር። ምርኮኛውም ከነጌታው በግዞት ይማቅቃል። የተክለ ጊዮርጊስ ባለቤት እቴጌ ድንቅነሽ ብቻ በእህትነታቸው ብዙ መጉላላት ሳይደርስባቸው፣ ላጭር ጊዜ በግዞት ወደ ሽሬ ተልከው በመጨረሻም ይኸው አገር እንደ ግዛት ተሰጧቸው[2] ያፄ ዮሐንስን እንደራሴ ራስ ቢቶደድ ገብረ ኪዳንን አግብተው ደጃዝማች ሥዩም አባ ጐበዝን ወልደዋል። ምንም ዐፄ ዮሐንስ የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ቢጭኑ ተከፋፍሎ መኖር የለመደው የሐማሴን፣ የቤገምድር፣ የወሎ፣ የጐጃም፣ የሸዋ መሳፍንት ሁሉ ገና አሜን ብለው አልገበሩላቸውም። እንኳን እነዚህ ራቅ ያሉት ከመረብ ወዲያ ያሉትም የሐጸጋና የጸሐዘጋ ባላባቶች እነ ወልደ ሚካኤል (እምቢ አለ ወልዱ) ገና አልተቀበሏቸውም። በአከለ ጉዛይም ደጃዝማች ካሳ ጐልጃ (ካሳ አባ ከይሲ) በዚሁ በነገሡበት ዓመት ሸፍተው ሲዋጉ ተማርከው ሳለ በ1867 ዓ.ም. ላይ ተገደሉ።[3] ነገር ግን፣ ከነገሡ ዠምሮ እስከ ሰባት ዓመት ድረስ ከሁሉ የበለጠ ላፄ ዮሐንስ ዋና ባላንጣ ሆነው የተገኙት፣ የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ናቸው። የርሳቸውንም ሁኔታ በሚቀጥለው ምዕራፍ እናነባለን።

---

1 Douin, T. III, 2e Partie, pp. 333—335

* የዐፄ ዮሐንስን ታሪክ ነጋሥት ሼን የሚባል ፈረንሳይ ዋናውን ከነትርጉሙ አሳትሞታል።

2 Ibid

3 Ibid





ዐፄ ዮሐንስ ከልጃቸው ከራስ አርአያ ጋር

(ከታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ)


በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ፡፡
አሜን፡፡

መልእክት፡ ዘሰዩመ፡ እግዚአብሔር፡ ካሳ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡
ዘኢትዮጵያ፡፡ ይድረስ፡፡

ከከበሩት፡ ንግሥት፡ ቢክቶርያ፡ ዘሀገረ፡ እንግሊጣር፡ እጅ ንግ፡ እንደ
ተ፡ ለሉ፡ አኔም፡ ደህና፡ ነኝ፡ እግዚአብሔር፡ ይመስገን፡፡ ሰሰለ፡ ከብረተ
ም፡ ሰላምታዎን፡ ከጓቹ፡ በኋላ፡ በርሰዎ፡ ምክር፡፡ በርሰዎ፡ ፍቅር፡ እን
ቴ፡ አለሁ፡፡ እጅግ፡ ደስ፡ ብሎኛል፡፡ አሁንም፡ ጠላቴ፡ ዋግ፡ ሹም፡ ጉበ
ዜ፡ ለጤ፡ ተከለ፡ ጊዮርጊስ፡ የተባለው፡፡ ካንሬ፡ ለድዋ፡ ከከተፔዬ፡ መ
ጥቶ፡ ተዋጋኝ፡ ድል፡ አደረግሁት፡፡ ከሰራዊቱ ጋራ፡ አርሱንም፡ ያዝሁ
ት፡ ከጠላቴ፡ ሁሉ፡ አንድ፡ አንዱ፡ ያመለጠ፡ የለም፡ ሁሉ፡ ተሰቀመው፡
ከጄ፡ ገቡ፡፡ ከሺዋው፡ ምኒይልክ፡ በቀር፡፡ የኢትዮጵያን፡ መንግሥት፡
ሁሉ፡ በእግዚአብሔር፡ ኀይል፡ በጄ፡ አደረግሁት፡፡ እንደ፡ ጥንት፡ ፍቅራች
ን፡ ሰይርሱኝ፡ ይዘነልኝ፡፡ አኔም፡ የእንግሊዝን፡ መንግሥት፡ ፍቅር፡ አረሳ
ሁም፡፡ እንደ፡ ጥንቱ፡ ነኝ፡፡ አባቶቼና፡ አባቶቹም፡ እኔና፡ እርሰዎ፡ እንደ፡ ተ
ፋቀርን፡ ከሮጥያ፡ ነገሥታት፡ ጋራ፡ ሁሉ፡ አንድያ፡ ፋቅሩኝ፡፡ ሰምነም፡
አለሁ፡፡ የክርስቲያን፡ ሃይማኖት፡ እንዲጠና፡ ከሁሉ፡ ጋራ፡ ፍቅር፡ እፈ
ልግ፡ አለሁ፡፡ እግዚአብሔር፡ አይመኑ፡ ጤና፡ ይስጥልኝ፡፡ አሜን፡፡



ተጽሕፈ፡ በ፳፩ ቀን፡ ሐምሌ፡፡
በ፲ወ፰፻፷ወ፲ ዓመተ፡
ምሕረት፡፡
በአድዋ፡ ከተማ፡፡



ደጃዝማች ካሣ (በኋላ ዐፄ ዮሐንስ) ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት

(ፐብሊክ ሪኮርድ ኦፊስ ፣ ለንደን)

10 mars 1870


[illegible]



[illegible]

ደጃዝማች ካሣ ሳይነግሡ በፊት ለፈረንሳዩ ንጉሠ ነገሥት ለናፖሊዮን የጻፉት

(ሚኒስቴር ዴዛፌር ኤትራንዠር ሚሟር ኤ ዶክዩማ አፍሪክ ፡ ፓሪ)



[illegible]

**ደጃዝማች ካሣ (በኋላ ዐፄ ዮሐንስ) ለእንግሊዝ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለግራንቪል የጻፉት**

**(ፐብሊክ ሪከርድ ኦፊስ ፣ ሎንዶን)**

# ምዕራፍ አራት

## የዙፋን ባላንጣዎች ያፄ ዮሐንስና የንጉሥ ምኒልክ ፉክክር በወዳጅ ጠላት ፊት

ካፄ ቴዎድሮስ ሥልጣን መያዝ ቀደም ብሎ ባለው ጊዜ ውስጥ ደንበኛው እንደራሴ ራስ ዐሊና የስሜኑና የትግራዩ ገዥ ደጃች ውቤ የሥልጣን ባላንጣዎች እንደነበሩ ሁሉ ፣ ካፄ ቴዎድሮስ ሞትና ካፄ ተክለ ጊዮርጊስ መሸነፍ ወዲህ ደግሞ ፣ አንዲቷ ኢትዮጵያ በዮሐንስና በምኒልክ ተከፍላ የሁለት ነገሥታት አገር ሆናለች ። ሁለቱም በቤገምድርና በጐጃም ፣ በወሎ በላስታ አውራጃ ላይ የውስጥ ፍልሚያ ሲያሳዩ ፣ እንደዚሁም የውጭ መንግሥታትን ወዳጅነት አጥብቀው በደብዳቤና በየመልክተኞቻቸው አማካይነት ይሻሙ ነበር ። ሁለቱም የውጭን አገር መንግሥታት ወዳጅነት የሚሻሙት ፣ አጠገባቸው ባሉት አገር ጐብኝዎችና ነጋዴዎች ወይም ምጥዋ በሚቀመጡት ቆንሲሎቻቸው አማካይነት ነው ። የሽሚያውም ዋና ዓላማ ፣ የጦር መሣሪያ ከማግኘቱ ጐን ባላንጣን አስጠልቶ ራስን ለማስወደድ ነው ።

በዚህም ምክንያት ፣ ዐፄ ዮሐንስ ገና ከመንገሣቸው በፊት በወዳጅነት ታላቅ አለኝታ ጥለውበት የነበረው አንዱ ሙንሲንጀር ፓሻ የሚባለው ነው ። ይህ ሰው ዘሩ የስዊስ ሲሆን ፣ ሙሉ ስሙ ገርን አልቤርት ወርነር ሙንሲንጀር ነበር ። ከስዊስ አገር በንግድና ባገር ጥናት ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ ጠረፍ መጥቶ በምጥዋና በከረን ብዙ ጊዜ አሳልፎ ባገር ውስጥ የታወቀ ሆኗል ። የእንግሊዝ ጦር ዐፄ ቴዎድሮስን ሊወጋ በመጣበት ሰዓት ውስጥ—ዐወቅ እንደ መሆኑ መጠን የደጃች ካሳንና (ዮሐንስን) የእንግሊዞችን ግንኙነት በማቃናት ፣ ስንቅ በማሰባሰብ ፣ የውስጥ ወሬ በማጠናቀር ፣ ካገር ተወላጅ ውስጥ እየመለመለ መንገድ መሪ ፣ ወሬ ነጋሪ በማቅራረብ በብዙ አገልግሏል ። አክበር ዐሊ የሚባለው በመቅደላ ጦርነት ጊዜ ወሎዎቹ ባፄ ቴዎድሮስ ላይ እንዲነሡ በሚያስተባብርበት ሰዓት ዋናው የበላይ አዛዡ ሙንሲንጀር ነበር ።

ይኸው ሰውዩ ፣ ከመቅደላ ጦርነት በፊት በምጥዋ የፈረንሳይ ምክትል ቆንሲል በነበረበት ጊዜ እንግሊዞችንም ያገለግል ነበር ።

በኋላ ደግሞ ፣ ግብጾች በምሥራቅ ሱዳንና በምጥዋ አገዛዛቸውን ባጸኑበት ሰዓት ዜግነቱን ከፈረንሳይ ወደ ግብጽ አዞሮ የፓሻነት ማዕረግ አግኝቶ የዚህኑ ክፍለ ሀገር እንዲያስተዳድር አገረ ገዥ ተብሎ ተሾመ።

ሙንሲንጀር የፈረንሳይ መንግሥት ቆንሲል ሆኖ በምጥዋ በነበረበት ሰዓት ፣ ገና ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት ሳይሆኑ ፣ ለፈረንሳይ ንጉሠ ነገሥት ለናፖሊዮን ሣልሳይ በጻፉት ደብዳቤ ላይ "...ደጅ ጥናት አምኃ (ገጸ በረከት) እንዳልሰድ ፈቃድዎን እስካገኝ ብዬ ነው ፣ እንኳን ለክርስቲያን ለእስላምም ወዳጅ ያደርጋሉ* ። ለክርስቲያን ሁሉ ጠባቂው እርስዎ ነዎ ። ለወዳጅነት ለዋናው** አይንፈጉኝ" የሚል ደብዳቤ ጽፈው ስለ መጣላቸው መልስ ፣ እላይ ለጠቀስነው ለሙሲንጀር ሲጽፉ ፣

"...መልእክት ዘደጃዝማች ካሳ...ይድረስ ከቆንስል ሙንስንጀር...ለብዙ ጥበብ ለብዙ ምክር ይሆኑኛል የምልዎ ወዳጄ እርስዎ ነዎ ። ከብዙ ሰው ጋር ፣ ከፈረንሲስ ንጉሥ ጋር ያፋቅሩኛል ያልሁዎ እርስዎን ነው የፈረንሲስ ንጉሥ ደብዳቤ በሐዋጃ ኮስታን እጅ ደረሰኝ ። ምላሹን ግን እኔና እርስዎ ስንገናኝ እነግርዎአለሁ እንጂ በወረቀት አልጽፍም ። ወረቀት የያዙ ሰዎች እሰዳለሁ ሳጥኑን ለነዚያ ይስደዱልኝ" ብለዋል ። "ምላሹን እኔና እርስዎ ስንገናኝ እነግርዎአለሁ እንጂ በወረቀት አልሰድም" ያሉት ፣ ምናልባት በጽሑፍ የሰፈረ ነገር በሰው እጅ ወድቆ ባዜ ተክለ ጊዮርጊስ ዘንድ እንዳይሰማና እንዳያሳጣ ለጥንቃቄ የተደረገ ይመስላል ። ሳጥን የሚሉትም ምናልባት የጦር መሣሪያና ጥይት ይሆናል ። ነገር ግን ፣ ይኸን የመሰለ የወዳጅነት እምነት የጣሉበት ሙንሲንጀር ፣ ዮሐንስ ካቶሊኮቹን በተቃወሙበት ሰዓት ቀጥሎም ራሱ ከፈረንሳዮች ወደ ግብጾች በዞረበት ጊዜ ፣ ኃይለኛ የወዳጅ ጠላት መሆኑን ወደፊት እናነባለን ።

ምኒልከም ፣ ከመቅደላ አምልጠው ሸዋ ከገቡ ወዲህ ግዛታቸውን በሸዋና በሸዋ ዙሪያ ፣ በወሎ እያስፋፉ በሚያስተዳድሩበት ሰዓት ፣ "ሞዓ እንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት" በሚል ማኅተም ይጠቀሙ ነበር ። ይኸንንም ስመ መንግሥት ለማጽደቅ ሲሉ ከእስክንድርያ ጳጳስ ለማስመጣት ከከዲቭ ኢስማኤል ጋር ይላላኩ ነበር ። እንደዚሁም እንዳዜ ዮሐንስ የእንግሊዝንና የፈረንሳይን ወዳጅነት ለማግኘት በደብዳቤ ይሻሙ እንደ ነበረ በፓሪስ ፣ በሮማና በሎንዶን ቤተ መጻሕፍት የሚገኙት ሰነዶች በግልጽ ያመለክታሉ ።

* እንኳን ከክርስቲያን ከእስላምም ይወዳጃሉ ለማለት ነው ።
** ለባዶው ለንጹሑ ወዳጅነት ።



በፊት ባዜ ተክለ ጊዮርጊስ ዘመን በ1861 ዓ.ም. ለናፖሊዮን ሣልሳይ በጻፉት ደብዳቤ ፣

"...የተላከ ከንጉሥ ምኒልክ ሀገረ ሸዋ...ይድረስ ለንጉሠ ነገሥት ናጶልዮን ዘሀገረ ፈረንሳይ እንደ..ት ነዎ እጅግን... የመልካም ሰውነትዎን ወሬ እየሰማሁ የርስዎን ወዳጅነት እጅግ እፈልጋለሁ ። የፈረንሲስና የሸዋ ፍቅር የተጀመረው በእያቴ በሣህለ ሥላሴ ነው ።* ከሌላ (ከሌሎች) ክርስቲያን ነገሥታት ወዳጆችዎ ጋር እንዲያስተዋውቁኝ" የሚል ይገኝበታል ። አሁን ደግሞ ባዜ ዮሐንስ ዘመን ፣ 'ንጉሠ ነገሥት' የሚል ማኅተም ካሠሩ በኋላ ፣ በ1866 ዓ.ም. ከሙንሲንጀር ቀጥሎ ምጥዋ ለሚቀመጠው የፈረንሳይ ቆንሲል ሲጽፉ ፣ "የተላከ ከንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ዘኢትዮጵያ ይድረስ ለቆንሲል ፈረንሳዊ ዶሳርዘከ...የርስዎን ጅግነት ርዕሰ መማክርት ጊዮርጊስ ነገረኝ** ስለዚህ ነገር ፍቅርዎን ፈለግሁኝ ። ከአውሮፓ ነገሥታት ሁሉ እንዲያፋቅሩኝ ብርሃን በኢትዮጵያ እንድትገባ እንዲጥሩልኝ..." ብለዋል ።[1]

በዚህ ዐይነት ፣ "ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት" በተባለው መጽሐፍ ላይ እንደ ተመለከትነው ፣ ደጃች ሰባጋዲስ በራስ ወልደ ሥላሴ ላይ ፣ ደጃች ውቤ በራስ ዐሊ ወይም ዐሊ በውቤ ላይ ለመጫን ፣ የውጭን መንግሥታት ወዳጅነት ይሻሙ እንደ ነበሩ ሁሉ ፣ አሁንም ዐፄ ዮሐንስ ባዜ ቴዎድሮስና ባዜ ተክለ ጊዮርጊስ ጊዜ በየቆንሲሎቻቸው አማካይነት ከአውሮፓ መንግሥታት መሪዎች ጋር ወዳጅነት ለመፍጠር ጥረት አድርገዋል ። ምኒልክም ባዜ ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥትነት ጊዜ የአውሮፓን መንግሥታት ወዳጅነት ለማግኘት በደብዳቤ ተሻምተዋል ። የሽሚያው ጊዜ አሳቡም ፣ መንፈሱም ፣ ምኞቱም አባባሉ ሳይቀር የሁሉም ተመሳሳይ ነበር ። በመሳፍንት ዘመን የነበረው መከፋፈል ፈጽሞ ስለ አልተወገደና ዘመኑ የባለጉልት ዘመን በመሆኑ ፣ መሳፍንቱ በየጉልት እውራጃቸው ባላቸው ሀብትና ተከታይ ብዛት በመመካት ፣ እንዱ በጳጳስ ቢቀባም ፣ ባይቀባም ለነገሠው ንጉሥ አሜን ብለው በመገዛት ፋንታ ፣ በየፊናቸው ከውጭ መንግሥታት

* ከናፖሊዮን ሣልሳይ በፊት በሮሼ ዲሪኩር አማካይነት የፈረንሳይ መንግሥትና የሸዋው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በ1836 ዓ.ም. የተዋዋሉትን የወዳጅነት ውል በማውሳት ነው ።
** ባላምባራስ ጊዮርጊስ የሚባሉት ብዙ ዘመን ጐንደርም ፣ ሸዋም የተቀመጡት የግሪክ ተወላጅ ይሆኑ ?
1 ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ፣ የእጅ ጽሑፍ ክፍል ፣ ቁ.793 ።

መሪዎች ወይም ከቆንሲሎቻቸው ጋር በቀጥታ እየተጻጻፉ ፣ መሣሪያ በመሰብሰብ የጦር ሠራዊታቸውን በማደራጀት ወደ ንጉሠ ነገሥታዊ ሥልጣን የሚያደርሳቸውን መንገድ በየፊናቸው በትጋት ይፈልጋሉ ። ባፄ ቴዎድሮስ ዘመን የተወጠነውም የማዕከላዊ መንግሥት ግንባታ ግና ራሳቸው ገንቢው በሕይወት ሳሉ ተቀልሎ እንደ ነበረ የእንቧይ ካብ መልሶ ፈራርሷል ። ይሁን እንጂ ፣ ዮሐንስና ምኒልክ ባላንጣዎች ቢሆኑም ፣ የማዕከላዊውን መንግሥት ግንባታ እያደር በጽኑ የደንጊያ መሠረት ላይ አኑረውታል ።

የምኒልክ የግዛት ይዞታ ለጊዜው ከበሽሎ ወንዝ ወዲህ ባለው በወሎና በሸዋ ሲሆን ፣ ዮሐንስ በዚያን ጊዜ በተለይ ካፄ ተክለ ጊዮርጊስ ድል መመታት በኋላ ከበሽሎ ወዲያ ባለው በላስታ ፣ በስሜን ፣ በትግራይና በትግሬ ላይ ግዛታቸውን አስፋፍተዋል ። ሁለቱም ፣ በዚህ ጊዜ ፣ እላይ እንዳልነው የቤገምድርና የጐጃምን ፣ የየጁንና የእዘቦን ግዛት ይሻሙ ነበር ። የነዚህ ክፍለ ሀገር መሳፍንትና ባላባትም ፣ አንድ ጊዜ ካንዱ ጋር ከቆዩ በኋላ የሌላውን መበርታት ሲገነዘቡ ወደዚያ ይደረባሉ ። በዚህ ምክንያት ፣ የወሎዎቹ ባላባቶች አባ ዋጠውና* መሐመድ ዐሊ** የቤገምድሩ ራስ ወልደ ማርያም ፣ የስሜኑ ደጃች ወሬኛ ለምኒልክ ከገቡ በኋላ ወደ ዮሐንስ ዞረዋል ። ምክንያቱም ቀድሞ ከእንግሊዞች ካገኙት የጦር መሣሪያ በተጨማሪ ተክለ ጊዮርጊስን ያሸነፉ ለት የእርሳቸውን ጦር እንዳለ ጠቅልለው ስለ ወሰዱና ኃይላቸው እየበረታ ስለሔደ ነው ።

ቢሆንም ፣ ሁለቱም (ዮሐንስና ምኒልክ) በየቤታቸው የዘመድ ባላንጣ ነበራቸው ። በዮሐንስ ላይ የራስ አርአያ ልጅ ፣ ደጃች ደብብ ፣ ደጃች ወልደ ሚካኤልና ደጃች ካሳ ጐልጃ (አባ ከይሲ) ሲሆኑ ፣ በምኒልክ ላይ ደግሞ ፣ ከበዛብህ ሞት ወዲህ አጐታቸው መርድ አዝማች ኃይሌና ያጐታቸው ያቤቶ ሰይፉ ልጅ ደጃች መሸሻ ሰይፉ ነበሩ ። በነዚህ አንጻር ደግሞ በባላንጣነት የማይከራከሩ ፣ ጊዜ እይተው ካንዱ ወደ ሌላው በመዛወር የማይዋዥቁ ፣ ለሁለቱም ታማኝና ነዋሪ የጦር አለቆች ነበሯቸው ። ለምሳሌ ያህል ለዮሐንስ ፣ አርአያ ፣ ኪዳነማርያም ፣ እሉላ ፣ የማርያም ባርያ ገብረ ጻድቅ ሐጐስ... ሲሆኑ ፣ የምኒልክ ደግሞ በዚህ ወቅት ዳርጌ ፣ ጐበና ፣ ወልደ ጻድቅ ፣ ወልደ ገብርኤል ፣ ወልዴ ፣

---

* አባ ዋጠው የወይዘሮ መስተዋት ልጅ በኋላ ዐጼ ምኒልክ ክርስትና አንሥተው ደጃዝማች ኃይለ ማርያም ተብለዋል ።

** መሐመድ ዐሊንም ዐፄ ዮሐንስ የክርስትና አባት ሆነው ራስ ሚካኤል ብለዋቸዋል ።



ናደውና ሌሎችም ነበሩ ። ቢሆንም ፣ በሁለቱ ዘንድ የነበረው መሣሪያ ብዛትና ጥራት ሲመዘን ፣ ከምኒልክ ይልቅ የዮሐንስ የኃይል ሚዛን ይበልጥ ነበር ።

በሁለቱም ዘንድ ነዋሪ ሆነው በንግድ ሰበብ ለገዛ አገራቸው በስለላ እየሠሩ ወዳጅ መስለው ወጣ ገባ እያሉ የሚመክሩ ፣በመላላክ የሚያገለግሉ የውጭ አገር ሰዎችም ነበሩ ። በዮሐንስ ዘንድ ኪርክሃም (የእስኮትላንድ ተወላጁ) ፣ ናሬቲ (ጣሊያኑ) ፣ሺምበር (ጀርመናዊው)... የነበሩ ሲሆን ፣ በምኒልክ በኩል ደግሞ ሽፍነ ፣ አርኑ (ፈረንሳዮቹ) ፣ አንቲኖሪ ፣ ማሳያ (ጣልያኖቹ)... ነበሯቸው ። ሁለቱም ፣ ትንሽ ሠልጠን ያሉ የውጭ አገር ቋንቋ የሚያውቁ ያገር ተወላጆች ፣ በመላላክና በትርጕም ሥራ የሚያገለግሉ ነበሯቸው ። እነዚህም ለዮሐንስ አለቃ ብሩ ፣ ማኅደረ ቃል ፣ ምርጫ ወርቄ ፣ ብሩ ወልደ ኢቲ ሲሆኑ ፤ ለምኒልክ ደግሞ ዮሴፍ ንጉሤ ፣ ገብረ ተክሌ ፣ አባ ሚካኤል ፣ መክበብ ፤ አጥሜ .. ነበሩ ።

ከምኒልክ የበለጠ ዮሐንስ ለኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀናዒ በመሆን ፣ በግዛታቸው የነበሩትን የካቶሊኮቹን ስብከት ሲቃወሙ ፣ በተለይ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ የተሸነፉ ዕለት ፣ ሰነድ ሲመረመር የካቶሊኮቹ መሪ ሞንሲኘር ዤን ቱቪዬ "ከካሳ ጋር በሚያደርጉት ጦርነት የጦር መሣሪያ በማቀበል እንረዳዎታለን" የሚል ለዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ የተጻፈ ደብዳቤ ስለተገኘ ፣ ቀድሞውኑም የማይወዱዋቸውን ካቶሊኮች ከዚህ ጊዜ ዠምሮ ንብረታቸውን በመውረስ ፣ እነሱንም በማሳደድ አጉላሏቸው ። በርሳቸው አንጻር ምኒልክ ፣ በካቶሊኮቹ በነ አባ ማስያስ በኩል ከኢጣሊያና ከፈረንሳይ መንግሥታት ባላንጣዬን የምቋቋምበት የጦር መሣሪያ አገኛለሁ በሚል ተስፋ ካቶሊኮችን ተንከባከቧቸው ። ካቶሊኮቹም በሰላም ባገር ውስጥ ተቀምጠው እንደ ልብ ለመሰበክ በመቻላቸው ምኒልክን ሲወዱ ፣ ሲያወድሱ ፣ የራሳቸው የአንኮበር ታላላቅ አብያተ ክርስቲያናት አለቆች እነ አለቃ ምላት ፣ እነ አለቃ ኪዳነ ወልድ. . . ባለቤታቸውን ወይዘሮ ባፈናን ተገን አድርገው በዮሐንስ ላይ አለኝታቸውን ፣ በምኒልክ ላይ ቅሬታቸውን ይገልጡ ነበር ። በእነዚህ ቅርታ የተነሣ ፣ ዐፄ ዮሐንስን ባነገሡት በአቡነ አትናቴዎስ ስብከት የምኒልክ በተዋሕዶ ሃይማኖት በኩል ያላቸው ዝና ባገር ውስጥ እንደ መበላሸት ብሎ ነበር ። በሌላው አንጻር በፈረንሳዩና በኢጣልያ አገር ግን ፣ ዮሐንስ እምቢ ባይ የካቶሊክና የእስላም ጠላት አሳበ ግትር (ፋናቲክ) እየተባሉ ሲነቀፉ ፣ ምኒልክ ደግሞ ታጋሽ፣ የሃይማኖት ነጻነት ሰጭ ፣ አገሩን ለማሠልጠን መልካም ፈቃድ ያለው ተብለው ተወድሰዋል ።

በዚህ ዐይነት ፣ ለሁለቱም በውጭና በውስጥ የተሟላ ምቹ ሁኔታ ሳይፈጠር ፣ ወደፊት እንደምናነበው ፣ በመካከሉ ግብጾች ባፄ ዮሐንስ ላይ ተነሡ ። ይኸም ሁኔታ በሸዎች ዘንድ ባላንጣቸውን ለመቃወም ተስፋ ሲጣልበትና በነአለቃ ብሩ ፣ በነአብዱራህማን ፣ በነሙንሲንጀር አማካይነት በግልጽም ፣ በምስጢርም ከግብጽ ባለሥልጣኖች ጋር መላላክና ገጸ በረከትም መለዋወጥ ከተዠመረ በኋላ ፣ የግብጽ መሪ ኢስማኤል ዓላማው ኢትዮጵያን በሙሉ ለመውረር መሆኑ ሲታወቅ ፣ ምኒልክ ወደኋላ አፈግፍገው ኢስማኤልን በደብዳቤ ከወቀሱ በኋላ ፣ የመንፈስ አንድነታቸውን ከዮሐንስ ጋር ለማስተባበር ሞከሩ ። በመሠረቱ መሳፍንቶቻችንን ይኸን ያህል የውጭን መሪዎች በደብዳቤ ፣ በገጸ በረከት የሚያለማምጣቸው ከሥልጣኔ ጉድለት የተነሣ የሚያስፈልጋቸውን ማናቸውንም መሣሪያ ራሳቸው ለመሥራት አለመቻላቸው ነበር ።

ስለዚህ ፣ እያንዳንዱ መስፍን የጉልቱን አገር ገበሬና ነጋዴ እያደኸየ፣ በየራሱ ጦር ሠራዊት እየተረዳ የባላንጣውን ኃይል አድክሞ የራሱን አቅዋም ለማጠንከር በግድ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ማግኘት ይፈልግ ነበር ። ሁሉም በየበኩሉ የውጭ መንግሥታትን ድጋፍ በመጸጸፍ ሲጠይቅ ፣ የውጭዎቹ መንግሥታት ደግሞ ፣ ራሳቸው ቅኝ አገር ያላቸው ፣ ወደፊትም ይኸንኑ የቅኝ ግዛት እያበራከቱ መሔድ የሚያምራቸው ነበር ። በዚህ በውስጣዊ የኢትዮጵያ መከፋፈል እየተጠቀሙም ለወዳጅነት ደጅ ለሚጠናቸው መስፍን ባንድ ወገን የወዳጅነት መልክ ማሳየታቸው ሳይቀር ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ፣ እንኳን ራሳቸው የጦር መሣሪያ ሲሰጡ ይቅርና ሌላ ገለልተኛ አገር እንኳን ቢሰጥ ይከሱታል፤ ይወቅሱታል ። ምናልባት ላንዱ መስፍን መጠነኛ መሣሪያ ቆጥበው ለመስጠት የሚገደዱት ፣ ይቃወመናል ብለው የሚፈሩትን ሌላውን መስፍን ለመውጋት መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ነበር ።

ስለዚህ ፣ መስፍኑ የውጭውን መሪ ድጋፍ እንደ መሣሪያ አድርጎ ለመጠቀም በሚፈልግበት ጊዜ ፣ ይልቅስ የተገላቢጦሽ ለውጭው መንግሥት የመግቢያ መሣሪያ የሚሆነው መስፍኑ ራሱ ነው ። ከመጸጻፉና ገጸ በረከት ከመለዋወጡ ውዝግብ በኋላ ፣ የሚገኘው ውጤት ለመስፍኑ ወዳጅና ተከላካይ ይመስል የነበረው የውጭ መንግሥት በመጨረሻ የዚሁ የዋህ መስፍን ጠላትና አጥቂ ሆኖ ይገኛል ። ይኸም እንግሊዞች ዐፄ ቴዎድሮስን ለማጥቃት ወይም ግብጾችን ከደርቡሾች እጅ ለማዳን ዐፄ ዮሐንስን በመሣሪያነት በደንብ ሲጠቀሙባቸው ቆይተው ፣ በመጨረሻ ንጉሡ በሐቅ መንገድ የተሰጣቸውን የውል ተስፋ መሠረት በማድረግ ግብጾች በሚለቁት በሐባብና በቦጎስ ፣ በምጥዋም ወደብ እገባለሁ እያሉ በተስፋ ሲጠባበቁ ፣ ወዳጆቼ የሚሏቸው እንግሊዞች በጒን ጣልያንን ጠቅሰው በማስያዝ ጠላት ፈጠሩባቸው ። በእንግሊዝ



አሳሳቢነትና አዋዋይነት ግብጾችንም በረዱበት ሰበብ ዮሐንስ በደርቡሾች አደጋ ፊት ፣ በመተማ ሲጋፈጡ የእንግሊዝ መንግሥት ምንም እርዳታ አላደረገላቸውም ።

እንደዚሁም ፣ ምኒልክ ከዮሐንስ ጀርባ ከኢጣልያኖች ጋር ሲወዳጁ ፣ ሲዋዋሉ ፣ ጣልያኖቹም ‘በርታ እንደግፍሃለን ፣ መሣሪያም እንሰጥሃለን’ እያሉ ሲያበረታቱ ቆይተው በኋላ ፣ ዮሐንስ ሞተው ምኒልክ ሲነግሡ ፣ “መላዋን ኢትዮጵያን መያዝ አለብን” ብለው የተነሡት ፣ በፊተኛው ጊዜ በወዳጅነት የተመኩባቸው በውነትም ከባላንጣቸው ካፄ ዮሐንስ ጋር የሚዋጉበት መሣሪያ ያቀበሉዋቸው ኢጣሊያኖች ናቸው ። በዚህ ዐይነት መሳፍንቱ ሁሉ በኋላ የሚከተለውን አስቀድሞ ባለማሰብ ፣ በመዠመሪያው ወቅት ደብዳቤና ገጸ በረከት በመላክ ፣ “እናንተም ወዳጅ ሁኑን ፣ ከየወዳጃችሁም አፋቅሩን” እያሉ ደጅ የሚጠኑአቸው ደንበኛ የኋላ ጠላቶቻቸውን መሆኑ በግልጽ ይታያል ።

አብዛኛውን ጊዜ ፣ መሳፍንቱ ወደ ሥልጣን ደረጃ ከመውጣታቸው በፊት ባላጋራቸውን ለማጥቃት ፣ ከነርሱ በፊት እሥልጣን ላይ የወጣውን ባላንጣቸውን ለመጣልና በርሱ ለመተካት ሲሉ አገሪቱ የምትጐዳበትን መንገድ ዐውቀውም ሆነ ሳያውቁ ይከተላሉ ። ቆይተውም ደንበኛ ያገር ፍቅር ስሜት አድሮባቸው አገራቸውን ከጠላት ለመከላከል ታጥቀው ሲነሡ የሚታዩት ፣ ባላንጣቸው ወድቆ ወደ ንጉሠ ነገሥታዊ ሥልጣን ከወጡና ለበላይ ገዥነት ያላቸው ምኞት ከተሟላ በኋላ ነው ።

የራስን ሥልጣን ከማፍቀር ጐን ባላንጣን የመጥላቱ ጉዳይ ቂሙ እየጠለቀ ፣ እልሁ እያየለ በሔደ መጠን አንዳንድ ጊዜ ‘እልህ መርፌ ያስውጣል’ እንደሚባለው ፣ አንዳንዱ የየትም ክፍለ አገር መስፍንና ቀንደኛ ያገሩ ልጅ ወይም የወንድም ባላንጣው ከሚገዛው ተዋግቶ መሞትን ሲመርጥ ይታያል ። ምኒልክና ዮሐንስ በመዠመሪያው ያገዛዛቸው ወቅት በየበኩላቸው የመፎካከር ፣ የመከፋፈል ፣ ለጠላት መሣሪያ የመሆን በደል ካሳዩ በኋላ ፣ በመጨረሻ ከሁለቱም በመነጨው ትዕግሥትና አስተዋይነት ሁለቱም አቅማቸውን እየገመቱ ፣ ዮሐንስ አየል ሲሉ ፣ ምኒልክ እየገበሩ በመገዛት ፣ ደግሞ የምኒልክ ኃይል እያደር መደርጀቱን ዮሐንስ ሲረዱ ከመዋጋት ሸብረክ ብለው በመተው ፣ ሁለቱ እከፋ ሁኔታ ላይ ተዳርሰው ሠራዊታቸውን እርስ በርሱ ሳያጫርሱ ፣ በየተራ ቴዎድሮስ የወጠኑትን ማዕከላዊ መንግሥት በየዘመነ መንግሥታቸው ገንብተዋል ። በዚህ መካከል የደረሰው የታሪክ ውዝግብ ወደፊት በየምዕራፉ የሚነበበው ነው ።

መልእክት፡ የተላከ፡ ከንጉሠ፡ ምኒልክ፡ ሀገረ፡ ሸዋ፡
ይድረስ፡ ወደ፡ ንግሥት፡ ቢክቶርያ። እንዴት፡ ነ
ሽ፡ እጅጉ ግ። ደኅና፡ ነሽ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር፡ ይመ
ሥገን፡ ደኅና፡ ነኝ፡ ሰዊም፡ አገሬም፡ ደኅና፡ ነው።
ቀድሞ፡ የሰደድሽልኝ፡ ደብዳቤ፡ ደረሰልኝ፡ እጅ
ጋ፡ ደስ፡ አለኝ። መልክተኛዎም፡ አቶ፡ ወክብም፡
ደኅና፡ ገባልኝ፡ ያንቺን፡ ወዳጅነትና፡ ፍቅር፡ እ
ጅጋ፡ ወደድሁ። እኔም፡ ያንቺን፡ ፍቅርና፡ ዝም
ድና፡ ተፈልጋሁ፡ ነበር፡ ቀኑ፡ ነው። መልክተኛዬ
ሳይመለስ፡ ወደ፡ አገቺ፡ የላከችኝ፡ እኔ፡ እራሴ፡ ወ
ዴ፡ መቅደላ፡ ዘምቼ። የቋሰሩትን፡ ሰዎችሽን፡ ለ
ማስፈታት፡ ነገሩ፡ ባይመቸኝ፡ ተመልሼ፡ አገ
ሬ፡ ገባሁ። ዲጋሞ፡ ሁለተኛ፡ ሰዊ፡ አዘምቼ፡ የ
ናንተ፡ ወታደሮች፡ ቀው፡ ያገሬ፡ ሰው፡ ተሲከኝ፡
ከዘመቻ፡ መዋል፡ አለመደምና፡ ተመልሶ፡ ገባ፡
ሰዊ፡ በገባ፡ በ፲ ቀን፡ እንግሊዞች፡ ድል፡ ዓደረ
ጉ፡ ቴዎድሮስ፡ ሞቱ፡ የሚል፡ የምሥራች፡ መ
ጣልኝ። ደህና፡ ብንማ፡ እጅጋ፡ ደስ፡ አለኝ። እኔ
ም፡ በፍቅር፡ ለመገናኘት፡ ተሰዎችሽ፡ ጋራ፡ ሰነ
ሳ፡ ቸኩለው፡ ተመለሱ፡ ቢሉኝ፡ ቀረሁ። አስሮ
ቹም፡ እና[illegible]፡ ደርጊም፡ ደኅና፡ ደረሱልኝ። እግ
ዚአብሔር፡ ይስጥልኝ። እኔ፡ ስለፍቅር፡ ያደረ
ጋሁትን፡ ሁሉ፡ ነገር፡ ሬሰም፡ ያውቃል። መስቃ
ር፡ ውትም፡ የመቅደላን፡ ነፍሮ፡ ሁሉ፡ አስበጅታ፡
ክርስቲያኝ፡ ሁሉ፡ ተወጋለቹ። ፩ ጠር፡ ከፊ፡ ፩ ቢ
ቃዋ፡ ሰዱዲ፡ አለሁ፡ ለንግሥት፡ ይጠቅማል፡ ብዬ
አይዋለም፡ ለመልክተኛው፡ ምልክት፡ ነው።
ሽፍታ፡ አምባ፡ እየያዘ፡ አስቸግሮኝ፡ አሉና፡ ለ
ዚዬ፡ መስበሪያ፡ ይፈለግልኛል።



ዐፄ ምኒልክ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት

(ፐብሊክ ሪኮርድ ኦፊስ ለንደን)

# ምዕራፍ አምስት

## ንጉሥ ምኒልክ በሸዋና በወሎ የሥልጣናቸው መጠናከር— አሳዛኙ የአቶ በዛብህ አሟሟት

ከ1864—1870 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ፤ ዮሐንስ ከበሽሎ ወንዝ ወዲያ ባለው በቤገምድር ፤ በትግራይና በትግሬ ፤ ምኒልክ ከበሽሎ ወንዝ ወዲህ በሚገኘው በወሎና በሸዋ ሥልጣናቸውን እያጠነከሩ ሁለቱም ያልታመኑላቸውን ሲያባብሉ ፤ የታመኑላቸውን ሲሾሙ ፤ ሲሸልሙ ፤ ያፈነገጠባቸውን ለመደምሰስ ሲጣጣሩ ኖረዋል ። ዮሐንስ "ንጉሠ ነገሥት ፤ ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ዘኢትዮጵያ" ፤ ምኒልክ "ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ፤ ምንይልክ ንጉሠ ነገሥት" የሚሉ ማኅተሞች በየበኩላቸው አሠርተው ፤ ካገር ውስጥም ከውጭ አገር ሰዎች ጋር በየማኅተማቸው ይጻጻፉ ነበር ።

ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት የተባሉት ፤ በራሳቸውና በተከታዮቻቸው ፈቃድ እንጂ ፤ በኢትዮጵያ መንግሥታዊ ባህልና ደንብ መሠረት እንደ ዮሐንስ በጳጳስ በወቅቱ አልተቀቡም ። በዚህ ምክንያት ከምኒልክ ንጉሠ ነገሥትነት የዮሐንስ ንጉሠ ነገሥትነት የበለጠ ሕጋዊ መንገድ የያዘ ነው ። በአንኮበርም ከመንገሥ በጥንታዊቷ ከተማ በአክሱም መንገሥ የበለጠ ያኮራል ። ነገር ግን ፤ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስም የነገሡት በጳጳስ ሳይቀቡ ነበር ። ባለፈው ዘመንም ፤ ጳጳስ ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ባቋረጠ ቁጥር ብዙ መሳፍንት ያለ ጳጳስ ቅባት እየነገሡ በነገሥታት ዝርዝር ተራ ገብተው የሚጠሩ ብዙ ናቸው ። ስለዚህ ከጳጳሱ ቅባት ጐን አብዛኛውን ጊዜ ፤ ሁሉንም መስፍን ለንጉሠ ነገሥትነት የሚያበቃው የጉልበት ኃይል ነው ። በቅባት ያልተገኘው ዘውድ ብዙ ጊዜ በኃይል በኩል እየተገኘ ይጸድቃል ። ስለዚህ ያለ ኃይል ድጋፍ የጳጳሱ ቅባት ብቻውን ለንጉሠ ነገሥትነት አያበቃም ።

ምኒልክ ከቴዎድሮስ ሞት ወዲህ ፤ ባፄ ተክለ ጊዮርጊስና እንዲሁም ባፄ ዮሐንስ የመዠመሪያዎቹ ዓመታት የጦር መሣሪያ ለማግኘትና ፤ ዘመድ ለመግዛት በነአባ ማስያስና በነ አባ ሚካኤል አማካይነት ከኢጣልያ ንጉሥ ከሁለተኛው ቪክቶርዮ አማኑኤል ጋር ፤ በዘይላው ባላባት በአቡበከር ልጅና በነአለቃ ብሩ አማካይነት ከግብጹ ኀዲቭ ከከዲቭ

ኢስማኤል ጋር ፣ በሙሴ እርኑ በኩል ከፈረንሳይ መንግሥት ፕሬዚ
ዳንት ጋር ደብዳቤ በመጻጻፍ ፣ ገጸ በረከት በመለዋወጥ ላይ ነበሩ ።
ከከዲቭ ኢስማኤል ጋር የተጻጻፉት የሚያነግሥ ጳጳስ ለማግኘት ጭምር
ነበር ። ዳሩ ግን ፣ በቅድሚያ አትናቴዎስ ተልከው መጥተው እያሉ በድ
ጋሚ ሌላ ጳጳስ ለመላክ ለእስክንድርያ ፓትርያርክ አመቺ አልሆነም።

በዚሁ ጐን ፣ ከወሎ ጋር ጐጃምንም ለመጨመር በደብረ መዊዕና
በሞጣ ፣ በደብረ ወርቅ በኩል ምኒልክ ራስ አዳልን ለማሳመን ተጉዘው
ሳለ ፣ በመካከሉ የዙፋን ባላንጣቸውና አጐታቸው መርድ አዝማች
ኃይሌ አንኮበርን መውረራቸውና ወኪሎቻቸውንም እነ አዛዥ ወልደ
ጻድቅን ማባረራቸው ስለ ተሰማ ፣ ጐጃምን ለቀው ወደ ሸዋ ለመመለስ
መንገድ እንደ ዠመሩ መርድ አዝማች ኃይሌ በምኒልክ ታማኞች በነ
ገርማሜ ፣ በነ ወልደ ጻድቅና በነ እፌ ንጉሥ በዳኔ ተማርከው መታ
ሰራቸው ተገለጸ ። ሌላው የዙፋን ባላንጣቸው መሸሻ ሰይፉ እንደዚሁ
ሸፍተው አስቸግረው ስለነበረ ፣ እርሳቸውንም በምኒልክ ትእዛዝ ደጃች
ዳርጌና ደጃች ወልደ ሚካኤል ለማሳመን ሔደው ሳለ ፣ መሸሻም ካፄ
ዮሐንስ እርዳታ ቢያገኙም የወሎው ባላባት መሐመድ ዐሊ ለምኒልክ
ለጊዜው ስለ ታመኑ ፣ መመከት የማይመቻቸው ሆኖ እጃቸውን ለዳርጌ
ሰጥተው በታሞ ታሰሩ ።[1] መሐመድ ዐሊም ለንጉሥ ምኒልክ ታማኝ
ነታቸውን በመግለጻቸው ፣ ምኒልክ በወሎ ግዛታቸውን አጽንተው ራሳ
ቸው በዚያን ጊዜ የደረሰች ሴት ልጅ ስለ አልነበረቻቸው ፣ የባለቤ
ታቸውን የወይዘሮ ባፈናን ልጅ ወይዘሮ ማናለብሽን ዳሩላቸው ።[2]

ለምኒልክ አገዛዝ የበለጠ እሥጊና እንቅፋት የነበሩት ስመ ጥሩው
አቶ በዛብህ (በዙ አባ ድክር) ነበሩ ። በዛብህ ማን መሆናቸው ፣
"ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት" በሚለው መጽሐፍ ላይ ተገ
ልጿል ። በዚህ ምዕራፍ ባጭሩ ለማስታወስ ያህል ፣ ቴዎድሮስ በመዠ
መሪያ ሸዋን ለማስገበር የመጡ ጊዜ በዠግንነት ሲዋጉ መቁሰላቸው፣
በኋላም ምኒልክን ይዘው የገቡ ጊዜ ፣ "በዘውዴ እንጂ በዠግንነት
አልበልጥህም" የሚል ቃል ከቴዎድሮስ አንደበት እንደ ተነገረላቸው
በሥፍራው ተወስቷል ።

በዛብህ ፣ ለቴዎድሮስም የተገዙት ባለመመቸት እንጂ ፣ ከልብ አል
ነበረም ። ባልተመቸበት ጊዜ ገብረውና ተሾመው ፣ በተመቸበት ጊዜ

1 ዐጥሜ (እጽሙ ጊዮርጊስ) የጋላ ታሪክ (የእጅ ጽሑፍ) ገጽ 134 ።
2 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 72-79



እንደ ሸፈቱ ሁሉ ፣ አሁንም ከምኒልክ ጋር በጋዲሎ ምንም በርትተው
ቢዋጉ ፣ ሕዝቡ ወደ ናፈቀው መስፍን ወደ ምኒልክ ስለ ዞረባቸው ወደ
አፍቀራ ሸሹ ። ቀጥሎም ተስፋ ስለቆረጡ ከልብ ሳይሆን በግዴታ ወደ
ምኒልክ በዕርቅ ገቡ ። በግዴታም የገባ ሁሉ ለመሸፈት ምቹ ጊዜን
ይጠባበቃል እንጂ ፣ እሱ የቀመሰውን ሹመት ለያዘው ሰው ታማኝ
ሆኖ እስከ መጨረሻ ሊዘልቅ አይችልም ።

ከቴዎድሮስ ከሸፈቱበት ጊዜ ዠምሮ (1853 ዓ.ም.) ምኒልክ
ከመቅደላ አምልጠው በጋዲሎ እስከ ተዋጉበት ጊዜ ድረስ (1857)
አራቱን ዓመት በዛብህ "የሸዋ ንጉሥ" የሚል ማኅተም አሠርተው
ማስተዳደር ጀምረው ነበረ ። አሁን በግዴታ ለምኒልክ ገባሁ ቢሉም
አላይ እንዳልነው ፣ ማንም ሰው ራሱን አንግሦ ማስተዳደር ከዠመረ
በኋላ በዚያው እንደ ንጉሥ በገዛበት አገር ፣ ይገዛቸው በነበሩት ሕዝ
ቦች መካከል ፣ ሌላውን ሰው እንደ ንጉሥ ተቀብሎና ራሱን ዝቅ አድ
ርጎ መገዛትን አይወድም ። ቀድሞ ለሚያዛቸው የበላያቸው መሆኑ
ቀርቶ እኩያቸው ሲሆን ለነዚያ ክብር ፣ ለርሱ ደግሞ ውርደቱ ነው ።
ደጅ በተጠናበት ፣ እጅ በተነሣበት ከተማ ፣ እርሱ ደጅ እየጠና እጅ
መንሣቱ የበለጠ አሳፋሪው ነው ።

በነጋሚው በምኒልክና በቀንደኛው ጐበዝ በበዙ አባ ድክር
መካከል ኅብረት የነሣው ችግር ይኸ ነው ። መፍትሔውም ከእስራ
ትም ዐልፎ ሞት ሆኖ ተገኘ ።

ሰዉም ምኒልክን በመስፍንነታቸውና በደግነታቸው ቢቀበልም ፣
ባንድ ወገን ደግሞ የበዛብህን ዠግንነት እንደዚህ እያለ በግጥምና
በሽለላ እያነሣሣ በማሟሟቅ ፣ ሁለቱ በጠላትነት እንዲቀጥሉ ሁኔታውን
የበለጠ አከበደው ።

መቼ ኮረብታው መች አፍቀራ ነው
መቼ ፈረሱ መች ቦራ ነው
መቼ መሣሪያው መች ጠበንጃው ነው
በዙ አባ ድክር እሱን ያኮራው
ሐሞቱ እንጂ ነው ፣ ባንድ የተሠራው ።

የበዛብህን ሐሞተ መራራነት ምኒልክም አይስቱት ። ነገር ግን ፣
እንደዚህ ያለው ዠግና ላንድ ቀን ይሆነኛል በሚል ስሜት በሹመትና
በፍቅር አሸንፈው ለመሳብ የተመኙ ይመስላል ። ነገር ግን የበዛብህን
የኅሾነት ምኞት ከነዠግንነቱ የሚያውቁት ፣ ከመቅደላ ምሽግ ከምኒ
ልክ ጋር አብረው በስደት ኖረው የመጡት መኳንንት እነ ደጃች

ገርማሜ ፣ እነ ደጃች ወልደ ገብርኤል ፣ እነ አዛዥ ወልደ ጻድቅ "በዛብህ በሕይወት እያለ ምንም ቢሆን እርስዎንም አያስገዛዎት ፣ እኛም ጤና አናገኝ ። ተይዞ ቢታሰር ይሻላል" ብለው ስለ ገፋፉአቸው ፣ እርሳቸውም ከነዚህ እንዳባት ከሚቆጥሯቸውና በስደት አብረዋቸው ከኖሩት ፣ ሕይወታቸውን ሠውተው ከመቅደላ ካወጡዋቸው መኳንንት ፈቃድ መውጣት አይሆንላቸውምና "እሺ" አሉ ። በዚያው ሰሞን በዛብህ ወደ ግቢ ተጠርተው ሳለ ፣ "ተያዝ ብለውሃል" ተብለው በድንገት በተያዙበት ጊዜ ፣ ዝናራቸውና ሽጉጣቸው ሲፈታ ሽጉጣቸው ጥይት ጉርሶ ተገኘ ።[1]

በዚህ ጊዜ ፣ "ሽጉጡን ጥይት አጉርሶ መግባቱ ምን ቢያስብ ነው" ተብሎ በዛብህ እንደ ተያዙ ከፍርድ አደባባይ ቀርበው ፣ አጋፋሪዎቹ ሌላም ወንጀል አጠረቃቅመው በፊት ጋዲሎ ላይ መዋጋታቸው ፣ በኋላም የአፍቀራን ምሽግ ሳያስረክቡ መቅረታቸው እየተጠቀሰ ፣ "አሁን ደግሞ ሽጉጥህን አጉርሰህ ወደ ግቢ ከመጣህ ወንጀለኛ ነህና ያስሞትሃል!" የሚል ፍርድ ሲጠይቁ ፣ በዛብህም "የጐረሰ ሽጉጥ ብታጠቅ ተኩሰሃል ፣ ገድለሃል ካልተባልሁ አያስሞተኝም" ብለው ከመለሱ በኋላ ፣ "ይፈረድ" ተብሎ ሲፈረድ ፣ ብዙዎቹ በጉባዔ የተቀመጡት "ያስሞትሃል" ብለው ፈረዱ ። የወይዘሮ ባፌና ባል የነበሩት አፈ ንጉሥ በዳኔም ፣ "ሽጉጥ በመታጠቅህ ብቻ አያስሞትህም ነበር ። ዳሩ ግን አንተ ለውም እያሳበርክ አሥግተሽናል ። አንተ እያለህ ጌታችንንም አታስገዛቸውም ። አሁንም ሽጉጥ ታጥቀህ መግባትህ ለነገር ነው (ጌታችንን ለመግደል ነው) ያስሞትሃል" ብለው ፈረዱ ። ይባላል ። ምኒልክም ይኸንኑ ፍርድ ስላጸደቁት ፣ ዠግናው በዛብህ ዕለቱን በጠበንጃ ተደብድበው ተገደሉ ። ጠበንጃውም ጨርቅና ባሩድ የተጨቀጨቀበት የቀድሞ አሮጌ ጠበንጃ ነበርና ቀርበው ሲተኩሱባቸው በባሩዱ እሳት የተያያዘው ጨርቅ እልባሳቸው ላይ ዐርፎ ገላቸው ነዶ ተቃጠለ ።

ስለ አቶ በዛብህ (በዙ አባ ድክር) ጭካኔ ሊቁ አቶ ዐጥሜ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን አስፍረዋል ። "...አቶ በዛብህ ብርቱ ፣ ጐበዝ ፈረሰኛ፣ ጨካኝ ፣ ግፈኛ ፣ ጀግና ፣ አንድ ጦር አንድ ክንድ (የሚበልጥ?) ነበራቸው ይላሉ ። በዚያ በጦር ያለቀው አሮሞና አምሐራ ቁጥር ሥፍር የለውም ፤ ከዚህም የተነሣ ነበር ፣

---

1 አቶ ዐጥሜ የጋላ ታሪክ በሚባለው መጽሐፋቸው ለግብር ተጠርተው ሲገቡ የጦር መሣሪያ በውጭ ስለሚቀመጥ ፣ በዚህ ዐይነት በዛብህ መሣሪያቸውን በውጭ ፈትተው ወደ ውስጥ ሲገቡ እንደ ተያዙ ይገልጻሉ ። ገጽ 121 ።



"አንተም ጨካኝ ነበርክ ጨካኝ አዘዘብህ
እንደገና ዳቦ እሳት ነደደብህ"

የተባለው ።

በዚህም በአቶ በዛብህ መገደል ምክንያት ፣ የበዛብህ የዠግንነት ጓደኞች እነ አቶ ኃይሌ እንዳርጋቸው ከምኒልክም ፣ ከነ ደጃዝማች ገርማሜም ተኳርፈው ኖሩ ይባላል ።

አቶ በዛብህም እንደ ሞቱ ፣ ያቶ በዛብህን የአሮሞ አበጋዝነት ላቶ ወሌ ቀጥሎ ላቶ ናደው ተሰጠ ። የጦር መሣሪያና ፈረሳቸውን ግን ለደጃች ገርማሜ ሰጡአቸው ። ደጃች ገርማሜ አንካሳ ከመሆናቸው ጋር የበዛብህን አገር ለመግዛት አለመመጠናቸውን ለማሳሰብ አንዲት የሸዋ ሴት እንደዚህ ብላ ገጠመች ይባላል ።

"የበዙ ፈረሶች ቦራና ጠለፉ እንዴት ይተርማቸው !
ገርማሜ ባንድ እግሩ ሲኰረኩራቸው
እሳቸው (ምኒልክ) ቢሰጡት እሱ (ገርማሜ) መቀበሉ
ክነልቡ ነወይ ክነአደፋፈሩ ።"[1]

---

1 የብላቴን ጌታ ኅሩይ የእጅ ጽሑፍ ገጽ 85 ፣ የራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ገጽ ያልተደረገበት የእጅ ጽሑፍ ፣ ከተ.ጸ.መ. ካ፯ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ምዕ.28 ገጽ 75-76 ።

# ምዕራፍ ስድስት

## በመጀመሪያዎቹ የንግሥ ዓመታት ባፄ ዮሐንስ ፊት የተደቀኑ የማሳመን ችግሮች—የካቶሊኮች አቅዋም

በየትም አገር ፣ ማንም አዲስ መሪ ለመጀመሪያ ጊዜ ሥልጣን ሲይዝ ብዙ የተደቀኑ ተግባሮች እንደሚገጥሙት የታወቀ ነው ። ያፄ ዮሐንስ ተግባር ከመጀመሪያው የአዲስ ማዕከላዊ መንግሥት ወጣኝ ከሆኑት ካፄ ቴዎድሮስ ተግባር ያነሰ ቢመስልም ፣ ባገሪቱ ሁኔታ አን ጻር ሲታይ የርሳቸው ብዙ ነበር ። ተግባራቸው እንደ መበርከቱ መጠን ወደ ሸዋ ዘምተው ዋና የዙፋን ባላንጣቸውን ምኒልክን ለመደምሰስ አላስቻላቸውም ። ወደ ሸዋ መዝመት ቀርቶ በዚያው ባሉበት አካባቢ የነበረው መስፍንና ቀንደኛ ባላባት ፣ ገና በኃይልም ይሁን በሰላም ጸጥ ብሎ አልተገዛላቸውም ። ለርሳቸው ታማኝ በሆኑት ባሎቻቸው በራስ አርአያ ፣ በዋና የጦር አለቃቸው በራስ ባሪያው ገብረ ጻድቅ ጐን ሌሎች ብዙ የሸፈቱ ባላጋራዎች እና እመካከል ላይ ሆነው በማወላወል ገና ታማኝነታቸውን ያልገለጡ መኳንንት ነበሩባቸው ።

እንደ ሌላው አገር ሁሉ ፣ በኢትዮጵያም ጉልተኝነት በጸናበት በዚያ ዘመን ፣ የበቃ ኃይል ካላስገደደው በቀር አንዱ መስፍን በጳጳስ ተቀብቶ ቢነግሥም ፣ ሌላው አሜን ብሎ መገዛቱን አይወድም ነበር ። ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት በጠፋበት ዘመን እያንዳንዱ መስፍን የዘውድ ሥልጣን በየቤቱ ይመኛል ። እያንዳንዱ የነገድ ባላባት በዘር ትውልድና በትምክህት ዘሩን ከላይ ከነገሥታቱ እየቆጣጠረ ሌላው ባላንጣው በነገሠ ጊዜ ኃይል ተጭኖት ጊዜ ሳይመቸው ቀርቶ ያለ ልክ ቢገብርም ፣ በተመቸው ጊዜ መልሶ የሚሸፍተው ብዙ ነው ።

ከመረብ ወዲያ በምድረ ባሕሪ (አሁን ኤርትራ)* ተብሎ በሚጠራው ክ/ሀገር ውስጥ በሐማሴን አውራጃ የሚገኙት የተስፋ ጽዮን

---

* ለክፍለ ሀገሩ ኤርትራ የሚል ሥያሜ የተሰጠው በ1882 ዓ.ም ማለትም ፣ ከዐፄ ዮሐንስ ዕረፍት በኋላ ነው ።

ወገኖች ካንድ ዘር የወረዱ ሆነው ሳለ ፣ ቡ.ን ብዛት ፣ አንደኛው ክፍል ደቀ ዘርዓይ (የዘርዓይ ልጅ) ፣ ሌላው ክፍል ደቀ ሚናብ (የሚናብ ልጅ) በመባል ከሁለት ተከፍለዋል ። ሚናብና ዘርዓይ የተስፋ ጽዮን ልጆች ናቸው ። አንደኛው ወገን ጸአዘጋን ፣ ሁለተኛው ወገን አጸጋን መሥር ተው እነዚህ ያንድ ሰው (የተስፋ ጽዮን) ተወላጆች ባጼ ዮሐንስ ጊዜ ወገን ለይተው የጸአዘጋው ባላባት ደጃን ኃይሉና የአጸጋው ባላ ባት ደጃች ወልደ ሚካኤል የርስ በርስ ጠብ እንደ ነበራቸው ዕውቅ ነው ። እንደዚሁም የደምበሳን ፣ የካርኔ ሹም ወገኖች ፣ በሠራዬ የባላምባራስ ተስፋ ማርያም ቤተሰብ ሲሆኑ ፣ አንዱ ላንዱ መገዛትን ይጠሉት ነበር ።

በዚህ መካከል ፣ ያጼ ዮሐንስ ባላባትነት ከመረብ ወዲህ ባለው በእንደርታ በራስ ወልደ ሥላሴ ቤት ነው ። በዐድዋም ከነራስ ስሑል ሚካኤል መወለዳቸውም የሚያኮራቸው ቢሆን እነዚያ ከመረብ ወዲያ ያሉት የጸአዘጋው እነኃይሉ ፣ የአጸጋው እነ ወልደ ሚካኤል በዘር ከወልደ ሥላሴ ቤት የሚያንሱ መሆናቸውን አይቀበሉም ። እንኳን ከመረብ ወዲያ ያሉት ቀርቶ ከመረብ ወዲህ ያሉትም አጋሜዎች ፣ የሰባጋዲስ ወገኖች ፣ ለእንደርታው ለወልደ ሥላሴ ወገን መገዛቱን ይጠሉታል ። በዚህ ምክንያት ፣ ዮሐንስ ራቅ ያሉትን የቤገምድርን ፣ የጐጃምን ፣ የወሎንና የሸዋን መሳፍንት ከማስገበራቸው በፊት እነዚህን ማሳመን ነበረባቸው ። ይሁን እንጂ ፣ የአጸጋው ባላባት ደጃች ወልደ ሚካኤል ዮሐንስ ከመንገሣቸው በፊት ከነገሡም በኋላ እምቢ አልገ ዛም ብለው በሽፍትነት ስለጸኑ ፣ "እምቢ አለ ወልዱ" እየተባለ ያን ጊዜ የተዘፈነላቸው እስከ ጊዜያችን ደርሷል ።

ዐጼ ዮሐንስን በሐማሴን ያስቸገራቸው ሌላው ባላገራ በተንኮሉ "አባ ከይሲ" እያሉ የሚጠሩት ካሳ አባ ጐልጀ ነው ። እርሱም እንደ ወልደ ሚካኤል ካጼ ዮሐንስ ጋር እየተዋጋ አልጠመድ ብሎ አስቸ ግሮ ሳለ ፣ በ1866 ዓ.ም. በሰኔ ወር ሲዋጋ ተማርኮ ተገደለ ። ወልደ ሚካኤልም ከውጊያ ላይ ተይዘው ከታሰሩ በኋላ አምልጠው ወደ ምጥዋ በመሔድ ከግብጾች ጋር ተደባልቀዋል ። በቤገምድር ራስ ወልደ ማርያም ፣ በሰሜን ደጃች ወሬኛ(ወልደ ሥላሴ) ፣ በየጁ ደጃች ዐሊ ብሩ በመሸፈት ላይ እንዳሉ ፣ ዐሊ ብሩ ለዮሐንስ በታመኑት በዋግሹም ተፈሪ ወታደሮች ተገደሉ ። ከዚህ በኋላ ዮሐንስ ከዐድዋ ወደ ጐንደር ወሬኛን ለመደምሰስ ሲጓዙ ፣ ወሬኛ ለመመከት ዐቅ ማቸው እንደማይፈቅድላቸው ተመልክተው ታጥቀው ላጼ ዮሐንስ ገቡ ። ንጉሠ ነገሥቱም በዚሁ ተደስተው "ወሬኛ" የሚባለውን ስም "በወልደ ሥላሴ" አስለውጠው ፣ የራስነት ማዕረግ ሰጥተው አስደሰቷ ቸው ።



እንደዚሁም ፣ በጐጃም ቀደም ብለው የደጃች ተድላ ጓሉን ልጅ ደጃች ደስታን በራስነት ማዕረግ ሾመዋቸው ሳለ ፣ የደስታ ባላንጣ ራስ አዳል የንጉሠ ነገሥቱን መራቅ ተመልክተው ራስ ደስታን በ1867 ዓ.ም. በሐምሌ ወር ገጥመው ፣ በጦርነት ገድለው የጐጃምን ግዛት በኃይላቸው እጅ ካደረጉ በኋላ ፣ "ጐጃም ጥንትም ያባታቸው ግዛት መሆኑን ጠቅሰው ምሕረት አድርገው ጐጃምን ከመረቁላቸው እየገበሩ እንደሚገዙ አረጋገጡላቸው ። ዐጼ ዮሐንስም ፣ ሌላ ብዙ የአገዛዝ ጣጣ እንዳለባቸው በመረዳትና ሰላም በመፈለግ ይኸንኑ እሺ ብለው ስለ መረቁላቸው ፣ ራስ አዳል ደንበኛ ያጼ ዮሐንስን መን ግሥት ደጋፊ ሆኑ ። ታማኝነታቸውንም ከገለጹላቸው ወዲህ የቤገ ምድር ግዛት ለዋግሹም ተፈሪ በመስጠቱ ፣ ቀጥሎም ተፈሪ በ1866 ዓ.ም. ሞተው ልጃቸው ከበደ (ዋግሹም) ስለ ተተኩ ፣ በዚሁ ምክንያት ተቀይመው የሸፈቱትን ራስ ወልደ ማርያምን በውጊያ በመግደል የዮሐንስን ጠላት አጥፍተዋል ።[1]

በዚህ ዐይነት ፣ ባገር ውስጥ የሸፈቱባቸውን ይነስ ይብዛ የመደ ምሰሱና የማሳመኑ መንገድ የተሻለ መሥመር ሲይዝ ፣ ሌላው ባዲሱ ንጉሠ ነገሥት አገዛዝ ችግር የፈጠረው የካቶሊኮች ይዞታ ነበር ። የነርሱም ይዞታ ያስቸገራቸው ገና ከመንገሣቸው በፊት መሆኑን የሚገልጽልን ፣ በ1862 ዓ.ም. ለናፖሊዎን ሣልሳይ የጻፉት ደብዳቤ ነው ። ቃሉም እንደዚህ የሚል ነው ።

> "በስመ አብ. . . የተላከ ከደጃዝማች ካሳ. . .የሰደዱት ወረቀት ደረሰኝ. . .አንድ ነገር እለምንዎታለሁ ። የካቶሊክ ካህናቶች እኔ አስተምሩ ሳልላቸው 'ቤተክርስቲያኑ የኛ ነው ፣ ካህናቱም የኛ ናቸው' እያሉ አስቸገሩኝ ። በዚህ ነገር የመጣ አይሆንልኝም ። ጥንትም በሴትና በካህን ነው ጠብ የሚመጣው ። አሁንም ከርስዎ ጋር እንዳያጣሉኝ ። የካቶ ሊክ ሃይማኖት ክፉ ነው ብዬ አይደለም ። ነገር ግን ፣ ዕጣዬ የማርቆስ የእስክንድርያ ሃይማኖት ነው. . . አሁንም እነዚ ህን ካህናት ቢከለክሉልኝ ስለብዙ ገንዘብ እቆጥረዋለሁ ። ነጋዴ ቢመጣ እጠብቅአለሁ ። አገር የሚአይ ቢመጣ እቀበ ልአለሁ ። የክርስቲያን አገር ነው አልከለክልም. . .ከርስዎ ጋር ፍቅር(ወዳጅነት) አጥብቄ ፈልጌአለሁ. . . ተጽሕፈት በ2 ቀን በመጋቢት 1862 ዓ.ም. አድመጐንቲ ላይ"[2]

---

1 አቶ ዐፅሜ ፣ የጋላ ታሪክ ፣ ገጽ 145 ።
2 ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ፣ የእጅ ጽሑፍ ክፍል ፣ ቁጥር ኢፍ 793 ።

ይኸን የጻፉት ከመንገሣቸው በፊት ነው ። ከነገሡ በኋላ በግድ ጳጳ
ሱም ፣ እርሳቸውም አንድ እርምጃ በካቶሊኮቹ ላይ ለመውሰድ ግዴታ
እንደ ሆነባቸው ይታያል ።

አባ ሰላማ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስን ቀብተው እንዳነገሡ ሁሉ ፤ ዐፄ ዮሐ
ንስንም አቡነ አትናቴዎስ ስላነገሷቸው ፣ በሃይማኖትም ባስተዳደርም
ንጉሡና ጳጳሱ ተባብረው ከመሥራት ላይ በሚገኙበት ጊዜ ከቀድሞ
ዠምሮ በከረን ፣ በሐላይ የካቶሊክ ፣ የላዛሪስት ሚሲዮኖች ተመሥርተው
ያገር ተወላጁንም እየሰበኩ ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት በመሳባቸው ምክ
ንያት የነርሱ አያያዝ ንጉሡንም ጳጳሱንም ስለ እናደደ ፣ በጳጳሱ ግፊት
ጭምር የካቶሊኮቹ ቤተ ክርስቲያናቸው እና የተማሪ ቤታቸው እንዲ
ዘጋ ተደረገ ። እነርሱ ደግሞ ፣ በፈረንሳይ መንግሥትና ምጥዋ በሚቀመ
ጠው ቆንሲል እየተመኩ በተለይም በፊት ወዳጃቸው አሁን የንጉሡ
ጠላት በሆነው በሙንሲንጀር እየተማመኑ ፣ የንጉሡን ያፄ ዮሐንስን
ትእዛዝ እምቢ ብለው ማስተማራቸውን እና ለተዋሕዶ ቤተ ክርስቲ
ያንም እንደ ባላንጣ ሆነው መስበካቸውን ቀጠሉ ። ውስጡን ከሙን
ሲንጀርና ካፄ ዮሐንስ ባላጋራዎች ከነካሳ አባ ጐልጃ ጋር እየተስ
ማሙ ወደነርሱ ጠጋ ላለውም ሕዝብ ፣ "እይዟችሁ ፣ ከኛ ጋር ብትሆኑ
ማንም አይነካችሁም ። ኃያሉ የፈረንሳይ መንግሥት ይጠብቃችኋል ።
አዲሱም የግብጽ ገዥ ይደግፋችኋል" እያሉ ስለ ሰበኩ ፣ በንዴት
በንጉሡና በጳጳሱ ትእዛዝ ወታደር ሔዶ ሐላይ ከተማ ያለውን የካቶ
ሊኮቹን ሠፈር ወርሮ ቤተ ክርስቲያናቸውንና መኖሪያ ቤታቸውንም
እስከ መዝረፍ ደረሰ ።

በዚህም ድርጊት ጳጳሱ ደስ ሲላቸው ፣ ባንድ ወገን ደግሞ ራሳ
ቸው ጳጳሱ የግብጽ ተወላጅና የከዲቭ ኢስማኤል ዜጋ ስለሆኑ ፣ ከኢስ
ማኤልና ከወኪሉ ከሙንሲንጀር የዛቻና የወቀሳ ቃል ደረሰባቸው ።
ጳጳሱ ግን ፣ ከዮሐንስ ጋር ትብብራቸውን አላቋረጡም ። በሌላ በኩል
ደግሞ ፣ ጳጳሱ አቡነ አትናቴዎስ ዐፄ ዮሐንስን በካቶሊኮቹ ፈረንሳዮች
ላይ እያስነሡና ውስጡን እያስጠሉ ፣ ያገራቸው መንግሥት መሪ
ኢስማኤል በፈረንሳይ ዘንድ እንዲወደድና የመሬት ፍለጋው እንዲ
ቃናለት አድርገዋል እየተባሉ በጐን ታምተዋል ።

በዚህ ዐይነት ፣ ዐፄ ዮሐንስ ባንድ ወገን የኢትዮጵያን ታሪካዊ
አውራጃ በጐስን ፣ ሐባብን ከወረሩ ከግብጾቹና የነርሱ መሣሪያ ከሆ
ኑት ከነካሳ ፣ ከነ ወልደ ሚካኤል ጋር ሲታገሉ ፣ በሃይማኖት በኩል
ደግሞ ካቶሊኮቹን በመቃወም ተዋሕዶ ሃይማኖትን በማጽናት ፣ ባገር
ውስጥ በተዋሕዶ እምነት ተከታዮችና በጳጳሱ ዘንድ ምስጋናን ፣ መደ
ነቅን አትርፈዋል ። በሌላ ወገን ደግሞ ፣ ካቶሊኮቹ በመጉላላታቸው



ምንም እንኳን በደብዳቤ ሁኔታውን ቢገልጡለት ፣ የካቶሊኮች የበላይ
ጠባቂያቸው ፈረንሳይ ባፄ ዮሐንስ ላይ ዛቻን የተንተራሰ ደብዳቤ በመ
ጻፍ ማስፈራራቱ አልቀረም ።

በካቶሊኮቹ አንጻር ፣ ያፄ ዮሐንስ አቅዋም ግልጽ ነበር ። ይኸም
"የኢትዮጵያ ሕዝብ ፣ ክርስቲያኑ አንድ ጊዜ በተዋሕዶ ሃይማኖት
ጥምቀተ ክርስትና ስለ ተቀበለ ፣ እርሱን ሰብከን ወደ ካቶሊክ ሃይማ
ኖት እንመልሰው አትበሉ ። ወንጌል ማስተማር ካማራችሁ በክርስቶስ
ወደማያምኑት እስላሞች ወይም ምንም ሃይማኖት ወደሌላቸው ነገዶች
ሒዳችሁ አስተምሩ" የሚል ነበር ። ይኸንንም ለውጭ አገር መሪዎች
በተለይ ለእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፣ ለግራንቪል ፣ ስሞታቸ
ውን በአሰሙበት ሰዓት በዘመኑ አነጋገራቸው እንደዚህ ሲሉ
ገልጸዋል ።

> . . . አንድ ነገር ልንገርዎ ይስሙኝ የካቶሊኮችን ነገር ፣
> ባገርህ የኛን ሃይማኖት ልናስተምር (እናስተምር) አሉኝ ።
> እኔ ግን መለስሁላቸው በሥላሴ ስም ተጠምቄአለሁ ። ክር
> ስቶስን በወንጌል አምናለሁ የሚያስተምረኝም በማርቆስ
> ወንበር የተቀመጠ የማርቆስን ዕጣ (ተዋሕዶ) የያዘ ከእስክ
> ንድርያ እርሱ ነው ። ለሕዝቤም የሚያስተምሩ እርሱ
> (የእስክንድርያው ፓትሪያርክ ወይም ጳጳሱ) የሾማቸው
> ቀሳውስት አሉኝ ። ደግሞ እልሁዋቸው ማስተማር ብትፈ
> ልጉ በዚች ዓለም በሥላሴ ስም ያልተጠመቁ ፣ ክርስቶስን
> በወንጌል የማያምኑ ብዙ አህዛብ አሉ ። እነዚያን አስተምሩ
> አልሁዋቸው ። ስለዚህ ነገር ነው ዋግሹም ጐበዜን
> (ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስን) ና ብለው ደብዳቤ ልከው በኢት
> ዮጵያ ያሉ (ያሉትን) የሕዝበ ክርስቲያንን ደም ያፈሰሱ
> እነዚያ(ካቶሊኮቹ) ናቸው ካሉ በኋላ ከዚሁ አያይዘው ፣
>
> ደግሞ ካለፈቃዴ ቤተ ክርስቲያን ሠሩ ። ካገሬ ሕዝ
> ብን ሁሉ ኑ ወደኛ ፣ ግብር እንዳትገብሩ አሉአቸው ። እኔም
> አንድ ሹሜን 'ሂድ ግብር አውጣ' ብዬ ሰደድሁት ። እነዚ
> ያም (በካቶሊኮቹ የተሰበኩት ባላገሮች) እምቢ አንገብርም
> አሉ ። አዝጌ የሰደድሁት ሹሜ ቤታቸውን ሲያቃጥል አብሮ
> ተኮሰባቸው (የነርሱንም ቤተ ክርስቲያን አቃጠለባቸው)
> ካሉ በኋላ ፣ ቀጥለው ስለ ዋና ባላጋራቸው ስለ ሙንሲንጀር
> እንደዚህ ሲሉ ደምድመዋል ።
>
> የኔን ስም ሊአስከፉት ነው ፤ ይህን ሁሉ ግፍ ይው
> ልኝ ፤ ይህን ሁሉ የሚአደርገኝ ምንስንጅር ነው ። ቱርክ

መርቼ መጥቼ አስግድልህአለሁ ብሎ ፈከረልኝ (ፎከረብኝ) ግፌን ይውት ። የካቶሊኮችን ከፋታቸውን ሁሉ ጽፌ ወደ ናንተ ብሰድ ምንስጅር (ቤይ) ቀምቶ ምጥዋ ላይ ከባሕር አገባው. . . ተጽሕፈ በ8 ቀን ነሐሴ በ1864 ዓመተ ምሕረት በዐድዋ ከተማ ።

ዳሩ ግን ፣ በዚህ ዐይነት እንደ ግራንቪል ለንግሥት ቪክቶርያም ፣ ለወዳጆቻቸው ለእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ሁሉ አቤቱታ ቢያሰሙም ፣ የሰጡአቸው ድጋፍ የቀዘቀዘ ነበር ።

ከቀድሞ ዠምሮ ወዳጅነቱን ይተማመኑ የነበረው የእንግሊዝ መንግሥት ፣ ባንድ ወገን ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር በዚህ የተነሣ መጋጨቱን በመጥላት ፣ ሁለተኛ ደግሞ ምጥዋን ፣ ቦጐስን ፣ ሐባብን እና የስዊዝ ቦይን መተላለፊያ ከያዘው ከግብጹ ከዲቭ ኢስማኤል ጋር ወዳጅነትን መሥርተው ፣ በርሱ አማካይነት በሱዳን ፣ በሌላውም የአፍሪካና የእስያ ክፍል መስፋፋት ስለ ተመኙ ፣ እንደዚሁም የካቶሊኮቹ መሪዎች እነ ሞንሲኞር ቱቪዬ ፣ በኢትዮጵያ ከነራስ ዐሊ ዘመን ዠምሮ የተቀመጡት እነ ዶክተር ሺምበር "የእስላም ተጽዕኖ 'እንፍሎያንስ' ባለበት በምጥዋ ፣ በበጐስ ፣ በሐባብ 'ሥርዓት የሌለው የሐበሻ አስተዳደር' ከሚገባ በብዙ ረገድ ግብጾቹ ይሻላሉ" እያሉ በገሃድም ፣ ውስጥ ለውስጥም እየጻፉ ፕሮፓጋንዳ ስለ አደረጉ ፣ እንግሊዞቹ ባዔ ዮሐንስ በኩል የሚደርሳቸውን የስሞታ ደብዳቤ አብዛኛውን ጊዜ ችላ እያሉ ወደ ጐን ተወት ያደርጉት ነበር ።

በተቻለ መጠን ፣ የእንግሊዝ እና የሌሎቹም የአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት በኢስማኤል ፓሻና ባዔ ዮሐንስ መካከል በነበረው የመሬትና የፖለቲካ ቅራኔ ላይ በወቅቱ የነበራቸው አቅዋም የገለልተኛነት ወይም የመካከለኝነት አቅዋም ነበር ። ፈረንሳይ በካቶሊኮቹ መጐላላት የተነሣ ዐፄ ዮሐንስን የመቃወም ፣ መስኮብ ደግሞ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ሳቢያ ከኢትዮጵያ ጋር በነበረው መቀራረብ ድጋፍ ቢያሳይም ፣ ሁለቱም ዞረው ፣ ዞረው እንደ እንግሊዞቹ የመረጡት መካከለኛውን ሥፍራ ነበር ። በተለይ ከእንግሊዝ ንግሥት ወደ ዐፄ ዮሐንስ ደብዳቤና ገጸ በረከት ይዞ መጥቶ በዐድዋ የሰነበተው ኮሎኔል ፕሪዶ የሚባለው የእንግሊዝ የጦር መኰንን ወዳገሩ እንደ ተመለሰ ፣ ለመንግሥቱ ባቀረበው ራፖር በምጥዋ የሙንሲንጀርን አስተዳደር እያመሰገነ ያዔ ዮሐንስን ስለ ነቀፈ ፣ እንግሊዝም ለወደፊት የመስፋፋት ዓላማው በግብጽም ፣ በኢትዮጵያም ለመጠቀም ስለ ፈለገ ፣ ሁኔታውን ለጊዜው ራቅ ብሎ በቻልታ መመልከትን መርጧል ።



አንባቢ በመዠመሪያው መጽሐፍ ላይ እንደሚያስታውሰው ፣ ፕሪዶና ሙንሲንጀር በመቅደላ ጦርነት ጊዜ ተገናኝተው ስለ ተወዳጁ ፣ ፕሪዶ በምጥዋም በሰነበተበት ጊዜ ሙንሲንጀር በመልካም መስተንግዶ ሳያንከባክበው አልቀረምና ፣ ያዔ ዮሐንስን አስተዳደር እየነቀፈ ፣ የርሱን አስተዳደር ያመሰገነበት ምክንያት ከዕውነታው ጐን ከመስተንግዶው ጋርም የተያያዘ ሳይሆን አይቀርም ።

የሆነ ሆኖ ፣ በተዋሕዶ ሃይማኖትና በካቶሊክ ሃይማኖት ቅራኔ ሳቢያ ያዔ ዮሐንስ ኢትዮጵያና የፈረንሳይ መንግሥት ግንኙነታቸው በሻከረበት ሰዓት እነሞን ሲኞር ቱቪዬ ፣ ወዲያና ወዲህ እያሉ ዐዔ ዮሐንስን በጽሑፍም በቃልም እየወነጀሉ ሲያስጠሉ ፣ እስላሙ የግብጽ መንግሥት ለአገባቡ እንዲመቸው በባላጋራዎቹ ክርስቲያኖች መካከል ገብቶ ፣ በጠባቸው እየተጠቀመ የካቶሊኮቹ ጠባቂና እንከባካቢ ሆኖ ተገኘ ። በዚህ ይዞታው ፣ ዐዔ ዮሐንስ በጳጳሱ ግፊት ጭምር ባደረጉት ሁሉ 'የሰውን መብት የሚጥሱ ፣ የሃይማኖትን ስብከት የሚፃረሩ' ተብለው ሲነቀፉ ፣ እስማኤል በርሳቸው አንጻር ሥልጣኑን አስተዳዳሪ ፣ የማናቸውንም ዜጋ መብት ጠባቂ ተብሎ መመስገን ዠመረ ። ቢሆንም ፣ ሙሴ ኤርኔስት ደሳርዜክ የሚባለው በምጥዋ የፈረንሳይ መንግሥት ቆንሲል ከመንግሥቱ እየተላከ ወደ ዐድዋ መጥቶ ሁለት ጊዜ ተገናኝቶ የቦጎስንም ወረራ ፣ የሃይማኖቱንም ጉዳይ በሰፊው ካዔ ዮሐንስ ጋር በመወያየት ከሰነበተ በኋላ ፣ በሐላይ ከተፈጸመው ከዘረፋውና ከቤት ቃጠሎው በቀር ፣ ካቶሊኮቹ ወገኖቻቸውን እየሰበኩ በማሸፈታቸው ፣ ግብር እንዳይከፍሉ በመከልከላቸው ፣ በታሪክ የኢትዮጵያ ይዞታ የነበረውን የቦጎስን ፣ የሐባብን አውራጃ ግብጾች በሙንሲንጀር እየተመሩ በመውረራቸው እየወቀሰ ፣ በሙሉ ያዔ ዮሐንስን አቅዋም ደግፏል ። በዚሁም ከካቶሊኮቹ መሪዎች እነሞንሲኞር ቱቪዬ ፣ "ይኸስ የዮሐንስ የጦር እሊቃ ነው" ብለው እስከ ማፌዝ ደርሰዋል ። ይሁን እንጂ ፣ ከካቶሊኮቹም ወገን እንደ እነ አባ ዳፍሎና ሌሎችም የኢትዮጵያ ካቶሊካውያን የዐዔ ዮሐንስን አቅዋም በመደገፍ ዐዔ ዮሐንስን ፣ ክርስቲያኑን ለማጥቃት ከእስላሙ መንግሥት ከተወዳጁት ከሞንሲኞር ቱቪዬ ጋር በአቅዋም የተለዩ ነበሩባቸው ።

የሆነ ሆኖ ፣ ባንድ ወገን የካቶሊኮቹ መሪ እኚሁ ቱቪዬ ፣ በሌላ ወገን የታወቀው ሙንሲንጀር ፣ "ቆንሲሉ ደሳርዜክ በፍጹም የፈረንሳይን ጥቅም ፣ የዜጎቿን መብት አይጠብቅም ፤ ከካቶሊኮቹ ጠላት ካዔ ዮሐንስና ከአቡኑ ከአባ አትናቴዎስ ጋር በመወዳጀት ተመሳጥሯል እያሉ ክሳቸውና ወቀሳቸው ስለ በረከተ ፣ የፈረንሳይ መንግሥት ባንድ ወገን ካቶሊኮቹን ፣ በሌላ ወገን የግብጽን ባለሥልጣኖች ለማስደሰት

ሲል ብዙ ጊዜ በሚጽፈመው ራፖር ሁሉ ፣ ዐፄ ዮሐንስን ይደግፍ የነበረውን ደሳርዜክን ሽሮ በርሱ እግር ካርሶኔል ተሾሞ ወደ ምጥዋ መጣ ።

በዚህ ጊዜ ፣ በክርስቲያንነት አንድነት ሊኖራቸው ይገባ የነበረው የካቶሊክና የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጠብ ተለያይተው በኢትዮጵያ ያሉት የካቶሊኮቹ መሪዎች እነሞንሲኞር ቱቪዬ ፣ በውስጥ ካሉት እስላሞች ጋር በማበርና ዐፄ ዮሐንስን በመቃወም ለከዲቭ ኢስማኤል እንደ ቃል ኪዳን ጓደኛ መሣሪያ ሆነውለት ነበር ።[1]

---


1 G. Douin, Histoire du regne du Kedive Ismael - Tome III[e] Partie, (1869—1873) p. 361—371.





ራስ አርአያ ሥላሴ ድምፁ በዓልጋዳ በተባሉበት ዘመን

(ከቲዎፊል ለፌቭር መጽሐፍ)



ዐፄ ዮሐንስ ለእንግሊዝ መንግሥት ምክር ቤት የጻፉት

(ፐብሊክ ሪኮርድ ኦፊስ ለንዶን)

# ምዕራፍ ሰባት

## በከዲቭ ኢስማኤል የሚመራው የግብጽ መንግሥት ባዲስ መልክ መቋቋም

መሐመድ ዐሊ (1797—1840) የግብጽን መንግሥት አቋቁሞ ከጨረሰ በኋላ ፥ ለግብጽና ለሱዳን ሕይወት የሚሰጠውን የአባይን ምንጭ በእጁ አድርጎ ለመቆጣጠር እንዲመቸው ፥ የመተማን ወሰን ዐልፎ የኢትዮጵያን አውራጃ በወረረበት ሰዓት ፥ እነራስ ዐሊ ለፈረንሳይና ለእንግሊዝ ነገሥታት ያቤቱታ ደብዳቤ ጽፈው ፥ በነዚህ ሁለት የኤሮፓ ኃያላን ነገሥታት ግፊት ምክንያት አሳቡን አቆመ ። እርሱም ወዲያው በ1840 ዓ.ም. ሞቶ የልጅ ልጁ አባስ ሥልጣን በያዘ ጊዜ ፥ አሳቡን ከሥልጣኔና ከልማት ይልቅ ወደ ሃይማኖት አጥባቂነት አዞሮ ሳለ በ1846 ዓ. ም. ሞተ ። ቀጥሎም የመሐመድ ዐሊ አራተኛው ልጁ ሰይድ ፓሻ ሥልጣን በጨበጠ ጊዜ ፥ በኢትዮጵያ ላይ አባቱ መሐመድ ዐሊ ያቀደውን የወረራ ዓላማ እርግፍ አድርጎ በመተውካዬ ቴዎድሮስ ጋር ደብዳቤና ገጸ በረከት በመላላክ መልካም የጉርብትና ወዳጅነት ለመፍጠር መሞከሩን ፥ "ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት" በተባለው መጽሐፍ ላይ አመልክተናል ።

ሰይድ ፓሻ ፥ በዘመኑ ከሠራቸው ተግባሮች ዋና ቁም ነገር ሆነው የተቆጠሩለት ፥ ከበላዩ ከቱርክ ሡልጣን አስፈቅዶ የስዊዝን ቦይ ደሊሴፕስ በሚባለው የፈረንሳይ መሐንዲስ አማካይነት በውል ማስቀደዱ ነው ። ቀድሞ በደቡብ አፍሪካ በኩል እየተዞረ ፥ ወይም በመካከለኛው ምሥራቅ በባሕርና በየብስ በብዙ የጉዞ ችግር አውሮፓና ሩቅ ምሥራቅ ይገናኙ የነበረው ፥ አሁን በዚህ የስዊዝ ቦይ መከፈት ምክንያት ሩቅ ምሥራቅና አውሮፓ በቀላሉ፡ዳንግድም ፥ የፖለቲካም ግንኙነት ስለ አደረጉ ፥ ለዚህ ግንኙነት አማካይ ለሆነው ለግብጽ መንግሥት በአውሮፓ መንግሥታት ዘንድ የመከበርና የተፈላጊነት ሁኔታ ፈጠረለት ። በዚህ ቦይ መከፈት የተነሣ በተቋቋመው ማኅበር ውስጥ በአክሲዮንም ፥ በቀረጥም በሚያገኘው ገቢ የኢኮኖሚውን አቅዋም ለጊዜው ለማሻሻል ቻለ ።

ዳሩ ግን ፥ ሰይድ ፓሻ ብዙ የማሻሻል ሁኔታ ባገሩ ላይ ካሳየ በኋላ ፥ በ1855 ዓ.ም. ስለ ሞተ ፥ የመሐመድ ዐሊ የልጅ ልጅ የኢብ

ራሂም ልጅ አህመድ ሊከተለው ሲገባ ፣ በድንገተኛ የባቡር አደጋ እሱም ስለ ሞተ ፣ ታናሽ ወንድሙ ኢስማኤል ሥልጣን ያዘ ። ኢስማኤልም ሥልጣን የያዘው የስመ ጥሩው የግብጽ ገንቢ የተባለው የመሐመድ ዐሊ የልጅ ልጅ በመሆኑ ነው ።

ኢስማኤል ፣ የዐረብኛውን ትምህርት በግብጽ አገር በካይሮ ከተማ ካጠናቀቀ በኋላ ፣ ወደ ፈረንሳዊ አገር ተልኮ ሴን ሲር በሚባለው ወታደራዊ ትምህርት ቤት ሲማር ቆይቶ ወደ ግብጽ ተመልሶ በአጐቶቹ ሥር ሲያገለግል እንደቆየ አሁን በ33 ዓመት ዕድሜው ፣ በ1865 ዓ.ም. ሥልጣን ያዘ ። ሹመቱን ለማጽደቅ ወደ ቱርክ ዋና ከተማ ወደ ቁስጥንጥንያ (ስታንቡል) በሔደበት ጊዜ ፣ ሡልጣን አብዱል አዚዝን አገሩን ግብጽን እንዲጐበኝለት ለመነ ። ሡልጣኑ በርሱው ልመና ግብጽን ስለ ጐበኘ ፣ የኢስማኤል ፓሻ ስም እየገነነ ሔደ ። ፈረንሳይ አገር በትምህርት እንደ መቆየቱ መጠን ፣ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ዠምሮ የአውሮፓን ሥልጣኔ በየመልኩ ባገሩ ለማስገባት የአስተዳደሩ ፣ የፍርዱ ሥራ እንዲሻሻል ፤ የቴክኒከም ፣ የኢንዱስትሪም ፣ የእርሻም ሥራ እንዲስፋፋ ይጣጣር ዠመር ።

ከርሱ በፊት የነበሩት የግብጽ መሪዎች ፣ በቀጥታ የቱርክ ሡልጣን ወኪል ሆነው ግብጽን ያስተዳድሩበት የነበረው የፓሻነት ሥያሜ ቀርቶ ፣ በእርሱ ጊዜ ለመዠመሪያ በሡልጣኑ ፈቃድ "ከዲቭ" እየተባለ እንዲጠራ ተፈቀደለት ። ከዲቭ ማለት በፋርስ ቋንቋ ከቡሩ ወይም ጌታው ማለት ነው ።[1] በቱርክ መንግሥት ውስጥ ከርሱ በፊት የነበሩት አባቶቹ የማዕረጋቸው ደረጃ ከቱርኩ ጠቅላይ ሚኒስትር(ወዚር) ቀጥሎ የነበረው ፣ አሁን ከዲቭ ኢስማኤል በቀጥታ ከሡልጣኑ እንዲቀጥል ተወሰነ ። ከዚህም ጋር አንድ ጊዜ ያመት ግብሩን ከ120 000 እስከ 150 000 የሚደርስ የቱርክ ገንዘብ (ቦርስ) ለጌታው ለቱርክ ሡልጣን ከመክፈል በቀር በአገሩ በግብጽ ከቀድሞው የላቀ ነጻነት ያለው የውስጥ አስተዳደር አስፈቀደ ።

በተለይ በሰይድ ጊዜ የተቀደደው የስዊዝ ቦይ ተከፍቶና በኩባንያ መልክ ተቋቁሞ በትክክል መሥራት የዠመረው በርሱ ጊዜ ስለ ሆነ ፣ በአውሮፓውያን ዘንድ ግንኙነቱን የማስፋፋት ዕድል አገኘ ። በ1867 ዓ.ም. በፓሪስ ዓለም ዐቀፍ ኤክስፖዚሲዮን በተከፈተበት ጊዜ በግብዣ ሔዶ ፓሪስ ሲገባ አቀባበሉም ፣ መስተንግዶውም ልክ እንደ አንድ የነጻ መንግሥት መሪ ነበር ። እርሱም በበኩሉ ፣ በራሱ ፈቃድ

1 Catawi Pacha, Coup d'oeil sur la chronologie de la Naticn Egypt, pp. 372—375.



ለፋ ያለ ሥልጣን የሰጠው የቱርክ ሡልጣን ቅሬታውን እስኪገልጥ ድረስ ፣ የውጭ መሪዎችን ወደ ካይሮ እየጋበዘ ማስተናገድ ዠመረ ።

ኬዲቭ ኢስማኤል ለወንዶችም ፣ ለሴቶችም የሚሆን ትምህርት ቤት ፣ ሙዚዩም ፣ ቤተ መጻሕፍት ፣ የቲያትር ቤት በያለበት እየከፈተ በሚያስፋፋበት ጊዜ ፣ በዙሪያው ምሁራን የነበሩትን ግብጻውያን ከመሰብሰቡ በላይ ፣ ብዙ የእንግሊዝና የፈረንሳይ ፣ የአውስትሪያ ፣ የጀርመን ፣ የአሜሪካ፣ የዴንማርክና የኢጣልያ ዜጎችን እየቀጠረ በየቢሮው ፣ በየጦር ድርጅቱ እያስገባ ፣ በየአውራጃው በማሠራጨት ያስተዳድር ዠመር ። ከዚህም ጋር የከተማው ሕንፃ ፣ የመንገዱ ቅየሳ ፣ ያበባው ማማር በሁሉም በኩል ድርጅቱ ሁሉ ደንበኛ አውሮፓዊ መልክ እንዲኖረው ከማድረግ ጋር የእጅ ጥበበኞች ፣ የግብርና ባለሙያዎች ፣ መሐንዲሶች ከየአገራቸው ወደ ግብጽ እየመጡ በልማት ሥራ እንዲካፈሉ ያበረታታ ዠመር ። ለዚህ ሁሉ ሥራው ቀኝ እጅ ሆኖ የሚያገለግለው የአርመንነት ዘር የነበረው ኑባር ፓሻ የሚባለው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ነበር ።

በዚህ ዐይነት ፣ ባገር ውስጥ አስተዳደሩ የዘረጋው የልማት ሥራ በመልካም ሁኔታ በሚካሔድበት ጊዜ ከሕዝብ ቀረጥም ፣ በስዊዝ ቦይ ከሚተላለፈውም ሸቀጥ በቀረጥና በአክሲዮን ክፍያ የሚገኘው ያገር ውስጥ ገቢ ያለ ጥናት የዘረጋውን የልማት ሥራ ገና ሳይደፍንና ግቡን ሳይመታ ፣ በውስጥ አስተዳደሩ አብዛኛውን ጊዜ በውጭ አገር ሰዎች እና ባገርም ውስጥ በነበሩት መመስገንን ስላገኘ ፣ አሳቡን ከልማት አውጥቶ ለግብጽ ሰፊ የቄሣር ግዛት ወደ ማስገኘት ምኞት አዞረው ። ይኸም በሚቀጥለው ምዕራፍ እንደሚታየው የመውደቂያው ምክንያት ሆነ ። የጣለውም ዋናው ባላጋራ ያለ በቂ የኢኮኖሚ አውታር ከልክ ያሰፈ የልማት መስፋፋትና ይልቁንም እላይ እንዳልነው ከካይሮ እስከ ኒያንሳ ሐይቅ የሚደርስ ሰፊ የቄሣር ግዛት ያለ ዐቅም ለመመሥረት ማቀዱ ነው ።



ኢስማኤል ፓሻ

(ከአባ ማስያስ መጽሐፍ፣ ቅጽ 9)

# ምዕራፍ ስምንት

## የግብጽ ጦር ምጥዋ ከገባ በኋላ ፡ ቦጐስን ስለ መውረሩ — የከዲቭ ኢስማኤል በኢትዮጵያ ላይ የመስፋፋት ምኞቱ

ከመሐመድ ዐሊ ጊዜ ጀምሮ ፡ የሱዳን ግዛት ተጠቃሎ በግብጽ አገዛዝ ውስጥ ገብቷል ። ባገራችንም የውስጥ ጦርነት መኖርንና የጠነከረ የማዕከላዊ መንግሥት መጥፋትን ሁኔታ በመጠቀም ፡ በቤገምድርና በሱዳን መካከል የሚገኙትን ቀድሞ የጐንደር ነገሥታት እነ ዐፄ ፋሲል ፡ እነ ዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ይፋለሙባቸው የነበሩትን የሰናርንና የመተማን አካባቢ ወርሮአል ፤ እንደዚሁም ከሱዳን ዐልፎ እስከ ኒያንሳ ሐይቅ ድረስ የግብጽን ግዛት አስፋፍቷል ። የሱአኪምና የምጥዋ ወደቦች ከ16ኛው መቶ ዓመት ጀምሮ በቀጥታ በቱርክ ቁጥጥር ሥር የነበሩ ሲሆኑ ፡ ኢስማኤል ለቱርኩ ሡልጣን ባሳየው ታዛዥነትና መግባባት ፡ በሡልጣኑ ፈቃድና ትዕዛዝ እነዚህ ሁለት ወደቦች እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1866 ዓ.ም. የግብጽ ግዛት እንዲሆኑ ስለ ተወሰነ ፡ ለቱርክ ሡልጣን ያመት ግብር 37 500 ስተርሊንግ ብቻ እየሰጠ ፡ በምጥዋ በኩል የሚገባውንና የሚወጣውን ሸቀጥና መሣሪያ የመቆጣጠርና ቀረጥ የመቀበል መብት በፈርማና በዐዋጅ ለከዲቭ ኢስማኤል ተሰጠው ።[1]

ከዚህ በኋላ ፡ ከዲቭ ኢስማኤል በወታደርነት በሠለጠኑ የውጭ አገር ተወላጆች እየተረዳ 30,000 የሚሆን የሠለጠነ የጦር ሠራዊት ከደንበኛ ትጥቅ ጋር ከአደራጀ በኋላ ፡ የገዥነት ምኞቱን ከካይሮ እስከ ዛንዚባር ከዚያም እስከ ኒያንሳ ሐይቅ ለማድረስና በነዚህ መካከል የሚገኘውን የኢትዮጵያንና አሁን ሱማሊያ ተብሎ የሚጠራውን ግዛት ከሱዳን ጋር በሙሉ ለመጠቅለል አሰበ ። ይኸንንም ሰፊ የግዛት አሳብ በቀላሉ እንደሚከናወን በጽሑፍም ፡ በቃልም እያስረዱ የገፋፉት እንግሊዞቹ እነ ሳሙኤል ቤከርና እነ ቻርልስ ዦርዥ ጐርዶን ፡ ጣልያኖቹ እነመስዳሊያ እነኢማሊያኒ እነ ሮሞሎጀሲ ፡ አሜሪካዊው ቫይሌ ሎንግ ፡ ዴንማርኩ አሬንድሩን ፡ ስዊሱ ሙንሲንጀር ናቸው ።[2]

---

1 E. Anghieri, Storia della politica Inglese, pp. 67—69.

2 ሮቢንሰን በገጽ 57 እ. ኤ. አ በ1846 መሆኑን ገልጿል ።

ወርነር ሙንሲንጀር በምጥዋ የፈረንሳይ ቆንሲል በነበረበት ጊዜ ዮሐንስ ገና ደጃዝማች ካሳ ሲባሉ ፣ ወዳጅና ረዳት አድርገውት ደብዳቤ ይጻጻፉ ነበር ። ከደብዳቤዎቹ አንዱ ፣ “. . .ለብዙ ጉዳይ ለብዙ ጥበብ ይሆኑኛል ከውጭ መንግሥታትም ያስተዋውቁኛል . . . ብዬ ያመንኩት እርስዎን ነው. . .” የሚል ቃል ይገኝበታል ።

ይህ ሰው ፣ እንግሊዞች እስረኞቻቸውን ለማስፈታት ወደ መቅደላ የመጡ ጊዜ ውስጥ ዐወቅ እንደ መሆኑ መጠን መንገድ በመምራት ፣ ስንቅ በማቅረብ ፣ የወሎንም ኦሮሞዎች በቴዎድሮስ ላይ ከእንግሊዞች ጋር እንዲያብሩ በማድረግ በብዙ ረድቷቸዋል ። ነገር ግን ፣ ደጃች ካሳ (ዐፄ ዮሐንስ) በመስፋፋት ላይ የነበሩትን ካቶሊኮች በተቃወሙ ጊዜ ሙንሲንጀር ለካቶሊኮቹ ጠባቂና ጠበቃ በመሆን ፣ “እንግሊዞችን መርቼ አምጥቼ ቴዎድሮስን እንዳስጠቃሁ እርስዎንም የፈረንሳይን ጦር እየመራሁ አምጥቼ እንደማጠቃዎ ይወቁ. . .ለጊዜው የፈረንሳዊ መንግሥት የደከመ ቢመስልዎት እርስዎን ለመደምሰሻ በቂ ኃይል አለው” የሚል የዛቻ ቃል ጽፎላቸው እንደ ነበር ይታወሳል ።[1]

ዐፄ ዮሐንስ ከነገሡ በኋላ መበርታታቸውን በመመልከት እንደገና ወዳጄ ዮሐንስ በመልእክት ከታረቀ በኋላ ፣ “ራስ ብለው በቦጎስ ፣ በሐባብና በመንሳ አገረ ገዥ ብለው ይሹሙኝና ከልብ እንታረቅ” ብሎ ለምኗቸው ነበር ይባላል ። ነገር ግን ፣ አሳቡን ስለ አልተቀበሉት በመጨረሻ ከርሳቸውም ፣ ከፈረንሳይም ርቆ ፈጽሞ የኢስማኤል አገልጋይ በመሆን ግብጾች በኢትዮጵያ ላይ ለመስፋፋት ላሰቡት ዓላማ ዋና መሣሪያ ሆነ ። ግብጾችም ምጥዋ በገቡ ጊዜ ዋናው አስተናባሪና መሪው እርሱ ስለነበረ ፣ በከዲቭ ኢስማኤል ፈቃድ የምጥዋና የአካባቢው አገረ ገዥ ሆኖ ናይቦቹን በበላይነት እያስተዳደረ ፣ ግብርም ከየባላባቶቹ በራሱ ውሳኔ እየተቀበለ ለግብጽ መንግሥት ገቢ ያደርግ ዠመር ። ግብር በሚወሰንበትም ወቅት ባላባቱ ለርሱ የግል ጉቦ በሰጠው ጊዜ ፣ ግብሩን ቀለል ያደርግ እንደነበር የፈረንሳይ ቆንሲል ደሳርዘክ መዝግቦት ይገኛል ።

በገንዘብም በንግግርም እያባበለ ፣ የአካባቢው ሕዝብ እየከዳ ለግብጾች እንዲገባ ፣ ክርስቲያኖቹም የሐማሴንና የአከለ ጉዛይ ባላባቶች እነ ካሳ አባ ጉልጃ ፣ እነ ደጃች ወልደ ሚካኤል ወደ ግብጾች እንዲገቡ አደረገ ። በመጨረሻም አለቃ ብሩ የሚባሉት የዐፄ ዮሐንስ መካርና መልክተኛ ፣ የውጭ አገር ሰዎች እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር

---

1 J. de Coursac, Le regne de Yohannes, pp. 86—88.



የሚያዩአቸውን አስከድቶ ከግብጾች ጋር በማስማማት ለኢትዮጵያ ጠላት ፣ ለኢስማኤል መሣሪያ እንዲሆኑ አድርጓል ።

ስለዚህ ፣ በኢስማኤል ፈቃድ ፣ የግብጽ ጦር ምጥዋ በ1863 ዓ ም እንደገባ ፣ ሙንሲንጀር የቤይ ማዕረግ አግኝቶ እንደቆየ በመጨረሻ የምጥዋውን ግዛት ለአራኪል ቤይ ለቆ በርሱው አሳሳቢነትና መሪነት የግብጽ ጦር ከምጥዋ እየወጣ ቦጐስን ፣ ሐባብንና መንሳን በ1864 ዓ. ም. ወረረ ። ቀጥሎ ከምጥዋና ከአሥመራ መንገድ እመካከል ላይ የሚገኘውን ጊንዳን በ1865 ዓ ም ያዘ ። እንደዚሁም የግብጽ ጦር በምዕራብ ሱዳን በኩል በኤደም ፓሻ መሪነት በ1864 ዓ ም መጥቶ የመተማን ወሰን ዐልፎ በቋራና በደምቢያ ግዛት ገባ ። የግብጽ መንግሥት የግዛት አሳቡም እንዲከናወንለት ከወሎ ባላባቶች ከነወይዘሮ መስተዋት ጋር ፣ ራቅ ብለው ከሚገኙት ከሸዋው ንጉሥ ከምኒልክ ጋር የወረራ እውነተኛ አሳቡን ሸፈንፈን በማድረግ ፣ ደብዳቤና ገጸ በረከት በመላክ ይወዳጅ ዠመር ።

የእስማኤል መንግሥት ፣ ይኸን የመሰለውን ወረራ በኢትዮጵያ ድንበር በሚፈጽምበት ጊዜ በአውሮፓም የርሱ ወገን ነን የሚሉት ፣ “የግብጽ ሡልጣን ከዲቭ ኢስማኤል ነጻ ሰውና የአውሮፓን ሥልጣን ተቀባይ ነው ፤ በያዘው አገር ለሚገኙት ካቶሊኮችና ለባላገሩ ነጻነትና ትክክለኛ ፍርድ ሰጥቶ በደንብና በሕግ ያስተዳድራቸዋል ። ዮሐንስ ግን ፣ የካቶሊኮችና የሥልጣኔ ጠላት ናቸው” እያሉ በመስበክ የኢስማኤል የወረራ ተግባሩ እንዲቃናለትና በወረራቸው አገሮች ጸንቶ እንዲኖር ይሰባብኩለታል ።

ባገር ውስጥ የሚገኙት የውጭ አገር ሰዎችም ፣ የኢትዮጵያን የዘወትር የርስ በርስ ጦርነትና የማዕከላዊውን መንግሥት ጸጥታ ማጣት እያመዛዘኑ ፣ “ቦጎስንና የምጥዋን አካባቢ ከኢትዮጵያ መንግሥት የግብጽ መንግሥት ቢይዘው የተሻለ ነው” እያሉ ጽፈዋል ።

ከነዚህም አንዱ ዶክተር ዋልሄልም ሺምበር ነበረ ። ሺምበር ከነራስ ዐሊ ዘመን ዠምሮ (1839 ዓ ም ) በኢትዮጵያ የኖረ የዕፀዋት ሊቅ መሆኑን ከዚህ በፊት አውስተናል ። ወይዘሮ ምርዊት የሚባሉ የኢትዮጵያ ተወላጅ አግብቶ ሴቶች ልጆቹ አንዷ ኤርምያስ ካሳን ፣ ሌላዋ ሶፍያ ወይም ፀሐይቱ የምትባለው ካሳ አባ ጉልጃን አግብታ ነበር ። ካሳ ያዬ ዮሐንስ ባላጋራ ፣ የግብጾች ወዳጅ ስለነበረ ፣ በዚሁ ካዬ ዮሐንስ ጦር ጋር ተዋግቶ በተሸነፈና በተገደለ ጊዜ ሴትዮዋ መጉላላት ደርሶባታል ።

የ80 ዓመቱ ሽማግሌ ሺምበርም ፣ በመዠመሪያው ወቅት ከዐፄ ዮሐንስ ጋር ሲኖር ንጉሡ በርሱ አማካይነት ከጀርመን ንጉሠ ነገሥት

ጋር እወዳጃለሁ በሚል ተስፋ በደህና ይዘውት ነበር ። በመካከሉ በአማቹ በካሳ አባ ጐልጃና ይልቁንም በልጁ በሶፍያ መጉላላት ተጣልተው ሳለ ፤ የፈረንሳዩ ቆንሲል ደሳርዜክ ለሁለቱም ወዳጅነት ስለ ተሰማው ፤ አስታርቋቸው ዐፄ ዮሐንስም በሺምበር አማካይነት ከጀርመን ንጉሠ ነገሥት ጋር እየተጻጻፉ ወዳጅነትን በቀጠሉበት ሰዓት እንደ ቆንሲል ዐይነት ሆኖ ይሠራ ነበር ።

አሁን በታሪክ የኢትዮጵያ አውራጃ የሆነው በጎስና አካባቢው በግብጽ ጦር በተያዘበትና ዐፄ ዮሐንስና ከዲቭ ኢስማኤል በጠብ ላይ ባሉበት ሰዓት ስለ ቦጎስ አያያዝ ለመንግሥቱ ሁኔታውን በራፖር መልክ ሲገልጥ ሺምበር እንደዚህ ብሏል ።

"... አሁን ግብጽ ... ባለፈው ዘመን የኢትዮጵያ ወረዳዎች የነበሩትን ቦጎስን ፤ ሐልሐልን ስለያዘ . . . ነገሩ ከፍ ያለ ክርክር አብቅቷል ። ዮሐንስ የፈረንሳይ ፤ የጀርመን ፤ የእንግሊዝና የመስኮብ መንግሥታት እንዲገላግሉት ጠይቋል ። እነዚህ ወረዳዎች ከ2 እስከ 3 መቶ ዓመታት ድረስ እንደዚሁ ችላ ተብለው በራሳቸው ሼኮች እየተመሩ ለማንም ንጉሥ ሳይገብሩ ይኖሩ ነበር ። የቦጐስም ነዋሪ ሕዝብ ግማሹ እስላም ስለሆነ ፤ ከሐበሾቹ በኩል ዐልፎ ዐልፎ ዘረፋ ይደርስበት ነበር ። በሌላ በኩል ደግሞ ፤ በግብጾችና በቱርኮቹ የሚደገፉት የሐባብ ባርካ ነገዶች ያጠቁዋቸው ነበር ።

አሁን ዋናው ፍሬ ነገር ፤ እነዚህ የቦጐስ ወረዳዎች የማን ናቸው ለሚለው ጥያቄ ፤ የጥንት የአበሻ ግዛት መሆናቸው ባይካድም ፤ ከ8ና ከ10 ዓመታት በፊት ደጃች ኃይሉ አባሐባል የሚባለው የሐማሴን ባላባት ባፄ ቴዎድሮስ ላይ ስለ ሸፈተና የቃል ኪዳን ጓደኛ ስለ ፈለገ፣ ቦጐስንና ሐልሐልን በጽሑፍ አድርጎ ለግብጽ ገዥ ለቆለታል ።

ጉዳዩ ብዙ አከራካሪ ነገር ያለበት ነው . . . ነገር ግን ምንም እንኳን ያበሻን መሬት መቀነሱን ብጠላው በእስላሞች መያዙንም ባልፈቅደው ፤ ወረዳው አሁን በግብጽ እንደ ተያዘ መርጋቱን እወዳለሁ ። ምክንያቱም ቦጐስ በግብጽ ይዞታ ውስጥ ሲሆን ፤ በዚያ የሚኖሩ የውጭ አገር ሰዎች ሁሉ ሰላም ያገኛሉ ። በነርሱም አማካይነት ያበሻ ክርስቲያኖች ሊጠቀሙ ይችላሉ ። የግብጽም አያያዝ በአውሮፓ ኃያላን ቁጥጥር ሥር ቢሆን መልካም ነው . . ."[1]

---

1 J. de Coursac, Le regne de Yohannes pp. 143—145.



በዚህ ዐይነት ፤ የኢስማኤል መንግሥት በፕሮፓጋንዳና በፖለቲካ እየተደገፈ ከምጥዋ ዐልፎ ቦጐስን ፤ በሰሜን ምዕራብ በኩል መተማን ዐልፎ ቋራን (ያፄ ቴዎድሮስን የትውልድ አገር) ያዘ ። ከያዛቸው ወረዳዎች ግብር ሲቀበል በወታደር ኃይል በቶሎ የተቋቋመው አልነበረም ። ከዐፄ ዮሐንስ የተጣሉት የክርስቲያን መኳንንትም ወደ እሱ ሲገቡለት ፤ የወሎ ባላባቶች ፤ የቦጎስ ፤ የመንሳ ፤ የሐባብ የነገድ ባላባቶች ፤ በተለይ የእስልምና ሃይማኖት የያዙት ለጊዜው ስለ ተባበሩለትና በሰላም መገበር ስለ ዠመሩ ፤ በእውነትም ለወደፊት ዐፄ ዮሐንስን አሸንፎ ፤ ምኒልክንም ቢቻል በገጸ በረከት ስጦታ አባብሎ ባይቻል የኃይሉን ሥራ አስከትሎ የግዛት ሥልጣኑን በሰፊው ለመዘርጋት ፤ በሰሜናዊ ምዕራብ ኢትዮጵያ ያለውን ሁሉ የወርቅ ማዕድን እጅ ለማድረግ ፤ በተለይ ደግሞ ለረጅም ዘመናት የግብጽ መሪዎች የሚያልሙትን የአባይን ምንጭ ይዞ በቁጥጥር ሥር የማድረጉ ጉዳይ በቀላሉ የሚፈጸም መሰለው ። ይኸን የመሰለውን ወረራ እያዘጋጀ ባንድ ወገን ደግሞ ለማዘናጋት ወዳጅነትና ሰላም ፈላጊነቱን የሚገልጽ ደብዳቤ ለዐፄ ዮሐንስ ይጽፍ ነበር ።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የቦጎስና የአካባቢው ወረዳ ኢትዮጵያዊነት

በገርምግራፊው ላይ እንደሚታየው፥ ይህ ዐፄ ዮሐንስና ግብጾች የሚጣሉበት የቦጎስና የአካባቢው ወረዳ አሁን ኤርትራ ተብሎ በሚጠራው ውስጥ የሚገኝ የኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍለ ሀገር ነው። በውስጡ የሚገኘው ነገድ ዘሩ፥ ቋንቋው፥ ሥያሜው ልዩ ልዩ ነው። የገርምግራፊያ አቀማመጡ በምጥዋ ወደብ አካባቢ ያለው ሰምሀር ይባላል። ከሰምሀር በስተደቡብ አርኪቆና አዱሊስ፥ ዙላ፥ የአሳሆርታ ነገድ፥ በሰሜን በኩል ቦሂል (ሳሂል)፥ ከሰምሀር በስተ ምዕራብ መንሳ፥ ከመንሳ ምዕራብ እስከ ባርካ ወንዝ ድረስ ከረንን ጨምሮ የቦጕስ ወረዳ ይገኛል። ከቦጕስ በስተምዕራብ ቀዮች ማርያም፥ ከነርሱ ቀጥሎ ጥቁሮች ማርያም የተባሉ የቤኒ አሚር ወረዳዎች ከሱዳን ጋር ይጋጠማሉ። በዚህም ክፍል ሉቢያ፥ አውዳብ፥ አድሐሰን፥ አድ ቀይህ ዤረባ፥ አድ ቢያል የሚባሉት ቤተ ሰቦች ከሌሎች ፋንጂ፥ ሹክሪያ፥ ባሪያ . . . ከሚባሉት ጋር እየተዋለዱም፥ እየተደባለቁም ይኖራሉ።

ከምጥዋ ሰሜናዊው ክፍል የቀይ ባሕርን ጠረፍ ተከትሎ ሾሂል ሲገኝ፥ ከርሱ ምዕራብ የሚገኘው ሰፋ ያለው ወረዳ ሐባብ ይባላል። ከሐባብ ምዕራብ አድ ተክሌ ከቀዮቹ ማርያም ጋር ይዋሰናል።

እነዚህ ሁሉ ወረዳዎች፥ የእስልምና ሃይማኖት በሰሜን ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት በትክክል አብዛኞቹ ነዋሪዎች ክርስቲያኖችና የአክሱም መንግሥት ትክክለኛ ክፍለ ሀገር እንደ ነበሩ አይጠረጠርም። የኛ ግዕዝኛ ጽሑፍ በጠቅላላ ‘የበለው ከለው ነገድ’ ይላቸዋል። የአክሱም መንግሥት፥ እንኳን እነዚህን ከቅርብ ያሉትን የራሱን ንብረቶች ይቅርና በምሥራቅ ቀይ ባሕርን በመርከብ ተሻግሮ እስከ ደቡብ ዐረብ፥ በምዕራብ የኑብያን (የዛሬውን ሱዳን) አገር ሁሉ በቁጥጥሩ ሥር አስብገቶ እንደ ነበር ሰነዱ ሁሉ ይመሰክራል።

የአክሱም መንግሥት ወድቆ በርሱ እግር የተተኩት ነገደ ዛጉዬ (ከ11ኛው—13ኛው መቶ ዓመት) ሲሆኑ፥ ከዛጉዬ ሥርወ መንግሥት ቀጥሎ የመንግሥት ሥልጣን ከይኩኖ አምላክ ጀምሮ የተረከበው ራሱን፥ “ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት” ብሎ የሚጠራው የአማራ

መንግሥት በሸዋ የረር ፣ ደብረ ብርሃን ፣ ቦካን ነበር ። የመንግሥቱ አቀማመጥ ምንም ከምጥዋና ከአካባቢው ርቆ ወደ ማኸል አገር ቢዛወር ፣ ካባቶቻቸው ከአክሱም የወረሱ ትን መንግሥት በመቀጠል ባሕር ነጋሽ ወይም መልአከ ባሕር ወይም ባሕር ነጋሽ እያሉ እየሾሙ በመላክ እነዚህን የኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍለ አገሮች ተሿሚዎቹ ያስተዳድሩአቸው ነበር ። ስለሆነም የአዱሊስና የዙላ የወደብ ታሪካውያን ከተሞች የኢትዮጵያ አንጡራ ገንዘብ እንደ ነበሩ አከራካሪ አይደለም ።

ዳሩ ግን ፣ ለአክሱም መንግሥትና የርሱም የቃል ኪዳን አንጋፋ ጓደኛ ለነበረው ለቁስጥንጥንያ የቄሣር (ባዛንቲን) መንግሥት ውድቀት ምክንያት የሆነው ፣ የዐረቦች መነሣትና በመካከለኛው ምሥራቅ ፣ በሰሜን አፍሪካ በመስፋፋታቸው ነበር ። በዚሁ ጊዜ እነዚህ ሕዝቦች ባህላቸውን ፣ ቋንቋቸውን ፣ ይልቁንም ሃይማኖታቸውን በውዴታም በሰይፍም በገቡበት አገር ሁሉ አስፋፉ ። የዐረብ ተወላጅ ወይም የነርሱን ሃይማኖት ከልቡ የተቀበለው አንዳንድ የነገድ ወገን በንግድም ፣ በመምህርነትም እላይ ወደ ዘረዘርናቸው የኢትዮጵያ ነገዶች እየገባ ፣ የእስልምና ሃይማኖትን ማስተማርና ከአገር ተወላጅ ሴቶችም ጋር እየተጋባ መራባት ዠመረ ። ቢሆንም ፣ ከ16ኛው መቶ ዓመት በፊት በሡልጣን ወይም በከሊፋ ስም የሚጠራ የዐረብ መሪ ሌላውን ሁሉ እየወረረ ግብጽን ጭምር ሲያንበረክክ ፣ ወደ ኢትዮጵያ ዘምቶ እነዚህን ወረዳዎች እንኳን ለማስተዳደር አልሞከረም ።

የዚህም ምክንያት ፣ ነቢዩ መሐመድ በ7ኛው መቶ ዓመት ላይ በብዙ በተለያዩ ጣኦታት ያመልኩ ከነበሩት ከሜካ ባላባቶች ጋር "አንዱን ፈጣሪ አምላክ አላህን አምልኩ እንጂ ፣ በሰው እጅ በተሠራ ጣኦት አታምልኩ" በማለት በተጣላና በተዋጋ ጊዜ ተሸንፎ ወደ መዲና ለመሸሽ ሲሰናዳ ፣ (614 ዓ. ም.) ተከታዮቹንና ዘመዶቹን ሁሉ ከርሱ ጋር ይዞ ለመሔድ ስለ ቸገረው ፣ ያጎቱን ልጅ ጅፋርንና ወገኖቹን "ወደ አበሻ አገር ሽሹ ፣ በዚያ እል ነጋሽ የሚባል የኢትዮጵያ ንጉሥ ፍርዱ የቀና በሰላም ሕዝቡን የሚያስተዳድር. . .አለና ወደርሱ ሒዱ" ብሏቸው 73 ወንዶችና 13 ሴቶች መጥተው በእርግጥም በመልካም መስተንግዶ በኢትዮጵያ ኖሩ ። መሐመድ በሥልጣኑ በተረጋጋበት ጊዜ ወዳገራቸው ሲመለሱ ፣ ለዚሁ ለዘመዶቹ ለተደረገው ውለታ ወደፊት የሚነሡትን የእስላም ባለሥልጣኖች "ሐበሻን አትንኩ" ብሎ ስለ አዘዘ ፣ ተከታዮቹ ሌላውን የመካከለኛ ምሥራቅ አገር በወረራ ሲያጠቁ ወደ ኢትዮጵያ አልመጡም ።[1]

1 R. Basset (ed. et trans.) Histoire de la Conquete de l'Abyssinia, 2! Vol., Paris, (1897—1901) pp. 416—449.



ምንም በኢትዮጵያ ፣ የዐረብ ጦር ባይዘምት የእስላም መምህራን "ሼኮች" በየጊዜው ከዐረብ አገር ወደ ኢትዮጵያ በየወደቡ እየገቡ ከዚያም ወደ መኻል አገር ሠርገው በመስፋፋት በማስተማርም ፣ በጋብቻም ብዙ ሰዎችን ፣ በቀን ብዛት ፣ ከክርስትና ወደ እስልምና መለሱ ። በዚህ ምክንያት ዛሬ በሐባብ ፣ በቦጎስ ፣ በመንሳ የሚገኙት የእስላም ባላባቶች ከላይ ዘራቸውን ሲቆጥሩ አያት ቅድም አያቶቻቸው የክርስቲያን ሹማምንት እንደ ነበሩ ይታወቃል ። እነርሱም በባሕር ነጋሹ ውስጥ "ናይብ ፣ ከንቲባ. . ." እየተባሉ በሸዋ ወይም በጐንደር በተቀመጠው ኢትዮጵያዊ ንጉሠ ነገሥት ሲሾሙ ፣ ሲሸለሙ 'አሜን' ብለው ለንጉሠ ነገሥቱ ወይም እርሱ ለሾመው ባሕር ነጋሽ ሲገብሩ ፣ ሲታዘዙ ኖረዋል ።

ለምሳሌ ፣ የሐባብ ባላባቶች ዘራቸውን እስከ ዐሥር ትውልድ ሲቆጥሩ ፣ ከላይ ዋናው የነገድ አባት ስሙ ገብረ ክርስቶስ (የአድገዲ ልጅ) ነው ። ገብረ ክርስቶስ ፣ ጊዮርጊስ አቢብን ይወልዳል ። አቢብ ወይም ኤቢብ ማፍለስን ፣ ማፍለስ ኤብቲስን ፣ ኤብቲስ ኤዛስን ፣ ኤዛስ ናአድን ፣ ናአድ ፈቃድን ፣ ፈቃድ ሐዳድን ፣ ሐዳድ ሐሰንን ፣ ሐሰን ሐሚድን ፣ ሐሚድ መሐመድን ይወልዳል ። የስሙ አጠራር እንደሚያመለክተው እስልምናን ለመዠመሪያ ጊዜ የተቀበለው ሰባተኛው ትውልድ ፈቃድ ነው ። ቢሆንም ፣ እርሱና ልጁ ሐዳድ እስላማዊ ስም ሳይቀበሉ የልጅ ልጁ ዘጠነኛው ሐሰን ፣ የሐሰን ልጅ ሐሚድና የሐሚድ ልጅ መሐመድ የስማቸው አጠራር በትክክል የእስላም ስም ሆኖ ይገኛል ።

እነዚህንም ከክርስቲያንነት ወደ እስላምነት ያዞሩዋቸው ፣ የሼክ ዐሊና የሼክ ዐሊ ተወላጆች የሆኑት ከዐረብ አገር መጥተው በእምበረሚ የሠፈሩት "አድ ሼክ — የሼክ ቤት" የተባሉት መምህራን ነበሩ ። ከነዚህ መካከል የሼክ ዐሊ ልጅ ፣ ሼክ መሐመድ በጣም የተከበረ ነበር ። በጊዜው በሠራው የጽድቅና የትሩፋት ተግባር ፣ በባሌ እንዳለው ፣ እንደ ሼክ ሁሴን ፣ በእምበረም በሚገኘው መቃብሩ ላይ ስብሰባ እየተደረገ በታላቅ በዓል በያመቱ ይከበራል ። የርሱም የጻድቅነት ስም ከታች ከቆላው ከምጥዋ ፣ ከሰሐጢ ፣ ከዶጋሊ ዠምሮ እስከ ከረን ፣ እስከ ሱዳን ወሰን ድረስ ፉታወቀና የተከበረ ነው ።

ቢሆንም ፣ ከላይ ከክርስቲያኒነታቸው ዘመን ጀምሮ እነዚህ የሐባብ ባለባቶች ብዙ ጊዜ ቦጐስንም እስከ ባርካ ወንዝ ድረስ እየጠቀለሉ ሲያስተዳድሩ ፣ ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ወይም ከባሕር ነጋሽ የሚሰጣቸው የማዕረግ ስም እንደ ሐማሴኑ ባላባት ከንቲባነት ነበር ። ከንቲባ ሐሰን በግብጾች ወረራ ጊዜ ከሙንሲንጀር ጋር ተባብሮ እንደቆየ የርሱ ልጅ ከንቲባ ሐሚድና የሐሚድ ልጅ ከንቲባ መሐመድ ከግብጽ በኋላ ኢጣልያኖች ምድሪ ባሕሪን በወረሩበት ጊዜ ነበሩ ።

ስለዚህ ፡ የሐባብና የቦጎስ ተወላጆች እንደ ሐማሴን ፡ እንደ ሠራዬ ፡ እንደ አከለ ጉዛይ በጠቅላላው አጋዕዝያን እየተባሉ ቋንቋቸው ትግረ ሲሆን ፡ ፍጹም የኢትዮጵያ ክርስቲያን ሆነው ሳለ ፡ ከመስለም ያደረሳቸው የመሬታቸው አቀማመጥና በቱርክና በግብጾች ተጽዕኖ ፡ እንደ ዚሁም ከነርሱ ቀደም ብለው እስልምናን በተቀበሉት በምጥዋና በደሀኖ ባላባቶች (በናይቦቹ) አስገዳጅነት መሆኑ በየመጽሐፉ ተጠቅሶ ይገኛል ።[1]

ሃይማኖታቸው እስላም ቢሆንም ፡ የቱርክ አገዛዝ ቀለል ባለ ጊዜ ከመካከላቸው ለንጉሠ ነገሥቱ ወይም ለእንደራሴው ታማኝ እየሆኑ በንግድና በመልእክት ፡ በአስተርጓሚነት የኢትዮጵያን መንግሥት የሚያገለግሉ ነበሩባቸው ። አንዳንድ የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታና ጥቅም እያስገደዳቸው ወደ ቱርክና ወደ ግብጽ ቢጠጉም ፡ ሊያስደንቅ አይችልም ። እንኳን እነርሱ በሃይማኖት የሚመሳሰሉት ቀርተው የክርስቲያኖቹ መኳንንት እንኳን ፡ ከወዲህ ከክርስቲያኖቹ ነገሥታትና መሳፍንት ሹመትና ምቾት ሲያጡ ወይም ሲጣሉ ፡ ወደ ቱርኮችና ወደ ግብጾች እየተጠጉ ለጠላት መሣሪያ ይሆኑ እንደ ነበር ግልጽ ነው ።

እላይ እንዳልነው ፡ ከዐረቦች በኋላ በተራው ተነሥቶ ክርስቲያኑን የቆስጥንጥንያን መንግሥት የጣለው የቱርክ መንግሥት 15ኛው መቶ ዓመት ዝምሮ በቁስጥንጥንያና በዐረቦች ግዛት እግር ተተክቶ መካከለኛው ምሥራቅን ፡ ሰሜን አፍሪካን ያዘ ። በኋላም በ1549 ዓ. ም. ምጥዋን ያዘ ። የእስላም ነክነት ያላቸው ሁሉ ወደ እስልምና ፈጽመው በገቡበትና ከቱርክ ጋር በተባበሩበት ሰዓት ከ1521 ዓ. ም. ዝምሮ እስከ 1535 ዓ. ም. ድረስ የግራኝ አህመድ ወረራ ተከተለ ። ቀድሞ በክርስቲያኑ መንግሥት ተጠቅተናል የሚሉት አጋማሾቹ የቦጎስና የሐባብ ፡ የበለው እስላማውያን ነገዶች ከግራኝ ጋር ስለ ተባበሩ ፡ የክርስቲያኑ መንግሥት ታላቅ ውድቀት ደረሰበት ። እንደሚታወቀው ፡ በፖርቱጋሎች እርዳታ ጭምር የክርስቲያኑ መንግሥት ተመልሶ ቢቆምም ፡ ቱርክ መጥቶ ምጥዋንና አካባቢውን ያዘ ። በአቅራቢያ የሚገኙት የነዚሁ የቦጐስ ፡ የሐባብ ፡ የመንሳ ፡ በወዲህም በሐልሐል ፡ በአሳሆርታ ፡ በጥልጣል ፡ በአዘቦ በኩልና ታቹንም በሐረርጌ በኩል የሚገኙት ሁሉ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ከኢትዮጵያ መንግሥት ቁጥጥር ሥር እየወጡ በየራሳቸው ባላባት መተዳደር ፡ በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ ማመጥ የዘወትር ልማዳቸው ሆነ ።

1 Perini, Abyssinaia ed Eritrea, pp. 283—290.



ሌላው የዘወትር ልማድ የሆነው ፡ በራሳቸው ባላባት በነጻ ለመተዳደር የበቃ ኃይል ስለ አልነበራቸው ፡ በየአጋጣሚው ጉልበቱ አይሎ በላያቸው ላይ ለተጫነው ለማናቸውም ወገን ፡ ይኸውም ማለት ለቱርክም ፡ ለኢትዮጵያዊው ወገንም እየገበሩ መቀመጥ የመረጡበት ጊዜ ሰፋ ያለ ነበር ። በሁለት ተፋላሚ መንግሥታት መካከል የሚገኝ ሕዝብ ዕድሉ ይኸን የመሰለ ነው ። በዚሁ ምክንያት ፡ የጐንደር መንግሥት በርስ በርስ ጦርነት ሲዳከም ፡ በዚያ አንጻር የቱርኩ ኃይል እየበረታ ሲሔድ ፡ በዚሁ ላይ የሃይማኖቱ ጉዳይ ስለሚያቀራርባቸው ከቱርክ ስለ ተባበሩ ፡ በምጥዋና በደሆኖ ይቀመጥ የነበረው ባሕር ነጋሽ ከቆላው ከባሕር ወደብ ወደ ደጋው ወጥቶ መቀመጫውን በደባሩዋ (ሠራዬ) ለማድረግ ግዴታው ሆነ ። ከዚያ በፊት ግን ፡ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የሚሾመው ባሕር ነጋሽ ከመረብ ወዲያ ባለው ግዛቱ ተስፋፍቶ ፡ ተዝናንቶ በተቀመጠበት ዘመን እንደ ጊዜው ሁኔታ በክረምት ወቅት በምጥዋ እየተቀመጠ ፡ የፀሐዩ ሐሩር በሚበረታበት ሰዓት ወደ ደጋው ወደ ሠራዬ እየወጣ በከተማው በደባርዋ ይቀመጥ ነበር ።

በዚህም የሚቀመጠው ባሕር ነጋሽ ፡ ሲመቸው መረብ— በለሳ ሙና —መልስ የሐማሴንና የሠራዬን ፡ የአካለ ጉዛይንና የአካባቢውን አገር እያስገበረ ሲኖር ፡ ባንዳንድ ምክንያት ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ጋር ቅያሜ ሲገጥመው ወደ ቱርኮቹ እየተጠጋ ፡ አገሩን እየከዳ ለጠላት መሣሪያ በሆነበት ሰዓት እነዐፄ ገላውዴዎስ ፡ እነ ዐፄ ሠርፀ ድንግል እስከ ዳባርዋ ድረስ እየዘመቱ ከቱርኮች ጋር መዋጋታቸውና በዚያ አካባቢ ያለውን የኢትዮጵያን ግዛት ማጠናከራቸው በታሪክ የታወቀ ነው ።

በመካከሉም ፡ የኢትዮጵያ የነገሥታቱ ሥልጣን ተዋድቆ ዘመነ መሳፍንት በተተካበት ዘመን ፡ የቱርክም ኃይል ወደሌላው በጣም ወደ ሰፋው የመካከለኛው ምሥራቅ የባልካን ግዛት እየተበተነ ከላይኛው ከቦጎስና ከመንሳ ፡ ከሐማሴንና ከአካለ ጉዛይ ወደ ቆላው እየተመለሰ በመውረድ ፡ በምጥዋ ወደብ ብቻ በሚወሰንበት ጊዜ በስሜንና በትግራይ የገነኑ የኢትዮጵያ መሳፍንት የዐድዋው ራስ ስሑል ሚካኤል ፡ የእንደርታው ራስ ወልደ ሥላሴ ፡ በቅርቡም በዐፄ ቴዎድሮስ የተሸነፉት ደጃች ውቤ ኃይለ ማርያም ይኸኙኑ በወቅቱ ምድረ ባሕሪ በመባል የታወቀውን ጠቅላላ ክፍለ ሀገር ያስገብሩት ነበር ። የነገድ አለቆቹም የቱርክን መራቅ ፡ የኢትዮጵያውያኑን ማየል ሲረዱት ፡ እላይ እንዳልነው ላየለው ወገን በሰላም እየገበሩ ይኖሩ ነበር ።

በዚህም መካከል ፡ በምጥዋ ያሉት የቱርክ ተወካዮች ከደጋው የኢትዮጵያ ክፍል ለኑሮአቸው የሚሆን እህልና የሥጋ ከብት ስለሚፈልጉ ፡

የኢትዮጵያም ነገሥታትና መሳፍንት በምጥዋ በኩል ልዩ ልዩ ሸቀጥ ፣ ልብስ ፣ የጦር መሣሪያ ከውጭ ለማግኘት ፣ ጳጳሳቸውንም ከግብጽ ለማስመጣት ስለሚፈልጉ ፣ ሁለቱ የሃይማኖትና የግዛት ጠበኞች ተዋውቀው ፣ ተቻችለው በዝምታ እየተስማሙ ፣ ብዙ ዘመን ሸቀጥ ለሸቀጥ እየተለዋወጡ በሰላም ያሳለፉበት ጊዜ ነበር ። ይህ ሁኔታ አሁን በ19ኛው መቶ ዓመት ላይ ሊደርስ የቻለው ፣ ቱርክ የሱአኪንና የምጥዋን ወደብ ለግብጽ በፊርማ ሲለቅለትና ኢስማኤል ደግሞ በፈረንጆች መካሮቹ እየተመራ የግዛት መስፋፋት አምሮት አድሮበት ከምጥዋ ወደብ እያለፈ ወደ ደጋው እየወጣ ቦጎስን ሲወርና የሐማሴንና የአካለ ጉዛይን ወረዳ ሁሉ ሲፋለም ነበር ።

ይኸም ዓላማው ፣ በገዥግናውና ባገር ወዳዱ ንጉሠ ነገሥትና በሕዝባቸው ተጋድሎ ለመከሸፍ ቻለ ። እንዲያውም የኢስማኤል ጦር በዐፄ ዮሐንስ ጦር ከተመታ ወዲህ መቅና አጥቶ በተለይም በሱዳን በመሀዲ አህመድ መነሣት ምክንያት ፣ ከየግዛቱ የመባረርና ታላቅ የኢኮኖሚ ውድቀት እንደ ገጠመው ወደፊት በየምዕራፉ እንመለከታለን ።



# ምዕራፍ ዐሥር

## ከጦርነት በፊት የዐፄ ዮሐንስ ሰላማዊ ስሞታ ለአውሮፓ ኃያላን

የክርስቲያን ደሴት ስትባል የኖረችው ኢትዮጵያ ፣ በዐረቦችና እስላም ነክ በሆኑ ነገዶች የተከበበች አገር እንደ መሆኗ መጠን ፣ ቱርክ ራሱ ወይም በርሱ የተደገፈ የእስላም መንግሥት ወይም ድርጅት ባስፈራራት ቁጥር ፣ እንደ ዛሬው አቤት የሚባልበት ወይም የሚከሰስበት የዓለም ማኅበር ስለ አልነበረ እርዳታ የምትጠይቀው ፣ ስሞታዋንና አቤቱታዋን የምታሰማው ፣ ለክርስቲያኖቹ ለአውሮፓ ኃያላን ነበር ። በመካከለኛው ዘመን (ከ14ኛው — 16ኛው መቶ ዓመታት) የክርስቲያን አለኝታዎችና አቤቱታ ሰሚዎች ፣ የአካባቢው ገናናዎችና ሰፋ ያለ የቅኝ ግዛት የነበራቸው የፖርቱጋልና የእስፓኝ መንግሥት ነበሩ ።

ከግራኝ ወረራ አስቀድሞ ፣ በዋዜማው ንግሥት ዕሌኒና ዐፄ ልብነ ድንግል ደብዳቤዎችን ለፖርቱጋል ነገሥታት ለአማኑኤልና ለልጁ ለዮሐንስ ፣ ለሮማው ሊቀ ጳጳስ ለቀሊምንጦስ ሰባተኛ ጽፈዋል ። የግራኝ ወረራ ከተፈጸመ በኋላ ፣ ዐፄ ገላውዴዎስ ደብዳቤዎችን ለሮማ ሊቀ ጳጳስ ለጳውሎስ ሦስተኛና ለፖርቱጋሉ ንጉሥ ለዮሐንስ ልከዋል ። በዚሁም መሠረት ፣ የፖርቱጋሎቹ እርዳታ ደርሶ ግራኝ አህመድ እንደ ወደቀና ማዕከላዊ መንግሥት ተመልሶ እንደ ቆመ በየታሪኩ መጽሐፍ ላይ ተመዝግቦ ይገኛል ።[1]

ግራኝ አህመድ ከወደቀና ማዕከላዊው መንግሥት ከተቋቋመ በኋላ ፣ በ1549 ዓ. ም. በምጥዋ የተሸነቀረው የቱርክ መንግሥት ሹምና ወታደር ፣ ዐልፎ ዐልፎ ጊዜ ሲያመቸው ወይም የኢትዮጵያው ባሕር ነጋሽ ከወዲህ ከንጉሠ ነገሥቱ ሲጣላና ወደርሱ ሲደረብለት ፣ ከቆላው ከምጥዋ ወደ ነፋሻው ወደ ሐማሴን እየወጣ ባጠቃ ቁጥር የኢትዮጵያ ነገሥታት እነ ዐፄ ሚናስ ፣ እነ ዐፄ ሠርፀ ድንግል ፣ እነ ዐፄ ሱስንዮስ በውጊያ መጋተራቸውን እየቀጠሉ እርዳታ ይጠይቁ

1 የግራኝ አህመድ ወረራ ፣ (አ.አ. ፣ ተ.ጸ.መ. 1966) ገጽ 17-26 ፣ 109-131 ።

የነበሩት ፤ በገናናነት ፖርቱጋልን ለተካው ለእስፓኙ ንጉሥ ነበር ። በ17ኛው መጨረሻና በ18ኛው መቶ ዓመት የፖርቱጋልና የእስፓኝ ገናናነት እየቀዘቀዘ ሲሔድ ፤ በነርሱ ምትክ እንግሊዞቹና ፈረንሳዮቹ በርትተው ተገኙ ።

በኢትዮጵያ ያሉት የውጭ አገር ሰዎች በተለይ የወንጌል ካቶሊካውያን መልክተኞች ፤ እምነታቸው ካቶሊክ የሆነው የኤስፓኙም የፈረንሳዩም ነገሥታት የሮሚው ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት የመንፈስ ልጆች ስለሆኑ ፤ በመንፈሳዊውም ሆነ ፤ በሥጋዊውም ጉዳይ ለነርሱ ጭምር መጸፍ እንደሚኖርባቸው ለኢትዮጵያ ነገሥታት ይመከሩ ነበር ። የካቶሊክ እምነት ተከታዮች እንዲሆኑም ይገፋፉአቸው ነበር ።

ይህ ደግሞ ፤ ለኢትዮጵያ ከእስክንድርያ ከማርቆስ መንበር ፈልቆ የተቀበለችውንና አጥብቃ የያዘችውን የተዋሕዶ ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖት ለቃ እርዳታ ለማግኘት ስትል ካቶሊክነትን ለማቀፍ የማይዋጥ መራራ ጉርሻ ሆነባት ። ከዚህም የተነሣ በጠቅላላው ጳጳሱም ፤ የአውሮፓ ኃያላንም በተለይ ካቶሊክ የሆኑት ነጋሥያን ለኢትዮጵያ የሚያደርጉት እርዳታ ብዙ ጊዜ ጕዶሎ ነበር ። በዚህም ሁኔታ በመጠቀም የቱርክ መንግሥትና በርሱ ጥገኝነት የሚገኙት የግብፅ መሪዎች የዘቢድ ፓሻዎች ሁሉ ኢትዮጵያን ለማጥቃት ይነሡ ነበር ። የእንግሊዝ መንግሥት ካቶሊክነትን ትቶ አንግሊካን ከሆነ ወዲህ በርሱ ጥላ ሥር በኢትዮጵያ የተሠራጩትን ወንጌላውያን የአማኝ ቁጥር ለማብዛት ከመጣጣር በቀር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፕሮቴስታንት እንድትሆን አይጣጣሩም ። ከካቶሊኮቹ ጋር ባላቸው ፍልሚያም አንዳንድ ጊዜ ለኢትዮጵያ ነገሥታት ሲረዱ ይገኛሉ ። ከመቅደላው ጠብ በፊት እንግሊዞችና ጀርመኖቹ ደጃች ንጉሤን በደገፉት በፈረንሳዮቹ አንጻር ቴዎድሮስን መደገፋቸው ይታወሳል ።

ቢሆንም ፤ የግብፅ የማምሉክ ባለሥልጣኖች ባስፈራሩት ቁጥር የኢትዮጵያ ነገሥታት ፤ "የአባይን ወንዝ እንዘጋባችኋለን" የሚል ማስፈራሪያ ሲወረውሩ ፤ ከግብጽም በኩል "እኛም የሃይማኖታችሁን የበላይ አለቃ አስረን ፍዳውን እናሳየዋለን ፤ ቤተ ክርስቲያናችሁን የሚጠብቀው ጳጳስም አይመጣላችሁም" የሚለው ዛቻ ሲደርስና ሲያወዛግብ ቆይቶአል ። በመጨረሻም በቅርቡ ፤ ባዬ ቴዎድሮስ አነሣሥ ዋዜማ ላይ የኢትዮጵያን ሰሜናዊ ክፍል በመጠቅለል ፤ ለግብጽ ሕይወት የሚሰጠውን አባይን እጁ ለማግባት መሐመድ ዐሊ ቢጣጣርም አሳቡ ሳይሳካለት ቀርቷል ።

አሁንም ከዲቭ ኢስማኤል የአባቶቹን የነመሐመድ ዐሊን ምኞት ፈጽሞ አልተወም ። መሠረታዊ አሳቡን ከአባቶቹ ለየት አድርጎ ከቱርክ



ራቅ ወዳሉት አውሮፓውያን ጠጋ አለ ። ለነርሱ የወዳጅነት ስሜት በማሳየትና የህብት ጥቅም ከማቅረብ ጋር በፈረንጀቹ ለመወደድ ሲል የአውሮፓን ሥልጣኔ ባገሩ የማስገባት መልክ እያሳየ ፤ ያዬ ዮሐንስን ኢትዮጵያ ዘመድ አሳጥቶ ፤ ኢትዮጵያን እንደልብ ለማጥቃት ነበረ ዓላማው ። ለዚህም ዓላማው የሚተባበሩ የእንግሊዝ ፤ የፈረንሳይ ፤ የኢጣሊያና የጀርመን ተወላጆችን እነ ሳሙኤል ቤከርን ፤ እነሻርል ጆርጅ ጕርዶንን ፤ እነ ሙንሲንጀርን ፤ እነ ሮሞሎ ጀሲን እየመለመለ ባለሟል በማድረግ ፤ የፓሻነት ማዕርግ እየሰጠ ፤ በርሱ ስም በወታደርነት በያዛቸው አገሮች ላይ የአገረ ገዥነት ሹመት እየሰጠ ፤ ወረራውን በያለበት በሱዳንና በዑጋንዳ አዋከቦ ተያያዘው ።

በኢትዮጵያ ባለፈው ምዕራፍ እንደ አመለከትነው፡በሰሜናዊ ምሥራቅ በኩል ግብጾች በሙንሲንጀር ፓሻ መሪነት ፡ ከምጥዋ ዐልፎ ቦጎስን ሐባብን 1863 ዓ.ም. ወረሩ።በሰሜናዊ ምዕራብ በኩል በሮሞሎ ጂሲ (ጣሊያኑ) የበላይነት ፤ በኤደም ፓሻ የሚታዘዘው ጦር ቋራን ይዞ ወደ ቤገምድር ሲያመራ ፤ ሙንሲንጀር ፓሻ ደግሞ በምሥራቅ በኩል በ1867 ዓ.ም. ዘይላን ሐረርጌን ያዘ ። ዐፄ ዮሐንስ ፤ በዚህ ወቅት ወዲያና ወዲህ እያሉ ንጉሠ ነገሥታዊ ሥልጣናቸውን የሚያጠብቁበት ጊዜ ነበር ። ግብጾች የኢትዮጵያን ክፍለ ሀገራት በወረሩበት ሰዓት በ1864 ዓ. ም. ላይ ፤ "የራያና የአዘቦኦሮሞዎች በአለቆቻቸው በአብደላ አባ ሾባና አባ ቤራ እየተመሩ በየአቅራቢያቸው የሚገኘውን ቤተ ክርስቲያን አቃጠሉ ። ክርስቲያኑንና ነጋዴውን በመንገድ ላይ እየጠበቁ በመግደል ሰለቡት" የሚል ወሬ በሰሙ ጊዜ ፤ ወደ ራያና አዘቦ ዘምተው አጥፊዎቹን በመቅጣት ታማኝ ሆነው ለገቡላቸው ሹመትና ሽልማት የሚሰጡበት ጊዜ ነበር ።[1]

ከራያና ከአዘቦ ዘመቻ ተመልሰው ወደ ከተማቸው ወደ ዐድዋ ሲገቡ የግብጾቹን ወረራ በትክክል ቢሰሙትም ፤ ገና ባልጸናውና ባዲሱ መንግሥታቸው ፊት የተደቀነ ብዙ አስቸኳይ የአስተዳደር ፤ የሃይማኖት ፤ ያላመኑትን መሳፍንት የማሳመን ጉዳይ ስለነበረ ፤ በቶሎ ወራሪዎችን በጦር ኃይል ገጥመው ለማባረር አልሞከሩም ።

እላይ እንዳልነው ፤ የግብጾችም ጦር ከደንበኛ ትጥቅ ጋር በበላይ የሚመራው በሠለጠኑ አውሮፓውያን መኰንኖች ስለነበረ ፤ ጉዳዩ አስቀድሞ ጥናትና ትዕግሥት የሚያስፈልገው ሆኖ አግኝተውታል ።

1 Bairu Tafla, (ed.) Chronicle Emperor Yohannes IV (1872—1889) F. 132—133.

ይልቁንም አሁን ለኢስማኤል ጉልበት የሆኑት ፣ እርሱን አሽከር ሆነው የሚያገለግሉት ፈረንጆች ጌቶች ፣ የአውሮፓ ኃያላን መሆናቸውን በማወቅ ፣ በክርስትና ሃይማኖት ሳቢያ የርሳቸውም አለኝታዎች እነዚሁ የአውሮፓ መንግሥታት ስለነበሩ ፣ ከዚህም ጋር ከራሱ ከኢስማኤል ጋር በፊተኛው ጊዜ ደብዳቤም ፣ ገጸ በረከትም መለዋወጥ ዠምረው ስለነበር ወደራሱ ወደ ኢስማኤል ፣ አልገበርቲ አልሐጅ መሐመድን ልከው ፣ እንግሊዙን ዦን ሲ. ኪርክሃምን ወደ እንግሊዝ ንግሥትና ወደ ፈረንሳይ መሪ ለመላክ ወሰኑ ። ለሌሎችም ለጀርመን ፣ ለኑምሳ (አውስትሪያ) ፣ ለመስኮብ የስሞታ ደብዳቤ አዘጋጁ ።

ለአውሮፓ ኃያላን ለመጻፍ ያሰቡበትን ምክንያት ፣ ለፈረንሳይ መልክተኛ ለአቬል ራፍረይ እንደዚህ ሲሉ ገልጠውለታል ።

> . . . የግብጽ መንግሥት በያለበት ከቦኛል . . . የአውሮፓ ክርስቲያን ነገሥታት መሣሪያ ይዘው መጥተው የኢትዮጵያን ንጉሥ ይጠብቁት አልልም. . . ነገር ግን ፣ ሐቀኞች ገላጋዮች ልከው በኔና በኢስማኤል መካከል ነገሩን በትክክል መርምረው ማንኛችን ጥፋተኛ እንደሆን ማናችን ወራሪ መሆናችንን ለይተው እንዲረዱ ነው. . .[1]

በዚህ ጉዳይ ፣ ባንድ ወገን ባለፈው ራሳቸው በነበራቸው የጠበቀ ወዳጅነት ፣ በሌላ ወገን በግብጽ መንግሥት ላይ ከሌሎቹ የበለጠ ሥልጣኑን ያሰማው የእንግሊዝ መንግሥት ስለነበረ ፣ ምንም ስለ ግብጽ ወራሪነት በደብዳቤያቸው ውስጥ ለሁሉም መሪዎች የተጠቀሰው ጉዳይ ተመሳሳይ ቢሆን ፣ ለእንግሊዝ ንግሥት ለቪክቶርያና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለሎርድ ዦርጅ ግራንቪል የጻፉት ሰፋ ይል ነበር ።

ለንግሥቲቱና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩም የጻፉዋቸው ሁለት ረዘም ያሉ ደብዳቤዎች ፣ ሁለቱም ተመሳሳይ ሆነው በንግሥቲቱ ደብዳቤ ላይ የሠፈረው ቃል ከአድራሻውና ከሰላምታው በኋላ ፣ ቀደም ብሎ በኮሎኔል ፒሪዶ እጅ የተላከላቸው ደብዳቤና በ10 ሳጥን የተከማቸ ገጸ በረከት መድረሱን ፣ ሌላው ደግሞ በሳጥን የተቀመጠው የጥይት ስጦታ ለጊዜው ኤደን መቆየቱንና በኋላ እንደሚደርሳቸው መላክተኛው ማረጋገጡን ፣ ከዚያ ወደ ፍሬ ነገሩ ገብተው ባለፈው ዘመን አህመድ ግራኝ የሚባል እስላም በኢትዮጵያ ተነሥቶ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አቃጥሎ ብዙ ክርስቲያኖችን መፍጀቱን ፣ አሁን ደግሞ

1 A. Raffray, Afrique Oriental — Abyssinie, pp. 273—274.



በግዛታቸው ውስጥ የአዘቦ ኦሮሞ ሸፍቶባቸው ያንን ለመውጋት ሔደው ፣ ቀንቷቸው ወደ ከተማቸው ወደ ዐድዋ ሲመለሱ ከኢስማኤል “ንጉሥ ነኝ ፣ ስለኔም ሆኖ እስከ መረብ ድረስ ያለውን የትግሬን ግዛት የሚያስተዳድረው ሹሜ ሙንሲንጀር ቤይ ነው” ብሎ የጻፈላቸውን ደብዳቤ ማግኘታቸውን. . . ኢስማኤል ፓሻ ምንም ሳይበድሉት በግዛቱም ውስጥ በምንም ዐይነት ሳይገቡበት አገራቸውን በመውረሩ ትክክለኛ ፍርድ ንግሥቲቱ እንዲሰጡአቸው ከመጠየቅ ጋር ያለርሳቸው ጥብቅ ወዳጅ እንደሌላቸው አሳስበዋል ።

በመጨረሻም ፣ ከአህመድ ግራኝ ወዲህ የኢትዮጵያ ነገሥታት እየተዳከሙ በሔዱ መጠን ፣ እስላሞቹ (ቱርኮች) እያየሉ መሔዳቸውን ጠቅሰው አሁንም የግብጾች አሳብ በእጃቸው ያለውን የኢትዮጵያን ግዛት በሙሉ ለመውሰድ መሆኑን አመልክተው ፣ የደብዳቤው መልስና የሚሰጧቸው ምክር የእንግሊዝ ዜጋ በሆነውና በሚያምኑት በኪርክሃም እጅ እንዲላከላቸው አሳስበዋል ። ከዚህም ጋር እግረ መንገዳቸውን በመቅደላ ጦርነት ጊዜ የሔደው የኩርዓተ ርእሱ ሥዕልና ክብረ ነገሥት መጽሐፍ እንዲላክላቸው አሳስበው ፣ የቀረው በካቶሊኮች ላይ ያላቸውን ቅራኔ የሚገልጽ ነበር ።[1]

በካይሮ ኮሎኔል ስታንቶን የተባለው በቆንሲልነት ሲያገለግል ከቆየ በኋላ ፣ በመጨረሻ መካከለኛውን ምሥራቅ ኢትዮጵያን ጭምር በሚመለከት ጉዳይ ዋና ተጠሪና ተጠያቂ ሆኖ በዋና ቆንሲልነት ስም የተቀመጠው ሰር ኢቭሊን ባሪንግ ወደፊት ሎርድ ክሮመር የሚባለው የእንግሊዝ ባለሥልጣን ነበር ።

በበኩላቸው የግብጽ ባለሥልጣኖች ከከዲቭ ኢስማኤል ዠምሮ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኑባር ፓሻ ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሸሪፍ ፓሻ ፣ የመከላከያ ሚኒስትሩ ራቲብ ፓሻ ይኑስ ይብዛ የፈረንሳይና የእንግሊዝ ቋንቋ ተናጋሪዎች ስለነበሩ ፣ ከእንግሊዝና ከፈረንሳይ ባለሥልጣኖችና መልክተኞች ጋር በቀጥታ እየተነጋገሩ በመጻጻፍ ፣ በመገባበዝ ከኢትዮጵያ በተሻለ እኳኋን ከአውሮፓ ኃያላን ጋር ግንኙነታቸውን አሳምረው ይገኙ ነበር ። ቋንቋ ለቋንቋ ተግባብቶ ይህን ዐይነቱን የመሳሰለ ግንኙነት ለማከናወን በኢትዮጵያ በኩል ጎድሎ ነበር ። እነ ማኅደረ ቃል ፣ እነመሸሻ ወርቄ ፣ እነ ምርጫ ወርቄ ፣ እነ ብሩ ወልቃኢት የውጭ አገር ቋንቋ ቢያውቁም ፣ ከማስተርጐም ምናልባትም አንዳንድ ምክር

1 Public Record Office London — Fo (95/73/12/195.)
J. de Coursac, Le Regne de Yohannes, p. 111.

ከመወርወር ዐልፈው ፣ በሥልጣን ረገድ ተሰሚነታቸው በጣም አነስተኛ ነበር ። እንዲያውም ምንም ሥልጣን አልነበራቸውም ማለት ይቻላል። ከንጉሡ በታች የነበረው ሥልጣን ይመራ የነበረው ምንም የውጪ ቋንቋን በማያውቁት ፣ የአውሮፓንም ሥልጣኔ ባልቀመሱትና ባላጣጣሙት ፣ ነገር ግን በዘርና በሥልጣን ከፍ ባሉት በንራስ አርአያ ፣ በንራስ ባርያው ፣ በንራስ አሉላ ፣ በንራስ ሐጐስ ነበር ። በነርሱም ጐን የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ንቡረ ዕድ ኢያሱ ፣ አለቃ ገብራይ ፣ አለቃ ገብረ እግዚአብሔር ፣ በኋላ የከዷቸው አለቃ ብሩ ሲሆኑ ፣ አቅዋማቸው ከታላላቁ መኳንንት ጋር የተሳሰረ በመሆኑ የቤተ መንግሥቱና የቤተ ክህነቱ ባለሥልጣኖች አስተያየታቸው የተሰያየ አልነበረም ።

ስለዚህም ፣ ለዚህ ከፍተኛ ጉዳይ ከኢትዮጵያ በኩል የንጉሠ ነገሥቱን መልእክት ለመሪዎቹ በማድረስ ብቻ ሳይሆን በቀጥታ ያለአስተርጓሚው በቃል ተነጋግሮ ፣ ተከራክሮ ፣ አሳቡን በጽሑፍ አስፍሮ ፣ ትክክለኛውን ያፄ ዮሐንስን ጥያቄ አሟልቶ መልስ የሚያመጣ ኢትዮጵያዊ መልክተኛ ጠፍቶ ፣ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ በአጠገባቸው ሆኖ በወታደርነትም ፣ በፖለቲካም ሲረዳቸው የቆየውን እላይ ስሙን የጠቀስነውን የእንግሊዙን ተወላጅ ኪርክሃምን ነበር የላኩት ። ይህ ሰው በሕንድ አገርና በመካከለኛው ምሥራቅ ፣ በቦምቤና በአደን ይመላለስ በነበረ መርከብ ላይ ተራ ሠራተኛና መጠጥም ያጠቃው እንደ ነበረ በየመጽሐፉ ተጠቅሷል ።[1]

እንደዚሁም ፣ በውጭ አገር እንደ ወኪል (ቆንሲል) ሆኖ ለመቀመጥና ጉዳይ ለመፈጸም የሚመጥን ኢትዮጵያዊ እየጠፋ ፣ ለወኪልነት የሚታጩውም የውጭ አገር ሰው ነበር ። ለምሳሌ ፣ በእንግሊዝ አገር ወኪል አድርገው ለማስቀመጥ የሞከሩት ሳሙኤል ሄንሪ ኪንግ የሚባለውን እንግሊዛዊ ነበር ።

በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ፣ አብዛኛውን ጊዜ የውጭ አገር ሰው ቅላቱና መጠነኛ ዕውቀቱ እንጂ ፣ ችሎታው ፣ ባገሩ መንግሥት ዘንድ ተሰሚነቱ የሚመዘንበት መለኪያ ስለ አልነበረ ፣ ተራው ፈረንጅ ሁሉ ወደቤተ መንግሥቱ ጠጋ ብሎ ንጉሡን በዝቅተኛ ዕውቀት ካስደሰተ ከከፍተኛ ሥልጣን ይደርስ ነበር ። ስለዚህም ነበር ኪርክሃም ፣ ተራው የመርከብ ሠራተኛ ፣ በኢትዮጵያ ተከብሮ ባገሩ ዐይነት የጄኔራልነት ማዕረግ ያገኘው ። እንደዚሁም ጃኮሞ ናሬቲ የሚባለው ተራ

1 J. de Coursac, Le regne de Yohannes, p. 108.



ኢጣሊያዊ አናጢ ፣ አንድ የዕንጨት ዙፋን አሳምሮ ሠርቶ በማቅረብ ካስደሰተ በኋላ ፣ ታላቁን የሰሎሞንን ኮርዶን ተሸልሞ አማካሪና ባለሟል ሆኖ ነበር ።[1] ይኸ ሁኔታ ከዐፄ ዮሐንስ በፊትም በኋላም ነበር ።

የሆነ ሆኖ ፣ ጄኔራል ኪርክሃም ካፄ ዮሐንስ ለንግሥት ቪክቶርያና ለሎርድ ግራንቪል የተጻፉትን ደብዳቤዎች ለሁለቱም ካቀረበ በኋላ ፣ ለፈረንሳይ ፕሬዚዳንት አቀርባለሁ ብሎ የተቀበለውንም ደብዳቤ ራሱ አድርሶ በማነጋገር ፈንታ ፣ ሎንዶን ለሚቀመጠው ለፈረንሳይ አምባሳደር አስረክቧል ። ከእንግሊዝ ንግሥትና ከሎርድ ግራንቪል ከፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ፣ ከሙሴ ቲየርም የመጣው መልስ በመሠረቱ ስለ ጉዳዩ ከዲቭ ኢስማኤል ተጠይቆ የሰጠውን መልስ የሚደግፍ ነበር ።

ታኅሣሥ 1865 ዓ.ም. በንግሥት ቪክቶርያ ተፈርሞ ከዊንጸር ቤተ መንግሥት የመጣው መልስ ፣

> . . . በአገልጋይዎ በጄኔራል ኪርክሃም እጅ የላኩልን ደብዳቤ ደርሶናል. . . በከዲቭ ኢስማኤል አድራጎት የደረሰብዎትን ስለ ገለጡልን ጉዳዩ አሥግቶናል ። እርሱም ወዳጃችን ስለሆነ እውነተኛውን ነገር ለመረዳት በቆንሲላችን በኮሎኔል ስታንቶን በኩል ጠይቀነው በሰጠን መልስ ላይ ፣ የግዛቱን ጸጥታ በድንበር ላይ ከሺፍቶችና ከቀማኞች ለመጠበቅ ወታደሮቹ ንቅናቄ ከማሳየት በቀር አገርዎን ለመውረር ምንም አሳብ እንደሌለው አረጋግጦልናል ። ከዚህም የተረፈውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችን በዝርዝር አሟልቶ እንዲልክልዎ አዘነዋል ካሉ በኋላ ፣ የኩርዓተ ርእሱ ሥዕል ተፈልጎ መጥፋቱንና የተገኘውን ሌላውን ክብረ ነገሥት መጽሐፍ እንዲላክ መወሰናቸውን ጠቅሰው "ይህ ደብዳቤ ሲደርስዎ ከከዲቭ ኢስማኤል በኩል በግዛትዎ ላይ ያሠጋዎት ጉዳይ በፍ[illegible] እንዲወገድ ተስፋ እናደርጋለን" ብለው ደምድመዋ[illegible]

ግራንቪልም በስሙ የላከላቸው ደብዳቤ ያንኑ የንግሥቲቱን አባባል ከመዘርዘር በቀር ብዙም አዲስ ነገር አልነበረውም ። ፍሬው ነገር "ኢስማኤል የእንግሊዝ መንግሥት እውነተኛ ወዳጅ በመሆኑ ዐፄ ዮሐንስ ላቀረቡት ስሞታ ተጠይቆ የኢትዮጵያን ግዛት ለመውረር አንዳችም ምኞት እንደሌለው ፣ ይልቅስ "ወሰን እያለፉ ፣ መልክተኞችን

1 A. del Boca, Gli Italianni in Africa Oriebtale, pp. 83—85


እየገደሉ ፣ ከብትና ሰው በምርኮ የወሰዱ ከኢትዮጵያ ግዛት የመጡት ሽፍቶች ናቸው ” ማለቱንና እነዚህን ተማርከው የሔዱትን ሰዎችና ከብቶች እንዲመለሱለት ጠይቆ መልስ ሰላጣ በወሰን ላይ ጸጥታ የሚ ጠብቁ ወታደሮች ማስቀመጡን ፣ እነዚህን ወታደሮች ቢመቱም እን ኳን ወሰን ዐልፈው ወደ ኢትዮጵያ ግዛት እንዳይገቡ ማስጠንቀቂያ መስጠቱን. . . ከመግለጽ ጋር በሁለቱ አገሮች መካከል ሰላምና ጸጥታ እንዲሰፍንና ሁለተኛ አለመግባባት እንዳይፈጠር የነበረውን ምኞት ይገልጣል ። በተረፈ በግራንቪል ደብዳቤ መጨረሻ ላይ ሳሙኤል ሔንሪ ኪንግ ለዐፄ ዮሐንስ እንደ ቆንሲል ወኪላቸው ሆኖ በሎንዶን እንዲቀመጥ አሳስበው የነበረውን ፣ ውክልናው በፊርማና በማኅተም ስለ አልጸደቀ ፣ ተሟልቶ ሲቀርብለት የሚቀበለው መሆኑን ያመለክ ታል ።[1]

ፈረንሳይ በ1870 ዓ.ም. ከጀርመን መንግሥት ጋር ተዋግታ ስለ ተሸነፈች ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ናፖሊዮን ሣልሳይም በቢስማርክ ጦር ስለ ተማረከና የዙፋን አገዛዝ ስለ ወደቀ ፣ ሬፑብሊኩን ለመምራት የተ መረጡት ፕሬዚዳንቶቹ እነ አዶልፍ ቲየር ፣ እነ ማርሻል ማክማሆ ባጫጭር ጊዜ ከመለዋወጣቸው የተነሣ ፣ ከፈረንሳይ በኩል ምንም ያህል ያለኝታ ተስፋ አልተጠበቀም ። በደሳርዚክ እጅ የመጣው መል ስም ምንም እጥጋቢ ስለ አልነበረ ፣ በመጨረሻ ንጉሠ ነገሥቱ ለፈረ ንሳዩ መልክተኛ “. . . እንግዲህ የአውሮፓ ኃያላን አቤቱታዬን ሰም ተው አንድ ነገር ካላደረጉ ከዚህ በፊት እንደ ተመከርኩት ፣ በሰላም መቀመጤ ቀርቶ ብቻዬን ተዋግቼ ቱርኮችን ከግዛቴ አባርራለሁ” ብለው ለቆንሲሉ እንደ ነገሩት ኩርሳክ የሚባለው ጸሐፊ አብራርቶ ገልጦታል ።[2]

በእርግጥም በፖለቲካው በኩል ባለው ወገን ብቻዋን የቀረች ውና በዲፕሎማሲ የግንኙነት ሜዳ በደንብ ለመጫወት የውጭ አገር ቋንቋ ዐዋቂ የሚያጥራት ያፄ ዮሐንስ ኢትዮጵያ በጦርነቱ መስክ ላይ በብዙ የፈረንጅ የጦር መኮንን ለተከበበችው ፣ የአንደበት ባለቤት ለሆ ነችው ለኢስማኤል ግብጽ የገፍግንነት ሙያዋን በደንብ ስታሳይ ወደ ፊት እናነባለን ።

1 Ibid.
2 Goursac, Le regne de Yohannes, pp. 113—117.





ቻርልስ ጆርጅ ጎርዶን (ፓሻ)

(ከድራሚ ኤ ሴክሬቲ)

ተጽሕፈት፡ በጐንደር፡ ከተማ። አመ፡ ፳ወ፫ ለሚያዝያ። በ፲፰፻ወ፸፰፸ወ፩ ዓመተ፡ ምሕረት፡


[illegible]

[illegible]




**ዐፄ ዮሐንስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት**

**(ፐብሊክ ሪኮርድ ኦፊስ ለንደን)**



ዐፄ ዮሐንስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት

(ፐብሊክ ሬኮርድ ኦፊስ ለንደን)



ዐፄ ዮሐንስ ለፈረንሳይ ፕሬዚዳንት የጻፉት

(ሚኒስቴር ዴዛፌር ኤትራንዤር ሚሞዋር ኤ ዶክዩማ አፍሪክ ፣ ፓሪ)

# ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

## ከስምታ በኋላ የመዠመሪያው ጦርነት—የሙንሲንጀር ፓሻ ፍጻሜ

ለአውሮፓ ኃያላን የስዎታው ደብዳቤ የሚያሳስባቸው አልሆነም ። ባለፈው ምዕራፍ እንዳስገነዘብነው ፣ ግብጽ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ በተለይ ከነዚህ ዐፄ ዮሐንስ ከጻፉላቸው መንግሥታት ጋር በፖለቲካም በባህልም ፣ በንግድም ከኢትዮጵያ በተሻለ ሁኔታ ግንኙነቷን አስፋፍታ ይዛ ስለ ነበረች ፣ ሁሉም የየመንግሥታቸውን ጥቅም መጠበቅ ስለ ነበረባቸው ፣ "በዚህ ፣ በግብጽና በኢትዮጵያ የወሰን ክርክር ፣ ኢትዮጵያን ብንደግፍ ከዚች በጣም ካልታወቀችና የፖለቲካም ፣ የንግድም ግንኙነት ከሌለን ኋላ ቀር አገር ምንድነው የምናገኘው ጥቅም ?" ለሚለው ጥያቄ በቂ መልስ የሚሰጥ የኢትዮጵያ ጠበቃ አልነበረም ። በመንግሥት ደረጃ መሪዎች ሁሉ የጥቅምን ጉዳይ መከተል እንጂ ፣ የሞራልን መንገድ ወደጐን ማድረግ ነበረባቸው ።

ስለዚህ ፣ የጀርመኑ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶን ቢስማርክ ለጀርመኑ ንጉሠ ነገሥት ለዊልሄልም በጻፈው ማስታወሻ ላይ "...በግብጽና በኢትዮጵያ የወሰን ክርክር ለመግባት ለጀርመን ምንም ዐይነት የፖለቲካ ጥቅም የለም ። በዚህ ጉዳይ የከዲቩን ምኞት የሚፃረር አቅዋም ብንወስድ በእሱ አገር ያለንን ቁም ነገር ያለውን የንግድ ጥቅማችንን እናበላሻለን..." ያለው የሁሉም አስተያየት ነው ።[1] በኦርቶዶክስ ሃይማኖቱ የተማመኑበት የመስኮብ መንግሥት አቅዋሙ ከነዚሁ ከእንግሊዝና ከጀርመን መንግሥታት የተለየ አልነበረም ።

የተቀሩትም የአውሮፓ መንግሥታት ከየቆንሲሎቻቸው ፣ ከየሚሲዮናውያኑ በተለይ ያፄ ዮሐንስ ጠበኛ ከሆነው ከሙንሲንጀር ፓሻ የተጻፈውን "የቦጎስ ፣ የሐባብ ፣ የመንሳ ፣ የሐልሃል ፣ የቤኒ አሚር ሕዝብ ሃይማኖቱ እስላም ስለሆነ ፣ ካልሠለጠነው ከኢትዮጵያ አገዛዝ ይልቅ በሠለጠነውና የሃይማኖት ዘመዱ በሆነው በግብጽ መገዛትን ይመርጣል ፤ አሁንም ወዶ ተቀብሏል" የሚለውን እያነበቡ የግብጽን አባባልና ወረራውን ደግፈውታል ።[2]

---

1 Zewde G.S., The Process of Reun. of the Eth, pp. 120—121.

2 G. Douio, Historire du regne du kedive Ismael, Tome III. pp. 769—770.

በዚህም ላይ የምኒልክን ከዮሐንስ ጋር አለመተባበር ፣ እንዲሁም የነራስ ወልደ ሚካኤል ፣ የነራስ ወልደ ሥላሴ ፣ የነራስ ወልደ ማርያም ካሤ ዮሐንስ መሸፈት ፣ የነአለቃ ብሩ ከዳት ለሙንሲንጀርና በርሱም ስብከት ለተማመነው ለከዲቭ ኢስማኤል ኢትዮጵያን ወርሮ ከሱዳን ጋር የመደባለቁ ጉዳይ ምንም ያህል እንቅፋት የሌለበት ጥርጊያ ጐዳና መስሎ ታያቸው ።

ዤኔራል ናፒየር ፣ ዐፄ ቴዎድሮስን ለመውጋት ሲመጣ ፣ "ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት" በተባለው መጽሐፍ ላይ እንደምናስታውሰው ፣ ሙንሲንጀር በመንገድ መሪነት ፣ በወሬ ነጋሪነት ፣ በፖለቲካው አመራር እንደ ኃላፊ ሆኖ አብሮ መጥቶ ጥሩ አገልግሎት ሰጥቶ ነበር ። እርሱም ከዚያ መልስ በእንግሊዞችም ፣ በፈረንሳዮችም ዘንድ ተከብሮ እስከ ቆንሲልነት ደረጃ ደርሶ ነበር ። ያሁኑንም ከዐፄ ዮሐንስ ጋር የሚደረገውን ጦርነት የተመለከተው በዚያው በመቅደላው ጦርነት ዐይነት ነበር ። ነገር ግን ፣ በሁለቱ ጦርነቶች መካከል ያለውን ልዩነት ሊገመግመው አልቻለም ፤ ወይም አልፈለገም ።

ከፈረንሳዮች ወደ ግብጾች ዞሮ የምጥዋ አገረ ገዥነትን ሲሾም የ"ቤይ" ማዕረግ ተሰጥቶት የነበረውን ፣ አሁን ደግሞ የግብጽ ጦር በርሱው አሳሳቢነትና አመራር ቦጐስና አካባቢውን ሲይዝ ፣ ባላባቶቹም ያለምንም ተቃውሞ ተገዥነታቸውን ሲያረጋግጡ በከዲቭ ኢስማኤል ፈቃድ ከፍ ያለውን የፓሻነት ሹመት አገኘ ። ባለቤቱም የቦጐስ ተወላጅ ነበረች ። ከዚህም ጋር ያፄ ዮሐንስ ዋና ታማኝ አገልጋይ የነበሩት አለቃ ብሩ ፣ እስከ ግብጽ አገር ድረስ ሔደው ጳጳሱን አቡነ አትናቴዎስን በማምጣትና ዐፄ ዮሐንስን በማንገሥ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያደረጉት ፣ አሁን ንጉሠ ነገሥታቸውን ከድተው ከሙንሲንጀር ጋር ሰምና ወርቅ ሆነው ስለ ተባበሩለት ፣ ሁኔታው ለጊዜው መልካም መሥመር የያዘ መሰለው ።

ይኸ ሁሉ ከታሰበና ፣ አስቀድሞ በፕላን እንደ ታቀደው ፣ በሰሜንና በምሥራቅ የሚዘምት የጦር ሠራዊት ከተዘጋጀ በኋላ ፣ በምሥራቅ በታጁራ በኩል ለሚዘምተው ዋና መሪ ራሱ ሙንሲንጀር ፓሻ ፣ በሰሜን በኩል በዘይላ ለሚዘምተው ራውፍ ፓሻና የጠቅላይ ሚኒስትሩ የኑባር ፓሻ የልጅ ልጅ (የርሱ ምክትል ኮሎኔል አራንድሩፕ (የዴንማርክ ተወላጅ) እንዲሆኑ ተመድበዋል ። ዋናውም አሳብ በሰሜን ራውፍ ፓሻ ፣ በትግራይና በትግሬ ዮሐንስን የከዱትን የክርስቲያን መኳንንት ከእስላሞቹ ባላባቶች ጋር አስተባብሮ ፣ በምሥራቅ በኩል የወሎንና የአውሳን ፣ እንዲሁም የአዘቦ አሮሞን ባላባቶች ቀስቅሶና ቢቻል ምኒልክንም ጨምሮ ፣ ዮሐንስን በሁለት ወገን



አዋክቦ በማድከምና በመጣል የግብጽን የበላይ ገዥነት በኢትዮጵያ ለመመሥረት ነበር ።

ይሁን እንጂ ፣ በምሥራቅና በሰሜን በሁለቱ አዝማቾች መካከል መቀናናት ነበር ይባላል ። የስዊሱ ተወላጅ ሙንሲንጀር ለግብጽ ሊያስገኝ ባቀደው ሰፊ ግዛት በኢስማኤል ዘንድ ሲወደድና ሲመሰገን ፣ በሰፋፊ ግዛት ላይ ሲሾም ፣ ራውፍ ፓሻ ፣ ግብጻዊው ግን ለዚያ ዕድል ባለመብቃቱ በቅናት እየተገፋፋ የሙንሲንጀር ፓሻ ተልዕኮ እንዲሰናከል ይጣጣር ነበር ይባላል ።

በ1868 ዓ.ም. በ17 መስከረም ኮሎኔል አሬንድሩፕ የጦሩ የበላይ አዝማች ሆነ ። የዚህም ጦር ዋናው ዓላማ ከምጥዋ ተነቃንቆ ወደ ዶጋው ወደ አሥመራ ወጥቶ ሐማሴንን ፣ ሠራዬንና አካለ ጉዛይን ወርሮ እስከ መረብ ወይም እስከ ዐድዋ በመዝለቅ ፣ የተያዘውን ሰፊ አውራጃ በቀጥታ የማስተዳደሩ ተግባር በግብጽ የበላይ ገዥነት የሚወሰን ጉዳይ መሆኑን ኢስማኤልና ኮሎኔል አሬንድሮፕ ተጻጽፈውበት ይገኛል ። "ይኸንንም አሳብ ዮሐንስ የተቃወሙ እንደሆነ በጐንደር ፣ በጐጃም ፣ በሸዋ በዮሐንስ ላይ የሚነሡትን መሳፍንት አግዛቸው" የሚል የኢስማኤል ደብዳቤ ለአሬንድሮፕ ደርሶታል ።[1]

ስለዚህ ፣ አሬንድሮፕ መስከረም 26 ቀን 1868 ዓ.ም. ምጥዋ ገብቶ ሲደራጅ ሰንብቶ ከምጥዋ ተንቀሳቅሶ በጥቅምት 14 ቀን ሠሐጢንና ዶጋሊን ዐልፎ ጊንዳዕ ደረሰ ። ከዚያም የግብጽ ጦር ግማሹ ሐማሴን ፣ የቀረውም አከለ ጉዛይ ሲገባ በንጉሠ ነገሥቱ በዐፄ ዮሐንስ ትእዛዝ የሐማሴኑ ገዥ ደጃች ገብሩ ፣ የሠራዬው ደጃች ማሩ ግዛታቸውን እየለቀቁ ንጉሠ ነገሥቱ ወደሚገኙበት ወደ ዐድዋ ሔዱ ።

በዚህም ጊዜ ፣ ለማታለልና ለማዘናጋት በከዲቭ ኢስማኤል እንደ ታዘዘው የጦር አዛዡ ". . .የግብጽ መንግሥት አበሻን ለመያዝ ሐማሴንንም ለመውሰድ ምኞት የለውም ። ነገር ግን ፣ ከርስዎ በኩል ዤኔራል ኪርክሃም የሚባለው እንግሊዛዊ የአሥመራና የጊንዳዕ አገረ ገዥ ተብሎ መሾሙን (ኢስማኤል ከዲቭ) ስለ ሰማና በወደብ ላለው ግዛቱ ስለ ሠጋ ፣ ደግሞም እንግሊዙ አገዛዙ መጥፎ የሆነባቸው ባላባቶች ለከዲቩ አቤቱታ ስለ አሰሙ ፣ ወደ ዶጋው ከፍ አልን እንጂ ከዲቩ እንደ ቀድሞ ከርስዎ ጋር በወዳጅነት ለመኖር እንጂ ፣ ለመዋጋት ምንም ዐይነት ምኞት የለውም" የሚል ደብዳቤ ጽፎ ላከ ።[2] ይኸን

1 Douin, Historie du regne du Kedive Ismael, Tom III pp. 770—772
2 J. de Coursac, Le regne de Yohannes, p. 305.

የመሰለውን የማዘናጊያ ደብዳቤ ከላከ በኋላ ፣ አሬንድሮፕ በ24 ሬጅመንት የተከፈሉ 2500 የሠለጠኑ የግብጽና የሱዳን ወታደሮች ብዙ የረሚንግቶን ጠበንጃዎችን ፣ 6 የተራራ መድፎችንና 6 ሮኬቶችን እንደያዙ ጉዟቸውን ዠመሩ ። ለተጻፈላቸው የማታለያ ደብዳቤ ዐፄ ዮሐንስ ምንም ዐይነት መልስ ስለ አልሰጡ ፣ አሁንም አሬንድሮፕ አብድኤልራሂምን (አብዱልራሂም) የሚባለውን ልኮ ፣ ዐፄ ዮሐንስ ስለ ሰላም ጉዳይ የሚነጋገሩ መልዕክቶችን እንዲልኩ ቢያስጠይቅ[1] ስለአልላኩ ፣ ጠሩ ጉዞውን ወደፊት ቀጥሎ እስከ መረብ ወንዝ ደረሰ ።

በቅርብ ጊዜ የታተመው ያፄ ዮሐንስ ዜና መዋዕል ፣ የዚህን የወረራና የጦርነት ጉዳይ እንደዚህ ሲል ያትታል “. . . ዐፄ ዮሐንስ በነገሡ በአራተኛው ዓመት[2] ከግብጽ ኢስማኤላውላን መጥተው የአግአዚ አገር የሆነችውን ሐማሴን የምትባለዋን ወረሩ ። በዚህ ጊዜ እስማኤላውያን የተባሉት ቱርኮች (ግብጾች) ወደ ሠፈሩበት ሔደው ሁኔታቸውን የሚስሉ ሰዎች ልከው ፣ እነዚህ ሰዎች ወደ ንጉሣቸው ተመልሰው የቱርኮችን (የግብጾችን) ፣ የፈረሶቻቸውን ብዛታቸውን ፣ ጽናታቸውን ገለጡላቸው” ካለ በኋላ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስ “ኃይለኛ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም ፣ ፈረሰኛም በፈረሱ ጽናት አያመልጥም” ብለው ዐይናቸውን ወደሰማይ ስቅለው ፣ “ሕዝብህን ከጥፋት አድን ፤ ርስትህንም ባርካት ፣ ለኛ ለአገልጋዮችህ የማሸነፍ ኃይል ስጠን” ብለው ጸልየው ወደ ጦርነቱ ጉዞ መዠመራቸውን ያመለክታል ።[3]

በሙሴ ሼን የታተመው ሌላው የግዕዝ ዜና መዋዕል ፣ በነገሡ ባምስተኛው ዓመት እስማኤላውያን . . . ብዙ መድፍና ጠበንጃ ይዘው ሠራዊቱ መጥተው ስለ ነበረ ፣ ዐፄ ዮሐንስ ይኸንኑ ሰምተው መረብን ተሻግረው ከእስማኤላውያኑ ጋር መሬት በደም እስከትታጠብ ድረስ ብዙ እልቂት አድርገው ፣ ከጠላቶቻቸው አንድም ሳያስተርፉ መፍጀታቸውን ያመለክታል ።*

1 Zewde G.S., The Process of Reun. . ., pp. 139—140.
2 Bairu Tafla, (ed.) A Chronicle of Emperor Yohannes IV, F. 140.
3 Ibid. pp.

* ወኮነ ዓቢይ ተቃትሎ እስከነ ትትሐፀበ ምድር በደመ እስማኤላውያን ወተቀትለ ኲሉ እመ ሰባዔቱ ለጎዳር ወኢያትረፉ አሐደ እምኔሆሙ . . . . Histoire de Yohannes IV — P 9—11 መሬቷ በደም ታጠበች የሚለው ቃል አጋና ነው ። በተለይ ደግሞ “አንድም ሳያስተርፉ ሁሉንም ፈጁት” የሚለው የተለመደ ያባቶቻችን አጻጻፍ ሆና ነው እንጂ ፣ ከዚህ ጦርነት የሸሸውም ፣ የተማረከውም ብዙ መሆኑ የታወቀ ነው ።



በምጥዋ የፈረንሳይ ቆንሲል ደሳርዜክ በዚሁ ጊዜ የፈረንሳይ መንግሥት መልእክት ይዞ ወደ ዐድዋ መጥቶ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ሆኖ ሁሉንም ይመለከት ስለነበረ ፣ ስለ ጉዞውና ስለ ጦርነቱ አዠማመር በበኩሉ እንደዚህ ይላል ። “. . . ዮሐንስ በ2 ኅዳር 1875 ዓ. ም. ቤተ መንግሥታቸውን ከጧቱ በአምስት ሰዓት ላይ በለቀቁ ጊዜ ታላቅ የመሬት መናወጥ ተቀስቅሶ ከሸሎዳ ተራራ ላይ የተፈነቃቀለው የደንጊያ ናዳ እየተንከባለለ ከንጉሡ እግር ሲደርስ ፣ ንጉሡ በግንባራቸው ተደፍተው ለሠራዊት አምላክ ሰግደው ቀና ካሉ በኋላ ፣ ፊታቸውን ወደ ሠራዊታቸው መልሰው ፣ “ይህ አስደንጋጭ ምልክት ዐረመኔዎቹ (ግብጾች) በጥንታዊቱ ኢትዮጵያ ተቀብረው ለመቅረታቸው አምላክ የሰጠው ምልክት ነው” ብለው ከተናገሩ በኋላ ፣ ከዐድዋ የሦስት ሰዓት ጉዞ ራቅ ብለው ንጉሠ ነገሥቱ እንደ ሠፈሩ የጦር ሠራዊቱም ቁጥር ከያለበት ተሰብስቦ ባንድ ጊዜ ከአንድ ሺ እስከ 70 000 መድረሱን ፣ አቡነ አትናቴዎስም ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በመተባበር ጦርነቱ ቅዱስ ጦርነት ነው እያሉ ወታደሩን ማበረታታቸውን ይገልጻል ።[1]

ከዚህ በኋላ ፣ የሁለቱም የጦር ሠራዊቶች ጉንደት ላይ ተያዩ ። በዚህ ጊዜ አሬንድሮፕ ግማሹን ጦር በጉንደት ትቶ ኮንት ዘኪ ወዳለበት ወደ ክሳድ ዒቃ እንደ ተደባለቀ ፣ ኢትዮጵያውያኑ ተጠግተው በኃይል ውጊያ ዠመሩ ። እርሱም በመዠመሪያ የወጠነውን የማጥቃት ተግባር ትቶ ምቹ ሥፍራ ይዞ መከላከል ዠመረ ። ነገር ግን ፣ ኢትዮጵያውያኑ በነሻለቃ (ወደፊት ራስ) አሉላ ፣ በነደጃች ሐጐስ ፣ በነደጃች ተሰማ የሚመራው ጦር ወታደሩን ስለ ፈጁበት ፣ ከአለበት ሥፍራ እንደገና ለቆ ወደ ጉዳጉዲ ሸለቆ ተዛውሮ ያንድ ሰዓት ጦርነት እንደ ተደረገ ግብጾቹ ሙሉ በሙሉ ተሸነፉ ። አሬንድሮፕ ከጦርነቱ ሜዳ ላይ ሞቶ ተገኘ ። ግማሹ ሲሞት ወይም ወደ ኋላው ሲሸሽ 150 ግብጻውያንና ሱዳኖች ፣ 3 ዩዝባሽ (ያገር ተወላጅ የቅጥር ወታደር ሹማምንት) ግማሾቹ ሲማረኩ አንዳንዶቹ በሽሽት አመለጡ ።

ከኢትዮጵያ ወገን ፣ በመዠመሪያ መረብ አጠገብ በተደረገው ጦርነት 31 ወታደር ሲሞቱ 55 መቁሰላቸውን ፣ በጉዳጉዲው ጦርነት 521 ሞተው 335 መቁሰላቸውን ደሳርዜክ ያመለክታል ።[2]

ከዚህም አያይዞ ንጉሠ ነገሥቱ ከዓዲኳላ ፣ “የምሥራች! ደስ ብሎኛል ደስ ይበልህ በእግዚአብሔር ቸርነት ጠላቶቼን አሸነፍሁዋቸው”

1 J. de Coursac, Le Regne de Yohannes, pp. 306.
2 Ibid. 303—306 Zewde G.S., The process of Reun,. . .pp. 140—143.
L. dei Sabelli, Storia di Abyssinia, pp. 247—248.

የሚል የደስታ ደብዳቤ ለእሱ እንደ ላኩበት ፣ ደሳርዜክ ይገልጽና የጦርነቱን ሁኔታ ለመንግሥቱ በጻፈው ራፖር ላይ ከኮሎኔል አሬን ድሩፕ ጋር ሆኖ ይዋጋ የነበረው ኮንት ዘኪ የሚባለው የአውስትሮ ሃንጋሪያን ተወላጅ በክሳድ ዒቃ በተደረገው ጦርነት ላይ ከፉኛ ቆስሎ በ8ኛው ቀን የርሱን (የደጎርዜክን) ዕድዋ መገኘት ሰምቶ ሳይበላ ፣ ሕክምና ሳያገኝ በጣም ተጐሳቁሎ ፣ ቆስሎና ተልቶ በመዳፋም ፣ በጉል በቱም እየዳኸ ሲሔድ ከመንገድ አግኝቶት እንደ ረዳውና በኋላ እንደ ሞተ ይገልጻል ።

ይኸ ሁሉ በሰሜን በኩል ሲደርስ ፣ በምሥራቅ በኩል ከዚህ በፊት እንዳወሳነው ፣ እነ አሬንድሩፕ በጥቅምት ወር 1866 ዓ. ም. ላይ ወደ መረብ ሲጓዙ ሙንሲንጀር ፓሻ ከአለቃ ብሩ ጋር ሆነው በከዲቭ ኢስማኤል ትዕዛዝ ከነበረበት ከሰንሂት ቀደም ብሎ በመስከረም ወር 1866 ዓ.ም. ላይ ወደ ምጥዋ ሔዶ ፣ ከዚያ ወደ አውሳ ሌላ ጦር ይዞ ለመሔድ ተዘጋጀ ። ዝግጅቱም እንዳለቀ በጥቅምት ወር 1866 ዓ.ም. ወደ አውሳ ጉዞውን ዠመረ ። ዋናው አሳብ በሰሜን በኩል አሬንድሩፕ ኃይሉን በዐፄ ዮሐንስ ላይ በሚያሳይበት በዚያው ሰዓት የአውሳን ፣ የራያንና የአዘቦን ፣ የወሎን ሕዝብ ቀስቅሶ በዚያ በኩል ዐልፎ ከምኒልክ ጋር ግንኙነት በማድረግና ለሸዋው ንጉሥ ማናቸውንም ስጦታና ተስፋ ሰጥቶ ዐፄ ዮሐንስን በሁለት ወገን ከቦ ለማስጨነቅ ነበር ።

ዳሩ ግን ፣ ይኸን ዓላማውን ወደ ፍጻሜ ከማድረሱ በፊት ባለፈው እንዳነበብነው ፣ በሰሜን የዘመተው ጦር ጉዳጉዲ ላይ ተመትቶ መሪው ኮሎኔል አሬንድሩፕ ራሱ በጦሩ ሜዳ ላይ እንደ ወደቀ ቀርቷል ። ስለዚህ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኑባር ፓሻ የጉንደቱን ውድቀት ገልጾ በዚያው ባለበት በአውሳ ግዛቱን አጠባብቆ እንዲይዝ እንጂ ፣ ወደፊት እንዳይገሠግሥ ከምኒልክም ጋር ግንኙነት ለማድረግ ጊዜው ምቹ ስለአልሆነ እንዲያቆየው ለሙንሲንጀር ደብዳቤ ልኮለት ነበር ። ሙንሲንጀር ደብዳቤው በፍጹም ሳይደርሰው ፣ በሰሜን የዘመተው ጦር መሸነፉንም ሳይገነዘብ ፣ የአሰል ሐይቅ በሚገኝበት ቦታ አድርጎ በአገሩ ባላባት እየተመራ ሲጓዝ ስለ መሸበት ፣ ከታጁራ ዐርባ ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ ከሚገኘው ቀበሌ ከነጓዙና ከነጦሩ አብሮ ሠፈረ ። ባላባቱም ፣ እነ አለቃ ብሩም አብረውት ነበሩ ። በኅዳር ወር እጋማሽ ላይ የበረሃ ጉዞ አድክሟቸው ሁሉም በተኙበት ሰዓት ከሌሊቱ በዘጠኝ ሰዓት[1] ላይ በርከት ያሉ የደንከል ሰዎች በደፈጣ በድንገት ደርሰው

1 ዘውዴ ገ/ሥላሴ በገጽ 63 ደንከሎች ጥቃት የሰነዘሩት ጠዋት መሆኑን ገልጸዋል ።



ወጉዋቸው ። በጭለማው ሰዓት ድካም የተጫናቸው ወታደሮች እንደ ሚገባ ሳይከላከሉ ብዙዎቹ አለቁ ። አደጋውን በጥሩምባ ሊያሰሙ የሚገባቸው አስቀድመው ስለ ተመቱ ምንም ማድረግ አልተቻለም ።

ሙንሲንጀር ፓሻም ከባለቤቱ ጋር በሠፈሩ መካከል እንደተኛ በነዚሁ በደንከሎቹ ተከበበ ። በጠበንጃም ፣ በሽጉጥም እየተከላከለ ከወራሪዎቹ መካከል ሊይዙት የሞከሩትን ሦስቱን ከገደለ በኋላ አንዱ ደንከል ጭንቅላቱን ሌላው ትከሻውን በጐራዴ ደብድበው ከጣሉት በኋላ ፣ በጦር ጨቅጭቀው ገደሉትና ሕይወቱ በዚህ ዐይነት ተፈጸመ ። ባለቤቱና ላንፍሬዲ የሚባለው ከርሱ ጐን ሕይወታቸው ዐለፈ ።

ከተከተለው ጠቅላላ ጦር 155 ግብጻውያንና 500 የደንከል ተወላጆች[1] ሞተው የተረፉት 73 ሱዳኖች 73 ዐረቦች (ግብጾች) ከአራት የጦር መኮንኖች ጋር ጭለማውን ተገን አድርገው ሌሊቱን በመሸሽ ከዚያም ቀን በመደበቅ ሌሊት በመጓዝ ከ8 ቀን በኋላ ታጁራ ገብተው ነፍሳቸውን አዳኑ ።[2]

በዚህም የሌሊት አደጋ ብልጡ አለቃ ብሩ ሸሽተው ከወንዝ (አዋሽ) ውስጥ ተደብቀው በነጋታውም በሕይወት ያሉትን ሱዳኖች ፣ ቁስለኞቻቸውን ትተው ፣ ከርሳቸው ጋር ወደ ታጁራ እንዲሸሹ አባብለው "እሺ" አሰኝተው ፣ ሱዳኖቹ አለቃ ብሩን ተከትለውና በሕይወት የተረፈውን አንድ መኮንን በቃሬዛ ተሸከመው ታጁራ (ቱጉሪ) በደህና እንዳደረሱዋቸው ኩርሳክ በጻፈው መጽሐፍ ያረጋግጣል ።[3] ነገር ግን ፣ በሌላ መጽሐፍ የአለቃ ብሩ በዚሁ ጊዜ መሞታቸው እንጂ ማምለጣቸው አልተመለከተም ።[4]


1 ዝኒ ከማሁ የሙንሲንጀር ወታደሮች በጠቅላላ 361 ብቻ እንደ ነበሩ ገልጸዋል ።
2 L. Sabelli, Storia di Abyssinia pp. 245—246.
Zewde G.S., The process of Reun., pp. 144—147.
A. Wylde, Modern Abyssinia, pp. 14—46.
3 J. de Coursac, Le regne de Yohannes, pp. 314—316.
4 S. Rubenson, The Survival of Eth. Indep., p.372



በስመ፡ እግዚኔ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሎቱ፡ ስብሐት፡
ወልእክት፡ ዘሥዩመ፡ እግዚአብሔር፡ ዮሐንስ፡ ንጉ
ሠ፡ ጽዮን፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ፡ ይድረስ፡
ኀበ፡ ክብርት፡ ወልዕልት፡ ንግሥት፡ ቢክቶርያ፡ በጸ
ጋ፡ እግዚአብሔር፡ እንግሊዝ፡ የሆኑ፡ የተባበሩ፡ ብሪታ
ንያና፡ የአየርላንድ፡ ንግሥት፡ የህንድ፡ ቄሳር
ያት፡ ወኩሉ፡ እደ፡ ያሚያ፡ ከጸፋኬለሙ፡ ወደብ፡ እጅ
ጉ፡ እንደ፡ ተ፡ ነው፡ እኔ፡ ከሠራዊቴ፡ ጋራ፡ በእግዚአ
ብሔር፡ ቸርነት፡ በአሞኑ፡ ደህና፡ አማልጅነት፡ እጅ
ሰኬ፡ ቴጅ፡ ፋን፡ ያከበር፡ ያወስግን፡ ያላና፡ ነፑ፡ መፊ
ረቱ፡ ለዘለዓለም፡ ነው፡ ለለእርቴ፡ ነገር፡ የተጻፈ
ውን፡ ደብዳቤ፡ የውሉን፡ ቶሎ፡ እስተማቻቹ፡ ተመ
ለሱ፡ ሰሁ፡ ደመንጌቾውን፡ ሎሳልቶ፡ ቺን፡ ልጅ፡ መርሚ
ያና፡ መሸሻን፡ ለደጆች ቀለሁ፡ ተደሳለ፡ በእኔ፡ ሙ
ክተማ፡ በ፲ወ፰፻፸ወ፯ ዓመት፡ ምሕረት፡ አመ፡ ፲ወ፱ለሐ
ም፡

ዐፄ ዮሐንስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት

(ፐብሊክ ሪኮርድ ኦፊስ ፥ ለንደን)




የኢትዮጵያ የጦር ሠራዊት ከግብጽ ወራሪ ወታደሮች ጋር የተዋጋባ ቸውን የጉንደትንና ፣ የጉንዳጉንዲን ፣ የጉራዕን ፣ የቀይሕቆርን ፣ ቦታዎች የሚያሳይ ካርታ ።

# ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

## ሁለተኛው ጦርነትና የኢትዮጵያ ድል አድራጊነት

የመዠመሪያው የጉንደት ጦርነት በኢትዮጵያ አሸናፊነት እንደ ተፈጸመ ዐፄ ዮሐንስ በድል አድራጊነታቸው በመጠቀም ወደ ቦጎስም፣ ወደ ምጥዋም አልተጓዙም ። ወደዚያ ለመሔድም ብዙ የሚገጥማቸው ችግር ነበር ። አንደኛው ቁጥሩ መጠነኛ ቢሆንም የግብጽ ጦር በቦጎስና በምጽዋ ወደብ ይገኝ ነበር ። ሁለተኛ ከሃምሳ እስከ ሰባ ሺ የሚደርስ ጦር እንደያዙ ከደጋው በሐማሴን ዐልፈው ወደ ቆላው ወደ ምጥዋ ቢወርዱ ለዚህ ሁሉ ሠራዊት ከነከብቱ የሚበቃ የእህልም ፣ የማርም ፣ የውሃም ስንቅ ይቸግራል ።

ስለዚህ ፣ የመዠመሪያውን ድል እንዳገኙ ወደፊት ገፍተው ወደብ በመያዝ ከሌሎቹ መንግሥታት ጋር ጠብ እንዳይፈጠር ጉዳዩን ዓዲኳላ ላይ ከመኳንንቶቻቸው ጋር መክረው ፣ ዘክረው ሁሉንም ትተው ወደ ዐድዋ ተመልሰው ኢስማኤል በቀድሞው ወሰን እንዲቆም አንድ ደብዳቤ ፣ እንደዚሁም ለንግሥት ቪክቶሪያ ሌላ ደብዳቤ ጽፈው ላኩ ። ለንግሥት ቪክቶርያ በጻፉት ደብዳቤያቸው ላይ ፣ አላግባብ የግብጽ ጦር አገራቸውን ወሮ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ተዋግተው ማሸነፋቸውን ፣ ኢስማኤልን "አንተም ከአባቶችህ አትበልጥም ፣ እኔም ከአባቶቼ አላንስምና ባገርህ ረግተህ የያዝኸውን አገሬን ልቀቅ" ቢሉት እምቢ ብሎ መዋጋቱን ፤ እርሳቸው ለንግሥት ቪክቶሪያና ለሌሎቹም ኃያላን የሚጽፉትን ደብዳቤ ምጥዋ ላይ ሙንሲንጀር ቀዶ እየጣለ ፣ በዚህ ፈንታ እርሳቸውን ጥፋተኛ ለማድረግ እርሱ እንደልቡ እየጻፈ መላኩን በዝርዝር ጽፈው ፣ በዚያው በአገልጋያቸው በጄኔራል ኪርክሃም እጅ ልከው ነበር ። ነገር ግን ፣ አሁንም የግብጽ ባለሥልጣኖች ምጥዋ ላይ መልክተኛውን 6 ወር አስረው አስቀምጠውት በመጨረሻ በሕመምና በችግር ተጉላልቶ ለመሞት በቅቷል ።

በግብጽ በኩል ፣ በጉንደቱ መሸነፍ የነኮሎኔል አሬንድሮፕ መሞት በካይሮ እንዳይሰማ በጥብቅ ተከለከለ ። በዚህ ፈንታ የግብጾች በኢትዮጵያውያን መሸነፍ ውርደት ስለሆነ ፣ ዐፄ ዮሐንስን እንደገና በመውጋት በደንብ ትምህርት ሰጥቶ ለመቅጣት የሚችል እና ያለፈውን መሸነፍ

ተቀብሎ የግብጽን የተዋጊነት ዝና የሚመልስ ከፍ ያለ የጦር ድርጅት በትጋት ይካሔድ ዠመር ። በግብጽ ባለሥልጣኖች ዘንድ ይኸን የመሰለ ራሳቸውን የማኩራራት ፥ ኢትዮጵያን በዝቅተኛ ደረጃ የመገመት ስሜት የሚያሳድርባቸውን ምክንያት በሁለቱ ቤተ መንግሥቶች (በካይሮና በመቀሌ) እና በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ያለውን የሥልጣኔ ድርጅት ፥ የወታደራዊ ትጥቅና የጦር መሣሪያ ልዩነት በመገመት መሆኑ ጥርጥር የለውም ። ይሁን እንጂ ፥ በሁለቱ ሕዝቦች መካከል የነበረውን የተዋጊነት መንፈስ በተለይ ጦርነቱ የሚካሔድበት ሠፈር ለኢትዮጵያውያኑ ቀና ፥ ለግብጾቹ አደናጋሪ መሆኑን የግብጾቹ መሪዎች በነርሱም ውስጥ ያሉት የፈረንጆቹ አዝማቾች ሊገመግሙት አልቻሉም ።

ስለዚህ ፥ በኩራት መንፈስ እንደ ተከበቡ አዲስ ለሚዘምተውና ቁጥሩ 15 000 ለሚደርሰው ጦር የበላይ አዝማች ፥ የግብጽ የጦር ኃይል ጠቅላይ አዛዥ ፥ መሐመድ ራቲብ ፓሻ ተሾመ ። ለርሱም ቺፍ ኦፍ ስታፍ (ኤታ ማዦር) ሆኖ በምክትልነት የሚረዳው የአሜሪካኑ ተወላጅ ዤኔራል ዊ.ዊ. ሎሬን ተመደበ ። ከነዚህም ቀጥለው ዊሊያም ማክዳይና ቻርልስ ፊልድ የሚባሉ ኮሎኔሎች ተጨመሩ ።[1] ከነዚህም ጋር ከጀርመን የጦር ትምህርት ቤት ሠልጥኖ የተመረቀው ልዑል ሐሰን የሚባለው የራሱ የኢስማኤል ልጅ ተመደበ ።

በዚህ ዐይነት ፥ ካይሮ ላይ ዝግጅቱ በኅዳር ወር ላይ እንዳለቀ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ታኅሣሥ 5 ቀን 1875 ዓ.ም. ከንጉሡ ከኢስማኤልና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ለራቲብ ባሻ በዝርዝር የተሰጠው መመሪያ "'ዮሐንስ ባለፈው ጦርነት ባሳዩት ድፍረት ምክንያት ሠራዊታቸውን በማፈራረስ ከሚሰጣቸው የበቀል ቅጣት ጐን ንጉሡ ከተመቱ በኋላ ግብጽ በምትፈልገው ዐይነት የዕርቅ ድርድር እንዲቀበሉ ማድረግ ፤ ምናልባት ወደ ሐማሴን መጥተው የግብጽን ጦር ለመማጠም የፈሩ እንደሆነ እዚያው አሉበት እከተማቸው ዐድዋ ድረስ ሔዶ በመምታትና የውስጥ ባላጋራዎቻቸውን በዚያው ሰዓት በማበረታታት የግብጽን ገዥነት ከመረብ ምላሽ እንዲጸና ማድረግ" የሚል የትምክህትና የኩራት አሳብ ይገኝበታል ።

በዚሁ ጊዜ ፥ የጦር ወታደሩ ቁጥር ከ15000 ወደ 20 000 ከዚያም እንደ ሁኔታው እየታየ ወደ 25 000 ከፍ እንደሚል ተነግሮት ጠቅላይ

1 ዘውዴ ገ/ሥላሴ በገጽ 151 ከጄኔራል ሎሬንግና ከሁለቱ ኮሎኔሎች ሌላ ስድስት አሜሪካውያን መኰንኖች እንደነበሩ ገልጸዋል ።



አዛዡ ከነጦሩ ጉዞውን ወደ ምጥዋ ዠመረ ። በ1875 እ.ኤ.አ. በታኅሣሥ ወር መጨረሻ ላይ ምጥዋ የገባው የግብጽ ጦር ፥ በጥር ወር ላይ ከምጥዋ ወደብ ለቆ ወደ ደጋው ወደ አሥመራ ወጥቶ ጉራዕ ደረሰ ። ጉራዕ ከአሥመራ ወደ ደቡብ ምሥራቅ ሲል ዐርባ ኪሎ ሜትር ላይ የሚገኝ የመንደር ከተማ ነው ። ከግብጽ የጦር ሠራዊትም ጋር ብዙ የሱዳንና አዲስ የተቀጠሩ የአገር ተወላጅ ወታደሮች "ባሽቡዙክ" ነበሩ ። ከሁሉም የበለጠ ከግብጾቹ የራስነት ማዕረግ የተቀበሉት የሐጸጋው ባላባት ወልደ ሚካኤል ስሎሞን የፈረስ ስማቸው አባ ጐሚዳ ስለሚገኙ ፥ ጦርነቱ እንደ ተዠመረ ብዙ መኳንንት እንደሚገቡላቸው በግብጾች በኩል ተስፋ ተደርጎ ነበር ።

በዚህ ዐይነት ፥ ዐፄ ዮሐንስ "እዩልኝ! ጥፋተኛውን መርምራችሁ ፍረዱ" እያሉ ለንግሥት ቪክቶሪያና ለሌሎችም የአውሮፓ መሪዎች በመጻፍ የለመኑት ፥ "አንተም ካባቶችህ አትበልጥ ፥ እኔም ከአባቶቼ አላንስምና በየአገራችን ረግተን ወዳጅነታችንን እንደ ቀድሞው እንቀጥል" እያሉ ለከዲቭ ኢስማኤል በደብዳቤ ያሳሰቡት ምንም ዐይነት ውጤት ሳያገኝ መቅረቱንና በዚህ ፈንታ የግብጽ ጦር ከቀድሞው በበለጠ አኳኋን ተዘጋጅቶ በራቲብ ፓሻ እየተመራ እንደገና መጥቶ ጉራዕ ላይ መሥፈሩን ሲመለከቱ በበኩላቸው እርሳቸውም ፥ "የአጋርና የኢስማኤል ልጆች ኢስማኤላውያን ፥ ሞዓባውያን ፥ ኤዶማውያን የተቀደሰችውን አገራችንን ለመውረር ሕዝባችንን ባሪያ አድርገው ለመግዛት መጥተውብናል ፤ ሁላችሁም ስለ አገራችሁና ስለ ሃይማኖታችሁ ጠላትን መመከት አለባችሁ" በሚል ዐዋጅ ሠራዊታቸውን ከቀሰቀሱ በኋላ ፥ ከከተማቸው ከዐድዋ የመዠመሪያ ጉዟቸውን ወደ እንደርታ አድርገው ስውም ፥ ስንቅም ፥ ገንዘብም ከሰበሰቡ በኋላ ተመልሰው በጉንደትና በአዲኳላ አድርገው ወደ ጉራዕ አመሩ ። የተከተላቸው የጦር ሠራዊት ቁጥር ከ15 000 እስከ 70 000 ሲደርስ[1] ከዚሁ ከዐሥር አንዱ ባለጠበንጃ እንደ ነበርና ከንጉሡ በታች ሆነው ጦሩን ይመሩ የነበሩት ራስ ባርያው እንደነበሩ በየመጽሐፉ ተመልክቷል ። የግብጽ ጦር ግን ፥ ቁጥሩ ከ15 ወይም ከ20 000 ላይ ቢመደብም ፥ ሁሉም ባለጠበንጃ ሆኖ በሥነ ሥርዓትና በደንብ የታጠቀ ነበር ። መሪዎቹም በደንበኛ የጦር ትምህርት ቤት የሠለጠኑ ነበሩ ።

በዚህም ጊዜ ፥ ራቲብ ፓሻ በጉራዕ ምሽጉን እየሠራ ዐርባ የሚሆነውን መድፍና ዐሥር ሮኬት በያለበት ጠምዶ ፥ ከዚህ ቀደም

1 ሀሮልድ ማርከስ የሠራዊታቸውን ቁጥር እስከ 200,000 አድርሶታል ። ከሁሉም ጠቅላላው 50,000 ወታደር ሆኖ ከዚህ ውስጥ 3,000 ፈረሰኛ ፥ 6,000 ባለጠበንጃ ያለው የሚመስል ነው ።

ጀኔራል ናፒየር ወደ መቅደላ በዘመተበት ሰዓት ለኢትዮጵያ መኳንንት ፡ "የእንግሊዝ ጦር እስረኞችን ለማስፈታት ሲል ከቴዎድሮስ ጋር ብቻ ከመዋጋት በቀር በምንም ዐይነት አገራችሁን አንፈልግም" ብሎ ያወጀውን እንደ ምሳሌ በመውሰድና በመጠቀም ፡ አሁንም መኳንንቱን ከንጉሡ ከዐፄ ዮሐንስ ለመለየት ሲል ፡ "እናንተን ከሚጨቁኑት ፡ የሰውን መብትና የሃይማኖትን ነጻነት ከማይጠብቁት ከዐፄ ዮሐንስ ጋር ከመዋጋት በቀር እናንተንም ፡ አገራችሁንም አንፈልግም" የሚል ዐዋጅ ባልተጣራ አማርኛ አጽፎ በንባብ አሰማ ። ምንም እንኳን እርሱ በያዘው አውራጃ አንዳንድ መኳንንትና ሹኮች ቢገቡለት ፡ የቀረው ባፄ ዮሐንስ በኩል ያለው ክርስቲያናዊው ጦር ከነመኳንንቱ ኅብረቱን አላላላም ።

ቢሆንም ፡ ባለፈው በጉንደቱ ጦርነት የደረሰውን የመሸነፍ ውርደት ያውቃልና ራቲብ ፓሻ ቁጥሩ የበረከተውን የኢትዮጵያን ጦር በሜዳ ላይ ፊት ለፊት መግጠሙ አደገኛ መስሎ ስለ ታየው ፡ እላይ እንዳልነው ደንበኛ ምሽግ በጉራዕና በቀይህ ኮር አሠርቶ በዚያ ላይ መድፉንና ጠበንጃውን ደግኖ እንዲቀመጥ ወታደሩን አዞ ስለ ነበረ ፡ ኢትዮጵያውያኑም ወደምሽጉ ሔደው መውጋቱ አደጋ መሆኑ ስለ ገባቸው ፡ ሁለቱም ቅርብ ለቅርብ እየተያዩ ሳይዋጉ ብዙ ጊዜ አሳለፉ ።

በመጨረሻ ግን ፡ የጦርነቱ ጊዜ መራዘም ለሁለቱም ወገን ተዋጊዎች በስንቅና በውሃ ረገድ ብዙ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑ ተሰማቸው ። በተለይ በማዦር ሐሰን ጉትጎታ የግብጽም ጦር ከምሽጉ ወጣ እንዲልና ያፄ ዮሐንስም ጦር ከሠፈረበት ቦታ እንዲንቀሳቀስ ተደረገ ። ያፄ ዮሐንስ ጦር ተነቃንቆ ባምስት መሥመር ሲጓዝ የሁለቱ ወገን የጦር ሠራዊት በመጋቢት 7 ቀን 1868 ዓ.ም. ውጊያ ገጥመው ለአራት ሰዓት ያህል እንደ ተዋጉ ወደ መጨረሻው በሜዳው ላይ ጦርነት አበሾቹ ማጥቃት ሲዠምሩ ግብጾቹ ወደየምሽጋቸው እየሮጡ መግባት ዠመሩ ። በዚህም ጦርነት ኢትዮጵያውያኑን በመናቅ ከሜዳ ወጥቶ መዋጋትን የተመኘው ማዦር ሐሰን ኢስማኤል ወዲያና ወዲህ እያለ በጉብዝና ተዋግቶ ነበር ይባላል ። ቢሆንም ፡ አደጋውን ሲያዩ ተዋጊውን አጋልጠው ከወታደሩ ቀድመው ወደ ምሽጉ የገቡ ዋናው አዝማች ራቲብና አሰን ናቸው ተብሎ መሳለቂያ ሆነዋል ።[1]

---

1 L. Dei Sabelli, Storia di Abyssinia - Vol. PP. 248—251.
Douin, Histoire dunlregne du Kedive Ismael, Rom. III. PP. 944—55.
S. Rubenson, The Survival of Ethiopian Independence, PP. 322-329
Zewde G.S., The Process of Reun., P. 154—170



ነገር ግን ፡ የኢትዮጵያ ወታደር እስከ ምሽጉ ድረስ እየተከታተለ ብዙውን የግብጻውያንን ወታደር በፈጀ መጠን ፡ ግብጾቹም በተለይ በምሽግ ያሉት በረሚንግተን ጠበንጃና በክሩፕ መድፍ እንደ ልብ እየተኮሱ ብዙውን የኢትዮጵያ ወታደር ፈጅተውታል ። በዚህ ዐይነት በሜዳ የተሰለፈው የግብጽ ጦር ቢሸነፍም ፡ በምሽግ ያለው ወታደር ሁለት ቀን በመመከቱ ሊደመሰስ አልቻለም ።

በዚህ ጦርነት ከግብጽ ወገን በሜዳ ግንባር ከገጠመው ከ5 ወይም ከ6000 ወታደር መካከል ሕይወቱ ተርፎ የተመለሰው ቁጥሩ ከ2.500 የማይበልጥ ሲሆን ፡ የሞተውና የተማረከው የግብጽ ጦር ቁጥሩ እስከ 3500 ይደርሳል ። ከምሽጉ ወጥቶ የተጠመደው 20 መድፍና 13000 ረሚንግተን ጠበንጃ በብዙ ሺ ከሚቆጠር ጥይት ጋር በኢትዮጵያውያኑ እጅ ተማረከ ። ቢሆንም ፡ በምሽግ ያለውን ጦር አጥቅተን መድፉን እንማርካለን በሚል ዓላማ ተነሣሥተው ወደ ምሽጉ የተጠጉ ቁጥራቸው ከ3 500 እስከ 4000 የሚደርስ ኢትዮጵያውያን ሞቱ ፤ 1000 የሚሆኑ ቆሰሉ ። የተማረከ ግን አንድም ኢትዮጵያዊ የለም ። ሐጋይ ኡርሊክ የሚባለው ጸሐፊ በዚህ ጦርነት አቡነ አትናቴዎስ መቁሰላቸውን ያወሳል ።[1]

በዚህ በጉራዕ ጦርነት ከ5 200 የግብጽ ወታደር ውስጥ የተረፈው 400 ብቻ ሲሆን ፡ የቆሰሉ 1600 ፤ የሞቱ 1000 ፤ የተማረኩ 2 200 መሆናቸውን ዱወ የሚባለው የፈረንሳዊ ጸሐፊ በበኩሉ መዝግቦት ይገኛል ። ይኸው ጸሐፊ ከኢትዮጵያውያን ወገን ከዘመተው 50000 ከሚሆን ጦር 5000 የሞተና የቆሰለ ሆኖ ግማሹም ዘማች ከውጊያው ላይ ብዙ የምርኮ መሣሪያና ዕቃ ስለአገኘ ፡ የማረከውን እየያዘ ያለ ስንብት ወደያገሩ ስለ ተበተነ ፡ ከዋናው ከጉራዕ ጦርነት በኋላ ምሽጉንም መደምሰስ ካስቸገረ ወዲህ ፡ በንጉሡ አጠገብ የተገኘው ጦር አጋማሹ ብቻ ፡ ማለትም 25000 ብቻ እንደነበረ አስገንዝቧል ።[2] ከኢትዮጵያውያን ወገን የተዋጉትን ፡ የሞቱትንና የቆሰሉትን ፡ ባገራችን በኩል በትክክል የሚገልጽ ጽሑፍ የለም ። ጦርነቱ ራሱ በደንብ ተዘርዝሮ አይገኝም ። አለቃ ለማ ኃይሉ በዚህ በጉራዕና ባለፈውም በጉንዳጉንዲ ጦርነት ላይ አባ ጉራጌ የሚባሉ ከጉራጌ አገር መጥተው አንኮበር

---

1 H. Erlech, A Political Biography of Ras Alula, pp. 60—61.
2 በአንደኛውና በሁለተኛው ጦርነቶች የተመለከቱትን አኀዞች በማብዛትም ሆነ በመቀነስ የተለያዩ ታሪክ ጸሐፊዎች የተለያዩ ቁጥሮችን አስፍረዋል ።
G. Douin, Histoire du Regoe du Kedive Ismael, pp. 832—962.

የኖሩ ፣ በኋላ ከአንኮበር ዐድዋ ሔደው የነበሩ መነኩሴ ፣ "በይው—የትግሬዋ ልጅ በይው የትግሬዋ ልጅ!" እያሉ ወዲያና ወዲህ እየተፈና ጠሩ ማዋጋታቸውን ጠቅሰውለታል ።[1] የዚህን የጉራዕን ጦርነት ብዙ የውጭ አገር ሰዎች ከዚህም ለየት እያደረጉ ሲተነትኑት እላይ እንዳልነው፣ ባገር ተወላጅ እጅ ተጽፎ ወደ ዘመናችን የተላለፈው በጣም ባጭሩ ነው ።

በቅርብ ጊዜ የታተመው ያዬ ዮሐንስ ዜና መዋዕል ፣ በራሱ የቃለ አጋኖ አነጋገር "በሁለተኛው ጦርነት ፣ ውጊያው የባሰ ሆኖ ዓለም ከተፈጠረ ዠምሮ ፣ ሆኖ የማያውቅ ጦርነት መደረጉን ፤ የመድፉና የጠበንጃው ጩኸት እንደ ክረምት ነጐድጓድ እየጮኸ ፣ ሕዝቡ ፣ ሰማይ ወድቆ የመሬትን መሠረት ያናወጠው እንደ መሰለው ፤ ጥይት እንደ በረዶ በመዝነቡ ሰዉ መደበቂያ ሥፍራ እንዳጣ ካመለከተ በኋላ ፣ በመጨረሻ ንጉሠ ነገሥቱ ከፈረሳቸው ላይ ወጥተው ሕዝባቸውን በንግግር አበረታትተው ሲቀድሙለት ፣ ሠራዊቱ የንጉሡን የልብ ጽናት በመመልከት ወደ ጦርነቱ ገብቶ የእስማኤላውያኑን አንገት አንድም ሳያስተርፍ እየቆራረጠ መጨረሱን ሲያወሳ የጦርነቱን ዓመትና ቀን ፣ የሠራዊት ቁጥር ፣ የሞተውንና የቆሰለውን ፣ ከጠላትም ወገን ሆነ ከኢትዮጵያም ወገን የሆነውን ዝርዝሩን አይሰጥም ።[2] በሙሴ ሼን የታተመውም ከዚህኛው አሳጥሮ በጥቂት መስመሮች ጠቅሶት ያልፋል ።[3]

የሆነ ሆኖ ፣ በዚህ በሁለተኛው ጦርነት መሸነፍ ጐን በዋናው የግዛት አቀንቃኝ በነበረው በወርነር ሙንሲንጀር ሞት ሳቢያ ከካይሮ እስከ ዛንዚባር ወይም ከሜዲተራኒ ባሕር እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ድረስ ሊዘረጋ ታስቦ የነበረው ሰፊው የኢስማኤል የቄሣር ግዛት የምኞት ዓላማ ከሸፈ ። የመዠመሪያው ድል አድራጊነታቸውን እንደ ጥፋት ቆጥሮት ዐፄ ዮሐንስን በደንብ ሊቀጣ ተዘጋጅቶ የመጣው ሁለተኛው የራቲብ ፓሻና የልዑል ሐሰን ጦር ራሱ ተቀጣ ። ኢስማኤል ለሦስተኛ ጊዜ ሊሳሳት ስላልፈለገ ፣ ሦስተኛ ጦር ለመላክ

1 መንግሥቱ ለማ ፣ መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ኃይሉ ፣ ገጽ 167-170 ።

2 ወባሕቱ በዳግማይ ጸብዕ ጸንዓ ተባዕስ ወኮነ ዓቢይ ቀትል ዘኢኮነ ከማሁ እም ተፈጥረ ዓለም እስከ ይእዜ እስመ ድምፀ መድፍዕ ወመንገኔ ተመሰለ ከመ ነጐድጓድ በወርኃ ክረምት ። ዐ እስ መሰሎሙ ጸድፈ እምርዕሱ ወነሕለ መሠረተ ምድር በታሕቱ ። አሜሃ ተሐጥአ መካነ ተኃብአ ወተሠውሮ እስመ ይዘንም አረር ከመ በረድ . . . አሜሃ ወጽአ ዮሐንስ ላዕለ ፈረሱ ። ወአስተጻነአሙ ለሕዝቡ . . . ወሶበ ርእዮ ሠራዊተ ንጉሥ ጥብዓተ ልቡ ለዮሐንስ . . . መልሑ አስይፍቲሆሙ ወመተሩ ክሳውዲሆሙ ። ወከመዝ ኃልቁ ወኢተርፈ አሐዱ እምውስቴቶሙ . . . ገጽ 140-141

3 M. Chaine, Histoire du Regne de Yohannes IV, PP. 10—11.



አልቃጣም ። ሁሉንም አመዛዝኖ "እንግዲህ በቃን" ብሎ ጦረኛ የመሰለው መሪ ሰላማዊ ሆኖ ፣ የሰላም ደብዳቤ በመጻፍ መሸነፉን ለመደባበቅ ይሞክር ዠመር ።

ከዚህ ድል ቀጥሎ ያለው ውዝግብ የዕርቁ ጉዳይ ነበር ። የተረፈውን ጦር ፣ በምሽጉ ውስጥ የነበረውን እንደ ያዘ ፣ ጠቅላይ አዝማቹ ራቲብ ፓሻ እንደ ምክትሉ የሚቆጠረውን ዋናውን ጸሐፊ መሐመድ ሪፋት ቤይ የሚባለውን ላከ ። እሱም ምንም ሳይፈይድ ተመለሰና በርሱ ፈንታ ዐሊ አል ሩቢ የሚባለው የዕርቁን ድርድር ከራቲብ ፓሻ በጽሑፍ ይዞ ወዳፄ ዮሐንስ መጣ ። ከራቲብ በኩል የቀረበው ድርድርም ፡—

1ኛ/ ሁለት ጊዜ በተደረገው ጦርነት ከግብጾቹ የተወሰደው (የተማረከው) የጦር መሣሪያ እንዲመለስ ።

2ኛ/ ምርኮኞቹ ተለቀው ወደ ግብጽ እንዲመለሱ ።

3ኛ/ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ነጻ የንግድ ልውውጥ እንዲደረግ የሚል ነው ።

ለዚህ ድርድር ፣ ዐፄ ዮሐንስ በበኩላቸው የሰጡት መልስ ፣ "የቦጎስን ግዛት ለቃችሁ ወደ ነበራችሁበት (ወደ ምጥዋ ወደብ) ተመለሱና እኔም ምርኮኞቹን እለቃለሁ ። ነጻ ንግዱንም እፈቅዳለሁ ፤ የተማረከው የጦር መሣሪያ ግን አይመለስም" ብለው መልስ ከሰጡ በኋላ ፣ የዚህን ጉዳይ ተነጋግረው እንዲጨርሱ የእንግሊዝ ቋንቋ ዐዋቂውን ሊቀ መኳስ ምርጫ ወርቄን ወከሉ ። ይኸው ጉዳይ ውሳኔ ሳያገኝ ከግብጾች ጋር ተደርበው የነበሩት ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ሐማሴንን ዘራርፈው ዐፄ ዮሐንስን በመፍራት ወደቆላው ወደ ዓይለት ሸሹ ። በምጥዋ በግብጾች እጅ ታስሮ የነበረው ያዬ ዮሐንስ ባለሚልና መልክተኛ ዤኔራል ኪርክሃም ታሞ እንደ ዕብደት አድርጎት መሞቱ ተሰማ ። የስምምነቱም ጉዳይ በየምክንያቱ ስለ ተራዘመ ፣ ዐፄ ዮሐንስም በጦር ኃይል የግብጽን ጦር ከቦጎስም ፣ ከሐባብም የማባረሩና ወደምጥዋ መዝመቱ ስለ አልተመቻቸው ፣ ለሐማሴኑ ግዛት ደጃች ኃይሉ እባ ሐባል የሚባሉትን የራስ ወልደ ሚካኤልን ዐይነተኛ ባላንጣ ሾመው ወደ ከተማቸው ወደ ዐድዋ ተመለሱ ። ዝርዝር ሁኔታው ወደፊት ይገለጻል ።

የዐፄ ዮሐንስን ወደ ዐድዋ መመለስ ፡ ለዚህ ጦርነት ተሰልፎ የነበረውም ዋናው ጦር መበተኑን ራቲብ ፓሻ ሲያውቅ እንደገና ወደ ሐማሴን መግፋት ዠመረ ። በርሱም የተደገፉት ደጃች ወልደ ሚካኤል በዐፄ ዮሐንስ የተሾሙትን ደጃች ኃይሉን በሐምሌ ወር ጸሐዘጋ ላይ

ወግተው ማርከው ገደሏቸው ። ቢሆንም እላይ እንዳልነው ፣ የግብጹ መሪ ኢስማኤል ፓሻ በአገሩም ፣ በውጭም ብዙ ችግር ስለ ገጠመውና በእርግጥም ከዐፄ ዮሐንስ ጋር ስምምነቱ እንጂ ፣ ጦርነቱ አለመጥቀሙን ስለ ተረዳ ፣ በመጨረሻ ለወልደ ሚካኤል የበቃ እርዳታ አታድርጉ የሚል ትእዛዝ ለራቲብ ፓሻ ላከ ። ወልደ ሚካኤል ከሁለት የወደቀ ዛፍ ሆኑ ። በዚሁ መካከል ፣ ዐፄ ዮሐንስ ለሻለቃ አሉላ እንግዳ ከመረብ ወዲያ ያለውን ግዛት ከራስነት ማዕረግ ጋር ሰጡአቸው ። አሉላም ወደ ግዛታ ወው እንደ ደረሱ እስካሁን ከግብጾች ጋር የነበሩትን ደጃዝማች ወልደ ሚካኤልን በመልዕክት አባብለው በማስገባት ፣ ደብረ ታቦር ወስደው ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር አገናኙአቸውና ዕርቀ ሰላም ወረደ ።

በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ፣ ወልደ ሚካኤል የራስነት ማዕረግ አግኝተው ከራስ አሉላ ጋር ወደ ሐማሴን ተመልሰው በቦጎስ እንዳሉ "እንደገና ከግብጾች ጋር በምስጢር ይላላካሉ" በሚል ሰበብ በራስ አሉላ ትዕዛዝ ታስረው ወደ መቀሌ ተላኩ ። ከዚያም በንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ ወደ አምባ ስላማ ተራራ ተልከው ተግዘዋል ። በኋላም ነጻ ሆነው በሽምግልናቸው ወራት የዐድዋንም ጦርነት ተካፍለዋል ።

ግብጾች በሁለቱም ጊዜ ጦርነት በጠቅላላው ከ12 እስከ 13000 ሰው ስለ ሞተባቸው ፣ 39 መድፍ ፣ 15000 ጠበንጃ ፣ 40000 በቅሎና ግመል ስለ ተማረኩባቸው ፣ በገንዘብም ረገድ ከግማሽ ሚሊዮን ስተርሊንግ በላይ ስላወጡ ፣ ከእንግዲህ ወዲያ የጦርነቱን ነገር እርግፍ አድርገው በመተው ከሐማሴን ፣ ከአካለ ጉዛይና ከሠራዬ ተጠቅለው ወደ ምጥዋ ወደብ ገብተው የወደቡን ሥራና አስተዳደር እያጠባበቁ ተቀመጡ ። የክርስቲያን ይዞታ የሆኑትን እነዚህን አውራጃዎች ሲለቁ ቦጎስና ሐባብ ግን በእጃቸው እንዳለ ቆየ ።

የግብጽ ባለሥልጣኖችና ራሱ ከዲቭ ኢስማኤል በነበራቸው የንቀት መንፈስ የመዠመሪያውን ጦርነት ውጤት እንደ ደበቁ ሁሉ ፣ ያሁኑን የሁለተኛውን የጦርነት ውርደት ሕዝባቸውም ፣ የውጭ አገር ሰዎችም እንዳያውቁ የበለጠ ይጣጣሩ ነበር ። ወሬውን ሰምቶ ፣ ከምጥዋም ከሱዳንም ወደ ካይሮም ፣ ወደ እስክንድርያም የሚገባው ሰው ወሬውን እንዳይነዛ የጠበቀ ቁጥጥር ለማድረግ ሞከሩ ።

"በኢትዮጵያ የተደረገው ጦርነት ቀንቶናል" የሚል ንጉሣዊ ማስታወቂያ ወደ ካርቱም ፣ ወደ ሰናሂት ለማስተላለፍ ከዲቭ ኢስማኤል ሲዘጋጅ አላዲን ቤይ የሚባለው ፣ "እንግዲያው ስለ ድሉ የደስታ መድፍ ለምን አንተኩስም" ብሎ ቢጠይቅ ፣ ፋሂሪ ፓሻ የሚባለው ፣



"የጦርነቱን ጠቅላላ ፍጻሜ መጠበቁ የተሻለ ነው" ብሎ መለሰለት ይባላል ። [1]

የጦርነቱ ጠቅላላ ሁኔታ ሲታይ ከሜዳ ላይ በተደረገው ዋነኛው ጦርነት ኢትዮጵያውያን እንዳሸነፉ ማናቸውም የውጭ አገር ጸሐፊ አረጋግጧል ። ነገር ግን ፣ በምሽጉ ጦርነት ግብጾቹ ተደብቀው በሙሉ ከመጨፍለቅ ራሳቸውን አድነው በሜዳ የተጋለጡትን ብዙ ኢትዮጵያውያን ስለ ጨረሱ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ የምሽጉን አለመበገር ተመልክተው ወደፊት ገፍተው ወደ ቆላ ለመውረድ ሆነ ጠብ ያበቀለውን የቦጎስንና የሐባብን ወረዳ ለመውረር ሳይመቻቸው ቀርቶ ፣ ወደ ዐድዋ መመለሳቸውና ከዚህ ጊዜ በኋላ እላይ እንዳልነው ሁለቱም ወገኖች ወደ ዕርቅ ድርድር ለመግባት መገደዳቸው የታወቀ ነው ።

የሆነ ሆኖ ፣ በዚህ በሁለተኛው ድል አድራጊነት ያፄ ዮሐንስ ዝና በያለበት እየተሠራጨ ሲሔድ ፣ የግብጽ መንግሥት ባገር ውስጥም በውጭም እየተዋረደ ሔደ ። ንጉሠ ነገሥቱም ቀድሞ በውስጡ ዘውድ የደፋ አንበሳ ያለበት ዙሪያውን ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ዘኢትዮጵያ የሚለውን ማኅተማቸውን አስፈርሰው ፣ "መስቀል ሞዓ እስማኤላውያን" የሚል አዲስ ማኅተም አሠርተው በዚህ ማኅተም ከውጭ አገር መሪዎች ፣ ካገር ውስጥ መኳንንትና መሳፍንት ጋር ይጻጻፉ ዠመር ። [2]

መስቀል ሞዓ እስማኤላውያን ማለት ፣ ክርስትና እስልምናን ወይም የእስማኤል ተከታዮችን አሸነፈ ለማለት ነው ።

የሆነ ሆኖ ፣ ዐፄ ዮሐንስ ሁለት ጊዜ በግብጾች ላይ ያገኙት ድል አድራጊነት በወታደርነት መስክ ዝናቸውን በያለበት እያደመቀው ሔዷል ። ድል አድራጊነታቸውን በማውሳት ስሙን የማናውቀው ያገራችን ገጣሚ እንደዚህ ሲል አሞግሷቸዋል ።

"ከላይ የወረደው ከጽዮን መቅደስ
ባባቱ ሚካኤል* በናቱ ሥላስ
አጨደው ከመረው ፣ ያን ያሕዛብ ገብስ
ወቃው ደበደበው ሰጠው ለነፋስ
ዐሊሙ ነፍጠኛ ዐፄ ዮሐንስ"

1 Zewde G.S., The Process of Reun. . ., pp. 168—170.
2 S. Petrides, Le Liver d' or de la dynastie Salomonienne d' Ethiopia, pp. 23—2
* አባቱ ሚካኤል የሚለው የራስ ስሑል ሚካኤል ተወላጅነታቸውን ለመጥቀስ ነው ።

# ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

## በግብጾችና ባፄ ዮሐንስ መካከል የምኒልክ አቅዋም

ካፄ ዮሐንስ ጋር በነበራቸው የንጉሠ ነገሥትነት የከረረ ፍልሚያ አንጻር ፥ ምኒልክ በግብጾችና ባፄ ዮሐንስ ጠብና ጦርነት መካከል የወሰዱት የገለልተኝነትና የቁጥብነት አቅዋም በብዙ የውጭ አገር ሰዎች ዘንድ ተመስግኗል ።[1]

ዮሐንስና ምኒልክ ፥ ሁለቱም ባንድ ዘመን ተገናኝተው ሁለቱም በየክፍለ ሀገራቸው በንጉሠ ነገሥትነት ሥያሜ እየተጠሩ ፥ በንጉሠ ነገሥትነት ማኅተም እያተሙ ፥ የውጭን አገር መንግሥታትን ወዳጅነትና እሠልጣኝነት ይሹ ነበር ። ሁለቱም የወሎን ፥ የቤገምድርን ፥ ያየጁንና የላስታን ፥ የጐጃምንና የስሜንን ባላባቶች ታማኝነት በትጋት ይሻሙ ነበር ። የነዚህም አውራጃዎች መሳፍንት የቤገምድሩ ራስ ወልደ ማርያም ፥ የስሜኑ ራስ ወልደ ሥላሴ(ወሬኛ) ፥ የየጁው ደጃች ወሌ ፥ የጨጨሆው ራስ ብሩ አሊጋዝ ፥ የሰቆጣው ዋግሹም ተፈሪ ወደ ዮሐንስ ፥ ወደ ምኒልክም ፥ ወደ ግብጽም እያሉ በመዋለል የዮሐንስ ጠላት ለምኒልክ ወዳጅ ፥ ምኒልክን እምቢ ብሎ ወዳፄ ዮሐንስ የተጠጋው ደግሞ ፥ ሹመትና ባለሙዋልነትን ሲያገኝ ፥ በዚሁ ረገድ የውጭ አገር ሰዎችም በሁለቱ ነገሥታት ላይ የነበራቸው አቅዋም የተለያየ ነበር ።

ከዮሐንስ ይልቅ ፥ ምኒልክ የሚሲዮናውያኑን የወንጌል ስብከታቸውን ስለ አልተቃወሙ ፥ ብዙ የፈረንሳይ ተወላጆች በቃልም በጽሑፍም ለምኒልክ ድጋፍ ያደርጉ ነበር ። የዐፄ ዮሐንስ የቅርብ ወዳጅና ደጋፊ የነበረው በምጥዋ የፈረንሳይ ምክትል ቆንሲል ፥ ኮንት ደሳርዜክ፥ በወሬ እንደ ሰማውና በደብዳቤም አጻጻፍ እንደ ተረዳው በሙሉ ልቡ ምኒልክን እንደሚደግፍ ገልጿል ።[2] ምኒልክም ይኸንኑ ወሬ ስለሰሙ በርሱ አማካይነት ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር ለመወዳጀት አስበው ፥ "የተላከ ከንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ዘኢትዮጵያ ይድረስ ከኰንሱል ፈረንሳዊ ደሳርዚክ. . . የርስዎን ደግነት ርእሰ መማከርት ጊዮርጊስ ነገረኝ ። ስለዚህም ነገር ፍቅርዎን ፈለግሁኝ ። ከአውሮፓ ነገሥታት

---

1 J. de Coursac, Le Regne de Yohannes..., p. 316.

ሁሉ እንዲያፋቅሩኝ ብርሃን በኢትዮጵያ እንድትገባ እንዲጥሩልኝ. . . ቤተ መንግሥትን የሚያጠና ተግባር ይፈልጉልኝ. . . ብለው በጥር 24 ቀን 1864 ዓ.ም. እንደ ኢትዮጵያ ቁጥር የጻፉለት ደብዳቤ ኩርሳክ ባሳተመው መጽሐፍ ላይ ይገኛል ።[1]

በእርግጥ የሌሎችን መንግሥታት ወዳጅነት እንደሚፈልጉ ሁሉ ከግብጽ መሪ ከከዲቭ ኢስማኤል ጋር ደብዳቤና ገጸ በረከት ተለዋውጠዋል ። በርሱ ወዳጅነት ከግብጽ አገር ፣ እንደ ባላንጣቸው እንደ ዮሐንስ ፣ ጳጳስ አስመጥተው በደንብ ለመንገሥ ፈልገው ዮሐንስን ከድተው ወደ ግብጾች በገቡት በአለቃ (ራስ) ብሩ ፡ በዘይላው ባላባት በአቡበከርና በልጁ በኢብራሂም ፡ በፈረንሳዩ በሙሴ ፒዬር አርኑ አማካይነት ተጣጥረዋል ። ከዲቭ ኢስማኤልም የወረራ ምኞቱን ላዩ ዮሐንስ እንደ ሸፈነው ሁሉ ፣ ለምኒልክም የግብጽ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ ምንም ዐይነት የመሬት ፍላጐት እንደሌለው ፣ የርሱም አሳብ ዮሐንስን በሰላምም ፣ በውጊያም ጥሎ የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥትነት ለምኒልክ ለማስጨበጥና እርሳቸውን ብቻ ለማወቅ መፈለጉን በደብዳቤም ፣ በነአለቃ ብሩም እንደበት አረጋግጧል ። ይኸም የመዠመሪያው ወቅት አሳቡ ለምኒልክ ሳይጥማቸው አልቀረም ። ስለዚህም በመዠመሪያው ወቅት በሁለቱ መካከል የደብዳቤውና የገጸ በረከቱ ልውውጥ ደመቅ ብሎ ታይቷል ። በዚህም ጊዜ ከዲቭ ኢስማኤል ለ"ሐበሻ ሡልጣን" በሚል አርዕስት ለምኒልክ በምጥዋ ወኪሉ በኩል የላከውን ደብዳቤ ፣ ወኪሉ የዮሐንስና የምኒልክ ሁኔታ ስለ ተማታበት አሳስቶ ለዮሐንስ ላከው ። ዮሐንስም ደብዳቤው በእርግጥ ለርሳቸው እንደ ተጻፈ በማመን በደስታና በአክብሮት ተቀብለው ከቆዩ በኋላ ፣ ስሕተት መሆኑን የተረዱትና በዚሁ ብዙ ውዝግብ የተፈጠረው በኋላ ነበር ።[2]

የሆነ ሆኖ ፣ የከዲቭ ኢስማኤል አያያዝ በቃልም በደብዳቤም የሚለውና በተግባር የሚፈጽመው ፣ ይኸውም ማለት ኢትዮጵያን በሰሜናዊ ምሥራቅና በሰሜናዊ ምዕራብ እየወረረ ግዛቱን ለማስፋፋት ከሚያደርገው ጥረት ጋር ስለ አልገጠመ ፣ ንጉሥ ምኒልክ ከርሱ እየራቁ ከዙፋን ባላንጣቸው ጋር ተቀራረቡ ። በዚሁ መሠረት በሁለተኛው ጦርነት ዋዜማ ላይ የግብጽ ጦር ተዘጋጅቶ ኢትዮጵያን ለመውረር መምጣቱን ገልጸው ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስና ጳጳሱ አቡነ አትናቴዎስ ፣ ይኸን የመጣውን ያገርና የሃይማኖት ጠላት የኢትዮጵያ ሕዝብ ተባብሮ እንዲመልስ ባደረጉት ዐዋጅ መሠረት ፣ ምኒልክም ላዩ ዮሐንስ ያንድ ክፍል

1 Ibid.
2 A. del Boca, Gli Italianni in Africa, p. 85.



የፈረሰኛና የእግረኛ ጦር ልከው ነበር ። ድሉም ከተገኘ በኋላ በዓሉ በዐድዋ ሲከበር እርሳቸውም በአንኮበር እንዲከበር አድርገዋል ይባላል ።[1]

ነገር ግን ፣ በመሳፍንት መካከል በየትኛውም ክፍለ ዓለም እንደ ዙፋን ባላንጣነት የበለጠ የሚያካርር ፡ የሚያዋጋና የሚያፋጅ ሌላ ምክንያት አልነበረም ። ዮሐንስና ምኒልክ በሰሜንና በደቡብ በተለያየ የትውልድ አውራጃቸው ሆነው በአንዲቷ የኢትዮጵያ ዙፋን በመፋለም ላይ እያሉ ፡ የኢትዮጵያን የየአውራጃ መሳፍንት ወደየራሳቸው ጐራ በመሳብና የውጭን አገር መሪዎች ወዳጅነት ለየግላቸው በሚሻሙበት ሰዓት ፣ ባላንጣቸው ዮሐንስ እንዲያሸንፉ ምኒልክ ከሸዋ ለዮሐንስ እርዳታ መላካቸውና ያዜ ዮሐንስ ማሸነፍ ሲሰማ ፣ በዓሉን በሸዋ ማክበራቸው አጠራጣሪ ይመስላል ።

ነገር ግን ፡ ምኒልክ በሕይወታቸው የራሳቸውን የግል ስሜት እያሸነፉ የሕዝብን ፍላጎት ሲያሟሉ ይገኛሉ ። "ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት" በተባለው መጽሐፍ ላይ እንዳነበብነው ፣ ከመቅደላ አምልጠው ከመጡ ወዲህ ፡ የቴዎድሮስ ሞት ሲሰማ እንዳይወረር ይሠጋ የነበረው ጦራቸው ከነመኳንንቱ በቴዎድሮስ ሞት ግባት እየተኮሰ ከውጭ ባደባባይ ሲደሰት ፣ እርሳቸው በእልፍኛቸው ውስጥ በሐዘን ላይ ነበሩ ። አሁንም ኢስማኤል ኢትዮጵያን ለመውረር መምከሩ ማንንም ኢትዮጵያዊ ሲያሠጋ ፣ ለእርሳቸው ካገር ጠላት ጋር መወዳጀቱ እንደማይጠቅማቸው ከመረዳታቸውም በላይ ፣ ገና ዐፄ ዮሐንስን አስጠቃለሁ በማለት የግብጽ ጦር በያለበት የሚያደርገውን ወረራ በአሳባቸው ለመቀበል አዳጋች ሆኖባቸው ነበር ።

የኢስማኤል ጦር በሜዳ ላይ ጦርነት ፡ ለሁለተኛ ጊዜ ተሸንፎ በምሽጉ ውስጥ እንዳለ የወረራውን አሳብ ለመተው ሁኔታው አስገድዶታል ። ጦርነቱ በመጋቢትና በሚያዝያ ወራት ላይ እንዳለቀ ከዮሐንስም ፡ ከምኒልክም ወዳጅነት በሚፈልግበት ሰዓት ምኒልክ በሰኔ 10 ቀን 1868 ዓ.ም. ለኢስማኤል የጻፉት በዲፕሎማሲ አነጋገር የተሸፈነው ደብዳቤያቸው ደንበኛ አቅዋማቸውን ይገልጻል ። ቃሉም ከዚህ የሚከተለው ነው ።

"ከዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ይድረስ
ወደ ከበረው ፣ ከፍ ካለው ከታፈረው ኢስማኤል ፓሻ. . .
የዛሬ 3 ዓመት ከኢብራሂም አቡበከር ጋር የሰደዱልኝ ገጸ

2 አፈ ወርቅ ገ/የሱስ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ፣ ገጽ 24 ።

በረከት. . .ደረሰኝ ። . . .አሁን ደግሞ አቶ ጴጥሮስ አርኑስ የፈረንሲስ ነጋዴ ወደ አውሮፓ የሚመለስ ቢሆን እርሱም የማምነው ሰው ስለሆነ ፣ የመንግሥትንና የንግድን ጉዳይ ሁሉ እንዲያደርግልኝ አዝዠዋለሁ. . . ከርሱም እጅ ጥቂት የፍቅር በረከት ምስክር እንዲሆን ይቀበሉኝ. . .የርስዎ መንግሥት ምክር ለኔ ሥራ በርን የሚደፍን መሰለኝ ። ጐረቤቶቼን (ዐፄ ዮሐንስን ወይስ የሐረርጌን ሡልጣን?) ሊወጉ የመጡ የርስዎ ወታደሮች በኢትዮጵያ ደቡብ (ሰሜን) በኩል ትግሬን ተዋጉት ። ዛሬም አላረፉም ። ከኒያ የተከፈሉት (ግማሹ የግብጽ ጦር) ተጐሪን (ታጅራን) ያዙት ። አውሳንም ጨውንም ያዙት ። የሸዋን መንግሥትና የኦሮሞን አገር ይዞ የነበረው አዳሉም ሐረርጌም በርስዎ ወታደሮች እጅ ሆነ ። ዛሬ ጦሩ በጥጋችን (በአጠገባችን) ነው ። ሦስተኛ ጦር በነጭ አባይ መጥቶ (በምዕራብ መጥቶ ቋራን የወረረው) በኦሮሞ አገር ታየ ይሉናል ። በሐረርጌና በዘይላዕ (ዘይላ) የወጣው (የመጣው) ከላይኛው ጦር ጋራ ጉራጌ ላይ እንዲገናኙ ተቃጥረዋል ይባላል። ይህም ምስጢር አይደለም ጉራጌውም የኔ ግዛት ነው።

አሁን ይህን ምን እንበለው ። የወታደሮችዎ ሥራና የወዳጅነት ፍቅር የሚያሳይ የደብዳቤዎ ቃል የተተካከለ አይመስለኝም ። እጅግ የሚያስፈራ ነገር ነው ። በዚህም እጅግ አዝኛለሁ ። ነገር ግን እርስዎ እኔን ወዳጅዎን አለአንድ ብልሃት ፣ አለአንድ ሥልጣን መጥተው ይወጉኛል አይመስለኝም አገሬ ድረስ መጥተው ። ለጊዜው ብቻ አሳዘነኝ እንጂ ነገር ግን ኢትዮጵያ በእናንተ ጦር መከበቧን ማሳየት ይገባናል ።

ዛሬ በባሕረ ኤርትራ ያሉ በሮች ፣ በሕንድ ውቅያኖስ አውራጃ ያሉ በሮች ወደኛ ከጨርቅ በቀር ሌላ ዕቃ እንዳ ይወጣ ከለከሉ ። ነፍጥ ባሩድ የወታደር መሣሪያ ሁሉ ለመጠበቂያ የሚሆን ሁሉ በዕውቅ ተከለከለ ። የግብጻውያን ጦር አገሩን ሁሉ ከበበው ። ጥቂት ቆይቶ አዋሽ ሊገባ ነው ከኔ ግዛት ላይ ። ይህ የሆነ እንደሆነ የፈራሁት ሁሉ ደረሰ ይህም ለርስዎ ማሳየት ይገባል ።”

ምኒልክ ስለ ግብጽ ወረራ ያላቸውን ሥጋት በዚህ ዐይነት ከገለጹ በኋላ በደብዳቤያቸው መጨረሻ ላይ . . .
“. . .ለመንገዱ ለበሩ ሳንከለከል በተጐሪ(ታጁራ) አውራጃ ያለ መካከለኛ መንገድ በማህል እንዲኖርልን ፣ የንግድ ዕቃ



ሁሉ ይህ ይቅር ሳይባል ከወዲያ (ከአውሮፓ) የሚመጣ ሁሉ ከዚህም የሚሄድ ሁሉ መሄድና መምጣት እንዳይከለከልብን. . .ስለዚህም አቶ አርኑስን ሥልጣን ሰጥቼ ሰድጄዋለሁ. . .ስለዚህ መልካም ፍሬ ከርስዎ እንዲያገኝ ተስፋ አለኝ ። እግዚአብሔር ያብራልዎ እድሜዎም ይርዘም ። 10 ለሰኔ 1868 በልቼ ከተማ ተጻፈ ።”
በማለት ደምድመዋል ።

ከዚህ ቀጥሎ ባለው ጊዜ የግብጽ መንግሥት ያለአቅም ፣ ያለበቂ ጥናት በያለበት እየፎለለ ብዙ አገር ከያዘ በኋላ ፣ በኢትዮጵያ ሰሜን ባፄ ዮሐንስ ሲሸነፍ ፣ በሱዳን የመህዲ መነሣት የወታደሩን አውታር ገረሰሰው ። በዚሁ ጐን በያለበት ያሠራጨውን ወታደር ፣ በያለበት የዘረጋውን የልማት ሥራ ለማራመድ የኢኮኖሚው አቅዋም ሳይችል ቀረ ። በመጨረሻም ከውስጥና ከውጭም በተነሣ ንቅናቄ የኢስማኤል መንግሥት ከመውደቅ አልዳነም ነበር ።

# ምዕራፍ ዐሥራ አራት

## በኢትዮጵያና በግብፅ መካከል ተንጠልጥሎ የቀረው የሰላም ውል

ከውጊያው በኋላ በዚያው በምሽግ ውስጥ እንዳሉ ልዑል ሐሰንና ዋናው አዝማች ራቲብ ፓሻ "ጥፋቱ ያንተ ነው ፤ የለም ያንተው ነው" በመባባል ከተጨቃጨቁ በኋላ ፣ ራቲብ ሳይወድ በግዱ ሁኔታውን ለግብጹ መሪ ለኢስማኤል በቴሌግራም አሳወቀ ። ቀጥሎ በራፖር ገለጸ ። ራሱንም ከወቀሳና ከቅጣት ለማዳን ጥፋቱን ሁሉ በአውሮፓውያኑ መሪዎች ላይ እንደዚህ ሲል ለጠፈው ።

". . . በመጋቢት 6 ቀን 1876 የጠላት ጦር ወደ ቀይህ ኮር መጓዙን እንደ ሰማሁ ጄኔራል ሎሪንግና ኮሎኔል ዳይ ከምሽግ ወጥተን እንግጠም ቢሉኝ ፣ ይኸ ዐይነቱ የሜዳ ጦርነት አደገኛ መሆኑን አጣርቼ ብነግራቸውም 'እምቢ' ብለው ስለወተወቱ ፣ አንደኛ ከነርሱ ጋር በስምምነት እንድሠራ ከበላይ ትእዛዝ ስለ ተቀበልሁ ፣ ሁለተኛም ጊዜው ስለ አጠረ 'እሺ' ብዬ በማግሥቱ ከምሽግ ወጥተው ስንጓዝ ንጉሡ ዮሐንስ በተመለከተን ጊዜ ወደ ቀይህ ኮር መጓዙን ትቶ 250000 ጦሩን እንደ ያዘ ወደኛ ቀልበስ ብሎ ገጠመንና የኛዎቹ በጀግንነት የጠላትን ጦር ገጥመው ታላቅ እልቂት ሆኖ ወደኋላ እንዲያፈገፍግ አደረጉት . . . ግሩም የሆነ የጨበጣ ጦርነት ነበር ። ልዑል ሐሰን ራሱ በእጁ የጠላትን ብዙ ወታደሮች ገድሏል ። ቢሆንም ከኛ ወገን የሰባት ባታሊዮ ጦር ፊርሶ 19 መድፎች ተማርከውብናል. . . ሆምበር ወደ መጥለቅ ስታዘነብል ፣ ወደ ምሽጋችን ገባን. . . በዚህ ሰፊ ራፖር እንደ ዘረዘርሁት ፣ መደምደሚያውን የዚህ ጦርነት መሸነፍ የደረሰው በጄኔራል ሎሪንግና በኤታ ማዦር መሆኑን በግልጽ አመለከታለሁ ።[1]

ይኸን ውሸት የበዛበት ራፖር ለከዲቭ ኢስማኤል ከምጥዋ ወደ ካይሮ ወስዶ የሰጠው ሶሊማን ኒያዚ ፓሻ ይባላል ። ኢስማኤል

---

1 G. Douin. Histoire du Kedive Ismaei, PP. 939—942.

ከራፖሩም በተጨማሪ ዝርዝር ሁኔታውን ከመላክተኛውም ፤ ከሌሎችም ከአዳመጠ ወዲህ በምሬትና በጸጸት ፤

> . . .በተደረገው ያመራር ስሕተት በጣም እናዝናለን . . . መቼም በጦርነት ጊዜ አንዳንድ ስሕተት መድረሱ የተለመደ ነው. . . የሆነ ሆኖ ለጊዜው ተገቢ የሆነውን እርምጃ የመውሰዱ ፋንታ ያንተው ነው ። ወታደርም ፡ መድፍም ጨምረን እንልክልሃለን. . . በጉብዝናህና በታማኝነትህ ሙሉ እምነት አለን . . . የሚያስፈልገውን እርዳታ ጨም ረን በኢስማኤል ሪፍኪ ፓሻ መሪነት እንልክልሃለን ። ከርሱ ጋር ካሉት 11 የባታዮ ጦር ጋር ጨምረን በድምሩ የ14 ባታዮ ጦር ይደርስሃል ።*
>
> ‘‘ከኡስማን ሪፍኪ ጋር በወታደራዊ ምልክት እየተግ ባባችሁ በኅብረት እየሠራችሁ በበኩልህ የጉራዕን ምሽግ ጠንክረህ ተከላከል ፤ ሌላም እርዳታ ቢያስፈልግህ ይደርስሃል። ሰላምታችንን ለልጆችንና ለጦር ሠራዊቱ ንገርልን’’ ሲል

መለሰለት ። [1]

በዚህ ዐይነት ፥ ብዋናው የሚዳ ጦርነት ያዬ ዮሐንስ ጦር አሸ ንፎ ቁጥሩ የበረከተ የጠላትን ምርኮኛ እንደያዙ ፥ መድፉንና ጠበንጃ ውን ሁሉ ሰብስበው እጅ ካደረጉ በኋላ ፥ ባንድ ወገን ምርኮኛውን በማስጠበቅ የሞተውን ወታደራቸውን በማስቀበር ላይ እንዳሉ ራቲ ቭና ሐሰን ከተረፈው ወታደራቸው ጋር ያሉበትን የጉራዕ ምሽግና ከዚህኛው ራቅ ብሎ የሚገኘውን የቀይህ ኮር ምሽግ ጭምር በወታ ደር አስከብበው ራሳቸው ከታላቅ የወርካ ዛፍ ሥር ተቀምጠው ሳለ የራቲቭ ፓሻ አስተርጓሚና ጸሐፊ መሐመድ ሪፋት የሚባለውን አንድ የኢትዮጵያ ፈረሰኛ ማርኮ በማስፈራራት በመደብደብም ከፊቱ አስ ቀድሞ አመጣና ከደጃች ማሩ ጋር አገናኘው ። ከዚያም በደጃዝማች ትዕዛዝ ያው ፈረሰኛ እየመራ ወስዶ ከንጉሠ ነገሥቱ ካገናኘው በኋላ በዚሁ ምርኮኛ አማካይነት የእርቅ ንግግር ተከፈተ ። ከኢትዮ ጵያ ወገን ቋንቋ ዐዋቂዎቹ ሊቀ መኳስ ምርጫ ወርቄ ፥ አቶ ደስታና አቶ ገብረ እግዚአብሔር የሚባሉት ተመደቡ ።

---

* ያንድ ባታዮ ጦር ቁጥሩ እንዳገሩ ይለያያል ። በጠቅላላው አንድ ባታዮ በውስጡ ስድስት ኮምፓኝ ጦር አለው ። ባንድ ኮምፓኝ (ክፍለ ጦር) 250 የሚሆን ተዋጊ ጦር አለው ።

1 Ibd PP. 943



በነዚህ አማካይነት ፡ ንጉሠ ነገሥቱ ለጦር አዛዦና ለልዑል ሐሰን ሁለት ደብዳቤዎች አሲዘው ላኩዋቸው ። ለራቲቭ ፓሻ የተጻ ፈው ፤

> . . .እስካሁን በሁለታችን መካከል የተደረገውን ጦርነት ያበቀለው ሙንሲንጀር ፓሻ ነው ። ያለዚያ በኔና በከዲቭ ኢስማኤል መካከል የነበረው ወዳጅነት የጸና ነበር. .የና ንተ ወታደር ሐማሴንን ወሮ እስከ መናገሻ ከተማችን ተጠ ግቶ ስለ ነበር * በሚያሳዝን አኳኋን ጦርነት ተደርጎ ብዙ ደም ፈሰሰ ።. . . ያም ሳይበቃ ቀርቶ እንደገና ጦር ሰብስባች ችሁ መጥታችሁ በመሬታችን ላይ መሽጋችሁ ተቀምጣ ችሁ ምክንያቱንም ሳትነግሩን ጦርነት ከፍታችሁ ፥ ሦስት ቀን ሙሉ ከሁለታችን ወገን በሰውም በአምላክም ዘንድ ያል ተወደደ ብዙ ደም ፈሰሰ. . .አሁን የዕርቅ ድርድር ትፈልጉ እንደሆነ ሁነኛ ሰው አድርጉና ከኛም አንዱን እንድንመድብ ዛሬውኑ መልሱን አስታውቁን. . . የሚል ነው ።

ይኸ ደብዳቤ ከደረሰው በኋላ ራቲቭ ፓሻ “. . .መልካም ነው እኛም ዕርቁን እንፈልጋለንና ሁነኛ ሰው ይላኩልን’’ የሚል መልስ ስለላከ ፥ ንጉሠ ነገሥቱ ፤

> . . .በሁለታችን መካከል የሚያጣላ ምንም ነገር አልነበ ረም. . .ያለፈው ጦርነት የሰይጣን ሥራ ነው...እኔና ወንድሜ እስማኤል ፓሻ አንድ ነን... ከወንሜድ ከኢስማኤል ልጅ ጋርም ምንም ጠብ የለንም. . .የወጋችሁንም የሽፍታ ነገር እየሰ ማችሁ ነው. . .አሁን ግን ፥ ያለፈው ዐለፈ. . .ለወደፊቱ በወ ሰናችን ረግተን በዝምድና ውል እንተሳሰር. . .ምርኮኞ ቻችሁን በሙሉ እንመልስላችኋለንና በኩራት (በሰላም ሳት ዋረዱ) ወደ አገራችሁ ትገባላችሁ. . .አምላክ በወሰን ከልሎ የሰጠንን ወሰን ማክበር እምቢ ካላችሁ በሁለታ ችን መካከል እሱ ይፈርዳል ። በቆየው የወዳጅነት ባህል ጦርነቱ ወይም ወዳጅነቱን የመምረጡን ጉዳይ ለናንተ ትተነዋል. . . * *

ካዬ ዮሐንስ በኩል ይኸን የመሰለ ግልጽ የሆነ የዕርቅ አሳብ ሲቀ ርብ፡ ከግብጹ መሪ የሚላከው መልስ ቅጥፈትና ማጭበርበር የመላበት

---

* ያለፈውን ዓመት የጉንደት (ጉዳ ጉዲን) ጦርነት ሲጠቅሱ ነው ።

** ትክክለኛውን ያማርኛ ደብዳቤ ስላላገኘነው ከዚህ በላይ ያስፈርነው ከፈረንሣዊው ትርጉም ላይ ወደ አማርኛ እየመለስን ነው ።

ነበር ። እንደ ፊተኛው ያሁኑም የሁለተኛው ጦርነት የመሸነፍ ውር
ደት በግብጽም ፣ በሱዳንም እንዳይሰማ ከምጥዋ ወደ ካይሮ በሚመላለስ
ሰውና የዚህን ወሬ በያዘ ደብዳቤ ላይ በየፖስታ ቤቱ ጥብቅ ቁጥጥር
እየተደረገ ፣ ያሁኑንም ካፄ ዮሐንስ የተላከውን የዕርቅ አሳብ ነገሩን
ዘወር አድርገው ፣ "ያበሻ ንጉሥ ስለ ተሸነፈ ግዴታ ሆኖበት ዕርቅ
ጠየቀ" ተብሎ እንዲወራ አደረጉ ። በሌላ ወገን ደግሞ "... ዮሐንስ በጦ
ርነቱ ላይ ከ40 እስከ 50.000 የሚደርስ ወታደር ስለ ሞተበት ፣ ከጦር
ነቱ ቦታ ወደ ከተማው ወደ ዐድዋ ተመለሰ" እየተባለ ይጻፍ ዠመር ።
የነዚህም የሟቾች ቁጥር እንደዚህ ሊበረክት የቻለው ራቲብ በሐሰት
ያፄ ዮሐንስን ከ50.000 የማያልፈውን ጦር እስከ 250.000 ስለ አደረ
ገው መሆኑ ነው ።

ነገር ግን ፣ የጦርነቱን ሁኔታ ከዲቨ ኢስማኤል ከራቲብ ፓሻም
ከልጁ ከሐሰንም በመልእክት ከሰማው ሌላ ትክክለኛውን ወሬ ከም
ጥዋ ከመጣ ሰው ላይ በዝርዝር ቢረዳውም "ኢጂብሺያን ሞኒተር"
የሚባለው ጋዜጣም ዐልፎ ዐልፎ ወሬውን ብልጭ ማድረጉ
ባይቀርም ፣ ከዲቩ ለራቲብ ፓሻና ለልጁ ለሐሰን ባንድ ወገን "መል
ካም ነው ምርኮኛውን በሙሉ ከተማረከው የጦር መሣሪያ ጋር የሚ
መልስልን ከሆነ አገሩንም እንለቃለን ፣ ዕርቁን እንፈልጋለን ብላችሁ
መልስ ስጡ" የሚል ትእዛዝ እያስተላለፈ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተሸን
ፈናል ማለቱ እየቆጨው ፣ "ምኒልክ ወደ ዐድዋ ዮሐንስን ለመ
ውጋት የመጣ እንደሆነ የጠየቀውን የጦር መሣሪያ ስጡ ። የቀሩትም
የቤገምድሩ ራስ ወሬኛ ፣ የሰቆጣው ዋግሹም ከበደ ፣ የሰለዋው
ራስ ኃይሉ ፣ የወሎው ይማም አህመድ በዮሐንስ ላይ ተባብ
ረው የሚነሡበትን መንገድ ፈልጉ ።እንደዚሁም ለምኒልክ መገዛት
አንፈልግምና የግብጽ መንግሥት ይጠብቀን ብለው የራያና የአዘቦ
ከደቡብም የጅማ ፣ የጐማና የእናርያ ባላባቶች የላኩዋቸውን መልክተ
ኞች በሚገባ አስተናግዳችሁ ፣በጋላባትና በጐጃም በኩል አድር.ጋ
ችሁ ፣ ከነርሱ ጋር መልካም ግንኙነት ፈጥራችሁ በዮሐንስ ላይ ሁሉም
እንዲያብሩ ማድረግ ነው ። በዚህ ዐይነት ዮሐንስ ከኛ በኩል የሚጠ
ይቀውን የዕርቅ አሳብ እምቢ ብሎ ምርኮኛውን ከተማረከው የጦር
መሣሪያ ጋር ካልመለሰ ፣ ባንድ ወገን የዕርቅ መንገድ የምትፈልጉ
እየመሰላችሁ በሌላ ወገን እነዚህን ሁሉ ማስተባበር ነው ። ከሁሉ የበ
ለጠ ራስ ወልደ ሚካኤልን ውስጥ ውስጡን በመሣሪያ ትጥቅና በስ
ንቅም እንዲጠናከር እያገዛችሁና እያበረታታችሁ አደርጁት ። አሁንም
400 ጠመንጃ ከነጥይቱ እንድትሰጡት ፈቅጃለሁ"የሚል ትእዛዝ ለራ
ቲቭ ፓሻ እያከታተለ ይጽፍ ነበር ።



ዐፄ ዮሐንስ ፣ በግልጽ በሜዳ ላይ ጦርነት ድልን እንዳገኙ እሁ
ንም በሐቀኛ መንገድ ሰላም ሲፈልጉ ፣ የራቲብ ጦር ግን የሜዳው
ጦር ሳይሆንለት ቀርቶ በምሽጉ ውስጥ ተደብቆ እንዳስቸገረ ሁሉ
የዕርቁንም መንገድ የሚፈልገው በድብብቆሽ ፣ በተንኮልና በማጭበርበር
መንገድ መሆኑ ግልጽ ነበር ። በኢትዮጵያ ጦር ተሸንፈን ታሪቅን
ማለቱ የማይዋጥ ጉርሻ ስለ ሆነባቸው ፣ የጦርነቱን ጉዳይ ራሳቸው
ያልቻሉትን በንጉሠ ነገሥቱ ላይ ለጊዜው ባፈነገጡ የኢትዮጵያ ባላ
ባቶችና ይልቁንም ከብዙ ጊዜ ዠምሮ የነርሱን ድጋፍ ባገኙት በወ
ልደ ሚካኤል በኩል ለማጥቃት ተመኙ ። ይሁን እንጂ ፣ ከወልደ ሚካ
ኤል በቀር የቀሩት ውስጥ ውስጡን ዐልፎ ዐልፎ መላላካቸው ባይቀ
ርም ፣ በመጨረሻ የዮሐንስ አሸናፊነት ተስፋ እያስቆረጣቸው ወደ እሳ
ቸው ለመግባት ግዴታቸው ሆኗል ። እስከ መጨረሻ ያፈነገጡት
ራስ ወሬኛ (ወልደ ሥላሴ) በራስ አዳል ተሸንፈው ሲታሰሩ ምኒል
ልከም ወዳፄ ዮሐንስ ሲገቡ ወደፊት እናነባለን ።

የሆነ ሆኖ ፣ ካፄ ዮሐንስ በኩል ሊቀ መኳስ ወርቄና እነ ደስታ ፣
ከራቲብ ፓሻ ወገን ከመሐመድ ሪፋት ወዲህ ዐሊ አፈንዲ አል ሩቢ
የሚባለው የፈረሰኛ ሹም ተልኮ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ መጥቶ የስምም
ነቱ ንግግር ተደረገ ። የግብጾቹ መሪዎች እንደ ላኩትም ምርኮኛ
ውን ፣ የተማረከውን መድፍና ጠበንጃ በሙሉ መልሱልንና ሐማ
ሴንን ለቀን ወደ ምጥዋ እንመለሳለን አለ ። ዐፄ ዮሐንስ ግን
ይኸንኑ ከመኳንንቶቻቸው ጋር ሲወያዩ "ምርኮኛው ፣ ግድ የለም
ይመለስላቸው ። ነገር ግን ከኛ ወገን ብዙ ወታደር ሞቶብን
እሁን የሞትንበት የጦር መሣሪያ ምንም ቢሆን አይመለስም ፤
ያውስ ቢሆን ጠመንጃው ከየማረከው ወታደርና ሹም ላይ እንዴት
ይሰበሰባል"ብለው መኳንንቱ በጥብቅ ስለ ጠየቁ ፣ንጉሡም አሳባቸ
ውን ደግፈው"ምርኮኛውን እንለቅላችኋለን ፣ የተማረከውን የጦር መሣ
ሪያ ግን አንመልስም" የሚል መልስ ሰጡ ።

ይህ የዕርቅ ድርድር በሚደረግበት ጊዜ ፣ ባንድ ወገን ደጃች ወልደ
ሚካኤልን በጦር መሣሪያና በገንዘብ ውስጥ ውስጡን በምስጢር እያ
ደራጁ በሌላ ወገን ላፄ ዮሐንስና ለነራስ ባርያው ፣ ለነራስ አርአያ ፣ ለነ
ራስ አሉላ የሰላምና የወዳጅነት መልክ ያሳዩአቸው ነበር ። አንዳንድ
የግብጽ የጦር ክፍል ከጉራዕ ምሽግ እየወጣ ወደ ቀይሀኮር ፣ ከቀይሀ
ኮር ወደ ምጥዋ ሲጓዝ ዝም ብለው የኛዎቹ አሳልፈውታል ። ከምጥ
ዋም የቆሰሉት ወደ ካይሮ ተሸኝተዋል ። በሚቀጥለው ጊዜ መሣሪያ
ውም ቢቆይ ወደፊት ንግግር እንደሚደረግበት ለጊዜው ግን ፣ እስረ
ኞቹ እንዲለቀቁ መልዕክት ተለዋውጠው ምርኮኞቹ በሊቀ መኳስ

ወርቄ ምርጫ አማካይነት ወደ ራቲብ ተላኩ ። ለሊቀ መኳሱ የተሰጠው መመሪያ ፣ "ሐማሴንን እንዲለቁ ካስፈረጠ በኋላ ምርኮኞቹን እንዲያስረክብ ሲሆን ፣ ግብጾቹ ግን በማጭበርበር ምርኮኞቹን ካገኙ በኋላ ፣ ቁጥራቸው እንዳልተሟላና ሲሟላ እንደሚፈርሙ በመግለጽ ጊዜ ስለ አራዘሙ ታላቅ ውዝግብ ተፈጥሮ ነበር ።

የሆነ ሆኖ ፣ በዚሁ የቃል ስምምነት በጉራዕ ምሽግ ተከቦ ተቀምጦ የነበረው ልዑል ሐሰን ከምሽጉ ወጥቶ ወደ ካይሮ ተመለሰ ። እሱን ለማስለቀቂያ የግብጽ መንግሥት ላዔ ዮሐንስ የከፈለውን ገንዘብ የተለያዩ መጻሕፍት የተለያየ ቁጥር ይሰጣሉ ። [1]

የግብጽ መንግሥትም የቃሉን ስምምነት መፈረም ቅር ቢለውም፣ ሐማሴንና አካለጉዛይን እየለቀቀ ወደ ምጥዋ ፣ ወደ ምንኩሉ ስለ ጠቀለለ ፣ በዚሁ አካባቢ ያዔ ዮሐንስ ግዛት እየተጠናከረ ሔደ ።ለሐማሴን ግዛትም የጸሐዘጋውን ባላባት ደጃች ኃይሉ ተወልደ መድኅንን (የፈረስ ስማቸው አባ ኃባል የሆነውን) ሾመው በዐድዋ ከተማቸው ተቀምጠው ከግብጾች በኩል የስምምነቱን ሁኔታ ሲጠባበቁ ግብጾቹ እስረኞቻቸውን ካገኙ ወዲህ ፣አንድ ጊዜ የምርኮኞቹ ቁጥር አልተሟላም በሚል ሰበብ ፣ሌላ ጊዜ ደግሞ ከካይሮ ትእዛዝ የሚጠብቁ በማስመሰል ምክንያት እየሰጡ ሲያራዝሙ ውስጥ ውስጡን ግን ፣ የደጃች ወልደሚካኤል ገዥነት በሐማሴን እንዲጠናከር ማድረጋቸውን እንደ ቀጠሉ ነበር ።

በዚህም ጊዜ ወደ ምጥዋና ወደ ካይሮም የሚላኩትን ያዔ ዮሐንስን መልክተኞች ሊቀ መኳስ ወርቄን ፣ አቶ ደስታንናን የዐድዋውን አቶ ገብረ እግዚአብሔርን ግብጾቹ በግብዣም ፣ በስጦታም እያስተናገዱ ለንጉሡም ያማረውን የልዑል ሐሰንን ድንኳን እንደ ገጸ በረከት አድርገው ላኩላቸው ። ዐፄ ዮሐንስም በበኩላቸው የግብጾቹን መላክተኞች እነ ዐሊ አል ሩቢን እየሸለሙ ለጊዜው ተረቆ የነበረው የንግድና የወዳጅነት ውል ግብጾቹ ምክንያት እየሰጡ በማራዛማቸው የተነጣ እንደዚሁ ተንጠልጥሎ ቀየ ።

ኢስማኤል ፓሻ ፣ በጠቅላላው የፊት ለፊት ጦርነቱንም ማሸነፍ አልቻለም ። በሐቅ መንገድ መሸነፉንም አምኖ የሰላም ውል ማድረጉንም አላወቀበትም ። ያዋጣኛል ብሎ ያመነበት የተንኮልና የማጭበርበር ዘዴውም አልጠቀመውም ። እርሱና የጦር መሪ አድርጎ የላከው

1 J.B. Coulbeaux, Histoire Politique et Relgieuse d'Abissinia, pp. 446—46 7



ራቲብ መሐመድ ፓሻ ፣'ባንድ አፍ ሁለት መላስ' እንደሚባለው ፣ ባንድ ወገን የሰላም ድርድር በቃልም ፣ በጽሑፍም ወደ ዐፄ ዮሐንስ እየላኩ ፣ በሌላ በኩል ደጃች ወልደሚካኤልን ማጠንከራቸው ፣ ይኸም እንዳይታወቅ ለወልደ ሚካኤል "ደጃች ኃይሉን እንዳትወጋ"ብለው ለይስሙላ ከጻፉ በኋላ ፣ በጐን "ስናብል ነው ፣ ደብዳቤውን ከምንም አትቁጠረው" ብለው መጻፋቸው ፣ የመንፈሳቸውና የሞራል ዝቅተኝነታቸው በግልጽ ይታያል ።

# ምዕራፍ ዐሥራ አምስት

## ለሥልጣን ጨበጣ የጦር መሣሪያ መፍትሔነት—
## የንጉሥ ምኒልክ ለዐፄ ዮሐንስ መገበር

በኢትዮጵያም ሆነ በሌላውም አገር ፣ አንድ የበላይ አስተዳዳሪ ሥልጣኑ በሰላም ከልጅ ወደ ልጅ በዘር የሚተላለፍበት ሕጉና ልማዱ ከፈረሰበት ፣ ወይም የዚህ ዐይነት ሕግና ልማድ በፍጹም ከሌለ ወደ ሥልጣን ለመውጣት ያለው መፍትሔ የወታደር ኃይል ነው ። በዚህም ጐን የመሪው ጽናቱ ፣ ዘዴው ፣ ጀግንነቱ ፣ ብልህነቱ በተጨማሪ አስፈላጊ መሆኑ አይካድም ።

ባለፈው እንደ ጠቀስነው ፣ ቴዎድሮስንም ተክለ ጊዮርጊስንም ፣ ዐፄ ዮሐንስንም ወደ በላይ ገዥነት ያደረሳቸው የየግል ኃይላቸው ነበር ። ይኸውም ማለት በእጃቸው ያለው የጦር መሣሪያና በጦር መሣሪያ የታጠቀው የወታደር ኃይል መሆኑ አይጠረጠርም ። በግራኝ አህመድ ጊዜም ወረራን ፣ ጥቃትን ፣ እልቂትን ያስከተለው የጠበንጃ ጉድለት ነበር ። ግራኝም ራሱ መልሶ በፖርቱጋሎች የተጠቃው በመሣሪያ ልዩነት መሆኑን ለመረዳት አዳጋች አይሆንም ። የሰይፍ ፣ የጐራዴ ፣ የጦርና የጋሻ ጊዜው ያለፈበት መሆኑን በዘመኑ የነበሩት መሪዎች በደንብ ገብቷቸዋል ። በመቅደላው ጦርነት ዐፄ ቴዎድሮስ በእንግሊዝ ፊት የተሸነፉት ፣ በመሣሪያ ልዩነት ነበር ። ራሳቸው ዐፄ ዮሐንስ በቅድሚያ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስን ከዚያም አከታትለው ሁለት ጊዜ ግብጾችን አሸንፈው የመለሱት ፣ የእንግሊዝ ጦር አገሩን ከመቅደላ ወዳ ገሩ ሲመለስ በተወላቸው ዘመናዊ ጠበንጃና መድፍ መሆኑን ንጉሠ ነገሥቱ በየደብዳቤዎቻቸው ገልጠውታል ። ስለዚህ በሕዝብ ከመወደዱ ጐን ፣ በዚያን ጊዜ ሥልጣን ለመያዝና በሥልጣንም ላይ ለመቆየት ዘመናዊ መሣሪያ ዋና መፍትሔ መሆኑን ዐፄ ቴዎድሮስ በግልጽ ቢረዱትም ፣ ራሳቸው ባገራቸው መሣሪያ ለማምረት የወረሱት ኢንዱስትሪ አልነበረም ። የጦር መሣሪያ ማምረቻ ፋብሪካ ለማቋቋምም አል ቻሉም ።

ንጉሥ ምኒልክ ከመቅደላ አምልጠው ወደ ሸዋ ሲገቡ ፣ ምንም እንኳን የዘር ሐረጋቸውን የሚሰቡት ከላይ ከልብነ ድንግል ከመሆኑ

ጋር በቅርቡም በቀጥታ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ የኃይለ መለ
ኮት ልጅ በመሆናቸው የሸዋ ሕዝብ ፡ መስፍንነት የሌላቸውን የዠግ
ናውን የበዙ አባ ድክርን የጦር ጐራ እየተወ ወደ ርሳቸው መገልበ
ጡን ባይስቱትም ፡ የሸዋን ግዛት ካጠባበቁ በኋላ ወደ ደቡብና ወደ
ማኸል ኢትዮጵያ መስፋፋት የቻሉት ፡ ከጣሊያኖችም ከፈረንሳዮችም
በኩል ባገኙት ጠበንጃና ጥይት መሆኑን በግልጽ ዐውቀውታል ።ስለ
ዚህም ከፈረንሳይም ከኢጣልያም አገር የመጣ የውጭ አገር መልክ
ተኛ ወይም መላከተኛውን የላከው የውጭ አገር መሪ በፊታቸው
ሞገስ የሚያገኘው የጠመንጃና የጥይት ገጸ በረከት ያበረከተላቸው ፣
ወይም በገንዘባቸው ገዝቶ ይዞላቸው እንደሚመጣ ቃል የሚገባላ
ቸው መሆኑን ብዙ ጸሐፊዎች ጠቅሰዋል ። [1]

ምኒልክ ፡አባ ታጠቅ ካሳ ራሳቸውን ከመግደላቸው 3 ዓመት
በፊት ፣ በ1857 ዓ.ም ወደ ሸዋ ከገቡ ወዲህ ፡ በተለይ ያፄ ቴዎድሮ
ስን መሞት ከሰሙ በኋላ ራሳቸውን በራሳቸው ንጉሠ ነገሥት አሰኝ
ተው በሸዋ ላይ ወሎን ጨምረው ወደ በጌምድርም ፡ ወደ ጐጃምም
ብቅ እያሉ እነዚህን ታላላቅ የአማራ አውራጃዎች ለማስገበር ሞክ
ረዋል ። ሸዋ በተመለሱ በሁለተኛው ዓመት በ1859 ዓ.ም ከቤገምድር ፡
ከአገው ፡ ከየጁ እየመጡ የእነ ደጃች ወሌ ፡ የእነ ደጃች መንገሻ አቲ
ከም ፣ የእነ ደጃች መሸሻ ወርቂ መግባት ወደ ደቡብና ወደ ሰሜን ምዕ
ራብ ፡ ወደ ምሥራቅም ወደ የጁ ጊዜያዊ የሆነ የመስፋፋት ሙከራ
ለማድረግ አግዟቸዋል ። የአውሳውን ባላባት መሐመድ አንፋሪን ፡ የዘ
ይላውን ጌታ አቡበከርን በወዳጅነትና በስጦታ በመሳብ አቀረቧቸው።
በነዚህ አማካይነት መሣሪያም ፡ ሸቀጥም ከአውሮፓ በማግኘት የራ
ሳቸውን ጦር ከአማራውም ፡ ከኦሮሞውም እየመለመሉ በሹመት በማ
ሳደግ መንግሥታዊ አቅዋማቸውን ለማደራጀት ሞክረዋል ። በዚህ
ምክንያት ፡ ዐፄ ዮሐንስ ከነገሡበት ከ1864 ዓ.ም. ዠምሮ እስከ 1870
ዓ.ም. ድረስ ሰባት ዓመት ሙሉ ላፄ ዮሐንስ ሳይገብሩ የሥልጣን
ተፎካካሪና የዙፋን ባላንጣ ሆነው ተቀምጠዋል ።

ይኸም ማለት ባንዲቷ አገር በኢትዮጵያ ሁለት ነገሥታት ነበሩ
ማለት ነው ።

ነገር ግን ፣ እስከ 1870 ዓ.ም. የዙፋን ባላንጣ ሆነው በቆዩት
በዮሐንስና በምኒልክ መካከል በጦር መሣሪያና በወታደር ድርጅት
በኩል ያለው ሲመዛዘን ፡ ከንጉሥ ምኒልክ ያፄ ዮሐንስ በጣም በልጦ ፣

1 Angelo del Boca, Gli Italiani in Africa, pp. 127—133.



ይገኛል ። የርሳቸውም የጦር ኃይል ምንጩ ልዩ ልዩ ነበር ። አንደኛ
የትውልድ አገራቸውና ሥልጣናቸው የተስፋፋበት የትግራይና የምድሬ
ባሕሪ አውራጃ ለምጥዋ ወደብ ስለሚቀርብ ፣ምንም እንኳን የቱርኮ
ቹና የግብጾቹ ቁጥጥር ቢኖርም በወደቡ አማካይነት በየጊዜውና በየ
አጋጣሚው የጦር መሣሪያ ለመሰብሰብ ቀንቷቸዋል ። በዚሁ መካከል
ዤኔራል ናፒየር ሲመለስ የተወላቸው ዘመናዊ 12 መድፍና ቁጥሩ
የበረከተ ጠበንጃና ጥይት በዚያ ሰዓት ላለ ኢትዮጵያዊ መስፍን
በቀላሉ የሚገመት አይደለም ።

ከዚያ ቀጥሎ በ1864 ዓ.ም በዚሁ ዘመናዊ መሣሪያ ዐፄ ተክለ
ጊዮርጊስን በጦርነት ያሸነፉለት የማረኩት ብዛቱ ያልታወቀ ፣ ዘመና
ዊነት የሌለው መድፍና ጠበንጃ ፣ በኋላ ደግሞ ፣ ግብጾችን ሁለት ጊዜ
ተዋግተው ያሸነፉ ጊዜ የማረኩት መድፍና ጠበንጃ የርሳቸውን የጦር
ኃይል ከቀን ወደቀን አበርትቶ በዚያን ሰዓት ማንም ኢትዮጵያዊ
መስፍን ከፊታቸው ሊቆም እንደማይችል አድርጓቸዋል ። በጦር ድር
ጅቱ ጐን ካፄ ተክለ ጊዮርጊስም ፣ ከግብጾችም በምርኮ ያገኙት ወር
ቅና የማሪያ ትሬዛ ብር በሀብት በኩል ግምጃ ቤታቸውን ሞልቶታል ።
ይኸም ብዙ መኳንንትን በስጦታ ፣በሽልማት ለመሳብ አገልግሏቸዋል ።

በዚህም ላይ ከዚህ በፊት እንደ ጠቅስነው ፣ የምኒልክ ያለ ጳጳ ስ
በገዛ እጅ መንገሥና ያፄ ዮሐንስ እንደ ደንቡ በጳጳስ እጅ ተቀብ ተው
በስመ ጥሩይቱ ከተማ በአክሱም በወግና በሥርዓት መንገሥ ራሱ
በሕዝብና በቤተ ክህነት ፊት የሚሰጠው ግምት ልዩ ስለሆነ ፣ በዮሐንስ
አንጻር የምኒልክ የነጋሢነት አቅዋም የላላ ነበር ማለት ይቻላል ።
በዚህም ላይ በ1870 ዓ.ም. ምኒልክ በብዙ ጥረት ያቋቋሙት የሸዋና
የወሎ ግዛታቸው በፖለቲካና በሃይማኖት ረገድ የመናጋት አደጋ
አግኝቶታል ።በሸዋ በዕርቅ ገብተው የደጃዝማችነት ማዕረግ የተቀበ
ሉት መሸሻ ሰይፉ የሸዋን ዙፋን በመመኘት ካፄ ዮሐንስ ጋር በመ
ላላክ ላይ ይገኙ ነበር ። በአባ ሰላማና ባፄ ቴዎድሮስ ዘመን የተጠ
ቁት ፣ የጸጋ ልደትን የሚደግፉት ያንኮበርና የሚጣቅ አጋማሾቹ ሊቃ
ውንት 'በርታ ያንተ ነን' እያሉ ይደግፏቸው ነበር ። በሌላ በኩል ደግሞ
ምኒልክ መሣሪያ ለማግኘት ሲሉ ከፈንንጆቹ ከነ አባ ማስያስ ፣ ከነ
ሙሴ አርኑ ጋር ጧት ማታ እየተገናኙ መወዳጀታቸውን የተመለከቱ
የተዋሕዶ ሊቃውንት ፣ "እርስዎ መጥተው የአባትዎን የማርቆስን ሃይ
ማኖት ቢያቀኑልን ነው እንጂ ፣ ዐፄ ምኒልክማ ፈረንጅ ይሁን ፣ ሦስት
ልደት (ጸጋ)ይሁን አይታወቅም በቶሎ ይምጡልን" እያሉ ከመርድ—አዝ
ማች ኃይሌ ወገኖችና ከወይዘሮ ባፈና ጋር ውስጥ ውስጡን ወደፄ ዮሐንስ

ይላላኩ ነበር ። እንደዚሁም በወሎ የእንጀራ ልጃቸውን ማንአለብሽን ድረው በሥልጣን ያጠናከሯቸው መሐመድ ዐሊ የዮሐንስን ብርታት ተመልክተው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ገብተዋል ።

ስለዚህ ፡ ከ1864 — 70 ዓ.ም ድረስ ያለው የሰባት ዓመት ጊዜ በመዛዛትና በመሰላለል እንዳለፈ ፡ ዮሐንስ እነ ደጃች ወሌን ፡ እነ ደጃች መሻሻ ሰይፉን ፡ እነወይዘሮ ባፈናን (የምኒልክን ባለቤት) እና ሊቃውንቱን በምኒልክ ላይ ለማሸፈት ሲጥሩ ፡ ምኒልክም ያፄ ዮሐንስ ጐራ እንዲዳከም ከሸፈተው ጋር ሁሉ ሲላላኩ ቆይተዋል ። ዐፄ ዮሐንስ እላይ በጠቀስነው ኃይላቸው በመተማመን ሁሉ ሲገብርላቸው የንጉሥ ምኒልክ ወደኋላ መቅረት ዕረፍት ስለ ነሣቸው ፡ በ1870 ዓ.ም "ምታ ነጋሪት ፡ ክተት ሠራዊት" ብለው ምኒልክን ለማስገበር ከዐድዋ ወደ ሸዋ ጉዞ ዠመሩ ። ከርሳቸውም ጋር የጐጃሙ ራስ አዳልና የወሎው መሐመድ ዐሊ አብረው እንዲያውም ግንባር ቀደም ሆነው ዘምተዋል ። ሆኖም የክርስቲያን ነገሥታት ለጦርነት መዘጋጀት በያለበት ስለ ተሰማ ፡ በነገሩ ብዙዎች ሊቃውንት አዝነውበታል ። ስለዚህም በአጽቢ ደራ በበረሃ የሚኖሩ የበቁ መነኮሳት * ከመካከላቸው አባ ገብረ ጻድቅንና አባ አኑን የሚባሉትን መርጠው ወደ ሁለቱም ነገሥታት ዘንድ ላኩ ። እነዚህም በቅድሚያ ከመነኮሳቱ ዘንድ ተልከው ወደ ንጉሥ ምኒልክ መጥተው ፡"..... ታረቁልን የክርስቲያን ደም በከንቱ አይፍሰስ. . ሁለታችሁ በፍቅር አንድነት ብትሆኑ ወንድማማች ሆናችሁ እንደ አብርሃና አጽብሐ በሰላም ትገዛላችሁ"[1] ብላችሁ በቅድሚያ ለንጉሥ ምኒልክ ንገሩ ፡ የንጉሡንም ልብ ካገኛችሁ በኋላ ወዳፄ ዮሐንስ ገብታችሁ መከራችሁ አስታርቁ" ብለውናል ብለው ተናገሩ ። ምኒልክ እሺታቸውን ካስታወቁ በኋላ ፡ እነዚህ ከከበሩት መነኮሳት የተላኩት አስታራቂዎች ወዳፄ ዮሐንስ ሔደው ይኸንኑ ነግረው ፡ እሺ አሰኝተው እንደ ተመለሱ ስለ ዕርቁ ዐይነት ካፄ ዮሐንስ በኩል በኸርሮንድ ለውጤ ፡ ከንጉሥ ምኒልክ በኩል በጅሮንድ ወርቄ ተወክለው በመልካም ስሜት የዕርቁን ጉዳይ ሲላላኩ ሳለ፣ በመካከሉ ዐፄ ዮሐንስ ከነጦራቸው ከትግራይ ወደ ወሎ ከዚያም በግሼ በኩል ዐልፈው መንዝ መግባታቸው ስለተሰማ ፡የዕርቁ ነገር

---

* የአጽቢ ደራ ገዳም የሚገኘው በደራ (በክልተ አውላዕሎ) አውራጃ ውስጥ ነው ። ዘውዴ ገ/ሥላሴ ግን በገጽ 92 ላይ መልዕክተኞቹ የተላኩት ከአብርሃ ወአጽብሃ ገዳም ነው ይላሉ ፤ ይህም ሥፍራ የሚገኘው በክልተ አውላሎ አውራጃ ውስጥ መሆኑን ገልጸዋል ።

1 አብርሃና አጽብሐ በአራተኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ ወንድማማች በፍቅር ፡ በሰላም አክሱምን በነገሥታትነት ያስተዳደሩ ናቸው ። ጸ.ት ገ/ሥ ፡ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ገጽ 79—81



እንደ ፈረስ ተቆጥሮ ንጉሥ ምኒልክ በአንጐለላ (ደብረ ብርሃን አጠገብ) የጦር ሰልፍ አድርገው ዋሉ ። በሰልፉም ጊዜ ከሸዋ መኳንንት አንዳንዱ ፉከራውን እያንደቀደቀው ለአምስት ስናድር ለዐሥር ስናድር 'ተዋሰኝ' እያለ ሲፎክር ዋለ ። *

በዚሁም ጊዜ ፡ የዐፄ ዮሐንስ ጦር ግንባር ቀደሙ ከመንዝ ዐልፎ ድንባሮ በደረሰ ጊዜ ፡ የሸዋ ጦር ፈረሰኛው ከትግሬ ፈረሰኛ ጋር ውጊያ ዠመረ ።አቤቶ ባሻህ አቦዬ ፡ የንጉሥ ምኒልክ አክስት የወይዘሮ አያህሉሽም ልጅ ፡ በደም ፍላት ሔደው ተዋግተው ብዙ ሰው ገድለው ስናድር ጠበንጃ ማርከው ተመልሰው ለምኒልክ ግዳይ ጣሉ ። በዚሁ ጊዜ ፡

"ላሥር ስናድር ፡ ላምሳ ስናድር ዋስ የጠራችሁ ፡
በሻህ አቦዬ ከፈለላችሁ"

ተብሎ ተገጥሟል ። [1]

ዐፄ ዮሐንስም ፡ በትዕቢት የሸዋን ጦር በኃይል ልደምስስ የሚል ስሜት አላደረባቸውም ። ንጉሥ ምኒልክም በበኩላቸው የኃይላቸውን መጠን በመገመት ፊት ለፊት የዐፄ ዮሐንስን ጦር ስመግጠም አልደፈሩም ። ብዙ ጊዜ ምኒልክ በማናቸውም ረገድ የራሳቸውንና የጠላታቸውን ኃይል ሳያመዛዝኑ በእልህ ወይም በችኮላ ዘለው ወደ ጦርነት አይገቡም ። በዝግጅት ጉልበታቸውን እያጠናከሩ ሁኔታውን አመዛዝነውና የሰላም መንገድም በትዕግሥት ሞክረው አልሆን ሲላቸው ውጊያውን የዠመሩ እንደሆነ እንደማይሸነፉ ሆነው አጥብቀው ይዋጋሉ ። በንጉሠ ነገሥትነት ዘመናቸውም ፡ በየትኛውም የጦር ግንባር ካገር ተወላጅም ፡ ከውጭ አገር ሠራዊትም ጋር ተዋግተው የተሸነፉበት ጦርነት የለም ።

ስለዚህ ፡ ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስ እላይ እንደ ዘረዘርነው ቁጥሩ የበረከተውንና በደንብ የታጠቀ ጦራቸውን ይዘው ሸዋ ሲገቡ ለማስገበር እንጂ ፡ለሰላምና ለወዳጅነት ጉብኝት እንዳልመጡ ሲያውቁት ምኒልክ የነበራቸውን ለድል አድራጊነት የማያስተማምነውን ጦር ይዘው ከመግጠም ተቆጥበዋል ። በዚህ ምክንያት በመጨረሻ ካፄ ዮሐንስ ወገን ደጃች ዋሕድ * * መምህር ገብረ ሥላሴ ፡ በጅሮንድ

---

* ስናድር ጠበንጃ ሸዋዎቹ የሌላቸው ባፄ ዮሐንስ ጦር እጅ ያለ በዘመኑ ወታደርን የሚያስጐመጅ ጠበንጃ ስለሆነ ተዋግቼ 5 ወይም 10 ማርኬ አመጣለሁ ለማለት ነው ።

1 ሳይጠረዝ በብትን የቀረው የብላቴን ጌታ ኅሩይ መጽሐፍ ፡ ገጽ 95 -96 ።

* * ደጃች ዋሕድ ያባታቸው የሹም ተምቤን ምርጫ ወንድም ናቸው ።

ለውጤ ፤ ከንጉሥ ምኒልክ ወገን የአንኮበር ሚካኤል አለቃ ምላት ፤ ያንኮበር መድኃኔ ዓለም አለቃ ሥነ ጊዮርጊስና የሚጣቅ ተክለ ሃይማኖት ገዳም መምህር አለቃ ሐሴቱ (ዕሴቱ) ከመኳንንት ደጃች ናደው በሁለቱም ነገሥታት መካከል የሽማግሌ አስታራቂ ሆነው ወዲያና ወዲህ በሚሉበት ፤ ጊዜ በዚሁ ሰሞን በሽዎች በኩል የነበረው የምክክሩ ዋና ፍሬ ነገር “እንዋጋ ወይስ እንገብር” የሚል ነበር ። በማናቸውም ቤተ መንግሥት እንደሚደርሰው በንጉሥ ምኒልክ መኳንንት ውስጥ እንደ ደጃች (በኋላ ራስ) ጉበና ፤እንደ ደጃች በሻህ አቦዬ ፤እንደ ደጃች ወሌ ያሉት“እንበለው ይለይልን”ሲሉ እንደነደጃች ናደው ፤ እንደነደጃች መንገሻ አቲከም ፤ እንደነደጃች ገርማሜ ያሉት ደመ በራድና አመዛዛኝ አማካሪዎች በሁለቱ ባላንጣ ነገሥታት እጅ ያለውን የጦር መሣሪያ ልዩነት በመረዳት ፤ “የዐፄ ዮሐንስ ጦር ሠራዊት ቀድሞ ከእንግሊዞች በስጦታ ፤ ቀጥሎ ካፄ ተክለ ጊዮርጊስና ከግብጾች በምርኮ ያገኘው የጦር መሣሪያ ቁጥሩ የበረከተና በኛ እጅ የሌለ ስለሆነ ፤ አሁን በእልህ ብንዋጋ ትርፉ መሸነፍና መዋረድ ነው ።ስለዚህ ከሁሉ የሚሻለው ‘አሁን እሺ ገብረናል’ ብለን እንመልሳቸውና ከዚያ በኋላ ፤ እኛም ወዲያ ወዲህ ብለን የጦር መሣሪያ ከሰበሰብን በኋላ ፤ ‘እምቢ እሻፈረን’ ለማለት የሚያውከን ነገር የለም” ብለው መከሩ ይባላል ።

ንጉሥ ምኒልክ ምንም እንኳን ፤ “ንጉሠ ነገሥት” እየተባሉ እየተጠሩ ፤ “ንጉሠ ነገሥት” የሚል ማኅተም አሠርተው በዚሁ ሲላላኩ ቆይተው ፤ አሁን የባላንጣቸው ንጉሠ ነገሥት ገባር መሆናቸው ነገሩ መራራ ቢሆንባቸውም ፤ እላይ በተጠቀሰው በኃይል ልዩነት ምክንያት ቁጭታቸውን ውጠው የዕርቁን ነገር እሺ አሉ ። ነገሩንም ለማቀዝቀዝ ሲሉ ዕርቁን የፈለጉት ወይም የተመኙት ዐፄ ዮሐንስ ፊት ሳይቀርቡ በመላላክ ያፄ ዮሐንስን የበላይ ንጉሠ ነገሥትነት ዐውቀው ለመመለስ ነበር ። ዐፄ ዮሐንስም ይኸንኑ ሐሳብ በመዠመሪያው ላይ ወደ መቀበል አዘንብለው ነበር ይባላል ። ነገር ግን ፤ ከሰዎቻቸው መከረው ዘክረው ፤ “ተገናኝተን ተነጋግረን በፍቅርና ባንድነት ብንኖር መልካም ነው” የሚል ቃል አጽፈው ለመተማመኛ መስቀልና ሥዕል ጨምረው ፤ በደጃች ዋሕድና በመምህር ግርማ ሥላሴ እጅ ወደ ንጉሥ ምኒልክ እንደገና ላኩ ። ምኒልክም ከመኳንንቶቻቸው ከነደጃች ጉበና ፤ ከነደጃች መንገሻ አቲከም ጋር መክረው “ዐፄ ዮሐንስ በኔ ላይ ክፉ ሥራ ላይሠሩ የማሉና የተገዘቱ እንደሆነ ምላሹን ስትልኩብኝ መጥቼ እገናኛለሁ”ብለው ላፄ ዮሐንስ እንደ መዠመሪያ ግብር እንዲሆን ባለወርቅ ቀብ አልጋና ባለወርቅ ቀብ



ወንበር ፤ አብረዋቸው ለነበሩት ለዕጨጌ ቴዎፍሎስ ግን ፤ ባለወርቅ ቀብ ወንበር ብቻ ገጸ በረከት ጨምረው ላኩ ።

ዐፄ ዮሐንስም ፤ ይኸንኑ እሳብና ገጸ በረከቱን ተቀብለው ምኒልክ በሚቀርቡበት ጊዜ ምንም የክፋት ሥራ ላይሠሩ ይኸውም ማለት ከገቡላቸው በኋላ“ለምን ሸፈትህብኝ’ ብለው ታሰር ፤ ተፈታ ላይሉ ቃላቸውን በመሐላ አረጋገጡ ።[1]

የመሐላው ቃል ምላሹ ከመጣላቸው በኋላ ፤ ምኒልክ በመጋቢት 12 ቀን 1870 ዓ. ም. ከልቼ ከተማ (ደብረ ብርሃንና እንኮበር መካከል) ተነሥተው ወዳፄ ዮሐንስ ሔዱ ። ንጉሠ ነገሥቱም ሰላሌ ግዛት (ጅጅጋ) እንዳሉ የምኒልክን ወደ ሠፈራቸው መጠጋት ሲሰሙ ተቀባዮች ዋግሹም ብሩን ፤ * ደጃች ማሩን ፤ ደጃች ተሰማንና * * ደጃች ዋሕድን ተቀብለው እንዲያጅቧቸው ልከው ራሳቸው ልብስ መንግሥት ለብሰው ፤ ዘውድ ጭነው ፤ በትረ መንግሥታቸውን ይዘው ፤ ወታደራቸውን ቀኝና ግራ አሰልፈው ምኒልክ ሲደርሱ ፤ መድፍ እያስተኮሱ እምቢልታና መለከት እያስነፉ በታላቅ ክብር ተቀብሏቸው ። በዚህም ጊዜ ታላቅ ደስታ እንደ ተደረገ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ሲገልጹ ፤ ከተገናኙ በኋላ የተደረገውን የዕርቁን ዐይነት አልዘረዘሩትም ። የተገናኙበትን ቦታ አንዱ ጸሐፍ ሰላሌ (ጅጅጋ) ሲል ፤ አቶ አጥሜ ወደራ (ሞፈር ውሃ) ብለውታል ። * * *

በቅርብ ጊዜ የታተመው ያፄ ዮሐንስ እንደኛው ዜና መዋዕል “ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ያባታቸው የነገሥታቱ አገር በሆነው በሸዋ ሀገር ላይ ዳግማዊ ምኒልክን አነገሧቸው” በማለት በአጭሩ ጠቅሶ ዐልፎታል [2] ። ይሁንና ደራሲው ያልታወቀና በሙሴ ሼን የታተመው ሌላው ዜና መዋዕል ዐፄ ምኒልክ ለመዋጋት ሠራዊት ከሰበሰቡ በኋላ ፤ የደብረ ሊባኖስን መነኮሳት ወዳፄ ዮሐንስ ልከው እንደ ታረቁና ከፍቅርም የተነሣ ዐፄ ዮሐንስ ዐፄ ምኒልክን እንግሠው ወዳገራቸው መመለሳቸውን ከመጥቀስ በቀር የውለታው ዝርዝር የለም ።[3]

---

1 ሳይታተም የቀረው የብላቴን ጌታ ኅሩይ ጽሑፍ ገጽ 96—97 ።
አቶ አጥሜ ፤ የጋላ ታሪክ ፤ ገጽ 139—140

* ያፄ ተክለ ጊዮርጊስ ወንድም ።

** የሠራዊ ሹም (አቀጽነ ሠራዊ) የገብረ ሚካኤል ልጅ ።

*** ጅጅጋና ወደራ ቅርብ ለቅርብ ይሆናሉ ። ወደራ ሞጆ አጠገብ ነው ።

2 አንገሦ ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት ለዳግማዊ ምኒልክ ወረሰዮ ንጉሠ ሸዋ እንተ ይእቲ መንበረ መንግሥቶሙ ለአበዊሁ ነገሥት . . . B. Tafla (ede.) p.142 Chsonicle oι Emperere Yohannes IV ( 1872-89)

3 በአፈ እሉ ካህናት ወኮነ ፍቅር ወሰላም ማዕከሌሆሙ ወእምብዝኃ ፍቅር ዐፄ ዮሐንስ አንገሦ ለምኒልክ ወተመይጠ መንገለ ሀገሩ . . . M. Chaine Histerre du regne de Yohannes IV Rei d. Ethopie' P. 13

በጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴም ታሪካዊ መጽሐፍ ላይ አይገኝም ። የውጭ አገር ጸሐፊዎች ካቆዩት ማስታወሻ ላይ እንደሚነበበው በመጋቢት14—1870 ዓ.ም የተፈራረሙት የዕርቁ ውል ከዚህ እንደሚ ከተለው ነበር ።

1ኛ/ ንጉሥ ምኒልክ ለዐፄ ዮሐንስ ይገብራሉ ።

2ኛ/ ያፄ ዮሐንስ ጦር በግዛታቸው ባለፈ ጊዜ የሚያስፈልገ ውን ነገር ንጉሥ ምኒልክ ይሰጣሉ ።

3ኛ/ ምኒልክ ለወደፊቱ ንጉሠ ሸዋ ይባላሉ እንጂ ንጉሠ ነገ ሥት መባልን ይተዋሉ ።

4ኛ/ ባስፈለገ ጊዜ ማናቸውንም እርዳታ ንጉሥ ምኒልክ ላፄ ዮሐንስ ይሰጣሉ ።

5ኛ/ ዐፄ ዮሐንስም በዚሁ ዐይነት ማናቸውንም እርዳታ ለን ጉሥ ምኒልክ ይሰጣሉ ።

6ኛ/ ንጉሥ ምኒልክ በሸዋና በአማራ ግዛት * መካከል ያሉ ትን የወሎ ኦሮሞ እስላሞች ይገዛሉ ። (ያስተዳድራሉ)

7ኛ/ ንጉሥ ምኒልክ በወሎ ኦሮሞዎች ውስጥ አብያተ ክርስቲ ያናትን እያሠሩ ክርስትናን ያስገባሉ (ያስፋፋሉ) ።

8ኛ/ ያፄ ዮሐንስ ጦር እስከ ደብረ ሊባኖስ የመጣ እንደሆነ ንጉሥ ምኒልክ በነጻ ያሳልፉታል ። በተገናኙበት ሰዓት ዮሐንስና ምኒልክ መሳሳማቸውንና በዮሐንስ ዙፋን ቀኝ ለምኒልክ ከዙፋኑ ዝቅ ያለ ዙፋን ተዘጋጅቶላቸው እንደነበረ በየመጽሐፉ ተጠቅሶ ይገኛል ። [1]

ከዚህ በላይ ከተዘረዘረው በተጨማሪ አባ ማስያስንና ሌሎችን የውጭ አገር ሚሲዮናውያንን በሸዋ ከምኒልክ ጋር ሆነው የመሣሪ ያና የፖለቲካ ጉዳይ ያካሒዱ የነበሩትን ከሸዋ እንዲያስወጡ ፣ የሸ ዋን የመግቢያ በር ለአውሮፓውያን እንዲዘጉ በማድረግ ንጉሥ ምኒልክ ከነዘራቸው የሸዋ ገዥ መሆናቸውን በይፋ እንዳረጋገጡላ ቸው ራሳቸው አባ ማስያስና አንቶኒዎ ቼኪ አመልክተዋል ። [2]

በእርግጥም ምኒልክ ለላሌ ላይ ከዐፄ ዮሐንስ ጋር ተስማምተው ወደ አንኮበር እንደ ተመለሱ ፣ "ጃንሆይ ይፈልጉዎታል" ብለው አባ

---

* በአማራ ግዛት ያለው አማራ ሳይንትን ለማለት ነው ።
1 Maurice de Coppet, Chronique du Regne de Menelik II, Vol. I, PP. 139—148.
2 L. dei Sabelli, Storia d' Abyssinia Vol. III, PP. 252—259.



ማስያስን ወዳፄ ዮሐንስ እንደ ላኩዋቸውና ዐፄ ዮሐንስም ከትግራይ በሱዳን በኩል ካገር እንዳስወጧቸው እርግጥ ነው ። በዚህም ጉዳይ ንጉሥ ምኒልክ ማዘናቸውን በደብዳቤ ለአባ ማስያስ ገልጸውላቸዋል ። [1] የሸዋን በር ለአውሮፓውያን የመዝጋቱ ነገር ምናልባት ቢነጋገሩበትም ፣ አሳቡ ወይም ትእዛዙ በሥራ ላይ አልዋለም ። ኢጣልያኖች በአሰ ብና በዘይላ ፣ ፈረንሳዮች በሐረርና በዘይላ በኩል ወደ አንኮበር ፣ ወደ እንጦጦ ም እየተመላለሱ የንግድም፣ የወዳጅነትም ግንኙነት ከማድረ ግና መሣሪያም ከማቀበል ታግደው አያውቁም ። ምኒልክም በፊተኛው ዘመን ያደርጉት እንደነበረ አሁንም ላፄ ዮሐንስ ከገበሩ በኋላ ከውጭ መንግሥታት መሪዎች ጋር መጻጻፋቸውንም አላቋረጡም ።

የሆነ ሆኖ በዚሁ ውል መሠረት ፣ ንጉሥ ምኒልክ ያፄ ዮሐንስን ንጉሠ ነገሥትነት ፣ ዐፄ ዮሐንስም የምኒልክን የሸዋ ንጉሥነት አጽድቀው በሰላማዊ መልክ ተለያዩ ። ይኸም በትግሬዎቹ በኩል ደስታ ሲፈጥር ፣ በሸዋዎቹ ዘንድ ደግሞ ቅሬታን አስከትሎ ነበር ። ሁኔታው በጸሐፌ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ ጽሑፍ ተገልጾአል ። እንደዚሁም አቧይ ገብረ ተክሌ የሚባል የትግራይ ተወላጅ ፣ የግራዝማች ዮሴፍ ንጉሤ ጓደኛ ፣ አደንና ዘይላ በመ መላለስ ከፈረንሳዊ መንግሥት ቆንስሎች ጋራ እየተጻጻፈ የንጉሥ ምኒ ልክን ጉዳይ የሚፈጽም አሽከራቸው ነበር ። እርሱም ከ1865 እስከ 1871 ዓ ም ድረስ የፈረንሳዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ለነበረው ለማርሻል ማክማሆ በዚሁ ዓመት ከአደን በጻፈው ደብዳቤ ላይ

ጌታዬ ንጉሥ ምኒልክ ፈረንሳያውያን ብርሃንን ወደ መንግሥታ ቸው ሲያመጡላቸው ማየትን እጅግ ይመኛሉ. በኋለኛው ጊዜ ከሸዋ የመጣልኝ ወሬ ለኔም ምክንያት ሆነልኝ ልንገርዎ ። ጌታ ራስ ሆይ ከብዙ ዘመን ጀምሮ ስምም ያልነበራቸው ሁለቱ የሐበሻ ነገሥታቶች በማይፈርስ ፍቅርና በብርቱ ውል ታረቁ ። የትግሬው ንጉሥ ዐፄ ዮሐንስ ያፄ ምኒልክን ፍቅር ለመፈለግ ሸዋ ሔዱ ። ከዚያም በጠነከረ ዕርቅ ከተፋቀሩ በኋላ የሚበልጠውን ግዛትና ዘውዳቸውን ላጤ ምኒልክ ሰጡ ። እነሆ አበሻ ዐረፈች ። በቦታ ሁሉ መንገድን (ለሚጓዙ) ለሚያደርጉ አውሮፓውያን የሚሰጋ (የሚያሰጋ) ነገር የለም. . . በ11 በሰኔ ። በ1870 እንደ ኢ.ት. ቁ በአደን ከተማ ። ማኅተም ኢትዮጵያ ፀባሀት ገብረ ተክሌ [2]

ራሳቸውም ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስ ከዕርቁ በኋላ ዕርቁን ያል ሰሙ ወታደሮቻቸው ቢዘርፉ ፣ "ከወንድሜ ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ታር ቄያለሁና ወታደር አገር አትዝረፍ ተወኝ" ብለው ዐዋጅ ያናገሩት

---

1 Archivio Storico dei Sopressi Ministero del Africa Italiana Documente. .
2 Ministere des Affaires Etrangeres - Afrique No. 261, Paris

ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው [1] አገባበሩ በጦርነት ሳይሆን በዕርቅና
በስምምነት ስለሆነ "አስገበርሁ" ወይም "ገበርሁ" የሚለውን ቃል
ሁለቱም ወገኖች ለስምምነት ሲሉ ይሸሹታል ማለት ነው እንጂ
ያዬ ዮሐንስ ማስገበር ፣ የንጉሥ ምኒልክ መገበር ግልጽ ነበር ። በምኒል
ክና በጦር አለቆቻቸው ዘንድ ቅሬታ የገባውም በዚሁ ምክንያት
ነው ።በተለይ ሁለቱ በተገናኙበት ጊዜ ምኒልክ ላዬ ዮሐንስ አደግድ
ገው በሰው ፊት ስለታዩ በሸዎች ዘንድ ቁጭቱ አልቀረም ። ስለዚህ
አንድ የሸዋ ገጣሚ ምኒልክ "ንጉሠ ነገሥት" ሲባሉ ቆይተው ያት
ሙበት የነበረው ማኅተም ፈርሶ "ንጉሥ ምኒልክ" በመባል መወሰና
ቸውንና በዮሐንስ ፊት ኩታቸውን ማደግደጋቸውን የተመለከተ እን
ደዚህ ብሎ ገጠመ ።

"ሲሆን ተከናንብ ሳይሆንም አጣፋው ፣
መታጠቅ (ማደግደግ) አይሆንም ለእንዳንት ያለ ሰው ።

እንዴት ያለ ሩቅ ነው ጭንቅ ያለው መንገድ ፣
አሻቅቦ ወጥቶ ወደታች መውረድ ።" [2]

ከዚህም ስምምነት በኋላ ፣ ሁለቱም የበላይና የበታች ሆነው
በየጊዜው በመገናኘትና በመላመድ በተለይ ደግሞ በፀዬ ዮሐ
ንስ ጥያቄ ልጃቸው ራስ አርአያ የንጉሥ ምኒልክን ልጅ ወይዘሮ
ዘውዲቱን ካገቡ ወዲህ ፣ እያደር በሁለቱ መካከል ወዳጅነታቸው እየ
ጸና ሔደል ። ሁለቱ በስምምነት ቦሩ ሜዳ ላይ እየተገናኙ መንግሥት
የሚጸናበትን እየተማከሩ ፣ የሃይማኖት ክርክር በመስማት የክርስ
ትና ሃይማኖት በተለይ ካራ ተዋሕዶ በኢትዮጵያ የሚስፋፋበትን
በመፈለግ እስከ ሺ880 ዓ. ም. ድረስ ዐሥር ዓመት በሰላም ኖሩ ።

ንጉሥ ምኒልክ በኢትዮጵያ የባሪያ ንግድ ስለ መቅረቱ ፣ ግብ
ጾች በሐረርና በአካባቢው ስለሚሠሩት ግፍ ፣ ወደብና የባሕር በር ስለ
ማግኘት ፣ በኢትዮጵያ የአውሮፓን ሥልጣኔ በሰፊው ለማስገባት
ስላላቸው ዕቅድ ለኢጣሊያ ንጉሥ ለኡምቤርቶ በጻፉት ረዥም
ደብዳቤ ውስጥ ". . ካባቱ ከወዳጄ ካዬ ዮሐንስ ጋር ተረቅሁ ። አንድ
አካል አንድ አምሳል ሆነ (ሆነን) ከእንግዲህ በእግዚአብሔር ባንተ
ወንድሜ ፈቃድ የሀበሻ ዓይኑ ይከፈታል ብርሃንም ያያል . . ."
የሚል ቃል ይገኝበታል ። [3] በሌላ ደብዳቤ ደግሞ ፣ ሐረርን ለመያዝ
ቁርጠኛ አሳብ ማድረጋቸውን ለዚሁ ለኢጣሊያ ንጉሥ በጻፉት ደብዳቤ

1 ጸ.ት. ገብረ ሥላሴ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 83 ።
2 አቶ ዐጥሜ ፣ የጋላ ታሪክ የእጅ ጽሑፍ በቤተ መጻሕፍት ወመዘክር ፣ ገጽ 141 ።
3 ተ.ጸ.መ ፣ የግራኝ አህመድ ወረራ ፣ ገጽ 837—839 ።




. . "ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ በእግዚአብሔር ኃይል ቱርኮችን (ግብ
ጾችን) ድል አድርገው ኢትዮጵያን አተረፏት . . " የሚል ቃል አክ
ለዋል ። ይኸ ሁሉ ንጉሥ ምኒልክ ምንም እንኳን እላይ እንዳልነው
"ንጉሠ ነገሥት" ሲባሉ ቆይተው በዚሁ ይላላኩበት የነበረው
"ንገሠ ነገሥት ምኒልክ" የሚለው ማኅተም ፈርሶ ይኸው ምኞታ
ቸው በውል መቅረቱ ቅር ቢላቸውም ፣ ቅሬታው እያደር በጋብቻና
በመልካም ግንኙነት ተፍቆ በመጨረሻ በ1880 ዓ.ም. ላይ በኢጣል
ያኖች ወረራ ምክንያት መልሶ እስኪደፈርስ ድረስ በሁለቱ መካከል
ልባዊ ወዳጅነት ተመሥርቶ ፣ ሁለቱም የኢትዮጵያን አንድነት በሰ
ላም ይገነቡ ዠመር ። ስለዚህም "እናንተ ብትታረቁና ብትስማሙ
እንደ አብርሃና እንደ አጽብሐ ወንድማማች ሆናችሁ በሰላም ትገዛላችሁ"
ሲሉ የአጽቤ ገዳም መነኮሳት የተመኙት የደረሰ ያህል ተቆጠረ ።

በሁለቱ ነገሥታት ትዕግሥት ፣ በነዚህ ሊቃውንት አስታራቂነት
እስከፊው የወንድማማች ጦርነት ባይወገድ ኖሮ ፣ በጠላት ግንባር ሊሰ
ለፍ የሚገባው የሁለቱ ጦር እርስ በርሱ ተላልቆ በኢትዮጵያ ላይ ለሚ
ያደባው የውጭ ጠላት ምቹ የመግቢያ ሁኔታ ይፈጥርለት ነበር ።

ዳግማዊ፡ ምኒልክ፡ ንጉሠ፡ ሸዋ ወከፋ ወዡ
ሉ፡ እጅ ያሚያ ለ-ብሔረ ጋላ ይድረስ ወደ ክበረ ወደ፡
ት ወደደ ንጉሠ ዑምበርቶ ሰጋር መርደ የኢጣሊያ ን
ጉሠ እጅግ እንዴት፡ ነዎ ከኔ ከማዚአብሔር፡ ደ
ጠስንግ ደኅና ነኝ ሠራዊቴም ሁሉ ደኅና፡ነው።
ከኮንት፡ አንቶኔሊ፡ ጋራ፡ የላክሁት፡ ጉደይ፡ሁ
ሉ፡ ቀና፡ ብሎ ኮንት አንቶኔሊ ቢልክብኝ እጅግ
ደስ ብሎኛል እሁንም የአስብኝ መሣሪያ ለአመ
ክሬት፡ እሸክሬን፡ ገብረ ሥላሴንግሬን፡ ብሁ ዕቃ፡
እስዴጋር፡ ሰንጉሥም ጥቂት የጥቅር በረከት፡ከኔ፡
ሠዕል ጋራ እስብ፡ ዱረስ፡ አስዴጋር ልኬዋለሁ።
ደህነንም ጥቂቶኝ የጥቅር ምልክት፡ በረከ
ቴን እንደብዙ አርገው እንዲቀበሉልኝ፡ እለምናለ
ሁ፡ ንጉሥ ሆይ የተረክቹ ጥረዜቶት ለኔ መንግሥ
ት እልበሄም ዕለት ዕለት እጅግ ከየአገሬ ...ዳ፡ከዚ
ህቀደም ተርክቹ ሐረርኄን ዜደዙብኝ፡ ለየውሮፓ፡ን
ጉሥታት ሰጦታ ልኬ ነበር እሁን ደግሞ ለርሰዎ፡ለ
ወንድሞ፡ ሰጦታዎን እልካለሁ። ሐረርኄን፡ ዜደዙ፡
እነሰቸውና እሌፈው እገሬን፡ ወበሬንና ደቱን ለመ
ያዝ መጥተዋል እንግዴህ የተዋጋኋቸው እንደሆኑ
የየውሮፓ ነገሥታት በደለኛ እንዳያደርጉኝ፡ እር
ሰዎ ወንድሜ ምስክሬ ነዎ፡ እገሬን፡ በከንቱ፡ እም
ለት እደደ ለሁም፡ የርሰዎን ምላሽ፡ በብዙ መጽሐፍት
ና በብዙ ናፍቆት እየጠበቅሁ ከእግዚአብሔር፡
ዘንድ እደሜዎን እለምናለሁ። በግንቦት፡ ፳፫ ቀን፡
በ፲፰፻፸፯ ... በደብረ ብርሃን ከተማ ተጻፈ።



**ዐፄ ምኒልክ ለኢጣሊያው ንጉሥ ለዑምቤርቶ የጻፉት**
**(አርኪቪዮ ስቶሪኮ ዴ ሶፕሬሶ ሚኒስቴሮ ዴል አፍሪካ ኢታሊያና ፣ ሮማ)**



## ዐፄ ዮሐንስ ለኢጣሊያው ንጉሥ ለዑምቤርቶ የጻፉት

(አርኪቪዮ ስቶሪኮ ዴ ሰግሬሶ ሚኒስቴሮ ዴል አፍሪካ ኢታሊያና፣ ሮማ)

[illegible]

## ዐፄ ዮሐንስ ለኢጣሊያው ንጉሥ ለዑምቤርቶ የጻፉት

(አርኪቪዮ ስቶሪኮ ዴ ሶፕሬስ ሚኒስቴሮ ዴል አፍሪካ ፤ ኢታሊያና ፤ ሮማ)

መልእክት፡ዘሠዮሙ፡እግዚአብሔር፡ዮሐንስ፡ንጉሠ፡
ጽዮን፡ንጉሠ፡ነገሥት፡ዘኢትዮጵያ፡ይድረስ፡
ኀበ፡ክቡር፡ለእሩቅ፡ኮዳይ፡የእንግዳ፡አገር፡በኢ[illegible]
ያ፡መንግሥት፡ለኢሌክ፡ማንቺኒ፡እንደት፡አለህ፡በዝና
እኔ፡ከሠራዊቴ፡ጋራ፡በእግዚአብሔር፡ቸርነት፡በእም
ጽዮን፡ለማሳጅነት፡አምላክ፡ቅዱሳን፡ደኅና፡ዘር፡
ዴ መክንን፡ደህና፡ነኝ፡ምሕረቱ፡ለዘለዓለም ፡ው
ስለ፡ፍቅር፡ማሳሰብያ፡ይሆናል፡ብዬ፡ማሕተመ፡
ሰሎሞን፡ሰጅ፳ ልኬአለሁ፡በንጉሠ፡ፈቃድ፡አቶ፡
ቢያንኪ፡ካንገትህ፡ይሰርልህ፡አዝዤዋለሁና፡፡
ተጽሕፈ፡በሀሸንጌ፡ከተማ፡አመ፡፲፯ ወ፲፯ ለየ
ካቲት፡በ፲ ወ፷፻፸ ወ፯፡ዓመተ፡ምሕረት

## ፀ፪ ዮሐንስ ለኢጣሊያው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለማንቺኒ የጻፉት

(አርኪቪዮ ስቶሪኮ ዴ ሶፕሬሶ ሚኒስቴሮ ዴል አፍሪካ ኢታሊያና ፣ ሮማ)

ዩቋጣይ ምኒልክ ንጉሥ ሸዋ ወከፋ ወሐረር ወኵሉ ጸ
ዴ ዩሙዓሣ ለበሐይ ጋሉ ይደረስ ከንጉሥ ዑምበርቶ በሰ
ም መዝመርያ ንጉሥ ኢጣልያ ሰላም ለርሰዎ ይሁን።
በትላንት ወሬዋ ሐረርጌን መያዜን ከከተማው ውስጥ ተ
ከሮው ያገኙኋቸውን የየውርሾ ስዎች፤ ከሠራት መውጣቱ
ን ለአጀኑ ለኢጣልያ ቱንስል ለእስብም ቱንስል ልኬ፤ነበር፤
ወደርሰዎ ግን ኩዋ አለመላኪም ለነዚያ ከላኩሁ ይሰመቱ
ል ብዬ ነው። አሁንም ሐረርጌን ስለሁላችን ነጋዴዎች ጥቅ
ም መያዜን የምሠራት እለሁ። ከዚህ የበለጠ ለኢጣልያ፤
መንግሥትና ለሸዋ መንግሥት የሚሆን ሁላት፤ጥቅም ከ
ዙ ተርፉ የሚገኝበት ነገር አለ የዘይላን በር ነገር።
በሚቻልዎ ነገር ሁሉ ተጣጥረው በኔ ዕጅ፤ቢሆን እንዲን
በሐረርጌና በአገሩ፤ በከንበታ በጀማ በከፋ ያለው፤ ንግድ
ሁሉ በዘይላ መንገድ አይርገው ነበር። ስለዚህ ጠንክረው
በየስፍራቱ ቶሎኝ እወዳለሁ። ይህንም ማለቴ ለርሰዎ፤ እንዲደ
ርጋርዎ በውቀው የኢትዮጵያ ልጆች በንጉሥ፤ዑምበር
ቶ ዘመን በንጉሥ ዑምበርቶ፤በርቱ፤ የዘይላ በር ከጀች
ን ተመልሶ ገባ እያሉ እንዲሉ ስምዎ በነገሥታት ታሪክኝ
ን ይገኙ ከለል። በሚያዝያ፤ በ፴ ቀን ተጻፈ በ፲ወ፰፻፸፱ ዓመ
ተ ምሕረት። በእንጦጦ ከተማ።



**ዐፄ ምኒልክ ስለ ሐረርጌ መያዝ ለኢጣሊያው ንጉሥ ለዑ ምቤርቶ የጻፉት**

**(አርኪቪዮ ስቶሪኮ ዴ ሶፐሬስ ሚኒስቴሮ ዴል አፍሪካ ኢታሊያና ፣ ሮማ)**

የተባለ ከንጉሡ ምኒልክ ንጉሠ ሰዋ ወከፋ ወሐረር ወዥሉ ቹ ዩ ደብ ዌ፡ ለብሔሌ ጋሎ ዪ ጁ ሌስ፡ ከመኒስትር፡ ፈ ዘሬር ዜቅ ሬ ንዝር፡ እጅግ እንዴት ነህ፡ እኔ እግዚአብሔር፡ ይመስገን ደኅና ነኝ። ሠራዊቴም ሁሉ ደህና ነው። በተጫሠ ወፈት ሐረርን መያዜን ከኮቱማው ውስጥ ቱሰራው ያገኙትውን ሆየውርም ስዎች ከሠፈተ ማውጣቴን፡ ለእጂኒ ለኢጣልያ ቴ ሃስል ለአሰብም ቴ ሃሰል ሌኬ ነበር፡ ወዲያ ቸ ኩዌ አለመለኪም ለነዚያ፡ ከለክሁቱ ስለምቀለህ ብዬ ነው፡ አሁንም ሐረርጌን ለለሁለ ትን ነጋዴዎች፡ ሞትም መያዜን ሆምሠራች አለለሁ ከዚህ የበለጠ ለኢጣልያ መንግሥት የ ለሸዋ መንግሥት፡ ቱለት ሞቶም ብዙ ትርፍ የሚገኝበት ነገር ደግሞ እለ ይህ ነገር የዘደዐላ፡ ብር ነገር ነው። እኔ በዚህ፡ነገር ወደ ከበፉ ንጉሡ ዑምበርቶ ልኬያለሁ እንተም ከርስቶውጋ ራ ተማክረህ በሚቻልህ ነገር ሁሉ በሬዲህልኝ እወዴ ነበር።

ኮንት አንቶኔሊ ወደ ኢጣልያ መመለሱ በሆንጊለሐዝባቹንና ለሃሬቶን የመልክም ፍቅር እንዳት እስደጊተልኝ ከኛ መለየቱ አጅግ አሰዘነኝ ከንተ አንቶኔሊ ከኛ ዘንዱ የኋመት ስለተቀመጠ ከዚህ ተጁም እልክለሁ ብዬ ወደ ንጉሡ ዑምበርቶ የለክሁት እ ምበስደርኝ ስልክ የተለዘበትን ምክንያት እርሱ ይነግራችኋል፡ መልክተኛ ቴ ጣ ከአንተ ዘገይ ስደመጠ በተራ ዩኔ ፍቅር ከአንተ ተከፊለ ኢይመስለኝ ሁ እለክሁት ፍሪስ ስንለለከው ለነበረ የንግዬ ጉዳዩትን እንዲያቴሪግ ብዬ ከኮንት አንቶኔሊ ጋራ ውል ተዋውያለሁና በንጉሡ ዑምበርቶ ማኅተት ሆኖ የተቀቀለነው ንውል መለኝ ከሁ እነዲያገኘው ያርዩልኝ ብዬ አጻፉ ብያቸዋለሁ እንተም በዚህም ነገር እንዴታረዳኝ ደሁን በተሌ ነገር ፍቅሬ ነም ጉዳዩንም ሁሉ ከነተ አንቶኔሊ ደንገሬሃሁ። በ፲፰፻፸ ዓመተ ምሕረት በግንቦት በ፬ ቀን ተጻፈ። በእንጦጦ ከተማ።



## ዐፄ ምኒልክ ሐረርን ስለመያዙ የምሥራች ለኢጣሊያው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የጻፉት

(አርኪቪዮ ስቶሪኮ ዴ ሚኒስቴሮ ዴል አፍሪካ ኢታሊያና ፣ ሮማ)

# ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት

## የሃይማኖት ክርክር በቦሩ ሜዳ — የመሐመድ ዐሊና የይማም ዐመዴ ክርስትና መነሣት ፣ እስላሞች ክርስትና እንዲነሡ ስለ መገደዳቸው

ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስና የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ፣ ባለፈው ምዕራፍ የተመለከተውን ስምምነት አድርገው ከመለያየታቸው በፊት ፣ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከጐንደር መንግሥት ዠምሮ ፣ ከሊቃውንቱ ዐልፎ ነገሥታትን ፣ መሳፍንትን ሲያጣላና ሲያከራክር የቆየውን ፣ ባፄ ቴዎድሮስም ዘመን ጳጳሱን አባ ሰላማንና የሸዋን ሊቃውንት ሲያበጣብጥ የኖረውን የቅባቶች ፣ የጸጐችንና የካሮችን ክርክር በጉባኤ አስመክረው አንድ ጊዜ ለዘለቄታ ለመወሰን እንዲቻል ሁለቱ ነገሥታት ወደ ፊት ጉባኤውን ለማድረግ ተስማምተው ነበር ።

በንጉሥ ምኒልክ ዘንድ የሃይማኖቱ ጉዳይ በቸልታ ሲታይ ፣ በዐፄ ዮሐንስ ዘንድ ግን ሞቅ ብሎ ይታይ ነበር ። ከዚህም ጋር በመቀሌ ባፄ ዮሐንስ ዘንድ ሊወነጀሉ የተመደቡት የጸጋ መሪዎች እነ አለቃ ተክለ ጽዮን ፣ እነ አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ እንኮበር በምኒልክ ዘንድ የቀረቡ አማካሪዎች ነበሩ ። ዐፄ ዮሐንስንና ምኒልክን አቀራርቦ በማስማማቱ ጉዳይ ከእንኮበር ሚካኤል አስተዳዳሪ ከአለቃ ምላት ጐን የጸጋው ተከታይ የደይ ሚካኤሉ ተወላጅ አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ ይገኙ ነበር ።

ስለዚህ የወደፊቱ ጉባዔ እነዚህን ሁሉ የሚያስጠቃ ጉባዔ መሆኑን ቢረዱትምና ባንድ ወገን ብዙዎቹ የእንኮበር ሊቃውንት እነ አለቃ ኪዳነ ወልድ ፣ እነ አለቃ ወልደ ያሬድ ሁሉ የካራን እምነት በመደገፍ ረገድ ውስጠ ስምምነታቸው ካፄ ዮሐንስ ጋር መሆኑን ባይስቱትም ፣ ምኒልክ የሃይማኖቱ ጉዳይ ሊታይ በተመደበበት ቦታና ጊዜ ፣ እነዚህኑ ባላንጣ የሆኑትን ሊቃውንት በዐዋጅ አሰብስበው ወደ ቦሩ ሜዳ ወሎ ሔዱ ። ጉባኤው ግንቦት 21 ቀን እንዲሆን የተወሰነ ሲሆን ሁለቱ ነገሥታት ቀደም ብለው በግንቦት 15 ቀን 1870 ዓ. ም. ቦሩ ሜዳ ላይ ተገናኙ ። በዚህ ጊዜ ባፄ ዮሐንስ ዘንድ ሊወነጀሉ የተመደቡት አለቃ ተክለ ጽዮን ከእንኮበር ከሌሎች ሊቃውንት ጋር

በሩ ሜዳ መጥተው ንጉሠ ነገሥቱን እጅ ከነሡ በኋላ፣ ቀደም ብለው ከቦሩ ሜዳ ጠፍተው በምጥዋ በኩል ወደ ሮማ ሔዱ ይባላል።

ንጉሠ ነገሥቱና ንጉሡ የየአውራጃው መሳፍንትና ሊቃውንት በተወሰነው ቀን በተሰበሰቡበት በዚሁ ጉባኤ ለሙግት በግራ በኩል ጸጎች፣ በቀኝ በኩል ካራዎች ቆሙ። የካሮች አባባል "ክርስቶስ (ወልድ) ከዓለም ፍጥረት በፊት ከእግዚአብሔር አብ፣ ከዓለም ፍጥረት በኋላ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሥጋውና መለኮታዊ ባሕርዩ ተዋሕዶ አንድ ሆኗል" በማለት በነርሱ ግዕዝኛ አነጋገር "ወልደ አብ ወልደ ማርያም በተዋሕዶ ከበረ" የሚል ሲሆን፣ በጸጎች በኩል ከዓለም ፍጥረት በፊት ከእግዚአብሔር አብ ከዓለም ፍጥረት በኋላ ከድንግል ማርያም መወለዱን ሳይከዱ በተጨማሪ ማርያም መለኮትን፣ እግዚአብሔር አብም ሥጋ ለባሹን መውለድ ስለማይሆንላቸው፣ ሥጋ የለበሰው ክርስቶስ (ወልድ) የእግዚአብሔር አብ ልጅ የሆነው በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀለት ስለሆነ፣ በሰውነቱ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ ሳይሆን የጸጋ ልጅ የሆነው በጥምቀቱ ነው። በዚህ ምክንያት፣ በጥምቀቱ ሦስተኛ ልደት አለው የሚል ነው። በተቀብአ (በመቀባት) ክርስቶስ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጁ ሆነ የሚሉትም ወደ ጸጋዎች ይጠጋሉ።

በመንፈስ ቅዱስ ተጸንሶ የማርያም ልጅ የሆነው ወልድ ሥጋውና መለኮታዊው ባሕርዩ በፍጹም ተዋሕዶ የባሕርይ አምላክ ነው ለሚሉት ለካሮች፣ አንጋፋ ተከራካሪ (አፈ ጉባኤ) የሆኑት ሊቀ ካህናት አለቃ ኪዳነ ወልድ ነበሩ። እኝህ ሰው የትውልድ አገራቸው ተጉለት (ሸዋ) ሆኖ ከዚህ በፊት ስለ ተዋሕዶ ሃይማኖት ከሸዋ ተሰደው በቤጌምድርና በትግራይ ሲኖሩ፣ በመጨረሻ ዐፄ ቴዎድሮስና አባ ሰላማ በኅብረት በሸዋ ያሉትን የጸጋ ተከታዮች አጥፍተው ተዋሕዶዎቹን (ካራዎችን) ባቋቋሙበት ሰዓት ኪዳነ ወልድ ዋና መንገድ መሪና አስተናባሪ ሆነው ጸጎችን ማስጠቃታቸው ይታወሳል። አሁንም ያፄ ዮሐንስ ይዞታ እንደዚያው እንዳፄ ቴዎድሮስ በመሆኑ ተደስተው ለክርክሩ ቆመዋል። ከርሳቸው ጋር እነ መምህር አካለ ወልድ፣ እነ መምህር ግርማ ሥላሴ፣ እነ አለቃ ወልደ ያሬድ ይገኙ ነበር።

በጸጎች በኩል አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ፣ አለቃ ሀብተ ወልድ፣ አለቃ ውቤ፣ ከቅባቶች ወገን እነ ዙርአምቤ እንግዳ፣ እነ ዋልድቤ እንግዳ ነበሩ። እነዚህ ከሁለት የተከፈሉ ሊቃውንት የየራሳቸውን የእምነት አባባል ከብሉይና ከሐዲስ፣ ከሊቃውንት እየጠቀሱ ሲመላለሱ በዳኝነቱ ዙፋን ለተቀመጡት በብሉይና በሐዲስ በሊቃውንት ትምህርት ያልበሰሉት ንጉሠ ነገሥቱና ንጉሡ ምስጢሩ እየረቀቀባቸው ክርክሩ ግራ አጋቢ ሁኔታ ላይ እንዳለ፣ ከተዋሕዶዎቹ መካከል አንዱ



ደብተራ ወልደ ዮሐንስ ብቅ ብለው ለነገሥታቱ በሚገባቸው፣ ግልጽ በሆነ፣ በጥያቄና በመልስ፣ በቀለጠፈ መንገድ ለጉባኤው ክርክር መፍትሔ ሰጡት።

ክርክሩን ሲከፍቱ ወልደ ዮሐንስ "የንጉሥ ገንዘብ በሒሳብ ይወጣል በሒሳብ ይገባል፤ ከሒሳቡ ያጐደለም የጨመረም ይቀጣል፤ ይህን ታምናላችሁ ወይስ አታምኑም" ብለው ቢጠይቋቸው፣ ጸጎች ማመናቸውን ገለጹ። ቀጠል አድርገውም ወልደ ዮሐንስ እንዲያው "የሥላሴ ገንዘብ ሃይማኖትም በመጽሐፍ ውስጥ ተቆጥሮ የሚገኝ ነውና ከዚህ ያጐደለም የጨመረም ይቀጣል ወይስ አይቀጣም ቢሏቸው ጸጎች አሁንም እንደሚቀጣ አመኑ። "እንግዲያው . . . የሃይማኖተ አበው መጽሐፍ 'ነአምን ክልኤተ ልደታተ' (ሁለት ልደትን እናምናለን) ብሎ በአኃዝ ወስኖ ተጽፏልና ከመጽሐፍ ውስጥ ሦስት ልደት የሚል አምጡ፤ ያለዚያም እኔ ባመጣሁት ተረታልኝ" ብለው ገደገዱ። በትርጉም ካልሆነ በቀር ጸጋዎችን የሚግደፍ በአኃዝ ሦስት ልደት የሚል በብሉይና በሐዲስም፣ በሊቃውንትም መጽሐፍ ስለሌለ፣ የወልደ ዮሐንስም ግልጽ ጥያቄና የተሰጠው መልስ ለነገሥታቱ በቶሎ ስለ ገባቸው፣ "ሦስት ልደት የሚል እንዳላችሁ አምጡ፣ ያለዚያ ተረታችኋል" ብለዋቸው የግራዎቹ ተረቱ፤ የቀኞቹ ረቱ ተብሎ ባዋጅ ተነግሮ ጉባኤው ተበተነ። ከመበተኑ በፊት ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስ ለረችው ለደብተራ ወልደ ዮሐንስ ነገሩን አብራርተው ስላስፈረዱ፣ ስሙን መልአከ ብርሃን ብዬዋለሁ ብለው እዚያው እጉባኤው ላይ ሾሟቸው። እኝህ የተጉለት ሊቅ መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ እየተባሉ ላፄ ምኒልክ መንግሥት ፍትሐ ነገሥት አውጭ ሆነው ሲያገለግሉ ኖረዋል።

የዚህ የሃይማኖት ክርክር ታሪኩ ብዙ ነው። ሁኔታውን በሰፊው ለመረዳት የፈለገ ሰው የሃይማኖተ አበውን፣ የጸሐፌ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይን፣ የመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬን መጽሐፍ በየምዕራፉ ፈልጎ ማንበቡ ይጠቅማል።[1] በዚያን ጊዜ ዘመኑ፣ ባንድ ወገን ከጥንት ተያይዞ እንደ መጣው ከሥጋዊው ጉዳይ፣ ይኸውም ማለት ከማናቸውም የልማት ሥራ፣ ከእጅ ጥበብ፣ ከእርሻም፣ ከሕክምናም ትምህርት የሃይማኖቱ ጉዳይ ቅድሚያ የሚሰጠው ነበር። በዚህም ላይ በአውሮፓ ተዠምሮ `በመካሔድ ላይ ያለው የአሳብና የሃይማኖት ነጻነት፣ ኋላ ቀርነቷ በግልጽ በታወቀው በኢትዮጵያ

1 ጸ.ገ.ሥ.፣ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ፣ ገጽ 27። መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ መጽሐፈ ቅኔ ገጽ 279 —283።

ውስጥ ምልክቱም ስላልነበረ፣ በዚሁ ጉባኤ ከተረቱት መካከል እነዙር አምቤ እንግዳ በንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ የአካል ቅጣት ደርሶባቸዋል ።

የዐፄ ዮሐንስ መሠረታዊ አሳብ፣ በክርስቲያኑ ሕዝባቸው መካከል "የጸጋ ልጅ፣ የቅባት ተከታይ" የሚባለው ሁሉ ተደምስሶ ሁሉም ክርስቲያን በተዋሕዶ እንዲያምን ነበር ። በዚሁ ጐን በኢትዮጵያ ያለው እስላም ሁሉ በክርስትና እንዲጠመቅ በየአውራጃው ትእዛዝ ስለ አስተላለፉ፣ በዚሁ በ1870 ዓመተ ምሕረት በያለበት ያለው እስላም ሁሉ በጭቃሹምና በመልከኛ ወደየአቅራቢያው ቤተ ክርስቲያን እየተነዳ በግድ እንዲቆርብ ተደረገ ። በዚሁ ጊዜ አንዱ እስላም፣

"ታናሽ ታላቅ በላን ክርካ አደባባይ፣
ክርስቲያን ሆይ፣ አለልብ ሥጋ ይጣፍጣል ወይ" ብሎ ገጥሟል ።[1]

ከዚህም ጋር የትምባሆ ሱረት ባፍንጫው የሚጠጣ ወይም የትምባሆ ድፍድፍ ባፉ ቋጥሮ የሚመጥ ሁሉ እንዲከለከል፣ "ትምባሆ ሲጠጣ የተገኘ አፍንጫውና መላሱ ይቆረጥ" የሚል ዐዋጅ አወጡ ። ልማዱ እያስገደደው እምቢ ያለውና ሲጠጣ የተገኘው በዚሁ የጭካኔ ቅጣት ሲቀበል፣ ከእስላሞቹም መካከል የፈራው እየቆረበ ክርስትና ሲነሣ፣ የቀረው ከሀገሩ ከኢትዮጵያ ወደ ጐረቤት አገሮችና ያፄ ዮሐንስ ሥልጣን ወደማይደርስበት አውራጃ እየተሰደደ ይሸሽ ገመር ። በዚህ ጊዜ ነው አንዳንድ የወሎ፣ የዋጅራት፣ የራያና የእዘቦ እስላም ባላባቶች ወደ ሱዳን በስደት ሔደው ከሃይማኖት ወገኖቻቸው ጋር ተደባልቀው፣ ባፄ ዮሐንስ ላይ ሲያሤሩ የቆዩትና በመጨረሻ በ1881 ዓ.ም. በመተማ ጦርነት ሊበቀሉ የቻሉት ።

ከጉባኤው በኋላ፣ መምህር አካለ ወልድ ለወሎ እንደ ሐዋርያ ሆነው የወሎን ሕዝብ እያስተማሩ፣ ወደ ክርስትና እንዲመልሱ ተሾመው ስለነበረ፣ በ1870 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ ከላይ ከይማም ዐመዴ ኮላስ የሚወለዱትን የወይዘሮ መስተዋትን ልጅ ይማም ዐመዴ ዐሊን በፈረስ ስማቸው አባ ዋጠው ይባሉ የነበሩትን ንጉሥ ምኒልክ የክርስትና አባት ሆነው ካነሷቸው በኋላ፣ ስመ ክርስትናቸው ኃይለማርያም ተብሎ የደጃዝማችነት ማዕረግ ተቀበሉ ። የርሳቸውንም

1 ደስታ ተክለ ወልድ፣ አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ ገጽ 126 ።



የዘመድ ባላንጣ ከግንደ በረቷ * ተወላጅ ከወይዘሮ ጌቴና ከዐሊ አባ ቡላ የሚወለዱት ይማም መሐመድ ዐሊን ራሳቸው ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስ ክርስትና አንሥተው ራስ ሚካኤል ብለው ሠየሟቸው ። እኚህም የልጅ ኢያሱ አባት ሲሆኑ፣ ኢያሱ ራሳቸው ሳይነግሡ ሥልጣን በያዙበት ዘመን "ንጉሥ ሚካኤል" ብለው የሾሙዋቸው ናቸው ።

"እስላሞችን በግድያ እያስፈራሩ ያጠምቃሉ፣ እምቢ ያለውንና ትምባሆ የሚጠጣውን በአካል ይቀጣሉ" የሚለው ወሬ በሱዳንና በግብጽ ጋዜጦች ወይም በሚሲዮናውያን አማካይነት በአውሮፓ ተነዛ ። ከዚህ በፊት፣ "የካቶሊክ ሚሲዮናውያንን አጉላሉ" ከሚለው ጋር ይኸው እየተዛመደ፣ በአውሮፓ መሪዎች ዘንድ ቅሬታን ፈጠረ ። አንዳንድ ወቀሳም ባፄ ዮሐንስ ላይ ተሰነዘረ ።

ስለዚህ በአውሮፓ የተወራውን፣ በኃይል እያስገደዱ የማጥመቁን ጉዳይ ለማስተባበል፣ ለሌሎቹም እንደ ጻፉት ሁሉ በተለይ ወዳጅነታቸውን ለሚንከባከቡት ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት እንደዚህ ይላል።

"...ሸዋ ዘምቼ ሳለሁ እኛ በኛ ክርስቲያኖቹ ** በሃይማኖት ተከራክረን አረተን በእስክንድርያ ሃይማኖት አገባናቸው (ጸጋዎቹን) እስላም ሁሉ ይኸንን አይቶ ሰምቶ 'ለካ ለኛስ አባት የለንም(የለንምን) ብሎ ያጥምቁን ክርስትና ያስነሡን' ብሎ ለመነኝ እሺ ከፈቀድህስ ከወደድህስ ክርስትና ግባ ብዬው የኢትዮጵያ እስላም ሁሉ ወዶ በፈቃዱ ክርስቲያን ሆነ ። አንድ (አንድም) ነገር በኃይል ያደረግሁት የለኝም ወዶ በፈቃዱ ነው እንጂ የገባ ። በወንጌልም ጌታ ሲጽፍ በኃይል አድርጉ አላለም አላዘዘም ። በኃይል የተደረገ የለም ።"

ይኸን የጻፉት በአሥመራ ከተማ በ1872 ዓ.ም. በኅዳር 11 ቀን እንደሆነ ደብዳቤው ይገልጻል ።[1] ያን ጊዜም እንደዛሬ ለአገሬ ለአስተዳደሬ ይበጃል ወይም ጠላቴን አጠቃለሁ ብሎ አንዱ መሪ በፈጸመው ወንጀል ከውጭ ወቀሳ ሲሰነዘርበት፣ "አላደረግሁም ወይም አልተደረገም" ብሎ በደፈናው ያስተባብላል እንጂ "አድርጌያለሁ" ብሎ በገሃድ አምኖ ራሱንም፣ መንግሥቱንም እንዲሳጣ አያደርግም።

* የወረሂመኑ ተወላጅ የሚሏቸው አሉ ።
** በተዋሕዶና በጸጋ የተከፋፈለ ነው ።
1 Public Record Office — London — FO 95-7.38-12-99.

# ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት

## የንጉሥ ምኒልክና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጠብ — የንጉሠ ነገሥቱ የዳኛ ገላጋይነት

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ዮሐንስ ፥ ከንጉሥ ምኒልክ ጋር በ1870 ዓ.ም. በስምምነት የሸዋ ንጉሥነታቸውን ሲቀበሉ ፥ ምኒልክም የዮሐንስን ንጉሠ ነገሥትነት ዐውቀው በሁለቱ መካከል ሰላም ከተፈጠረ ወዲህ ፥ በአራተኛው ዓመት በ1873 ዓ.ም. ምኒልክ ባሉበት ፥ ራስ አዳል እየተባሉ ለቆዩት ለጐጃሙ መስፍን ዘውድ ሰጥተው ፥ "ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት" አሰኝተው በጐጃምና በከፋ ላይ አነገሡዋቸው ። "'አለያይተህ ግዛ' በሚለው ዘዴ በመጠቀም ንጉሠ ነገሥቱ ለምኒልክ አኳያ ባላንጣ መፍጠራቸው ነው" ተብሎ በዘመኑ መወራቱ አልቀረም ። ነገር ግን ይኸን የመሰለውን ፖለቲካ በዓለም ያለ መሪ ሁሉ የሚጠቀምበት ስለሆነ ፥ ለዐፄ ዮሐንስ እንደ አዲስ ያስተዳደር ሥልት አይቆጠርም ።

እውነትም ሁለቱ የሸዋና የጐጃም መሳፍንት ፥ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ንግሥ ወዲህ ፥ በተለይ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በጐጃም ላይ የከፋ ንጉሥ ሲባሉ ፥ ምኒልክ በነራስ ጐበና አማካይነት ከፋንና አካባቢውን በከፊል የያዙበትና የቀረውንም ለመያዝ የሚዘጋጁበት ወቅት ነበር ። የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ጦር ቀደም ብሎ ወለጋ ገብቶ ስለነበረ ፥ በሁለቱ ነገሥታት ዘንድ ጠቡ የማይቀር ሆነ ። ሁለቱም በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያን ደቡባዊ ክፍል እያቀኑ ግዛት ለማስፋፋት ሲሻሙ ነበር ። ከምኒልክ ወገን ስመ ጥሩው ራስ ጐበና ዳጨው ፥ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በኩል በስመ ጥሮነት ከጐበና የማያንሱት ራስ ደረሶ አባ ጠቦ የጦር አበጋዞች ነበሩ ።

ንጉሥ ምኒልክ ፥ የእንጦጦን ከተማ ሲያሠሩ ራስ ደረሶ ከኩታይ ዝምሮ ጉድሩን ፥ አሞሮን ፥ ሆሮን ፥ ኖኖን ፥ ጅማን ፥ ባንቴን ፥ ትቤን ፥ ጨሊያን ፥ ሊሙን ይቴን ፥ ጅማ አባ ጅፋርን ፥ ሌቃን ፥ ወለጋን ፥ ጉማን፥ ጌራን ወግተው አገሩን ዘራርፈው ፥ የሰበሰቡትን ዝባድና የዝሆን ጥርስ እናሪያ ፥ ሊሙ ላይ አኑረው ከፋን ለማሳመን ሲጓዙ ፥ በመካከሉ ራስ ጐበና በበኩላቸው ዳቄን ፥ ደራን ፥ ቦረናን ፥ ጉለሌን ፥ ሰላሌን ፥ አቦቴን ፥

ጃርሶንና ሜጫን እየወጉ መጥተው እናሪያ ሊሙ ሲደርሱ ራስ ደረሶ ሰብስበው ያስቀመጡትን የዝሆን ጥርስ እጅ አደረጉ ። [1]

በዚህ ጊዜ በራስ ጐበና በኩል ያለ ገጣሚ ፡—

"እነዚህ ጐጃሞች በምን ይሥቃሉ ፣
ጥርሳቸውን ሊሙ ጥለውት ሔዱ አሉ"

ብሎ ገጠመ ይባላል ።

የዚህን ወሬ ራስ ደረሶ ሲሰሙ ፣ ከከፋ ተመልሰው ከራስ ጐበና ጋር ለጦርነት ተፋጠጡ ። በዚህ ጊዜ ራስ ጐበና "ግዛቱ የኔ ነው" በማለት ከትግራይ የመጡትን ነጋዴዎች ዳኛ አውጥተው "በዮሐንስ አምላክ አገሬን ልቀቅ" ያሉትን መሠረት አድርጎ የራስ ደረሶም ገጣሚ እንደዚህ ብሎ መለሰ ይባላል ።

"እበላለሁ ፣ እገዛለሁ ብሎ ከእንጦጦ ገሥግሦ ፣
በዮሐንስ አምላክ አስኘው ደረሶ" [2]

ራስ ደረሶ ካገር ላይ የሰበሰቡት ዝባድና የዝሆን ጥርስ በዳኛ እንደ ተያዘ ቆይቶ ሁለቱም ራሶች ሁኔታውን ለየጌቶቻቸው ማስታወቅ ግዴታ ሆነባቸው ። ራስ ደረሶ ለጌታቸው የላኩትን አላገኘነውም ። በጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴና በብላቴን ጌታ ኅሩይ መጽሐፍ ላይ "ራስ ደረሶ ወደ ከፋ ሔደው ከጉማው ባላባት ከአባ ጆቢር ጋር ተዋግተው ገደሉት የሚል ወሬ ለምኒልክ ሲደርሳቸው ፣ ራስ ጐበናን በግሥጋሤ ላኩ" የሚል ከተገለጸ በኋላ ፣ ቀጥሎ ምኒልክ ወዳሩሲ ዘምተው ሲመለሱ ፣ "ከራስ ደረሶ ጋር ጉማ ላይ ተገናኝተን ከባላገር ላይ የተቀበሉትን ከብት አስመለስናቸው ፤ ወደፊትም ንጉሥ ምኒልክ በፈቃዳቸው ከሰጧችሁ አገር እንዳታልፉ ብለን አስገዝተን ሰደድናቸው ። እኔም ወደዚያ ወደ ንጉሥ መምጣቴ ነው" የሚል ከራስ ጐበና የተጻፈ ለምኒልክ እንደ ደረሳቸው ያረጋግጣሉ ። [3]

ነገር ግን ፣ ምኒልክ በፈቃዳቸው የሰጧቸው ከየት እስከየት ድረስና የማንን አገር መሆኑ አልተገለጸም ። የዝሆን ጥርሱም በዳኛ ያስይዙት ወይም እጅ ያድርጉት አልተለየም ።

1 አለቃ ተክሌ ግን በዳኛ እንደ ተያዘ ይገልጻሉ ፤ የእጅ ጽሑፍ ገጽ 124 ።
2 አለቃ ተክሌ (ተክለ ኢየሱስ) የእጅ ጽሑፍ ፣ ገጽ 124 ።
3 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግሥተ ሰባ እስከ ዐድዋ ጦርነት (የእጅ ጽሑፍ) ገጽ 103—104 ።



ራስ ደረሶ ፣ ከራስ ጐበና በስምምነትና በመሐላ ከተለያዩ ወዲህ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት "... ለምን ትመለሳለህ? መሐላውና ግዝቱስ ለምንህ ነው? አትሞትም ኖሯልን?... አሁን ልጄን ራስ በዛብህን ጨምረህ ..ተዋጋው ። ራስ ጐበና አገሩ የገባ እንደሆነ አንተም አገርህ አትገባም ፤ ወዲያው ቅር ። ንጉሥ ምኒልክ የመጡ እንደሆነ ላከብኝ እንድመጣ ፤ ንጉሥ ሆኜ ከራስ ጋር አልዋጋም ከንጉሥ ጋር እንጂ..." ብለው ወደ ራስ ደረሶ መላካቸው ይገኛል ። [1]

ዮሐንስ ለተክለ ሃይማኖት የንጉሥነት ደረጃ ከመስጠታቸውም በላይ ምኒልክን በባላንጣነት እንደሚጠረጥሯቸው ፣ ተክለ ሃይማኖትን ግን ፣ ከልብ እንደሚወዷቸውና እንደሚያምኗቸው በማወቅ ፣ 'ተክለ ሃይማኖትን ብወጋ ንጉሠ ነገሥቱ ይቀየሙኛል' የሚል ጥርጣሬ በምኒልክ ዘንድ ነበርና ፣ ቅሬታቸውን ለዐፄ ዮሐንስ ቀደም ብለው በደብዳቤ አሳውቀዋቸው ነበር ። ከዐፄ ዮሐንስ የደረሳቸው መልስም የሚከተለው ነበር ።

> መልእክት ዘሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ...ይድረስ ከንጉሥ ምኒልክ በአማን እስራኤላዊ ዘአልቦ ጽልሑት ..ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከዚህ በፊት ልኬያለሁ ። እንግዲህም እሺ እልካለሁ ። ነገር ግን ፣ አንድ ጳጳስ ሦስት ኤጲስ ቆጶሳት አራት ሆነው ሲመጡ ፣ በኢትዮጵያ ተደርጎ የማያውቅ ሐዲስ ነገር ሲደርስ* የረከሰ በሚቀደስበት የተጣላ በሚታረቅበት ጊዜ እላንተ ትጣላላችሁን ። እኔም ለሠራዊቴ ስንቅ አስይዝ ብዬ ነው እንጂ ምን አደርጋለሁ ይኸው መጣሁ። ተነሥቻለሁ ። ሲሆን ወደ ዋድላ ወይ ከቤጌምድር ላይ ከእኔ ስንገናኝ አለያያችኋለሁ ። አትቸኩሉ ። እስክመጣ ድረስ ቆዩ ። የቸኮላችሁ እንደሆነ ግን ፣ ካለሁበት ድረስ እየራሳችሁ... አንዳንድ ሰው(ነገረ ፈጅ) ስደዱ... ተጽሕፈ በመቀሌ ከተማ ፣ ኅዳር 28 ቀን 1874 ዓ.ም.**

ንጉሠ ነገሥቱ ፣ በዚሁ ዐይነት ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የጻፉትን እንደዚሁም ሁለቱ ነገሥታት የመለሱትን አናውቅም ። ይሁን እንጂ ፣ ሁለቱም የየራሳቸውን ስሞታና ለተጻፈላቸው መመለሳቸው የማይቀር ነው ።

1 አቶ በጥሜ የጋላ ታሪክ ፣ ገጽ 152 ።
* ከዚህ በፊት ከግብጽ የሚመጣው ጳጳስ አንድ ብቻ የነበረውን አሁን በርሳቸው ጊዜ አራት መምጣታቸውን ሲያስታውሱ ነው ።
** ቀንና ዓ.ም. የተጻፈው በግዕዝኛ አጻጻፍ ነው ።

ሁለተኛ ጊዜ ካፄ ዮሐንስ ፤

. . . ደብዳቤው ደረሰኝ. . . አትጣሉብኝ ፡ ተፈቀሩልኝ ፤ እንደ ሽማግሌ እንደ አባት እንደ እናት እመክራለሁ ፤ እገላግላለሁ እንጂ እንደ ንጉሥ ይህ ይሁን ብዬ ያዘዝሁት ነገር የለኝም ። አሁንም የአሕዛብና የሰይጣን መሳለቂያ እን ዳንሆን ከባሕር ወዲህ ፡ ከባሕር ወዲያ ብዙ ጠላት ሳለን እርስ በርሳችን ብንዋጋ የክርስቲያን ደም በከንቱ ቢፈስ ለክርስቶስ ደስ አይለውም. . . እኔ እስከመጣ ድረስ ታገሡልኝ ጦራችሁ በያለበት ይቆይ ። ደግሞ እኔ ፊቴን ወደ ትግሬ ብመልስ በወረባቦ ፡ ባርጐባ ፡ በወሎ ብዙ ነገር ይደረጋል ማተቡን ይቆርጣል ሲሉ እሰማለሁ ። ቀድሞውንም ያጠፉ ያባ ዋጠው ምክር ይሆንን ብዬ ነበር ። አሁንም ቢመከር በት ይሻላል ። ነገር ግን እኔ ባጠፋው ቸግሮኝ አይደለም ። ከወንድሜ* እንዳልከፋፋ (እንዳልጣላ) ብዬ ነው እንጂ ።

ተጻፈ ጥር 8 ቀን 1874 ዓ.ም.

የሚል ደብዳቤ ለንጉሥ ምኒልክ ስለመጣ ፡ በዚህ ዐይነት በቅድሚያ ልናገኘው ያልቻልነው ከምኒልክ ላፄ ዮሐንስ መጻፉን ያስረዳል ።

ከወሎ የታወቁት ባላባቶች አንደኛው መሐመድ ዐሊ አባ ሻንቆ የሚባሉትን ንጉሠ ነገሥቱ በሚካኤል ስም ክርስትና እንሥተው የራ ስነት ማዕረግ ሰጥተውና አክብረው ባለሟል አድርገዋቸዋል ። ሌላው የራስ ሚካኤል ባላንጣ ይማም አህመድ አባ ዋጠው የሚባሉት የወ ይዘሮ መስተዋት ልጅ ናቸው ። ወሎ ላይ ዮሐንስና ምኒልክ ተገናኝ ተው ቅባቶችንና ጸጋዎችን አውግዘው ተዋሕዶ ሃይማኖትን ካጸኑ በኋላ ፡ መሐመድ አባ ሻንቆን ንጉሠ ነገሥቱ ክርስትና ሲያነሡ አባ ዋጠውን ምኒልክ ኃይለ ማርያም አሰኝተው ክርስትና አስነሥተው የደጃዝማችነት ማዕረግም ሰጥተዋቸዋል ። አባ ዋጠው የምኒልክ የክር ስትና ልጅ እንደ መሆናቸው መጠን ባንዳንድ ሁኔታ ለምኒልክ እያ ደሉ ንጉሠ ነገሥቱን እንዳሳዘኑና ንጉሠ ነገሥቱ ደግሞ አባ ዋጠውን እንዳያጉላሉዋቸው ምኒልክ ይቀየማሉ ብለው እንደሠጉ ደብዳ ቤው ያስታውቃል ።

እንደዚሁም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ለጻፉላቸው ደብዳቤ ፡ “. . . ደብዳቤውም ደረሰኝ ። እኔም የሁለታችሁን ነገር እየሰማሁ መከራ

---

* ከንጉሥ ምኒልክ ለማለት ነው ።



እየተቀበልሁ ተቀምጫለሁ ። ነገር ግን ፡ ‘ኢትማአ ለእኩይ በእኩይ ፡ አላ በገቢረ ሠናይ’ (ክፉን በክፉ አታሸንፈው ፡ በበጐ ሥራ እንጂ)[1] እንኳን በቅርብ ያለውን ጠላቴን በሩቁ እንኳን ያለውን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጐዳልኛል እንጂ ፡ እኔ አልጐዳውም ። አሁንም መግፋት ክፉ ነው እንጂ ፡ የተገፋ ሰው ምን ተጐድቶ ያውቃል ። ለሁሉም እኔ ወደዚያው መጣሁ ፤ ሁሉም ስንገናኝ ይሆናል ። ተጽሕፈት በዐድዋ ከተማ በ1874 ዓ.ም.” የሚል መልስ ካፄ ዮሐንስ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ተመልሷል ።

ንጉሠ ነገሥቱ ፡ ለምኒልክና ለተክለ ሃይማኖት የጻፉት ደብዳቤ ቃሉም መንፈሱም ይለያያል ። ለምኒልክ ከጻፉት ላይ ለሁለቱም ጭፍሮቻቸው በሐቅ መካሪና አስታራቂ ይመስላሉ ። ለተክለ ሃይማ ኖት ከጻፉት ላይ ፡ “ግፍም ቢሠራብህ በመጨረሻ የተገፋ ሰው ያሸን ፋል” የሚል ቃል ስለ አለበት ፡ ሁኔታው ሲታይ ምኒልክን ገፊ ተክለ ሃይማኖትን ተገፊ ያደረጉዋቸው ይመስላል ። በዚህም ላይ በመ ጨረሻ ፡ “ለሁሉም እኔ ወደዚያው መጣሁ ፡ ሁሉም ስንገናኝ ይሆናል” የሚል ቃል ስለ ተጨመረበት ፡ ዐፄ ዮሐንስና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የተስማሙበት በአሳብ ከልብ የተቀራረቡበት ነገር ያለ ይመስላል ። ደግሞም ለተክለ ሃይማኖት በጐጃም ላይ ከፋን ጨምረው ስላነገሡ ዋቸውና ምኒልክ ይኸን ክፍለ ሀገር ወደ ራሳቸው መደረብ ስለ አማ ራቸው ፡ በንጉሠ ነገሥቱ ላይ በትክክል ያልተገለጠ ቅሬታ እንደ ነበረና ወደ ርሳቸው የተደረቡትንም የወሎውን አባ ዋጠውንም (ደጃች ኃይለ ማርያምን) ለመምታት እንዳሰቡ ይታወቃል ።

---

1 እዚህ ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮማውያን በጻፈው መልእክቱ በምዕራፍ 12 ቁ. 21 ላይ የጻፈውን መጥቀሳቸው ነው ።

# ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት

## በእምባቦ የንጉሥ ምኒልክና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጦርነት

## የንጉሥ ምኒልክ ማሸነፍ

ምንም እንኳን ንጉሠ ነገሥቱ ፣ ለሁለቱም ነገሥታት ደብዳቤ እየጻፉ የሁለቱን ጠብ ለማብረድ ቢሞክሩ ፣ የሁለቱ ነገሥታት ምኞት የተራራቀ በመሆኑ በወረቀትም ሆነ ቃል ለቃል ተገናኝተው በመነጋገር በመካከላቸው ስምምነት ሊፈጥሩ አልቻሉም። የተክለ ሃይማኖት አሳብ ፣ "ከምኒልክ ጦር በፊት የኔ ጦር በወለጋ ስለገባ ፣ ከንጉሠ ነገሥቱም በጐጃም ላይ የከፋ ንጉሥ ተብዬ ስለ ተሾምሁ ፣ ከፋና አካባቢው ጉማ ፣ ሊሙ ፣ ከወለጋ ጋር የኔ ግዛት ነው" ሲሉ ምኒልክ ደግሞ፣ "ጐጃሞች ከአባይ ወንዝ ወዲህ ምንም ግዛት የላቸውም" ከማለት ጋር የከፋ ንጉሥነታቸውንም አልተቀበሉትም ።

ስለዚህ ፣ ለነገሩ መፍትሔ የሚሰጠው በውይይትና በግልግል ፋንታ ጉልበት ብቻ መሆኑ በግልጽ ይታይ ነበር ። ነገር ግን የሁለቱም የጦር አለቆች ጐበናና ደረሶ በየግንባራቸው መሬት ሲፋለሙ ፣ ሁለቱም ከየጌቶቻቸው ሳያስፈቅዱ ወይም ጌቶቻቸውን ሳይዙ በገሃድ መዋጋቱን አልፈለጉትም ነበር ። እንደዚሁም ሁለቱ ነገሥታት ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር እየተጻጻፉ ተበዳይ እንጂ ፣ በዳይ አለመሆናቸውን ከማመልከት ጋር በተለይ ምኒልክ የዮሐንስ ልብ ወደ ተክለ ሃይማኖት ማዘንበሉን ስለ ዐወቁ በተቻለ መጠን ጠብ አጫሪ ፣ ጦር ቀስቃሽ መስለው ላለመታየትና በዚህም ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በገሃድ ላለመጣላት ነገሩን በዘዴና በትዕግሥት መያዝ የመረጡ ይመስላል ።

ለዐፄ ዮሐንስ ሰላማዊ መልክ እያሳዩ በግዛት ፍልሚያው ላይ ግን ጐበናን "በርታ ፣ ግፋ" እያሉ ከማበርታት ፣ ጦራቸውን በዚያ ግንባር ከማደርጀት በቀር መላላትን አላሳዩም ። የጦር አለቃቸው ራስ ጐበና ምንም እንኳን የራስ ደረሶን ጦር ለማጥቃት የሚችል ኃይል እንዳላቸው ቢረዱትም ፣ "የንጉሥ ምኒልክን አገር ለቃችሁ ሒዱ ፤ እናንተም ወደ ጌታችሁ ላኩ እኔም ወደ ጌታዬ እልካለሁ እንጂ ከናንተ ጋር አልዋጋም" ብለው ለራስ ደረሶ ላኩ ። ደረሶም በግዴታ ስምምነት ከየባላባቱ የተቀበሉትን በዳኛ እንደ ተያዘ እንዲቆይ

አድርገው እርሳቸው ወደ ጐጃም ሔደው ሁኔታውን ለጌታቸው አስረዱ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ለራስ ደረሶ ጦር ጨምረው መልሰው ልከው እርሳቸውም ፤ "ምታ ነጋሪት ፤ ክተት ሠራዊት" ብለው በዐዋጅ ጦራቸውን ሰብስበው ጉዞ ዠምረው የአባይን ወንዝ ተሻግረው ወደ ጉድሩ ድንበር ገቡ ። በዚህም ጊዜ ካፄ ዮሐንስ "አትዋጉ" የሚል የመጣላቸውን ትእዛዝ ደስታ ኃይሉ የሚባል ተንኰለኛ ሽፍታ ከመንገድ አግኝቶ እንደ ቀደደው አለቃ ተክሌ ጽፈዋል ።[1]

ንጉሥ ምኒልክም በበኩላቸው ይኸንኑ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን መዝመት ሰምተው ኖሮ ፤ ጦራቸውን በዐዋጅ ሰብስበው በመጋቢት 13 ቀን 1874 ዓ.ም. ከከተማቸው ከእንጦጦ ተነሥተው በበቾ ፤ በገጃ ፤ በጥቁር ምድር አድርገው ተጓዙ ። ራስ ጐበናም ከጅማ የጊቤን ወንዝ ተሻግረው ይጓዙ ኖሮ ፤ አንድ ከጅማ የመጣ ነጋዴ የንጉሥ ምኒልክን መምጣት ስለ አስረዳ ፤ ወደፊት ዐልፈው በሚጠባበቁበት ጊዜ ኖኖ ላይ ንጉሡ ሠፍረው ሳለ ፤ ራስ ጐበና ደርሰው ከንጉሣቸው ጋር በደስታ ተገናኙ ። ኖኖ ከወሊሶና ከአማያ ዐልፎ ወደ ጊቤ ወንዝ ቀረብ የሚል ወረዳ ነው ።

ከዚህ ቀጥሎ ራስ ጐበና ዝርዝር ሁኔታውን ለጌታቸው ካስረዱ በኋላ ፤ ጠቅላላው የሸዋ ሠራዊት በንጉሡ እየተመራ ወደ ጉድሩ ሲጓዝ እንደዚሁ ያባ ዋጠው (ራስ ኃይለ ማርያም) እናት የወሎዋ ባላባት ወይዘሮ መስተዋት የግል ጦራቸውን ይዘው ከሸዋ ጦር ጋር ተሠልፈው ይጓዙ ነበር ። በዚህ ጊዜ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በጉዞ ላይ እንዳሉ አባይን ከመሻገራቸው በፊት ከመኳንንቶቻቸው ጋር መክረው "ወደ ንጉሥ ፊታውራሪ ይመር የሚባሉትን ሹማቸውን ጠርተው ፤ "ወደ ንጉሥ ምኒልክ ሔደህ ይህ አሁን እርስዎ ያሉበት አገር ባፄ ዮሐንስ ፈቃድ ያቀናሁት የኔ ግዛት ስለሆነ ፤ የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስ ትተው ይመለሱልኝ ብለህ ንገር" ብለው ልከውት ነበርና ወደ ምኒልክ መጥቶ ይኸንኑ ቢነግራቸው ከምኒልክ የተሰጠው መልስ ፤ "ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከአባይ ወዲህ ምን ግዛት አለው ፤ እኔ ስለ ወዳጅነትና ስለ ፍቅር ብዬ አሞሩን ፤ ሐሮን ፤ ጉድሩንና ግንደ በረትን የባላባቱን የቀዲዳን አገር እንዲያቀና ብሰጠው እያለፈ ሌላውን አገር ይይዝ ዠመር ። አሁን ግን ፤ በፈቃዴ የሰጠሁትን መልሼ ወስጃለሁና ከአባይ ወዲህ ያለው የርሱ ሠራዊት እየተመለሰ እንዲሻገር ይሁን" የሚል ሆነ ።[2]

1 ያለቃ ተክሌ የእጅ ጽሑፍ ፤ ምዕ.38 ፤ ገጽ 124-125 ።

2 ያለቃ ተክሌ የእጅ ጽሑፍ ምዕ.38 ፤ ገጽ 151-152 ።



ፊታውራሪ ይመር ይኸን ቃል ሰምተው ወደ ጌታቸው ከተመለሱ በኋላ ፤ ንጉሥ ምኒልክ የጦርነቱ ጉዳይ የቀረ መስሏቸው በነበሩበት አካባቢ ፤ ጐጃሞቹ ቀደም ብለው ይዘውት በነበረው ወረዳ ሹምሽር አድርገው ወደ እንጦጦ ለመመለስ ሆርጀሬ ከሚባል ሥፍራ ሲደርሱ ፤ በግንቦት 21 ቀን "ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ተልከናል" ብለው ሰዎች መምጣታቸው ተሰማና ከምኒልክ ፊት ቀረቡ ። የመልክተኞቹም ዋንኛው ይግዛው መኮ ይባላል ። ስለዚህ ምኒልክ "ደብዳቤ ይዛችሁ እንደሆነ አቅርቡ ፤ የቃልም እንደሆነ ተናገሩ" ቢሏቸው "መኳንንቱ ሁሉ ካልተሰበሰቡ ለብቻዎ እንዳንነግር ታዘናል" ብለው መለሱ ። ስለዚህ መኳንንቱ ከተሰበሰቡ በኋላ ፤ "እንግዲህ ተናገሩ" ቢሏቸው ፤ "ጌታችን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ንገሩ ያሉን ቃሉ ይህ ነው ። ምነው እርስዎ ሁልጊዜ እኔን ያዋርዱኛል ። ከዚህ ቀደም በኃይል መጥተው አገሬን ጐጃምን አጥፍተውት ሔዱ ።[1] አሁን ደግሞ ያቀናሁትን የኦሮሞውን አገር እያጠፉ ሹምሽር አደረጉበት ። ከእንግዲህስ ወዲህ መጣሁ አይሒዱ ከጉድሩና ከሐሮ ፤ ከጅማ * እና ከጨሊያ በወደዱት አገር የጦሩ ሜዳ ይዘው ይቆዩኝ ። ይኸንንም ቃል በደብዳቤ አለመላኬ ደብዳቤውን ብቻዎን አይተው ቀደው ጥለው ፤ ሰምተው እንዳልሰማ ሆነው ሸሽተው ይሔዳሉ ። በቃል የሆነ እንደሆነ ግን ፤ ይኸን ሰምተው ቢሸሹ አሽከሮችዎ ይታዘቡዎታልና በቃል መላኬ ስለዚህ ነው" ብለዋል አሉ ።

"ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፡ ይኸን የመሰለውን የትዕቢት ቃል እንደምን ላኩ" በማለት የሚያጠያይቅ ነው ። በእርግጥም የንጉሡ ነገሥቱ ውስጠ ድጋፍ እንደ ነበራቸው ይታመናል ። ነገር ግን ፤ "ከሸዋው ንጉሥ ውጊያ ስገጥም መጥተው ይረዱኛል" ብለው እንዳያምኑ ሁለቱ ያሉበት መንቆረርና ደብረ ታቦር የተራራቀ ነው ። ይኸን ደብዳቤ ሲልኩ ደግሞ ፤ አባይን ተሻግረው ወደ ጉድሩ ስለተጠጉ የበለጠ ርቀዋል ።

ንጉሥ ምኒልክ ይኸን ቃል በሰሙ ጊዜ ፤ "ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ይኸን የመሰለ ቃል አይልክብኝም ፤ እውነት ቢሆን ኖሮ በማኅተሙ አትሞ በደብዳቤ ይልክብኝ ነበር ። ስለዚህ እናንተ ዋሽታችኋልና

1 ምኒልክ ገና ላፄ ዮሐንስ ሳይገቡ ጐጃምንና ቤጌምድርን አስገብረለሁ ብለው የዘመቱትን ሲያስታውሱ ነው ። ጸ. ት. ገ. ሥላሴ ፤ ታሪክ ዘመን ዘዳግ. ምኒልክ ፤ ገጽ 104 ።

* በዚያው ከአባይ ወንዝ ወዲህ ማዶ ያሉ ወረዳዎች ናቸው ። ጅማ የሚለውም እዚሁ አጠገብ ያለውን እንጂ ከጊቤ ወንዝ ወዲያ ያለውን የከፋውን ጅማ አይደለም ።

ተይዛችሁ ተቀመጡ” ቢሏቸው ፣ መልክተኞቹ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ቃል መሆኑን በመሐላ አረጋገጡላቸው ። ከዚህ በኋላ ንጉሡ ፣ “እንግዲያው ከእናንተ አንዱ ሔዶ ‘አወን ልኬያቸዋለሁ’ የሚል ደብዳቤ ይዞ ይመለስ ፣ የቀራችሁት እንደ ተያዛችሁ እዚሁ ቆዩ” ብለው “እኔ ላንተ ጦርነት ሠግቼ ሸሽቼ አልሔድም ። ነገር ግን ፣ ከኔ ጋራ ለመዋጋት ከዐፄ ዮሐንስ ፈቃድ አግኝተህ እንደሆነ ፈቃድ ማግኘትህን በደብዳቤ እንድትልክብኝ ብዬ ነው እንጂ ፣ ለጦርነቱስ እዚያው አገርህ ደረቤ* ሜዳ ላይም ቢሆን እመጣልሃለሁና አንተን መንገድ አይምታህ ። ይኸንን ም በደብዳቤ አለመላኬ አንተ ደብዳቤውን ስት ጠላው አይቼ ነው” ብለህ ንገረው ብለውት መላክተኛው ወደ ጌታው ወደ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሔደ ።

ከዚህ በላይ ያለውን የምኒልክን አባባል የጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴና የብላቴን ጌታ ኅሩይ ጽሑፎች ሲያመለክቱን በጐጃም በኩል አለቃ ተክሌ ያሠፈሩት ፣ በመሠረቱ አንድ ሆኖ በአነጋገር እንደዚህ ሲል ይለያያል ። “ንጉሥ ምኒልክም መኳንንቱን ሰብስቦ ቃሉን ሰምቶ አዘነ ። የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ቤት የጐበዝ መካር ነው እንጂ የሽማግሌ መካር የለበትም አለ ። ከዚህ በኋላ ለመላክተኞች ሐያ ሐያ ብር ሰጥቶ ፣ እኔ በጉልበቴ ፣ በሠራዊቴ እንዳንተ አልመካም ። ጉልበቴ ክርስቶስ ነው ። ቢሆንም እንታረቅ ሕዝቡ አይለቅ ግድ(እምቢ) ያልህ እንደሆነ እንደ መጣህ እቆይሃለሁ” 1

ምኒልክ መላክተኞቹን ወደ ተክለ ሃይማኖት ከላኩ በኋላ አከታትለው ፣ “እስቲ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ለጦርነት በእርግጥ መጥቶ እንደሆነ ወደ አባይ ወንዝ ብቅ ብለህ መርምር” ብለው ደጃች ወልዴን ላኩዋቸው ።** ደጃዝማቹም ሔደው ሁኔታውን አጣርተው እንደ ተመለሱ ፣ “አወን ከአባይ ወንዝ ወዲህ ብዙ የድንኳን ሠፈር አይቻለሁ” ብለው ተናገሩ ። ምኒልክም ከሠፈራቸው ተነሥተው ወደ ጉድሩ በመጓዝ ይላሉ እንደ ደረሱ በግንቦት 28 ቀን በበረህ ሜዳ ላይ ሠራዊታቸውን አሠልፈው ጐበኙ ። በግንቦት 30 ቀን ማለዳ

* ደብረማርቆስ ከመከተሙ በፊት የንጉሥ ተክለሃይማኖት ከተማ መንቆረር ነበር ፤ ደረቤ ወደ መንቆረር አጠገብ የሚገኝ ሜዳማ ሥፍራ ነው ።

1 ያለቃ ተክሌ የእጅ ጽሑፍ ፣ ገጽ 125

** ደጃች ወልዴ የኤፍራታ ተወላጅ ፣ በኋላ ራስ ወልዴ የተባሉት የደጃች መሸሻ አባት ናቸው ።



እምባቦ ሜዳ ሲደርሱ የጐጃሞች ግምባር ቀደሙ (ፊታውራሪ) ጦር ታየ ።1

እዚህ ላይ የሁለቱም ወገን የጦር ሠራዊት መልኩም ልብሱም ተመሳሳይ ፣ ሃይማኖቱም ክርስቲያን ስለሆነና አብዛኛውም እርስ በርሱ በመልክና በስም የማይተዋወቀው ተደበላልቆ ሲዋጋ ፣ ወገን ለወገኑ ጠላቱን ያገኘ መስሎት መትቶ እንዳይገድለው የመለያ አነጋገር (ርችት ወይም ምልክት) በሸዋዎቹ በኩል እንደዚህ የሚል ተፈጠረ ።

ጥያቄ ፡ የማን ነህ?

መልስ ፡ ያባ ዳኘው (የምኒልክ)

ጥያቄ ፡ ዳኘው ምን አለ?

መልስ ፡ ስለበው አለ2

በዚህ ዐይነት ያንዲቱ የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነው የሁለቱ ወገን ጦር ሠራዊት ማክሰኞ ግንቦት 30 ቀን 1874 ዓ.ም. ከቀኑ በአምስት ሰዓት ውጊያ ገጠመ ። በጦርነቱ ሰዓት ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የሸዋው የፈረሰኛ ጦር እንደማይቻል እያጋነኑ ፣ ከእርሳቸው ወገን አንድም ሰው በፈረሱ ላይ እንዳይወጣ አስጠንቅቀው ነበር ይባላል ። ይኸንንም ማለታቸው ተዋጊው ጦራቸው የሚሸሽበት ፈረስ እንዲያጣና ጠንክሮ እንዲዋጋ ነበር ። በሸዋ በኩል ደግሞ ምኒልክ“ አንድ ጐጃሜ እንዳያመልጥህ ጠብቅ ፣ ካላዘዝኩህ በቀር አትዋጋ ፣ ከበህ ተመልከት” የሚል ትእዛዝ ለራስ ጐበና ሰጥተው ወደፊት ተጓዙ ። ጐጃሞቹ የመድፍ ጥይት አከታትለው በመተኮስ ብዙ ሰው ሲፈጁ እያዩ ፣ ምኒልክ አሁንም ጦራቸው እንዳይተኩስ አስጠንቅቀው ወደፊት መጓዝ ቀጠሉ ። በጣም ሲጠጉም ባጠገባቸው ለነበሩት ለሰናድር ያዥ ዘበኞች ፣ ለባለሚሎች ፣ ለባሩድ ቤቶች* “ተመሬት ተኛ” ብለው አዘዙ ። ከዚያም ራሳቸው ጠጣው በሚባለው ፈረሳቸው ላይ እንደ ወጡ ፈረሱ አንገቱ ላይ ተመትቶ መውደቁን አለቃ ተክሌና ነጋድራስ

1 ያለቃ ተክሌ የእጅ ጽሑፍ ገጽ 124-130 ።

2 በዚህ የርቼት ቃል ምኒልክ ሰለባን እንደ ፈቀዱ ያሳያልና እውነት እንደሆነ የማይገባ ሥርተዋል ማለት ነው ። በኋላ ደግሞ የሰለቡትን ሰዎች ስለ ወቀሱና በዐዋጅ ስለ ከለከሉ ፡ ሁኔታው ትንሽ የተማታ ነው ። የብላቴን ጌታ ኅሩይ የእጅ ጽሑፍ፣ ገጽ 107-109 ።

* ሰናድር ያዥ ፣ ባለሚል ፣ ባሩድ ቤት የሚባሉት ልዩ ልዩ የወታደሩ ክፍልና ባለ ጠመንጃ ነው ።

አፈወርቅ ይገልጻሉ ። አባ ዳኛው በሌላ ፈረስ ቢወጡም ይኸኛውም
ፈረስ በጥይት ቆሰለ ። በዚህ ጊዜ የተያዘላቸውን ዣንጥላ ዒላማ አድርጎ
የጐጃም ጦረኛ ተኩሶ እንዳይመታቸው በመሥጋት ጥላ ያዥው ቢያ
ጥፍ ፡ "የኔ ጥላ አይታጠፍም ፡ ዘርጋ" ብለው ተቆጡ ። ወዲያው የጐ
ጃም ጦር በፉከራ እየተታኮሰ ሲቀርብ "በል እንግዲህ ሳትነሣ ተኩስ"
ብለው ለጦራቸው ትዕዛዝ ሰጡ ። ጦሩም እንደ ዔሊ እንገቱን ብቻ
ቀና እያደረገ የጥይት እሩምታ ሲዘራ ብዙ የጐጃም ዐርበኛ ወደቀ ።
ከሁለት ሰዓት ውጊያ በኋላ ፡ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከብዙ ቦታ ላይ
ቆስለው መማረካቸውን ፤ ተማርከው እንደ ቀረቡም "ይማሩኝ" ብለው
መውደቃቸውንና ምኒልክም ፡ "አይዞህ ምንም አላደርግህ ተነሥና
ሳመኝ" ብለው በእጃቸው አንሥተው ፡ ሁለቱ ነገሥታት መሳሳማቸ
ውን ፤ ቁስላቸውንም አይተው በማዘን ምኒልክ ፡ በገዛ እጃቸው አክ
መው እንዳዳኗቸው ጸሐፌ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ በዝርዝር አመልክተዋል ።
በመገምገሪያ ማርከው ወደ ንጉሥ ምኒልክ ያመጡዋቸው ደጃዝማች
መንገሻ አቲከም(በኋላ ራስ ቢቶደድ) መሆናቸውን አለቃ ተክሌ ዘግ
በዋል ።

በዚህም ቀን ጦርነት ፡ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከመማረካቸው
በፊትና በኋላ በዐፄ ምኒልክ የንጉሠ ነገሥትነት ዘመን አንድ ጊዜ
ንቡረ ዕድ ቀጥሎም ፡ እጨጌነት ይዘው የነበሩት አባ ወልደ ጊዮር
ጊስ በጐጃሞቹ በኩል ሆነው በተፋፋመ ጦርነት ማኸል ለማኸል
ሰይፋቸውን እንደ ታጠቁ እየተዘዋወሩ 'ወታደር ሆነህ የሸሸህ ገዝቻ
ለሁ' እያሉ በርትተው ማዋጋታቸውን ከጦር አለቆች ዋናው መሪ ራስ
ደረሶና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከተማረኩ በኋላ ፡ "ንጉሣችሁ ተማር
ከዋልና እጃችሁን ስጡ" የሚል የለፈፉ ድምፅ ቢሰሙ ፡ "ወጊድ
በለው ፡ ንጉሥ ያለ በደብረ ታቦር ነው" ብለው በዝግንነት እስከ
ዘጠኝ ሰዓት ድረስ መዋጋታቸውን ፡ ከሸዋ በኩል በመስተዋት የተመ
ራው የወሎ ጦርና ደጃች ወሌ የጀግንነት ሙያ ማሳየታቸው በነጋድ
ራስ አፈወርቅ ጽሑፍ ተጠቅሷል ።[2]

ነገር ግን ራስ ደረሶም ፡ ራስ በዛብህም ፡ ደጃች ሥዩምም (ራስ
ኃይሉ) ፡ አባ ወልደ ጊዮርጊስም ምንም ጠንክረው ቢዋጉምና ቢያዋጉ

---

1 አቶ ዐጽሜ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን መማረክ ጦርነቱ ከተጀመረ ከአንድ ሰዓት በኋላ አድርገውታል ። ገጽ 154 ። ማርከስ ደግሞ በገጽ 69 ከ4 ሰዓት ጀምሮ እስከ ሰዓት በኋላ ድረስ መቆየቱን ገልጿል ።

2 ጸ.ት. ገ/ሥላሴ ፡ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፡ ገጽ ፤02-፤07 ። ጸ.ት. ገ/ሥላሴ ፡ ታሪክ ... ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ፡ ገጽ 32-37 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወ/ሥላሴ አፈወርቅ ገ/የሱስ ፡ ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ፡ ገጽ 32-37 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወ/ሥላሴ የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐድዋ ጦርነት ፡ ገጽ ፤04-108



ዋናው መሪ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከተማረኩ በኋላ ፡ በጐጃሞቹ
በኩል የድል አድራጊነት ተስፋ እንደማይኖር ግልጽ ነበር ። እንደ
ኢትዮጵያ ያለ ኋላ ቀርና በበላይ መሪው ብቻ የሚታዘዝ ጦር ከመሪው ጋር
ያላገኘውን ድል ብቻውን ያገኘዋል ማለት ከንቱ ነው ። ቢሆንም
ጦርነቱ በአምስት ሰዓት ተዠምሮ ወደ ሰባቱ ሰዓት ላይ ንጉሡ ከተ
ማረኩ በኋላ ፡ እነራስ ደረሶ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ሁለት ሰዓት
ለብቻቸው መቀጠላቸው በእርግጥም የነራስ ደረሶን እልህና ዤግንነ
ታቸውን በትክክል የሚያሳይ ነው ማለት ነው ።

የቀድሞ ጸሐፊዎቻችን የሁለቱን ወገን አሰላለፍ ፡ ይኸውም ማለት
የያንዳንዳቸውን የሠራዊት ቁጥር ፡ የባለ ጠበንጃውንና የባለ ጦሩን ፡
በጦርነት ላይ የቆሰለውንና የሞተውን በየታሪካዊ ጽሑፋቸው ላይ
አሥፍረው አላቆዩንም ። ቢሆንም ፡ የጦርነቱ አዝማሚያ ሲገመገም
በጐጃሞቹ በኩል እልህ የተበረዘበት የጀብዱ ሥራ ሲታይ ፡ በሸዋዎቹ
በኩል ለተኩስ ሳይቸኩሉ ለጠላት ደረትን ሳይሰጡና ለጥይት ሳይመቹ
ተኝቶ ጠላትን በጥይት እየመቱ በመጣል የተሻለ የአወጋግ ዘዴና
ዝግጅት እንደ ነበረ ይታያል ። የዚህም ምክንያት ፡ ንጉሥ ተክለ ሃይማ
ኖት አዳል ተሰማ እየተባሉ በዚያው ባገራቸው ፡ በጐጃም ፡ በዘመዶ
ቻቸው በነደጃች ብሩ ጐሹ ፡ በነደጃች ተድላ ጓሉ ቤት የወጣትነት
ጊዜያቸውን ሲያሳልፉ ፡ ምኒልክ ከ12 ዓመት ዕድሜ ዠምረው ባፄ
ቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት ባለሟልም ፡ አማችም ሆነው የ10 ዓመት
ጊዜ ሲያሳልፉ ብዙ የጦርነት ሁኔታ በቃልም በልምምድም ያጠኑ
ይመስላል ።

በመጨረሻ ፡ መቅደላ በግዞት በነበሩበት አጭር ጊዜ ውሏቸው
ከተጋዙት ፈረንጆች ጋር እንደ ነበረ ፡ ወደ ሸዋም ተመልሰው በሸዋ
እንዳባቶቻቸው የነጋሢነት ሥልጣን ከያዙ ወዲህ ፈረንሳዮቹን እነ
ሙሴ ፒዬር አርኑን ፡ ኢጣልያኖቹን እነ አንቲኖሪን ፡ እነ ማርቲኒን
እያቀራረቡ የአውሮፓዎችን ባህልና ሥልጣኔ መጠየቅና መረዳት
ይወዱ ስለነበረ የጦርነቱንም ሥልት ተራመድ ፡ ተኩስ ፡ ውደቅ ፡
ተነሡንም በመጠኑ ከፈረንጆቹ አጥንተው በቃል ያጠኑትን በዚህ
በእምባቦ ጦርነት ከሥራ ላይ አውለውታል ማለት ነው ።

በዚህ በእምባቦ ጦርነት ፡ ከሸዋ ወገን የሞቱት ቁጥር 913 ፡
የቆሰለው 1648 ፡ በጦርነቱ ሜዳ በውጊያ የወደቀው ፈረስ 534 መሆ
ኑንና በሰሞኑ በተነሣው በሽታ የሞተው ቁጥር 3123 መድረሱን
ከጦርነቱ ቀደም ባለው ጊዜ ፊታውራሪ ሸዋረገድ የሚባሉት
የራስ ዳርጌ ልጅ በሚያዝያ 10 ቀን ከፈረስ ወድቀው በዶዶሳ ወንዝ
ሠፈር በተደረገበት ጊዜ ሞተው ሬሳቸው በሳጥን ሆኖ እየተጓዘ ቆይቶ

ወደ እንጦጦ ተመልሰው ላባታቸው አስረከበው በታላቅ ሐዘን መቀበራቸውን አቶ ዐፅሜ ገልጸዋል ።[1] በጉጃም በኩል ስለ ደረሰው ጉዳት የሚገልጽ መረጃ አልተገኘም ።

1 አቶ ዐፅሜ ፣ የጋላ ታሪክ ፣ ገጽ 154- 155
ከደጃዝማች መታፈሪያ መልክ ጻዲቅና ከብላታ ደሬሳ አመንቴ የቃል ገለጻ የተገኘ ።






ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የተዋጉበት የእምባቦ ቀበሌ

# ምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ

## የአሸናፊ በጎ አድራጊ — የንጉሥ ምኒልክና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጉዞ ወደ እንጦጦ—ወረይሉ ላይ ካፄ ዮሐንስ ተገናኙተው በሁለቱም ላይ የደረሰው ቅጣት

በዚህ በአሁኑም ፥ ባለፈውም ወደፊትም በሚያደርጉት ጦርነት ሁሉ ምኒልክ በጉልበታቸውና በኃይላቸው የመመካት ፥ ጦር የማጫር ሁኔታ አይታይባቸውም ። ተዋግተው ካሸነፉ በኋላ እጃቸው በወደቀው ምርኮኛ ላይ 'በለው ፥ ግረፈው ፥ ቁረጠው' የሚባል የጭካኔና የዕብሪት ሥራ አያሳዩም ። በዚህ ፈንታ በርኅራኄ ለሁሉም የሚገባውን በጎ አድራጎት ከፈጸሙ በኋላ ፥ ጠቅላላው የባላጋራ ጦር በውድም በግድም ታዞ የመጣ መሆኑን ስለሚረዱት ፥ ጠቅላላ ምሕረት ከማድረግ በቀር ተሠልፎ የወጋኝን ሁሉ አስሬ ላጉላላው ወይም ልግደለው አይሉም ።

አሁንም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፥ ምንም እንኳን ከውጊያው በፊት የትዕቢት ቃል በመላክና አባይን ተሻግረው መጥተው ቢወጉዋቸው ፥ ቆስለውና ተማርከው ከፊታቸው ሲደርሱ በምን አኳኋን እንደ ተቀበሏቸው ከጐጃምም አለቃ ተክሌ ሲያወሱ እንደዚህ ብለዋል ። "ያን ጊዜ ንጉሥ ምኒልክ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የርኅራኄ ሥራ ሠራለት እንጂ ፥ ስድቡን ቂም አድርጎ አልጨከነበትም ። ከብዙ ላይ ቆስሎ ነበርና ሐኪም ፈልጎ አረሩን (ጥይቱን) አስወጥቶ ፍሪዳና ማር ፥ ቅቤ እየመገበ ጧት ማታ እየተመላለሰ እየጠየቀ አዳነው ።" 1

ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ይኸን በጎ አድራጎት ሲያሳዩ እርሳቸውን ተከትሎ ለተዋጋው የጐጃም ጦር ፥ "እኔ ሳልፈልጋችሁ እናንተ ፈልጋችሁኝ መጣችሁ ፥ እግዚአብሔር ግን በትዕቢታችሁ ጣላችሁ አሁንም በያገራችሁ ግቡ" የሚል ዐዋጅ አድርገው ፥ ከጌታዩ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አልለይም ያለው እንዲከተል ፥ ወዳገሬ እገባለሁ ያለውን አደጋ እንዳያገኘው ራስ ጐበና እየጠበቁ አባይ ወንዝ ድረስ

---

1 ያለቃ ተክለ ሥላሴ የእጅ ጽሑፍ ፥ ገጽ 126-127

እንዲሸፍ ፤ የቆሰለውንና የደከመውን ያገሩ ባላባቶች እነ ፊታውራሪ
ቀዲዳ በየቤታቸው ተቀብለው ፣ አስታመው ሲድኑ እንዲሸፍ አድር
ገው ፣ በበቅሎ ለመሔድ ያልቻሉትን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን በእ
ልጋ አስተኝተው በዝግታ የመልስ ጉዞው በሰኔ 5 ቀን ተዠምሮ በሰኔ
19 ቀን እንጦጦ ከተማቸው ገቡ ።[1]

እንደ ገቡም ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የተለየ አዳራሽና እልፍኝ
ተዘጋጅቶ ፣ ምርኮኛውን ንጉሥ ከእምባቦ የተከተላቸውንና ከጐጃም
የመጣውንም ጭፍራቸውን ከእንጦጦው ቤተ መንግሥት ምግብና
መጠጥ እየቀረበ ግብር ሲያበሉ ፣ ሁለቱም ነገሥታት እንደ ባላጋራ
ሳይተያዩ ፣ እንደ ሁለት ወንድማማች በሰላምና በደስታ ወግ እየተለ
ዋወጡ ሲጫወቱ ሰነበቱ ። ከዕለታት አንድ ቀን በዚሁ የጭውውት ጊዜ፣
"ለማህ ወይ ፣ እኔ ማርኬ እንደዚህ እንቀባርሬ እስቀመጥሁህ ፣ ተሸንፌ
እንተ ማርከኸኝ ቢሆን ኖሮ ምን ታደርገኝ ነበር?" ብለው ምኒልክ
ለተክለ ሃይማኖት ጥያቄ ቢያቀርቡ ፣ የጐጃሙ ንጉሥ ፣ "እኔማ ብሆን
ቆራርጬ ነበር የምጥልዎ" ብለው መለሱና ሣቅ ሆነ ። ቀጠል አድር
ገው ምኒልክ "ታዲያ የሚሻለው ያንተ ነው ወይስ የኔ" የሚል ጥያቄ
ቢያስከትሉ ፣ "ሲያሸንፉ ለተሸነፈ ኀራራት እግባብ ነው" ብለው
የምኒልክን አቅዋም የተሻለ መሆኑን አጸደቁ ይባላል ። "እኔ
ብሆን ቆራርጬ ነበር የምጥልዎ" ያሉትም ምናልባት ለማሣቅና
ምኒልክን ለማስደሰት ይሆናል እንጂ ከልብ ላይሆን ይችላል ።[2]

ሁለቱ ነገሥታት በሚዋጉበት ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስ
ደብረ ታቦር ከተማ ነበሩ ። ቀደም ብለው ፣ "እኔ መጥቼ በዳኝነት
እስከገላግላችሁ ድረስ በየወሰናችሁ እርጉ ፣ እንዳትዋጉ" ብለው በደ
ብዳቤ ማስጠንቀቃቸው ይታወሳል ። አዲስ የመጡት ጳጳሳትም ፣ በንጉሠ
ነገሥቱ ማሳሰቢያ ላይ ውግዘት ጨምረው ለሁለቱም ነገሥታት ከላ
ኳቸው ደብዳቤዎች ለምኒልክ የደረሳቸው ከተዋጉ በኋላ ነበር ። ለን
ጉሥ ተክለ ሃይማኖት የተጻፈውንም አንዳንዶቹ ደስታ ኃይሉ የሚባ
ለው ሽፍታ ፣ አንዳንዶች ደግሞ ራስ ደረሶ ተቀብለው ንጉሡ ያዩት
እንደሆን ጦርነቱን እንዳያስቀሩት በመሥጋት ሳያሳዩአቸው ደበቁት
ይባላል ።

1 እቶ ዐጥሜ የጋላ ታሪክ ፣ ገጽ 155 ።
2 ጸ.ት.ገ.ሥላሴ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ገጽ 102-107 ።
ጸሐፌ ትእዛዝ የጥያቄና የመልስ ጭውውቱን እስታ ተክለ ሥላሴ በምኒልክና በን.ተ.ሃይማኖት
መኳንንት መካከል አድርገውታል ፤ ገጽ 127 ።



ዐፄ ዮሐንስ የሁለቱን ነገሥታት ውጊያ የምኒልክን ማሸነፍ ፣
የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን መማረክ ሲሰሙ ፣ መኳንንቶቻቸውን ሰብስ
በው "ክረምት ሲወጣ ወደ ሸዋ እንዘምታለንና ከብታችሁን እያጠነ
ከራችሁ ክረሙ" ቢሏቸው ፣ ከመኳንንቱ የሚበዙት "ንጉሥ ምኒልክ
እንኳን የጐጃሞችን መሣሪያ ጨምረው በራሳቸውም ቢሆን የሚያስ
ፈሩ ሆነዋልና አሁኑኑ ቁስለኛው ሳይሽር ፣ የደከመው ሳይበረታ ፣ ገመ
ምተኛው ሳይነሣና ሳይጠነክር ብንደርስባቸው ይሻላል እንጂ ክረምት
ውጭስ እንችላቸውም" ብለው ስለ መከሩዋቸው ፣ "ሰኔ ሲያልቅ
ሐምሌ ሲገባ ከደብረ ታቦር ተነሥተው በአማራ ሳይንት በኩል
ተጓዙ" ሲሉ ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴና የርሳቸውንም ጽሑፍ
መሠረት ያደረጉት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ያረጋግጣሉ ።[1]

ይኸ ሁኔታ ከሁለቱ ነገሥታት ጦርነት በፊት ንጉሠ ነገሥቱ
በሁለቱ ተዋጊዎች ላይ የነበራቸውን ስሜት በትክክል ይገልጸል ። በጦ
ርነቱም ጊዜ ተክለ ሃይማኖት ምኒልክን አሸንፈው ኃይላቸውን ቢቀንሱ
ላቸው ይወዱ እንደነበረ አይጠረጠርም ። ተክለ ሃይማኖት ቢያሸንፉም
በአሸናፊነት እኔን ይጫናል በማለት እንዝመትበት የሚልም ስሜት
በርሳቸውም ፣ በመኳንንቶቻቸውም ልብ እያድርም ነበር ለማለት አይ
ቻልም ። በዚህ ምክንያት ፣ ከእምባቦ ዠምሮ ምኒልክና ተክለ ሃይማ
ኖት ባላጋራነታቸውን ረስተው ሲወያዩ ፣ ሲወዳጁ የምኒልክ የአሸና
ፊነት ወሬ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መሣሪያ በንጉሥ ምኒልክ እጅ
መግባት በዐፄ ዮሐንስ ሠፈር ሲሰማ ሥጋት ሳይጥል አልቀረም ።

ስለዚህ ፣ ዐፄ ዮሐንስ በሸዋ ላይ ለመዝመት ከነሠራዊታቸው ፤
በዋናው ክረምት በሐምሌ ወር ፣ በውሃ ሙላት ብዙ ሰውም እያለቀባ
ቸው ወደ ወሎ ተጓዙ ። በዚህም ጊዜ ደጃዝማች መሸሻ ሰይፉ የምኒ
ልክ የዙፋን ባላንጣ ሸፍተው ብዙ ጊዜ ከራስ ዳርጌም ፣ ከነደጃች
ወልደ ሚካኤልም ጋር በሚዋጉበት ጊዜ በገሃድ ያዬ ዮሐንስ ድጋፍ
እንደ ነበራቸው ይገመታል ።[*] በኋላ ደግሞ ምኒልክ ለዮሐንስ ገብ
ተው ስምምነቱ ስለ ተዠመረ ፣ ዮሐንስ ለመሸሻ የሚሰጡትን ድጋፍ
ቀዝቀዝ አድርገው የነበረውን አሁን በምኒልክ ትእዛዝ ከታሰሩበት
ሥፍራ ከአትሮንስ ማርያም ፈትተው ግንባር ቀደም በማድረግ በም
ኒልክ ላይ ለመጫን ይዘው በለጋምቦ በኩል አድርገው ወደ ወረይሉ

1 ብ.ጌ.ኅሩይ ፣ የኢት ታሪክ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐድዋ ጦርነት ፣ ገጽ 109-110
* መሸሻ ሰይፉ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ ያቤቶ ሰይፉ ልጅ ስለሆኑ ከንጉሥ
ኃይለ መለኮት ልጅ ከምኒልክ ጋራ የታናሽና የታላቅ ልጆች ናቸው ማለት ነው።

በግሥጋሜ ሲጓዙ ፣ ምኒልክ ምንም እንኳን ከተክለ ሃይማኖት ተራር ቀው ቢወዳጁ ያዬ ዮሐንስ በክረምት ወደ ወሎ ግሥገሣ ለሰላም አለ መሆኑን ቢረዱትም ፣ እንደ ልማዳቸው ስሜታቸውን በልባቸው ይዘው የእምባቦን የጦርነት ሁኔታ በደብዳቤ አድርገው መልከተኞቻቸውን ደጃች መሸሻ ወርቄንና የሻነው ተፈሪ የሚባሉትን ወዳዬ ዮሐንስ ልከው ሁኔታውን በትዕግሥት ሲጠባበቁ ቀጥሎ ያለው ደብዳቤ ካዬ ዮሐንስ መጣላቸው ።

> መልእክት ዘሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ. . .ይድረስ ከንጉሥ ምኒልክ . . . በጌምድር ሳለሁ ሁለቱ ነገሥታት ተዋግተው ድሉ ለንጉሥ ምኒልክ ሆነ ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይ ማኖትን ይዘው ወደ ሸዋ ተጓዙ ሲሉ ብስማ እግዚአብሔር የፈቀደውን ሠርቷል ። የክርስቲያን ደም በማይረባ ነገር በመፍሰሱ (ሳዝን) የናንተን ደብዳቤ ስጠብቅ ደብረ ታቦር ላይ ወር ሙሉ ተቀመጥሁ ። ኋላ ግን ወሬያችሁ ቢጠፋ ብኝ ይህስ ነገር አለበት ብዬ ተነሥቼ ስመጣ ሳይንትን ሳል ፈው የንጉሥ ወረቀት ደረሰልኝ ። ደብዳቤውንም አይቼ ፣ መዘግየቱ በመንገዱ ርዝመት ሆኖ ተንኮል አለመኖሩን ሳውቅ ወደ ቤገምድር ለመመለስ አሰብሁ ። ነገር ግን፣ክረምቱ ተጭኗልና ሠራዊቱ የሚጐዳብኝ ሆነ ። በወሎ እንድከርም ፈቃድ ይደረግልኝ ። እኔም አገር አልበድልም ። በጥቢ(ክረ ምት ሲወጣ) ተገናኝተን ሁሉንም ተማክረን ወደ ቤገም ድር መመለስ ይሻለኛል ብዬ ነው እንጂ ሌላ ጉዳይ ኖሮ ብኝ አይደለም ። ደግሞ ይህም የሚያሳዝን ነገር ሲሆን ተመልሼ ሠራዊቱ በውሃ ሙላት በጭቃ ያለቀው አልቆ የተረፈውን ይዤ መመለስ ይሻለኛል ።[1]

በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ፣ "ወሬያችሁ ቢጠፋብኝ ይህስ ነገር አለ በት" የሚለው ቃል ምኒልክን "በኔ ላይ የሸፈቱ መስሎኝ" ለማለት ነው ። ከዚያ ደግሞ ዝቅ ብለው ፣ "ተንኰል አለመኖሩን ባውቅ ወደ ቤገምድር ለመመለስ አሰብሁ" የሚሉት ፣ ደብዳቤው የዘገየው በመን ገድ ርዝመት እንጂ ፣ በኔ ላይ ለማመጥ አሳብ እንደሌለዎ ስለተረዳሁ ወደ ቤገምድር ለመመለስ አሰብሁ ማለታቸው ነው ። ከዚህ ጋር መደምደሚያውን የመላዋ ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆነው ለምኒል ክም የበላይ ገዥ መሆናቸው ሲታወቅ ፣ "በወሎ እንድከርም ፈቃድ ይደረግልኝ" ማለታቸው ፣ ንጉሥ ምኒልክ ገና ዐፄ ቴዎድሮስ ሳይሞቱ በሸዋ ላይ ወሎን የራሳቸው ግዛት አድርገው በወረይሉ ከተማ ከት መዋል ። ወደ እምባቦ ሲዘምቱ የወሎዋ ባላባት ወይዘሮ መስተዋት ጭፍራ ይዘው ምኒልክን የተከተሉበት ምክንያት ይኸው ነው ።

ስለዚህ ዘመኑ ምንም የበላይ ንጉሠ ነገሥት ያለበት ቢሆን የባለ ጉልት ጊዜና እያንዳንዱ መስፍን በቤቱ አዛዥ ፣ ናዛዥ እርሱ ስለሆነ ያለርሱ ፈቃድና መስተንግዶ አንዱ መስፍን ፣ ንጉሠ ነገሥትም ቢሆን በግዛቱ ውስጥ አይገባበትም ። "አገር አላጠፋም" ማለታቸውም አንዱ ንጉሥ ወይም መስፍን ካንዱ አገር ወደ ሌላው ሲሔድ ከተነሣ በት አገር በቂ ስንቅ መያዝ ይቸግረዋል ። ቢይዝም የጉዞው ወይም የዘመቻው ጊዜ በረዘመ መጠን ስንቁ ያልቅና ለወታደር ያለው ምርጫ ከሠፈረበት አውራጃ ካለው ነዋሪ ሕዝብ ላይ ዘርፎ መብላት ነው ። ከዚህ የተነሣ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ አገር አልበድልም ማለታቸው በትዕዛዝ ወይም በይሉኝታ በነራስ ሚካኤል አማካይነት ሕዝቡ ዐውቆ ይሰጠ ኛል እንጂ እንዲዘረፍ አላደርግም ማለታቸው ነው ።

የዚህን ዐይነቱን ያዬ ዮሐንስን የትሕትና አባባል ፣ የንጉሥ ምኒ ልክ መልስ ሞገስ ሰጥቶት ይገኛል ። ንጉሠ ነገሥቱና ንጉሡ እንደ መልካም የፖለቲካ ሰው በቃል ልውውጥ እየተሜወቱ ፣ እንደ ኃይለኛ ባላጋራ ውስጥ ለውስጥ እየተጐነታተሉ ፣ በይፋ ደግሞ በጨዋነት እየ ተከባበሩ ፣ በሁለቱ ጐን ላሉት ወደ ጠብ ለሚገፋፉዋቸው የጦር ባለሥ ልጣኖች መንገድ ከመስጠት እንደሚቆጠቡ ይታያል ።

በዚህ ምክንያት ፣ ምኒልክ ደብዳቤው እንደ ደረሳቸው በእምባ ቦው የጦርነትና በጉዞ ሠራዊታቸው መድከሙንና የክረምቱን መከ በድ ሳያመካኙ ፣ "ጃንሆይ ፣ እንደዚህ ከቀረቡ ሳንገናኝ አንከርምም ። እኔም መጣሁ ። ከድንኳን ቤት ይሻላልና ወረይሉ ከኔ ቤት ይግቡ" የሚል ደብዳቤ አስቀድመው በሐምሌ 14 ቀን 1875 ዓ.ም. ከእን ጦጦ ተነሥተው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን እንደያዙ በሐምሌ 16 ቀን ደብረ ብርሃን አድረው በነሐሴ 7 ቀን ወረይሉ ሲደርሱ ንጉሠ ነገሥቱ በታላቅ ክብርና በመድፍ ተኩስ ተቀበሏቸው ። በዚያን ጊዜ ያዬ ዮሐንስም መኳንንት "ጦራቸው ከኛ ይበልጣል ለምን አልወጉ ንም" እያሉ ምኒልክን አሙ ይባላል ።[1]

እንደ ተገናኙ ምንም እንኳን ሁለቱ የቀድሞ ጠበኞች እንጦጦ ሳሉ ላለመከሳሰስ ውስጠ ስምምነትና ልባዊ ዕርቅ ቢያደርጉም ፣ ንጉሠ

---

1 ብ.ጌ. ኀሩይ የኢት- ታሪክ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐድዋ ጦርነት ፣ ገጽ 110-111

1 አቶ ዐጥሜ ፣ የጋላ ታሪክ ገጽ 155-156 ።

ነገሥቱ ሁለቱን ግራና ቀኝ አጳቁመው "እኔ መጥቼ እስክገላግላችሁ ድረስ አትዋጉ" ያሉትን ትዕዛዝ አፍርሰው በመዋጋታቸውና ሰዎቻቸውን በከንቱ በማስጨረሳቸው እንደ ተወቀሱ አለቃ ተክሌ ገልጸውታል ። ጸሐፊው በምኒልክ ላይ የተሠነዘረውን ወቀሳና ከምኒልክ ወገን የተሰጠውን መልስ ሳይጠቅሱ ተክለ ሃይማኖት ከንጉሠ ነገሥቱ ፣ "ለምን ተዋጋህ?" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ፣ "ንጉሥ ምኒልክ እምቢ ብሎ ገፍቶ መጥቶ ያለውድ በግድ ገጠመኝ. . .አሽከሮቼ ያቀኑትን አገር ቀምቶ ምርኮውን ሁሉ እጅ አደረገ ፤ የጃንሆይ ደብዳቤ ቢዘገይብኝ አገሬን ገንዘቤን አልሰጥም ስል ተዋጋሁ" ሲል ፣ ዐፄ ዮሐንስም "አትዋጋ ብዬ የላክሁብህን ደብዳቤ ማን ወሰደው" ብሎ መላክተኞቹን ቢመረምር * "ደስታ ኃይሉ የሚባል ሽፍታ ከመንገድ ቀማን" ብለው እንደ መለሱ ከጠቀሱ በኋላ ዐፄ ዮሐንስ ያለ ትእዛዝ በተዋጉበትና ሕዝቡን ባስፈጁበት ከንጉሥ ምኒልክ ላይ ወሎን ወስደው ለልጃቸው ለራስ አርአያና ለራስ ሚካኤል ፣ ሰባት ቤት አገውን (አገው ምድርን) ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወስደው ለራስ አሉላ መስጠታቸውን ያረጋግጣሉ ።[1]

በመጨረሻ ጊዜ ቤገምድርን ፣ ደምቢያን ለራስ አርአያ ሰጥተው የወሎን ግዛት ጠቅልለው ለክርስትና ልጃቸው ለራስ ሚካኤል ስለ ሰጡዋቸው በምኒልክ ዘንድ ቅሬታ ነበር ። በተለይ እርሳቸው እንደ ወገን ያደረጉዋቸው ወይዘሮ መስተዋትና ልጃቸው ኃይለማርያም እየተዳከሙ ራስ ሚካኤል የወሎን ጠቅላላ ግዛት በመጨበጥ ስለ ተጠናከሩ በምኒልክ ዘንድ ቅሬታው እየባሰ ሔዶ ነበር ።

* አለቃ ተክሌ ባጻጻፋቸው ላይ ዮሐንስም ለማንም የአንቱታ ክበረታ አይሰጡም ።

1 ያለቃ ተክሌ የእጅ ጽሑፍ ገጽ 127-128 ።





ራስ ሚካኤል

(ከሞሪስ ደ ኮፒ)

# ምዕራፍ ሐያ

## የራስ አርአያና የወይዘሮ ዘውዲቱ የጋብቻ መሣሪያነት — የእምባቦው ጦርነት ያስከተለው ውዝግብ — የወሎ ግዛት ከምኒልክ እጅ ወጥቶ በንጉሥ ነገሥቱ ቁጥጥር ውስጥ መግባት

በዓለም ያሉ ነገሥታት ፣ በፈላጭ ቆራጭነት በነበሩበት ዘመን ያንድን አስፈሪ መስፍን ወይም አሥጊ ቀንደኛ መሪ በቀጥታ ማሳ መን ሲያቅታቸው ፣ ወደ ራሳቸው ጐራ ለመሳብ ዘራቸውን ከዘሩ ይደባልቁ ነበር ። ከተደባለቀው ዘር ውስጥ የተገኘው መስፍን ለልጅ ልጅ እንዲገዛና በርሱ አማካይነት የነርሱ ስም ፣ የነርሱ ዝና ለታሪክ እንዲቆይ ጽኑ ምኞታቸው ነበር ። ብዙ ጊዜ ለዚህ ፖለቲካና ለገዥነት ዓላማ ሲባል ለወንድ ያልደረሰች ልጅ አገረድ ፣ ለሴት ያልደረሰ ወጣት መሣሪያ ሆነው በመሥዋዕትነት ሲዳሩ ሲኳሉ ኖረዋል ። ይህ ዐይነቱ ንቅናቄ ግፊት የዘውድ አገዛዝ በሬፑብሊክ ሲለወጥ ፣ ወይም የዘ ውዱ ፈላጭ ቆራጭነት በሕገ መንግሥት ዐዋጅ የተወሰነ ሲሆንና የአስተዳደሩ ሥልጣን ወደ ሕዝብ ወኪሎች የተዛወረ ጊዜ ብቻ ነው ።

በዚሁ መሠረት ፣ ቀደም ባለው ጊዜ ውስጥ ዐፄ ቴዎድሮስ ብዙ ታላላቅ ልጆች እያሏቸው ሕፃኑን ዓለማየሁን አልጋ ወራሽ ያደረጉበት ፣ ወይም ቤት ልጃቸውን ወይዘሮ አልጣሽን ለሸዋው የወጣት መስፍን ለምኒልክ የዳሩበት ከዚሁ ስሜት ጋር የተያያዘ ነበር ። ለጋ ብቻ ከልባቸው ጣይቱን የተመኙት ምኒልክ በተጽዕኖ የጣይቱን ጋብቻ ወደጐን አቆይተው የንጉሡ ነገሥቱን ልጅ አልጣሽን ለማግ ባት ተገድደዋል ።

በዚሁ ዐይነት ፣ ምኒልክና ተክለ ሃይማኖት አንድ ጊዜ ወረይሉ ፣ አንድ ጊዜ ቦሩ ሜዳ በነበሩበት ሰዓት ከንጉሠ ነገሥቱ ካሄ ዮሐንስ ወደ ንጉሥ ምኒልክ ስለ ጋብቻ የተላከውን መልእክት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ እንደዚህ ሲሉ አስፍረውት ይገኛል ። “. . .ዐፄ ዮሐንስ መቼም ቢሆን ለኢትዮጵያ የሚያስቡት አሳብ መሠረት ያለው ነበርና የንጉሥ ምኒልክ ኃይላቸው እየበረታ ፣ ሠራዊታቸው እየበዛ መሔዱን አይተው ፣ “ከእንግዲህ ወዲህ ለእኔም ያለኝ አንድ ወንድ ልጅ

ብቻ ነው ። ለንጉሥ ምኒልክም ያለቻቸው አንዲት ሴት ልጅ ብቻ ናትና የኔ ወንድ ልጅ የንጉሥ ምኒልክን ሴት ልጅ ያገባ እንደሆነ ፣ እኛም ብንሞትና ብናልፍ የሁለታችንም ዘር በአልጋው እንዲቀመጥ ሴት ልጅዎን ለልጄ ይስጡልኝ" ብለው ራስ አሉላን ፣ ራስ ገብረ ኪዳንን ፣ ቢቶደድ ገብረ መስቀልን ወደ ንጉሥ ምኒልክ ላኩዋቸው ። ንጉሥ ምኒልክም ይህን የጋብቻውን ነገር በሰሙ ጊዜ ፣ "የልጅቱ ዕድሜ ገና 6 ዓመት ስለሆነ ፣ ሕፃን በመሆኗ ብቻ ነው እንጂ ጋብቻው እጅግ ያማረ ነውና ጃንሆይ ፈቃዳቸው ከሆነ የኔም ፈቃዴ ነው" ብለው ተናገሩ ። ዐፄ ዮሐንስ አሳባቸው በመፈጸሙ ደስ አላቸው ። ወዲያውም ስለ እምባቦ ጦርነት መቀጫ ከንጉሥ ምኒልክ የተወሰደባቸው የወሎ ግዛት ለራስ አርአያ እንዲሆን ተማከሩና ዐዋጁ ተነገረላቸው ።[1] የራስ አርአያም ዕድሜ በዚህ ጊዜ 12 ዓመት ሲሆን ፣ የዘውዲቱም ዕድሜ እላይ እንደ ተባለው 6 ዓመት ነበር ። የጋብቻውን ዕድሜ እንደ ዚህ ያሳጠረው የፖለቲካው ጋብቻ መሆኑ ነው ። ይኸን የመሰለው ጋብቻም ፣ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ቀደም ብሎ በሌላውም ዓለም ይደረግ ነበር ። የፈረንሳዊ ንጉሥ ሉዊ 15ኛ በ11 ዓመቱ የ3 ዓመቷን የእስፓኝ ንጉሥ ሴት ልጅ ማጨቱ በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል ።[2]

ስለዚህ ፣ በሁለቱም ቤተ መንግሥት የተደገሰውን ድግስ ፣ ለሙሽራውና ለመላከተኞቹ ለነራስ ገብረ ኪዳን ፣ ለነራስ አሉላ የተሰጠውን የሽልማት ብዛቱንና ዐይነቱን ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በሙሉ በመጽሐፋቸው በምዕራፍ 33 ላይ በደንብ ዘርዝረውታል ። ለሙሽራው ለራስ አርአያ ከምኒልክ ከተሰጠው ስጦታ ውስጥ 1 መድፍ ፣ 500 ጠበንጃ ፣ 500 ፈረስና በቅሎ ፣ 500 አገልጋይ ፣ 100 ስርፍና ሥጋጃ ይገኝበታል ። ዐፄ ዮሐንስም ለሙሽራይቱ ለወይዘሮ ዘውዲቱ ከወረይሉ ወደ መኖሪያ ቤታቸው እስኪደርሱ ያደሩበትን ቦታ ሁሉ ርስት ጉልት አድርገው ሰጧቸው ይባላል ።[3]

1 ብ.ጌ.ኅ.ወ/ሥላሴ ፣ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐድዋ ጦርነት ፣ ገጽ 1፤2 ። ጸ.ት. ገብረሥላሴ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ በሚባለው መጽሐፋቸው ልጅቱ ሕፃን ነች እንጂ ምን ከፋኝ ቢሉ ዮሐንስ "የንጉሥ ልጅ ባንቀልባና በማደጉ ይሔዳል (ሔዶ ይዳራል) ግድ የለም" ብለው መለሱ የሚል ይገኝበታል ፤ ምዕ.33 ።

2 M. de Coppet, Chronique du Regne de Menilik p.185,No. 719.

3 Ibid .pp. 185-186 No. 11 ምኒልክ ዘውዲቱን የወለዱዋቸው ከደንበኛ ሚስት ሳይሆን ከወሎ ባላባት ከሚወለዱት ከወይዘሮ አብቺው ሲሆን ፣ ዐፄ ዮሐንስም አርአያን የወለዱ ካንዲት አሊማ የክርስትና ስማቸው (ጥበበ ሥላሴ) ከሚባሉ የደንከል (ጥልጣል) ተወላጅ መሆናቸውን ፣ ሴትዮዋም ክርስትና ተነሥተው እንደቆዩ አርአያ በተወለዱበት ቀን መሞታቸውን አንዳንድ ሰነዶች ይጠቁማሉ ።



ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ ምንም ለግብር ይውጣ "ጥፋቱ የንጉሥ ምኒልክ ነው ፤ የኔ አይደለም" በማለት ዐፄ ዮሐንስ ላይ ክርክር ቢያደርጉም ፣ ከእምባቦ ጦርነት ወዲህ ፣ በጉዞም ላይ ሆነ እንጦጦም ሳሉ በምኒልክ ዘንድ በተደረገላቸው እንክብካቤ ልባቸው ከምኒልክ ጋር ነበር ይባላል ።

ንጉሥ ምኒልክ ፣ በእምባቦ ጦርነት የማረኩትን የጦር መሣሪያ በንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ ፣ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንዲያስረክቡ በመገደዳቸው ቅሬታ ተሰምቷቸው እንደነበረ ብላቴን ጌታ ኅሩይ እንደዚህ ሲሉ ገልጸዋል ። "አንዳንድ ጊዜ ዐፄ ዮሐንስ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የሚያደሉ በመሆናቸው ፣ ንጉሥ ምኒልክ የሞትሁበትን መሣሪያ ለምን ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አስረክብ ይሉኛል በማለት እጅግ አዘኑ ። ቢሆንም የንጉሥ ቃል ረዘመ ብለው አያሳጥሩት ፣ አጠረ ብለው አያስረዝሙት የሚባል ነገር አለና መድፉንም ፣ ስናድሩንም በሙሉ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አስረከቡ ።"

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወዳገራቸው ወደ ጐጃም ሲመለሱ የተማረከባቸውን መሣሪያ በምን አኳኋን እጅ ለማድረግ እንደቻሉ ሲያስረዱም ፣ ብላቴን ጌታ ኅሩይ እንደዚህ ብለዋል ። "...የሠርጉ ወራት ካለፈ በኋላ ንጉሥ ምኒልክ ከወረይሉ ተነሥተው ባንድ ቀን ግሥጋሤ ቦሩ ሜዳ ገብተው ካፄ ዮሐንስ ተገናኙ ። የትግራይ መኳንንትም የንጉሥ ምኒልክን አኳኋንና የሠራዊታቸውን ብዛት በማየት ሥጋት ስለ አደረባቸው ክፉ ምክር ይመክሩባቸው ጀመር ።"

ይኸን "ክፉ ምክር" የተባለውን ብላቴን ጌታ በትክክል አልገለጹትም ። ምናልባት ፣ "ምኒልክ በዚህ ዐይነት ከበረቱ ለእርስዎም በሕይወትዎ አይገዙልዎትም ፤ ወደፊት ልጅዎንም አያስገዙምና አሁን ቦሩ ሜዳ እንዳሉ እጃቸውን ይዘን እንሰርና በርሳቸው ፋንታ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴን የልጅ ልጅ ደጃች መሸሻ ሰይፉን አንግሠን ወደ ሸዋ እንላክ" ብለዋቸው ይሆናል ። ዐፄ ዮሐንስ ግን ፣ በተፈጥሮአቸው ከተንኮል ይልቅ የሐቀኝነት ዝንባሌ ስለሚታይባቸው ፣ "ትናንትና ልጃቻችንን አጋብተን እንዴት እንደዚህ ያለውን ክህደት እንሠራለን?" ብለው እምቢ ብለው ይሆናል ። ደግሞም ምኒልክ በሸዋ በሕዝባቸው ዘንድ ያሠፈኑትን መወደድና ዝና በምንም ዐይነት መሸሻ ሰይፉ ሊያሟሉት ስለማይችሉ ፣ መሸሻን ለሸዋ አንግሠው ቢልኩ ብጥብጥ እንደሚፈጠር አልሳቱትም ነበር ።

ከዚህ ይልቅ ምኒልክን እንዳሉ ትተው ፣ በዘዴ ተክለ ሃይማኖትን እንደገና በጦር ማጠናከሩንና ምኒልክን ማዳከሙን የሚሻል አድርገው የገመቱት ይመስላል ። ስለዚህም ነበር በጋብቻው ሰበብ አድርገው

የወሎን ግዛት ከምኒልክ ወስደው ፣ ለልጃቸው ለራስ አርአያ የሰጡዋቸው ። በዚሁ አያያዝ ይሆናል ከእምባቦ ጦርነት የተማረከውንም የጦር መሣሪያ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንዲመለስ ያደረጉት ።

ከዚህ ሁኔታ ጋር የተያያዘ መሆኑና የተመለሰበትን ዘዴ ለማመልከት ብላቴን ጌታ ኅሩይ እንደዚህ ሲሉ አብራርተውታል ።

> . . . ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወዳፄ ዮሐንስ ገብተው ፣ "እባክዎ ጃንሆይ ወደ አገሬ እንድገባ ይፍቀዱልኝ" ብለው ቢለምኗቸው ፣ "ወደ አገሬ ልግባ የምትለኝ መቼ ማርሁህና ነው ። አሁንም ስለ ጥፋትህ ሁሉ ምሕረት እንዳደርግልህ ንጉሥ ምኒልክን አማላጅ ላክብኝና ከዚያ በኋላ አሰናብትሃለሁ" አሏቸው ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ፣ ወደ ንጉሥ ምኒልክ ሔደው ፣ "ወደ አገሬ እንድገባ ከጃንሆይ ጋር ከልብ ያስታርቁኝ" ብለው ወደቁባቸው ። ንጉሥ ምኒልክም ባፄ ዮሐንስ ልብ የታሰበውን ሳያውቁ ፣ "እባክዎ ጃንሆይ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ከልብዎ ይታረቁትና ወደ አገሩ ይግባ" ብለው ቢለምኗቸው ፣ "እኔ ባነግሠው እርሱ በጥጋቡ ለቆታልና መንግሥት አይገባውም ነበር ። ነገር ግን ፣ ንጉሥን አማላጅ ከላከ ምን ይደረጋል? ትናንትናም ንጉሥ አድርገን ዛሬ ብንሽረው ለእኛም አያምርልን ምና ምሬዋለሁ ። ዳሩ ግን ፣ ንጉሥ ሆኖ ያለ መሣሪያ በጀሌ ወታደር ታጅቦ ወደ አገሩ ቢገባ ውርደቱ ለእኛው ነውና የተማረከበት መድፉም ነፍጡም እንዲመለስለት ይሁን" ስለ አሏቸው ፣ ንጉሥ ምኒልክ በድንጋጤ አዘኑ ። የሸዋ መኳንንትም ይኸን ወሬ በሰሙ ጊዜ ፣ "ጥንቱንም የፈራነው ይኸንኑ ነበር ። መቼስ ምን እናደርጋለን? ይልቅስ የባሰ ነገር ሳያገኘን ተሰናብተን ብንመለስ ይሻለናል" በማለት ምክራቸውን ጨረሱ ። [1]

ዐፄ ዮሐንስ ፣ ደጃች መሸሻ ሰይፉን ቀደም ብለው ምኒልክ ካስሩአቸው ቦታ አስፈትተው ፣ አጠገባቸው በማስቀመጥ ባለሟል አድርገዋቸው ነበር ። ገባ ወጣ ማለታቸውን ሰው ሁሉ እያየ ፣ "በመኳንንቶቻቸው ምክር ምኒልክን አስረው መሸሻን አንግሠው ወደ ሸዋ ሊልኩ ነው ። የምኒልክም ባለቤት ኃይለኛዋ ወይዘሮ ባፈና ውስጥ ለውስጥ ልባቸውን ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር አድርገው የደጃች መሸሻን

---

1 ብ.ጌ.ኅሩይ ፣ የኢት ታሪክ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐድዋ ጦርነት ፣ ገጽ 113 ።



አነጋገሥ ይደግፋሉ" እየተባለ ይወራ ነበርና አሁን መኳንንቱ በምርኮ የተገኘውን የመሣሪያውን መመለስ ሲሰሙ ፣ "ይልቅስ የባሰ ነገር ሳያገኘን ወደ አገራችን ወደ ሸዋ እንመለስ" ያሉት ስለዚህ ነበር ። 'የባሰ ነገር' ማለትም ሳያስሩዎ ወይም ሳንታሰር ማለት ይመስላል ።

ምኒልክም የባሰ ነገር እንዳይመጣባቸው በመጠንቀቅ ፣ የወሎም ግዛት ለራስ አርአያ ሲሰጥና የተማረከውም የጦር መሣሪያ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ይመለስ ሲሏቸው በልባቸው እየተናደዱ ፣ ባፉቸው "ይሁን" እያሉ ንዴታቸውን እየደበቁ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በሰላም መለያየትን ብቻ እንደ ፈለጉ ያሳያል ። ይሁን እንጂ ፣ ውስጡን እየተበሳሰሉ ሁለቱም ላይ ላዩን ተቻችለው በጨዋነት ለውጭው ሕዝብ ቢጋብቻ ተሳስረው እንደ ተፋቀሩ ይመስላሉ ። ስለዚህ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ወደ ዝርዝሩ ውዝግብ ሳይገቡ የሁለቱንም በስምምነት መለያየት ሲገልጹ ፣ ". . .በፍቅር አብረው ሰንብተው በየካቲት 2 ቀን ሁለቱ ነገሥታት ተሰነባብተው . . . ዐፄ ምኒልክ ወደ ሸዋ ተጓዙ" ብለዋል ።[1]

የሆነ ሆኖ ፣ ምኒልክ ከሐምሌ ወር 1875 ዓ ም ጀምሮ እስከ የካቲት ወር 1876 ድረስ ብዙ ጊዜ ወረይሉ እራሳቸው ባሠሩት ቤተ መንግሥት ሲቀመጡ አንዳንድ ጊዜም ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ሠፈሩበት ወደ ቦሩ ሜዳ እየተመላለሱ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ስለ ሠርጉም ስለ ሌላውም ጉዳይ እየተነጋገሩ ፣ ከመንፈቅ በላይ በወሎ ቆይተው በመጨረሻ ከንጉሠ ነገሥቱ ተሰናብተው በየካቲት 2 ቀን 1876 ዓ ም ከቦሩ ሜዳ ተነሥተው ፣ በጨፋ መንገድ አድርገው ፣ ልቼ ደርሰው ከዚያ በደስታና በዕልልታ ደብረ ብርሃን ከተማ ገቡ ።

በዚህ ዘመን ፣ ዐፄ ዮሐንስ ከእስክንድርያ ፓትርያርክ ተላልከው በማስፈቀድ ለኢትዮጵያ አራት ጳጳሳት አስመጥተው ነበር ። ይኸም በኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ለመዠመሪያ ጊዜ መሆኑ ነው ። ከአራተኛው መቶ ዓ ም ዠምሮ እስከዚህ ዘመን ድረስ ለአንድ ሺ አራት መቶ ዓመት ያህል ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከእስክንድርያ የሚላከው ጳጳስ አንድ ብቻ ነበር ። አንድ ብቻ ከመሆኑም የተነሣ ክህነት ፣ ዲቁናና ቅስና ከጳጳሱ ለመቀበል ጳጳሱ ወደሚቀመጡበት ከተማ በመጓዝ የነበረው ድካም ከፍ ያለ ነበር ።

አሁን ግን ፣ እላይ እንዳልነው ዐፄ ዮሐንስ፣ "ኢትዮጵያን ለሚያህል የክርስቲያን አገር አንድ ጳጳስ አይበቃም" ብለው ከእስክንድርያው

---

1 ጸ.ት. ገ/ሥላሴ ፣ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 113 ።

ፓትርያርክ ጋር ተጻጽፈው አራት ጳጳሳት አቡነ ጴጥሮስ ፣ አቡነ ሉቃስ ፣ አቡነ ማቴዎስ ፣ አቡነ ማርቆስ የሚባሉትን አስመጥተው አቡነ ጴጥሮስን ለትግረና ለትግራይ ይኸውም ማለት ለራሳቸው ፤ ሁለተኛውን አቡነ ማቴዎስን ለሸዋ ለንጉሥ ምኒልክ ፣ ሦስተኛውን አቡነ ሉቃስን ለጐጃም ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ አራተኛውን አቡነ ማርቆስን ከወሎ በኋላ የቤገምድርና የስሜንን ግዛት ለሰጡቸው ለልጃቸው ለራስ አርአያ ደልድለው ሰጡ ። ማርቆስ ግን ምንም ጊዜ ሳይቆዩ ሞቱ ።

ምኒልክ ከንጉሠ ነገሥቱ ከተሰነባበቱ ወዲህ ፣ አቡነ ማቴዎስን ይዘው ከወሎ ወደ ሸዋ ተጉዘው ልቼ ገብተው ጥቂት ካረፉ በኋላ ደብረ ብርሃን ከተማ ገቡ ። የአገባባቸውን ሁኔታ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ከዚህ እንደሚከተለው አሥፍረውታል ። "በየካቲት 23 ቀን ንጉሡ በሥርዓተ መንግሥት ዘውድ ደፍተው ፣ አቡነ ማቴዎስም ሙሉ የጵጵስና ልብስ ለብሰው ፣ ሠራዊቱም ተሰልፎ በታላቅ ሥርዓት አምረው ደብረ ብርሃን እከተማዎ (እከተማቸው) ገቡ ። በሸዋም ያሉ ካህናት አጊጠው በታላቅ ክብር ተቀበሉዎ ። ያን ጊዜ የተደረገ የቀለም ድርሰት ፣ የሠራዊት ደስታ እጅግ ብዙ ሆኗልና ካህናቱም እንዲህ አሉ "ንሕነስ ነአምን በአብ ማርቆስ ዘላዕለ ኵሉ ወበወልዱ ተክለ ሃይማኖት ዘደብረ ሊባኖስ የምስ ዓባይ ትፍሥሕተነ ሶበ መጽአ ማቴዎስ ወነበረ በየማነ ንጉሥ ዐፄ ምኒልክ ። በዚህም ጊዜ 101 ጊዜ መድፍ ነፍጥም (ጠበንጃም) ሙሉ ግባት ተተኰሰ ። ንጉሡም ሙሉ ግብር አግብተው አዳራሽ ተገኝተው ዋሉ ።"[1]

የሆነ ሆኖ ፣ ከዚህ በፊት ተደርጎ የማያውቀውን በዘመናቸው አራት ጳጳሳት ማስመጣታቸው ፣ ካስመጡ በኋላ በተለይ እንደ ባላንጣ የሚመለከቷቸው ምኒልክ "ጳጳስ ካገኘ በጳጳስ ተቀብቶ ንጉሠ ነገሥት ነኝ ይልና ከኔ ያፈነግጣል" የሚለውን ሥጋት አሸንፈው ፣ ጳጳስ ሰጥተው ንጉሥ ምኒልክን በሰላም ወደሸዋ ማሰናበታቸው ፣ ያፄ ዮሐንስን ልበ ሰፊነትና ቅንነት በግልጽ ያሳያል ። ምኒልክም ፣ "ድርጅቻለሁ ፣ ሠራዊቴ በዝቷል ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ የበላይነት ቀንበር ልላቀቅ" ብለው በትዕቢትና በኩራት ተፈንቅለው በመሸፈት ለብዙ ሕዝብ እልቂት ሰበብ አለመፍጠራቸው ታጋሽነታቸውን ያመለክታል ።

በዚሁ አንጻር ፣ የራሳቸውን ንጉሠ ነገሥታዊ ሥልጣን ለማጠናከርና የምኒልክንም የግዛት ኃይል ለማዳከም ዐፄ ዮሐንስ መሞከራቸው አልቀረም ። ምኒልክ ከቴዎድሮስ ጊዜ ዠምረው ብዙ ጊዜ ወደ ወሎ እየተመላለሱ በወረይሉ በመቀመጥ "እሺ" ብሎ የተገዛላቸውን የወሎ ባላባት ሲሾሙ ሲሽልሙ ፣ ያፈነገጠውን ሲሽሩ ሲያግዙ ወሎን በማናቸውም ረገድ ልክ እንደ ራሳቸው ግዛት ቆጥረውት የነበረው አሁን ከርሳቸው ፣ ባለሟላቸው ከሆኑት ከወይዘሮ መስተዋትም እጅ ወጥቶ ወደራስ አርአያ እጅ ሲዛወር መጠነኛ ቅሬታ እንደ ገባቸው አይጠረጠርም ። ቢሆንም "ተጋብተናል ፣ ግዴለም የተሰጠውም ለልጅ ባል ነው" በሚል ስሜት ችለውት ሳለ ፣ በሚቀጥለው ጊዜ ራስ አርአያ የቤገምድርና የስሜን ገዥ ተብለው ወሎን ሲለቁ በርሳቸው እግር በወሎ የወይዘሮ መስተዋትና የልጃቸው የአባ ዋጠው ባላንጣ ለሆኑት ለራስ ሚካኤል (መሐመድ ዐሊ) በመሰጠቱ የበለጠ ቅር አሰኝቷቸዋል ። ስለዚህም ምኒልክ ከውጭ አገር ሰዎች እየተጻጻፉ መሣሪያ በመሰብሰብና ዐልፎ ዐልፎ ፣ በዘዴ በማፈንገጥ ንጉሠ ነገሥቱን አዳከመዋል ። ይኸንንም ንጉሠ ነገሥቱና ንጉሡ በፉስ ዳርጌ አማካይነት ሲወቃቀሱ ወደፊት እናነባለን ።

ይሁን እንጂ ፣ ምኒልክ በማኸል ኢትዮጵያ የወሎን ግዛት ቢያጡም ፣ በሚቀጥለው ጊዜ በደቡብ በኩል አሩሲን ፣ ባሌን ፣ ቀጥሎም ሐረርጌን በማግኘታቸው ቅርታቸው ለጊዜው እየጠፋ ሔዷል ። ከዚህም በቀር ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር ያጣላቸው የጉድሩ ፣ የጨሊያ ፣ የሊሙ ፣ የከፋ ፣ የወለጋ ፣ የኢሉባቦር አውራጃዎች ሁሉ እያደር በርሳቸው ቁጥጥር ውስጥ ፣ ስለ ተጠቃለሉ ፣ የየአውራጃው ባላባት ሁሉ በራስ ጐበና መሪነት እየመጣ የሚገባውን ግብር እየሰጠ ስለ ታመነላቸው ፣ በዚሁ የበለጠ ሳይጽናኑ አልቀሩም ።

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ገጽ 113—114 ።

# ምዕራፍ ሐያ አንድ

### የግብጽ መንግሥት አወዳደቅ ፣ ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀራረብ ያደረገው ሙከራ—የጀኔራል ጐርዶን መሾም— የመህዲ አነሣሥ — የጐርዶን አሟሟት

ዐፄ ዮሐንስ ፣ በግብጽ ጦር ላይ ሁለት ጊዜ የማሸነፍ ዕድል ስለ ገጠማቸውና የዙፋን ባላንጣቸውን ምኒልክን ያለምንም ጦርነት ስለ አስገበሩ ፣ በፊታቸው ሁሉም ነገር እየቀናቸው ፤ ባገራቸው የማንም ኃያል መንግሥት የበላይነት ሳይኖርባቸው በኢትዮጵያ ሥልጣናቸው እየተጠናከረ ሔደ ። በርሳቸው አንጻር ዋናው የውጭ መንግሥት ባላጋራቸው ከዲቭ ኢስማኤል በእንግሊዝ ቁጥጥር ውስጥ ገብቶ በውስጥ አስተዳደርና በውጭ አገር አገዛዝም ፤ በኢኮኖሚም አቅዋሙ እየወደቀ ሔደ ። መውደቅም የጀመረው ሁለት ጊዜ (1867 እና 1868 ዓ.ም.) ጉንዳጉንዲና ጉራዕ ላይ በኢትዮጵያ ጦር ከተመታ በኋላ መሆኑን ራሳቸው ግብጾቹ ያምናሉ ።[1]

በኢትዮጵያ ድል ከመመታቱም በላይ ፣ ሊጥለው የቻለው ያለ ብዙ ጥናት ፣ ያለ በቂ ሀብት አንደኛ በጦርነት ግዛት ማስፋፋቱ ነበር ። በዚህም ኢትዮጵያ ብቻ እያሸነፈች ስትመልሰው ፣ የቀረው በአካባቢ ያለው አገር ሁሉ ለጊዜው በግብጽ ሥር ወድቆለት ነበር ። የግብጽ ጦር የሱዳንን አገር በሙሉ በቁጥጥር ውስጥ ከአደረገ ወዲህ ወደ ደቡብ ዘልቆ ኤኳቶርን ዐልፎ እስከ ኒያንዛ ባሕር ደረሰ ። በምሥራቅ በኩል የዘይላን አካባቢ በጁ ካደረገ ወዲህ በ1867 ዓ.ም. በራውፍ ፓሻ መሪነት ሐረርን ያዘ ። እነዚህንም የተያዙትን አገሮች ለመቆጣጠር ከ30.000 እስከ 45.000 የሚደርስ በደንብ የታጠቀ ጦር በያለበት ማስቀመጥ አስፈለገው ። በመጨረሻ ግን ለነዚህ ሁሉ የሚከፈል ገንዘብ ተቸገረ ።

ከዚህ በተጨማሪ ፣ የግብጽ መንግሥት በሱዳን ውስጥ የነበረውን የበላይነት ሥልጣን የሚቀናቀን ኃይለኛ የማህዲስቶች እንቅስቃሴ በዚያው ወቅት ተቀስቅሶ ነበር ። በዚያም ሳቢያ በየጊዜው የተፋፋሙ

1 Catawi Pacha, Coup d'Oeil sur la Chronologie de la Nation Egyp. ,pp.378-379.

ውጊያዎች በየሥፍራው እየተደረጉ በግብጽ ከዲቭና በእርሱም እየተ ሾሙ በሱዳን ውስጥ ከፍተኛ የአስተዳደር ሥልጣን በነበራቸው አማ ካሪዎቹ ዘንድ ሥጋትን አስከትሏል ።

በዚህ ምክንያት የግብጹ መሪ ከእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ጋር በመስማማት ፣ "ለማናቸውም ቢያላችሁበት እየተከላከላችሁ ተቀመጡ" የሚል ትእዛዝ በካርቱምና በአምዱርማን ለነበሩት አገረ ገዥዎች አስተላልፎ ፣

1ኛ/ ይኸን የማህዲን እንቅሥ ደምስሶ በሱዳን ሰላምና ጸጥታ ሊመሠርት የሚችል ጠንካራ ሰው እንዲገኝ ለማድረግ ፣

2ኛ/ የሱዳን ሁኔታ እየባሰበት ሔዶ የግብጽ መንግሥት የጦር ሠራዊቱንም ፣ የሲቪል አስተዳዳሪዎቹንም ከሱዳን በሰላም አስወጥቶ በኢትዮጵያ ግዛት አሳልፎ ወደ ምጥዋ ከማዛወር በፊት የኢትዮጵያና የግብጽ መንግሥታት በከዲቭ እስማ ኤል ዘመን ሁለት ጊዜ ተዋግተው በጠብ ላይ ስለነበሩ ፣ ባሁኑ የችግር ጊዜ ሁለቱንም መንግሥታት ማስታረቅ የተሻለ መሆኑን አመነበት ።

በርግጥም ዐፄ ዮሐንስ ምንም ሁለት ጊዜ የግብጽን ጦር በጉንዳጉንዲና በጉራዕ አሸንፈው ቢመልሱም ፣ የግብጽን አገዛዝ ከምጥዋና ከአካባቢው ከሐባብ ፣ ከቦጎስ ፣ ከከረን ማስወጣት አልሆነላቸውም ነበር ። ከጦርነቱም በኋላ ከግብጾች በኩል መሐመድ ሪፋት ቤይ እና ራቲብ ፓሻ ፣ ከዐፄ ዮሐንስ ወገን ሊቀ መኳስ ምርጫ ወርቄና ዐሊ አልሩቢ ተመድበው የዕርቅ ስምምነት ለማድረግ ብዙ ጊዜ ተሞከሮ የግብጽ መንግሥት ቦጎስንና የቦጎስን አካባቢ አለቅም ከማለቱም በላይ ፣ በዐፄ ዮሐንስ ላይ የተነሡትን እነደጃች ወልደ ሚካኤልን እያከበረ ፣ መሣሪያ እያስታጠቀ ፣ በሐማሴን የተሾሙትን እነ ራስ ባሪያውን ፣ እነ ራስ አሉላን ማስጠቃቱን እንደ ቀጠለ ነበር ። የዚህንም ሁኔታ ለእንግሊዝ መንግሥት ባለሥልጣኖች ደጋግመው ቢያሰሙም ፣ ባለሥልጣኖቹ ከግብጽ በኩል የሚያገኙትን ጥቅም በመገምገም የርሳቸውን ስሞታና ጥያቄ በቁም ነገር አልተመለከቱትም ነበር ።

አሁን ግን ፣ በኢትዮጵያ በኩል ሁኔታው በዚህ ላይ እንዳለ ፣ በሱዳን የማህዲ መነሣት የግብጽንና የእንግሊዝን መንግሥታት አሥጊ ሁኔታ ላይ ስለ ጣላቸው ነገሩ በካይሮም ፣ በሎንዶንም ውይይትና ንግግር ሲደረግበት ሰነበተ ። በመካከሉም ዐፄ ዮሐንስ በኢትዮጵያና በግብጽ መካከል በሚደረገው የፖለቲካና የመሬት ጠብ የእንግሊዝ መንግሥት ባለሥልጣኖች ለግብጽ መንግሥት ማድላታቸው ስለ ተሰማቸው ፣



በመቅደላ ጦርነት ጊዜ ተዋውቀው ለተዛመዱት ለጄኔራል ናፒየር ጉዳዩን እንሥተው በተለይ ማሳሰቢያ ጽፈውለት ነበር ። የማሳሰቢያው መሠረተ ሐሳብ በመቅደላ ጦርነት ጄኔራሉ ተመልሶ ወደ አገሩ ሲሔድ በተወላቸው የጦር መሣሪያ ጠላቶቻቸውን አሸንፈው ለዙፋን መብቃታቸውን ፣ ከዚያ ወዲህ ደብዳቤ ጽፈውለት እንዲትም መስመር መልስ ስላልጻፈላቸው ማዘናቸውን ገልጸዋል ። ከዚሁ አያይዘው ከቱርኮችና ከግብጾች በኩል ብዙ በደል እንደ ደረሰባቸው ለርሱና ለእንግሊዝ መንግሥት ሁለት ደብዳቤዎችን ጽፈው በጄኔራል ኪርከሃም እጅ ቢልኩ ቱርኮቹ* እርሱንም አስረውና መርዘው በመግደል ደብዳቤዎቹንም ቀዳደው ከባሕር እንደ ጣሏቸው ከእንግሊዝ በኩል ምንም ዐይነት ሽቀጥና ጠበንጃ እንዳይመጣላቸው በማድረጋቸው ስለ ተጐዱ ፣ ጄኔራል ናፒዬር በነገሩ ገብቶ በወዳጅነቱ እንዲረዳቸው ያሳስባል ። በዚሁም ጊዜ ለእንግሊዝ ንግሥትም የጻፉት ይህንኑ የመሰለ ቃል ያዘለ ነበር ።[1]

ሎርድ ናፒዬር ይኸ ደብዳቤ ሲደርሰው ፓሪስ ነበር ። ከፓሪስ በ25 መስከረም 1872 ዓ ም የደረሰውን ደብዳቤ ከነትርጉሙ አድርጎ የራሱንም ደብዳቤ ጨምሮ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሎርድ ሮበርት ሳልስቤሪ ጻፈለት ። በራሱ ስም በጻፈው ደብዳቤ ላይ ፣ "ዐፄ ዮሐንስ ምነው እስካሁን ሳትጽፍልኝ ቀረህ" ብለው በመውቀሳቸው ምክንያት፣እውነትም ከመቅደላው ዘመቻ 1860 ዓ.ም. በኋላ አንድ ጊዜ ብቻ ለራሳቸውና ለባላንጣቸው ለዋግሹም ጐበዜ (ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ) ከጎረቤቶቻቸው ጋር ሰላም እንዲያደርጉ ከጻፈላቸው ወዲህ ምንም ሳይጽፍ ብዙ ዘመን ማለፉን አረጋገጠ ። መልሱን ያልጻፈበትም ምክንያት እርሱም አማርኛ ባለማወቁ በእንግሊዝኛም ቢጽፍ ምን ያደርጉታል በማለት መሆኑን ገልጾ ፣ "ከዐፄ ዮሐንስ ጋር በመቅደላ ጊዜ ከአደረግነው ወዳጅነት በቀር በክርስቲያንነታችን እንደምንረዳቸው ስለሚያምኑ ፣ ልንረዳቸውና ወደ ሥልጣኔ ልናመጣቸው ይገባል" የሚል ቃል ጨምሮ፣ መደምደሚያውን ንጉሡ ዮሐንስ ለአቀረቡት አቤቱታ መልካም አስተያየት እንደሚደረግለት ተስፋ አደርጋለሁ" የሚል ቃል ጨምሯል ።[2]

---

* ዐፄ ዮሐንስ ቱርኮች የሚሉት አብዛኛውን ጊዜ ግብጾቹን ጭምር ነው ። በተለይ የቱርክ ሡልጣን ምጥዋን ለግብጽ ከለቀቀ ወዲህ በዚህ ወደብ የሚገኙት በብዛት ግብጾች ነበሩ ።

1 Correspondence respecting the relations between Egypt and Abyssinia (1878-79) -Confidenetial, pp. 26,No. 28-Public Record Office, Londomn- FC 407-11-11897.

2 Public Record Office Londoo-F.C. p.407.

የግብጽንም ችግር ፣ የኢትዮጵያንም አቤቱታና እሮሮ ደህና አድርገው የተገነዘቡት ፣ በካይሮ ዋናው ቆንሲል ባሪንግ (ክሮመር)ና አውግኀተስ ዋይልድ የሚባለው በጅዳና በምጥዋ የሚቀመጠው የእንግሊዝ ቆንሲል ፣ ጉዳዩን በዝርዝር ከአጠኑ በኋላ ፣ በዚሁ ዓመት በመስከረም ወር ከሳሊስበሪ በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ለተሾመው ለግላድስተንና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለግራንቪል ባቀረቡት ሪፖርት ውስጥ “በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያንና የግብጽን መንግሥታት በዕርቅ ማስማማቱ ለእንግሊዝ መንግሥታት ጠቃሚ ነው” የሚል ስለ ጻፉና መንግሥቱም የነርሱን አስተያየት ስላመነበት ፣ የዚህን ጉዳይ ከሁለቱም መንግሥታት መሪዎች ጋር ተነጋግሮ እንዲጨርስ አላይ ስሙ የተጠቀሰው ጄኔራል ጆርጅ ቻርልስ ጐርዶን ተመረጠ ። ይህም ጄኔራል ትውልዱ እንግሊዛዊ ሲሆን የሩቅ ምሥራቅንና የመካከለኛውን ምሥራቅ ጉዳይ የሚያውቅ ፣ አስቀድሞም በካርቱም ከተማ በግብጽ መንግሥት አገረ ገዥ ሆኖ የተሾመ ፣ የአፍሪካን ባህልና የሕዝቡን ጠባይ የሚያውቅ ፣ በአስተዳደር ብልህነቱ በወታደርነትም የቆራጥነት ዝና ያተረፈ ነበር ። ስለዚህ ይኸው ጄኔራል ጐርደን በዐፄ ዮሐንስና በግብጽ መንግሥት መካከል የተነሣውን የመሬት ጠብ በስምምነት እንዲጨርስ ተደረገ ።

ጄኔራል ጐርዶን ፣ በእንግሊዝ መንግሥት ፈቃድ ከሎንዶን ወደ ካይሮ ሔዶ ፣ በፓሻነት ማዕረግ የሱዳን ጠቅላይ ገዥ ተብሎ ከተሾመ ወዲህ የግብጹ ከዲቭና እርሱ በሚግባቡበት በፈረንሣይ ቋንቋ እንደዚህ ብሎ ጻፈለት ። “የተወደዱት ፓሻ እንደሚያውቁት በአበሻና በግብጽ መካከል መለያየት (በጠብ) አለ ። በልምድዎ ፣ በታማኝነትዎ ከሁሉ የበለጠ እምነት አለኝ ። የመንግሥቱ ጉዳይ በእርስዎ በኩል ከመፈጸም በቀር ሌላ ምርጫ የለውም ። ስለዚህ በዚህ ደብዳቤ አማካይነት ወደ ንጉሡ ወደ ዮሐንስ ሔደው ሁኔታውን እንዲያስተካክሉ ወክየዎታለሁ ። የአሁኑ ሁኔታ (መጥፎ) የተፈጠረው በእኔ ምክንያት አለመሆኑን ፣ ከጐረቤቶቼ ጋር በሰላም ለመኖር የምወድ መሆኔና የኔ ስሜት በርስዎ ዘንድ የታወቀ ነው ። ስለዚህ በሁለቱ መንግሥታት (ግብጽና ኢትዮጵያ) መካከል መልካም ግንኙነት እንዲመሠረት ፣ የግብጽ መብቶች እንዲጠበቁ ፣ ለሐበሻ ምንም የምንሰጠው (ቦጎስና የምጥዋ አካባቢ) ሳይኖር የአሁኑ ወሰን እንዲከበር ፣ ለሁለቱ አገሮች ጥቅም እንዲሆንና ማናቸውም ግጭት እንዲወገድ የእርስዎ የአሁኑ መልእክት የሚያተኩረው በነዚህ ጉዳዮች ላይ ነው ።” 1

1 G. Douin , Histoire du Regne du Kedive Ismael, Tome III, 2c partie, pp.580-582.



ጐርዶን ፓሻ ከሎንዶን ባለሥልጣኖች ልዩ መመሪያ በደብዳቤ መልክና እነዚህን አሳቦች ከከዲቩ ተቀብሎ በምጥዋ በኩል መጥቶ ከዐፄ ዮሐንስ ጋር ደብረ ታቦር (ቤጌምድር) ላይ በ1871 ተገናኘ። ነገር ግን የዐፄ ዮሐንስ ጥያቄና በከዲቭ ስም ለማስፈጸም ጐርዶን የመጣበት ጉዳይ በፍጹም የተራራቀ ሆነ ። የዐፄ ዮሐንስ ጥያቄ “ከሱዳን ወሰን አካባቢ ያሉት ጋላባት ፣ መተማ ፣ ከረን ፣ በምጥዋ አካባቢ የሚገኙት ሐባብና ቦጐስ ፣ ሰሐጢና ዶጋሊ እነዚህን የመሳሰሉት ሁሉ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ግዛቶች ናቸውና ለኔ መመለስ አለባቸው ። በነዚህ ወረዳዎች የሚገኙትም ባላባቶች ጥንት ለኢትዮጵያ ነገሥታት ይገብሩ እንደ ነበረው ፣ አሁንም ለኔ መገበር አለባቸው” ሲሉ ፣ እርሱ ግን ከከዲቩ እንደ ተቀበለው መመሪያ ፣ “እነዚህ ሁሉ ንጉሡ የሚጠይቋቸው ወረዳዎች የግብጽ ግዛቶች ስለሆኑ ፣ ለኢትዮጵያ ሳይመለሱ እንዳሉ ለግብጽ ረግተው ዕርቁንና የሰላሙን መንገድ ብቻ መቀበል አለብዎት” የሚል ነበር ። በዚህ ምክንያት ባለፉት ዓመታት የቦጐስን ከንቲባ በእርሳቸው ላይ እያስነሣ ፣ ለነደጃች ወልደሚካኤል የራስነት ማዕረግ እየሰጠና ፣ እያስታጠቀ ራስ አሉላን ማስወጋቱን ጠቅሰው “ግዛቴን ሳላገኝ እንደዚህ ያለውን ባዶ የሰላም ዕርቅ እንዴት እቀበላለሁ” ቢሉ ፣ ጐርዶን ፓሻ በአንድ ወገን በእንግሊዝ ጄኔራልነቱ እና በነጭነቱ ፣ በሌላው ወገን በሱዳን ጠቅላይ አገረ ገዥነቱ እየተኩራራ በማስፈራራት ጭምር እርቁን ጠይቆ ሳይሳካለት ስለቀረ ፣ ሁለቱም በጠብ ተለያዩ ።

በዚህ መካከል ፣ በሱዳን የማህዲስቶች አነሣሥ በእንግሊዝና በግብጽ ወታደሮች ላይ የሚያደርሱት ጥቃት ፣ በየወረዳው የሚገኙትን የእንግሊዝ ፣ የጀርመን ፣ የፈረንሳይና የጣሊያን ተወላጆች ግማሾቹ በንግድ ፣ የቀሩትም በወንጌል ሰባኪነት የተቀመጡትን ወደ እስላምነት ግቡ እያሉ በማጉላላት ታላቅ ችግር ተፈጥሮ ነበር ። አንዳንዶቹ አውሮፓውያን ሕይወታቸውን ለማትረፍ እያሉ ከክርስትና ሃይማኖት ወደ እስላምነት የተለወጡ ይገኙባቸዋል ። ከእነዚህም መካከል አንዱ የጐርዶፉን ገዥ የነበረው ሩዶልፍ ሳላቲን ይባል የነበረው የጐርዶን ወዳጅ በማህዲስቶቹ ተገዶ የሰለመው ነበር ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት ፣ ጐርዶን ፓሻ ከዐፄ ዮሐንስ ጋር ያለውን ንግግር አቋም በቶሎ ወደ ካርቱም መሔድ ግዴታ ሆነበት ። ካርቱም ሲሔድ ከሎንዶን ባለሥልጣኖች ጋር የተስማማው ፣ “ከሱዳን የግብጽን አገዛዝ ሽሮ ፣ በሱዳን ውስጥ ከግብጽ ነጻ የሆነ መንግሥት አቋቁሞና የዚህን ሥልጣን ባገር ላሉት ባላባቶች አስጨብጦ ፣ አዲሶቹ ባለሥልጣኖች ማህዲን እንዲቃወሙ ማድረግ ይቻላል” የሚል አሳብ አለበት ።

ዋናው መሠረታዊ ዓላማ ግን ፣ በማናቸውም ረገድ የእንግሊዝ የበላይ ገዥነት በሱዳን ውስጥ እንዲመሠረት ነው ።

ስለዚህ ፣ ጐርዶን ፓሻ ደብረ ታቦርን ለቆ ላዩን በበርበር አድርጎ በየካቲት 18 ቀን 1878 ካርቱም ገባ ። ከበርበር ፣ ከዋናዎቹ ከተማዎች ከካርቱምና ከአምዱርማን ወይም ከኢትዮጵያ አዋሳኞች ከመተማና ከከሰላ በቀር ሁሉም ከተማዎች በማህዲስቶች ተይዘዋል ወይም ተከበዋል ። ከዚህ በፊት ስሙን የጠቀስነው ሩዶልፍ ሳላቲን የሚባለው የአውስትሪያ ተወላጅ ሠላጢን ፓሻ እየተባለ የጉርዶፋን አውራጃ ያስተዳድር የነበረው ፣ ብዙ ቀን ተከላከሎ ሳይሆንለት ስለቀረ በዕርቅ ገብቶ ሕይወቱን ለማዳን ሲል ፣ ሰልሞ ከተቀመጠ በኋላ በጥርጣሬ ታስሮ ወህኒ ቤት ገብቷል ። ሎፕቶን የእንግሊዝ ተወላጅ ባሕር ኤልጋዛል የሚባለውን አውራጃ ይገዛ የነበረው ፣ እንደ ጓደኛው እንደ ሠላጢን እጁን ለማህዲስቶች ሰጥቶ ሰልሞ ተቀምጧል ። ሺናይድለር የሚባለውን ኤሚን ቤይ ተብሎ የተሠየመው የጀርመን ተወላጅ ብቻ ግዛቱ ፣ ኤኳቶርያ ፣ ወደ ደቡብ ራቅ ስላለ የነገሩን አስፈሪነት በመገንዘብ ፣ ከነሱው ወደ ላይ ኒያዛ ሐይቅ አጠገብ ሸሽቶ ራሱን ለማዳን ችሏል ።

ስለዚህ ፣ ጐርዶን ፓሻ ካርቱም ሲገባ ወታደሩም ፣ ሲቪሉም በክብርና በአለኝታ ከተቀበለው በኋላ ፣ ካገር ተወላጆችና ከውጭ አገር ታላላቅ ሰዎች ጋር በመመካከር ባንድ ወገን የወታደር ዝግጅቱን እያጠነከረ ፣ በሌላው በኩል ከማህዲ ጋር ለመስማማት ሞከረ ። ለማህዲም ፣ "ጦርነቱን አቁመህ ወደኔ ብትገባ የጉርዶፋንን ሡልጣንነት እፈቅድልሃለሁ" ብሎ ላከበት ። ማህዲ ግን በዚህ ጊዜ በፊቱ ሁሉም ነገር ስለ ተሳካለት ፣ እንኳን ወደ ጉርዶፋ ሊገባ እንዲያውም "ይልቅስ አንተ እጅህን ለኔ ስጥና ሰልመህ ነፍስህን አድን" ብሎ መለሰለት ።

ከዚህ በኋላ ከመቶ ሺ በላይ ጦር እንደያዘ* ማህዲ አምዱርማንና ካርቱምን ከበበ ። ከካርቱምም በፊት በአቅራቢያው ያለው አምዱርማን ወድቆ ተበዘበዘ ። ካርቱም ግን ፣ ራሱ ጐርዶን በደንብ አጠናክሮ ስለ መሸገው ከበባው ብዙ ቀን ፈጀ ። ወሬውም በሎንዶን ስለ ተሰማ ለእርሱ እርዳታ የሚደርስ ዘማች ጦር ተዘጋጀ ። ከዚህ በፊት በካይሮና በእስክንድርያ የነኮሎኔል አራቢን እንቅሥቃሴ በጦር ኃይል የደመሰሰው ጄኔራል ወልስሌ የሚባለው በዘማቹ ጦር ላይ ተሾሞ በካይሮ ዐልፎ በጥቅምት ወር 1879 ዓ. ም. ዋዲ ኃልፋ ደረሰ ።

* ከባቢውን ጦር ኡቱሬ አልጊዬሪ እስከ 200.000 አድርሶታል ።



ወልስሌይ በጄኔራል ጐርዶን ጄግንነት በመተማመን ከነሠራዊቱ በዝግታ ሲጓዝ ፣ የካርቱምን ከበባ ከቀን ወደ ቀን እያዋከበ በማጣደፍ ጥር 26 ቀን 1878 ዓ.ም. የማህዲ ጦር ተጨፈጨፎ ጥሶ ወደ ከተማው ገብቶ ብዙ እልቂትና ብዝበዛ በሚደረግበት ጊዜ ያንዱ ክፍል የማህዲ ጦር ጐርዶን ፓሻ ወደአለበት ቤተ መንግሥት ደርሶ ጐበዙ ጄኔራል በኩራት እንደቆመ እጁን ተይዞ አንገቱ ተቆረጠና በደስታና በጭፈሮ ለማህዲ ቀረበለት ። የዚህንም ወሬ በጉዞ ላይ የነበረው ጄኔራል ወልስሌይ ሲሰማ ጦሩን እንደያዘ ወደ መጣበት ተመለሰ ። ከዚህ ጊዜ ዠምሮ የሱዳን ግዛትና ሥልጣን በማህዲ እጅ ተጠቀለለ ። ዳሩ ግን ፣ ከዚህ ድል በኋላ ማህዲ ብዙ ዘመን ሳይቀመጥ ጐርዶን በተገደለ በአምስተኛው ወር ስለሞተ በርሱ እግር ከአራቱ ከሊፋዎች አንዱ አብዱላሂ ተተካ ።

ጐንደር የተቃጠለው ፣ የጐጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ተዋግተው የተሸነፉት ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስ በመተማ ተዋግተው መጋቢት 1 ቀን 1873 ዓ.ም. የሞቱት በማህዲ ተከታይ በከሊፋ አብዱላሂ ኤል ታእሺ ጊዜ ነው ። ዝርዝር ታሪኩ ወደፊት ይነበባል ።



አህመድ መህዲ

(ድራሚ ኤ ሴክሬቲ ከሚለው መጽሐፍ)



ጎርዶን ፓሻ ሲገደል

(ከሶርድ ኤንድ ፋየር መጽሐፍ)



የጎርዶንን የተቆረጠ ራስ ለሠላጢን (ሩዶልፍ) ሲያ ሳዩት
(ሶርድ ኤንድ ፋየር ከተሰኘ መጽሐፍ)

# ምዕራፍ ሐያ ሁለት

የጐርዶን አሟሟት በለንደን ስለ መሰማቱ—ያፄ ዮሐንስ ተከታታይ
ስሞታ ለአውሮፓ ኃያላን—የእንግሊዝ መንግሥት
የተጠቃሚነት ችሎታ—የሰር ዊልያም ሔዊት መሾም

የጄኔራል ጐርዶን አሟሟት እንደ ተሰማ ፥ በፓኪንግሃም ቤተ መንግሥት ፥ በዌስት ሚኒስቴር (ፓርሊያሜንት ሐውዝ) ምክር ቤት ፥ በዳውኒንግ ስትሪት (የጠቅላይ ሚኒስቴር) ፥ በፎሬይን ኦፊስ የውጭ ጉዳይ ታላቅ ቁጭትንና ሐዘንን አስከትሏል ። በምክር ቤት እንደ ነበሩ የተናደዱት አባሎች ፥ "አሁኑኑ አዲስ ጦር ተልኮ የማህዲን ሱዳን በሾርባው ውስጥ እንዳለ መቀቀል ነው" እስከ ማለት ደርሰዋል ።

ነገር ግን ፥ የእንግሊዝ መንግሥት የበላይ መሪዎች ዋናው አሳባቸው ግብጽን በገዛ አገሩ በኢኮኖሚና ባስተዳደር አዳክመው ፥ በግዛቶቹ በሱዳንና በኢኳቶር "የባሪያን ንግድ እናጠፋለን" በሚል ሰበብ ገብተው ፥ የራሱን አስተዳደር አዳክመው ራሳቸው በርሱ እግር ለመተካት ስለሆነ ፥ አሁን ጐርዶን ፓሻ ላገሩ ጥቅም እንደ ተሠዋ ዐውቀውለት ፥ በሌላው ወገን ያለችኮላ በትዕግሥትና በእርጋታ ፥ በጥናት ፥ ሁኔታውን አመዛዝነው ወደፊት ባለው ጊዜ የሚከተለውን ለመፈጸም በቀዱ ።

1ኛ በሱዳንና በኢትዮጵያ ጠረፍ በስናር ፥ በጋላባት ፥ በከሰላ ገና እጃቸውን ለማህዲስቶች (ደርቡሾች) ሳይሰጡ በመከላከል ላይ ያሉትን የቱርክና የግብጽ ወታደሮች በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል አሳልፎ ወደ ምጥዋ ለማድረስ እንዲቻል በቅድሚያ በቦጐስ ፥ በሐቢብ ፥ በሐማሴንና በአካለ ጉዛይ ጉዳይ ላይ ከጉንደትና ከዋናው ከጉራዕ ጦርነት ወዲህ ምንም የታወቀ ስምምነት ያላደረጉትን የግብጽንና የኢትዮጵያን መንግሥታት ማስታረቅ ። ዐፄ ዮሐንስ ዕርቁን እንዲቀበሉ የዘወትር ጥያቄያቸው የነበረውንና በከዲቭ ኢስማኤል እምቢተኛነት ተንጠልጥሎ የቆየውን የቦጐስንና የምጥዋን ወደብ ጉዳይ ማሟላት ።

2ኛ መሠረታዊ ዓላማቸው የሆነውን የግብጽን አገዛዝ ከሱዳን አስለቅቀው በደንብ እነርሱ ከመተካታቸው በፊት ለዚህ ሰፊ ዓላማ የተሠዉትን ዤኔራሎች የጐርዶንንና የሂክሰን ፣ የስቲዋትን ደም ለመበቀል ጥናቱን በጐንደርና በካይሮ በሰፊው መቀጠል ።

ስለዚህ የእንግሊዝ መንግሥት ፣ በቪክቶርያ ዘመነ መንግሥት ፣ ከመቼውም ዘመን በበለጠ በጦርና በፖለቲካ ፣ ባስተዳደር የበሰሉ መሪዎች በብዛት የሞሉበት ፣ ግዛቱ በእስያና በሩቅ ምሥራቅ ፣ በደቡብ አሜሪካና በአፍሪካ የተስፋፋበት ፣ የኢኮኖሚው አቅዋም ደንበኛ መሠረት የያዘበት ጊዜ ስለነበረ ፣ የነዤኔራል ጐርዶንን መሞት ቀጥሎም ባምስተኛው ወር የራሱን የማህዲን ሞት እንደሰማ በችኮላና በደም ፍላት በቶሎ ዘማች ጦር ልኮ ደርቡሾቹን ለመበቀል ሳያስብ ፣ ሆኖም ግን ፣ የበቀሉን ጉዳይ ሳይረሳ ረዘም ላለ ጊዜ መድቦ በቅድሚያ እላይ እንዳልነው ፣ አንድ ከጀርጅ ቻርልስ ጐርዶን ለዘብ ያለና ምራቁን የዋጠ ሰው ኢትዮጵያንና ግብጽን ለማስታረቅ የሚችል መርጦ ለመላክ ምክር ሲደረግ ቆይቶ በሕንድ የባሕር ኃይል ምክትል አዛዥ የሆነው ሬር አድሚራል ሰር ዊልያም ሔዊት ተመረጠ ።

በበኩላቸው ዐፄ ዮሐንስ ፣ በፊት ኢስማኤል ፓሻ ባንድ ወገን ዕርቅ የፈለገ እየመሰለ ፣ በሌላ ወገን እነ ደጃች ወልደሚካኤልን እያስታጠቀ ሲያስወጋቸው ከቆየ ወዲህ ፣ አሁንም ደግሞ ልበ ደንዳናውና ግትሩ ጐርዶን ከተውፊቅ ፓሻ ተልኮ መጥቶ ለርሳቸው የመሬትና የወደብ ጥያቄ ምንም ዋጋ ሳይሰጥ የላከውንና የሾመውን የተውፊቅን ምኞት ብቻ ለማሟላት በመከጀሉ ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በጠብ ተለያይቶ ወደ ሱዳን ቢሔደበትና በተከበበበት ጊዜ ሁሉ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ እንደ ኢትዮጵያ ቁጥር ሚያዝያ 25 ቀን 1871 ዓ.ም. ፣ ኅዳር 10 ቀን 1872 ፣ ሚያዝያ 22 ቀን 1872 ዓ. ም. አከታትለው ለንግሥት ቪክቶርያ ስለ በደላቸው ደብዳቤ ጽፈዋል ። ወዳጇ ከሚሏቸው ከንግሥት ቪክቶርያም አልፈው ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለሎርድ ግራንቪልም ጽፈዋል ። እንደዚሁም በየካቲት 11 ቀን 1873 ዓ.ም. ፣ በሚያዝያ 2 ቀን 1875 ዓ.ም. ለጀርመን ንጉሠ ነገሥት ለዊልሄልም ቀዳማዊ ጽፈው ጉዳዩ ፍጻሜ እንዲያገኝ በተላመዱት በዶክተር ጀርሃርድ ሮልፍስ አማካይነት ለቻንስለሩ ለቢስማርክ ጭምር ጽፈዋል ። እንደዚሁም ለነምሳ (አውስትሪያ) ንጉሠ ነገሥት ፣ ለፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ፣ ለሩሲያ ንጉሠ ነገሥት ስሞታቸውን በደብዳቤ ከማሰማት ቦዝነው አያውቁም ።

ለሁሉም የጻፉት ቃሉ ተመሳሳይ ነበር ። ሁሉንም በዚህ ምዕራፍ ላይ ማስፈር አስፈላጊ ስላልሆነ ፣ በተለይ የጥያቄያቸው ዐይነት



በብዛት ሠፍሮበት ከሚገኘው ለንግሥት ቪክቶርያ ከጻፉት ውስጥ ዋና ዋናው አሳብ ከዚህ የሚከተለው ነው ።

አንደኛ ፣ ለንግሥቲቱ የሚጽፉትን ደብዳቤ ሁሉ የምጥዋን ወደብ የሚቆጣጠሩ ግብጾችና ቱርኮች መላክተኞቻቸውን እየያዙ በማሰር ደብዳቤውን እየቀደዱ ወደ ባሕር መጣላቸው ።

ሁለተኛ ፣ "ኢትዮጵያን በጠብ ጊዜ (በመቅደላ ዘመቻ) ያልራቋት አሁን በፍቅር (በሰላም) ጊዜ ምነው ራቋት ።" (ይኸውም ማለት በመቅደላ ዘመቻ ጊዜ ወዳጅነቴን ፈልገው ተፋቅረን ሳለ አሁንም ምነው ረሱኝ ለማለት ነው ።)

ሦስተኛ ፣ ጐርዶን ከከዲቭ ተውፊቅ ተልኮ እንታረቅ ብሎ መጥቶ አክብረው ከተቀበሉት በኋላ ፣ "ያልሆነ ያልሆነ ነገር እየተናገረ . . . ሰደበኝ ፣ አዋረደኝ ። ደካማ ነህ ጉልበት የለህም ፣ ጦር አምጥቼ እወጋሃለሁ አለኝ ።"

አራተኛ ፣ "እኔ ወደ አዘቦ ኦሮሞ ለዘመቻ በሔድኩበት ሰዓት የግብጹ መሪ ከዲቭ ኢስማኤል ጦር ልኮ ቢወጋኝ በእግዚአብሔር ኃይል አሸነፍኩት ። ምን አደርጋለሁ ብዬ ምርኮኛውን ሁሉ ብሰድ ሁለተኛ ልጁን ሐሰንን ከሠራዊት ጋር ሰደደ ። እግዚአብሔር ኃይል ሰጥቶኝ ደግሜ ባሸንፈው የዚህን ብድር ለመመለስ ብሎ አገሬን ያዘብኝ ።"

አምስተኛ ፣ "የኢትዮጵያ አቡን ከእስክንድርያ እንዳይመጣ ከለከለብኝ ።"

ስድስተኛ ፣ "መሣሪያ ነፍጥ (ጠመንጃ) ባሩድ (ጥይት) በገንዘቤ ገዝቼ እንዳላስመጣ የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ነጋዴ እንዳይገበያይ የምጥዋ በር ተዘጋብኝ ። ስለዚህ የሸቀጡንና የዋጋውን ተመን የሚቆጣጠር ለኔ እንደ ምስክር የሚሆነኝ የእንግሊዝ መንግሥት ምጥዋ ላይ አንድ ቆንሲል ያስቀምጥልኝ" ካሉ በኋላ ፣ የእንግሊዝን እሺታ ለማግኘት ሲሉ ፣ "ለሌላው (ለግብጽና ለቱርክ) አልሰጥም እንጂ ከእንግሊዝ ቤተ መንግሥት ጋር ተአረመኔ አገር ያለውን ሁሉ (ቦጎስ ሐባብ) ተካፍዬ ብበላው አልጠላም" ሲሉ ደብዳቤያቸውን ደምድመዋል ።*

* ምንአልባት ያረመኔ አገር የሚሉት እስላም ነክ የሆኑትን ወረዳዎች በሪ ፣ አሳውርታ ፣ ዙላ ፣ ሐልሃል ፣ ቦጎስ (ምገስ) ታንዴር ፣ ሐባብ ፣ ቁናማ ፣ መንሣዕ ፣ ገዳሪፍ ፣ ሽሆ ፣ ጥልጣል ፣ ደንከል ፣ አዘቦ እነዚህን የመሳሰሉትን መሆን አለበት ።

ለነዚህ ሁሉ መንግሥታት የሚጽፉበት ምክንያት ፣ ከግብጽ መሪዎች ጋር ገላግላችሁ የያዙትን አገር አስመልሱልኝ ለማለት ነው ። በደብዳቤያቸው ማሰሪያ ላይ ፣ “ነገሥታተ ምድር ካላስታረቃችሁኝ ነገሥተ ሰማይ ወርደው ያስታርቁኛልን” የሚል ይገኝበታል ።[1]

ዐፄ ዮሐንስ ፣ በሐቅ መንገድ በእንግሊዝ ወዳጅነትና በክርስቲያንነቱ በመተማመን ይህን የመሳሰለውን ቃል እያሠፈሩ ደብዳቤ አከታትለው ሲጽፉ ፣ የእንግሊዝ መንግሥት ጉዳዩን የሚመለከተው ከራሱ የግል ጥያቄ ጋር በማያያዝ ነበር ። የእንግሊዝ ንግሥትም ምንም ዐፄ ዮሐንስ የጻፉላት ደብዳቤ እውነትን የተንተራሰ መሆኑን ብትረዳውም ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩና ጠቅላይ ሚኒስትሩ በጠቅላላው ለእንግሊዝ ጥቅም ከሚያስቡትና ከሚወስኑት ዐልፋ በንግሥትነቷ ልትረዳቸው የምትችልበት አንዳች ነገር አልነበረም ።

ከርሳቸው ቀጥ ያለ ወይም ግልጽ የሆነ ጥያቄ ሲላክ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እየተረቀቀ በንግሥቲቷ ስም የሚመጣላቸው ደብዳቤ የተጠማዘዘ ፣ የዲፕሎማሲ አነጋገር የሠፈረበትና አወላዋይ ዐረፍተ ነገር የሞላበት ነበር ። በታኅሣሥ 12 ቀን 1872 ዓ. ም. የመጣላቸውና ተተርጉሞ የቀረበላቸው ደብዳቤ እንደዚህ ይላል ።

አንደኛ ፣ ለግብጹ ከዲቭ እንደሚጻፈው ለልዑል ዮሐንስ የኢትዮጵያ ንጉሥ የሚል ነበር ። ተውፊቅን ልዑል ብለው እርሳቸውን ግርማዊ እንዳይሉ ይጠነቀቃሉ ማለት ነው ።

ሁለተኛ ፣ ወደ ፍሬው ጉዳይ ሲገቡ “ በርስዎና በልዑል ከዲቭ መካከል የተነሣውና እኛንም ያሠጋውን አለመግባባት ፣ በወዳጅነትና ሁለታችሁን በሚያስደስት መንገድ እንደሚፈጸም ተስፋ እናደርጋለን።

ሦስተኛ ፣ “በሁለታችሁ መካከል የተወጠነው የስምምነት ንግግር ግቡን እስኪመታ ድረስ ፣ የጠብ አጫሪነት ሰበብ እንዳይፈጠር ከልብ እመኛለሁ ።

አራተኛ ፣ “በሁለታችሁ መካከል ስምምነት በቀጥታ ማድረግ ቢሳናችሁ የእንግሊዝ መንግሥት አማካይ ሆኖ ለማስማማትና በሁለታችሁ መካከል ያለውን ጠብ ለማራቅ ደስተኛ ነው” የሚል ነው ። ይህ ዐይነቱ አባባል ፣ የዲፕሎማሲ አነጋገሩም ፣ የዘዴውም ሥልት ባልሠፈነበት ኋላ ቀር ለሆነው የኢትዮጵያ መንግሥት ግር ማለቱ አይቀርም ።

1 Public Record Office, London-Fo95- (7-38-2) 99-Fo95-739- Fo95- 73. B.Tafla, Ethiopia and Germany,p.200.



የእንግሊዝ መንግሥት ፣ በዚህ በ19ነኛው መቶ ዓመት ኃያሉ የቱርክ ግዛት ሊወድቅ ሲንገዳገድ እርሱን ለመተካት በሚያደርገው የፖለቲካ ዘዴው ፣ ትከሻውን እየሰጠ በመጠኑ የሚፈታተነው የፈረንሣይ መንግሥት ነበር ። የጀርመንና የኦውስትሪያ ፣ የሩስያ ተቃውሞ እምብዛም ሩቅ አይሔድም ። የግብጽ የበላይ ጌታ የነበረው የቱርክ ሡልጣን በስጣንቡል ቤተ መንግሥቱ ተቀምጦ ባካባቢው ያሉትን ብቻ እየተቆጣጠረ ፣ ባለፈው ኃይሉና ዝናው እየተኩራራ ፣ ያረጀ የመንግሥቱን በትረ መንግሥት ገና እንደ ጨበጠ ፣ ዕለት በዕለት በርሱ ግዛት ውስጥ የነበሩትን ፣ ከራሱ አንጡራ መንግሥቱ ራቅ ያሉትን ፣ በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ አካባቢ የሚገኙትን ወደቦች ፈረንጆቹ ሲቀራመቷቸው ለይስሙላ ተቃውሞውን በቃልም ፣ በጽሑፍም እያቀረበ በዝምታ ተቀምጧል ። ለስሙ የርሱ ተገዥ የነበረው የግብጽ መንግሥት የኢኮኖሚውም ፣ የአስተዳደሩም እጅና እግሩ በእንግሊዞች ታስሮ በነርሱ ፈቃድና ውስጠ ትእዛዝ ዐይኑን ጨፍኖ ይገዛ ነበር ። በግዛቱ በሱዳን በማህዲስቶቹ እጥቂነት ቢያለቡት ስለ ተዋከበ ፣ ለመቆየት ሳይሆን ለመውጣት እንኳን የሚጠቀመው በእንግሊዞች ሥልጣንና ዘዴ ነበር ።

በበኩላቸው ዐፄ ዮሐንስ ሎርድ ናፒዬርንና ንግሥት ቪክቶርያን በመማጠን ቢታሪክ የኢትዮጵያ የነበረውን ነገር ግን ፣ በመጨረሻ በቱርኮችና በግብጾች እጅ ወድቆ የቆየውን የቀይ ባሕር አካባቢና ከሱዳን ወሰን ላይ የሚገኘውን በእንግሊዝ ረዳትነት ላገራቸው ለኢትዮጵያ ለመጨመር እመጣጣር ላይ ሳሉ ፣ እንግሊዝ ግን ሁሉንም እየሸነገለ በበኩሉ የሚያስበው የራሱን ጥቅም ብቻ ነበር ።

የኢጣሊያ ግዛት ግማሹ በፈረንሳይ ፣ የቀረውም በኦውስትሪያ ተወስዶ በውስጡም ተከፋፍሎ ሲኖር በ1853 ዓ. ም. ላይ አንድነቱን መሥርቶ የኢጣልያ መንግሥት ለመባል በቃ ። አስተዳዳሪዎቹም በእንግሊዝ ጥላ ውስጥ ተከልለው ከቅርምቱ ድርሻቸውን ለማግኘት ሲሉ የእንግሊዝን ባለሥልጣኖች ደጅ ይጠኑ ነበር ።

ዘዴኛው የእንግሊዝ መንግሥት ፣ የሁሉንም መሣሪያነት እንዳያጣ “እንተኛው ታገሥ ፣ ያንተም ችግር ገብቶኛል ፣ አቀናዋለሁ ወይም ሁለታችሁን ለማስታረቅ ዝግጁ ነኝ” ሲል ለግማሹ ደግሞ ፣ “ያንተኛውንም ጉዳይ አጥንቼ ለመርዳት የተዘጋጀሁ ነኝ ፣ ወይም አንተ በዚህ ወደብ አልፈህ ቁራጭ መሬት ብትይዝ አልቃወምም ፣ እንተኛውም ከበረታህ በግዛትህ ብትቆይ ግዴለኝም” እያለ ለሁሉም ምክር እየሰጠ ፣ አለኝታነቱም እንዳይጠፋ በዘዴ ተስፋ እየለገሠ ፣ እርሱን መሣሪያ ሊያደርጉ የፈለጉትን ሁሉ በመጨረሻ ፣ ትንሽ አሳይቶ ብዙ በመውሰድ ፣ የርሱ መሣሪያና ለግዛት መሸጋገሪያ ያደርጋቸዋል ።

ወደፊት እንደምናየው ፣ ግብጾችን ባሼ ዮሐንስ መሣሪያነት ከተከ በቡት ሥፍራ በነጻ ካስለቀቀ በኋላ ፣ ጣልያንን ወደ ምጥዋ መጋበዙ የባላጋራውን የፈረንሳይን ኃይል ለማድከም ብቻ ሳይሆን ፣ እንደ ኢትዮጵያውያኑ ጣልያኖች በከሰላ በኩል የበረቱትን ማህዲስቶችን (ደርቡሾች) እንዲዋጉለትና ደርቡሾቹ ሲዳከሙ ፣ የተዳከሙትን በቀላሉ ደምስሶ የራሱ ግዛት ለማድረግ ነው ። አሁንም ዐፄ ዮሐንስንና ግብጾችን ሲያስታርቅ በእርቁ ውስጥ ላይ ላዩን የግብጽና የኢትዮጵያ ጥቅም ያለበት ሲመስል ፣ በኋላ ግን ከፍጻሜው ላይ ወለል ብሎ የሚታየው የርሱ ጥቅም መጠበቁ ነው ። ባሼ ዮሐንስ እርዳታ ግብጾቹ ከሱዳን ለቀው ሲወጡ እርሱ እንደሚተካ ያውቅ ነበር ። ግብጾቹንም ፣ “ሱዳንን ከመልቀቅ በቀር ሌላ መፍትሔ የላችሁም” እያለ የዘመድ መካር መስሎ ሲገፋፋ ፣ ለመውጫና ለጉዞ ገንዘብ በቸገረ ቁጥር እያበደረ የራሱን ገዥነት በሱዳን ተካ ። በዚህ ሁኔታ ደግሞ ዐፄ ዮሐንስ ወደ ፊት ከምናነበው ከሔዊት ውል በኋላ ወደፊት ከደርቡሾቹ ጋር ብቻ ቸውን ተዋግተው ሲሞቱ ፍጻሜውን የጠላቶቹን የደርቡሾቹን ኃይል እንደሚያዳክሙለት እያወቀ ፣ መጠነኛ እርዳታ እንኳን ሊለግሣቸው አልፈለገም ። እርሱ በፖለቲካ ስሌትና ዘዴ አስቀድሞ ዐውቆ የጐነጐነው፣ ኢትዮጵያና ሌሎቹም መታለላቸውን የሚያውቁት ለማሻሻል ወይም ወደኋላ ለመመለስ በማይችሉበት በመጨረሻው የችግር ሰዓት ነው ።

ቢሆንም ፣ ሁሉም መንግሥት በየበኩሉ እንዳቅሙ ይኸን የመሰለውን የፖለቲካ ዘዴ መጫወት ይፈልጋል ። ነገር ግን ፣ የመሪዎቹ ዐይነት እንደ እንግሊዞች በራድነት ፣ ጽናትና ታጋሽነት ስለሚጐድላ ቸው ፣ የዘዴያቸው ዓላማ እንደ እንግሊዝ ሩቅ ሳይደርስ በቅርቡ ፣ ባል ሆነ ግርግርና እድራጎት ፣ በሰበብ አስባብ ይቀጭና ይጋለጣል ። መንግ ሥትን ከፍም ዝቅም ሊያደርግ የሚችለው የሰዎች የችሎታቸው ዐይ ነት መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው ።

ስለዚህ የእንግሊዝ መንግሥት ባሁኑ በ19ነኛው መቶ ዓመት ከማንኛውም የአውሮፓ ኃያል መንግሥት የበለጠ የመርከብ ጌታ ስለሆነ ፣ ብዙ ጊዜም ሊይዛቸው የፈለገውን አገሮች በመዠመሪያ ለመርከብ መተላለፊያ ፣ ለሸቀጥ ማውረጃና መጫኛ ፣ ለወታደር ማከ ማቻ የሚስማሙትን ወደቦችና ሸቀ ጉን ሊበትን የሚችልባቸውን አገ ሮች በመሆኑ የሱአኪን ፣ የዘይላን ፣ የአደንን ፣ የበርበራን ወደቦች . . . መያዝ ከዚሁ ዓላማ ጋር የተዛመደ ነው ። በሎንዶን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ የሚቀመጡት ባለሥልጣኖች ፣ በዋናው ምክር ቤት ለአባልነት የተመረጡት መማክርት በፖለቲካ የበሰሉና ከነዚህም ጋር የጦር መርከብ እድሚራሎች ፣ የምድር ጦር አዛዦች ሁሉ ንቃትም ፣ ጽናትም ፣ ድፍረትም ፣ ዘዴም ያላቸው ሲሆኑ



ሲያስፈልግም በጀግንነት መሞትን ወይም ማፈግፈግን የሚያውቁ፣ ለጠላት ብቻ ሳይሆን ለወዳጅም የማይመቹ ጠምዛዛና ጥብቅ ሰዎች ናቸው ።

በዚህም ላይ ፣ የእንግሊዝ መንግሥት በእንዱስትሪ የበለጠገ አገር እንደ መሆኑ መጠን ፣ የራሱን ሸቀጥ በያዛቸው ወይም በሚይዛቸው ወደቦች አማካይነት ለብዙ አገር እየበተነ ፣ ባገሩ የሌለውን ሸቀጣ ሸቀጥና ለእንዱስትሪ የሚያገለግለውን ጥሬ ሀብት እያጋዘ ፣ ከብዙ ጊዜ ዠምሮ መንግሥቱ በኢኮኖሚና በማናቸውም መስከ እየደረጀ መጥቷል።

ባሁኑ ጊዜ በግብጽ ላይ ከሁሉም የበለጠ ያተኮረበት ምክን ያት ፣ እንደኛ የሰዊዝ ካናል ከተከፈተ ወዲህ ሥፍራው ለአውሮ ፓም ፣ ለአፍሪካም ለእስያም መተላለፊያ አቋራጭና ዋና በር በመሆኑ ነው ። ይኸን ሥፍራ ያለ ጦርነት ለመያዝ ያገዘው እንደ አጋጣሚ ቀድሞ በ17ኛውና በ18ኛው ክፍለ ዘመን ዓለምን ያንቀጠቀጠው የቱ ርክ የቄሣር ግዛት በዚህ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መዋደቁ ምቹ ሁኔታ ስለ ፈጠረለት ነው ። የቱርክን ግዛት ለመያዝ ዐውቆ እንደ በሰለ ፍሬ ሲወድቅ እየጠበቀ ከመልቀም በቀር በማናቸውም ግንባር ከቱርክ መንግሥት በኩል ወታደራዊ ኃይል አልገጠመውም ።

ከቱርክ መዳከም የግብጽ ውድቀት ስለ ተወለደ ፣ ይኸን የተረ ዱት እንግሊዞችና ፈረንሳዮች ቱርክ ወይም ግብጽ በሚለቀው አገርና ወደብ ለመግባት አሰፈሰፉ ። በኢኮኖሚ ፣ በአስተዳደርም ፣ በጦር ድርጅ ትም በምንም ዐይነት የድጋፍ ሁኔታ ሳያሳዩ ፣ እንዲያውም የሚወድቅ በትን መንገድ ብቻ እየጠረጉ ከኋላ ይገፉት ነበር ። እላይ እንደ ተባ ለው ከሁለቱም የበለጠ ነገሩን በትዕግሥትና በጽናት እየተከታተለ በግብጽም ፣ በሱዳንም ረዥም እግሩን የሰደደው እንግሊዝ ነበር ። ከቱ ርክም ፣ ከግብጽም ጋር ምንም ዐይነት ገሃድ የሆነ ጠብ ሳያሳይ እንዲ ያውም የልብ ወዳጅና ለችግር ደራሽ እየመሰለ ፣ በስጣንቡል ፣ በካ ይሮ ፣ በየሌጋሲዮኑ ፣ በየቆንስላው ፣ በየንግዱ ማኅበር ለፖለቲካው አገ ባብ ችሎታና ትጋት ያላቸውን እየመረጠ በሹመት አስቀምጦ ውስጠ ግዝገዛውን በደንብ ያካሒድ ነበር ። በካይሮ የፖለቲካና የንግድ ወኪል ሆኖ የተቀመጠው ሰር ባሪንግ ኤቭሊን ፣ በኋላ ሎርድ ክሮመር የተባ ለው ዋና የእንግሊዝ ፖለቲካ አውጠንጣኝ ነበር ። ይኸም ሰውዬ በሎንዶን ቤተ መንግሥትና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስተያየቱ ተሰ ሚና በግብጾቹ ዘንድ ተፈሪ ነበር ። ስለዚህ ከሌሎቹ የበለጠ ከባሪንግ በሚሰጠው አስተያየት መሠረት ቀይ ባሕርንም ፣ የአባይ ሸለቆንም በበላይ ሆኖ ለመቆጣጠር በቅድሚያ ግብጽንና ኢትዮጵያን በተቻለ ማስማማቱ ይጠቅማል ብሎ ያቀረበው አሳብ በእንግሊዝ መንግሥት ዘንድ ተቀባይነት አግኝቷል ።

ስለዚህ ፡ ግብጽና ኢትዮጵያ በጦርነት ሲቀሳቀሱ ግዛቴን ከሜዲትራኒ ባሕር እስከ ሕንድ ውቅያኖስ አደርሳለሁ በሚል ምኞት ተውጦ የነበረውን ኤስማኤልን ዐፄ ዮሐንስ ሁለት ጊዜ አሸንፈው መመለሳቸው ይታወቃል ። ነገር ግን ፡ ከዚህ በፊት እንዳልነው ፡ ሁለት ጊዜም ቢያሸንፉ ለግዛት ወደ ደጋ የመጣውን የግብጽን ጦር በሜዳ ላይ ውጊያ አሸነፉ እንጂ ፡ ከጉራዕና ከቀይሀኮር ምሽግ ለማስለቀቅ ወይም ወደቆላ ወደ ምጥዋ ዘልቀው ወደቡን ሊያስለቅቁትና ይገባኛል የሚሉዋቸውንም ወረዳዎች በጦር ኃይላቸው ወደ ኢትዮጵያ መመለስ አልቻሉም ። እነዚህን ወረዳዎች ለማግኘት የተማመኑት በራሳቸው ኃይል ሳይሆን በእንግሊዝ አጋዥነትና በሰላም መንገድ ነበር ።

ኢትዮጵያ ፡ የረዥም ዘመን ነጻነት እንደ ማግኘቷ መጠን ፡ ዜግና ተዋጊ ወታደር ፡ በጠባዩ ብልህ የሆነ መሪና ሕዝብ ሳታጣ ልዩ ልዩ ሀብት የያዘ መሬትም እያላት ፡ ለረዥም ዘመን ከሥልጣኔ ወደኋላ የቀረች አገር በመሆኗ ፡ ቴዎድሮስም ፡ ተክለ ጊዮርጊስም ፡ ዮሐንስም ፡ ምኒልክም የወደብን አስፈላጊነት ቢረዱት እና ጥያቄ ቢያቀርቡም ፡ እንግሊዞች ወደቡን የራሳቸው ደጋፊ ለነበረና ከኢትዮጵያ የተሻለ ጥንካሬ ለነበረው ለአንድ አውሮፓዊ መንግሥት (ለኢጣሊያ) ለመስጠት ይፈልጉ ነበር ።

ደግሞም በዚህ ዘመን በዓለም ላይ የቅኝ እገዛዝ ተፋፍሞ በበርሊን በ1884 ዓ. ም. የአውሮፓ የቅኝ አገር ገዥዎች አፍሪካን ያለጦርነት በሰላም ለመከፋፈል ተዋውለው ከዚያ ወዲህ በብሩክሴል በጋርዮሽም ፡ በተናጠልም ስምምነት ያደረጉት ከማናቸውም ከሠለጠነው የአውሮፓ ሀገር የጦር መሣሪያ ለአፍሪካውያን እንዳይተላለፍ ነበር ። በዚሁ ዐይነት ማንም በአፍሪካ ያለ አገር የማስተዳደር ችሎታ ያለው መንግሥት ቢሆን ራሱ የወደብ ጌታ ሆኖ መሣሪያም ፡ ሸቀጥም እንደ ልቡ ከውጭው ዓለም እንዲያገኝ አይፈልጉም ። ስለዚህ ነበር አውሮፓውያን በተለይ ቱርክ በሚለቋቸው የአፍሪካና የእስያ ወደቦች እየተሻቀዳደሙ ሱአኪንን ፡ በርበራን ፡ ዘይላን ፡ አደንን ፡ ጅቡቲን ፡ ዛንዚባርን የያዙት ። ግብጽም ለስሙ የሰዊዝ በር ባለቤት ቢሆንም ፡ በፊትም በቱርክ ውስጥ ስለነበረ ፡ አሁንም በእንግሊዝ ተቆጣጣሪነት ሥር ስለሆነ በራሱ ፈቃድ የሚያደርገው ነገር አልነበረም ። እንኳን አስተዳደሩ የማኅበሩ አክሲዮን በዕዳ የተነሣ አብዛኛው ለእንግሊዝ ፡ የቀረውም ለፈረንሣይ መሸጡን ባለፈው አንብበናል ።

በተለይ ደግሞ ፡ በዚህ በ1872—76 ዓ. ም. ላይ ግብጽ በሱዳን በማህዲስቶች ጦር እየተዋከበ ኢኮኖሚውም በእንግሊዝና በፈረንሳይ




እየተገዘገዘ ስለ ደከመ ፡ ያሁኑ መሪ ከዲቭ መሐመድ ተውፊቅ በአባቱ በኢስማኤል ጊዜ የነበረውን የመስፋፋት ዓላማ ትቶ ከእንግሊዝ መንግሥት አስፈቅዶ ፡ "ካፄ ዮሐንስ ጋር አስታርቀኝ" ብሎ ጐርደንን የላከው ከመቸገሩ የተነሣ ነበር ። ጐርደን ግን ፡ ካፄ ዮሐንስ እንደ ተገናኘ ንጉሠ ነገሥቱን በመናቅ የተውፊቅን ጉዳይ ለማስፈጸም በኃይል ማስፈራራትን ስለ ጨመረ ፡ ካፄ ዮሐንስ በጠብ በመለያየት የእንግሊዝን የልስላሴ ፖለቲካ አጠፋፍቶ ወደ ሱዳን ሔዶ ለመሞት በቃ ። ስለዚህ በሁለቱ መካከል የእንግሊዝ መንግሥት እንደ በላይ ዳኛ ሆኖ የነገሩ ሁሉ አዝማሚያ ወደርሱ ጥቅም እንዲያመራ በሰፊው እየተመለከተ በየአንጻሩ ለግብጽም ፡ ለኢትዮጵያም የወዳጅነት መልክ እያሳየ ለእንዳንዳቸው ችግር መፍትሔ ይሰጥ እየመሰለ ፡ መደምደሚያውን ግን ወደፊት የሚመጣውን የራሱን ጥቅም ያደላድል ነበር ።

በኋላ ግን ፡ በአለፈው እንደ ተመለከትነው በሱዳን የርሱ ጄኔራሎች በማህዲስቶች ስለ ተገደሉ ፡ በኢትዮጵያና በሱዳን ጠረፍ የሚገኙት የግብጽና የቱርክ ወታደሮች ተከበው ከታላቅ ጭንቅት ላይ ስለሚገኙ ፡ ለዚህ ጉዳይ መፍትሔ ይሆናል ብሎ ያመነበት ኢትዮጵያንና ግብጽን የማስታረቁ ጉዳይ ነበር ።


በዚህ ዕርቅ ፡ ግብጾችና ቱርኮች ከሱዳን ፈጽመው ለቀው ሲወጡ እርሱ ለመተካት አመች ሁኔታ እንዲፈጠርለት ከማወቁ ጐን የነጭና የጥቁር አባይ የሚተላለፉባቸውን የሱዳንን ግዛት ሲይዝ ፡ በነዚህ ወሃዎች ሕይወት ያላትን ግብጽን በቀላሉ ለዘለቄታ ለመግዛት እንደሚቻል ጉዳዩ ቀደም ብሎ በነሳሙኤል ቢከር ፡ በነባሪንግ በሰፊው ተጠንቶ የቀረበና በእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ ጉዳይ ነበር ። እንደዚሁም በሱዳንና ከሱዳን ወደ ደቡብ ያሉትን ኤኳተርን ፡ ዩጋንዳን ከታላላቆቹ ሐይቆች ጋር ሲይዝ በታንጋኒካና በካሜሩን የገቡት ጀርመኖች በኮንጎ የተሠማሩትን ፈረንሳዮችንና ቤልጂኮችን ለመቆጣጠር አመች ነበር ።

ስለዚህ እነ ባሪንግ ፡ እነ ዋይልድ አስቀድመው በጠቆሙት መሠረት ጐርደን ከአምስት ዓመት በፊት ተውፊቅንና ዮሐንስን ለማስማማት መጥቶ ያበላሸውን ግንኙነት ብማሻሻል ያፄ ዮሐንስን የዘወትር የግዛት ጥያቄ በከፊል በማሟላት ፡ ንጉሡ በከሰላ አካባቢ የተከበቡትን ግብጾችና ቱርኮች በመርዳት ባገራቸው አሳልፈው ወደ ምጥዋ እንዲያደርሱ ሁለቱን በቅድሚያ ለማስማማት ለዘብ ያለ ጠባይና ችሎታ ያለው ሰው ሲፈለግ ፡ ምርጫው ሬር አድሚራል ዊሊያም ሒዊት ከሚባለው ላይ ወደቀ ። ይኸም ሰው ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የተፈራረመውን ውል ወደፊት እናነባለን ።



**ዐፄ ዮሐንስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት**

**(ፐብሊክ ሬኮርድ ኦፊስ ፥ ሎንዶን)**



፴፪ ዮሐንስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት ሌላው ደብዳቤ

(ፐብሊክ ሬኮርድ ኦፊስ ፥ ለንደን)

# ምዕራፍ ሐያ ሦስት

## በሬር አድሚራል ሔዊት አማካይነት የእንግሊዝ ፡ የኢትዮጵያና የግብጽ ስምምነት

ባለፈው ሁሉ እንዳመለከትነው ፡ የእንግሊዝ መንግሥት የግብጽን የውስጥ አስተዳደሩን ለባላባቱ ለከዲቭ ተውፊክ ትቶ በበላይ በማናቸውም ረገድ ቁጥጥሩን እያጸና እንደዚሁም በሱዳን የነበረውን የግብጽ ገዥነት በራሱ ለመተካት ሲል ግብጽን በሱዳን ግዛት እንዲቆይ ሳይሆን ፡ እንዲለቅ ለመርዳት ማናቸውም ጥረት በማድረግ ላይ ነበር ። ግብጾችም ቢሆኑ በሱዳን የማህዲስቶች የውጊያ አጥቂነት በጣም ስለ አስጨነቃቸው ፡ ቀድሞ በመሐመድ ዐሊና በከዲቭ ኢስማኤል ጊዜ እንደ ልባቸው ገብተው የተስፋፉትን ያህል አሁን ከእስራት ፡ ከምርኮ ፡ ከሞት የተረፉትና በኢትዮጵያ ጠረፍ አካባቢ ተከበው እየተከላከሉ በሥጋት መካከል የቆዩት ዋና ምኞታቸው በምን አኳኋን ከየምሽጋቸው ወጥተው ነፍሳቸውን አድነው ወደ አገራቸው የመግባቱ ነገር ነበር ።

በግብጾቹ አንጻር ፡ ያፄ ዮሐንስ ምኞት ደግሞ በግብጾች እጅ የነበረውን የኢትዮጵያን ግዛት ማስመለስ ፡ ከውጭ አገር ማናቸውንም መሣሪያ ገዝተው በምጥዋ ወደብ በኩል ያለችግር አስገብተው መንግሥታቸውን ማጽናት ፡ ቀብቶ ንጉሥ የሚያነግሠው ፡ ለካህናት ቅስና ፡ ዲቁና ፡ ለወጣት ተማሪ ክህነት እየሰጠ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በበላይ የሚጠብቀው ጳጳስ ከግብጽ ሲመጣ ችግር እንዳይገጥመው ስለነበረ ፡ የሁለቱ መንግሥታት ችግርና ምኞት የገባው የእንግሊዝ መንግሥት የራሱ ጥቅም የሚገኘው ከሁለቱ ችግርና ከመፍትሔው መሆኑን በመገንዘብ ፡ ሁለቱን የቀድሞ ጠበኞች ለማስማማት ሬር አድሚራል ዊሊያም ሔዊትን ከመደበ በኋላ ፡ የዚህን አሳብ የእንግሊዝ ምክር ቤት በመጋቢት ወር 1876 ዓ.ም. ላይ አጽድቆታል ።

ሔዊት የጠቅላላው[1] የእንግሊዝ የባሕር ኃይል ምክትል አዛዥ በእንግሊዝ አገር በመካከለኛው ምሥራቅ በሕንድ አገር የታወቀ

---

1 ዘውዴ ገ/ሥላሴ በገጽ 125 ላይ ሬር አድሚራል ሰር ዊልያም ሔዊት በወቅቱ የነበረው ሥልጣን በቦምቤይ የኢስት እንዲስ ጠቅላይ አዛዥ እንደነበረ ገልጸዋል ፡፡

የባሕር ኃይል ባለሥልጣን ነበር ። እርሱም ለዚህ መልእክት ከተመደበ በኋላ ዤኔራል ቪ ቤከር* የሚባለውን የጦር አዛዥ በሱአኪንና በምጥዋ በኩል በቅድሚያ ወደ ሐማሴን ዐልፎ ከራስ አሉላ ጋር ግንኙነት በማድረግ የጉዞውን ሁኔታ እንዲያደላድል አስቦ ሳለ ፣ ቤከር በሱዳን ዑስማን ዲግና ከሚባለው ከደርቡሾቹ (ማህዲስቶች) የጦር አለቃ ጋር የሚያደርገው ጦርነት ፋታ ስለ አልሰጠው ፣ በሱ ምትክ በጅዳ ቆንሲል የነበረውና የመካከለኛውን ምሥራቅ ሁኔታ ደህና አድርጎ ያጠናው አውግስጦስ ብላንዲ ዋይልድ ተመደበ ። እርሱም ከባሪንግ ጋር በመስማማት ከዚህ በፊት ፣ "በሱዳን ለመጣው ችግር መፍትሔ ግብጽንና ኢትዮጵያን በቅድሚያ ማስማማት ነው" ብሎ ለመንግሥቱ አሳብ ማቅረቡ ይታወሳል ።

ስለዚህ ፣ አድሚራል ሒዊት በሚያዝያ 18ና በግንቦት 13 ቀን ለባሕር ኃይል ሴክሬተር(ሚኒስትር) ፣ በሰኔ 30 ቀን 1876 ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለኤርል ግራንቪል በላከው ሪፖርት እንደሚያመለክተው ፣ በመጋቢት መጨረሻ ላይ ምጥዋ እንደገባ ጥቂት ጊዜ ዐርፎ ሚያዝያ 7 ቀን ከምጥዋ ተነሥቶ ወደ አሥመራ ጉዞ ዠመረ ። ከርሱም ጋር ግብጻዊው የምጥዋ አገረ ገዥ ሚሰን ቤይ ፣ አብሮት እንዲመጣ አድርጎ ከርሱ በቀር በተጨማሪ በመቅደላ ጦርነት ስሙ የታወቀውና በእንግሊዝ አገር ለምርኮኛው ወጣት ለዓለማየሁ ቴዎድሮስ ሞግዚት የነበረው ካፒቴን ስፒድ ፣ ኮማንደር ኤርነስ ሮልፍስ ፣ ሌፍቴኔንት ወልተር ግራሀምና ሌሎችም ተከተውለታል ።

በጉዞም ላይ እንዳለ ፣ እነዚህን የመጨረሻዎቹን የጦር መኰንኖች ቀደም አድርጎ ወደ ሐማሴኑ ገዥ ወደ ራስ አሉላ ጉዞውን እንዲያቃኑ አስቀድሞ ልኮ ቀጥሎ ራሱ ከምጥዋ ሚያዝያ 7 ቀን ተነሥቶ በየመንገዱ እያረፈ በመጓዝ ከአራት ቀን በኋላ አሥመራ ሲገባ ፣ ራስ አሉላ 2000 የፈረሰኛ ብዛት ያለው ፣ የእግረኛ ጦር አሰልፈው በክብር ተቀበሉት ። ከርሳቸውም እንደ ተገናኘ የጉዞው ዓላማ በእንግሊዝ መንግሥት አማካይነት ኢትዮጵያንና ግብጽን ለማስማማት መሆኑን በመዠመሪያ ለራስ አሉላ ገልጾ ፣ ቀጥሎ መቀሌ ለሚገኙት ላፄ ዮሐንስ ልኮ ነበርና ንጉሡ ዐድዋ ከተማ ላይ እንደሚቀበሉት በራስ አሉላ አማካይነት ተገለጸለት ።

ከዚህ በኋላ ፣ ንጉሡ ከዋናው ቤተ መንግሥታቸው ከመቀሌ ተጉዘው እ.አ.አ. በግንቦት 26 ቀን 1876 ዐድዋ ሲገቡ ፣ እርሱም ከራስ አሉላ ጋር ተጉዞ በማግሥቱ በግንቦት 27 ቀን ከንጉሡ ጋር ተገናኘ ።

---

* የሳሙኤል ቤከር ወንድም



የንግሥቲቱን ደብዳቤና የተላከላቸውን ገጸ በረከት በዝርዝር አቀረበ ።* በዚህ ጊዜ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ገጸ በረከቱን ከተቀበሉና የደብዳቤውንም ቃል ባስተርጓሚ ከሰሙ በኋላ ፣ ዙፋናቸውን ራሱን ያገኙት በእንግሊዝ መንግሥት እርዳታ መሆኑን ጠቅሰው ፣ ያሁኑንም ውለታ ምን ጊዜም የማይረሱት መሆኑን ገለጹለት ።

ቀጥሎ በግንቦት 28ና በ31 ቀን እ.አ.አ. 1884 እንደገና ተገናኝተው ፣ ስለ ጠቅላላው ስምምነት በመሸሻ ወርቄ አስተርጓሚነት ሒዊትና ዐፄ ዮሐንስ በሚወያዩበት ጊዜ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከሰላን ለመውሰድና የምጥዋንም የቀረጥ ገቢ ከግብጽ መንግሥት ጋር እኩል ለመካፈል ጥያቄ ቢያነሡ ፣ አንደኛ ከሰላን እንዲወስዱ ለመፍቀድ ከመንግሥቴ ሥልጣን አልተቀበልሁም ካላቸው በኋላ ፣ ስለ ቀረጡ ገቢ "ባይሆን እርስዎ የሚያስመጡትና የሚልኩት ዕቃና ሸቀጥ በነጻ እንዲተላለፍልዎ እናደርጋለን እንጂ ፣ የቀረጡ ገቢ ክፍያ የሚቻል አይደለም ። እርስዎ ግን በምጥዋ ወደብ ዐልፎ ወደ ርስዎ ግዛት የሚገባውን ለመቅረጥ ኬላ ለማቋቋም ይችላሉ" ሲል መለሰ ።

ከዚህ በኋላ ፣ በጠቅላላው ጉዳይ ንጉሠ ነገሥቱና ሬር አድሚራሉ እንደዚሁም የግብጽ መንግሥት ወኪል የቃል ስምምነት ካደረጉ በኋላ ፣ ውላቸውን ከዚህ እንደሚከተለው በጽሑፍ አሥፍረው በሰኔ 3 ቀን 1876 ዓ. ም. ተፈራረሙ ። በእንግሊዝኛ የተጻፈው የውሉ ቃል በመጽሐፉ መጨረሻ አባሪ ሆኖ ገብቶአል ።

ሬር አድሚራል ፣ በእንግሊዝኛ ያሠፈረውን የውል ቃል የመንግሥቱ የይፋ ቋንቋ ወደሆነው ወደ አማርኛ ለመተርጐም ችግር — ተፈጥሮ ስለነበረ ፣ ካፒቴን ስፒዲ ከካይሮ ይዞት በመጣው ሰው ወደ አማርኛ ማስተር ጐሙን በሪፖርቱ ውስጥ ይጠቅሳል ። ካንድ አርመንና ካንዲት ኢትዮጵያዊት የተወለዱት መሸሻ ወርቄና ወንድሞቹ ምርጫ ወርቄና ብሩ ወርቄ እንግሊዝኛ ንግግር ቢያውቁም ፣ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ በትክክል ከመተርጐሙ ላይ ድካም አሳይተው ይሆናል ። በታላቁና በነጻነት የብዙ ዘመን ዕድሜ ባሳለፈው መንግሥት ውስጥ አንድ አማርኛና እንግሊዝኛ አጣርቶ የሚያውቅ ጠፍቶ ከካይሮ በመጣው ሰው እጅ መተርጐሙ የሚያሳዝን ነው ። የሆነ ሆኖ ፣ በዚያው ዘመን ከእንግሊዝኛው ላይ ተተርጕሞ በአማርኛ የሠፈረውና ተፈርሞ የታተመበት ቃል ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

---

* ወደፊት ለንግሥት ቪክቶርያ በሚጽፉት ደብዳቤ ላይ እንደ ተገለጸው 2 መድፍ ከነመሣሪያው ከነጥይቱ ፣ 12 ማለፊያ ፣ 5 መናኛ ጠበንጃ ፣ 1 ልዩ ጠበንጃ (መርቡጥ —ነፍጥ) 2 ሽጉጥ ጠበንጃ (አጠር ያለ ጠበንጃ) አንድ ግምጃ ድንኳን ፣ (ባለ ቀለም) ሁለት ምንጣፍ (ሥጋጃ)

## መጀመሪያ ክፍል*

ይህ ውል ከሚታተምበት** ቀን ጀምሮ በምጥዋ ወደ ሐበሻ የሚገባ ከሐበሻም የሚወጣ ዕቃ ሁሉ የጦር መሣሪያ ነፍጥና መድፍ ጥይትም ቢሆን በእንግሊዝ ውክልና ነጻ እንዲወጣና እንዲገባ ተፈቅ ድዋል ።***

## ሁለተኛ ክፍል

ከዲሴምበር መባቻ**** ጀምሮ በ1884 በሐበሻም በመስከረም 8ኛ ቀን 1877 ቦጎስ የሚባለው አገር ላፄ ዮሐንስ***** ይመለሳል ። በከሰላ ፡ በአመዲብ ፡ በሰንሂትም ያሉት የከደዊ****** ወታደሮች ተነሥ ተው አገራቸው ሲሔዱ ፡ አሁን በምስር ከደዊ እጅ ያለው የጦሩ ቤት በውስጡ ካለው የጦር መሣሪያና ዕቃ ሁሉ የዐፄ ዮሐንስ ገንዘብ ይሆናል ።

## ሦስተኛ ክፍል

ጃንሆይም ንጉሠ ነገሥቱ የከደዊ ወታደሮች ተከሰላ ፡ ተአመዲብ በኢትዮጵያ አድርገው ወደ ምጥዋ እንዲያልፉ ይረዳሉ ።*******

## አራተኛ ክፍል

ክቡር ከደዊም ፡ ጃንሆይ ንጉሠ ነገሥቱ ለኢትዮጵያ አቡን የፈለጉ እንደሆነ ከምስር ደህና አድርገው ይሰዳሉ ።********

## አምስተኛ ክፍል

ጃንሆይም ንጉሠ ነገሥቱና ክቡር ከደዊም ወንጀለኛና ወንጀለኞች (አንድም ብዙም ቢሆኑ) ቅጣት ፈርተው ካንዳቸው አገር ወዳንዳቸው

---

* እንደ ዛሬው አባባል አንደኛ አንቀጽ በማለት ፈንታ

** ከተፈረመበት በማለት ፈንታ እንደ እንግሊዝኛው

*** የእንግሊዝኛው ቃል መድፍ አይጠቅስም ። ውክልና በማለት ፈንታ ጠባቂነት ወይም ዋስትና ሊለው በተገባ ።

**** መባቻ የሚለው የወሩን መጀመሪያ ነው ። (ታኅሣሥ 1 ቀን ለማለት ነው)

***** እንግሊዝኛው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ነው የሚለው ፤ ነገር ግን ያው ነው ።

****** ልዑል ከዲቭን ከደዊ የሚለው በኢትዮጵያ ፊደል በ የሚባለው ፊደል ስለ ሌለበወ ለውጦታል ።

******* ይረዳሉ ለማለት ነው እንግሊዝኛው ለማቃናት ቃል ገብተዋል ነው የሚለው ።

******** ጉዳዩን አቃንተው ለመስደድ ግዴታ ገብተዋል ።



አገር የኰበለሉ እንደሆነ እጁን ይዘው አንዱ ላንዱ ሊሰጡ ተዋ ውለዋል ።

## ስድስተኛ ክፍል

ንጉሠ ነገሥቱ ፡ ይህ ውል ከታተመ በኋላ ፡በእርሳቸውና በክቡር ከደዊ መካከል ጠብ የተነሣ እንደሆን ፡ ስለ ዕርቅ ወደ እንግሊዝ ንግ ሥት ሊያሳዩ* ውል ገብተዋል ።

## ሰባተኛ ክፍል

ይህ ውል ፡ እንደገና በትልቅ (ታላቂቱ) ብሪታንያና በኤርላንድ ንግሥት ፡ በሕንድም ንግሥተ ነገሥታት በከበሩም በምስር ከደዊ ዘንድ ታይቶ ታትሞ** በቶሎ ወደ ዐድዋ ተመልሶ ይመጣል ።

ለዚህም ምስክር አድሚራል ሴር ዊሊያም ሔዊት ስለ ትልቅ ብሪታንያና ስለ ኤርላንድ ንግሥት ፡ ስለ ሕንድም ንግሥተ ነገሥታት እንደራሴ ሆነው ጃንሆይም ንጉሠ ነገሥቱ ስለ ራሳቸው ሆነው ክቡር ሜሰን ቤይም ስለ ክቡር የምስር ከደዊ ሆነው በዚህ ውል ማኅተማቸ ውን አትመዋል ። ተጻፈ ዐድዋ በዩኒ (ጁን) በሦስተኛው ቀን በ1884 በሐበሻ 26 ግንቦት በ1876 ።

የንጉሥ ማኅተም
ውሊያም ሔዊት
ሜሰን ቤይ [1]

ይኸን ውል የተረጐመው አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ከአማርኛው ትርጉም ግርጌ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል አስፍሯል ። "ማሳሰቢያ ይህ ውል በታተመ በስድስተኛው ወር እንግሊዞች ምጥዋን ለኢጣልያ ሰጡና ውሉን አፍርሰው ዐፄ ዮሐንስን አዋጉዋቸው ። ዐፄ ዮሐንስ ግን ፡ በውላቸው ቁመው ከደርቡሽ ጋር እየተዋጉ በሱዳን የተከበበ ውን የምስር ወታደር ወደ አገሩ አገቡት ።"[2]

---

* ለመፍትሔው ለእንግሊዝ ንግሥት ለማመልከት ተስማምተዋል ።

** ጸድቆ ለማለት ነው

1 S. Rubensen ,Survival of Ethiopan Independance በሚል ርዕስ ላይ ያሳተሙት ያማርኛ የውል ሰነድ የእነጋገር አካሔድ ይለዋወጣል ። ምናልባት በሁለት አስተርጓሚ የተሠራ ይሆናል ፤ ገጽ 357-358 ።

2 Correspoondence relating to the mission of vice-Admiral Sir W. Hewett to a-king Joho of Abyssinia and treaty betweeo Great Britain, Egypt and Abyssinia printed by Narrison and Son,s pp. 1· -7. ——————
Carlo Rossetti, Storia Diplomatioua dell' Ethiopina Durante il Regno di Menelik II, pp. 25-27.

ወደፊት በዝርዝር እንደምናነበው ፣ የተርጓሚው አባባል ትክክል ነው ። የሆነ ሆኖ ፣ ውሉ በአራት ግልባጭ ተዘጋጅቶ ሦስቱ ባለሥልጣኖች ማኅተማቸውን ከውሉ ላይ ካተሙና ሔዊትና ሜስን በየማኅተማቸው አቅጣጫ ከፈረሙ በኋላ ፣ አንዱ ግልባጭ ለንጉሠ ነገሥቱ ፣ ሁለተኛው ለሜሰን ቤይ ሲሰጥ ፣ ሁለቱን ሬር አድሚራሉ ተቀብሎ ለንግሥቲቱ መንግሥት አቅርቦ ውሉን እንዲጸድቅ ካደረገ በኋላ ፣ አንዱን አስቀርቶ አራተኛውን ግልባጭ መልሶ ላዬ ዮሐንስ እንዲልክ ተስማሙ ።

ሬር አድሚራል ፣ ይኸን ውል ተዋውሎ ወደ ሎንዶን ከተመለሰ በኋላ ፣ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለግራንቪል የውሉን ግልባጭ ሰጠ ። ከዚሁ ጋር አያይዞ ባቀረበው ራፖር ላይ ለዚህ መልእክት አብረውት የሔዱት የእንግሊዝ ሹማምንት ያበረከቱለትን አገልግሎት ከምስጋና ጋር አስረድቷል ። ይኸን ውል ለማድረግ ከምጥዋ—ዐድዋ ሲሔድና ወደ ምጥዋ ሲመለስ ፣ በንጉሡ ዘንድ የተደረገለትን አቀባበልና በተለይ በራስ አሉላ በኩል ያገኘውን ምንም ጉድለት የሌለበትን መስተንግዶና የንጉሡ አስተርጓሚ መሸሻ ወርቄ ያበረከተለትን አገልግሎት በምስጋና ገልጧል ።[1]

1 ዝኒ ከማሁ ገጽ 7—8



## ARTICLE I

From the date of the signing of this Treaty there shall be free transit through Massowah, to and from Abyssinia, for all goods, including arms and ammunition, under British protection.

## ARTICLE II

On and after the 1st day of September, 1884, coresponding to the 8th day of Maskaram, 1877, the country called Bogos shall be restored to His Majesty the Negoosa Nezust; and when the troops of His Highness the Khedive shall have left the Garrisons of Kassala, Amedib, and Sanhit, the buildings in the Bogos country, which now belong to His Highness the Khedive, together with all the stores and munitions of war which shall then remain in the said buildings, shall be delivered to and become the property of His Majesty the Negoosa Negust.

## ARTICLE III

His Majesty the Negoosa Negust engages to facilitate the withdrwal of the troops of His Highness the Khedive, from Kassala, Amedib and Sanhit through Ethiopia to Massowah.

## ARTICLE IV

His Highness the Khedive engages to grant all the facilities which His Majesty the Negoosa Negust may require in the matter of appointing A boonas for Ethiopia.

## ARTICLE V

His Majesty the Negoosa Negust and His Highness the Khedive engage to deliver up, the one to the other, any criminal or criminals who may have fled, to escape punishment, from the dominions of the one to the dominions of the other.

## ARTICLE VI

His Majesty the Negoosa Negust agrees to refer al[1] differences with Hhis Highness the Khedive which may arise after the signing of this Treaty to Her Britannic Majesty for settement.

## ARTICLE VII

The present Treaty shall be ratified by Her Majesty the Queen of Great Britain and Ireland, Emperess of India, and by His Hıghness the Khedive of Egypt' and the ratification shall be forwarded to Adowa as soon as possible.

In witness whereof Rear-Admital Sir W.Hewett, on behalf of Her Majesty the Queen of Great Britain and Ireland, Empress of India, and His Majesty the Negoosa Negust on his own behalf, and his Excellency Mason Bay on behalf of His Highness the Khedive of Egypt, have signed and affixed their seals to this Treaty, made at Adowa, the 3rd day of June, 1884' corsesponding to the 27th day of Guinbot, 1876.

(King's Seal.)

L.S. W.Hewett.

L.S. Masson.



## ምዕራፍ ሐያ አራት

### በሔዊት ውል ያፄ ዮሐንስ ጊዜያዊ ደስታና አሳሳች ድል — ራስ አሉላ በኩፊት ከደርቡሾች ተዋግተው ግብጾቹን ስለ ማስለቀቃቸው

### የውሉ ጐደሎነት ያስከተለው ችግር

የሔዊት ውል ፣ ጠቅላላውን ያፄ ዮሐንስን የዘወትር ጥያቄ አያሚ ላም ። በምጥዋ አካባቢ ያሉት ወረዳዎች ወደፊት ለማን እንደሚሆኑ ባይገልጽም ፣ ንጉሠ ነገሥቱ በውሉ ሳይደሰቱ አልቀሩም ። ከጉራዕ ጦርነት ወዲህ ከግብጽ ጋር ተንጠልጥሎ የቆየው ስምምነት ወደ ፍጻሜ ሊደርስ የቻለው ፣ "በእንግሊዝ መንግሥት የወዳጅነት ርዳታ" ነው ብለው ከልብ አምነዋል ።

ደግሞም በዚህ በአሁኑ ውል ለጊዜው ዐፄ ዮሐንስ ከብዙ ዘመናት ዠምሮ እርሳቸውንም ፣ አባቶቻቸውንም ሲያወዛግብ የኖረው አንደኛ በምጥዋ በኩል የጦር መሣሪያና ሸቀጥ የማስመጣቱ ፣ ሁለተኛ አቡን ከእስክንድርያ በየጊዜው የማግኘቱ ፣ ሦስተኛ እስካሁን ከኢስማኤል ፓሻ ጋር በሁለት ጊዜ ጦርነት ሲያቆራቁሳቸው የኖረው ዋናው የቦጎስ አውራጃ ጉዳይ በከፊል ውሳኔ ስላገኘላቸው እንደ ታላቅ ድል ቆጥረውታል ። በዚህ ምክንያት ፣ ስለ ተላከላቸው ገጸ በረከትና በተለይ ስለውሉ ያላቸውን ባለውለተኛነት ለመግለጽ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ለእንግሊዝ ንግሥት ጻፉ ።

በስመ እግዚእነ. . . መልእክት ዘሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ወኩሉ አድያሚሃ። ይድረስ ኀበ ክብርት ወልዕልት ንግሥት ቪክቶሪያ በጸጋ እግዚአብሔር አንድነት የሆኑ የቢርታንያና የአየር ላንድ ንግሥት የህንደኬ ቄሣርዩት. . . ከጸፍሁልዎ ወዲህ እጅጉን እንዴት ነዎ. . . ክቡር ብሩህ የሆነ መስተፍሥሒ አልባብ በ1876 ዓ ፣ ምሕረት በግዛትዎ (በነገሡ) በ42 ዓመት የተጻፈ ደብዳቤዎ በቡርከት ሰዓት ከለማኀተሙ ደረሰኝ። ስለፍቅር ብለው የሰደዱልኝ ገጸ በረከትም 2 መድፍ ከለመሳሪያው ፣12 ማለፊያ 5 መናኛ ጠበንጃ ፣ 1 መርቡጥ ፣

2 ሽጉጥ ጠበንጃ ፣ 1 ግምጃ ድንኳን ፣ 2 ምንጣፍ በመርከብ አለቆች እራስ የሕንድ ምስለኔ በታመነ ሎሌዎ በሬር አድሚራል ሰር ውሌም ሕይወት እጅ ተቀበልሁ ደረሰኝ ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ ። የምጽዋንም በር እኔን ደስ ይበለው ብለው እንደ ከፈቱልኝ ኢየሱስ ክርስቶስ የማያልፈውን የመንግሥተ ሰማይን በር ከፍቶ ደስ ያሰኝልኝ ። በመንግሥትም ውስጥ ያሉን መማከርትም እኔን ደስ ሊያሰኙ ይኸን አሰበው ስለ መከሩ እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማያት ደስ ያሰኛቸው ። እኔንም ከርስዎ ጋር በምክር አንድ ሆኜ ከፈቃድዎ ለመዋል ያብቃኝ ። ጥንቱንም በእግዚአብሔር ፈቃድ ለመንግሥት የበቃሁ እርስዎ በሰጡኝ መድፍ ነፍጥ ባሩድ ነው ። * አሁን ደግሞ ይልቁን ፈጽመው ደስ አሰኙኝ ። ከዚህ በፊትም እናት ለልጅዋ እንድትጨነቅ ለኔ መንግሥት ሲጨነቁ ይኖራሉ ። ነገር ግን በቅርብ ቀን ቀርቶ ነው እንጂ ፣ እንኳን እርስዎ የአውሮፓ ነገሥታት መላው ያውቃሉ ፤ የምጽዋ በር የአባቶች የነገሥተ ኢትዮጵያ ነው ፤ አሁንም እንበለ በር ቤተ መንግሥት አይቀናምና በርስዎ ወኪልነት የምጽዋን በር እንድይዝ ያድርጉኝ ብዬ እለምናለሁ ። የቀረው ነገር ሁሉ ሲወሰን የዚህ ነገር አልተወሰነልኝም ። ደግሞ ሬር አድሚራል ሴር ውሌም ሕይወት ሹምዎ የምጽዋን ቀረጥ እኩሌታውን ይያዙ አለኝ ፤ እሺ አትምልኝና ልያዝ ብለው ማተምስ ንግሥትን ሳልጠይቅ አላትምም ብሎኝ መጥቷል ። ተጽሕፈ በአክሱም ከተማ አመ በ19 ሰኔ 1872 ዓ.ም. * *

ይኸን ደብዳቤ ከጻፉ በኋላ ዮሐንስ በሁለተኛውና በሦስተኛው አንቀጽ የተጻፈውን መሠረት በማድረግ ባመቱ በሰኔ 22 ቀን 1877 ዓ.ም. ከሊፋ አብዱላሂ ከቦ ያስጨነቃቸውን የግብጽና የቱርክ ወታደሮች ለማዳን ዋና የጦር አለቃቸውን ራስ አሉላን ከ10 000 ወታደር ጋር ወደ ኩፊት ላኩ ። ኩፊት የሚገኘው በሰበርደትና በአልገዴን አጠገብ ነው ። በዚያም በራስ አሉላና በማህዲስቶቹ አዝማች በዑስማን ዲግና መካከል የዛቻ ቃል[1] ልውውጥ ተደረገ ። ራስ አሉላ

* ናፒዬር በተወላቸው የጦር መሣሪያ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስን አሸንፈው መንገዳቸውን ሲያወሱ ነው ።

** እንደ ኢት. ቁጥር መሆኑ ነው ። አኃዙም የተጻፈው በኢትዮጵያ ነው ።

1 ዘውዴ ገ ሥ በገጽ 177 ዛቻ ያዘለ ደብዳቤ የጻፈው ሙስጠፋ ሃዳል ሲሆን ፣ የተላከው ግን በዑስማን ዲግና ነው ይላል ።



ከአሥመራ ወደ ከረን ከዚያም ወደ ኩፊት ከዘለቁ በኋላ ፣ በነሐሴ ወር 1885 (እንደ ኢት. ቁጥር 1877) ጭፍሮቻቸው በብላታ ገብሩ መሪነት ጦርነት አድርገው ማሕዲስቶቹ አሸንፈው በዚሁ ጦርነት ስመ ጥሩው አርበኛ ብላታ ገብሩ አባ ጭቁንና ሌሎችም የጦር አለቆች ሞተዋል ። ደርቡሾቹ የተሻለ ስትራቴጂያዊ ቦታ ይዘው በመቆየታቸው ራስ አሉላ ቢዋጉም ራሳቸው እስከ መቁሰል ደረሱ ።

ከዚህ በኋላ ፣ ራስ አሉላ ባዲስ ኃይል ሠራዊታቸውን አከማችተው እንደገና ገጥመው ሲዋጉ ውለው በመጨረሻ ቀናቸው ። ከሁለቱም ወገን ቁጥሩ የበረከተ ወታደር ከሞተ በኋላ ፣ አዝማቹ ዑስማን ዲግና ስለሸሸ ድሉ[1] በማያጠራጥር ሁኔታ የኢትዮጵያውያን ሆኖ የአካባቢውን ወረዳ ከመያዛቸው በቀር በከሰላ ፣ በአመዲብ ፣ በሰንሂት የተከበቡትን ነጻ አውጥተው ባገራቸው ላይ ለንቅም ፣ ማናቸውንም እርዳታ እየሰጡ አሳልፈው በመሸኘትና በሰላም ወደ ምጥዋ በማድረስ ግዴታቸውን ፈጸሙ ።[2]

ዐፄ ዮሐንስ ፣ በቅንነት ለንግሥቲቱ የምስጋና ደብዳቤ ሲጽፉ ፣ ይኸን ግዴታ ሲፈጽሙና የምጥዋ በር ጉዳይ እንደ ተንጠለጠለ መቅረቱን በደብዳቤያቸው እንዳነሡ ይታወቃል ። ነገር ግን ፣ ውሉ ራሱ ጊዜያዊ ደስታ የሚሰጥ ቢሆንም ፣ በሙሉ ድብብቆሽ ያለበት ሰንካላ ውል ነበር ። በመዠመሪያው አንቀጽ ላይ የኢትዮጵያ ሸቀጥና የጦር መሣሪያ በነጻ ማለፉን ከመጥቀሱ በቀር ፣ የወደፊቱ የምጥዋ ወደብ ባለቤትነቱ ለማን እንደሚሆን አልተጠቀሰም ። አድሚራል ሔዊት ሁለቱን ጠበኞች ለማስማማት ሲላክ ፣ እንግሊዞች በቅርቡ የኢጣልያ ጦር ምጥዋን ገብቶ እንደሚይዝ በድብቅ ስለ ተስማሙ ፣ ባሁኑ ግብጾችን ካፄ ዮሐንስ ጋር በሚያስማማቸው ጊዜ የምጥዋ ጉዳይ እንዳይነሣ መመሪያ ተቀብሏል ። ስለዚህ አሁን በግብጽና ኢትዮጵያ በዚህ ዓመት ባደረጉት ውል ውስጥ ራሱ የምጥዋው ወደብና የአካባቢው የመንኩሎ ፣ የአርኪቆ (ደሆኖ) ወረዳ የወደፊት ዕድሉ አልተጠቀሰም ። እላይ እንዳልነው በቅርብ ጊዜ ግብጾች እንደሚለቁትና በነርሱም እግር ኢጣልያኖች መጥተው እንደሚይዙት የሎንዶንና የሮማ ባለሥልጣኖች በምስጢር የተስማሙበት ሲሆኑ ፣ ላፄ ዮሐንስ እንዲደበቅ

1 በጦርነቱ ወቅት ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት የዑስማን ዲግና ሠራዊት ነው ። ድል መሆኑ የታወቀው ዑስማን ስለሸሸ ሳይሆን ፣ በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሠራዊት ስለ ተደመሰሰ ነው ። ዘውዴ ገ/ሥ ገጽ 178

2 P.A. Colmedin, Tradition de Tsazega et Hazzega ,P.106. Lucca dei Sabelli, Storia d' Abyssinia' Vol. pp. 339-340.

ተደርጓል ። ምክንያቱም የዐፄ ዮሐንስ ምኞት ፣ “ግብጽ ሲለቀው ወደቡ ለኢትዮጵያ ይገባል” ስለሚሉ ፣ የሰሙ እንደሆነ ክርክር ያነሣሉ ። ይኸንንም ሲያነሡ የተከበቡትን ግብጾች ከደርቡሾቹ በውጊያ አድነው ባገራቸው ላይ አሳልፈው ወደ ምጥዋ ለመሸኘት እምቢ ይላሉ ። እነሱም ካልወጡ እንግሊዝ ሱዳንን ለመያዝ ይቸግረዋል በሚል አስተሳሰብ ነገሩ በምስጢር ስለተያዘ ፣ በዚህ ውል ውስጥ ሊጠቀስ አልተፈለገም ። ዐፄ ዮሐንስ ደግሞ ይኸን ወጥመድ ካለማወቃቸው የተነሣ ፣ “ለጊዜው ቦጎስን ካገኘሁ ፣ የጦር መሣሪያና ለቤተ መንግሥቴ የሚያስፈልገኝን ሸቀጥ በምጥዋ ወደብ በኩል በነጻ ካስመጣሁ ለጊዜው ይበቃኛል ፤ የቀረውን በእንግሊዝ መንግሥት ድጋፍ ወደፊት አገኛለሁ” የሚል ስሜት እንዳደረባቸው ይታወቃል ። ለኢትዮጵያም የምጥዋ ወደብ አስፈላጊነቱን የወደብ በር የሌለው መንግሥት ማናቸውም ነገር እንደማይቃናለት በደብዳቤያቸው ገልጠውስታል ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ፣ ነጻነቱን ጠብቆ እስከዚህ መድረሱ ሲያስደንቅ ፣ በረዥሙ የነጻነት ዘመን ባለመጠቀም በማናቸውም መስክ ከሥልጣኔ ወደኋላ የቀረ በመሆኑ ፣ በውሉ ላይ ሊጠቀሱ ሊሟሉ የሚገቡትን ሕጋዊ መንገዶች የሚመረምርና ላፄ ዮሐንስ አሳብ የሚያቀርብ የሕግ ምሁር የሆነ ኢትዮጵያዊ አልነበረም ። ራሳቸውም እንደ ቀደሙት የሥልጣን አባቶቻቸው የቀሩትም ካገራቸው ትምህርት በቀር የውጭውን አገር ትምህርትና ሕግ አያውቁትም ነበር ። ስለዚህም ወደቡን ተረክቦ ለማስተዳደር የሚችል የተማረ ሰውም ድርጅትም ካለመኖሩም በቀር ፣ እንግሊዞች ወደቡን ፣ የራሳቸው ደጋፊ ለሚሆን ከኢትዮጵያ የተሻለ ጥንካሬ ላለው ለኢጣሊያ ለመስጠት በመፈለጋቸው ፣ ወደቡን ኢትዮጵያ የመረከቧ ጉዳይ ተቀባይነት አላገኘም ።

ዐፄ ዮሐንስ ፣ በቅን ልቦና በንጹሕ ሕሊና በእንግሊዞች ወዳጅነት ይተማመኑ ስለነበረ ፣ ከእንግሊዞች በኩል የሚሰነዘረውን ማናቸውንም አሳብ ከዘመድና ከወዳጅ ዘንድ እንደመጣ ሲቆጥሩት ፣ የእንግሊዝ መንግሥት ግን በቅርብ ቀን ወደቡን ጣልያኖች እንደሚረከቡት ራሱ እያወቀ ፣ “ያፄ ዮሐንስ ሸቀጥ በምጥዋ ወደብ በነጻ ይወጣል” ብሎ በመዠመሪያው አንቀጽ ያሠፈረው ለማታለል ያህል እንደ ተደረገ የሚቆጠር ነው ። የተማረ ወኪል በሎንዶንም ፣ በሌሎቹም ከተሞች ባለማስቀመጣቸው የአውሮፓን ሁኔታ ፣ የእንግሊዝንና የኢጣልያንንም ውስጠ ሽርክና ተከታትሎ የሚያሰማቸው አልነበረም ። በተለይ ደግሞ በዚህ ዘመን በአውሮፓውያን መካከል በበርሊንና በብሩክሴል ለአፍሪካውያን የጦር መሣሪያ እንዳይደርስ በውል የተወሰነ መሆኑን የእንግሊዝ መንግሥት ስለሚያውቀው ፣ ዐፄ ዮሐንስ ከግብጾች ጋር የተዋዋሉትን ውል ጣልያኖች እንዲያከብሩላቸው አላደረገም ። የኢጣልያኖችም ዓላማ ምጥዋን ለመተላለፊያ እንጂ ፣ ወደፊት መላ ኢትዮጵያን በጠቅላላው ለመውረር ስለሆነ ፣ ይኸን የመሰለውን ውል ተቀብለው በምንም ዐይነት የጦር መሣሪያ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እጅ እንደ ልብ እንዲገባ የማይፈቅዱ መሆናቸውን የእንግሊዝ መንግሥት በቅድሚያ ያውቀው ነበር ። ራሱም እንደዚህ ያለውን ጥቁሮቹን በመሣሪያ የማስታጠቁን ጉዳይ አይቀበለውም ። ስለዚህ ይኸን ሁሉ እያወቀ የእንግሊዝ መንግሥት በየዋሁ ባፄ ዮሐንስ ላይ ትልቅ ደባ ሲውልባቸው በርሳቸው ደብዳቤ ተደጋግሞ ለተገለጸው ዝምድና ምንም ዋጋ አልሰጠውም ነበር ።

ንጉሠ ነገሥቱ ግን ፣ በሐቀኛው መንገድ በሬር አድሚራል ሔዊት አማካይነት በተዋዋሉት ውል የሦስተኛውን አንቀጽ መሠረት በመከተል ፣ ከማህዲ ሞት በኋላ የተከታዩ የከሊፋ አብድላሂ ወታደሮች ከበው ያስጨነቁዋቸውን የግብጽ ወታደሮች ፣ ቀላይ እንዳልነው በራስ አሉላ የሚመራ ጦራቸውን ልከው ፣ ከደርቡሾች ጋር አዋግተውና አስጥለው በትግራይና በምድረ ባሕሪ አሳልፈው ምጥዋ ከወገኖቻቸው ጋር በሰላም እንዲደባለቁ አደረጉ ። በእንግሊዝ አለኝታና ተስፋ ለኢትዮጵያ ጥቅም ሲሉ ይኸን ሲያደርጉ በሌላ ወገን ግን በደርቡሾቹ በኩል በራሳቸው ላይ ቁጭትንና ቂምን አትርፈዋል ።

ባለፈው እንዳነበብነው ፣ ዐፄ ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ ዠምሮ ኢትዮጵያ ከካቶሊክም ፣ ከእስላምም ነጻ ሆና በፍጹም የክርስቲያን አገር ብቻ እንድትሆን ምኞታቸው ስለነበረ ፣ በትግሬና በትግራይ ፣ በወሎ ፣ በዋጅራት ፣ በራያና በአዘቦ በሌላውም አውራጃ ያለው እስላም ሁሉ ፣ (በ1870—1875 ዓ. ም.) ክርስቲያን እንዲሆን ዐውጀው እስላሙ ሁሉ እየተያዘና እየተሰበሰበ ተጠመቀ ፣ ቁረብ በተባለ ጊዜ የፈራውና ከንብረቱ መነቃነቅ የጠላው በግዱ እየቆረበ ያለልቡ ክርስቲያን ሲሆን ፣ የቀረው ግን እየተሰደደ ሱዳን ገብቶ ከማህዲስቶች ጋር በመተባበር በዚህ ጊዜ ባፄ ዮሐንስና በኢትዮጵያ ላይ ዘመቻ እንዲዘመትባቸውና ማታ ይወተውቱ ዠመር ። ሱዳኖቹ (ደርቡሾች) ግን አቅማቸውን በመገመትና ባንድ ጊዜም ከእንግሊዞች ፣ ከግብጾችና ከኢትዮጵያም ጋር መጣላቱን ስለ ሡጉበት ፣ ለጊዜው የኢትዮጵያን ጦርነት ታግሠው ቆይተው ነበር ። አሁን ግን ፣ ዐፄ ዮሐንስ ጦራቸውን ልከው ከሱዳኖቹ ጋር ተዋግተው ግብጾቹን ስለረዱ በቂም ላይ ቂም አደረባቸው ።

ይህ ውለታ ለግብጾች ደህንነትን ፣ ይኸውም ማለት ከደርቡሾች የሞት አደጋ መዳንን ሲሰጣቸው ፣ በዚያው አንጻር ለጐንደር ወረራና


ዘረፋ ፡ ለጕጃሙ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መሸነፍና ለብዙ ቤተሰብ ጥፋት ፡ ለራሳቸው ለንጉሠ ነገሥቱ በመተማ ላይ በደርቡሾቹ እጅ ሕይወታቸው ለማለፍ ምክንያት ሆነ ። በዚሁ ጐን ደግሞ ያፄ ዮሐንስ መሞት ባንድ ወገን በግብጾች እግር ለመጡት ኢጣልያኖች ምጥዋን ከያዙ በኋላ ፡ ወደ አሥመራና ወደ ከረን ለመስፋፋት ጠቀማቸው ። እንግሊዝ ግብጾችን በዚህ ውለታ አድኖ ካወጣ ወዲህ ከግብጽ ጋር በመዛመድ ፡ የኢጣልያንን ተባባሪነት በማግኘት በራሱ በግብጽ ላይ ተቆጣጣሪነቱን ለመዘርጋትና በሱዳንም ከግብጽ ጋር ተስማምቶ በጋርዮሽ አብሮ ግዛቱን ለማስፋፋት ጠቀመው ። ከመዠመሪያውም በፕላን የተከተለው ዓላማ ይኸው ነበር ።






በማህዲስቶችና በግብጾች መካከል ውጊያ

(ከሩዶልፍና ከዊንጌት መጽሐፍ)



ዐፄ ዮሐንስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት

(ፐብሊክ ሬኮርድ ኦፊስ ፥ ሎንደን)

# ምዕራፍ ሐያ አምስት

## የግብጽ ወደ ሐረር መግባትና መውጣት—

## የሐረርጌ ከኢትዮጵያ ጋር መዋሐድ

ሐረርጌ በአክሱሞችና በዛጉዬዎች ዘመነ መንግሥት ሁኔታው ከምን ላይ እንደ ነበረ በትክክል አይታወቅም ። ከኢትዮጵያ የተለየ በዚህ አካባቢ ራሱን የቻለ መንግሥት ስለ አልነበረ ፡ ጉልበት ያለው ባላባት ብቻ አንዱ ሌላውን እያስገበረ ወይም ከአክሱም ወይም ከዛጉዬ (ላስታ) በሸዋ ላይ የተሾመ ጉልበተኛ ብቅ ባለ ጊዜ ፡ ባላባቶቹ ለርሱ እየገበሩ ኖረው ይሆናል ። ከቱርክና ከግብጽ በፊት የዐረብ አገር የሃይማኖት መሪዎች እንጂ ፡ ከማዶ ከዐረብ አገር ዘማች ወታደር ጦር ይዞ መጥቶ ይኸን ታላቅ አውራጃ አስገብሮ በሥልጣኑ ውስጥ ያደረገ አልነበረም ። በአክሱሞችና በዛጉዬዎች ዘመነ መንግሥት እንደ ዛሬ የሐረርጌ ግዛት የሚታወቅ አይመስልም ።

የላስታ መንግሥት በ13ኛው መቶ ዓመት ሸዋ ወደሚቀመጠው ወደ ዐፄ ይኩኖ አምላክ እጅ ሲዛወር ፡ ከዐረብ አገር መጥቶ በይፋት የተቀመጠው ዑመር ወላስማ ባፄ ይኩኖ አምላክ ተሹሞ ይፋትን ሲገዛ ሞተ ። የርሱ ተከታዮች ሐቅ አድዲን (ሐቀዲን) ናስር አድ ዲን (ነስረ ዲን) ጋማል አድ ዲን (ገመልዲን) ሳብር አድ ዲን (ሰብረዲን) በድላይ ሺሃብ አድ ዲን (አርዊ በድላይ). . .* ለይኩኖ አምላክ ተከታዮች ለነዐፄ ዐምደ ጽዮን ፡ ለነዐፄ ዳዊት ፡ ለነዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሲመቻቸው እየሸፈቱ ፡ ሳይመቻቸው እየገበሩ ብዙ ዘመን አሳልፈዋል ። [1]

ከነዚሁ ከዑመር ወላስማ ተከታዮች በሚወለደው በአቡበከር ጊዜ ወላስሞች ከይፋት ወደ አውሳ ተዛውረው ጥቂት ጊዜ እንደቆዩ በ1512 ዓ.ም. አካባቢ ከአውሳ ወደ ሐረር ተዛውረው ደንበኛ መቀመጫቸው አደረጉት ። በዚሁ ጊዜ ከቀይ ባሕር ማዶ ያሉት ዐረቦች እየበረቱ በሔዱ መጠን ፡ ወደ አውሳና ወደ ሐረር እየሠረጉ በመግባት

---

* በቅንፉ ውስጥ ያለው የግዕዝኛው ታሪክ ነገሥት አጠራር ነው ።

[1] ጌርል ፒሩሾ ያሳተመው ያፄ ዓምደ ጽዮን የጦርነት ታሪክ ፡ በየምዕራፉ ፤ የኢ.ት. ታሪክ ካፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል ተ.ጸ.መ. ፡ ገጽ 59 ፡ 122 ።

የሐረርጌና የአካባቢውን የእስላም ተወላጅ አጠናከሩ ። በዚህ ጐን የሃይማኖት መሪዎች (ሸኮች) ያልተማረውንና ያላመነውን በጋብቻም በንግድም እየተጠጉና እያስተማሩ ፤ ወደ እስልምና በማግባት በቀን ብዛት የእስላሙን ቁጥር እያበረከቱት ሔዱ ።

ይህ በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ በ(1519—1533) ግራኝ ከውጭም ከውስጥም የነዚህን ድጋፍ በማግኘት የክርስቲያኑን መንግሥት በምን አኳኋን እንደ ወረረ 14 ዓመታት ያህል በክርስቲያኑ ሕዝብና በታሪካዊ ቅርሱ ላይ ብዙ ጉዳት ካደረሰ በኋላ ፤ በክርስቲያኖቹ ፖርቱጋሎች እርዳታ የግራኝ የወረራ አገዛዝ እንደ ወደቀ በየታሪኩ ተጽፏል ። [1]

ምንም የግራኝ የጭካኔ አገዛዝ ቢወድቅ እነ ዐፄ ገላውዴዎስ (1533—1551 ዓ ም.) ፤ እነ ዐፄ ሠርፀ ድንግል (1555—1589 ዓ.ም.) ሐረርን ወደ ኢትዮጵያ እንደገና ለመመለስ ቢጣጣሩ አልሆነላቸውም ። በተለይ በሚቀጥለው ጊዜ ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ዋና መዲና (ከተማ) ከሸዋ ተጠቅሎ ሔዶ በጐንደር ስለ ተመሠረተ ያገሩ ርቀት ፤ ወደ መጨረሻ ዘመን (17—18ኛው መቶ ዓመት) የጐንደር ነገሥታት ሥልጣን መዳከም ፤ የነ ዑመር ወላስማን ተከታዮች ሥልጣን የገፋፉት መሳፍንት ራሳቸው አቅም ስላጡና የርስ በርሱም ጦርነት ፋታ አልሰጥ ስላለ ፤ ሐረርንና አካባቢውን እንደሌላው የኢትዮጵያ ደቡባዊ አውራጃ ሁሉ ፤ ከኢትዮጵያ ተለይቶ የአቡበከርና የግራኝ አህመድ ተከታዮች "ሡልጣን" ወይም "አሚር" እየተባሉ በነጻነት ሲያስተዳድሩት እስከ 19ነኛው መቶ ዓ ም. ደረሱ ። [2]

በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳሉ ባለፈው እንዳነበብነው ፤ የግብጹ ከዲቭ ኢስማኤል የግብጽን ግዛት ከሜዴትራኒ ባሕር እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ወይም እስከ ዛንዚባር አደርሰዋለሁ ብሎ በተነሣበት ሰዓት በቱርክ ሡልጣን ፈቃድ የምጥዋንና የሱአኪምን ወደብ ሲይዝ በዚሁ ዐይነት አሁንም በቱርኮች ፈቃድ በ1869—70 ዓ. ም. የዘይላን ወደብ ያዘ ። በቀጥታ በቱርኮች ይታዘዝ የነበረው ባላባቱ አቡበከርም ከግብጾቹ ጋር ተስማምቶ የነርሱን የበላይ ገዥነት ተቀበለ ። ቀጥሎ በ1875 ዓ.ም. ራውፍ ፓሻ የዘይላና የአካባቢው ገዥ (የዘይላ ማአሙር) የሚል የማዕረግ ስም ጨምሮ በሐምሌ 16 ቀን ዘይላ ገባ ።

---

1 ተ.ጸ.መ. ፤ የግራኝ አህመድ ወረራ ፤ ገጽ 109—131 ።
2 E.Cerulli L, Islam d' Ieri di Oggi , pp. 157--321



ወደ ዘይላ ሲመጣ በምስጢር ከከዲቭ ኢስማኤል የተሰጠው መመሪያ ፤ "በዘይላና በአካባቢው ፤ በሐረርም የሚገኙትን ዐረቦችና ሕዝቦች በደህና እያያዝ ልባቸውን በመሳብ ከዘይላ ወደ ሐረር የሚወስደው መንገድ ለነጋዴም ፤ ለተመላላሽም እንዲያመች ጸጥታውን ማስጠበቅ ያስፈልጋል" የሚል ሲሆን ፤ ዋናው አሳብ ሐረርን ጭምር በቀጥታ ለመያዝ ስለነበረ ፤ "እንደዚህ ያለውን አሳብ እንግሊዞችም ሆኑ ማንም ሌላ ሰው እንዳያውቅ በምስጢር ተጠንቀቁ ። አገሩን ለመያዝ ወደ ሐረር ስትጓዙም 'ምነው' የሚል ጥያቄ ለሚያቀርቡላችሁ ያገርና የወንዛወንዝ ካርታ ለማዘጋጀት ነው በሉ ። ሐረርንም ከያዛችሁ በኋላ እንግሊዞች ለምን ያዛችሁ የሚል ጥያቄ ቢያቀርቡላችሁ የሐረሩ ኢሚር እያጉላላ ስላስቸገረን ፤ እናንተ ጠብቁን ብለው ነዋሪዎቹ ራሳቸው ስለ ለመኑን ነው ብላችሁ መልስ ስጡ" የሚል ነበር ።

በዚህ ጊዜ ከ1855 ዓ.ም. ዠምሮ ሐረርንና አካባቢውን ይገዛ የነበረው ሼክ ሙሐመድ ኢብን ዐሊ ኢብን አብድል ኤል ሻኩር ይባል ነበር ። እርሱም ለመዠመሪያ ጊዜ ራውፍ ፓሻ ከዘይላ መጥቶ ሐረርጌ ግዛት በገባ ጊዜ ተዋግቶ ነበር ። ዳሩ ግን ፤ የግብጾቹ ትጥቅ ዘመናዊ ስለነበረ መመከት ባለመቻሉ ልጁን ሐጂ የሱፍን በቅድሚያ ልኮ ለግብጽ ከዲቭ ገባርነቱን መግለጥ ግዴታ ሆነበት ። ነገር ግን ፤ የግብጽ ጦር ወደ ሐረር ከተማ ለመግባት ሲጓዝ በዙሪያው ያሉት ኦሮሞዎች የአላ ፤ የጀርሲ ፤ የባቢሌ ፤ የአቡራ. . . ነገዶች ተሰብስበውና ጠንክረው በእግርም ፤ በፈረስም እየጋለቡ በጦርና በቀስት ሰባት ሰዓት ያህል ከግብጾቹ ጋር ተዋግተው በመጨረሻ ሲሸነፉ ፤ እነሱም እንዳገር ልማድ ሴቶቻቸውን ልከው መገበራቸውን አስታወቁ ። ቀጥለውም መሪዎቹ በየተራ እየመጡ ለራውፍ ፓሻ እጃቸውን ሲሰጡ የግብጽ ባንዲራ ኢሚሩ ቤት ላይ በገሃድ ተሰቅሎ ሐረር በግብጽ አገዛዝ ሥር መሆኑ ታወጀ ። [1]

ከዚህ በኋላ ፤ ከከዲቭ ኢስማኤል ለራውፍ ባሻ በተሰጠው መመሪያ ላይ እንደ ተገለጸው የግብጽ መንግሥት ሐረርን ለመያዝ ሲያቅድ ፤ የእንግሊዝ መንግሥት ብቻ ሰምቶ እንዳይቆጣው ከማሰብ በቀር ስለ ኢትዮጵያ መንግሥት ምንም ዐይነት ሥጋት አላደረበትም ። የፈረንሳይንና የኢጣልያን መንግሥታት ከምንም አልቆጠራቸውም ። ይሁን እንጂ ፤ ፍሬያማ በሆነው አየሩ ለሰውነት ተስማሚ በሆነው ስፌ የሐረር ግዛት ላይ ፈረንሳይም ኢጣልያም የምኞታቸውን ዐይን ሳይወረውሩ አልቀረም ።

---

1 G. Douin, L, Histoire du Regne du Kedive Ismael, pp. 583-627.

ሙሴ ዱወ የሚባለው ጸሐፊ ግብጾች በገቡበት ሰዓት የሐረር ከተማ ዙሪያውን አምስት በሮች ባሉት የግምብ አጥር የተከበበ መሆኑንና የግምቡ ቁመት በአንድ በኩል ከ3 እስከ 4 ሜትር መድረሱን ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እስከ አንድ ሜትር ተኩል ማጠሩን ፤ ከተማዋ የተቆረቀረችው በቋጥኛማ ሥፍራ መሆኑንና የከተማዋ ስፋት 481 812 ሜትር ካሬ ሲሆን ፣ በውስጧ እንደ አባይ የመሰለ ውሀ ያለባቸው 9 ጉድጓዶች መኖራቸውን ፣ በከተማው ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ ቁጥር 35 000 ሆኖ ቤተሰቡም የሚኖረው አንድ ፎቅ ብቻ ባለው ፣ ጣራው አሸዋ በተከደነና መስኮት በሌለው ቤት ውስጥ መሆኑን ፤ የቤቱም ሥራ ከግብጾች ቤት ሥራ ጋር ተመሳሳይ መሆኑንና በጠቅላላው በከተማው 9560 የደንጊያ ቤቶች ፣ 346 የሣር ክዳን ጐጆዎች መኖራቸውን ያመለክታል ።[1]

ከዚህም ጋር ትክለኛው የሐረሩ ባላባት ኤሚር መሐመድ ኢብን ዐሊ የሐሰት ገንዘብ (ሞሀለቅ — መሐለቅ) በማውጣትና በማታለል ንግዱን ሁሉ የግል አድርጎ ሀብት በመሰብሰብ ፣ ሕዝቡን ፣ በማጉላላት የተጠላ ስለነበረ ፣ አሁን ግብጾቹ ገብተው አዲስ የተሻለ አስተዳደር በማሳየታቸው መደሰታቸውን ይኸው ጸሐፊ ያወሳል ።[2]

በዚህ ዐይነት ፣ ግብጾች በሐረርም ፣ በዘይላም በሌላውም የኢትዮጵያ ዙሪያ ግዛታቸውን ማስፋፋት እንደ ዠመሩና በሐረርም ዐሥር ዓመት ያህል እንደቆዩ ፣ ባለፈው እንዳነበብነው በሱዳን የማህዲስቶች አጥቂነትና በኩፊት የኢትዮጵያውያን አሸናፊነት የተነሣ ከፍ ያለ የኢኮኖሚ ውድቀት ስለ ገጠማቸው ፣ በደስታ የተስፋፉትን ያህል በሐዘንና በጸጸት ከያዙበት አገር እየለቀቁ መውጣት ግዴታ ሆነባቸው ። ሐረርንም መልቀቅ ስለ ተገደዱ ፣ ከራውፍ ፓሻ ወዲህ በመጨረሻ የሐረር ገዥ ተብሎ ተሾሞ ለመጣው ለዐሊ. ሪዳፓሽ በ1878 ዓ. ም. ግንቦት 20 ቀን ፣ ያገሩን ተወላጅ ባላባት አሚር አብዱላሂ የሚባለውን የመሐመድን ልጅ ለሐረር ገዥነት ሾሞ እርሱ ጦሩን ጠቅሎ እንዲወጣ ትእዛዝ ከካይሮ ደረሰው ። አሚር አብዱላሂ ከላይ ዘሩ የመጣው ዐሊ ኢብን ዳውድ ከሚባለው በ1639—40 ላይ ሐረርጌን ከሚያስተዳድረው ነው ። ኤሚር ዐሊ ኢብን ዳውድ የማዕረግ ስሙ "ኤሚር" እንደሚያመለክተው ምናልባት ዘሩ ሐረርን ካስገነባው ከኤሚር ኑር ቤን ሙጃሂድ የወረደ ይሆናል ። ከወላስሞች ቢወለድ ኖሮ አሚር በመባል ፈንታ ሡልጣን ይባል ነበር ።

1 G. Douin, Histoire du Regne du Kediye Ismael, III Tome 3e Parties, p.615.
2 Ibid.



የሆነ ሆኖ ፣ ግብጾች ሐረርን ሲለቁ በዘይላም ፣ በበርበራም ሊቆዩ አልቻሉም ። ስለዚህም በነዚህም ወደቦች እንግሊዞች ተተኩ ። በታጁራና በጅቡቲም ፈረንሳዮች ለመግባት አልመዋል ። በአሰብ ወደብም ኢጣልያኖች ገና ቀደም ብሎ 1869—70 ተመሥርተዋል ። በዚህ ምክንያት ፣ እንግሊዞች ሐረርን ከዘይላና ፈረንሳዮች ወደፊት ሊይዙ ካሰቡት ከጅቡቲ ጋር ለመደባለቅ ሲመኙ ፣ በበኩሉ የኢጣልያ መንግሥት በተለይ ምጥዋ ከገባ በኋላ በሐረር ላይ ዐይኑን ጥሎ ነበር ። የአገር ተወላጆቹን እነ አንቶኒዎ ቸኪን ፣ እነ ኮንቲ ፓሮን እየላከ መንገዱን ፣ ወንዛ ወንዙንና ተራራውን ሲያስመረምር የመጨረሻው መልእክተኛ ኮንቲ ፓሮ በዚሁ ዓመት (1870 ዓ.ም.) ገረስሌ አጠገብ ሐርቲ ከሚባለው ቦታ ሲደርስ ፣ ሰላይነቱ የገባቸው የአሚር አብዱላሂ ሰዎች ከነሰዉ ፈጁት ። ይኸም ለኢጣልያ "ዜጋዎቼ ከተገደሉ የነርሱን ደም ተበቅዬ ወዲያውም ሐረርን እይዛለሁ" በማለት ፕላንና ጊዜ ሲያማርጥ በሸዋው ንጉሥ በምኒልክ ተቀደመ ።

ንጉሥ ምኒልክ በ1870 ዓ.ም. በዕርቅ ላጼ ዮሐንስ ገብተው ከተሰማሙ በኋላ ፣ በጽሞና ወደ ደቡብ የኢትዮጵያ አውራጃ እየተስፋፉ ከዕለት ወደዕለት ኃይላቸውን ከማጠንከር ላይ ነበሩ ። በተለይ ልጃቸውን ወይዘሮ ዘውዲቱን የንጉሠ ነገሥቱ ልጅ ራስ አርአያ ካገቡ ወዲህ በሁለቱ መካከል ያለው መግባባት በኋላ መልሶ እስኪደፈርስ ድረስ እየሠመረ ሔዷል ።

ስለዚህ ምኒልክ ቀደም ብሎ እነ ራስ ዳርጌን ፣ እነ ደጃች ወልደ ገብርኤል አባ ሰይጣንንና እነ ደጃች አስፋው ዳርጌን ወደ ደቡብ እየላኩ የአሩሲን ፣ የጨርጨርን ፣ የኢቱን ፣ የባሌን አገር ጠቅልለው በሐረርም አካባቢ ይዞታቸውን አጠንክረው ነበረ ። ሐረርጌም ከጥንት ፣ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር መሆኑን በመገንዘብ ይኸንኑ ፍሬያማ አገርና የደመቀ ከተማ ለመያዝ ዝግጅት በማድረግ ላይ ነበሩ ። በዚሁ ጊዜ ምንም ላፄ ዮሐንስ በያመቱ ቢገብሩም ፣ በውጭ ጉዳይ ራሳቸውን እንደ ነጻ የመንግሥት መሪ በመቁጠር ከእንግሊዝም ፣ ከፈረንሳይም ፣ ከኢጣልያም ነገሥታትና መሪዎች ጋር በቀጥታ የወዳጅነት ደብዳቤ ይጻጻፉ ነበር ። ከሦስቱም የበለጠ ከኢጣልያ ንጉሥ ከኡምቤርቶ ጋር ቀድሞ በአባ ማስያስና በአንቲኖሪ በኩል የዠመሩትን አሁን በኮንት አንቶሊ አማካይነት በደብዳቤና ገጸ በረከት እየተለዋወጡ ወዳጅነታቸውን የበለጠ አጥብቀዋል ።

ቢሆንም በሐረር ላይ ብዙ መንግሥታትና ራሱም የኢጣልያ መንግሥት ጭምር ዐይናቸውን እንደ ጣሉበት ንጉሥ ምኒልክ ያውቁ ስለነበር ፣ በርሳቸው ወደ ሐረር መዝመት የተነሣ በአውሮፓ አገሮች ፣

በተለይም በኢጣልያ መንግሥት ዘንድ ከፍ ያለ ግጭት እንዳይፈጠር በመጠንቀቅ ፣ በተለመደ የፖለቲካ ዘዴያቸው የዘመቻውን መንገድ ለማቃናት ማሰባቸውን ከዚህ ቀጥሎ ያለው ለኢጣልያ ንጉሥ የጻፉት ረዘም ያለ ደብዳቤ ያሳያል ።

"የተላከ ከንጉሥ ምኒልክ ፣ ይድረስ ከከበረ ከታፈረ የኢጣልያ ንጉሥ ኡምቤር (ኡምቤርቶ). . . ንጉሥ ሆይ. . . አሁን እምነግርዎ ነገር እጅግ የከበደ የበረታ ነገር ነው ። በዚህ ደብዳቤ ቃል ፍቅሬንና ማክበሬን እንዲያውቁልኝ ተስፋ አለኝ ። ይህ ደብዳቤ ሲደርስ ሐረርጌንና የሐረርጌን አውራጃ አገር ሁሉ መያዜ ጥርጣሬ የለውምና ይወቁት ብዬ ነው ። ይህም አገር በአያቴና በቅድመ አያቴ ዠምሮ የሸዋ ግዛት ነበር ። * በዚህ ነገር የተነሣ የአውሮፓ ሰዎች የሚሉትን አላውቅም ። ይከፋ አይመስለኝም ። አሁን ንጉሥ የሚገባኝን ገንዘቤን አገሬን ነውና የወሰድሁት ስለኔ ሆነው ለዚህ ነገር የሚነሣውን ሁሉ ይመልከቱልኝ ብዬ እለምንዎታለሁ ።

"ዳግመኛም ይህን አገር የያዝሁበት ምክንያት ባጭሩ አስረዳዎታለሁ ። ሐረርጌ ቀድሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ሳለ የአገሬ ጭማሪ ነበር ። የእስላሞች ጦርነት የተነሣ ጊዜ ከሁሉ ይልቅ የግራኝ ጦርነት ኢትዮጵያን ያጠፋ ጌታ በተወለደ በ1600 ዘመን ብዙ አገር ሔደብን ። ከሔደብን አገር ሁሉ ቁጥር አንዱ ሐረርጌ ነው ። እግዚአብሔር ግን ፣ ክርስቲያንን አይጥልምና እኛ በጉልበታችንም ሆነ እውነትንም ይዘን ሆነ እስላሞች ያጠፉብንን አገር ሁሉ እየተዋጋን እንደገና እያቀናን መለስነው ።

"የእስጣንቡል መንግሥትና የምስር መንግሥት ያባቶቻችን መንግሥት ጥፋት አገዛቸውና በባሕር ዳር የነበረውን አገራችንን ሁሉ ሐረርጌን ጨምረው ይዘውብን ነበር ። ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ በእግዚአብሔር ኃይል ቱርኮችን ድል አድርገው ኢትዮጵያን አተረፏት. . . እኛ ግን ዕርቅን ሰላምን እንወዳለን ። ዳግመኛ ጦርነቱን ብንጠላው ቱርኮች ሐረርጌ ላይ ቢቀመጡ ዝም ብለናቸው ነበር ። አሁን

* በአያቴና በቅድመ አያቴ ሲሉ በነዘርዓ ያዕቆብ ፣ በነልብነ ድንግል ማለታቸው እንጂ ፣ በወሰን ሰገድና በሣህለ ሥላሴ ጊዜ ማለታቸው እንደማይሆን ዕውቅ ነው ።



ግን ነገሩ ተለዋወጠ ። ሐረርጌ ላይ ያሉት ወዳጆቼ ከ6 ወር ዠምረው አገሩ በኦሮሞዎች እጅ ሆነ ከዚያ ያለ ሰው ሁሉ ፈርቷል እያሉ ዕለት ዕለት ይጽፉልኛል ። አሁን እንኳን በመጨረሻ የመጣው ደብዳቤ ቱርኮች ጨርሰው ለቀቁት የሚል ነው. . . ያያቶቼን መንግሥት የእስላም ሽፍታ ወጥቶ እንዳጠፋው ዳግመኛ የእስላም ሽፍታ ወጥቶ በኔ መንግሥት ይጫወትበት ብዬ ዝም ብዬ አላይም. . . ሐረርጌ ስንገባ ሰውን ሁሉ በሃይማኖቱ እናኖራለን። ሀብታሙንም ደሀውንም እኩል እንገዛለን ፣ እንጠብቃለን ፣ ንግድም እንዲቀና በጣም እንጥራለን. . . ይህ መልካሙ ሐሳባችን በንጉሥ ፊት የተወደደ እንዲሆንልን ተስፋ አለን ። ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር ንጉሥንም ፣ ሕዝብዎንም መንግሥትዎንም እንዲጠብቅ እለምናለሁ ። [1] ደብዳቤው የተጻፈው በግንቦት መሆኑን ሲያመለክት ዓመተ ምሕረቱ እንደሌላዎቹ አልተጻፈበትም ። ነገር ግን ዓመተ ምሕረቱ እንደ ኢት. ቁ. 1877 ዓ. ም. መሆን አለበት ። [2]

በዚሁ ዓመት በግንቦት ወር 1877 ዓ.ም. ንጉሥ ምኒልክ ይኸን ደብዳቤ ጽፈው በስምንተኛ ወር በታኅሣሥ 1878 ዓ.ም. ወደ ሐረርጌ ዘመቱ ። በዚህ ጊዜ አሚር አብዱላሂ ከግብጾች ተሾሞ በሐረር ግዛት የቆየው ሰባት ወር ብቻ ነው ። ስለ ሐረር ዘመቻ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በመጠኑ ዘርዘር አድርገው እንደዚህ ሲሉ አሥፍረውታል ። ". . . ዐፄ ምኒልክ የራስ ዳርጌና የደጃች ወልደ ገብርኤል ከዲና (ያሩሲ ተዋጊ ባላገር) ጋራ ተሰላልፈው መክረማቸው አሳዝኖዎ (አሳዝኗቸው) * በ1879 ዓ. ም. በኅዳር 4 ቀን ወደ አሩሲ ለመሔድ ተነሡ. . . በታኅሣሥ 10 ቀን ገለምሶ ከገለምሶ ተነሥተው ወደ ሐረርጌ ተጓዙ ። በ18 ቀን (ታኅሣሥ 1879) ሒርና ሰፈሩ ። በ21 በወበራ መገናኛ ቡርቃ ወንዝ ሰፍረው. . . በ24 ቀን ገበያ ወንዝ ላይ ሠፈሩ ።

"በዚያ ቀን አሚር አብዱላሂ ምሽግ መሽጎ ጨለንቆ ላይ ተሠልፎ ይጠብቅ ነበር ። ነገር ግን ፣ በነጋው (በማግሥቱ) ለቆት ሔዶ ባዶውን ተገኘ ። በ25 ቀን ሜታና ወበራ መገናኛ ጨለንቆ ላይ

1 I. Guidi, I Framenti Relativi alla Storia di Abisinia በሚል ርዕስ ካሳተመው ውስጥ ። ተ.ጸ.መ. የግራኝ አህመድ ወረራ ፣ ገጽ 155 ። Marcus, Life and Times of Menelik

2 በገጽ 90 ምኒልክ ደብዳቤውን የጻፉት እ.ኤ.አ. ጁን 4/1885 ነው ይላል ። ይህም ግንቦት ወር 1877 ዓ.ም. መሆን አለበት ። ልዩነቱ የ8 ዓመታት ነውና ።

* በርሳቸው አነጋገር አሳዝኖዎ ይላል ። ባባቶቻችን አጻጻፍ ስለ ንጉሥ ሲጻፍ አሳዝኗቸው አይባልም ።

ሠፈሩ ። በ26 ቀን በዓለ ልደት (ገና) ቀርቦ ነበርና ሰርድ ከብት
ለማምጣት ወራሪ (ዘራፊ) * ሔዶ ብዙ ላም ተያዘ ። የሐረሩም ገዥ
የአሚር አብዱላሂ ሠፈር ወራቢሊ ላይ ታየ ። ከዚያ ለዕርቅ አስበው
'ግባ እኔ ላንተ ነው እንጂ የመጣሁት አገር ለማጥፋት አልመጣሁም።
ተገባህ ተተገዛህ አገር አልነሣህም ኋላ ይጠጥትሃል' ብለው ላኩ
በት ። እርሱ ግን ፥ ይህን ቢልኩበት የፈሩት መስሎት መልክተኞችን
አሰራቸው" በማለት ከዘረዘሩ በኋላ ፥ ጸሐፌ ትእዛዙ ስለ ውጊያው
እንደዚህ ብለዋል "...አሚር አብዱላሂ 'ዛሬ (ታኅሣሥ 29 ቀን)
በዓለ ልደት ነውና ክርስቲያኖች አይሰለፉም(አይዋጉም)' ብሎ መክ ር
ጦሩን ጠቅልሎ ሰኔድሩን (ባለጠበንጃውን ) ከፊት ፥ መድፎቹን ከመካ
ከል ፥ ቀስተኛውን ከኋላ ፥ ከዚያ ቀጥሎ ፈረሰኛውን ጋሸኛውን * *
አሰልፎ በአምስት ሰዓት ወደ ሠፈር መጣ...ንጉሡ መነጥራቸውን
ከዙፋናቸው ፊት አቁመው ሲመለከቱት ከሠፈር ማዶ ያለውን ቁል
ቁለት ወርዶ ከደኑ * * * (አፍሱላቱን) * * * * ሰግዶ ለጀሀድ
(ለቅዱስ ጦርነት)ሲመጣ አዩት ።

"በዚህ ጊዜ በቁጣ... ሠራዊታቸውን 'ሔደህ በለው' ብለው
አሰልፈው ሰደዱት ። ንጉሡም የቤት አሽከሮቻቸውን ፥ ዘበኞቻቸውን
...ይዘው ተከተሉ ። አሚር አብዱላሂም መድፎቹን ማስተኮስ ዠመረ ።
በዚህ ጊዜ ከመኳንንትም ፥ ከቤት አሽከሮችም ፥ ከሠራዊትም አጫሪው
ፈረሰኛ ሔዶ ገጠመው ። በዚያ ጊዜ ጽኑ ውጊያ ሆነ ። የንጉሡ ሠራ
ዊት መድፎቹን እጅ አድርጎ (ማርኮ) አዞረበት ። የግንባሩም (ግን
ባር ቀደም ተዋጊ) ሲዘልቅና ሲገጥመው አሚር አብዱላሂ ድል ሆነ ።
ነፍጡንም (ጠበንጃውንም) መድፉንም ፥ ሠራዊቱንም ሥላሴ ለቀቡት
ንጉሥ (ለምኒልክ) አበርክቶ ባንድያ ፈረሱ (ጋልቦ በማምለጥ) ራሱን
አዳነ ። የንጉሡ ሠራዊት ከወራቢሌ በታች ያቦት ከባሕሩ ድረስ
እያሳደደ ድል አድርጎ የሠፈሩን ድንኳን ተቃዶ (ቀዳዶ በመካፈል)
ተመለሰ ። ባላገሩንም ለውጊያው ሰብስቦት ነበርና አንማረከም እያለ
ጠንክሮ ተዋግቶ ድል ሆነ...ንጉሡም ሠራዊታቸው ጠቅሎ ሲገባ
ሲመለስ አይተው ፥ ከሠፈራቸው ገብተው ለእግዚአብሔር ምስጋና አቅ
ርበው መላልሰው መድፍ(የደስታ) አስተኰሱ ።[1]

---

* በጠላት ወገን ሆኖ የሚዋጋውን ባላገር ይዝረፍ ብለዋል ማለት ነው ።

* * ጋሸኛ የሚሉት በግራ ክንዱ ጋሻውን እየመከተ በቀኝ እጁ በጦር ወይም በጐራዴ የሚዋጋውን ክፍል ነው ።

* * * ከደኑ ወጣ ብሎ ያለው በር ።

* * * * ከውጊያ በፊት የሚደገም ጸሎት ።

1 ጸ.ት. ገብረ ሥላሴ ፥ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፥ ገጽ 145 ።



ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የጦርነቱን ሁኔታ በዚህ ዐይነት
ካመለከቱን በኋላ ፥ በማግሥቱ ስለ ከተማው አያያዝ ንጉሡ በድል
አድራጊነት ግርማ በእንዴት ያለ አኳኋን እንደገቡ አጠር አድርገው
እንደዚህ ብለዋል ። "...በታኅሣሥ 30 ቀን ከጨለንቆ ተነሥተው
በወራቢሌ ወርደው ያቦት ከባሕሩ ዳር ሰፈሩ ። የያቦት ሰዎችም ግብ
ራቸውን አገቡ ። ከዚህ በኋላ ራስ ዳርጌን ለጓዝ (ጥበቃ) ደጀን ትተው
በጥር 10 ቀን ወደ ሐረርጌ ገሠገሡ ። አሚር አብዱላሂም ጦር እንደ
ደረሰበት ባየ ጊዜ 'ልግባ ፥ ልገዛ ፥ አገርዎንም አያጥፉት' ብሎ ላከ ።
ዐፄ ምኒልክም '... እሺ ምሬሃለሁ' ብለው አማሬሳ ወንዝ ላይ ሠፈር
አደረጉ ። እርሱም ፈርቶ ሌሊቱን ሚስቱንና ልጆቹን ይዞ ጠፋ ።

"በነጋው የአሚር አብዱላሂ አጐት ሀሊ አቡበከር ፥ ዮሱፍ በር
ከሊን ፥ ቃዲ አብደላንና ሌሎችንም ብዙ ሽማግሌዎች ይዘው 'አሚር
አብዱላሂ ሌሊት ጠፋብን ግምብዎን (ከተማውን) ይቀበሉን ሕዝቡ
ንም አያጥፉት ንጉሥ ሆይ' አሉ ። በዚህ ጊዜ ንጉሡ በጅሮንድ አጥ
ናፌን * ከተማውንም ዕቃውንም ለመቀበል ሰንደቅ ዓላማቸውን
አሲዘው ሰደዱ ። የሻቃ ተክሌን * * ባላምባራስ ዳምጠውን * * *
የሻቃ አድነውን * * * * የሻቃ ገበየሁን * * * * * በሩን ለመ
ጠበቅ አዘዙ። በዚያም ቀን በመካከል ላይ በድዋንበር ፈረስ መጋላ በሚባ
ለው አደባባይና በአምስቱ በር የንጉሡ ባንዲራ ቆመበት* * * * * *

ከዚህ በኋላ ፥ ንጉሡ በሦስተኛው ቀን (ጥር 3 ቀን) በሥርዓተ
መንግሥት ሆነው ዘውዳቸውን ደፍተው በልብሰ መንግሥታቸው
አጊጠው ፥ ሠራዊቱ አምሮ ተሰልፎ መድፉም ፥ ጠበንጃውም ሙሉ
ግባት ተተኩሶ ሐረርጌ ከግንቡ ገቡ ። በዚያም ጊዜ አብረው የዘመ
ቱት ካህናት ወደ ጃንሆይ ገብተው "ኃዲጎ ተስዓ ወተሰዓተ ነገደ
ቆመ ሣህለማርያም *******ማዕበለ ባሕር ምድረ ሐረርጌ ገብአ ወወጽአ

---

* በኋላ ቢቶደድ ተብለው በዐድዋ ጦርነት ጊዜ ዋና የስንቅ ኃላፊ የነበሩት ።

** በኋላ ፊታውራሪ ተብለው ወለጋን ሲያስተዳድሩ ኖረው ዐድዋ ከጦርነት ላይ የሞቱት ።

*** በኋላ ፊታውራሪ ተብለው መስኮብ ተልከው ሲመለሱ ዐድዋ ጦርነት ላይ የሞቱት የነራስ ደስታ አባት ።

**** የሻቃ አድነው በኋላ ሊቀ መኳስ ሆነው ዐድዋ የዘመቱ ።

***** በኋላ ፊታውራሪ ተብለው በዐድዋ ጦርነት ጊዜ የጦር አበጋዝ ሆነው በታላቅ ጀግንነት ሕይወታቸውን ከጠፉ ሜዳ የሠዉ ።

****** የኢትዮጵያ ባንዲራ ተተከለ ለማለት ነው ።

******* ሣህለ ማርያም የምኒልክ የክርስትና ስም ነው ።

በሰላም" ብለው በወረብ ማሸብሸባቸውን ፤ ከዚያም ንጉሡ የሐረርጌን ሰዎች ገንዘባቸውም ቤታቸውም እንዳይነካ በየደጃቸው ጠባቂ ዘበኛ ማስቆማቸውን ከገለጡ በኋላ ፣ በመጨረሻ በጥር 20 ቀን ሐሙስ የሐረርጌን ግዛት ለባላምባራስ መኰንን ፣ የደጃዝማችነት ማዕረግ ጨምረው ከሰጡ ወዲህ አሚር አብዱላሂን ለመፈለግ (ለማሳደድ) በጥር 22 ቀን ወደ ባቢሌ ገሥግሠው የሁለት ቀን ዘመቻና ወረራ ካደረጉ በኋላ ብዙ ሰው አስገብረው ብዙ ከብት ይዘው ወደ ሐረር እንደ ተመለሱ ከተማረከው ውስጥ ለማራኪው ሁለት እጅ ለንጉሥ ፣ ሦስት እጅ (ከ5 ውስጥ 2 እጁ ለማራኪው 3 እጅ ለመንግሥት ለማለት ነው) ሰጥተው ከዚሁ ከዘመቻው ላይ ከተዘረፈው ውስጥ በጦርነቱ ሰዓት በቅሎው ፣ ፈረሱ ፣ አህያው ለሞተበት ወይም ለጠፋበት አደላድለው በመስጠት ከጦር ሠራዊቱ ፣ ከመድፉና ፣ ከጠበንጃው ከፍለው ለደጃዝማች መኰንን ትተው ወደ ከተማቸው ወደ እንጦጦ በየካቲት 28 ቀን መግባታቸውን ፣ ጊዜው የሁዳዴ ወራት በመሆኑ በከበሮ በጽናጽል ማኀሌት (ምስጋና ማቅረብ) ማድረግ ምንም በተለምዶ ክልክል ቢሆንም ፣ ሕግን በሕግ እንሻር (ንሥቱ ሕገ በእንተ ሕግ) በማለት "መንክር ተአምሪሁ ለመድኃኒነ ሣህለ ማርያም" * እያሉ የሦስቱ አድባራት ካህናት በክብርና በወረብ እንደ ተቀበሏቸው ጸሐፌ ትእዛዙ ለታሪክ በተዉልን መጽሐፍ አብራርተውታል ። [1] ደግሞ ከሐረር ወደ እንጦጦ ሲመለሱ ከያዙት ምርኮ ውስጥ በሰንሰለት የተያዙ ውሾችና በቀፎ ውስጥ ያሉ ርግቦች ስለነበሩ ሥራ ቤቶቹ "የምኒልክ ነገር ይመስለኛል ተረት ፣ አሞራው በቀፎ ውሻው በሰንሰለት" እያሉ ዘፈኑ ይባላል ።

ከዚህ በፊት የግራኝ አህመድ ወረራ በሚባለው መጽሐፍ እንዳመለከትሁት ፣ ምኒልክ በሕይወታቸው ለኢትዮጵያ ከሠሩት ታላላቅ ውለታዎች ውስጥ ሐረርጌን ግብጾች ከሾሙት ከአሚር አብዱላሂ እጅ በዚህ ዐይነት ውጊያ መውሰዳቸው ብቻ ሳይሆን ፣ እንግሊዞች በቅርቡ ከያዙት በዘይላና ፈረንሳዮች ወደፊት ከሚይዙት ከጅቡቲ ለመደባለቅ ሲያደቡ ፣ በእንግሊዝ የተደገፈው የኢጣልያ መንግሥት እንደ ምጥዋና እንደ አካባቢው ግብጾች በሚለቁት አውራጃ መተካትን እንደ ደንበኛ መብትና ተግባር በመቁጠር ሐረርን ለመያዝ በሚመኝበት ሰዓት ከኃያላኑ መንግሥታት ቀድመው መያዛቸው አንደኛውን ከፍተኛ ሥፍራ መያዝ አለበት ። ከርሳቸው መኳንንቱ ፣ እመቤቶቹ ፣ ተራው ወታደር ፣ የወንዱ አሽከር ፣ የሴቷ ገረድ ለዚህ ብሔራዊ አንድነት ደማቸውንና ወዛቸውን ያፈሰሱት ሁሉ በሕይወት ላለነው ባለውለታ ናቸው ።

በዚያን ጊዜ ፣ እርሳቸው ችላ ብለው ወይም የኃያላኑን መንግሥታት ጠብ በሩቁ በመፍራት በወዳጅ ዐይን ከሚያዩት ከኢጣልያ ንጉሥ ጋር ላለመጣላት ሲሉ ሐረርን በዚህ ዓመት ተሽቀዳድመው ባይዙ ኖሮ ፣ ሁለቱ መንግሥታት ፈረንሳይና እንግሊዝ እንኳን ምንአልባት ቅኝ አገር በመጥገባቸው ችላ ይሉት ነበር ቢባልም ፣ ቅኝ አገር የናፈቀው የኢጣልያ መንግሥት ሐረርን ቀድሞ ቢይዘው ኖሮ የኢጣልያ ሐረርን መያዝና የኢጣልያ ሱማሌ ይባል ከነበረውና በኋላ ከያዘው ከቅኝ ግዛቱ ጋር መደባለቁ የማይቀር ስለነበረ ፣ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ የእንግሊዝና የኢጣልያ ሱማሌ የተባሉት በኅብረት የመንግሥት አቋም ሲያገኙ የሐረርጌ ዕድል እምን ውዝግብ ላይ ያርፍ ነበረ ብሎ ለማሰብ ቀላል ነው ። ስለዚህ የኋለኛው የ1940—45 ዓ. ም. የነበረው ውዝግብ በ1879 ዓ. ም. የልደት በዓል ዕለት ጨለንቆ ላይ በቅድሚያ ተወገደ ማለት ነው ። ያገር ወሰን እንዳይደፈር ከመታገል ጋር ማስወገዱን አንድ ጊዜ ለዘለቄታ የማድረጉ ተግባር ያሁኑና የሚመጣው ትውልድ ፈንታ ነው ።

የሐረርጌ አውራጃ በንጉሥ ምኒልክ መያዙ እንግሊዞችንም ፣ ፈረንሳዮችንም በጣም ቆጭቷቸዋል ። እንደ ተያዘም ለመቃወም ሳይሞክሩ አልቀሩም ፣ በጦር ኃይል መቃወሙንም አልፈለጉትም ። ነገር ግን በሎንዶን የእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሳሊስበሪና የፈረንሳይ አምባሳደር ሙሴ ዋዴግተን በ1880 ዓ. ም. ስለ ሱማሌ ቅኝ ግዛታቸው በተለዋወጡት የስምምነት ጽሑፍ ላይ በቁጥር 4 "ሐረርጌን ይዘን ወደየግዛታችን ለመደባለቅ ምኞት የለንም ። ሌላም ኃይል ይኸንኑ አውራጃ እንዲይዘው አንፈቅድለትም" የሚል ቃል አስፍረው ተስማምተውበት ነበር ። [1] ነገር ግን የኢጣልያ መንግሥትና እነዚህ ሁለት ኃያላን መንግሥታት የሚቃወሙበትን መንገድ ጊዜና መሣሪያ ሲያማርጡ ፣ ምኒልክ በሐረርጌ ላይ ይዞታቸውንና የሐረርጌን ኢትዮጵያዊነት እያደረ እያጠባበቁ ስለሔዱ ፣ በነዚያ በኩል የታቀደው ተቃውሞ ዐውቆ በመኰሸፍ የውሃ ላይ ኩበት ሆኖ ቀረ ።

---

* ካህናቱ ለጥምቀት በዓል ከድጓ ላይ ተጠቅሶ ለክርስቶስ የተደረሰውን ለምኒልክ አወራርሰው ማዜማቸው ነው ።

1 ጸ.ት ገ/ሥላሴ ፣ ታሪክ ዘመን ዘዳ. ምኒልክ ፣ ገጽ 147 ።

1 „. . . the two governments engage not to endeavour to annex Harar, nor to place it under their protectorate. In taking this engagement, the two governments do not renounce the right of opposing attempts by any other power to acquire or assert any rights over Harar. . ." (S. Petrides, L'Ethiopie et les Covoitises Allemandes, pp. 135—139.)

ጥንት እነ ዐፄ ዓምደ ጽዮን ፥ እነ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የነበሩበት ፥ በግራኝ ወረራ ዋዜማ እነ አባ ገብረ እንድርያስ ፥ እነ ራስ ደገልሃን ፥ እነ ራስ ወሰን ሰገድ ፥ ከግራኝ ወረራ ፍጻሜ በኋላ እነ አዝማች ፋኑኤል ፥ እነ አቤቶ ሐመልማል የተጋደሉበት ሐረርጌ አሁን በመጨረሻ ዐፄ ምኒልክ ከያዙት ወዲህ ራስ መኰንን ከመኳንንቶቻቸው ጋር ከሸዋውና ከቤጌምድሩ ፥ ከጐጃሜውና ከትግሬው ፥ ከኦሮሞውና ከጉራጌው ተወላጅ ጋር ለዚህ ምድር የአዕምሮና የጉልበት ኃይላቸውን አፍሰውበታል ። የነዚህ የቀደምቱ የትክለኞቹ ተወላጆች ዛሬ በሕይወት የሚገኙት አገሬ ሸዋ ነው ፥ ቤጌምድር ጐጃም ፥ ትግራይ ነው በማለት ፈንታ የሐረር ተወላጅ ነን ይላሉ ። ከሀገሬው ተወላጅ ከአደሬው ፥ ከሱማሌው ፥ ከኦሮሞውና ከኢሳው ፥ ከአዳሉ ጋር ዘራቸውንና ልማዳቸውን ደባልቀው ይኖሩበታል ።





የመጨረሻው የሐረር ገዥ አሚር አብዱላሂ

(ከሪቻርድ ፓንክረስት ዝግጅት)
(ኢትዮጵያ ኢንግሬቨድ)




ንጉሥ ምኒልክ ከአሚር አብዱላሂ ጋር የተዋጉበት
የጨለንቆ ቦታ

[illegible]

[illegible]

[illegible]

# ሐረርን ስለመያዛቸው ዐፄ ምኒልክ ለኢጣሊያው ንጉሥ ለው ምቤርቶ የጻፉት

(አርኪቪዮ ስቶሪኮ ዴ ሶፕሬሶ ሚኒስቴሮ ዴል አፍሪካ ኢታሊያና ፡ ሮማ)

[illegible]



## ሐረርን ስለመያዛቸው ዐፄ ምኒልክ ለኢጣሊያው ንጉሥ ለዑምቤርቶ የጻፉት

(አርኪቪዮ ስቶሪኮ ዴ ሶፕሬሶ ሚኒስቴሮ ዴል አፍሪካ ኢታሊያና ፡ ሮማ)

# ምዕራፍ ሐያ ስድስት

## የደጃች ኃይሉና የደጃች ወልደ ሚካኤል የዘር አንድነት

## የባላባቶቹ የሥልጣን ፍልሚያ

ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስ ሁለት ጊዜም በሜዳ ጦርነት ግብጽን ቢያሸንፉም ፣ የእሸናፊ ወሰን የለውም በማለት በተለይ ከጉራዕ ጦርነት ወዲህ የተከበበውን የግብጽን ጦር ወደኋላቸው እንዳለ ትተው ከነሠራዊታቸው ወደ ምጽዋ ገሥግሠው ከቀይ ባሕር ወዲህ ማዶ የነበረውን የግብጽ አገዛዝ ጠራርገው ማስወጣት ሳያምራቸው አልቀረም ነበር ። ነገር ግን ፣ ይኸን ለማድረግ በቅድሚያ በመላው የኢትዮጵያ ግዛት በየአውራጃው የሚገኙትን መሳፍንትና ባላባት በቁጥጥራቸው ሥር ማድረግ ነበረባቸው ። ይኸን ከማድረጋቸው በፊት ከሐማሴን ወደ ቆላው ወደ ምጽዋ ወርደው ፣ ወደ ግራም ፣ ወደ ሐባብና ወደ ቦጐስ ፣ ወደቀኝም ወደ ዙላና ወደ አራፋሊ ታጥፈው ከግብጾችና እነርሱንም ከተጠጉት የእስላምና የክርስቲያን ባላባቶች ጋር በመዋጋት ያለ ኃይላቸውን እዚያ ላይ ቢያደክሙ ኖሮ ፣ ከዚህ በፊት ደጋግመን የጠቀስናቸው የሸዋ ፣ የወሎ ፣ የሰቆጣ ፣ የቤጌምድር ባላባቶች በላያቸው ላይ ሊነሡ ፣ ወይም ባይነሡም የንጉሠ ነገሥቱ ኃይል ሲዳከም ለወደፊቱ የማይበገሩ ባላጋራዎች ሊሆኑ በቻሉ ነበር ።

ይኸን አስቸጋሪ ሁኔታ በትክክል ተገንዝበውት ስለነበር ሁለት ጊዜ ከሩቅ አገር ፣ ባሕር ተሻግሮ ፣ ከግብጽ በምጥዋ በኩል ጦር ልኮ ከአስወጋቸው ጠላታቸው ከከዲቭ ኢስማኤል ጋር ነገሩ እንዳይከር "ወንድሜ ወዳጄ" እያሉ ደብዳቤና ገጸ በረከት እየተለዋወጡ በሰላም ድርድር የግብጽ ጦር ከሐማሴንና ከአካለ ጉዛይ ለቆ እንዲወጣ መጣጣር ግዴታ እንደ ሆነባቸው አንባቢ ሊገነዘበው ይችላል ። እንደዚህ በልስላሴ ካልያዙት ፣ "ለእንደርታው ለወልደ ሥላሴና ለዓድዋው ለራስ ሚካኤል ስሑል ተወላጅ ለዮሐንስ አንገዛም" የሚሉት እላይ ከጠቀስናቸው ሌላ በዚያው በቅርቡ ከነበሩት ከደጃች ወልደ ሚካኤል በቀር የአጋሜው የሰባጋዲስ ወገኖች ሳይቀሩ ለመሸፈትና ቢመቻቸውም መንግሥታቸውን ከመቀማት አይመለሱም ነበር ።

በዚያን ሰዓት ፣ ከሁሉም የበለጠ ያሠጋቸው የነበሩት ዋናው የዙፋን ባላንጣቸው የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ነበሩ ። ስለዚህ ከጉራዕ

ጦርነት በኋላ አሳባቸውን ወደ ሸዋ አምርተው ወደዚያ ተጉዘው ምኒልክን ለማሳመን ሲዘጋጁ በግብጾች ግንባር የነበረውን ጉዳይ በለዘብታ ለመያዝና የሰላም ድርድር ለማድረግ እንደ ተገደዱ ሁኔታው ያስረዳል ። ሆኖም ጉዳዩ ካገር ወረራ ዐልፎ የሃይማኖት ጦርነት ጠባይ ጭምር ስለያዘ ፣ ምኒልክም ሌሎቹም ፈንገጥ የማለት መልክ ቢያሳዩም ከአገርና ከሃይማኖት ባላንጣ ጋር በግልጽ አልተደረቡም ።

ከዐፄ ዮሐንስ በኩል ሐቀኛ የሰላም መንገድ ቢፈለግም ፣ በስምምነት እስረኛውንና የገዛ ልጁን ካገኘ ወዲህ ፣ በመሸነፉ የቆጨውና ዘመናዊው የጦር መሣሪያው ባፄ ዮሐንስ እጅ በመግባቱ እንደ እሳት ያንገበገበው ኢስማኤል በሰላሙ ድርድር ጊዜ ከዐፄ ዮሐንስ መላክተኞች ከነእቶ ገብረ እግዚአብሔር እጅ የወዳጅነት ደብዳቤና ገጸ በረከት እየተቀበለ ፣ የራሱንም ገጸ በረከትና ወዳጅ መስል ደብዳቤ ወደ ዐፄ ዮሐንስ በሚልከበት በዚያው ሰዓት ለዐፄ ዮሐንስ ባላጋራ ለደጃች ወልደ ሚካኤል ውስጥ ውስጡን እርዳታ እየሰጠ ለማጠናከር ይሞክር ነበር ። በዚህ ምክንያት ፣ ለዋናው አዝማች ለራቲብ ፓሻ እንደዚህ ብሎ ጽፎለት ይገኛል . . . "ደጃች ወልደ ሚካኤል ወታደሩን ይዞ ለሐማሴን ግዛት ተሾሞ የመጣውን ደጃች ኃይሉን ሒጂ ልሰር ብሎ ቢያማክርህ አትከልክለው ። በዚህ መስመር እንዲያውም መፍቀድ ብቻ ሳይሆን ያገሩን ተወላጅ ሰብስቦ የሚዋጋበትን መሣሪያም ገንዘብም ልትሰጠው ይገባል ። ይሁን እንጂ ፣ ወልደ ሚካኤል ኃይሉን ሊወጋ መሔዱ በኛ ፈቃድ መሆኑን እንዳይገልጽ መጠንቀቅ አለበት ። ምናልባት ወልደ ሚካኤል ኃይሉን ወግቶ መማረኩ የተወራና ከንጉሡ ከዮሐንስ ዘንድ 'ምንድነው ምክንያቱ' የሚል ጥያቄ የተላከብህ እንደሆነ ነገሩን በፍጹም እንደማታውቅና ወልደ ሚካኤል ያደረገው ያለፈቃድህ መሆኑን መግለጽ አለብህ ። እንዲያውም አጠራጣሪውን ሁኔታ ለማስወገድ ለወልደ ሚካኤል 'ከኃይሉ መዋጋትህን እንቃወማለን' የሚል ጻፍለትና 'በጐን ደግሞ የጻፍነው ለውሸት ነው እንዲያውም በርታ' ብለህ በጽሑፍ አስረዳው" ።[1]

በዚህ ደብዳቤ ላይ በሕዝብ መሪነት በከፍተኛ ደረጃ የተቀመጠው የኢስማኤል የቅጥፈትና የማጭበርበር አቅዋሙ በግልጽ ይታያል ። በዚህ ዐይነት ራሱ ሁለት ጊዜም ጦር ልኮ በማዋጋት ዮሐንስን ማጥቃት ያቃተውን አሁን በገዛ ወገናቸው ለማስጠቃት ፈለገ ። በዚሁ ጐን ደግሞ ፣ ደጃች ኃይሉ ባፄ ዮሐንስ ፈቃድ ተሾመው ወደ ሐማሴን

1 G. Douin, Histoire du Kedive Ismael, pp. 1029 1042.



መምጣታቸውን ሲረዳ በፊተኛው ጊዜ ከራቲብ ፓሻ ጋር የተጻጻፉትን ደብዳቤ ፈልጎ ፣ "ይኸው እርስዎን ከድተው ጽፈውልኝ ነበር" አስኝቶ ንጉሡን ከታማኞቻቸው ለማጣላት ጥረት አድርጓል ።[1]

በእንዱ በሐማሴን ግዛት ዘመዳሞቹ ወልደ ሚካኤልና ኃይሉ ሊዋጉ ከዝግጅት ላይ ይገኙ ነበር ። የወልደ ሚካኤልና የኃይሉ አባቶች ከጐንደር ነገሥታትና መሳፍንት ሲሾሙ ሲሻሩ የኖሩ ናቸው ። በዕድሜ ከደጃች ወልደ ሚካኤል ደጃች ኃይሉ 15 ዓመት ያህል ይበልጣሉ ። እነዚህ ሁለት ባላባቶች ርስተ ጉልታቸው የደጃች ኃይሉ ጸሐዘጋ ሲሆን ፣ የወልደ ሚካኤል ሐጸዘጋ ይባላል ። ሁለቱም እዚያው ሐማሴን ውስጥ በዘር ግንድ የተገናኙ ሆነው ሳለ ፣ እንደ እነሱ አባቶቻቸው በሐማሴን ግዛት ሲዋጉም ፣ ሲታረቁም ብዙ ዘመን አሳልፈዋል ።

ሁለቱ ባላባቶች የኖሩት ፣ የኢትዮጵያ ነገሥታት ሥልጣናቸው የወደቀበትና መሳፍንት በየአውራጃው ተመሥርተው እርስ በርስ በተዋጉበት ዘመን ነበር ። በሸዋ መርዕድ አዝማች ወሰን ሰገድ ፣ በጐጃም እነ ራስ መርዕድ ኃይሉ ፣ በስሜን እነ ራስ ገብሬ ፣ በቤገምድር እነ ራስ አሥራትና እነ ራስ ወልደ ገብርኤል ነበሩ ። ከነዚህም በኋላ እነ ራስ ጉግሣ መርሶ በጐንደር የእንደራሴነቱን ሥፍራ የያዙበትና በየጊዜው እርስ በርሳቸው እየተዋጉ በመተላለቅ ሥልጣን የሚሻሙበት ጊዜ ነበር ።

በዚሁ ጊዜ ፣ ከመረብ ወዲያና ከመረብ ወዲህ ባለው የትግሬና የትግራይ ግዛት እነ ራስ ወልደ ሥላሴ በእንደርታ ፣ እነ ደጃች ገብረ ሩፋኤል በተምቤን ፣ እነ ደጃች ሰባጋዲስ ወልዱ በአጋሜ የገኑበት ጊዜ ነበር ። የደጃች ወልደሚካኤል አያትና አጐት እነ ከንቲባ ተስፋና እነከንቲባ ዘርዓይ ሐማሴንን ሲገዙ ኃይሉ በሐማሴን ውስጥ የወጣትነት ጊዜያቸውን ካሳለፉ ወዲህ ለደጃች ሰባጋዲስ ልጅ ለሹም አጋሜ ካሳ አድረው ከርሳቸው ጋር ሳሉ ፣ የስሜንን ፣ የወልቃኢትንና የጸገዴን ግዛት ከያዙት ከደጃች ውቤ ኃይለ ማርያም ጋር ለጦርነት በተሰለፉበት ሰዓት ኃይሉ ከካሳ ጋር ሆነው በ1832 ዓ. ም ውቤን ተዋግተዋል ። ድሉ የውቤ ሆኖ ጌታቸው ካሣ ሲማረኩ እርሳቸው አምልጠው ወደ ሀገራቸው ወደ ጸሐዘጋ(ሐማሴን) ሔደዋል ። በዚህም ጊዜ አባታቸው ተወልደ መድኅን እርጅተው እቤት መዋል ዠምረው ነበርና በአባታቸው ፈንታ እርሳቸው ከሹም አጋሜ ካሳ የደጃዝማችነት ማዕረግ

I Ibid.

እንዳገኙ ከጦርነቱ መልስ የጸአዘጋን ግዛት ይዘው ማስተዳደር እንደ ዠመሩ ከላይ እንዳልነው ፣ የሹም አጋሜ ካሣና የደጃች ኃይሉ ባላጋራ ደጃች ውቤ የሁለቱን ተቃዋሚዎች እየመለሱ ግዛታቸውን ከመረብ ወዲያ ባለው በሐማሴን ፣ በአካለ ጉዛይና በሥራዬ አውራጃ አስፋፉ ።

በዚህ ጊዜ ኃይሉ ግዴታ ሆኖ ለደጃች ውቤ ስለ ገቡላቸው ፣ የሐማሴንን ግዛት መርቀውላቸው ወደ ስሜን ተመለሱ ። ከዚህ በኋላ የሥራዬ ሕዝብ "እኛንም ጭምር ይዘው ከውቤ አገዛዝ ያድኑን" የሚል አሳብ ስላቀረቡላቸው "እሺ" ብለው የሥራዬንና የሐማሴንን ግዛት ይዘው በውቤ ላይ እንደ ሸፈቱ ሳይቀናቸው ቀርቶ በውቤ ትእዛዝ ታስረው ወደ ስሜን መጥተው በግዞት ላይ እንዳሉ በ1847 ዓ ም ዐፄ ቴዎድሮስ ከውቤ ጋር ተዋግተው ያሸነፉ ጊዜ ኃይሉ ከስር ቤት ወጥተው በሹመት እንደገና ወደ ሐማሴን ተላኩ ። ቀጥሎ ባለው ጊዜ በ1852 ዓ ም ባፄ ቴዎድሮስ ላይ የደጃች ውቤ እህት የወ/ሮ የውብዳር የልጅ ልጅ ደጃች ንጉሤ (አገው ንጉሤ) ሸፍተው ከሰሜን አልፈው በትግራይና በትግሬ ላይ በተስፋፉበት ሰዓት ኃይሉ ለቴዎድሮስ በመታመን ከንጉሤ ጋር ከተዋጉ በኋላ ተሸንፈው ንጉሤ የሐማሴንን ግዛት ለወልደ ሚካኤል ወንድም ለደጃች መርዕድ ሰጡ ። በዚህ ዐይነት ኃይሉ በደጃች ውቤና ባፄ ቴዎድሮስ እንደዚሁም ባፄ ተክለ ጊዮርጊስና ባፄ ዮሐንስ ጊዜ አንድ ጊዜ ሲሾሙ ፣ ሌላ ጊዜ ሲሻሩ ወይም ሲጋዙና ሲታሰሩ ቆይተዋል ።

ከዐፄ ቴዎድሮስ ሞት ወዲህ ዋግሹም ጐበዜ ላስታንና ትግራይን በሚገዙበት ጊዜ ቀደም ብለው ወልደ ሚካኤል ስለ ገቡላቸው ፣ ኃይሉን ሽረው ለወልደ ሚካኤል የደጃዝማችነት ማዕረግ ጨምረው ስለ ሰጡዋቸው ፣ ከአገው ንጉሤ ሞት በኋላ ለቴዎድሮስ ታማኝ የሆኑት ደጃች ኃይሉ በዚህ ጊዜ ከደጃች ወልደ ሚካኤል ጋር ተዋጉ ። ቢሌላ ቢኩል ደግሞ በዚሁ ዘመን በእንደርታ ፣ በተምቤን ፣ በዐድዋ የገነኑት ደጃች ካሳ (የወደፊቱ ዐፄ ዮሐንስ) በዚህ ጊዜ ኅብረታቸው ከደጃች ወልደ ሚካኤል ጋር ነበር ። በተረፈ በዚሁ መካከል የሸፈው ባላባት ራስ ባርያው ገብረጻድቅ በትግራይ ላይ ካፄ ቴዎድሮስ ተሾመው ከነ ደጃች ካሳ ጋር በደብረሲና ተዋግተው ባርያው ስለ ተሸነፉ በደጃች ካሳ ፈቃድ ወልደ ሚካኤል ወደ ግዛታቸው ተመለሱ ። ቀጥሎ ባለው ጊዜ ካሳ (ዮሐንስ) እንደገና ወልደሚካኤልን ሽረው ኃይሉን በሐማሴን ሲሾሙ ፣ ወልደ ሚካኤልን በእናታቸው አገር በቃርኒሽምና በደምበሳን ወስነዋቸው ቆይተው ነበር ።

በዚህ ዐይነት ምስቅልቅልና ዝውውር ሁኔታ ላይ እንዳሉ ካሳ ከዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ተዋግተው ንጉሠ ነገሥት በሆኑበት ጊዜ ባርያው



ከልብ ስለታመኑላቸው ፣ በጠቅላላው ከመረብ ወዲያ ባለው በሥራዬና ሐማሴን ላይ ጠቅላይ ገዥ አደረጉዋቸው ። በዚሁ ጊዜ የግብጽ መንግሥት ባለፈው እንዳነበብነው ፣ በኢትዮጵያ ላይ መስፋፋት ስለዠመረ ከራስ ባርያውና ካፄ ዮሐንስ ጋር ያላቸውን ጠብ ለመበቀል ሲሉ ወልደ ሚካኤል በግድ ወደ ግብጾች ተጠጉ ። ነገር ግን ዐፄ ዮሐንስ በጉራዕ ጦርነት ፍጻሜ ላይ እስከ ካይሮ ድረስ እነ አቶ ገብረ እግዚአብሔርን እየላኩ ከከዲቭ ኢስማኤል ጋር የሰላም ውል በሚደራደሩበት ጊዜ ለሐማሴን የደጃች ወልደ ሚካኤልን ነዋሪ ባላንጣ ደጃች ኃይሉ ተወልደ መድኅንን ሾመው ልከው እርሳቸው በዚሁ ዓመት (1870) ዓ ም የሸዋውን ንጉሥ ምኒልክን ለማስገበር ረዥሙን የሸዋ ጉዞ ዠመሩ ።

# ምዕራፍ ሐያ ሰባት

## ደጃች ኃይሉና ራስ ባርያው ከደጃች ወልደ ሚካኤል ጋር በየተራ ተዋግተው እንደሞቱ ፣ በሐማሴን የሻለቃ አሉላ እንግዳ መሾም ፣ የራስ ወልደ ሚካኤል ፣ ከምሕረት በኋላ እስራት

በፊት ደጃዝማች በሚባሉበት ጊዜ ፣ በጉንደት (ጉንዳጉንዲ) ጦርነት ወልደ ሚካኤል ካፄ ዮሐንስ ወገን ሆነው ከግብጾች ጋር በዠግንነት እንደ ተዋጉ ብዙ ግብጻውያንንም በመማረክ ንጉሠ ነገሥቱን አስ ደስተው የሐማሴንን ግዛት ተቀብለው ነበረ ። በኋላ ግን ፣ የጉራዕ ጦር ነት ሲቃረብ ዐፄ ዮሐንስ ሠራዊታቸውን ይዘው መረብን ተሻግረው ወደ አከለ ጉዛይ ሲጓዙ የወልደ ሚካኤልን የሥልጣን ተፋላሚ ደጃች ኃይሉን አስከትለው ስለመጡ ፣ እኔን ሽረው ሹመቴን ለኃይሉ ሊሰጡ ነው በሚል ጥርጣሬ ከንጉሠ ነገሥቱ ሸፍተው ወደ ግብጾች መግባታቸውን በዚህም ጊዜ የግብጽ ባለሥልጣኖች ለወልደ ሚካኤል የራስነት ማዕረግ ሰጥተው እንዳስደሰቷቸው ተጽፏል ።

በፊተኛው ወቅት ያሰቡትን አናውቅም እንጂ ፣ ንጉሠ ነገ ሥቱ በጉራዕ ጦርነት ድልን ከተጐናጸፉ በኋላ ፣ ከመረብ ምላሽ ያለውን የሐማሴንን ግዛት ለደጃች ኃይሉ ተወልደ መድኅን መስጠታ ቸው የተረጋገጠ ነው ። በዚህም ጊዜ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከሐማሴን ዐድዋ ከዚያ ወደሸዋ ሲጓዙ ኃይሉ ወደ ሐማሴን ሔደው ማስተዳደር ዠመሩ ። ከጉራዕ ጦርነት በፊት በውድም ፣ በግድም ወደ ግብጾች ተጠግተው ከነበሩት ውስጥ ብዙ ሰዎች እየመጡ ገቡላቸው ።

ዳሩ ግን ፣ በሜዳ መዋጋት ያልሆነላቸው ፣ ወይም በውል ሰላም አድርጎ ከልብ መታረቅም የቆጫቸው ግብጾች [illegible]ው እንዳመለከት ነው ፣ ባንድ ወገን ላፄ ዮሐንስ የሰላም እጃቸውን እየዘረጉ ፣ ሁለተኛ ውን እጃቸውን በዚያው ሰዓት ለወልደ ሚካኤል ዘርግተው የጦር መሣሪያም ፣ ገንዘብም በጐን እያቀበሉ በቁጥጥራቸው ሥር የነበሩትን እነ አቶ አስገዶምን ፣ እነ አቶ ወልደ ጋብርንና ሌሎቹንም እንዲተባበ ሩዋቸው አድርገው ከኃይሉ ጋር ለመዋጋት በሚዘጋጁበት ሰዓት በወታደራዊ ትጥቅ ረገድ የወልደ ሚካኤል ከኃይሉ የበለጠ ዘመናዊ ነት ነበረው ። ስለዚህ ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል በግብጾች ውስጣዊ

ድጋፍ እየተረዱ በራሳቸው ታማኝ የሐጸጋ ጦራቸው ላይ የአከለ
ጉዛይን ፣ የሐልሃልንና የሰሐርትን ተዋጊ ጦር በማስተባበር መጥተው
ዳዕሮ ካውሎስ ሠፍረው ፣ "የኔ የሆንክ ተከተለኝ" የሚል መልእክት
በያለበት ልከው ስለነበር የሚናብ ዘርዓይ ፣ የካርኔሽም ፣ የደምበሳን
ተወላጅ አጋማሹ ገባላቸው ። ወጣቱ ልጃቸው ደጃች መኰንንም አብ
ረው ስለነበሩ ፣ ከዚህ ቤፊት በዕሮ መኸንና በእምባዘሪብ ላይ በተደረ
ገው ጦርነት ዤግንነት ማሳየታቸውን እባትዮው በማስታወስ ፣ "እሁ
ንም ዕድላም ነህና የድል ዝንጣፊ* ይዘህ አዝማች ሁነን " እሉዋ
ቸው ይባላል ።

በበኩላቸው የደጃች ኃይሉ ሰዎች ከፊሎቹ "ያለንበት ሠፈር ስለ
ማይመችን ፣ ወደ ቋራ ጉብታ ሔደን እንዋጋ" ብለው እሳብ ቢያቀ
ርቡ ሌሎቹ ደግሞ "ግዴለዎትም እዚሁ ሆነን እንዋጋ አይሥጉ"
ብለው ስለመለሱላቸው እሳቸው ም፣

"እኔ ኃይሉ
የደም ደመና
ትልቁ ወርካ**

ብወድቅም ብዙ ቅርንጫፍ ይዤ ነው የምወድቀው" ብለው
ረው ፣ "ሁልህም ታጠቅ" ብለው አዘዙ ። ከዚያ ከመንደር ወጣ ብለው
በገበያ እጠገብ በነበረ ሜዳ ላይ ጦራቸውን እሰለፉት ።

በዚህ ጊዜ ወልደ ሚካኤል ከጦራቸው ለየት ብለው አንድ ሰው
ብቻ አስከትለው ፣ የጠላታቸውን ሠፈር የመዋጊያውን ምቹ ቦታ ለመ
መርመር የጸሐዘጋን ከተማና የኃይሉን የጦር ሠፈር ወለል አድርጎ
ከሚያሳይ ቦታ ሆነው እየተመለከቱ ለድሉ ሥጋት ስለ አደረባቸው ፣
"በውነት ይኸን ጦር እችለው ይሆን? ይኸን ድል ብትሰጠኝ ስመለስ
የሚገባህን ስለት አቀርብልሃለሁ" ብለው ለቅዱስ ጊዮርጊስ እንደ ተሳሉ
ዮሐንስ ኮልሞዲን ያሰባሰበው እፈ ታሪክ ያመለክታል ።

እኝሁ ጸሐፊ ጦርነቱ ከመዠመሩ በፊት አንዳንድ የጸሐዘጋ ሰዎች
ባንድ ወገን ከደጃች ኃይሉ ጋር ሆነው ውስጡን ከደጃች ወልደ ሚካ
ኤል ጋር እየተላላኩና ገንዘብ እየተቀበሉ ከድተው ስለነበረ ይኸን

* የድል ሰራቂ
** በትግርኛ —እነ ኃይሉ
እነ ሰርብ ደም
እነ ዐባይ ጸዕሮ



ያወቀው ሁሉ ፣ "እነዚህ ጌታውን እንደ ሸጠ እንደ ይሁዳ ናቸው"
እያለ በማማት ሲያወግዝ እንዳንዶቹም ፣ "የሰኞ ቀን አይሆነንምና
የዛሬው ውጊያ ይቅርብን" ብለው ቢያመለክቱ ፣ "ከዚህ በፊት እኔ
ያልኩትን አልተቀበላችሁም ፣ አሁን ዝም ብላችሁ መዋጋት አለባ
ችሁ" ብለው ደጃች ኃይሉ ወደ ወከዳባ ጉዟቸውን ቀጠሉ ። የተጓዙትም
ወደቤት ምካህ የሚያደርሰውን መንገድ ወልደ ሚካኤል ሳይዙት
ለመቁረጥ ነበር ። ዳሩ ግን ፣ ወልደ ሚካኤል ከዚሁ ከቤት ምካህ ሌሊ
ቱን ገሥግሠው ሲነጋጋ ወደ ወከዳባ ደረሱና ወታደሮቻቸው ምቹ
ምቹውን ሥፍራ ይዘው ፣ በልባቸው ተኝተው እያነጣጠሩ ሲጠብቁ
ደጃች ኃይሉ ይኸን ሁሉ ሳያውቁ ዝም ብለው ወደ ጠላቶቻቸው
እቅጣጫ ሲጓዙ ፀሐዩዋ ፊት ለፊት ሆና የጠላታቸውን ሠፈር ለመ
መልከት አስቸግራቸው እንደነበረ ጸሐፊው ያመለክታሉ ።

ስለዚህ የጸሐዘጋ ሰዎች ሳያስቡት ከደጃች ወልደ ሚካኤል በኩል
የጻዳከስታኑ ፣ ያቶ ወልደ ገብርኤል ልጅ ጉግሣ በፈረስ ሆኖ ወዲያና
ወዲህ ሲል ስለታየ ፣ ወዲያው የደጃች ኃይሉ ሰዎች የጌታቸውን ድን
ኳን ተክለው ለጦርነት ሲዘጋጁ መሪውም ደጃች ኃይሉ በበቅሏቸው
ላይ ሆነው 'እነ እገሌ በዚህ ፣ እነ እገሌ በዚያ ሁኑ' እያሉ ሲያስተና
ብሩ የደጃች ወልደ ሚካኤል ወታደሮች ከተደበቁበት ቦታ እነጣጥ
ረው ተኩሰው መቷቸው ። በዚህ ጊዜ መመታታቸው የገባቸው የገዛ
ሰዎቻቸው ደጋግፈው ከበቅሎ እውርደው እተነጠፈ እንበሳ ቆዳ ላይ
እንዳስቀመጧቸው ወዲያው ሞቱ ።

የጸሐዘጋ ሰዎች በብዛት ተኩስ ቢከፍቱ የደጃች ወልደሚካኤል
ሰዎች (ሐጸጐች) ፀሐይዋ በጀርባቸው ስለ ነበረች ፣ ምንም ሳይቸገሩ
የነዚህን ዐይኖቻቸውን እያጭበረበረች እነጣጥሮ ለመተኰስ ባስቸግ
ረቻቸው በደጃች ኃይሉ ወታደሮች ላይ እያነጣጠሩ በመተኮስ ብዙ
ሰው ይጥሉ ዠመር ። ከነዚህም ወገን ግን ፣ የሚተኰሰው 'የመታውን
ይምታ' እየተባለ እንደዚሁ ቢሆንም ብዙ ሰው መግደላቸው አልቀረም ።
በዚሁ ጊዜ የራሳቸው የደጃች ወልደሚካኤል ልጅ ደጃች መኰንን
ተመትቶ ወደቀ ።

ከዚህ በኋላ ፣ የጸሐዘጋ ሰው ከጦሩ ሜዳ እየሸሸ መሔድ ሲዠምር
ደጃች ወልደ ሚካኤል ድል በማድረጋቸው ተደስተው ፣ "ምርኮኛውን
እሰሩ እንጂ አትግደሉ" ብለው ሳለ በኋላ ግን ፣ የሚወዱት ልጃቸውን
የደጃች መኰንን በውጊያው ላይ መሞቱን ባዩ ጊዜ ፊታቸው ባንድ
ጊዜ በቁጣ ተለውጦ ጸሐዘጋውን ፣ "ያዘው! በለው! ግደለው! ቆራር
ጠው!" እያሉ በፊታቸው ያገኙትን ሁሉ ይገድሉ ነበረ ። ወደ ጸሐዘጋ
መንደር ገብተው የጸሐዘጋ ተወላጅ የሆነውን ሁሉ እንዳስፈጁት መሬቱ

ሁሉ በጸሐዘጋዎች ሬሳ ተሸፍኖ እንደነበረ ጸሐፊው ይገልጹና ከዚሁ አያይዘው በደጃች ኃይሉ ሬሳ ጐን ካቶ ተስፋ ጽዮን የተወለደው የልጅ ልጃቸው ፤ የካሳና የእቶ አላ (አሉላ) ልጆች ፤ የልጅ ሽፋርና የልጅ አባይ ሬሳ ፤ የሌሎችም ወድቆ ይታይ ነበረ ። በዚህ ቀን የጸሐዘጋ ከተማ የእዲ ገብሩ ፤ የእዲ ተከላይ ፤ የእዲ ኸፈለት መንደሮች መቃጠላቸውን ባገር ተወላጁ ጸሐፊ በትግርኛ ተጽፎ ኮልሞዲን ባሳተሙት መጽሐፍ ላይ ተዘርዝሮ ይገኛል ።

የስመ ጥሩው የደጃዝማች ኃይሉ አባ ሐባል ሕይወት በዚህ ዐይነት ተፈጽሟል ። ሲታሰሩ ሲፈቱ መኖራቸውን በጠቅላላ ዕድሜያቸው 68 ዓመት መሆኑን ካመለከተ በኋላ ፤ ሐማሴንን የገዙበት (ያስተዳደሩበት) ዘመን 30 ዓመት መድረሱን ዜና መዋዕሉ ይገልጻል ።

ዐፄ ዮሐንስ ፤ በሸዋ ምኒልክን በ1870 ዓ.ም. እሳምነው ቦሩ ሜዳ (ወሎ) ላይ ከንጉሥ ምኒልክ ጋር በመተባበር የሃይማኖትን ጉዳይ በጉባዔ አከራከረዋል ። ተዋሕዶ ሃይማኖትን ካጸኑ በኋላ ፤ እስላሞች ክርስትና እንዲነሡ ዐውጀው ከሁለት የታወቁ የወሎ ባላባቶች እንደኛውን መሐመድ ዐሊን በሚካኤል ሥያሜ ክርስትና ራሳቸው እንሥተው በራስነት ማዕረግ በወሎ ሾመዋል ። ከዚያም ዐፄ ዮሐንስ ከወሎ ወደ ሰለዋ ሔደው ያመፁባቸውን ራስ ኃይሉን በማባረር ላይ በነበሩበት ሰዓት በሐማሴን ላይ የሾሟቸውን የደጃች ኃይሉንና የደጃች ወልደ ሚካኤልን ጦርነትና የኃይሉን መሞት ሰሙ ። ሁኔታው ብዙም ያስገረማቸው ወይም ያናደዳቸው አይመስልም ። ምክንያቱም በፊተኛው ዘመን ኃይሉም እንደ ወልደ ሚካኤል የእርሳቸውን እነሣሥ ሲቃወሙ የኖሩ ነበሩ ። ባፄ ዮሐንስም እጅ 16 ዓመት እንደ ታሰሩ ዜና መዋዕሉ ያወሳል ።

ስለዚህ ደጃች ኃይሉ በወልደ ሚካኤል እጅ መሞታቸውን ዐፄ ዮሐንስ እንደ ሰሙ በንዴት ሔደው ደጃች ወልደ ሚካኤልን በመግደል የኃይሉን ደም በመበቀል ፈንታ ነገሩን ውጠው በትዕግሥት ፤ “ባለፈው ጥፋትህ ምሕረት አድርጌልሃለሁ ፤ ወደኔ ብትገባ በሐማሴን ላይ እሾምሃለሁ” ብለው ሦስት መነኮሳትን ቢልኩባቸው ፤ ወልደ ሚካኤል ባደረጉት ሁሉ ንጉሠ ነገሥቱ ከልብ እንደማይምሩአቸው በመጠራጠር ወይም በስመ ጥሩው በደጃች ኃይሉ ላይ ባገኙት አሸናፊነትና በእጃቸው በገባው የጦር መሣሪያ በመተማመን ይሁን አይታወቅም ፤ ለጊዜው አልገባም ብለው የእምቢታ መልስ ሰጡ ። ከዚህ በኋላ ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ለሐማሴን ራስ ባርያው ገብረ ጻድቅን ሾመው ላኩ ።



ራስ ባሪያው በሐማሴን ላይ ሲሾሙ የጌታቸውን ትእዛዝ በመፈጸም በ1870 ዓ.ም. ወደ ሐማሴን ሔደው በቤት ምኻእ ሠፈሩ ። እዚያም ሳሉ “ደጃች ወልደ ሚካኤል መጣብዎ” ቢሏቸው “እንዴት እኔ እባ ጋላ እኔ እሔድበታለሁ እንጂ እሱ አይመጣብኝም” ብለው ፎከረው ፤ ወደ ወልደ ሚካኤል ሲጓዙ ፊታውራሪ ገብረ አብ የሚባሉት “ከደጃች ወልደ ሚካኤል ጋር መዋጋቱን እንተውና ከዚህ ሥፍራ ብንሔድ ይሻላል . . .” ቢሏቸው ፤ “ዝም በል አይዞህ አትፍራ ወልደ ሚካኤል እኔን ሰመዋጋት የሚችል ይመስልሃልን” ብለው ተቆጥተው ለውጊያ ተዘጋጁ ።

በበኩላቸው የጦር ዘዴ ከራሳቸውም ፤ ከግብጾችም የተለማመዱት ኃይለኛው ደጃች ወልደ ሚካኤል ጦራቸውን ሰብስበው ወደ ካርኔሽም ሲጓዙ ፤ “በድንገት ደርሰን አደጋ ለመጣል እንዲመቸን አትነጋገሩ ፤ አትሸልሉ” የሚል ትእዛዝ ሰጥተው በዝምታ እየተራመዱ እምባዶርሆ* ደረሱ ። በጉዞም ጊዜ አንድ ወታደር በፊተኛው የጦርነት ጊዜ ሰኞ ቀን በወከድባ በደጃች ኃይሉ ላይ የተገኘውን ድል አወራርሶ “ላሌ ላሌ. . . ” እያለ የሽለላ ግጥም መግጠም ሲዠምርና ጓደኞቹ “ዝም በል!” እያሉ ሲቆጡት ወልደ ሚካኤል ተዉት ይጨርስ ስላሉ ፤

“ላሌ! ላሌ! ሰኑየ ሰኑየ ሰኑይ ወከ ድባ
ድራርይ ትኸልእ ምሳሕ ሂባ**”

ብሎ ከሸለለ በኋላ ፤ ወልደ ሚካኤል በደስታ “አይዞህ አንድ በቅሎ እሰጥሃለሁ” ብለው ተስፋ ሰጥተውት ጉዞአቸውን ቀጥለው እድ ነፋስ ከደረሱ በኋላ፤ እንዳለፈው ከደጃች ኃይሉ ጋር እንዳደረጉት ዐሐይዋ በጀርባቸው እንድትሆን ሲሉ ወደ ቀኛቸው ወደ ቤተ ጊዮርጊስ ታጥፈው ቤት ምኻእ ከሚባለው ቦታ ላይ ሰኞ ግንቦት 12 ቀን የሚካኤል ዕለት ከራስ ባርያው ጋር ውጊያ ዠመሩ ። በዚህም ጊዜ ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል በፈረሳቸው እንዳሉ እየፎከሩ ገብተው በመዠመሪያ ጦርነቱን የዠመረውን ፊታውራሪ ገብረ አብን*** እነጣጥረው ከፈረሱ ላይ እንዳለ መቱት ። በዚህ ጊዜ ከራስ ባርያው ጦር ጋር ተባብሮ የነበረው የጸሐዘጋ ሰው መሸሽ ሲገምር በዚሁ መካከል

* 12 ኪሎ ሜትር ከአሥመራ ።

** ሰኞ ለት (በወከዳባ ከደጃች ኃይሉ ጋር የተዋጉበት ቦታና ቀን) የሰጠኸንን የድል ምሳ በዛሬው ሰኞ ምሳችንን አትነሣንም እንደ ማለት ነው ።

*** የብላታ ገብረ መድኅን ልጅ ፤ ገብረ መድኅን የብላታ አገልድም ልጅ ።

ራሳቸው ራስ ባርያው ተመትተው ወደቁ ። ከርሳቸውም ጋር ብዙ መኳንንትና የጸዓዳ ክህስታኑ አቶ ገብረ ሥላሴ (የአቶ አስገዶም ልጅ) ሞቱ ። ድሉም በማያጠራጥር አኳኋን በደጃች ወልደ ሚካኤል አሸናፊነት ተደመደመ ።

በዚሁ ጊዜ ፣ ዐፄ ዮሐንስ ከሰለም ወደ ዐድዋ ተመልሰው የትንሽ ጊዜ ዕረፍት ካደረጉ በኋላ ፣ በወልደ ሚካኤል ላይ ለመዝመት ወደ ሐማሴን ሲጓዙ ደጃች ወልደ ሚካኤል በቦጐስ ፣ በሐባብና በመንሳ ያሉትን የግብጾች እርዳታ ይዘው ንጉሠ ነገሥቱን ለመቋቋም ሞክረው ነበር ። ከዚህ ቀደም ብሎ በደጃች ኃይሉና በራስ ባርያው ላይ የተከታተለ ድል ስለአገኙ ፣ ግብጾቹ ውስጥ ደስታ እየተሰማቸው በራቲብ ፓሻ እግር ተተክቶ ቆላማውን የቦጎስን ክፍል የሚያስተዳድረው ሶሊማን ኒያዚ ፓሻ ፣ ወደ ካይሮ ተላልኮ የራስ ወርቅ አሠርቶ በመስጠት በመንግሥቱ ስም ቀደም ብለው የተቀበሉትን የራስነት ማዕረግ አጸናላቸው ። በወዲህ በዐፄ ዮሐንስ ወገኖች ዘንድ ግን ፣ ወልደ ሚካኤል ከግብጾች ጋር መተባበራቸውን በመንቀፍ ሐጂ ወልደ ሚካኤል እየተባሉ መጠራት ዠምረው ነበር ።[1]

በዚህም ጊዜ ፣ ዐፄ ዮሐንስ የአከለ ጉዛይን ግዛት ለአጐታቸው ለትልቁ ራስ አርአያ ድምፁ ሰጡ ። ራስ አርአያም ወደ ግዛታቸው ወደ አከለ ጉዛይ ሔደው በጉራዕና በቀይህ ኮር ግብጾች ያሠሩትን ምሽግ እያፈራረሱ አገር በሚያረጋጉበት ሰዓት ፣ እስካሁን ድረስ ጸሐዘጋዎችንና ሐጸጋዎችን ሲያቀጣቅጥ የኖረውን የሐማሴንንና የሠራዬን ግዛት ባስተዳደርም ፣ በወታደርነትም ሲያገለግሉ ለቆዩት ለተምቤኑ ተወላጅ ለሻለቃ አሉላ እንግዳ የራስነት ማዕርግ ጨምረው ሰጧቸው ። ስለዚህም ከዚህ ጊዜ ዠምሮ እኝህ ሰው በሚጽፉት ደብዳቤ ላይ "ራስ አሉላ ዘውእቱ ቱርክ ፓሻ" እያሉ በማኅተም ሲጻጻፉ ይታያል ። 'ቱርክ ፓሻነት'ም ትልቅ ወታደራዊ ሥልጣን ነው ። በዚህ ዘመን በቱርክ ሡልጣን ሥር ያሉትንም ግብጾችን ጭምር ቱርክ ይሏቸው ነበር ።

የሆነ ሆኖ ፣ የዚህን ሁሉ ወሬ ደጃች ወልደ ሚካኤል ሲሰሙ ቀድሞውኑ ነዋሪ በሆኑት ታማኞቻቸው ላይ ፣ ወዲያና ወዲህ እያሉ ካገር ውስጥና ከግብጾችም ጦር ለማስተባበር ሞክረው ነበር ። ነገር ግን ፣ ባሁኑ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስ በግብጾች ላይ የሁለት ጊዜ ድል ጌታ ሆነው ፣ የሸዋውን ንጉሥ ምኒልክን አሳምነው ፣ እነ ራስ

1 G. Douin, Histoire du Kedive Ismael, pp. 1088—1043.



ወሬኛን አስረው ፣ የወሎን ባላባቶች ክርስትና አስነሥተው ኃይላቸውን በያለበት አጠንክረው ወደ ሐማሴን በታላቅ ግርማ በሚጓዙበትና ለሐማንሴና ለሠራዬ ራስ አሉላን ፣ ለአከለ ጉዛይ ራስ አርአያን በሾሙበት ሰዓት ፣ ለወልደ ሚካኤል እንደ ቀድሞው ሰው ሊተባበርላቸው አልቻለም ።

በተለይም ደግሞ ፣ የግብጽ መንግሥት በፊተኛው በከዲቭ ኢስማኤል ጊዜ መላ ኢትዮጵያን ለመውረርና ከሱዳን ጋር ለማደባለቅ ባለመበት ዘመን በየአውራጃው የነበሩትን የኢትዮጵያን መሳፍንት ፣ በሩቅ የሚገኙትን እነጂማን ፣ እነ ጉማን ፣ እነ እናርያን ሳይቀር በመላላክ በሚያባብልበት ወቅትና በቅርብ አጠገቡ ለነበሩት ለወልደ ሚካኤል በገንዘብም ፡ በጦር መሣሪያም ያደርገው የነበረው ሰፋ ያለ እርዳታ ባሁኑ በመጨረሻው ሰዓት አቋሟል ።

ከዚህ ቀደም እንደተባለው ፣ ከዲቭ ተውፊቅ ሥልጣን ሲጨብጥ ባገር ውስጥ እነ ኮሎኔል አህመድ ቤይ አራቢ ያነሡት ንቅናቄ የበለጠ ከችግር ላይ ስለ ጣለው፣ ይኸን ሁሉ ክስረትና ውድቀት ያስከተለውን የአባቱን የመስፋፋት ዓላማ ሰርዞ ወደቤቱ ሰብሰብ በማለት የቤቱን ጸጥታ ማረጋጋትን መረጠ ። በሱዳን የተነሣውንም የማህዲን ንቅናቄ ለማብረድ በቅድሚያ ካፄ ዮሐንስ ጋር መታረቅ አስፈላጊነቱ ስለ ተሰማው ፣ ለዚህ ሁሉ እንዲረዳው ጐርዶን ፓሻ የሚባለውን እንግሊዛዊ ለሱዳን አገረ ገዥነት ሾመ ። በሱዳን ላይ ጠቅላይ ገዥነት የተሾመ ሁሉ በዚያ አካባቢ ያለውን የግብጽ ጦር የሠፈረበትን ቦጐስን ፣ ሐባብንና ሰናሂትን ሁሉ በቁጥጥር ውስጥ ማድረግ ስለ አለበት ፣ በዚህ ጊዜ የንጉሠ ነገሥቱ ወደ ሐማሴን ጉዞና የራስ አሉላ ሹመት ያሠጋቸው ደጃች ወልደ ሚካኤል ከጐርዶን ፓሻ ጋር ግንኙነት ለማድረግና እርዳታ ለማግኘት ቢሞክሩ ነገሩ ሁሉ ተለዋውጦ አገኙት ። ስለዚህ ከግብጽ በኩል ተስፋ ያደረጉት እርዳታ በፍጹም ሳያስቡት ተስፋ አስቆራጭ ሆነባቸው ። እንዲያውም ቀድሞ በነራቲብ ፓሻ ዘመን የነበረው የግብጽ መንግሥት ገንዘብም ፣ የጦር መሣሪያም እንደልብ እየሰጠ የሚያበረታታቸው ሲሆን ያሁኑ አዲሱ ሹም ጐርዶን ፓሻ ፣ "ይኸን አድርግ ፣ ይኸን አታድርግ ፣ አገር አትዝረፍ ፣ ራስ አሉላን አታስቸግር" የሚል ትእዛዝ እየሰጠ በሌላ በኩል ደግሞ ፣ ይኸው እንግሊዛዊ የግብጽ አገረ ገዥ ካፄ ዮሐንስም ፣ ከራስ አሉላም ጋር በጐን እርሳቸው ሳያውቁ መላላኩን ከመንገድ ባስያዙት የልውውጥ ደብዳቤ ላይ ለመረዳት ችለዋል ። ስለዚህም በጣም ተስፋ ቆርጠው ፣ "ይኸስ እጄን ይዞ ለመታረቂያ ለመስጠት አይመለስም" በማለት ሳይወዱ በግድ ወዳፄ ዮሐንስ ለመግባት ይላላኩ ዠመር ።

ጎርደን ፓሻ የዚህን ጉዳይ በሰፊው ለመንግሥቱ ባስተላለፈው
የራፖር ማስታወሻ ውስጥ “ራቲቭ ፓሻ ‘ሁለተኛ የሐበሻን መሬት
(ሐማሴንን) እወስዳለሁ ብለህ እንዳትዋጋ’ ብሎ ለወልደ ሚካኤል
ቢነግረው አሾፈበት ። ራቲቭ ሔዶ እኔ ሥልጣን ስይዝ መጥቶ
አየኝ ። ለወታደሩም ስንቅ ሰጠሁት ። በኋላ ግን ወደ ሐማሴን እየዘ
ለቀ ዝርፊያ ስለጀመረ ፤ የወቀሳ ደብዳቤ ብጽፍለት ተቆጣ ። እን
ዲያውም በተገናኘን ጊዜ ከዮሐንስ እንዲስማማ ብነግረው ‘ይልቅስ
ዮሐንስ በምኒልክ ላይ ለመዝመት ወደ ሸዋ ሲሔድ እንውጋው’ ቢለኝ
እምቢ ስላልሁት ተጣላን . . . ” የሚል ይገኛል ። በዚህ ዐይነት
ወልደ ሚካኤል ከራቲቭም ከተከታዩም፤ ከጎርደን ፓሻም ስለተጣሉ፤
ያላቸው ምርጫ ተላልከው ካፄ ዮሐንስ ጋር መታረቅ ነበር ።

ስለዚህ በመስከረም ወር 1871 ዓ ም ላይ ደጃች ወልደ ሚካ
ኤል ወደ ራስ አሉላ ደብዳቤ ላከው ፤ “ወደ ንጉሠ ነገሥቴ ለመግባ
ትና ለመታረቅ አስቢያለሁና እርስዎ ያስታርቁኝ” የሚል ደብዳቤ ላኩ።
ራስ አሉላም ፤ ማናቸውንም ሁኔታ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ተነጋግረው
ከተወያዩ ወዲህ ፤ “መልካም ነው አስታርቅዎታለሁ” ብለው መሐላ
ጭምር ስለ ላኩባቸው ፤ ደጃች ወልደ ሚካኤል የመሐላውን የምሕረት
መልስ ተማምነው በታኅሣሥ ወር ላይ ወደ አክሱም ሔደው ከራስ
አሉላ ተገናኙ ። ራስ አሉላም መልካም አቀባበል አድርገው ከተገናኙዋ
ቸው በኋላ ፤ በዚሁ ዓመትና በታኅሣሥ ወር ላይ ወደ ደብረ ታቦር አም
ጥተው ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር አገናኙዋቸው ። ንጉሠ ነገሥቱም በደስታ
ተቀብለው ፤ “ምሬሃለሁ ከግብጾችም የተቀበልኸውን የራስነት ማዕርግ
መርቄልሃለሁ ፤ በራስ አሉላ ውስጥ ከመረብ ወዲያ ባለው አገር ሾሜ
ሃለሁ” ብለው አሰናበቱዋቸውና ከራስ አሉላ ጋር ወደ አከለ ጉዛይ
ተመልሰው ጉራዕ ላይ አብረው ሠፈሩ ።

ከዚህ በኋላ ራስ አሉላ ፤ “በቆላው በኩል ያለው አገር (ቦጐስና
ሐባብ ፤ መንሳ) ገና ለመንግሥታችን አልተገዛምና አብረን ሔደን
እንድንወጋው ሠራዊትዎን ይሰብስቡ” አሏቸው ። እሳቸውም ‘እሺ ’
ብለው በይፋ ተላልከው ሰዋቸው ሁሉ ሲሰበሰብ ፤ በራስ አሉላ ፈቃድ
የራስ ወልደ ሚካኤል ጦር ሁሉም ወደ ቦጎስና ወደ መንሳ ዘመተ ።
ወዲያውኑ በ1871 ዓ ም በነሐሴ ወር ላይ ፤ በራስ አሉላ ግፊት ፤ ከንቲባ
ኃይሉ የሚባሉት ያቶ ገብራይ ልጅ* “የጦር መሣሪያዎን ግማሹን
በምጥዋ ወደብ ግማሹን በየገዳሙ ደብቀዋል” ብሎ በራስ ወልደ

* የራስ ወ/ ሚካኤል የቅርብ ዘመድ ።



ሚካኤልና በልጅዬው በደጃች መስፍን ላይ ክስ አቅርበው ስለነበሩ
በዚሁ የተነሣ ፤ የምሕረት ቃል ተሰጥቷቸው የነበሩት ራስ ወልደ
ሚካኤል “ተረትተዋል” ተብለው በመስከረም ወር 1872 ዓ.ም.
ከልጆቻቸው ከደጃች መስፍንና ከልጅ ኃይለ መለኮት * ጋር በአ
ምባ ሰላማ ታሰሩ ። በዚህ ዐይነት ኃይለኛውና ስመ ጥሩው ወልደ
ሚካኤል አባ ጕሚዳ ከሁለት የወደቀ ዛፍ ሆነው የወደፊት ዕድላ
ቸው ግዞትና በእርጅና እቤት መዋል ሆነ ። ጀግንነታቸውን ፤ እምቢ
ባይነታቸውን የሚያወሳ “እምቢ አለ ወልዱ” በሚል የቅጽል ስም
የተቀረፀ የሽከላ ዘፈን ነበራቸው ።

በወሎና በሸዋ እንደ ቀናቸው ሁሉ ፤ ከመረብ ምላሽ ባለው አው
ራጃ በትውልዳቸው የሚመኩት የጸሐጸጋው ባለባት ደጃች ኃይሉና
የሐጸጋው ራስ ወልደ ሚካኤል በዚህ ዐይነት ሲወገዱ ፤ ዐፄ ዮሐንስ
ባላባትነት የሌላቸውን ራስ አሉላን በመሾም ግዛታቸው ፤ የጣልያን
ጦር በግብጽ እግር መጥቶ እስኪያደፈርሰው ድረስ ፤ ለጊዜው በደንብ
ጸና ። በዚህ ዐይነት ለበላይ መሪ ሁሉ ባላባትነት ካለው ተመኪ
ሹም ይልቅ ፤ መሪው ራሱ ከድህነት አንሥቶ በሹመት ያሳደገው የበ
ለጠ ይታመንለታል ማለት ነው ።የዚህንም ዐይነት ያሿሿም መስመር
ላገዛዛቸው ጥቅም ሲሉ ብዙ መሪዎች ይከተሉታል ። የሆነ ሆኖ ፤
ከዚህ ጊዜ ዠምሮ የወልደ ሚካኤል ገናናነት እየጨለመ ሲሔድ ፤ የራስ
አሉላ ዝነኛነት እንደ አጥቢያ ኮከብ እየደመቀ ይሔድ ዠመር ።

* በቀ.ኃ.ሥላሴ ጊዜ ራስ ተብለዋል ።

# ምዕራፍ ሐያ ስምንት

## ያፄ ዮሐንስና የኢጣልያ መንግሥት የመዠመሪያው ግንኙነት

የኢጣሊያ መንግሥት አንድነቱን ገና በደንብ ሳያቋቁም ባፄ ቴዎድሮስ ዘመን ከደጃች አገው ንጉሤ ጋር ተላልኮ እንደነበረ "ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት" በሚለው መጽሐፍ ላይ ጠቅሰናል ። ነገር ግን ፣ ከዚህ ወዲህ 1852 ዓ.ም. የኢጣልያ ንጉሣዊ መንግሥት በደንብ ከተቋቋመና የአሰብን ወደብ እጁ ካደረገ ወዲህ ወደ ኢትዮጵያ በልዩ ልዩ መልክ ዜጐቹን እየላከ አገሪቱን ያስመረምር ዠመር ።

የኢጣልያ ንጉሣዊ መንግሥት ሲቋቋም በያገሩ ተበትኖ የነበረው የኢጣሊያ ተወላጅ ሁሉ ፣ "አገርና መንግሥት አገኘን" እያለ በብዛት ከየጐረቤት አገር ተሰብስቦ መጥቶ ስለ ነበረ ፣ ለጊዜው የሰው ብዛትና የሥራ እጦት ባዲሱ የኢጣሊያ መንግሥት ላይ ክብዶበት ነበረ ። በተቻለ መጠን ሕዝቡ በሌላውም ክፍለ ዓለም በተለይ በአፍሪካ እየተበተነ ሥራ ማግኘትንና በንግድ መክበርን ፣ ሕዝቡም መንግሥቱም በትጋት የሚያስቡበት ጉዳይ ሆኖ ነበር ።

ስለዚህ በቅድሚያ በሃይማኖትም ፣ በንግድም መልክ እነ ሳፒቶ ፣ እነ ፒያጃ ፣ እነ ስቴላ ፣ እነ ናሬቲ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ እየገቡ ከመሳፍንቱና ከሕዝቡም ይተዋወቁ ዠመር ። ለአሰብ ወደብ የኢጣሊያ መንግሥት የሾሟቸው እነ ብራንኪ በመልእክት ካፄ ዮሐንስ ጋር መወዳጀት ዠመሩ ። በተለይ ጃኮሞ ናሬቲ የሚባለው በ1862 ዓ.ም. ወደ ዐፄ ዮሐንስ መጥቶ እንደ ደንበኛ ታማኝ አሽከር ሆኖ በአናጢነት ሙያው የመቀሌን ቤተ መንግሥትና የሚቀመጡበትን ዙፋን አሳምሮ በመሥራት አስደሰታቸው ። ወደ ዐፄ ዮሐንስ የሚመጡትንም የኢጣልያ ተወላጆች ሁሉ እያገናኘ በንጉሡ ዘንድ ያገሩ ሰዎችና መንግሥቱ እንዲታወቁና እንዲወደዱ እያደረገ በርሱም ሰበብ ወንድሙ ጆሴፒ ናሬቲ ወደ መቀሌ መጥቶ ንጉሠ ነገሥቱን ያገለግል ዠመር ።

ናሬቲ ምንም የኢጣሊያ ተወላጅና በዘሩ አውሮፓዊ ቢሆን ፣ በተለይ ቤተ መንግሥቱንና ዙፋናቸውን ሠርቶ ካስደሰታቸውና የሰሎሞንን ፒሻን ከሸለሙት ወዲህ በበዓል ቀን እንግዳም በመጣ ጊዜ

እንደ ኢትዮጵያ መኰንን ጃኖ ወይም ኩታውን አደግድጐ ወደ ንጉሠ ንገሥቱም ዘንድ ገባ ወጣ እያለ ትእዛዝ እየተቀበለ ሲያስተናብር ብዙ የውጭ አገር ሰዎች እንዳዩት በየመጽሐፋቸው ገልጸውታል ።[1] ባለቤቱ ቴሬዛ ትባል ነበር ። ዶክተር ሽምፐር የሚባሉት የጀርመን የዕፀዋት ሊቅ ካንዲት የኢትዮጵያ ወይዘሮ (ወለተ ሩፋኤል) የወለዷት ናት ። ቴሬዛ የአማርኛና የኢጣሊያንኛ ቋንቋ ስታውቅ ጃኮም ናሬቲ በመጠኑ አማርኛም ዐረብኛም እያደበላለቀ ይናገር ነበር ይባላል ።

በዚሁ ሰዓት ፣ በኢጣልያ አገር በሮማ ፣ በጀኖቫ ፣ በቶሪኖ በሚላኖ ብዙ እንዱስትሪዎች ስለነበሩ እነዚህ እንዱስትሪዎች የሚያመርቷቸውን ሸቀጦች የሚሸጡበት አገር ብጣም የሚፈልጉበት ሰዓት ነበረ ። ሸቀጡን በንግድ መልክ ከመላክ በፊት በትድሚያ በኢትዮጵያ ከነበሩት መሳፍንትና ነገሥታት መወዳጀትና ሁኔታውን መመርመር ያስፈልጋል ተብሎ ሲመክርና ሲዘክር ቆይቶአል ። ቀደም ብሎ እነ ጆሴፒ ሳፒቶ በስሜን ኢትዮጵያ ፣ እነ ሳሊምቤኒ በጐጃም ፣ እነ አባ ማስያስና እነ አንቲኖሪ ወደ ሸዋ ገብተው ስለነበር ፣ በእነርሱ አማካይነት ፣ "ከሁሉ የበለጠ የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ባገሩ የአውሮፓን ሥልጣኔ ለማስገባትና ንግድን ለማስፋፋት ፈቃደኛ ነው" የሚል ወሬ በአውሮፓ ተስፋፍቶ ነበር ።"ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት" በሚለው መድሐፍ ላይ እንዳነብበነው ፣ አባ ሚካኤል የሚባሉ በቱርክ አገር የኖሩ ኢትዮጵያዊ ከምኒልክ ወደ ኢጣልያ ንጉሥ፣ ሙሴ ፒዬር አርኑ የሚባለው የፈረንሳይ ተወላጅ ወደ ካይሮም ፣ ወደ ፈረንሣይም አገር እየሔዱ ሁለቱም ስለ ምኒልክ ፕሮፓጋንዳ ማድረግ ዠምረው እንደነበረ ይታወሳል ።

ስለዚህ በሚላኖ የነበረው የንግድ ምርመራ ማኅበር ወደ ሸዋ ሔዶ የዚህኑ የንግድ ጉዳይ የሚመረምርና ለምኒልክ የተዘጋጀውን ልዩ ልዩ ገጸ በረከት የሚያቀርብ አንድ የመልእክት ጓድ እንዲመረጥ ተደረገ ። ለዚህም ተግባር የሱዳንና የኢትዮጵያን ሁኔታ ያውቃል ተብሎ ፒሌግሪኖ ማቲዎቺ ተመረጠ ። ከርሱም ጋር ጉስታቮ ቢያንኪና ሌሎችም ተደልድለውና ተዘጋጅተው በ1871 ዓ.ም. በኅዳር ወር ከሚላኖ ተነሥተው ወደ ሸዋ በሚያደርሰው ወደብ በዘይላ ወይም በአሰብ በማለፍ ፈንታ በታኅሣሥ ወር ከምጥዋ ወደብ ደረሱ ። አሳባቸው በስሜን ኢትዮጵያ አድርገው ትግራይንና ጐጃምንም ጐብኝተው ወደ ሸዋ ለማለፍ ነበር ።

1 A. Del Boca, Gli Italiani in Africa Orientale, pp. 83—100.



በዚህ ጊዜ ውስጥ ዕውቁና ያፄ ዮሐንስ ባለሟል የነበረው ጃኮሞ ናሬቲ ከወንድሙ ከጆሴፔ ናሬቲና ከሚስቱ ከቴሬዛ ጋር በካይሮ የዕረፍት ጊዜያቸውን አሳልፈው ወደ ዐድዋ ሊመለሱ ሲሉ ከነዚህ መልክተኞች ጋር በምጥዋ ወደብ ተገናኝተው ተወያዩ ። ናሬቲ በዚያን ሰዓት የመላዋ ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ዮሐንስ መሆናቸውን ፣ ንጉሥ ምኒልክም ወዳፄ ዮሐንስ ገብተው ታማኝነታቸውን ማረጋገጣቸውን ገልጦ ወደ ምኒልክ የመሔዱን አሳብ እንዲሰርዙ አድርጎ ወደ ዋናው ገዥ ወደ ዐፄ ዮሐንስ ቢሔዱ ለኢጣልያ የበለጠ ጥቅም የሚሰጥ መሆኑን በምክር አስገንዝቦ እሺ ከአሰኘ በኋላ ፣ ወዳፄ ዮሐንስ የነዚህን መልክተኞች መምጣት ፣ የነርሱን ደብዳቤ ጨምሮ ፣ በጽሑፍ አስታወቀ ።

ለዚህ መልስ ካፄ ዮሐንስ ፣ "ያንተና የዘመዶችህ ደብዳቤ ደርሶኛል ። ቀድሞ ፈረንሳዮችና እንግሊዞች ሲመጡ ፣ መልካምነታቸውን ገልጸውልኝ ወዳገር ከገቡ በኋላ ለመንግሥቴ እንቅፋት ይፈጥሩብኛል ፣ የሃይማኖትም ችግር ይፈጥሩብኛል ፣ አንተን ስለማውቅህ ሌሎቹም ያንተ ወገኖች እንዳንተው መልካም ይመስሉኛል ፣ አገር የአምላክ ስለሆነ ለክፉዎች ካልሆነ በቀር አገሬን ለማንም አልዘጋም ። ስለዚህ እነዚህን ደጐች ኢጣልያኖች ለማየትና ለመገናኘት እወዳለሁ" የሚል መልስ መጣለት ። የደብዳቤውንም ቃል ሚስትዮዋ ቴሬዛ ናሬቲ ከአማርኛ ወደ ኢጣልያንኛ ተረጐመችላቸውና ጉዞው ከምጥዋ ወደ ዐድዋ ተዠመረ ።ዐድዋ ገብተው ጥቂት ጊዜ እንዳረፉ ንጉሠ ነገሥቱ ወደሚገኙበት ወደ ደብረ ታቦር መጥተው በግንቦት 20 ቀን 1871 ዓ ም ሲደርሱ ለክብራቸው አምስት ጊዜ መድፍ ተተኰሰላቸው ።

ከዚያም በዚሁ በናሬቲ መሪነት ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀርበውና፣ እንዳገሩ ልማድ እጅ ነሥተው ለምኒልክ ያዘጋጁትን ዲስኩር በርሳቸው ፊት ተናግረው ፣ ለምኒልክ የያዙትንም ገጸ በረከት አንድ ጠበንጃ ፣ ሁለት ሽጉጥ ፣ አንድ የብረት አልጋ ፣ አንድ የወርቅ ዘውድ ከመከዳ ጋር ፣ የሐርና የከፋይ ጨርቃ ጨርቅና መሐረብ ፣ ሳሙና ፣ ክብሪት ፣ መጠጥ የያዙ ጠርሙሶች አቅርበው ንጉሡን አስደሰቱ ። ቀጥሎም ወደ ማረፊያቸው ሔደው ዕረፍት ካደረጉ በኋላ ፣ በአምስተኛው ቀን የመልእክቱን ዓላማ የሚገልጥ ጽሑፍ ዋናው መሪ ሰጣቸው ። ያንንም ንጉሠ ነገሥቱ በቴሬዛ አማካይነት ትርጕሙን በአማርኛ ከሰሙት በኋላ ፣ ስለንግዱ ጉዳይ "እሺ" ብለው እርሳቸውም ስለ አውሮፓ ሁኔታ ፣ ስለ ኢጣልያ ንጉሥ ስለ ኡምቤርቶ ጤንነትና ሁኔታ ጠያይቀዋቸው ሲጨርሱ ፣ በበኩላቸው ንጉሠ ነገሥቱም ለኢጣልያ ንጉሥ ደብዳቤና ገጸ በረከት ለመላክ ይዘጋጁ ዠመር ።

ጉስታቮ ቢያንኪና ሌሎችም በኢትዮጵያ ሲቀሩ ወደ ኢጣሊያ አገር ለሚመለሰው ለማቲዎቺ ሁለት የአንበሳ ግልገሎችና አንድ ደብዳቤ ለኡምቤርቶ እንዲሰጥ አስረከቡት ።

ለኢጣልያ ንጉሥ የላኩት የደብዳቤው ቃል ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

"መልእክት ዘሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት. . . ይድረስ ከንጉሥ ኡምቤርቶ ፈተኛው ዘኢጣልያን* እንዴት ነዎ ። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ። ከዚህ በፊት ደብዳቤ ያልጻፍኩለዎ መንገዱ በእስላም እጅ ተዘግቶብኝ ነው ።** አሁን እንኳን ይህን ወረቀት የጻፍኩለዎ ከኢጣልያን በመጡ ነጋዶች ምክንያት ነው ። ሌላ ጉዳይም እንዳልጽፍልዎ በፊት ወዳጅነትዎን አገኘው ብዬ ነው ። አሁንም የፍቅር ምልክት ይሆን ዘንድ አንድ ተባት (ወንድ)ና አንድ እንስት (ሴት) ሁለት የእንበሳ ጉቺላ (ግልገል) ሰድጃለሁ ። ተጽሕፈ በጐንደር ከተማ ሰኔ 14 ቀን 1871 ዓ.ም.

በዚህ ዐይነት ፣ እኔ ማቲዎቺ "በሰሜን በኩል አድርገን ፣ ወደ ሸዋ ዘልቀን ፣ ከምኒልክ ጋር የንግድ አሳብ እንለዋወጣለን ብለው ዐቅደውት የነበረውን (አሳብ) ጃኮሞ ናሬቲ ምንም እንኳን በዚህ ጊዜ ዮሐንስና ምኒልክ በስምምነት ላይ መሆናቸውን ቢያውቅ ፣ የመልከተኞቹ ወደ ሸዋ መሔድ ንጉሠ ነገሥቱን ቅር እንደሚላቸው በመገመት በምክር አስቀራቸው ። ስለዚህ ማቲዎቺ በምርመራና በአደን ምክንያት የጣናን ሐይቅና ጐጃምን ጐብኝቶ ከንጉሠ ነገሥቱም ጋር የንግዱን ልውውጥ ተነጋግሮ በየጊዜው ንጉሡ ግብር በሚያገቡበት (በሚያበሉበት) ሰዓት እየተጠራ ተጋብዞ ሲጨርስ ፣ በሰኔ ወር ላይ ከዚህ በላይ የተጻፈውን ደብዳቤና ሁለቱን የአንበሳ ግልገሎች ተረክቦ ከንጉሠ ነገሥቱ ተሰናብቶ በምጥዋ በኩል አድርጎ ወዳገሩ ተመለሰ ።

ጉስታቮ ቢያንኪ ግን ፣ ከማቲዎቺ ተለይቶ አንድ ጊዜ ወደ ጐጃም ፣ አንድ ጊዜ ወደ ሸዋ እየተዘዋወረ ብዙ ጊዜ እዚያው መቀሌ ንጉሠ ነገሥቱ ባሉበት ቆየ ።

ማቲዎቺ ወደ እገሩ ከተመለሰ በኋላ ፣"በሐበሻ እገር" በሚል ርዕስ ከንግዱ ግንኙነት በቀር ስለ ጉዞውና ስላየው ነገር ሁሉ ባሠፈረው

* ኡምቤርቶ ቀዳማዊ ለማለት ነው ።

** የግብጾቹን አያያዝ መጥቀሳቸው ነው ።



ጽሑፍ ላይ ስለ መልካቸው እንደዚህ ይላል ። "ዮሐንስ የዐርባ ዓመት ሰው ናቸው ። ቆንጆ ሳይሆኑ አስደሳች መልክ አላቸው ። ከዕድሜያቸው በላይ የሸመገሉ ይመስላሉ ። ባለፈው ብዙ የሁካታ ፣ የእድማና የጦርነት ዘመን እንዳሳለፉ ከፊታቸው ላይ ይነበባል ። የጢማቸው ጠጉር እጭርና ትንሽ ነው ። የራስ ጠጉራቸው ተጠላልፎ ተሠርቷል ።" *...[1]

ማቲዎቺ በሐቅ መንገድ ኢትዮጵያና ኢጣልያ ተስማምተው ንግድ እንዲለዋወጡ ከልቡ ሲመኝ ፣ ቢያንኪ ግን የሻምበልነት ማዕረግ የነበረው ወታደር ስለነበረ ፣ ዋና ምኞቱ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ የገዥነት ሥልጣን የምታገኝበትን መንገድ ያውጠነጥን እንደነበረ የሁለቱም አሳብ ከየመጽሐፋቸው ላይ ይነበባል ።

በመካከሉ ሸዋንና የኢትዮጵያን ደቡባዊ ክፍል ለመጐብኘት የተመደቡት አንቶኒዎ ቼኪና ኪያሪኒ ጀዎቫኒ የሚባሉት የጉስታቮ ቢያንኪ ጓደኞቹ በጌራ ሲያልፉ የጌራ ባላባት (ጌራ ጌኔ) ሁለቱንም የምኒልክና የጐበና ሰላዮች ናችሁ ብሎ አስሯቸው ስለ ነበረ ፣ ይኸንኑ ላዩ ዮሐንስ አመልክቶ ካዬ ዮሐንስ ወደ ራስ አዳል ትእዛዝ አስተላልፎ በራስ አዳል ማስፈራራት ከሁለቱ የኢጣልያ አገር ጐብኝዎች አንዱ ኪያሪኒ ጀዎቫኒ እዚያው ጌራ ሲሞት ፣ አንቶኒዎ ቼኪ ተለቆ ወደ ሸዋ እንዲመጣ አደረገ ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት ፣ ቢያንኪ ካዬ ዮሐንስ ተላምዶ የንጉሠ ነገሥቱን መልእክት ይዞ በ1873 ዓ ም ወደ ኢጣልያ አገር ተመልሶ በ1875 ዓ ም እንደገና ወዳዬ ዮሐንስ ከኮንት ሳሊምቤኒ ፣ ከዲያናና ከሞናሪ ጋር መጥቶ ባለሟል ሆነ ። በእርሱም አማካይነት ንጉሠ ነገሥቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሲኞር ፓስኩአሌ ማንቺኒና ለሌሎች አራት የኢጣልያ ባለሥልጣኖች የሰሎሞንን ኒሻን ፣ ለራሱም በቅሎ ከሙሉ መሣሪያዋ ጋር እንዲሁም ጦርና ጐራዴ ከሙሉ ልብስ ጋር ሸልመው መልሰው ወደ ኢጣልያ ሊሰዱት ሲዘጋጁ፣ በቅድሚያ ንጉሠ ነገሥቱ ለኢጣልያ ንጉሥ እንደዚህ የሚል አንድ ደብዳቤ አዘጋጁ። "መልእክት. . . ለትግራይም ፣ለሸዋም ፣ ለሌላው ለአማራውም አገር የሀገርዎ መንግሥትም ፣ የኢጣልያ ሰው ጉዳይ ያለው ሁሉ በአርሆና በጨው በኩል እየወጣ (እያለፈ) ወደ ከተማዬ ወደ መቀሌ እየገባ (እየመጣ ጉዳዩን ያደርጋል ፣ ይፈጽማል) ከአቶ ቢያንኪ ጋር ተማክሬ ወረቀት ጽፌልዎ ነበር ። እንግዲህ ግን አቶ ቢያንኪን ወደ ሌላ ጉዳይ

* ሹሩባ ነው ማለቱ ነው ።

1 P. Matteucci, In Abyssinia, pp. 11—50.

አይስደዱብኝ እየተመላለሰ የእርስዎና የኔ ተግባር (ጉዳይ) በእርሱ እንዲፈጸም . . .”

ዳሩ ግን ፡ ጉስታቮ ቢያንኪ በ1876 ዓ.ም. “ወደ አውሳ ሐጂ አገር እመረምራለሁ ፡ መንገድም እከፍታለሁ” ብሎ ከሁለት ጓደኞቹ ከዲያና ከሞናሪ ጋር ጉዞ ጀመረ ። “አገሩ በረሃማና ውሃ የሌለበት ለሕይወትም አደጋ ያለበት ነው” ብለው ንጉሠ ነገሥቱም ፡ ሌሎቹም የመከሩትን ሳይሰማ መሪ ይዞ ወደ ማኸል በረሃ ሲደርስ መሪው ከድቶት ጥሎት ጠፋ ። ደንከሌዎቹም አግኝተው ከሁለቱ ጓደኞቹ ጋር ተደብድቦ የሕይወቱ ፍጻሜ ሆነ ። በጐን ጭፍራ ልኮ ያስደበደበ ውም ያገሩን መመርመር የማይወደው ራሱ የአውሳው ባላባት መሐመድ አንፋሪ ነው ይባላል ።[1]

እንደዚሁም ፡ ዐፄ ዮሐንስ በኋላቸው በእንግሊዝና በኢጣልያ ውስጠ ሽርክና የሚዘጋጅባቸውን ወረራ በምንም ዐይነት ሳይጠረጥሩ የኢጣልያን ንጉሥ ወዳጅነት ያገኙ መስሏቸው ገጸ በረከትና ደብዳቤ አንድ ጊዜ በማቲዎቺ እጅ ፡ ዳግመኛም በዚሁ በጉስታቮ ቢያንኪና ብራንኪ ጄዎቫኒ በሚባለው አሰብ በሚቀመጠው የኢጣልያ አስተዳዳሪ (ኮሚሳሪዮ ቺቪሌ) አማካይነት በቅንነት መንፈስ ይለዋወጡ ነበር ። ዐፄ ዮሐንስ በዚህ ሰዓት ግብጾችን ሁለት ጊዜ ድል ካደረጉና ምኒልክንም ካስገበሩ በኋላ ፡ በፊታቸውም ሁሉም ነገር የተቃና ሆኖ በሰሜን በኩል በግብጽ ይዞታ ሥር የነበሩትን ቦጎስንና ሰናሂትን ለመረከብ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር የሚላላኩበት ጊዜ ነበር።

ነገር ግን ፡ ንጉሠ ነገሥቱ በቅንነት ወዳጅነቱን ሲፈልጉ የኢጣልያ መንግሥት ባንድ ወገን በግብጽና በቱርክ እግር ጦር ልኮ ምጥዋንና አካባቢውን ለመያዝ እየተዘጋጀ ፡ በሌላ በኩል ወዳጄ ዮሐንስ በርከት ያለ ስጦታና ወዳጅነት አዘል የሆነ የተንኰል ደብዳቤ በመላክ ለማዘንጋት ይጣጣር ነበር ። የእንግሊዝ መንግሥትም በበኩሉ ፡ ዐፄ ዮሐንስ በርሱ ላይ የነበራቸውን መተማመን እያወቀ ከግብጾች ጋር በሒዊት አማካይነት ሲያዋውላቸው የኢጣልያን የወረራ እሳብ ምልክቱንም እንኳን ሳይገልጥላቸው፥ የራሱን ጥቅም ብቻ በማደላደል በሱዳን በኩል ለገጠመው ችግር እርሳቸውን መሣሪያ አድርጓል ። የሁለቱም መንግሥታት ተንኰል ሊገለጥ የቻለው በተከታዩ ዓመት የኢጣልያ ጦር ምጥዋ ገብቶ ወደ ዶጋሊ ሲስፋፋና ራስ አሉላ ከኢጣልያ ጋር ዶጋሊ ተዋግተው ባሸነፉበትና የእንግሊዝ መንግሥት እንደ አስታራቂ ገብቶ ለኢጣልያ አድላዊነቱን በቃልም በጽሑፍም በገለጸበት ጊዜ ብቻ ነበር ።

1 Guido Cortese, Eritrea, pp. 28—30.






መልእክት፡ ዘሥዩመ፡ እግዚአብሔር፡ ዮሐንስ፡ ንጉሠ፡
ነገሥት፡ ንጉሠ፡ ጽዮን፡ ዘኢትዮጵያ፡ ይድረስ፡ ከን
ጉሥ፡ ዑምቤርቶ፡ ፈተኛው፡ ዘኢጣልያን፡፡ እንዴት
ነም፡፡ እኔ፡ እግዚአብሔር፡ ይመስገን፡ ደኅና፡ ነኝ፡፡
ከዚሀ፡ በፊት፡ የብጄቢ፡ የልኳፍኩለም፡ መንገኜ፡ በ
ሊሳቄም፡ እጅ፡ ተዘጋጅብኝ፡ ነው፡፡ እሁን፡ እንኳ፡ ይህ
ን፡ ወረቀት፡ የጻፍኩለም፡ ከኢጣልያን፡ በመጡ፡ ነገ
ደች፡ ምክንያት፡ ነው፡፡ ሌላ፡ ጉዳይ፡ ምንም፡ እንዷልጅፍ
ለም፡ በፊት፡ ወዳጅነት፡ እንጂ፡ ብዬ፡ ነው፡፡ እሁ
ንም፡ የፍቅር፡ ምልክት፡ ይሆን፡ ዘንድ፡ አንድ፡ ተግት
እንድ፡ እንስት፡ ሁለት፡ ደንበኛ፡ ጉቾ፡ ለጅጃ ለሁ፡
ተጽሐፈ፡ በጕንደር፡ ከተማ፡ ፲ወ፬ለ፡ በ፲ወ፰፻
ርወ፬ ፍ መት፡ ምሕረት፡፡ ፡፡ ፡፡ ፡፡ ፡፡ ፡፡ ፡፡

ዐፄ ዮሐንስ ለኢጣሊያው ንጉሥ ለዑምቤርቶ የጻፉት

(አርኪቪዮ ስቶሪኮ ዴ ሶፕሬሰ ሚኒስቴሮ ዴል አፍሪካ ኢታሊያና ፡ ሮማ)



ዐፄ ዮሐንስ ለኢጣሊያ ቆንሲል ለብራንኪ የጻፉት

(ከአርኪቪዮ ስቶሪኮ ዴ ሶፕሬሶ ሚኒስቴሮ ዴል አፍሪካ ኢታሊያና ፣ ሮማ)

# ምዕራፍ ሐያ ዘጠኝ

## የኢጣሊያ መንግሥት የመዠመሪያው አገባብ በአሰብ

የኢጣልያ መንግሥት ንግዱን የሚያሠራጭበት ፣ ሕዝቡን የሚያሠፍርበት ፣ ራሱም የሚጠቀምበት ቅኝ አገር የፈለገው ፣ ካሚዮ ካቩር ጠቅላይ ሚኒስትር ከሆነበትና ቪክቶር አማኑኤል ገና የሣርዴኛ ንጉሥ ብቻ ከሚባልበት ከ1857 ዓ.ም. ዠምሮ ነበር ።

በፈቃዳቸውም እየወጡ ፣ ከመንግሥትም ፣ ከሮማ ሊቃነ ጳጳሳት ከቫቲካን ድርጅትም እየተላኩ በኢትዮጵያ የተሠራጩት አገር መርማሪዎች ፣ የአልአዛሪስትና የካፑቺን ፣ የጄሱዪት ሚሲዮን አባሎች ፣ በተለይ ደግሞ በሮማ የኢጣሊያ የዢዎግራፊያ ምርመራ ማኅበርና በሚላኖ የንግድ ምርመራ ድርጅት ከተቋቋመ ወዲህ ከነዚህ ከሁለት ድርጅቶች ለስንቅ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ፣ ለየመሳፍንቱና ለየባላባቱ የሚቀርበውን ገጸ በረከት ፣ ለመከላከያ የሚሆነውን ሽጉጥና ጠበንጃ ፣ ለአደን የሚያስፈልገውን የረሽ መሣሪያ እየያዙ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ዠመሩ ። ከመጡ በኋላም የየመሳፍንቱን አቅዋም ፣ የሕዝቡን ጠባይ ፣ የኢትዮጵያን አውራጃ መውጫ መግቢያውን ፣ ወንዛወንዙን ፣ የአየሩን ጠባይ ፣ የመሬቱን ሀብት እየተዘዋወሩ በመጽሐፍና በራፖር መልክ ለየላካቸው ድርጅት እያዘጋጁ ያቀርቡ ነበር ።

የጥናት ራፖራቸው ሁሉ በደንብ በየክፍሉ እየተመዘገበ በከፍተኛ ደረጃ ይጠና ዠመር ። የኢጣሊያ ያንድነታቸው ጉዳይ ከ1857 ዠምሮ በተለይም በ1860—70ዓ.ም. ድረስ እየጸና መጥቷል ። በ1870—80ዓ.ም. ድረስ የነበሩት ባለሥልጣኖች አሁንም መልክተኞችን ወደ ኢትዮጵያ ወዳፄ ዮሐንስም ፣ ወደ ንጉሥ ምኒልክም ፣ ወደ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ፣ ወደ ሌሎቹም እየላኩ በገጸ በረከትና በሙያ አገልግሎት በኩል እየገቡ በመገናኘትና ባለሟል በመሆን ፣ ወደቅኝ አገዛዝ የሚመራውን የምርመራውንና የስለላውን ሥራ በአዲስ ኃይል ይከታተሉ ዠመር ።

ይሁን እንጂ ፣ በቅኝ አገር ፍለጋው ጉዳይ የኢጣልያ ባለሥልጣን የነበረው ሁሉ ፣ በውጭም ሆነ በምክር ቤትም ውይይት ላይ አልተስማማበትም ። ካሉት የፖለቲካ ቡድኖች ግማሹ ኢጣልያ እንደ እንግሊዝ፣

እንደ ፈረንሳይ ፣ እንደ ፖርቱጋል ፣ እንደ ኤስፓኝ በቀጥታ ይዛ የምታስተዳድረውና በሀብቱ የምትጠቀምበት የቅኝ ግዛት ያስፈልጋታል ሲል ግማሹ ክፍል ደግሞ ፣ በተለይ የግራው ክፍል የፖለቲካ ቡድን አባሎች አዲሲቱን አገራችንን በኢንዱስትሪና በእርሻ በጠቅላላው በኢኮኖሚ እናጠቁም ። ያለንን መጠነኛ ሀብታችንንና የሰው ጉልበታችንን ለቅኝ ግዛት ፍለጋና ለጦርነት በማዋል ፈንታ ላገራችን ጉዳይ ብቻ እናውለው ሲሉ ፣ የቀሩት ደግሞ ከየሚሲዮናውያኑ እነሳፔቶ — እነስቴላ ፣ እነ ማሳያ ፣ ከአገር አሳሾቹ እነቢያንኪና እነቸኪ በሚያቀርቢቸው ጽሑፎች የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሀብት ብዛት ፣ የወንዛወንዙን የደሴቱን ፣ የተራራውን የዕፀዋቱን ውበት ፣ የቀንድና የጋማ ከብቱን ብዛት ስለሚያስገነዝባቸው ፣ ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና ከየመሳፍንቱ ጋር በሐቅና በቅንነት በመዛመድ በልማትና በንግድ ተዋውለን አገራችንን ማክበር እንችላለን ይሉ ነበር ።

ይሁን እንጂ ፣ የነዚህ የመጨረሻዎቹ ቅን አስተያየት ፣ እየተዳከመ በዚህም ዘመን የስዊዝ ቦይ ሊከፈት በተቃረበበት ሰዓት እንግሊዝ በግብጽ ፣ በሱዳን ፣ በበርበራ ፣ በአደን ፣ ፈረንሳይ ደግሞ ፣ በታጁራና በአቦክ(ጅቡቲ) መግባት ስለ ጀመሩ ፣ የአውሮፓ መንግሥታት ዐይናቸውን በቀይ ባሕር ላይ አበከረው ጣሉ ። የኢጣልያ መንግሥትም ከዚህ አንጻር ደካማነቱን በመገንዘብ ፣ እንደነዚህ መንግሥታት በመርከብ ጦር ልኮ ወደብ በኃይል የመያዙን ነገር ለኋላ ጊዜ አቆይቶ ፣ ከባላባቶች ጋር በመዛመድ በግዥ መንገድ ለጊዜው ጠቃሚነቱ ያልታወቀና ለወደፊት ግን ፣ በወደብነት የሚያገለግል ቁራጭ ቦታ ለማግኘት ይጣጣር ዠመር ።

ይኸውም እርምጃ በመንግሥት ደረጃ ሳይሆን በግል እንዲሆን ታሰበ ። የዚህንም ጉዳይ ከሁሉ ይበልጥ ያውጠነጠነው ዡሴፔ ሳፔቶ የሚባለው ቀደም ብሎ የላዛሪስት ሚሲዮናዊ የነበረ በወቅቱ ግን ፣ በፍጹም ወደ ሹመትና ወደ ንግድ ያዘነበለ ነበር ። ዡሴፔ ሳፔቶ ገና የኢጣልያ አንድነት ሳይመሠረት ከኢጣልያ አገር ተነሥቶ በመጋቢት 3 ቀን 1830 ዓ.ም. ወደ ምጥዋ መጣ ። ከዚያም ዐልፎ ወደ ዐድዋ ደረሰ ። ይኸም ጊዜ ፣ የመሳፍንት ዘመን ወደ መጨረሻው የተቃረበበት፣ በጐንደር ራስ ዐሊ ፣ በስሜንና በትግራይ ደጃች ውቤ ፣ በሸዋ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የነበሩበት ጊዜ ነበር ። በመጀመሪያ አመጣጡ የወንጌል መልእክተኛ ሆኖ ነበር ። አንዳንድ ጊዜ ከረን ላይ ከተመሠረተው ስቴላ ከሚባለው ሚሲዮናዊ ጋር ፣ ብዙም ጊዜ ብቻውን ሆኖ በሰሜን ኢትዮጵያ በመንሳና በበጎስ እየተዘዋወረ ሲያስተምርም ፣ ቋንቋም ሲያጠና ፣ አገር ሲመረምር ከ1840 ዓ.ም. ዠምሮ እስከ 1870 ዓ.ም. ድረስ ረዥም የሠላሳ ዓመት ጊዜ አሳለፈ ።



በዚህ ጊዜ ፣ የኢጣልያ አንድነት ስለ ተቋቋመ እርሱም በግብጽ በኩል ወዳገሩ ይመላለስ ነበር ። የስዊዝ ቦይም በመከፈቱ ተደስቶ ፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ ወደፊት የሚጠቀሙበትን በቀይ ባሕርና በአደን ሰላጤ በየወደቡ መስፋፋታቸውን በመመልከት ፣ የአዲሲቱ ኢጣልያ መሪዎችም ወደዚሁ ጉዳይ እንዲያዘነብሉ በቃልም በጽሑፍም ያሳስብ ዠመር ። ከየባለሥልጣኖቹም እየታዘዘ ፣ በጀትም እየተሰጠው በዚህ ጉዳይ ሰፊ ምርመራ እንዲያደርግ ብዙዎቹ ያበረታቱት ዠመር ።

በኢጣሊያ መንግሥት ባለሥልጣኖች እየታዘዘም ፣ በራሱም ፈቃድ እየተነሣሣ ኢጣልያ በቀይ ባሕር ዳርቻ አንድ ወደብ የምታገኝበትን መንገድ ሲፈላለግ ከሁሉ ቀና መስሎ የታየው አሰብ ስለነበረ ፣ ቀደም ብሎ ከአካባቢው ባላባቶች ጋር በገጸ በረከት መወዳጀት ዠመረ ።

ስለዚህ በ1861 ከአድሚራል ጉሊዮልሞ አክቶን ጋር በመርከብ ወደ ቀይ ባሕር መጥቶ ሁሉንም አብረው እየተመካከሩ ከመረመሩ በኋላ ፣ አገር የመያዙን ጉዳይ የኢጣልያ መንግሥትም ፣ የፋብሪካ ባለቤቶችም ስለ ተስማሙበት ለሩባቲኖ የመርከብ ኩባንያ አምስት መርከቦች የሚሠራበት 4.000.000 ሊሬ ተፈቀደለት ።*

በዚሁ ጊዜም ለዡሴፔ ሳፔቶ ለወደቡ ግዥና ለሌላውም ወጭ የሚያደርገው 80.000 ሊሬ ለብቻው ተፈቀደለትና አፍሪካ በሚባለው መርከብ እንደገና ከጓደኛው ከአንድሬያ ቡዘሊኒ ጋር ሆኖ ወደ አሰብ መጣ ። ባንድ ወገን ሁለቱ የኢጣሊያ ባለሥልጣኖች በሌላው ወገን የአሰብ ጌቶች የሆኑት የራሄታ ባላባቶች ሐሰን ቤን አህመድ — አብዶላ ሻሂሚ ፣ ኢብራሂም ቤን አህመድ ሻጮች ፣ ምስክሮች ከኢጣልያኖቹ ወገን ኦራሲዮ እንቲኖሪና ካፒሎ ግራንዶኒ ሲሆኑ ፣ ከሻጮቹ ወገን አብዶላ ኤበንና አሊ ኬሲ ምስክሮች ሆነው ከቀይ ባሕር ዳር የሚገኘውን በራሲ ሉማህና በአላላ መካከል የሚገኘውን የባሕር ዳር መሬት በ3.100 ማሪያ ቴሬዛ ብር መሸጣቸውን ፣ ኢጣልያኖቹም መግዛታቸውን ከተስማሙ በኋላ ፣ ውሉ በኢጣልያንኛና በዐረብኛ ቋንቋ ተጽፎ ተፈራረሙ ። በመንግሥት ደረጃ የሆነ እንደሆነ የፈረንሳይን ወይም የግብጽንና የቱርክን መንግሥት እንዳያስቆጣ ተብሎ ግዥው በግለኛው በሲኞር ራፋኤሊ ሩባቲኖ የመርከብ ኩባንያ ስም መሆኑ በውሉ ላይ ተጠቅሷል ።[1]

* 20 ሊሬ አንድ የማሪያ ቴሬዛ ብር ሲሆን 200.000 ብር ይሆናል ።

1 G. Cortese, Eritrea‘ pp. 20—22. Bardi, Pionieri E Soldati, Commissario Civile pp. 59—68 ,

ኢጣልያኖቹ የያዙት ገንዘብ የአገራቸው ሊሬ ስለነበረ ፣ ገዥዎቹም
ሻሙቹም ወደ አደን ከተማ ሔደው ምንዛሪውን እንደ ሒሳቡ በሩቢና
በማሪያ ቴሬዛ ተመንዝሮ ሻሙቹ ተቀበሉ ። ከዚህ በኋላ በ1861
ዓ.ም. ለመዠመሪያ ጊዜ ሲፈሩ ሲቸሩ ኢጣልያኖቹ በዚያው በአሰብ
ባሠሩት ቢሮአቸው ላይ ያገራቸው የኢጣልያ ባንዲራ ተሰቅሎ መውለ
ብለብ ዠመረ ። ከዚህ ጊዜ ዠምሮ በዚህ ርዝመቱ ባሕሩን ይዞ ለባት
ኪሎ ሜትርና ከሐያ እስከ ሠላሳ ኪሎ ሜትር ካሬ ስፋት ባለው
የባሕር ዳር ሥፍራ ላይ ጣልያኖች እግራቸውን ለመዠመሪያ ጊዜ
አስገብተው በሚቀጥለው ጊዜ እየተስፋፉ ሔዱ ። የዚህም ወሬ በሮማ
በጋዜጣ በተሰማ ጊዜ የቅኝ ክፍሎች ፣ የፋብሪካ ቤቶች ፣ የንግድ ማኅ
በር የነበራቸው ነገሩን በደስታ ሲቀበሉት ፣ የቀሩት ይህ ደረቅና በረ
ሃማ ሥፍራ ለኢጣልያ ምንም ጥቅም አይሰጣትም ፤ እንዲያውም ይኸን
ሥፍራ በመያዛችን ከሌሎቹ የወደብ ጌቶች ከእንግሊዝና ከፈረንሳይ
ጋር ሊያቀያይመን ይችላል ። ከአካባቢው ጌቶች ከግብጽና ከቱርክ
ጋራም ያጣላናልና ይቅር ብን የሚል ክርክር አቅርበው ነበር ።

ነገር ግን ፣ በአፍሪካ ለመግባት ስፊ ዓላማ የነበራቸው ወገኖች
እያደር እያሸነፉ ሔዱ ። የግብጽ መንግሥትም እንዳይቆጣ ደማርቲኖ
ጃኮሞ የሚባለው በካይሮ ተቀማጭ የሆነው የኢጣልያ ዋና ቆንሲል
የአሰብ ግዥና የኢጣልያኖች በዚህ ሥፍራ መመሥረት ለግብጽ የኢ
ኮኖሚ ዕድገት የሚረዳ መሆኑን አስፋፍቶ ለማስረዳት ሞክሮ ነበር ።
ይሁን እንጂ ፣ የግብጽ ባለሥልጣኖች አባባሉን ሳይቀበሉ ከግብጹ
ከዲቭ ከኢስማኤል ታዞ ሞታዝ ፓሻ በካርቱም በተሠየመው መር
ከብ ያንድ ክፍል ጦር ይዞ መጥቶ ወዲያና ወዲህ በማለት ኢጣልያ
ኖቹንም ፣ ሻሙቹንም የደንከል ሡልጣኖች ለማስፈራራት ሞክሮ
ነበር ። በካይሮም መንግሥቱ ራሱ በውጭ ጉዳይ በኩል ለኢጣልያ
መንግሥት ተቃውሞውን በጽሑፍ ቢያቀርብ ፣ "የግብጽ መንግሥት
ከምጥዋ ወደ ደቡብ በሚገኘው በዚህ በአሰብ አካባቢ ምንም የገዥ
ነት ሥልጣን የለውም" በማለት ተቃውሞውን በመወርወር ፣ ጣልያ
ኖቹ የራሳቸውን እያያዝ በየጊዜው ያጠባብቁ ዠመር ።

"የግብጽ መንግሥት ግዛቴን ከሜዲቴራኒ እስከ ሕንድ ውቅያ
ኖስ አደርሳለሁ ፣ ኢትዮጵያንም ከሱዳን ደባልቄ እገዛለሁ" በሚል
ምኞት ከተዋጠ ወዲህ ፣ ባንድ ወገን በዚሁ የተነሣ በጉንዳጉንዲና በጉራዕ
ጦሩ ባፄ ዮሐንስ ጦር ከተፈታና በሱዳንም አል ማህዲ ተነሥቶ የግብ
ጽንና የቱርክን ጦር እያዋከበ ማስወጣት ስለ ዠመረ ፣ በዚህ ሁሉ ምክ
ንያት የግብጽ መንግሥት የኢኮኖሚም ፣ የወታደርም ውድቀት ስለገ
ጠመው ፣ ኢጣልያኖች እንደ ልባቸው አሰብን አጠንክረው ለመያዝ
ምቹ ጊዜ አጋጠማቸው ። ስለዚህም በኢትዮጵያ የኢጣልያ የቅኝ



አገዛዝ ታሪክ የተወጠነው በዚህ ወደብና በገርሴፔ ሳፔቶ አማካይነት
መሆኑ ነው ። አገር ጐብኝዎቹ ወደ ሸዋም ፣ ከሸዋም እየተነሡ
ደቡባዊውን ክፍላችንን ለመመርመር የረዳቸው በአሰብ በቅድሚያ
እግራቸውን ማስገባታቸው ነበር ።

እንደ እውነቱ የዚህ የአሰብ አካባቢ ቀበሌ ባላባቶቹ ሻሙቹ
እና ሡልጣን ኢብራሂም ቢሆኑም ፣ በዢዎግራፊ አቀማመጥና በታሪክ
የበላይ ባለቤቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ስለሆነ ከሩቅ መጥተው ምጥ
ዋንና አካባቢውን ከያዙት ከግብጽና ከቱርክም ፣ ከፈረንሳይና ከእንግ
ሊዝም የበለጠ መጠየቅም መፈራትም የነበረበት የኢትዮጵያ ንጉሠ
ነገሥት ነበር ። ዳሩ ግን ፣ ኢትዮጵያ የተከፋፈለችበትን የመሳፍንት
ዘመን አሳልፋ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ አንድነቷንና ንጉሠ ነገሥታዊውን ሥል
ጣን መሥርተው በ1860 ዓ ም በመቅደላ ከሞቱ ወዲህ ፣ ይህን የአሰብ
ወደብ ባላባቶቹ ለሩባቲኖ ማኅበር በሳፔቶ አማካይነት በ1861 ዓ ም
ሲሸጡ ፣ ከቴዎድሮስ ቀጥለው በኢትዮጵያ የነገሡት ዐፄ ተክለ ጊዮር
ጊስ ነበሩ ።

በዚህም ጊዜ ፣ በትግራይ ዐፄ ዮሐንስ (ደጃች ካሳ ርዕስ መኳንንት)
በሸዋም ምኒልክ ንጉሠ ሸዋ እየተባሉ የየአውራጃ ግዛታቸውን የሚ
ያስተዳድሩበትና በሦስቱም ዘንድ በዚህ ጊዜ ፋታ የማይሰጥ የውስጥ
ያስተዳደር ጭቅጭቅና የዙፋን ባላንጣነት ክርክር ያዋከባቸው ነበር ።
ወደ ንጉሠ ነገሥታዊ ሥልጣን ለመውጣት ሦስቱም እርስ በርሳቸው
በጠብ ፣ ለውጊያ የሚፈላለጉበት ጊዜ ነበር ። ምናልባት የሳፔቶን የአ
ሰብ ወደብ አገዛዝና የባላባቶቹንም አሻሻጥ ወሬውን እንኳን የሰሙት
በኋላ ጊዜ ይሆናል ። ቢሰሙም ቁርጠኛ እርምጃ በባላባቶቹ ላይ ለመው
ሰድ በሥፍራው ርቀትና በበረሃማነቱ ፣ በጠቅላላውም እነሱ የነበሩበት
የባላንጣነት ሁኔታ አያስችላቸውም ነበር ። ላዲሱ ንጉሠ ነገሥት አሸዋ
ማና በረሃማ የሆነውን ሩቁን የባሕር ጠረፍ ከመከላከል በፊት በቅድ
ሚያ በለምለሙ በማኸል ኢትዮጵያ በባላንጦቻቸው ግንባር አቅዋማ
ቸውን ማጽናቱ ይብስባቸው ነበር ። ደግሞም ምጥዋና የአሰብ አካባቢ
ከቀይ ባሕር ወዲህ ማዶና ወዲያ ማዶ ያለው የባሕር ጠረፍ ሁሉ በቱ
ርክ ቁጥጥር ውስጥ ከገባ ብዙ ዘመን እንዳለፈው ይታወቃል ። በውስ
ጡም የነበረው ነዋሪ ሕዝብ አዳሉና ሌላውም እስላማዊ ሕዝብ ከኢት
ዮጵያ መንግሥት ቁጥጥር ውስጥ እየራቀ እንዲሔድ ተደርጓል ።

በዚህ ምክንያት ፣ የኢትዮጵያ የውስጥ የመከፋፈሉና የኋላ ቀር
ነቱ ሁኔታ ለኢጣልያኖቹም ፣ ለባላባቶቹም ስለ አገዛቸው የሩባቲኖ
የመርከብ ኩባንያ በኢጣልያ መንግሥት በቀጥታ እየተረዳ 13 ዓመ
ታት ያህል በስሙ ይዞ እያስተዳደረ ወደቡንም እያስፋፋ ከቆየ በኋላ ፣

በ1874 ዓ ም 416.000 ሊሬ ተቀብሎ ለኢጣልያ መንግሥት በይፋ ሸጠው ። ይኸም ወደ ማሪያ ትሬዛ ብር ሲለወጥ 20.800 ብር ስለሚ ሆን ፡ ኩባንያው 17.700 ብር አትርፏል ማለት ነው ።

የኢጣልያ መንግሥት ከማኅበሩ ላይ ይኸን ወደብ በገዛበት በ1874 ዓ ም የነበሩት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ዮሐንስ ናቸው ። ባለፈው እንዳነበብነው ፡ ንጉሠ ነገሥቱ በዚህ ጊዜ ግብጾችንም ቢያሸ ንፉ ፡ ምኒልክንም ቢያሳምኑ ከግብጾችና እነርሱን ተጠግተው ከሸፈቱ ባቸው ከነራስ ወልደ ሚካኤል ጋር የነበረባቸው ውዝግብ ፋታ ባለመ ስጠቱ የኢጣልያን በአሰብ ላይ መግባት ሊቃወሙ አልቻሉም ። የኢ ጣልያ መንግሥትም ባንድ ወገን በቀጥታ በአሰብና በአካባቢው አገ ዛዙን አጠንክሮ ወደቡንም እያስፋፋ ለአሰብ የበላይ አስተዳዳሪ* እነ ብራንኪ ጆዎቫኒን ፡ እነ ፒስታሎዛጁ ሊዎኔን ስለሾመ ፡ ንጉሠ ነገ ሥቱ ከነዚሁ የኢጣልያ ወኪሎች ጋር ደብዳቤና ገጸ በረከት እየተለ ዋወጡ እንዲያውም ደንበኛ ወዳጅነት ወጥነው ነበር ።

የኢጣልያ መንግሥት ፡ በአሰብ እግሩን ከ1861—74 ከሰደደ ወዲህ ፡ ባንድ ወገን በአሰብ በኩል ወደ ሸዋ ገብቶ ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ተወዳጀ ። በሌላ ወገን ወደ ትግሬና ወደ ትግራይ የሚያስገባውን የምጥዋን ወደብ ከተዳከሙት ከግብጾች እጅ ለመረከብ የእንግሊዝን መንግሥት ድጋፍ ለማግኘት በመጣጣር ከ1874—76 ዓ ም ድረስ እንዳሳለፈ እንግሊዞችም በሱዳን የተቀሰቀሰውን የማህዲስቶችን አነሣሥ ለመደምሰስ የኢጣሊያንን ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ ደጋፊነታቸውን እን ዳልነፈጉ በዚህ ዐይነት ሁለቱም በየዋሂቷ ኢትዮጵያ ጀርባ ላይ እንደ ልባቸው መገቢያየታቸውን ወደፊት እናነባለን ።

---

* በኢጣልያንኛው አጠራር Commissario Civile ይባላል ።



# ምዕራፍ ሠላሳ

## አፍሪካን በሰላም ለመከፋፈል በርሊን ላይ

## የአውሮፓ ኃያላን ያደረጉት ስምምነት

አውሮፓ ከግሪክና ከሮማ ወርሶ በአስፋፋው ሥልጣኔ የተነሣ ከሌሎች አህጉር ከእስያም ፡ ከደቡብ አሜሪካም ፡ ከአፍሪካም የበለጠ በማናቸውም መስክ በኢንዱስትሪ ፡ በቴክኒክ ፡ በንግድና በርሻ ፡ በሥነ ጥበብና በሥነ ጽሑፍ የበረታ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው ። የአውሮፓ መሪዎች ከ14ኛው መቶ ዓመት ዠምሮ በዚያው በአውሮፓ ውስጥ በወሰን ግዛት ፡ በጥቅም ፡ በጋብቻ ፡ በዙፋን ፡ በሃይማኖት እርስ በርሳ ቸው ዐልፎ ዐልፎ ሲቀጣቀጡ ኖረዋል ። ከሌላው አህጉር ሁሉ የበ ለጠ ከመዠመሪያ ዠምሮ እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ ድረስ የሰው ልጅ ጦርነት ያደረገበት አገር ሲታሰብ ከሁሉ በልጦ የሚገኘው የሠለጠነው የአውሮፓ አህጉር ነው ።

የአውሮፓ ነገሥታት ለረዥም ዘመናት እየተዋጉም ፡ እየታረቁም ፡ እየተጋቡም ዙፋንና መንግሥት እየተወራረሱ ፡ ቢጋብቻውና በኃይሉም አንዱ ሌላውን ሲጠቀልለው ከቆዩ በኋላ ፡ ከነዚሁ መካከል አንዳንዶቹ መንግሥታት በጦር መሣሪያና በመርከብ ሥራ የታወቁት እነ ፖር ቱጋል ፡ እነ ኤስፓኝ ከአውሮፓ እየወጡ ወደ ደቡብ አሜሪካ ፡ ወደ አፍሪካም እየዘመቱ ከባላንጣቸው ከኦቶማን የቄሣር ግዛት ጋር እየተ ፋለሙ ብዙ አውራጃ ለመያዝ በቁ ። ከነርሱም ተከታትለው እንግሊዞች፡ ፈረንሳዮች ፡ ቤልዥኮች ፡ ጀርመኖች ፡ ሆላንዶች ቢያለበት ቅኝ አገር ፍለጋ ሲሠራጩ የቀረው ዓለም ግማሹም የነበረው ሥልጣኔና ገናንነት እየተዳከመ ስለሔደ ሌላውም ድንቁርና ስለተጫነው ፡ ያለው ዕድል ለነዚህ አዲስ ለተነሡትና ለሠለጠኑት በሥልጣኔያቸው የተነሣ በመ ርከብና በባቡር ለሚጓዙት የመድፍ ፡ የጠመንጃና የሽጉጥ ሥራ በማ ወቅ ኃይል ላገኙት መግዛት ብቻ ሆነ ።

አውሮፓውያን በአገር መርማሪዎቻቸው በነስታንለይና በነሊቪ ንግሥተን በሌሎቹም እየተመሩ በተለይ እንግሊዝ በግብጽ ፡ በሱዳን ፡ በናይጄሪያ ፡ በኬንያ ፡ በጋና ፡ ፈረንሳይ በምዕራብና በሰሜን አፍሪካ ፡ ፖርቱጋል በአንጎላ ፡ በሞዛምቢክ ፡ ጀርመን በታንጋኒካ (የዛሬ ታንዛኒያ)

እና በቶጐ ፣ ቤልጅክ በተለይ ንጉሥ ዳግማዊ ሊዎፖልድ ኮንጎን እንደ ግል ግዛቱ አድርጎ ቢያዘበት ጊዜ ከሥልጣኔ ኋላቀር የሆነውንና ሀብት የሞላበትን አፍሪካን ሳይጣሉና ሳይዋጉ የሚይዙበትን ፣ ያገር ክፍያው ፣ የወሰን ክለላው ፣ የንግዱ መስፋፋት ፣ የመርከቡ ዝውውር በሰላም የሚከናወንበትን ሁኔታ ማጥናት ዠመሩ ። ለዚህም ዋና የጉዳዩ ጠንሳሾቹም ፣ አበረታቾቹም ስሙን እላይ የጠቀስነው የቤልጅክ ንጉሥ ሌዎፖልድና የጀርመን ቻንስለር ቢስማርክ ነበሩ ።

ኃያላኑ የአውሮፓ መንግሥታት ባንድ ወገን ባገር መርማሪዎቻቸውና በወንጌል መልክተኞቻቸው በኩል ፣ ቀጥሎም በየቆንሲሎቻቸውና በንግድ ወኪሎቻቸው አማካይነት የየግል ጥቅማቸውን የሚያስፋፉበትን ፣ ከዚህ በፊት በእጃቸው ያገቡትን ፣ ወደፊት ለመያዝ ያለሙትን ክፍለ ሀገር ፣ መርከባቸው የሚተላለፍበትን የባሕር መስመርና የሚያርፍበትን ወደብ በደንብ ካጠኑና አያያዛቸውን ካጠባበቁ በኋላ በመንግሥታት መሪዎች ደረጃ በባለሥልጣኖቻቸው አማካይነት በስብሰባም ፣ በመልእክትም ፣ በቃልም ፣ በጽሕፈትም ከ1875 እስከ 1876 ዓ ም በነበረው ጊዜ ውስጥ አሳብ ለአሳብ እየተለዋወጡ ሲወያዩበት ከቆዩ በኋላ ፣ በመጨረሻ በየካቲት 26 ቀን 1877 ዓ ም በጀርመን ዋና ከተማ በቤርሊን ተገናኝተው ቀጥሎ ያለውን ስምምነት በፊርማቸው አጸደቁ ።

ስምምነቱ በሰባት ምዕራፍ በ38 አንቀጽ የተከፈለ ነው ።

ሀ/ የመዠመሪያው ምዕራፍ ስለ ንግድ ነጻነት ፣ ስለ ቀረጥ ፣ ስለ ንብረት መያዝ መብት ፣ ስለ ሚሲዮኖች ፣ ስለ ተወላጆች ደህንነትና አጠባበቅ ፣ ስለ ደብዳቤ አላላክና ስለ ቴምብር ቀረጥ ፣ ለዚህ ሁሉ ክንውን የተቋቋመው ኮሚሲዮን የንግዱን ሁኔታና የመርከቡን ዝውውር የሚያከናውንበት ፤

ለ/ ሁለተኛው ምዕራፍ ኃያላኑ በያዙት አገር ክልል ውስጥ የባሪያን አገዛዝ ሠርዘው ባሪያን ነጻ እንዲያወጡና የባሪያ ንግድ እንዳይፈጸም እንዲከለክሉ ፤

ሐ/ በሦስተኛው ምዕራፍ እያንዳንዱ አውሮፓዊ መንግሥት በያዘው አገር ወይም ባሕርና ወንዝ ላይ መርከብና ሸቀጥ በሚተላለፍበት ጊዜ ሌላውን እንዲያግዝ እንጂ እንዳያውክ ፤ በተቻለ መጠን በመንግሥታቱ መካከል ሰላምና አብሮ የመሥራቱ ዓላማ እንዲስፋፋ ። ምናልባት በሁለት መንግሥታት መካከል ጠብና ጦርነት ቢነሣ ፣ ሌሎቹ በሰላምና በገለልተኝነት የገላጋይነት አቅዋም እንዲኖራቸው እንጂ ካንደኛው ወገን ተደርበው ሌላውን በማጥቃት



የሰላሙ አስተዳደርና የሰላሙ ንግድ እንዳይደፈርስ ። የተጣሉት መንግሥታት ከውጊያ በፊት ራሳቸው አስታራቂ በስምምነት መርጠው እንዲገላገሉ ።

መ/ በአራተኛው ምዕራፍ በኮንጎና በሌሎቹም ወንዞችና ባሕሮች ሁሉም በትክክለኛነት መርከብና ሸቀጣቸውን የማስተላለፍ መብታቸው የተጠበቀ እንዲሆንና በየወደቡ የማንም መርከብ በሚቆምበት ጊዜ ፣ የመጠበቁ ፣ ሸቀጥ የማውረዱና የመጫኑ ጉዳይ ለሁሉም ያለ አድልዎ እንዲሆን ፤ ቀረጡም ተመሳሳይ መሆኑን የሚቆጣጠር የአንድ ኮሚሲዮን አቋቋሙና የኮሚሲዮኑ ዝርዝር ተግባርና ሥልጣን ፣

ሠ/ በአምስተኛው ምዕራፍ በኒጀር ወንዝ ላይ በመርከብ የመተላለፉ ጉዳይ ከኮንጎው ወንዝ መተላለፊያ ደንብ ጋር ተመሳሳይ እንዲሆን ።

ረ/ በስድስተኛው ምዕራፍ አንዱ ኃያል ፣ አንድ የአፍሪካን ክፍል በያዘ ጊዜ መያዙን ለሌሎቹ ኃያላን ማስታወቅ እንዳለበት ፤ ኃያላኑ አዳዲስ አገር በያዙ ቁጥር በዚህ ስምምነት የተጠቀሱትን ሕጐች እንዲያከብሩ ።

ሰ/ በመጨረሻውና በሰባተኛው ምዕራፍ ይኸን ያሁኑን ስምምነት አባሎቹ በስምምነት ወደፊት ማሻሻል እንደሚችሉና ሌሎች ኃያላን በዚሁ ስምምነት ለመግባት ቢጠይቁ ፣ ጥያቄያቸውን ለጀርመን ንጉሠ ነገሥት በቅድሚያ እያቀረቡ መግባት እንደሚችሉ ያረጋግጣል ።

በዚህ ውል ውስጥ ተስማምተው የተፈራረሙት ቅኝ አገር የነበራቸው እንግሊዝ ፣ ፈረንሳይ ፣ ጀርመን ፣ ፖርቱጋል ፣ ቤልጅክ ሲሆኑ እንደሚታየው ኢጣልያ አንድነቷንም ያቋቋመችው በቅርቡ ከሐያ ዓመት በፊት ስለነበረ ፣ ቅኝ አገርም በዚያን ሰዓት ለመያዝ በየትኛውም ክፍለ ሀገር ልዠምር የምትልበት ወቅት ነበር ። ወደ ምጥዋም ገና ወታደር ለመላክ የምታዘጋጅበት ጊዜ ስለነበረ ፣ በዚህ የኃያላን ጉባዔ ላይ ለመካፈል ዐቅሟ በማናቸውም ረገድ አልፈቀደላትም ። በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ እንደ ተመለከተው ለሚቀጥለው ጊዜ ግን በውሉ ውስጥ ገብታለች ።

ከ16ኛው መቶ ዓመት ዠምሮ የአፍሪካ ሰሜን ፣ የመካከለኛው ምሥራቅ ፣ የባልካን አገሮች ጌታ የነበረውን ቱርክን በዘሩና በሃይማኖቱም ባዕድ በማድረግ ፣ ባሁኑ በ19ኛው መቶ ዓመት መጨረሻ ላይ በውስጥ አስተዳደሩም እየተዳከመ ፣ ኢኮኖሚውም እየወደቀ ስለ

ሖደና የርሱ መሣሪያ የነበረው ግብጽም በእንግሊዝ ቁጥጥር ውስጥ ስለገባ ፣ የቱርክ መንግሥት በስብሰባው እንዲካፈል አልፈለጉም ።

ከዚህም ጋር እነዚሁ በቅኝነት የተያዙት የአፍሪካ ተወላጆች መከላከያ መሣሪያ እንዳያገኙ በሚቀጥለው ጊዜ በብሩክሴል ሌላ የተ ለየ ስምምነት አደረጉ ።

እነዚህ የቤርሊን ስምምነት ተካፋዮች በስምምነቱ መሠረት የአ ፍሪካን አገሮች እንደ ሥጋ ቅርጫ በሰላም ቢከፋፈሉም ፣ ወደ ጠብ በደረሱ ቁጥር በውሉ መንፈስ እየታረቁ ፣ በይፋ የጦርነቱ በር ባይከፈ ትም እርስ በርስ በሽሚያው ጊዜ መፋጠጥና መጐነታተል አልቀረም። ቱርክና ግብጽ በሚለቋቸው በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ ወደቦች እንግሊዝና ፈረንሳይ በጣም በብዙ ቦታ ለጦርነት ይፋጠጡ ስለነበረ ፈረንሳይ ወደምጥዋ ቀድሞ ገብቶ ወደብ ይዞ ከዘይላና ከበርበራ ወደብ ጋር እንዳይፎካከር ጣልያንን በጕን ጋብዞ ያስያዘ እንግሊዝ ነው ። በዚህም የተነሣ ፣ ዐፄ ዮሐንስ በምጥዋ ወደብና በአካባቢው ባሉት ወረዳዎች ላይ ከኢጣሊያ ጋር ሲጣሉ ከርሳቸውም በኋላ ዐፄ ምኒልክ ከኢጣልያ ጋር በነበራቸው የመጨረሻ ጠብ ጊዜ ፈረንሳይ የኢትዮ ጵያ ረዳት ሆና ለእንግሊዝና ለኢጣልያ መንግሥታት ክፉ ባላንጣ ሆኖባቸው ነበር ።

በተለይ በኦቦክና በጅቡቲ ፈረንሳይ ፣ በአደንና በዘይላ እንግሊዝ ፣ ጣልያኖችም በአሰብ በተተከሉበት በ1860—85 ዓ.ም. ከመሬት ይዞ ታው በቀር የጅቡቲ ወደብ የአደኑን ወደብ ተፎካክሮ እንዳይጥለው ፣ ሀብታም ሆና በኖረችውም ኢትዮጵያ በቅድሚያ እንዱ ገብቶ ሌላውን እንዳያስወግድ እንግሊዝ በጐን ጣልያንን እየጠቀሰ ፣ ጀርመንንም እየገ ፋፋ የፈረንሳይን መንግሥት ለማዳከም በሚያደርገው ሙከራ ፈረን ሳይም በምትችለው መንገድ ኢትዮጵያን የመደገፍ መልክ እያሳየች በእንግሊዝና በኢጣልያ ላይ የምታደርገው ተቃውሞ በየሰነዱ ላይ በግልጽ ይታያል ። ወደፊትም ባፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በ1890 ዓ.ም. የፈረንሳይ ጦር ፋሾዳን (በሱዳን ውስጥ) በመያዙ በሱ ዳን ቀድሞ ከገባው ከእንግሊዝ ጦር ጋር ለውጊያ ከተፋጠጡ በኋላ የቤርሊን ስምምነት እንዳይፈርስ ፈረንሳይ ሸብረክ ብሎ ወደኋላ በማ ፈግፈጉ ሁለቱ የቅኝ አገር ኃያላን ከትልቅ የርስ በርስ ውጊያ ድነዋል ።

ነገር ግን ፣ ሌላው አህጉር (እስያ ፣ መካከለኛው ምሥራቅና አሜ ሪካ) "ባለቤትና በመጠኑም ቢሆን ሥልጣኔ ያለው በዋዛም ሊያ ዝና ሊገዛ አይችልም" ብለው ችላ በማለት አፍሪካን ግን ባለ ቤት ፣ አዛዥና ተቀናቃኝ እንደሌለበት እምነው ፣ ከሥልጣኔም ኋላ ቀርነቱ አግዟቸው በሰላም ለመከፋፈል በ1877 ዓ.ም. ይኸን ውል



ቢያደርጉም ፣ በሚቀጥለው ጊዜ ከ1906 —10 ዓ.ም.ና በ1931—37 ዓ.ም. ሁለት ጊዜም ያደረጉት የዓለም ጦርነት ሰበቡ በግዛት ነበር።የመዠ መሪያው ጦርነት በሳራዬቮ የአውስትሮ ሁንጋሪ መስፍን በመገደሉ ሰበብ ሲሆን ፣ የግዳዩ ምክንያት ደግሞ ለምን በናንተ እንገዛለን የሚል ነበር ። በመዠመሪያው የዓለም ጦርነት ጀርመን እንደ ቅጣት የአፍ ሪካ ቅኝ አገሮቿን በእንግሊዝና በፈረንሳይ ስትነጠቅ ፣ በ1925—31 ዓ.ም. ከሂትለር አነሣሥ ውስጥ ዋነኛው ሰበብ እንግሊዝና ፈረንሳይ አፍሪካን ተከፋፍለው የኛንም ግዛት ቀምተው በሰፊ ግዛት ሲንደ ላቀቁ ፣ ጀርመን በምን ምክንያት በአውሮፓ ግዛቷ ብቻ ተወስና ትኖራለች በሚል ቁጭት ነበር ።

በዚህ መካከል የሚታየው አሳዛኝ መልክ ፣ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከተፈጸመ በኋላ ፣ አፍሪካውያን የፖለቲካ ነጻነት አግኝተው የቀድሞ ገዥዎች የሆኑት አውሮፓውያን ባገራቸው ተሰብስበው ይነስ ይብዛ በሰላም ሲኖሩ ነጻነታቸውን ያገኙት አፍሪካውያን ግን ፣ በየም ክንያቱ አንዳንድ ጊዜም ያለበቂ ምክንያት እርስ በርሳቸው እየተጣሉ ብዙ ደም እስከ መፋሰስ መድረሳቸው ነው ። የዚህም ዋናው መን ሥዔ የቀድሞዎቹ ቅኝ ገዥዎች በሥውርም በግልጽምም ከሚፈጥ ሩት ደባ ጐን ራሳቸው የአፍሪካ መሪዎች በልዩ ልዩ ያስተዳደር ፍልስፍና በመለያየት ወይም የብሔረተኝነት ስሜት እያደረባቸው ለሰላሙ መንገድ የበቃ ጥረት ባለማድረግ ነው ።

# ምዕራፍ ሠላሳ አንድ

## ቅኝ ግዛት የማግኘቱ ጉዳይ በኢጣልያ ምክር ቤት ያስከተለው ውዝግብ

ባለፈው ምዕራፍ እንደ ተገነዘብነው ፣ የኢጣልያ አውራጃዎች ግማሾቹ በመሳፍንት ፣ የቀሩት በሬፑብሊክ አገዛዝ ፣ እንደ ኢትዮጵያ የመሳፍንት ዘመን ፣ ተበታትኖ የነበረው በካርሎ አልቤርቶና በቪክቶር አማኑኤል ዳግማዊ ትጋት ባንድ መንግሥት ከመዋሐዱ በፊትና በኋላ በሮማ ፣ በሚላኖ ፣ በጀኖቫ ፣ በቶሪና ፣ በቬኒዚያና በፊሬንሴ ከተቋቋሙት የንግድ ማኅበሮች ፣ ያገር ምርመራ ድርጅት የሚላኩት መላከተኞች ካፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ዠምሮ ባተለይ ባሁኑ ባፄ ዮሐንስ ጊዜ በልዩ ልዩ መንገድ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ፣ የወታደራዊ፣ የአስተዳደርና የኢኮኖሚ አቅዋም በደንብ አጥንተውታል ። በዚሁ ጉን የሕዝቡና የመሬቱ ፣ የአየሩ ጠባይ ፣ የወንዛወንዙ ፣ የሐይቁና የደሴቱ የተራራና የሸለቆው ሁኔታ ፣ መገናኛ መንገዱንም ሁሉ በራፖርና በመጽሐፍ መልክ በሥልጣን ላይ ለነበሩት እየቀረበ ሲጠናበትና ሲመከርበት ቆይቷል ።

የኢጣልያ አላይ የጠቀስናቸው አውራጃዎች በሰላምም በጦርነትም ተጠቃልለው ፣ የሮማንም ግዛት ከርእሰ ሊቀ ጳጳሱ እጅ ወስደው ፣ የሣርዴኛ ንጉሣዊ መንግሥት የሚባለው ተሠርዞ የኢጣልያ መንግሥት የሚባለው ሥያሜ ከመጋቢት 17 ቀን 1853 ዓ.ም. ጀምሮ ሲጠና ቆይቶ በይፋ በ1862 ዓ.ም. ሲታወጅ ፣ በኢትዮጵያ ላይ በማተኮር የጥናቱም ፣ የቅኝ አገር ፍላጐቱም ጉዳይ እየተፋፋመ ሔደ ። ባለፈው እንዳነበብነው ፣ ግማሾቹ ኢጣልያኖች በምጥዋ በኩል ወደ ዐድዋና ወደ መቀሌ እየመጡ ካፄ ዮሐንስ ጋር እና ከዚያም ወደ ጐጃም እያለፉ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር እየተገናኙ ፣ በአሰብ በኩል አውሳን እያቋረጡ የዚህን አገር ባላባት የመሐመድ አንፋሪን ወዳጅነት ከጨበጡ ወዲህ ከርሱ መሪ እየተቀበሉ ወደ ሸዋ በመዝለቅ እለከ አንኮበር ደረሱ ። ከንጉሥ ምኒልክ ጋር የወዳጅነት ግንኙነታቸውን በደንብ አጠበቁ ። ከአንኮበርም አልፈው በዘይላ በኩል እየመጡ የኢትዮጵያን ደቡባዊውን ክፍል የኦሞንና የጊቤን ወንዛ ወንዝ ተራራና ሸለቆውን በረሃውንና ለምለሙን ከሕዝቡ ጠባይ ጋር ከመመርመርና ከማሰስ አልተቆጠቡም ።

የዚህ ሁሉ ምርመራ ውጤት ያተኮረው ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመግባት ስለሚቻልበት ሁኔታ ነበር ። የኢጣልያ መንግሥት እንደ ተቋቋመ የፈላጭ ቆራጭነት ጠባይ ያላቸውን የጀርመንና የአውስትሪያን የመሰለውን የቄሣር አገዛዝ አልተከተለም ። ላንድነቱ መሪ ሆኖ መንግሥቱን ያቋቋመው ንጉሡ ቪክቶር አማኑኤል ከተከታዮቹ ጋር ስለነበረ ፣ እንደ ጐረቤት አገራቸው እንደ ፈረንሳይ የሬፑብሊክ አገዛዝ ለመመሥረትም አልፈለጉም ።

ስለዚህ የኢጣልያ መንግሥት እንደ ተቋቋመ የታወጀው የመተዳደሪያ ሕገ መንግሥት ፣ ከእንግሊዝ አገር አስተዳደር ጋር በተመሳሰለ ሕገ መንግሥት የሚመራ ንጉሣዊ አገዛዝ ነበር ። በዚህ ምክንያት በምክር ቤቱ ውስጥ እንደ ልባቸው የሚከራከሩ በርከት ያሉ የፖለቲካ ቡድኖች ስለነበሩ ፣ የቅኝ አገር የማግኘቱ ጉዳይ በጉባኤ ብዙ ንትርክና ውዝግብ አስከትሏል ። ሆኖም ከመማክርቱ አብዛኞቹ የንጉሡን ክብር ከኢጣልያ ዕድገት ጋር በማጣመር አሳቡን በቶሎ ይቀበሉት ነበር ።

በዚህ ምክንያት ፣ ደጃች አገው ንጉሤ ከተላላኩት ከመዠመሪያው ጠቅላይ ሚኒስትር ከካሚሊዮ ካቩር ወዲህ 1851 — 1874 ዓ ም ቁጥራቸው ከዐሥር በላይ የሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ሲለዋወጡ ቆይተው ፣ አሁን የቅኝ ግዛቱ ጥያቄ እየጐላ በሔደበት ጊዜ ከ1873 ዓ ም ዠምሮ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አጐስቲኖ ዴፕሬቲስ ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ማንቺኒ ፓስኩአሌ ፣ የጦር ሚኒስትሩ ኤ ፌሬሮ ይባሉ ነበር ።

ቀድሞም ንጉሡ ቪክቶር አማኑኤል ፣ አሁንም ልጁ ኡምቤርቶ ቀዳማዊ ፣ "ከኢኮኖሚው ጥቅም ጋር ለወግና ለዝና ኢጣልያ ግዛት ያስፈልጋታል" የሚሉትን ከልብ የሚደግፉና የሚያበረታቱ ነበሩ ። ከነርሱም ጋር በፈረንሳይና ይልቁንም በአውስትሪያ ንጉሠ ነገሥት ጦር ሠራዊት ውስጥ የነበሩ አሁን አገራቸው ነጻነቷን አግኝታ አንድነቷን ስታቋቁም ፣ ዘራቸውን ጠቅሰው የመጡ የጦር ሹማምንቶች ሁሉ የንጉሡ ታዛዦችና በአሳብ ከቅኝ ፈላጊዎች ጋር ነበሩ ። በነዚህም መካከል በሶሻሊስት ቡድን ውስጥ ከነበሩት ውስጥ ፣ "ቅኝ አገር ለኢጣልያ አያስፈልጋትም ስንል የኢጣልያን ዕድገት የምንቃወምና አገር ፍቅር እንደሌለን እንቆጠራለን" በማለት ብዙዎቹ ወደ ቅኝ ፈላጊዎቹ ሲደረቡ ይታዩ ነበር ።

በዚህ ሁሉ የተነሣ ፣ "ኢትዮጵያን እንውረር ፣ በቅድሚያ ወደ ምጥዋ ጦር ልከን ወደቡን እንያዝ" የሚለው ክርክር በምክር ቤት በተፋፋመበት ጊዜ ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሽማግሌው በዴፕሬቲስና በወጣቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በማንቺኒ መካከል ሁለቱም በሶሻሊስትነት



ተመዝግበው ሳሉ በሁለቱ መካከል የአሳብ ልዩነት ነበር ። ሽማግሌው ጠቅላይ ሚኒስትር ለኢጣልያ ቅኝ አገር ማስፈለጉን ቢያምንም ፣ የቅኝውን ፍላጎት ቀዝቀዝ አድርገን ጉዳዩ በትዕግሥት መጠናት አለበት ሲል ማንቺኒ "አሁኑኑ በቶሎ" እያለ እየወተወተ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ታሞ እተኛበት እቤቱ ድረስ እየሔደ ጤና ነሥቶት እንደነበረ በዚያን ዘመን የተጻፈው ሁሉ ያስረዳል ።

የዚህ የቅኝ ፍለጋ ጉዳይ በምክር ቤት ከፍ ያለ ክርክር እያስነሣ ፣ ወደ ሁካታ በሚዞርበት ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሳምባውን ታሞ እቤት በዋለበት ሰዓት ሳይቀር ማንቺኒ እቤቱ ድረስ ይኸን ፍቀድ ፣ ይኸኛውን ፈርምበት እያለ ሲያስቸግረው ሳለ ፣ በሽታው እየጠናበት መሔዱን የሰማ አንድ ወዳጁ ሊጐበኘው ሔዶ "እንደምን አደርክ?" ብሎ ቢጠይቀው ፣ "ምን ደህንነት አለ ብለህ ነው? ሌሊት በሳል ስጐበሰት አድራለሁ ፤ ቀን ማንቺኒና አፍሪካ (የአፍሪካ ጉዳይ) ይወጥሩኛል ፤ ሳልፈነዳ ብቀር እንደ ተአምር ይቆጠራል " ብሎ መለሰለት ።[1]

የሆነ ሆኖ ፣ በቅኝ ግዛት አፈላለጉ ጉዳይ በአንደኛና በሁለተኛ ቁጥር የነበሩትና ከቀሩትም ውስጥ ከየጓደኞቻቸው እየተገነጠሉ ለኢጣልያ ቅኝ ግዛትና ወደብ አስፈላጊነቱን እያመኑ ስለ ተደረቡ ፣ የኢጣልያ መንግሥት በምስጢር ወደ ምጥዋ የሚዘምት የጦር ጓድ ማዘጋጀት ዠመረ ። የጦር ጓዱም አላላክ በቱርክ ፣ በፈረንሳይም ፣ በኢትዮጵያም ዘንድ እንዳይታወቅ በምስጢር እንዲያዝ ሲባል ለምክር ቤቱም ፣ ለጋዜጠኞችም ወሬው ለጊዜው እንዲሰወር ተደረገ ።

1 F. Martini, Cose Africane da Saati ad Abba Garima, p. 144.

# ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት

## ስለ ምጥዋ ወደብ ፥ የኢጣልያ ጦር ምጥዋ መግባትና መስፋፋት

### ሀ/ ስለ ምጥዋ ሁኔታ

ደንበኛው የአክሱም መንግሥት ወደብ ፥ አዱሊስ ከአክሱም ውድቀት ወዲህ ሲቀዘቅዝ ምጥዋ እየገነነ ሔደ ። ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ወዲህ ኢትዮጵያ በሥልጣኔ ወደፊት በመራመድ ፋንታ የኋሊት በመሔዱዋና በአቀማመጥም ፥ በታሪክም [ገንዘቧ] የሆነውን ምጥዋን ይዛ ለመሸጥ ፥ ወይም ለመግዛት የምትፈልገውን ሸቀጥ በመላክና በማስመጣት መጠቀም ስለ አልቻለች ፥ በ1557—60 ዓ ም የምጥዋ የወደብ ከተማ በቱርኮች እጅ ወደቀ ። በምጥዋና በአርኪቆ ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ይሾሙ ከነበሩት ባሕር ነጋሾች አንዳንዶቹ ከንጉሠ ነገሥቱ እየተጣሉና ከቱርኮቹ ጋር እየተደረቡ መጣሪያ ይሆኑ ነበር ። ካፄ ገላውዴዎስ ውጊያ ወዲህ በ1551—1555 ዓ ም የነገሡት ዐፄ ሠርፀ ድንግል በደባርዋ የሚቀመጠው ሹማቸው ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ከድቶ ከቱርኮቹ ጋር በመደረቡ በዚሁ በደባርዋ አካባቢ ያደረጉት ጦርነት በታሪክ ዕውቅ ነው ።[1]

### ለ/ የኢኮኖሚ አቅዋምና የንግድ እንቅስቃሴ

በኢኮኖሚ ረገድ በኢንዱስትሪና በቴክኒክ ፥ በእርሻና በንግድ ኢትዮጵያ ወደኋላ የቀረች አገር መሆኗ ቀደም ሲል ተወስቷል ። ከዚህም በላይ ወደቡን ከያዙባት ከቱርኮችና ከግብጾቹ ጋር አብዛኛውን ጊዜ በጠብ ላይ ነበረች ። በዚህ ወደብ አማካይነት የምታስገባውና የምትልከው ነዋሪ ሸቀጥም የተፈለገውን ያህል አልነበረም ። በመተማና በከሰላ በኩል እንደሚደረገው ተባራሪ የምጥዋና የደሆኖ ባላባቶች (ናይቦች) ወይም ነጋዴዎች ወደ ጐንደር ወደ ዐድዋ ብቅ

---

1 ተ.ጸ.መ. ፥ የኢ.ት. ታሪክ ካፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ ፥ ምዕ.21.22 ።

እያሉ ከነገሥታቱና ከየመሳፍንቱ እየተገናኙ እንደ እህል ፥ እንደ ቆዳ የመሳሰለውን ሲወስዱ ለየመሳፍንቱም አንዳንድ የጦር መሣሪያና ልብስ ያቀብሉ እንደነበረ የታወቀ ነው ።

በዚህ በ19ነኛው መቶ ዓመት ወደ መጨረሻው ጊዜ ፥ ኢጣልያ ኖች ከመግባታቸው በፊት በምጥዋ ወደብ ላይ ቢያመቱ የነበረውን የመርከብና የሸቀጥ የከብደት ንቅናቄ እላይ የጠቀስነው ሙሴ ዱወ የተባለው የታሪክ ጸሐፊ ከዚህ እንደሚከተለው አሥፍሮታል ።[1]

| ዓ.ም. | የግብጽ | | የሌሎች አገሮች | |
|---|---|---|---|---|
| | መርከብ | ከብደት | መርከብ | ከብደት |
| 1873 | 1679 | 63530 ቶን | 264 | 19292 ቶን |
| 1874 | 1568 | 44779 ” | 231 | 19431 ” |
| 1875 | 845 | 31697 ” | 305 | 67218 ” |
| 1876 | 555 | 16130 ” | 398 | 107645 ” |
| 1877 | 827 | 46271 ” | 458 | 39912 ” |

በዚህ ሰሌዳ ላይ የሌሎች አገሮች የሸቀጥ ንቅናቄና በተለይ ያስ ተዳዳሪው የግብጽ የንግድ ንቅናቄ ፥ የቶኑ ከብደት በብዛት ሲታይ የኢትዮጵያ እላይ በጠቀስነው ኋላቀርነት ምክንያት ምንም የለም ። የሌሎች አገሮች የተባሉትም እንግሊዝ ፥ ፈረንሳይና ቱርክ ናቸው ።

## ሐ/ የኢጣልያ ጦር ቤይሉል መግባት

የኢጣልያ መንግሥት በ1876 ዓ.ም. ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ውስጠ ስምምነቱን ከፈጸመ በኋላ ፥ ከምጥዋ ቀደም ብሎ ለሙከራ ያህል በመርከብ ጦር ልኮ በመዠመሪያ የወረረው ቤይሉልን ነበር ። ቤይሉል ከአሰብ በሰሜን በኩል 51ኛው ኪሎ ሜትር ላይ በቀይ

1 G. Douin, Histoire du Regne du Kedive Ismael, Tome III, 2ᵉ Partie, pp. 1242—1246.



ባሕር ዳር በወዲህኛው ማዶ በሞካ ፊት ለፊት የሚገኝ የመንደር ከተማና ቀበሌ ነው ።

ግዛቱ በጥንት ታሪኩ እንደ ምጥዋ ፥ እንደ ዙላና እንደ ሌላው ቀበሌ ሁሉ ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በሚሾመው በባሕር ነጋሽ ውስጥ ሆኖ ከርሱ በታች የራሱ የደንከል ባላባት ያስተዳድረው ነበር ። ነገር ግን ፥ ከ17ኛው መቶ ዓመት ወዲህ የኢትዮጵያ ነገሥታት እያደር ሥልጣናቸውን በየእንደራሴዎቻቸው ሲነጠቁ ፥ በዘመነ መሳፍንት ማዕ ከላዊው መንግሥት ሲዳከም ፥ የምሥራቅና የደቡብ አውራጃዎች በየባ ላባታቸው ሲተዳደሩ ይኸም የቤይሉል ቀበሌ ከነገሥታቱ ቁጥጥር ወጥቶ በራሱ ባላባቶች ይተዳደር ዠመር ። ከነርሱ በላይ የአውሳው ባላባት ከርሱ በላይ ደግሞ የግብጽ ከዲቭ ነበር ። ግብጽ ደግሞ ምጥዋ ንና የዚህን ቀበሌ ባላባቶች እያስገበረ በበኩሉ መቀመጫው ስጣን ቡል ለሆነው ለቱርኩ ሡልጣን ይገብር ነበር ።

የኢጣልያ መንግሥት አሰብን እጅ ከማድረጉ ቀደም ብሎ በነበ ረው ጊዜና ከሩባቲኖ ኩባንያ ገዝቶ በቀጥታ በሚቆጣጠርበት ጊዜ ሁሉ ፥ በአሰብ የሚቀመጡት ኮሚሳሮቹም ፥ መንገደኞቹም ሁሉ ለአው ሳውና ለሌሎቹም ባላባቶች ጥሬ ገንዘብና ሸቀጣ ሸቀጥ ፥ ጠበንጃና ጥይት ሽጉጥ በመስጠት ልባቸውን ስበውታል ።

ስለዚህ ኅዳር 16 ቀን 1877 ዓ.ም. የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ማንቺኒ በወኪሉ በደማርቲኖ አማካይነት ከእንግሊዝ መንግሥት ተወ ካይ ጋር ስምምነት ካደረገ በኋላ ፥ ከጓደኛው ከባሕር ኃይል አዛዥ ጋር ተነጋግሮ ያንድ ክፍል ጦር በመርከብ ሔዶ አደን ላይ እንዲጠባበቅ አድርጎ በዚሁ ጊዜ የአሰቡ ኮሚሴር ዡሊዮ ፔስታሎዛ የቤይሉል ባላባቶችና የነርሱ የበላይ የሆነው መሐመድ አንፋሪ እንዳይቃወሙ ግንኙነት እንዲያደርግና እንዲያግባባቸው አድርጎ በመጨረሻ ወታደ ሮቹ በምስጢር ከሲራኩዛ (ሲሲሊያ) ወደብ በመርከብ በኅዳር 27 ቀን 1877 ዓ.ም. ተነሥተው በጥር 25 ቀን 1877 ዓ.ም. ደርሰው ቤይሉል ላይ ተራግፈው ያለ ምንም ግጭት በባሕሩ ዳር ሠፈሩ ።

በዚህ ዐይነት ፥ የኢጣልያ ጦር፡ በምስጢር መጥቶ ቤይሉልን ሲይዝ የበታች ባላባቶች ትንሽ ቢከራከሩም ፥ ከኢጣልያኖች በየጊዜው የሸቀ ጥና የገንዘብ ስጦታ እየተቀበለ ሲወዳጅ የቆየው የአውሳው ባላባት መሐመድ አንፋሪ ተቆጥቶ ዝም አሰኛቸው ። እንደዚሁም በግብጽ መንግሥት ውስጥ ሆኖ ምሥራቅ ሱዳንን ፥ ምጥዋንና አካባቢውን የሚያስተዳድረው ኮሎኔል ቸርሚሳይድ የሚባለው እንግሊዛዊ ከእንግ ሊዝ መንግሥት ካይሮ ባለው በእንግሊዝ ቆንሲል በባሪንግ አማካይ ነት በምስጢር በተላለፈለት ትእዛዝ መሠረት ለግብር ይውጣ ያህል

የቃል ተቃውሞ አድርጎ በተግባር ግን ፣ ሠፈሩን ለቆ በሰላም እንዲመጣ ቤይሉል ላለው አዛዥ ትእዛዝ ስለ አስተላለፈለት ፣ የኢጣልያ ወታደሮች አላይ እንዳልነው ምንም ተቃውሞ ሳይደርስባቸው በሰላም ተቀመጡ ።[1]

## መ/ የኢጣልያ ጦር በምስጢር ምጥዋ ገብቶ በግልጽ መስፋፋት

ከዚህ ቀጥሎ አሁንም ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ስምምነቱ በዚሁ ዓመት በታኅሣሥ ወር እንዳለቀ ወደ ምጥዋ የሚላከው ጦር በምስጢርና በትጋት ይዘጋጅ ዠመር ። የሚያዘጋጁትም ሦስቱ የውጭ ጉዳይ ፣ የመርከብና የጦር ሚኒስቴር ባለ ሥልጣኖች ነበሩ ። ሦስት ባለ ላባ የእግረኛ ጦርና አንድ የመድፈኛ ጦር በጠቅላላው አራት የጦር ክፍል ተዘጋጀ ። የነዚህም ድምር 38 የጦር መኰንኖች ፣ 767 ወታደሮችና 2 ተራ ሠራተኞች በድምሩ 807 ነበሩ ። የነዚህም አዛዥ እንዲሆን ኮሎኔል ታንክሬዲ ሳሌታ ተመረጠ ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ጦሩ የሚላከው ምጥዋን ለመያዝ ሆኖ ሳለ ፣ ወሬውን ካገር ውስጥም ከውጭም ተወላጆች ለመደበቅ ሲባል የወታደሩ አላላክ ወደ አሰብ መሆኑንና ዓላማቸውም የአሰብን ወደብ ለማጠናከርና ቢቻልም የጉስታቮ ቢያንኪን ገዳዮች ለመፈለግ ነው የሚል አስወሩ ። ሚኒስትሮቹ ጉዳዩን ከራሳቸው ምክር ቤትም ደብቀዋል ። የሆነ ሆኖ ፣ ወታደሮቹ ከነስንቃቸውና ከነመሣሪያቸው በልዩ ልዩ የጦር መርከብ ተሣፈሩ ። የመርከቡም የበላይ አዛዥ ካይሚ ፒዬትሮ የሚባለው ተሾመ ። ለርሱም ሦስቱ ሚኒስትሮች የተስማሙበት ከዚህ ቀጥሎ ያለው መመሪያ በምስጢር ተሰጠው ።

1. ስለ ምጥዋ አያያዝ የኢጣልያ መንግሥት ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ያደረገው ስምምነት በጥብቅ ምስጢር መያዝ አለበት ። የነርሱ ስምምነት በቃልም በጽሑፍም አይጠቀስም ።
2. በምጥዋ ያለው ኮሎኔል ቸርሚሳይድ ዜግነቱ እንግሊዝ ቢሆንም ፣ አገረ ገዥነቱ የግብጽ መንግሥት መሆኑ እንዲታወቅ ፣
3. የኢጣልያ ጦር ምጥዋ ከገባ በኋላ ፣ አገረ ገዥውና የግብጽ የክፍል ጦር በምጥዋ ላይ ላጭር ጊዜ ይቆዩ ይሆናል ።
4. በዘይላና በበርበራ ፣ ከእንግሊዞች ጋር እንደ ሆነው በምጥዋም የግብጽ መንግሥት ባንዲራ በኢጣልያ ባንዲራ ጐን አዲስ ትእዛዝ እስኪመጣላችሁ ድረስ መውለብለቡን ይቀጥል ።
5. የባሕሩ አዛዥ የምጥዋን ወደብ ከያዘ በኋላ ፣ ለሕዝቡ በሚያስማው የይፋ ማስታወቂያ ላይ የኢጣልያ መንግሥት የእንግሊዝና የቱርክ ፣ የግብጽና የሐበሻም መንግሥታት ወዳጅ መሆኑን መግለጽ ጠቃሚ ይሆናል ።



የኢጣልያ ባለሥልጣኖች ፣ ይኽን የመሰለውን መመሪያ ለመርከቡ አዛዥ በሚሰጡበት በዚያው ሰዓት በግራንቪልና በማንቺኒ ፣ በሰርባሪንግና በዲማርቲኖ ፣ በከዲቭ ተውፊቅና በኑባር ፓሻ እንደዚሁም ምጥዋ ባሉት የግብጽ ባለሥልጣኖችና በኑባር ፓሻ መካከል ስለምጥዋ መያዝ ጉዳይ የመጻጻፉ ውዝግብ ቀጥሏል ። ከዚህ ሁሉ የቃልና የደብዳቤ መመላለስ የሚታየው ፣ የእንግሊዝ መንግሥት በሱዳን በኩል ለገጠመው ችግር ረዳቱ እንዲሆነው ሲል የምጥዋ ወደብ በኢጣልያ መያዙን ሲወደውና ሲደግፈው ፈቃዱና ድገፉው ግን ፣ በይፋ እንዳይታወቅበትና ከወዳጆቹ ከቱርክ መንግሥትና ከኢትዮጵያም በኩል ወቀሳ እንዳይደርስበት ይፈልጋል ። ደካማው የግብጽ ከዲቭ ደግሞ በኢኮኖሚና ባስተዳደር ጉሮሮውን ካነቀው ከእንግሊዝ መንግሥት ፈቃድ መውጣቱ አስቸግሮታል ። ስለዚህ የግብጹ ጠቅላይ ሚኒስትር ኑባር ፓሻና ኃይለኛው የእንግሊዝ ቆንሲልና ዲፕሎማት ባሪንግ ጧት ማታ እየተገናኙ ስለ ምጥዋ ወደብ በኢጣሊያኖች መያዝ ሁኔታ ይመካከሩ ነበር ።

የኢጣልያ ጦርም ከሲራጉዛ ወደብ ተጉዞ ሱአኪም በቆመበት ጊዜ ሕዝቡንና የምክር ቤት አባሎችን ለማደናገር ፣ “የጦሩ ጉዞ አሰብን ለማጠናከርና የቢያንኪን ገዳዮች ለመፈለግ ነው” ተብሎ በየጋዜጣው ተወርቶ የነበረው ቀረና አሁን የመከላከያው ሚኒስትር ዠኔራል ሪኮቲ ቀደም ብሎ ለዋናው የመርከቡ መሪ ለካይሚ በምስጢር የተነገረውን በማጽደቅ ወደ ምጥዋ እንዲጓዝ ትእዛዝ አስተላለፈ ። በዚህ ምክንያት ፣ በየካቲት 3 ቀን 1877 ዓ.ም. ከሱአኪም ተንቃንቀው በ4 የካቲት ወደ ማታ ምጥዋ ደርሰው በማግሥቱ የካቲት 5 ቀን ከመርከብ እየወረዱ የወደቡን ሥፍራ ይይዙ ዠመር ።


ነገሩን የሚያውቀው የእንግሊዙ ተወላጅና በግብጽ መንግሥት የምጥዋ አገረ ገዥ ኮሎኔል ቸርሚሰይድ ከጭቅጭቁ ለመዳን ሲል እዚያም ተገኝቶ ሳይከላከል ዝም ብሎ የኢጣልያን ጦር መቀበሉን ስለ ጠላው ፣ ከምጥዋ ዘወር ብሎ ወደ ሱአኪን ወደብ ሔዶ ተቀመጠ ። በዚህ ምክንያት ፣ ዋናው የመርከቡ አዛዥ ከነሹማምንቱ ወደ ወደቡ ወርደው ግማሹ ክፍል ወደ አርኪቆ የቀረውም ወደ አራፍሌ እየሔዱ ይዞታቸውን ሲያጠባብቁ ፣ ምክትሉ የምጥዋ አገረ ገዥ ኢዜትቤይና ዋናው ጸሐፊ ማርኮፖሊ ለስሙ ያህል እየተከራከሩ በቸልታ ወረራውን ይመለከቱ ዠመር ። ከልባቸው ለመከላከል ያሰቡትንም ዋናው ጸሐፊ ማርኮፖሊ ዐልፎ ዐልፎ እየተቆጣ ዝም አሰኛቸው ። ለስሙ ያህል ምክትል አገረ ገዥው ፣ “ምንም እንኳን እናንተን የምቋቋምበት

በቂ ኃይል ባይኖረኝ ስለ አደረጋችሁት ወረራ ተቃውሞዬን በጽሑፍ እገልጻለሁ” የሚል ለኢጣልያኑ የጦር አዛዥ ደብዳቤ ልኮ ዝም ብሎ ተቀመጠ ። የመርከቡም አዛዥ ሕዝቡን ለማጭበርበር ፣ “የኢጣልያ ጦር የመጣው በሰላም ንግድን ለማስፋፋት ነው ። የኢጣልያ መንግሥት ለእንግሊዝ ፣ ለቱርክ ፣ ለግብጽ ፣ ለሐበሻ መንግሥትም ጭምር ወዳጅ ነው” የሚለውን ማስታወቂያ አወጣ ። አባባሉም ወደዚህ ወደብ የገባነው በነዚህ መንግሥታት ፈቃድ ነው ለማለት ነው ። የመርከቡ አዛዥ በዚህ ዐይነት ኮሎኔል ሳሌታን ካጠነካከረ በኋላ እርሱ ወደ ኢጣልያ ተመለሰ ።

ኮሎኔል ሳሌታ ፣ በለሰለሰ አንደበት ምጥዋ ከነበሩት ከግብጾቹ ባለሥልጣኖች ጋር በተለይም ከዋናው ጸሐፊ ከማርኮፖ'ሊ ጋር እየተ ስማማ ለወታደሩ መኖሪያ የሚሆን ቤት ፣ ዕቃና ስንቅ ፣ መድኃኒቱን የሚያስቀምጥበት መጋዘን አሠራ ። በተለይ ባሁኑ ጊዜ የምጥዋ አየር አዲስ ለመጣው ጦር እንግዳ ሆኖ ስላልተስማማው ፣ በዚህም ላይ የምጥዋ ባሕር ጨውና ለመጠጥ የማይመች ስለሆነ ከምጥዋ 8 ኪሎ ሜትር ርቆ ከሚገኘው ከእርኪቆ (ደሆኖ) ከጉድጓድ እያስቀዳ አስጋዘ ። የሕክምና ክሊኒክም አሠራ ። በዚሁም ጐን “ኢጣልያ ምጥዋ የገባው ለሰላም ፣ ለንግድና ለልማት ነው” የሚባለውን ሐሰተኛውን ስብከት እያስፋፋ ያገር ተወላጁን ለማቀራረብ ይሰብክ ዠመር ። ብዙ እስላ ሞችም እንዲጠጉት አደረገ ። ለቀረቡትም የሐባብ ተወላጆችና ባላባ ቶች “ጠባቂያችሁ ነን ፤ አይዟችሁ” እያለ ይናገር ዠመር ። የሐባብ ባላባቶችም አንዳንድ ጊዜ ለነራስ አሉላ አንገርብም እያሉ እየሸፈቱ አስቸግረው የነበረው ፣ አሁን ወደ ኢጣልያ ተጠግተው የነራስ አሉላን ትእዛዝ ለመቃወም ቀናቸው ።


በየካቲት 5 ቀን ምጥዋን የያዘው የኢጣልያ ጦር እስከ ኅዳር ወር መጨረሻ በዐሥር ወራት ውስጥ ይዞታውን እያጠባበቀ ሲሔድ ከግብጾቹ ባለሥልጣኖች ጋር እያደር ተስማማ ። በግብጽ ባለሥልጣኖች ይታዘዙ ለነበሩት ለሲቪሎቹም ለባሽ ቡዙቆችም ከግብጽ በኩል የሚከፈላቸው ቀለብ ስላቆመ ፣ አንዳንዶቹም ወደ አገራቸው ሲመለሱ ለቀሩት በሙሉ ቀለባቸውን እየከፈለ እንዳሉ ወደርሱ ዞረው እንዲያ ገለግሉት አደረገ ። በሚቀጥለውም ጊዜ በካይሮ የእንግሊዝና የኢጣ ልያ ባለሥልጣኖች ከዲቭ ተውፊቅንና ጠቅላይ ሚኒስትሩን ኑባር ፓሻን ገፋፍተውና አግባብተው ወደ ምጥዋ ትእዛዝ እንዲተላለፍ አድ ርገው አስተዳደሩም ፣ ጉምሩኩም ሁሉ በሙሉ ከታኅሣሥ 2 ቀን 1878 ዓ.ም. ዠምሮ በኢጣልያ መንግሥት እጅ እንዲዞር አደረጉ ። በኢጣልያ ባንዲራ ጐን ይውለበለብ የነበረውም የግብጽ ባንዲራ ወርዶ ከባለሥልጣኖቹ ጋር ተጠቅልሎ አገሩ ገባ ።





የኢጣሊያ ጦር ምጽዋ ላይ ከመርከብ ሲወርድ

(ከኢጣሊያኢን አፍሪካ
የሩዶልፍ ማዙኮኒ መሐጽፍ ተወሰደ)



የኢጣሊያ ጦር ምጽዋ ከገባ በኋላ የተስፋፋባቸውን የምንኩሎን ፡ የዶጋ ሊን ፡ የሰሐጢን ፡ የዊአን ፡ የዙላንና የአራፋሌን ቦታዎች የሚያሳይ ካርታ

# ምዕራፍ ሠላሳ ሦስት

## በምጥዋ መያዝ የኢጣልያና የእንግሊዝ መንግሥት ውስጠ ስምምነት—የቱርክ መንግሥትና የኢትዮጵያም ተቃውሞ

፩

የኢጣልያ መንግሥት ለመያዝ ያለመው አገር ብዙ ነበር ። እዚያው አጠገቡ አልባንያንም ወይም በአፍሪካ ሰሜን ላገሩ ቀረብ የሚሉትን ቱኒዚያንና ሊቢያን ለመያዝ አስቦ ነበር ። ነገር ግን፣ በሊቢያ ቱርክን ፈራ ። ቱኒዚያም በፈረንሳይ መንግሥት ስለ ተያዘ መሪዎቹ በጣም ተናደዱ ። በእስያም በኩል ሰቆጥራ ታስቦ ነበር ፤ አመቺ አልሆነም ።

ስለዚህ በማናቸውም ረገድ ደፕሬቲስና ማንቺኒ በጉዳዩ ከእንግሊዝ መንግሥት መሪዎች ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሎርድ ግላድስተን ፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከሎርድ ግራንቪል በየአምባሳደሮቻቸው አማካይነት ሲጻጻፉበት ፣ ሲወያዩበት ቆይተው የቅኝ ግዛት ፍላጎታቸውን ግብጽ ለመልቀቅ በሚሰናዳበት በምጥዋ ወደብና በምድረ ባሕረ የቀይ ባሕር አካባቢ ላይ ወሰኑ ።

በዚህ ጊዜ ፣ የእንግሊዝ መንግሥት በአደን ፣ በዘይላና በበርበራ ከወዲህም በግብጽና በሱዳን ላይ ሥልጣኑን ዘርግቶ በጠቅላላው ከቱርክና ከግብጾቹም ሳይጣላ የራሱን ግዛት በሚያጠብቅበት ጊዜ ምጥዋን ከፈረንሳይ ቀድሞ የኢጣልያ መንግሥት ሲይዘው እንደማይቃወም ለኢጣልያ መሪዎች በገሃድ አረጋገጠ ። ይሁን እንጂ ፣ ኢጣልያኖች ምጥዋን ስንይዝ ከኢትዮጵያ የበለጠ ከቱርክ ወይም ከፈረንሳይ ጋር እንጋጭ ይሆን እያሉ በመፍራት በጉዳዩ ማለትም በወደቡ እያያዝ የእንግሊዝ መንግሥት እንዲተባበር ለማግባባት ሲጥሩ ፣ እንግሊዝ ደግሞ ከነዚህ አገሮች ጋር በሰላም ለመኖር ምኞቱ ስለነበር ፣ ከኢጣልያ ጋር በግልጽ ለመተባበር አልፈለገም ። እንግሊዝ በከለላና በለናሂት ከደርቡሾች ጋር በሚያደርገው ትግል ኢጣልያ በጦር ኃይል ጭምር እንድትረዳው ሲፈልግ ፣ ኢጣልያ ምጥዋን መያዟን ሲሰማ የሞራሉን ድጋፍ ዐልፎ በጦር ኃይል መተባበሩን በፍጹም አልፈለገውም ። መፍቀዱም ራሱ እንዳይታወቅበት ይጣጣር ነበር ።

ኢጣልያ በቤርሊኑ የስምምነት ክፍያ በመዠመሪያው ላይ እንደ ኃያል መንግሥት ባለመቆጠሯ አልተካፈለችም ነበር ። ለመካፈል ገና የቅኝ አገር ካለመያዟ በቀር የመንግሥትነቷ አቅዋም ስለ አልተጠና ከረ ፡ ብትዘገይም ባሁኑ ጊዜ ለእንግሊዝ መንግሥት መሣሪያ ሆና ባንድ የአፍሪካ አሀጉር ገብታ ለመስፋፋት ፍላጎቷ ስለ ገፋፋት በሚ ቀጥለው ጊዜ ወደ ስምምነቱ ገብታለች ።

ስለዚህ ባለፈው እንዳመለከትነው በምክር ቤትም ፡ በጠቅላይ ሚኒስቴርም ፡ በውጭ ጉዳይም ሚኒስቴር አካባቢ የሚያዘው አገርና ወደብ ምቹነቱ ፡ ቅርበቱ ፡ ጥቅሙ ፡ የሚያስከትለው መዘዝ በብዙ አቅ ጣጫ ሲጠና ከ1872—77 ዓ.ም. ድረስ ቆየ ። በመጨረሻ ቅኝ ግዛት ለማግኘት የጓጓው የኢጣልያ መንግሥት ዐይን ፡ በተለይ በምጥዋ ወደ ብና በጠቅላላውም በኢትዮጵያ ላይ ዐረፈ ። ምጥዋም ከተያዘ በኋላ አብዛኛው ለሜናዊውና ማዕከላዊው ክፍል ለኢጣልያ የመስፋፊያ ክፍል ተብሎ እንግሊዞቹም በጽሑፍ ሳይሆን በቃል ተስማሙበት ። ጣልያኖች በኢትዮጵያ ላይ ለማተኮር የቻሉበት ምክንያት ፡—

ሀ/ በነጻ የተቀመጠች አገር በመሆኗ ፡

ለ/ ኋላቀር በመሆኗ ወደቡን ይዤ አስተዳድራለሁ የሚለው አቅዋሟ የመነመነና በሌሎቹም ኃያላን መንግሥታት ዘንድ ተቀባይነት ስለ አልነበራት ፡

ሐ/ በውስጧ ያለው የሕዝቡ ኅብረት ፡ የመሳፍንቱ አንድነት ያልተዋሐደና ጠላትን ለመከላከል በቂ ጉልበት ያለው ማዕ ከላዊ መንግሥት ስለአልነበራት ፡

መ/ በቱርክና በግብጽ የደካማነት መሽቆልቆል ጐን በእንግሊ ዝና በፈረንሳይ ባላንጣነት መካከል ያን ጊዜ ኃይሉ በማና ቸውም መስክ በርታ ብሎ የሚታየው የእንግሊዝ መንግ ሥት ድጋፉነቱ ስለ ተገኘ ነበር ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት ፡ የኢጣሊያ መንግሥት ለዚህ ለቅኝ አገር ዓላማው በተለይ ወደ ምጥዋ ወደብ ያንድ ክፍል ጦር ለመላክ ከመዠ መሩ በፊት ፡ በሎንዶን በሚቀመጡት አምባሳደሮቹ ወይም ሮማ በሚቀ መጡት የእንግሊዝ ወኪሎች በኩል የኢጣልያ መንግሥት ወደ ምጥዋ የሚገባው በእንግሊዝ ፈቃድ ሲሆን ፡ በዚህ ምክንያት ከማናቸውም አቅጣጫ ጠብ ቢነሣ የእንግሊዝ ፖለቲካዊና ቢያስፈልግም ወታደ ራዊ እርዳታ እንዲገኝ የኢጣልያ ባለሥልጣኖች በተለይ ለዚህ ጉዳይ አግባብ የነበረው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ማንቺኒ እንግሊዞቹ ሰልች ቷቸው እስኪመረሩ ድረስ በቃልም በጽሑፍም ሲወተውት ነበር ።



አንድ ጊዜ ማንቺኒ ምጥዋን ለመያዝ እንግሊዝ ከኢጣልያ ጋር ተባብ ሯል የሚል ቃል በምክር ቤት ጉባዔ ላይ መወርወሩ ስለተሰማ ፡ በእንግሊዝና በኢጣልያ መንግሥታት መካከል መጠነኛ ቅራኔ ተፈጥሮ እንግሊዞቹ ለማስተባበል ተገደው ነበር ።

የእንግሊዝ መንግሥት ፡ የባለብዙ አገር ጌታ እንደ መሆኑ መጠን ጉዳዩን የሚመለከተው በብዙ አቅጣጫ ነበር ። የኢጣሊያንና የኢትዮ ጵያን መንግሥታት በተቻለ መጠን ለራሱ በሱዳን በኩል ለገጠመው ችግር በመጠኑም ቢሆን መሣሪያ ለማድረግ ይፈልጋል ። ይሁን እንጂ ፡ ራሱ ለኢጣልያ የመስፋፋት ዓላማና ለኢትዮጵያ የመከላከል ተግ ባር ግልጽ መሣሪያ ሆኖ ኢጣሊያ ምጥዋ የገባችው በእንግሊዝ ፈቃድ ነው ተብሎ ከቱርክም ፡ ከፈረንሳይም ፡ ከኢትዮጵያም ጋር በገሃድ መጣ ላቱን በፍጹም አይፈልገውም ። ቱርክም ግብጽም በሚለቋቸው በዘ ይላ ፡ በበርበራ ፡ በአደን ፡ በሱዳን መተካት የሚፈልገው ከነዚህ መን ግሥታት ጋር ተጣልቶ ሳይሆን ባንድ ወገን የነርሱ ወዳጅ መስሎ ፡ በሌላ ወገን በዚያው ሰዓት ውድቀታቸው እንዲፋጠን በነዚሁ አገሮች ባስቀመጣቸው በራሱ የፖለቲካ ወኪሎቹ አማካይነት እየገዘገዘ ነው።

ስለዚህ ፡ እላይ እንዳመለከትነው ፈረንሳይ ሳይገባበት ፡ አበሻም እጅ ሳይወድቅ ኢጣልያ ወደ ምጥዋ መግባቷን ውስጡን በቃልም በምስ ጢራዊ ጽሑፍም ሲስማማ በገሃድ መጸፋንም መናገሩንም አይፈልገ ውም ። ኢጣልያም የእንግሊዝን የቃል ኪዳን ጓደኝነትና ሙሉ ትብ ብር ሳይጨብጥ ምጥዋን ይዞ ከፈረንሳይም ከቱርክ ጋርም መጣላቱን ፈራ ። በዚህ የተለያየ አሳብ ውስጥ ሁለቱም በቃልም ፡ በጽሑፍም በገሃድም ፡ በምስጢርም ሲወዛገቡ ቆዩ ። አንድ ጊዜ የኢጣልያ መን ግሥት ባለሥልጣኖች "ወታደሮቻችን ወደ ቀይ ባሕር የሚዘልቁት ለእንግሊዝ ጥቅም ነውና በወታደራዊ ተግባርም በኩል በኅብረት እን ሥራ" የሚል አሳብ ቢወረውሩ ፡"የእንግሊዝ መንግሥት የማንንም እርዳታ ሳይፈልግ የራሱንም ጉዳይ በራሱ ይወጣዋል ። እናንተም ወደ ምጥዋ የምትገቡት ፡ በራሳችሁ ምኞትና ለራሳችሁ ጥቅም ነው እንጂ ለእንግሊዝ ስትሉ አይደለም" የሚል ቁጣ የተንተራሰ ደረቅ መልስ ግራንቪል ሰጥቶ ነበር ። የሆነ ሆኖ ፡ የእንግሊዝ መንግ ሥት አቅዋም ኢጣልያ ከሌላ መንግሥት (ፈረንሣይ) ቀድማ ወደ ምጥዋ ብትገባ ወይም በቀይ ባሕር አካባቢ አንድ ወደብ ወይም ቀበሌ ብትይዝ የሚደሰት እንጂ ፡ የማይከፋ መሆኑን ገልጾ ይኸንንም የኢጣልያ መንግሥት ከእንግሊዝ ጋር እንዳደረገው ስምምነት ፡ ከቱርክና ከግብጽ መንግሥት ጋርም መልካም ስምምነትና ግንኙነት ፈጥሮ በወዳጅነት በኩል ቢፈጸም የበለጠ የሚደሰት መሆኑን ቁርጥ ባለ አኳኋን ተናግሮአል ።

በዚህ ዐይነት ፡ የኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማንቺኒና በሎንዶን የነበረው አምባሳደሩ ኒግራ ኮስጠንጢኖስ ከእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ከሎርድ ግላድስተንና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከሎርድ ግራንቪል ጋር አሳብ ለአሳብ በቃል እየተለዋወጡ ሲወያዩበትና በደብዳቤም ሲጻጻፉበት ከቆዩ በኋላ ፡ በጠቅላላው በገሃድ ጽሑፍም ባይሆን በቃልና አወላዋይ ሁኔታ ባለበት የጽሑፍ ሰነድ የእንግሊዝን ውስጠ ፈቃድና ድጋፍ ካገኘ በኋላ ፡ ኢጣልያ የምትልከውን ጦር ታዘጋጅ ዠመር ። የእንግሊዝ መንግሥትም በያለበት በካይሮም ፡ በምጥዋም ለነበሩት የራሱ ወኪሎች የኢጣልያ ጦር ወደ ቤይሉልም ፡ ወደ ምጥዋም ሲገባ ለይምሰል ስለ ቱርክና ስለግብጽ አድልተው ለግብር ይውጣ ቢከራከሩም ፡ በጠቅላላው ግን በማንኛውም መንገድ ኢጣልያኖችን እንዲደግፉ እንጂ ተቃውሞ እንዳያደርጉ በምስጢር ትእዛዝ አስተላለፈ ።

የግብጹ መሪ ከዲቭ ተውፊክና ዘተለይም የአርመኑ ተወላጅ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኑባር ፓሻ ካይሮ ከሚገኙት ከእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ከነባሪንግ ፡ ከኢጣልያ ዋና ቆንሲል ከማርቲኖ ጋር አብሮ በመብላትና በመጠጣት ፡ የቱርክን መዳከም ፡ የራሱም የግብጽ መንግሥት በየሥፍራው ፡ በየወደቡ ላስቀመጣቸው ወታደሮቹ የሚከፍለው ገንዘብ እስከ ማጣት ደርሶ በኢኮኖሚ መውደቁንና በርሱ አንጻር የእንግሊዝን ፡ በማናቸውም መስክ መበርታቱን በመገንዘብ ፡ ልቡን ወደ እንግሊዝ አድርጎ ዋና መሣሪያ ሆኖ ነበር ።

በዚህ ሁሉ የፖለቲካ ውዝግብ ውስጥ የምጥዋ ወደብ በታሪክና በጂዎግራፊ አቀማመጥ ባለቤትነቷ የታወቀው ኢትዮጵያ ከምንም አልተቆጠረች ። በእንግሊዝም ሆነ በኢጣልያ በኩል ያለው ሥጋት ከቱርክ መንግሥት ወይም ከፈረንሳይ በኩል ለሚሠነዘረው ተቃውሞ እንጂ ፡ ከኢትዮጵያ ወገን ያለው አሥጊ ሆኖ አልተገኘም ። በዚህ ምክንያት የኢጣልያ መንግሥት ወደ ምጥዋ የሚያዘምተውን ጦር በምስጢር ያዘጋጅ ዠመር ።

የእንግሊዝና የኢጣልያ መንግሥታት ግብጽን እንደ አግባቡ ሁሉ በልዩ ልዩ ዘዴ የቱርክ መንግሥትንም በጉዳዩ እንዲስማማበት ለማድረግ መሞከራቸው አልቀረም ። በባሪንግና በደማርቲኖ ፡ በኑባር ፓሻ ግፊት "በዐቅም ማጣትና በኢኮኖሚ ውድቀት የተነሣ አገሩን መያዝ አልተቻለኝም ምን ይሻላል ?" ብሎ የግብጹ ከዲቭ ለቱርኩ ሡልጣን እንዲጽፍ አድርገው ቱርክም እንዲለሰልስ በቀጥታም በጎንም ከመጣጣር አላለፉም ። የቱርክ መንግሥት ምጥዋንና አካባቢውን ሁሉ እንደራሱ ግዛት ስለሚቆጥረውና ግብጽም 16.000 ስተርሊን ያመት



ግብር እየከፈለ ምጥዋን ሊያስተዳድረው የቻለው በቱርክ መንግሥት ፈቃድ ስለነበረ ፡ ለጊዜው በምጥዋ መያዝ በእንግሊዝና በኢጣልያ ፊት እንደ ግብጽ አልተስማማም ነበር ። እንዲያውም ኢጣልያኖቹ ምጥዋ ስንደርስ የቱርክ የጦር መርከቦች መጥተው ይወጉን ይሆን የሚል ሥጋት ስለ ነበረባቸው ፡ ከናፖሊ በስዊዝና በሱአኪም ሲያልፉ ጉዟቸው ምሥጢራዊ ነበር ። ይሁን እንጂ ፡ በፊትም ቤይሉል የተያዘ ጊዜ በሮማም ፡ በእንግሊዝም አገር የነበሩት የቱርክ የፖለቲካ ወኪሎች የኢጣልያ መንግሥት በፊት አላግባብ አሰብን መያዙ አንሶት በቅርብ ጊዜ ቤይሉልን መያዙን ሲቃወሙ ሰንብተው ነበር ። አሁን ደግሞ ፡ ስለምጥዋ መያዝ ጉዳይ የግብጽ ከዲቭ ተውፊቅ ፓሻ ራሱን ከቱርክ ሡልጣን ቁጣ ለማዳን ሲል ፡ "ኢጣልያኖቹ ምጥዋን ይዘዋል ዐቅም በማጣት በኃይል ለመቋቋም ስለ አልቻልኩ ተቃውሞዬን በጽሑፍ አገልጣለሁ" ብሎ ወደ ስጣንቡል ለሡልጣኑ ስለላከ ፡ ሮማ የሚቀመጠው የቱርክ ጉዳይ ፈጻሚ ፡ አሁንዲ ሚህልን የሚባለው ለኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለማንቺኒ ከመንግሥቱ የተላለፈለትን ትእዛዝ መሠረት በማድረግ የኢጣልያ መንግሥት በቤይሎልና በምጥዋ ወታደር የላከ ጊዜ ያላላኩ ሁኔታ አገር ለመውረርና መሬት ለመያዝ እንዳልነበረና የሡልጣኑንም ግዛት በሙሉ እንደሚያከብር ገልጾ የነበረውን በመጥቀስ በቃልም ፡ በጽሑፍም ክርክሩን አቀረበ ።

እንደዚሁም በዚሁ ጊዜ ሎንዶን ተቀምጦ የነበረው ምስሩስ የሚባለው የቱርክ አምባሳደር በዚሁ ዐይነት ከእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖች ጋር ተከራክሮ ነበር ። ነገር ግን ፡ የእንግሊዝ ዲፕሎማቶች 'ምን ይደረግ የቱርክ መንግሥት ቀበሌውን ራሱ ይዞ በደንብ ሊቆጣጠር አልቻለም ፤ ግብጽም በደርቡሾች አነሣሥ ስለ ተዳከመ አስተዳደሩን ይዞ ለመቀጠል አልተቻለውም' በማለት በተለመደው ዘወርዋራ የፖለቲካ የአነጋገር ዘዴ አንድ ጊዜ የሆነውን የቱርክ መንግሥት በትዕግሥት እንዲቀበለው ስለገፋፉ ፡ የቱርክ መንግሥትም ከ16ኛው መቶ ዓመት ዠምሮ በመካከለኛው ምሥራቅ ፡ በባልካን ፡ በአፍሪካ ምሥራቅና ለሜን ግዛቱን ከልክ ያለፈ አስፋፍቶ ሳለ ፡ አሁን እንግሊዞችና ፈረንሳዮች በያለበት እየገዘገዙ ባስተዳደርም በኢኮኖሚም ስለ አደከሙት ፡ የኢኮኖሚ መድከም የጦር ኃይልን መዳከም በግድ ስለሚያስከትል ፡ በእንግሊዝ የተደገፈው ጣልያን በግዛቱ ሲገባ ከቃልና ከጽሑፍ ክርክር ዐልፎ በጦር ኃይል ለመቃወም ስለ አዳገተው ፡ ጉዳዩን ፈጽሞ ችላ ማለትና የቀረውን ግዛቱን ለመጠበቅ ወሰነ ። ስለዚህ በዚህ ጉዳይ የመጨረሻዋም ፡ የመዠመሪያዋም የፖለቲካና የኃይል ተቀዋሚ ኢትዮጵያ ብቻዋን ሆና ተገኘች ።

ዐፄ ዮሐንስ ፡ የኢጣልያ ምጥዋን መያዝ ዝርዝር ሁኔታውን ከብዙ አቅጣጫ ሰምተውታል ። አንደኛ በተግባር በራስ አሉላ ውስጥ ሆነው ጊንዳን ከሚያስተዳድሩት ከባላምባራስ ተሰማና የአይለትን አካባቢ ከሚያዙት ከሻለቃ አርአያ በቀጥታም በራስ አሉላም በኩል ሰምተውታል ። ሁለተኛ ዶክተር ፖሪሲስ ኒኮላ የሚባለው የግሪክ ተወላጅ ከግሪክ ንጉሥ ከጆርጅ አንደኛ ተልኮ መጥቶ ያፄ ዮሐንስ ባለሟል አገልጋይ ሆኖ ነበርና እርሱ ከየጋዜጣውም እያነበበ ሁኔታውን ሳያስረዳቸው አይቀርም ። ሦስተኛ ከሁሉ የበለጠ እያስፋፋ ነገሩን ከምንጩ በሎንዶንና በሮማ መካከል የተደረገውን ውስጠ ስምምነት እየተነተነ ያስረዳቸው ሙሴ ጋስቶን ለሜይ የሚባለው የፈረንሳይ ቆንስል ነበር ፡

እርሱም ከአደን ወደ ሱዳን ሔዶ በቆንሲልነት እንዲሠራ ስለታዘዘ ፡ ከአደን መጥቶ ምጥዋ ውሎ ባደረበት ጊዜ የኢጣልያ ጦር በወደቡ ሲራገፍ ባይኑ ያየውን በደብዳቤ አድርጎ ልኮባቸዋል ። ከዚህ በኋላ ራሱ ከምጥዋ ወደ መቀሌ መጥቶ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በተገናኘበት ጊዜ መቸም እንግሊዝና ኢጣልያ የተመሳጠሩት በኢትዮጵያ ላይ ብቻ ሳይሆን በፈረንሳይ ላይ ጭምር ስለነበረ ፡ ቆንሲሉ የእንግሊዝና የኢጣልያ ባለሥልጣኖች በአውሮፓ የተለዋወጡትን ውስጣዊውንም ውጫዊውንም ስምምነት ፡ ከመንግሥቱም በሚላክለትና ራሱም ከየጋዜጣው በሚያነበው መሠረት ለነዐፄ ዮሐንስ ፡ ለነራስ አሉላ ስውር የሆነውን የፖለቲካ የጽሑፍ ልውውጥ እርሱ የተረዳውን ያህል ባሁኑ ጊዜ ላፄ ዮሐንስ በትክክልና በዝርዝር አስገንዝቧቸዋል ። [1]

በዚህ መካከል ፡ በመቀሌ ሆኖ ችግር የገባው ጃኮሞ ናሬቲ የሚባለው የኢጣልያ ተወላጅ ነበር ። እርሱም ለዚያን ዘመን በተለይ ለኢትዮጵያ ብርቅና ድንቅ የሆነውን የመቀሌን ቤተ መንግሥት በሕንፃ አሳምሮ ከነዙፋናቸው ከሠራ ወዲህ በጣም ባለሟል ሆኖ ተሾሞ ፡ ተሸልሞ በፊተኛው ጊዜ የሚመጡትን ያገሩን አገር ጐብኝዎች እንደ ልቡ እያስወጣ ፡ እያስገባ ቆይቶ ሳለ ፡ አሁን የርሱ ወገኖች ምጥዋን ወርረው በጠላትነት አቅዋም ሲገኙ የርሱ የባለሟልነት ይዞታው ተበላሸበት ። ስለዚህም ራሱ ምጥዋ ለነበረው ለኢጣልያ የቆንሲል ወኪል ፡ ለሲኞር ሎካርዲ ጆሴፔ በጻፈለት ደብዳቤ ላይ ፡

"...ኢጣልያ ከእንግሊዝና ከግብጽ ተስማምታ ምጥዋን በያዘችበት ባሁኑ ጊዜ የፈረንሳይ ቆንስል ለሜይ ይኸንኑ በደብዳቤ ስለገለጠላቸው ፡ ንጉሠ ነገሥቱ በምን ምክንያት ይኸንኑ እንግሊዝ

1 A. Del Boca, Gli Italan in Africa, pp. 193—220.



ሳይነግረኝ ቀረ ብለው መቆጣታቸውን ከገለጸ በኋላ ከዚሁ እያይዞ ፡ "የምጥዋ እያያዝ በኔ ምክንያት እንደሆነ በማሰብ ሰሞኑን ፊት ነሥተውኛል" የሚል ይገኝበታል ። ከዚህም በኋላ አሁንም ምጥዋ ለኢጣልያ እንደ ቆንሲል ሆኖ ከግብጾቹም ፡ ከእንግሊዞቹም ጋር በመተባበር የኢጣልያኖቹን አያያዝ ወዲያና ወዲህ እያለ ያከናውን የነበረው ሌላው ማይላ ፌሊቼ የሚባለው በበኩሉ ለኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የናሬቲን ራፖር በላከው ጽሑፍ ላይ ፡ "ባሁኑ ጊዜ የንጉሠ ነገሥቱ አስተያየት በኢጣልያ ላይ መጥፎ ነው ። በምጥዋ የኛን ይዞታ በርከት አድርጎ እያስፋፋ ፡ እየቀባባ ከሚያስረዳቸው ከፈረንሳዩ ቆንሲል ከለሜይ መስማታቸው ጥሩ አልሆነም ። የፈረንሳዩም ቆንሲል ባሁኑ ጊዜ በአጠገባቸው ተቀምጦ የኛን ዓላማ ለማፈራረስ ይጣጣራል" የሚል ይገኝበታል ።

የሆነ ሆኖ ፡ ዐፄ ዮሐንስ ይኸን ሁሉ እየሰሙ ከብዙ ጊዜ ዠምሮ እንደ ወዳጅ የሚቆጥሩት እንግሊዝ ይኸን በማድረጉ ከፍ ያለ ትዝብት ቢያሳድርባቸውም ፡ ለጊዜው ለጠብና ለውጊያ አልቸኮሉም ። አምናውን በሔዊት አማካይነት ከግብጾች ጋር የተዋዋሉትን ውል መሠረት በማድረግ ከእንግሊዞችም ጋር ከመቅደላው ጦርነት ዠምሮ በነበራቸው ወዳጅነት ላይ በመተማመን ፡ "በውሉ መሠረት በግብጽና በቱርኮች ይዞታ የነበረውን ወረዳ ሁሉ እጄ አደርጋለሁ ፡ በምጥዋ ወደብም እንደልቤ የፈቀድሁትን ሸቀጥና የጦር መሣሪያ ያለቀረጥ አገኛለሁ" ብለው ተስፋ በማድረግ በብዙ ቦታ የተከበቡትን ግብጾች ከደርቡሾቹ ጋር ተዋግተው ከሞትና ከምርኮ በማስጣል መሪና ስንቅ እየሰጡ በሰላም ወደ ምጥዋ በብዙ ድካም ከሸኙ ወዲህ አሁን የእንግሊዝና የኢጣልያ መንግሥታት ከግብጽም ጋር ውስጣዊ ስምምነት አድርገው ውሉን በማፍረስ ወይም ወደ ጐን በማድረግ የኢጣሊያ ወታደሮች ወደቡን መያዝ ብቻ ሳይሆን ፡ እያለፉ አገር መያዛቸው የኢትዮጵያንም ነጋዴ መቅረጣቸው ፡ "ይኸ ይለፍ ፡ ይኸ አያልፍም" እያሉም ማስቸገራቸው በጣም እንዳሳዘናቸው ከዚህ ቀጥሎ ለንግሥት ቪክቶርያ የጻፉት ደብዳቤ ያስረዳል ። ደብዳቤው የተዘጋጀው በራሳቸውና በዘመኑ አነጋገር መሆኑን አንባቢው ይረዳዋል ።

"በስመ እግዚአብሔር ... ይድረስ ኃበ ክብርት ወልዕልት ቪክቶርያ ... ቀድሞ ስንዋዋል ከቱርኮች * ጋራ ስንታረቅ መሬቱን

* ዐፄ ዮሐንስ በየደብዳቤያቸው ላይ ግብጾችን ቱርኮች ነው የሚሉት ፤ ይሁን እን ሁለቱ ሕዝቦች በአገዛዝና በአስተዳደር በሃይማኖት ቢገናኙም ፤ በዘርና በቋንቋ ይለያያሉ ።

አገሬን ሊለቅልኝ (ሊለቁልኝ) በሞገስ (በጎስ) በእመጂ ፥ በኬሰላ ፥ በመተማና በጌራ ያለ የቱርክ ወታደር ሲለቅ መድፉን ጠበንጃውን አረሩን (ባሩዱን) ትተውልኝ ሊሔዱ እርቅ ነበረን ። እነዚያ እንኳንስ መድፍና ጠበንጃ. . . ሊተዉልኝ ገንዘባቸውን ሰብስበው ይዘው ሔዱ. . . ሠራዊቴን እያሰፈጀሁኝ ቱርኮችን እያወጣሁኝ ወዳገራቸው ሰደድሁ. . . ሠራዊቴን በክረምት ሰድጄ በጦርና በጕርፍ እያለቀ አስወጥቼ አመጣሁ ። ይህን ሁሉ ማድረጌ የናንተን ፍቅር ፈልጌ ነው እንጂ ስንዋዋል ፥ ስንጽፍ ፥ ስናትም አውጥቼ ልሰድ ከውል አላገባነውም ። ለጥንት ልጅ ለልጅ ሊሆን የታረቅነውን አሁን ዓመት ሳይሆነው ውሉ ፈርሶ የምጥዋን በር እይዛለሁ ስል ቱርኮች ቢለቁ ኢጣልያ መጥቶ ምጥዋንም ፥ ሌላውንም አገሬን ያዘብኝ ። የቀድሞ ነገሥታት አባቶቼ ከአውሮፓ ነገሥታትና ከሌሎች የክርስቲያን ነገሥታት ፍቅር ነበሩ እንጂ ጠብ አልነበራቸውም ። ከቱርኮችና ከእስላሞች ጋር ሁልጊዜ ጠበኞች ናቸው ። አሁን እኔ ይህን ማለቴ የላንተን ፍቅር የላንተን ልብ የያዝሁ መስሎኝ ነው ። ውሉ ፈርሶ እንዲሆን እኔ ግድ የለኝም ። ገንዘባችሁንና ሰዋችሁን የፈጀ ደርቡሽ ነው እንጂ እኔ የበደልሁት ነገር የለኝም መልካም ነገር ከማድረግ በቀር ። አሁንም የኢጣልያ ጦር መምጣቱ በላንተ ፈቃድ ነው ። እሱ ተጋፍቶ የኔን አገር ሊወስድ ነው ። የዚህ ብልሃቱ ጠፍቶኛል ። በላንተ ፈቃድ መጥቶ እንዲሆን ውሉ ከቀረ ካገሬ ከመጣብኝ የምፈራው የለኝም ። እሱም (የኢጣልያ ንጉሥ) እምባጫራ ሳለሁ ሰው ሰዶ እንደ እንግሊዞችና እንደ ቱርኮች እኔም ልጻፍ ፥ ላትም(ልዋዋል) ብሎ ላከብኝ ። እኔም ካገሬ አትድረስብኝ እንጂ በነዚያ ውል እሺ ጻፍ አትም ከፍቅር ላይ ፍቅር ቢጨመርልን ጠልቼ ብዬ ላከሁበት ። አሁን ይህን ትቶ ነፍጥ እንዳይወጣ (ጠበንጃ እንዳልገዛ) ከለከለ ። ደግሞ ቱርኮች ይዘውት የነበረውን አገር እስከ ጨው (እሰል) ዳርቻ ድረስ ወታደር ሰዶ እያሰለለ መያዝ ዠመረ ። አሁንም የምጥዋን በር ይሰጡኝ ቀድሞም የአባቶቼ የነገሥታት እንደሆነ ያውቃሉ ። የተለቀቀበት ጊዜም ቅርብ እንደሆነ አይጠፋዎም ። የመጣውም ጠላት ቢይዝብኝ ግድ የለም ። ካገሬ የመጣብኝን ጠላት እችላለሁ ።”

ደብዳቤውን የጻፉት ደብረ ታቦር ላይ ነሐሴ 23 ቀን 1877 ዓ.ም. መሆኑን በግርጌው ላይ በተለመደው የግዕዝኛ አጻጻፍ ተመልክቷል ።[1]

በዚህ ደብዳቤ ዐፄ ዮሐንስ በሒዊት ውል ላይ በትክክል መቆማቸውን እንግሊዝ ግን ፥ ከውሉ ወደ ኢጣልያ አጋድሎ እንደ ከዳቸው ሸፈንፈን ባለ የዲፕሎማሲ አነጋገር ገልጸውታል ። በእንግሊዝ ፈቃድ የኢጣልያ ጦር መምጣቱንም ልባቸው እያወቀ እንዳላወቁ በመምሰል ነገሩን ላለማባባስ ፥ “አሁንም የኢጣልያ ጦር ምጥዋ መምጣቱ በናንተ ፈቃድ ነው” የሚል የጥያቄያዊ ዐረፍተ ነገር ካስደገፉ በኋላ ተጋፍቶ የመጣውን ጠላታቸውን ግን ፥ አመጣጡ በእንግሊዝ ፈቃድም ቢሆን ለመመለስ አቅም እንደማያንሳቸው ገልጸዋል ። ከዚህም እያይዘው የምጥዋ በር ቀድሞ የአባቶቻቸው የኢትዮጵያ ነገሥታት መሆኑን ጠቅሰው እንዲሰጣቸው በጠየቁበት ዐረፍተ ነገር ላይ የምጥዋ ወደብ ከኢትዮጵያ ነገሥታት ቁጥጥር እጅ የወጣበትን ጊዜ ቀረብ አድርገው የገመቱት ይመስላል ።

ነገር ግን ፥ ባለፈው ምዕራፍ እንዳመለከትነው ፥ ከአክሱሞች ዠምሮ እስከ ግራኝ አህመድ አነሣሥ ምጥዋ በኢትዮጵያ እጅ ቆይቶ አል ። ከዚያም በቱርኮች እጅ ከወደቀ በኋላ ከ1555—1589 ዓ.ም. የነገሡት ዐፄ ሠርፀ ድንግል በ1571 ዓ ም በወታደር ኃይል ላጭር ጊዜ እጅ አደረጉት ። ቱርኮቹ በ1580 ዓ ም አካባቢ መልሰው እጅ ማድረጋቸውንና በመጨረሻም ያመት ግብር እየከፈለ ራሱ እንዲያስተዳድረው ለግብጹ መሪ ለኢስማኤል ፓሻ መስጠታቸውን ባለፈው አመልክተናል ።

1 F. Harison Smth, Through Abyssinia, pp. 70—71.

# ምዕራፍ ሠላሳ አራት

## የካፒቴን ሖሪስን ስሚዝ ወደ መቀሌ መምጣት ፣ ከራስ አሉላ ጋር የተመሳለሱት ቃል—የንጉሠ ነገሥቱ የመልስና የስሞታ ደብዳቤ ለንግሥት ቪክቶሪያ

የእንግሊዝ መንግሥት ፣ በግብጽና በሱዳን ላይ አገዛዙን ለማጠንከር ሲል የማህዲ እንቅስቃሴ ስላሠጋው ፣ ይኸን የማህዲን እንቅስቃሴ ለመደምሰስ እንዲረዳው መሣሪያ ለማድረግ የፈለገው ኢጣሊያን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያንም ጭምር መሆኑ በትክክል የሚታወቀው በሒዊት ውል ነው ። የሁለቱ አገሮች ዓላማ የተለያየ በመሆኑም ማስማማቱ ችግር ስለሆነበት ፣ እንግሊዝ ከሁለቱ ወዳጅ ሊያደርጋቸው ከፈለጋቸው አገሮች ውስጥ ምርጫው ከኢጣልያ ላይ ወድቋል ።

አሁን የኢጣልያ መንግሥት ምጥዋን ከያዘ በኋላ ፣ ለእንግሊዝ መንግሥት አቤቱታም ፣ ስሞታም ፣ ወቀሳም ፣ ማስፈራራትም ያለበት ያፄ ዮሐንስ ደብዳቤ ስለደረሰው በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ጠብ እንዳይባባስ በሚፈልግበት ጊዜ ፣ "ጠቡን ለማብረድና በጠቡ ፋንታ ሁለቱ መንግሥታት በጄኔራል ፖዞሊኒ አማካይነት የወዳጅነት ውል ሊያደርጉ ነው" ማለትን ስለሰማ ፣ ይኸንኑ ለማጠናከርና ወደ ፍጻሜ ለማድረስ በሎንዶን ተመክሮና ተዘክሮ ካፒቴን ሖሪስን ስሚዝ እንዲላክ ተወሰነ ። ካፒቴን ስሚዝ ባለፈው ዓመት በውሉ ጊዜ ከሬር አድሚራል ሒዊት ጋር ወደ ዐድዋ መጥቶ ካፄ ዮሐንስም ፣ ከራስ አሉላም ጋር ተዋውቋል ።[1] "ከካፒቴኑም ጋር ሰአድ አፌንዲ የሚባለው ግብጻዊ መኰንን ግብጾቹን ከደርቡሾች እጅ ለማውጣት ዐፄ ዮሐንስ የረዱትን ምስጋና ለማቅረብ አብሮ መጥቷል" የተባለው ውሸት መሆኑን ራሱ ካፒቴን ስሚዝ በመጽሐፉ ፣ "ሐሰት የፈጠራ ወሬ ነው" ብሎ አስተባብሏል ።[2] ወልቃኢቲ ብሩ የሚባሉት

---

1 A. Del Boca, Gli Italani in Afıca, p· 215.

2 F. Harson Smith, Throught Abyssina, p. 113

የነአቶ ሚካኤል ፣ የነአቶ መንገሻ አባት ግን ፣ ለአስተርጓሚነት
ተመርጠው አብረው መጥተዋል ።

ካፒቴን ስሚዝ የንግሥቲቱን ደብዳቤና ገጸ በረከት እንደያዘ
በየካቲት 13/1878 ዓ ም ምጥዋ ደርሶ ከጄኔራል ፖዞሊኒ ጋር ተገና
ኝቶአል ።

ዳሩ ግን ፣ በመካከሉ በኮሎኔል ሳሌታ እግር ተሾሞ ወደ ምጥዋ
የመጣው ዠኔራል ካርሎዠኔ የሚባለው የኢጣልያ ጦር አዛዥ ከወ
ደቡ እያለፈ የሰሐጢንና የዊአን አገር በመያዙ የተነሣ ሁኔታው ስለ
ደፈረሰ ፣ ጄኔራል ፖዞሊኒ ወዳፄ ዮሐንስ ሳይደርስ የውሉን ረቂቅ
እንደያዘ በበላይ ትእዛዝ በመጋቢት 13/1878 ወደ ሮም ተመለሰ ።
ካፒቴን ስሚዝ ከኢጣልያ አዛዥ ከጄኔራል ካርሎ ዠኔ ለመጓጓዣና
ለስንቅ መጫኛ የሚያስፈልገውን ከብት መሪውንም ፣ አጃቢውንም
ተቀብሎ ወደ አሥመራ ተጓዘ ።

አሥመራም ሲደርስ ራስ አሉላ በክብር ተቀብለው ካስተናገዱት
በኋላ ፣ በወልቃኢቴ ብሩ አስተርጓሚነት ስለ ሑዊት ውል አሳብ ለአ
ሳብ ተለዋውጠው ነበር ። በውይይታቸውም ላይ ራስ አሉላ ውሉ
በምን ምክንያት እንደ ተሻረ እንዲያስረዳቸው ቢጠይቁት ፣ ካፒቴን
ስሚዝ ግብጾች ምጥዋን ለማስተዳደር ብዙ ሥራ ስለ አጋጠማቸው
አውሮፓውያን (ኢጣሊያኖች) እንዲይዙ የአውሮፓ ኃያላን ፣ ከቱርኮች
በቀር ፣ በሙሉ ፈቅደዋል ሲል መለሰላቸው ። ወደፊትም ኢትዮጵያ
ከኢጣሊያኖች ግንኙነቷ የሠመረ እንደሚሆንና ኢጣሊያኖችም ከንግድ
በቀር መሬት እንደማይፈልጉ ሊያረ‍ምናቸው ሞከረ ። ራስ አሉላ ግን ፣
አንድ ሰው ንግድና ወዳጅነትን ሲፈልግ ከቦታው ተቀምጦ ነው
እንጂ የወዳጅን መሬት አይወስድም ። ጣሊያኖች ወደ እኛ የሚያስ
መጣውን የቤሪንና የአራፋሌን ወረዳ ይዘዋል የሚል ቅሬታቸውን አቀረ
ቡለት ። በዚህም ጊዜ ካፒቴን ስሚዝ ጣሊያኖች እነዚያን ሥፍራዎች
የያዙት ጸጥታ ለመጠበቅ እንደሆነ አስረድቶ የኢጣሊያ የመልዕክት
ጓድ ሲመጣ ሁሉንም ከእርሱ ጋር መነጋገር እንደሚችሉ ገለጸላቸው ።

በዚህ አነጋገር ፣ ካፒቴን ስሚዝ ኢጣሊያ ምጥዋን ለመያዝ ከቱ
ርክ በቀር የአውሮፓ ኃያላን ፈቅደዋል ሲል ከዕውነት የራቀ ሐሰ
ተኛ መልስ ሰጥቷል ። የኢጣልያን ምጥዋን መያዝ ፈረንሳይና መስ
ኮብ በግልጽ ተቃውመዋል ። እንግሊዝና ጀርመን የኢጣልያንን ይዞታ
ሲደግፉ የቀሩት የአውሮፓ ሀገሮች ግን ፣ ለጉዳዩ ግድ የሌላቸው ነበሩ ።
ከዚሁም አያይዞ እንግሊዛዊው ሙኩንን ፣ "ኢጣልያኖች ከና
ንተ ጋር በወዳጅነት ከመነገድ በቀር መሬታችሁን አይፈልጉም"
ያለው ወይም በኢጣሊያኖች ስብከት ራሱ ተታሏል ። አለዚያም



የሚያውቀውን እንደማያውቅ አድርጎ ራስ አሉላን በሐሰት ሊያግባባ
ልፈጓል ማለት ነው ።

መቸም በሥልጣኔ የተራመደው ፣ በኤኮኖሚ በልማት የፋፋው
አውሮፓዊ በዚያን የቅኝ አገዛዝ በሠፈነበት ዘመን የፈቀደውን የሚ
ናገርበት ፣ የወደደውን የአፍሪካ ክፍለ አህጉር ከጓደኞቹ ጋር ተስማ
ምቶ ወይም ተሻምቶ የሚይዝበት ፣ ኋላ ቀር የሆነውን የማናቸውንም
ክፍለ ሀገር ተወላጅ በንቀት ዝቅ አድርጎ የሚመለከትበት ጊዜ ስለነበረ ፣
ለአገዛዙም ለአነጋገሩም ወሰንና ገደብ አልነበረውም ። ስለዚህ ከአ
ገር ፍቅርና ከዠግንነታቸው በቀር የአውሮፓን ሥልጣኔ ያልቀመሱ
ትና የፖለቲካውን የውዝግብ ወሃ ከምንጩ ከአውሮፓ ያልጠጡት
ራስ አሉላም እንደ ጌታቸው እንዳፄ ዮሐንስ የኢጣልያንንም ወረራ
ከመቅደላ ዠምሮ እንደ ወዳጅ ይመለከቱት የነበረውን የእንግሊዝን
ከዳትና የኢጣልያንን ደጋፊነት እየተገረሙ ከመደነቅ ፣ በጦር ሜዳ
ተሰልፈው ከመመከት በቀር የቅጥፈት አንደበቱን በደንበኛ መልስ
ዘግተው ለማስተባበል አልቻሉም ።

የሆነ ሆኖ ራስ አሉላ ፣ ካፒቴን ስሚዝንና ጓደኞቹን ከነጓዙ ሲያስ
ተናግዱ ሰንብተው ቀጥለው መሪ ጨምረው ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስ
ወደ ሚገኙበት ወደ አሸንጌ ልከዋቸው ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በሚያዝያ
ወር መጨረሻ ላይ ተገናኝተው ደብዳቤውንና ገጸ በረከቱን በዝርዝር
አስረከቡ ። ንጉሠ ነገሥቱ ባሁኑ ጊዜ ከቤተ መንግሥታቸው ከዐድ
ዋና ከመቀሌ ርቀው አሸንጌ የተገኙት በወሎና በዋጅራት በሃይማ
ኖት የተነሣ እነሸከ ጦልሃ የቀሰቀሱትን ሽፍትነት ለመደምሰስ መጥ
ተው ነበር ።

ካፒቴን ስሚዝ ያመጣውን ትክክለኛ የንግሥት ቪክቶርያ ደብ
ዳቤ አላገኘሁትም ። ነገር ግን ፣ ቀደም ብሎ ስለ ኢጣልያኖች አገባብና
አያያዝ ንጉሠ ነገሥቱ በደብዳቤ ላቀረቡት ስሞታ የመጣ መልስ ሆኖ
በደብዳቤው ውስጥ ንጉሠ ነገሥቱ ከኢጣልያኖቹ ጋር እንዲስማሙ
የሚጠይቅ መሆኑ አይጠረጠርም ። መቸም በንግሥቲቱ ስምና ማኅ
ተም የሚመጣው ደብዳቤ ሁሉ ፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በጠቅላይ
ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት ተጠንቶና ተረቆ የቀረበው ነው ። ብዙም
ጊዜ ዐፄ ዮሐንስ የሚጽፉትንና ከንግሥት ቪክቶርያ ለንጉሠ ነገሥቱ
የሚመለሰውን ደብዳቤ ሁሉ የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ሎንዶን በሚ
ቀመጠው የኢጣልያ አምባሳደር በኮርቲና ወይም በጉዳይ ፈጻሚው
አማካይነት ለኢጣልያ ባለሥልጣኖች እያሳዩና እየተመካከሩ ነው ።

በዚህም ሁለቱ መንግሥታት ፍጹም ስምምነታቸውና በኢትየ
ጵያ ላይ በኅብረት መሥራታቸው ይታወቃል ። 1

ካፒቴን ሐሪሰን ስሚዝ ፣ ከደብዳቤው ጋር ለንጉሠ ነገሥቱና ለል
ጃቸው ለራስ አርአያ ጭምር ያመጣውን ገጸ በረከትና ደብዳቤ አቅ
ርቦ ሲነጋገር ሰንብቶ ፣ ራሱም ተስተናግዶ ሽልማትም ባለጐፈር የወ
ርቅ ለምድ ከነቀሚሱ ሁለት የብር ጦርና ጋሻ ከሰሎሞን ኒሻን ጋር
ተሸልሞ በሚመለስበት ጊዜ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ በበኩላቸው ለመጣላ
ቸው ደብዳቤ መልሱን አዘጋጅተው በመስጠት አሰናበቱት ። የደብዳ
ቤው ቃል ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

. . . በነገሡ በ49 ዓመት አመ 8 ለኅዳር በ1885 ዓ. ም.
በዊዘር ግምብዎ (ቤተመንግሥት) የተጻፈ ክቡር ደብዳቤዎ
ከለማኅተሙ አመ 30 ለሚያዝያ (ለግንቦት) ደረሰን ደግሞ
ከፍቅርዎ ላይ ፍቅር ለማብዛት አንድ ለኔ አንድ ለልጄ ለራስ
አርአያ የሰደዱልኝን የከብረት (የከበረ) ሁለት ጐራዴ በምስተር
ሐሪስን ስሚዋስ እጅ ተቀበልሁ ደረሰኝ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ ።
በፊትም ቱርኮች (ግብጾች) ጉልበት ተሰማኝ ጥበብ አበዛን ብለው
ጥንተ ነገሥታት ኢትዮጵያ አባቶች ሲገዙት የነበረውን አገሬን
ቢይዙብኝ ፣ ደግሞ የምፅዋን በር የጦር መሣሪያ ሌላም ለቤተ
መንግሥት የሚሆን ዕቃ እንዳይወጣ ቢዘጉብኝ ከዚህ በኋላ ቀጥለው
በግፍ እቤቴ ድረስ መጥተው ቢወጉኝ ይኸን ሁሉ በደሌን
ለርስዎ ጻፍሁልዎ ።

እርስዎ ግን አስተውለው ፣ አውጥተው አውርደው
ከቤተ መንግሥት ሹማምንቶችዎ ጋር መክረው የምጽዋ
በር ይከፈት በእንግሊዝ ጠባቂነት የሀበሻ ነጋዴ ምጽዋ
ላይ አይቀረጥ እንደልቡ ይውጣ ይግባ የጦር መሣሪያም
ሌላም ለቤተ መንግሥት የሚገባ ዕቃ ይውጣ አይከልከል
ቱርኮችም የነበሩበትን አገር ለቀው ወደ አገራቸው ይመ
ለሱ እነዚያ ከነበሩበት የተገኘ የጦር መሣሪያም አገሩም
ለንጉሠ ኢትዮጵያ ይሁን ተብሎ ተዋውለን ይኸም የቃል
ኪዳን ደብዳቤ ተጻፈ ታተመ ። ምጥዋ ግን ቱርኮች ሲለቁ
ለሀበሻ ንጉሥ ይሁን ተብሎ እውነት ነው ከውል አልገባም ።
አልተጻፈም አልታተመም ።

---

1 L'Itala in Africa — Tome VI - Documenti (1887—1888), pp. 170—173.



ነገር ግን ከዚህ ማሀል ኢጣልያኖች መጥተው ምጽዋ
ላይ ተቀምጠው ውል አፍርሰው የሀበሻን ነጋዴ ቀረጡ ።
ደግሞ ከዚያው ተቀምጠው የሆነ ያልሆነውን እየጻፉ እንዳያ
ጣሉኝ በውላችን የሀበሻ ነጋዴም እንዳይቀረጥ የሚጠብቅ
ልኝ በደሌን የምነግረው ከእንግሊዝ ቤተ መንግሥት አንድ
ሰው ምጥዋ ላይ ይቀመጥልኝ ። ከኢጣልያኖች ጋር ተፋቀሩ
ብለው ቢጽፉልኝ (የሚጽፉልኝ) ነገርዎ አገሬን እንያዝ
ብሀ አይበሉኝ እንጂ እንፋቀር ቢሉኝ አልፋቀርም አላል
ሁም ይህ ስለሆነ ግን አላረፉም የያዙትንም በእጃቸው
ይዘዋል ያልያዙትንም እንይዛለን ይላሉ ። እየተላላኩ የሀበ
ሻን መሬት ሁሉ ይመረምራሉ ። ከኢጣልያ ጋር ተፋቀሩ
ያሉኝንም ከዚህ በፊት ጠብ አልነበረንም ። ደግሞ አገሬን
ይዘውብኛል እንጂ እኔ ካገራቸው አልደረስሁም ። ነገር
ግን የምፋቀርበትን ብልሃቱን አላወቅሁትምና የዚህን ብልሃ
ቱን ገልጸው እንዲልኩብኝ ይሁን ። የዚህን ምላሹን ሰምቸ
እኔም ምላሹን እጽፋለሁ ። ተጽሕፈ ሐሸንጌ ከተማ ። የደ
ብዳቤው ቀን እንደ ኢትዮጵያ ቁጥር ሚያዝያ 18 ቀን
1878 ዓ.ም. ነው ።

በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ፣ ዐፄ ዮሐንስ ከሁለት ዓመት በፊት በሔ
ዊት አማካይነት ምጥዋንና አካባቢውን ያስተዳድር ከነበረው ከቀድሞ
ባለጋራቸው ከግብጽ መንግሥት ጋር ሲዋዋሉ ፣ በመዠመሪያው አን
ቀጽ ላይ በምጥዋ ወደብ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባውም ዕቃና የጦር
መሣሪያ ፣ መድፍም ጥይትም ቢሆን ከኢትዮጵያ የሚወጣውም በእንግ
ሊዝ ወኪል ተቆጣጣሪነት በነጻ እንዲያልፍ በግልጽ ተጽፎ የነበረ
ውን አሁን ጣልያኖች እንኳን የጦር መሣሪያ ጥይት ጠባንጃና መድፍ
ወደ ኢትዮጵያ በነጻ እንዲገባ መፍቀድ ቀርቶ ቀረጥ እየተከፈለ እን
ኳን እንዲገባ አይፈልጉም ። እንግሊዞችም ኢጣልያኖች ምጥዋን እን
ዲይዙ ሲፈቅዱላቸው ይኸን የሔዊትን ውል እንዲጠብቁ ውል አላስ
ገቧቸውም ። ኢጣልያኖቹ ባሁኑ ጊዜ የሚከተሉት ዓላማ ቀደም ብሎ
ኢስማኤል ፓሻና የግብጽ ባለሥልጣኖች ይከተሉት የነበረውን የማ
ጭበርበር ሥራ ነው ። ባንድ ወገን ፣ "የኢትዮጵያ ወዳጅ ነን" እያሉ
በሌላ በኩል ነዋሪውን የእስላምና የክርስቲያን ሕዝብ በሐሰተኛ ስብ
ከት አንድ ጊዜ "ምጥዋን የያዝነው በእንግሊዝና በቱርክ ፣ በግብጽና
በኢትዮጵያ ፈቃድ ነው" እያሰኙ ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ገንዘብ በመስገሥ
"ወደኛ ኑ ፣ እኛ የናንተ ጠባቂና አሠልጣኝ ለመሆን ፣ ንግድ
ለማስፋፋት ፣ አገር ለማልማት ነው የመጣነው" እያሉ በመስበክ በዚሁ
ኑን መተላለፊያ የሆነውን መንገድና በር እየተሽቀዳደሙ በመያዝ

በያዙት አገር ይዞታቸውን እያጠናከሩ ለመከላከያ ምሽግ እየሠሩ ተቀ
ምጠዋል ። ይኸንንም ንጉሠ ነገሥቱ ከሐማሴን ገዥ ከራስ አሉላ ፣
ደግሞ ከአይለቱ ወረዳ ገዥ ከሻለቃ አርአያና ከጊንዳው አስተዳዳሪ
ከባላምባራስ ተሰማ በዝርዝር ሰምተው ዐውቀውታል ።

በዚህ መካከል ፣ ይህን ከመሰለ አጥቂ ባላጋራ ጋራ ከእንግሊዞች
በኩል የመጣው "ታረቁ ተስማሙ" የሚለው መልእክት በእርግጥ
ለንጉሠ ነገሥቱ ግራ አጋቢ ሆኖባቸዋል ። ስለዚህ ነው ለንግሥቲቱ
በጻፉት ደብዳቤ ላይ ፣ "...የምንፋቀርበትን ብልሃቱን አላወቅሁትምና
ብልሃቱን ገልጸው ይላኩብኝ" እስከ ማለት ያደረሳቸው ። [1]

በዚህ ምክንያት ፣ ካፒቴን ሐሪሰን ስሚዝ ይዞ የሔደው ይህ ደብ
ዳቤና የደብዳቤውም ስሞታ የተመሠረተበት የሒዊትን ውል ጣልያ
ኖቹ ሲያፈርሱት ፣ እንግሊዞቹ በፈረንሳዮችና በሱዳን ግምባር ከኢጣ
ልያኖች በኩል የሚያገኙትን የመሣሪያነት ጥቅም ብቻ በመመልከት
ወኪላቸውን እንደ ውሉ ቃል ምጥዋ ላይ አስቀምጠው ፣ ውሉን ለማስከበ
ርም ሆነ በሐቀኛ ውል ላይ የተመሠረተውን የኢትዮጵያንም በደል ተመ
ልከተው በኢጣልያ ላይ ምንም ዐይነት ተጽዕኖ ለማድረግ አልፈለጉም ።

በሎንዶንም የመሪዎች ለውጥ ተደርጎ ሌቤራሎቹ ግላድስተንና
ግራንቪል ተሸረው ወግ አጥባቂዎቹ እነሳሊስበሪ በሥልጣን ቢተኩም ፣
በውስጥ አስተዳደርና በኤኮኖሚ አያያዝ ይለያዩ እንጂ ፣ በውጭ ፖሊ
ቲካ ፣ በቅኝ አያያዝና በግዛት ማስፋፋት በኩል የሚከተሉት ፖሊሲና
ስልት የባሰ ወይም የሁሉም ተመሳሳይ ነው ። በኢጣልያም አገር ጠቅ
ላይ ሚኒስትሩ ደብረስቲስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ማንቺኒ በፍራንቾስኮ
ክሬስፒና በነካርሎ ቢላ ቢለወጡም፣ በኢትዮጵያና በቀይ ባሕር ወደቦች
ላይ በዝመራት የመስፋፋት ጉዳይ ዓላማቸው አንድ ዐይነት ነው ።

በዚህ ምክንያት ፣ ቀድሞ በእንግሊዝ መንግሥት ወዳጅነት ከልብ
ይመኩ የነበሩት ዐፄ ዮሐንስ ፣ ባሁኑ ጊዜ ኢጣልያ ወደ ምጥዋ የመ
ጣው በእንግሊዝ መንግሥት ፈቃድ መሆኑን ስለ ተረዱ ፣ እንግሊዞች

1 F. Harison Smith, Through Abyssinia, p 219.



ቀድሞ ከመቅደላው ጦርነት ወዲህ በመቀሌ ቤተ መንግሥት የተወደ
ዱትን ያህል ባሁኑ ጊዜ መጠላታቸውን ተልኮ የመጣው ራሱ ካፒ
ቴን ስሚዝ በደንብ ተረድቶታል ። [1]

ስለዚህም በሃይማኖት ፣ በወታደርነት ፣ በነጻነት አጠባበቅ ብቸኛ
ሆና የኖረችው ኢትዮጵያ ያላት የመጨረሻ ዕድል አሁንም በአርበኞች
ልጆቿ በመተማመን ብቻዋን መከላከል ስለሆነ ፣ ወደፊት በኢጣልያ
ተስፋፊነት አንጻር በዶጋሊ ፣ በሰሐጢ በኳዓቲት በሰናፌ ፣ በሃይላ ፣ በአ
ምባ አላጌና በመቀሌ ሲዋጉ ቆይተው የሁለቱ ተዋጊዎች ዕድል
በመጨረሻ ዐድዋ ላይ ይወሰናል ።

1 F. Harison Smith , Through Abyssinia, pp. 194—195.

# ምዕራፍ ሠላሳ አምስት

## በዶጋሊ ጦርነት ዋዜማ የኢጣልያኖች የማታለል ዘዴ ፤ በባላባቶች ፍልሚያ መካከል የውስጥ አንድነታችን መላላት ፤ የነሳሊምቤኒ ሰላይነት ፤ የፈረንሳዮች ኢትዮጵያን ደጋፊነት

የኢጣልያ ጦር ወደ ምጥዋ የገባው ፤ በትክክል ለቅኝ አገዛዝ
ዓላማ መሆኑን የኢጣልያ ንጉሥ ኡምቤርቶ እያወቀው ፤ "ዐፄ ዮሐ
ንስ ፍጹም ክርስቲያን ናቸው አምላካቸውን ይፈራሉ" ማለትን ከየ
ወኪሎቹ ስለሰማ ፤ አገባቡን በአምላክ ፈቃድ ነው ለማስኘትና በዚ
ህም ለማጭበርበር ሲል በጻፈላቸው ደብዳቤ ላይ ፤ "ወደ ምጥዋ የገ
ባነው ምስጢሩ በማይመረመረው በአምላክ ፈቃድ ነው" የሚል ዐረ
ፍተ ነገር በመጨመር ሊያታልላቸው ሞክሮ ነበር ። ዐፄ ዮሐንስ
ምንም አምላካቸውን ወዳድና የሃይማኖት ሰው መሆናቸው የታወቀ
ቢሆንም ፤ በአጭበርባሪው ደብዳቤ ሊታለሉለት አልቻሉም ።

ከዚሁ አያይዞ ኢጣልያዊው ንጉሥ በምጥዋና በአካባቢው መያዝ
ሊጠቀም የፈለገው እሱና ሕዝቡ መሆኑን በግልጽ እያወቀው ፤ ኢት
ዮጵያን ለመጥቀም አገር አቋርጦ ባሕር ተሻግሮ የመጣ በማስመሰል ፤
"የኛ ምጥዋ መግባት ከኛ ይልቅ ለሐበሻ ይጠቅማል" ያለውም ሁለ
ተኛው ማጭበርበር ነው ። ሦስተኛው ማጭበርበር የእንግሊዝም ፤
የኢጣልያም የውጭ ጉዳይ ባለሥልጣኖች የምጥዋን መያዝ ግብጽ
እንዲያውቀውና የቱርክ መንግሥትም ፤ ነገሩን እንዲቀበለው በጉንም
በቀጥታም ሲያባብሉ ኢትዮጵያን ግን ፤ በንቀት ዐይን ከመመልከት
የተነሣ ሁኔታውን ላፄ ዮሐንስ ደብቀው ሳለ ጦሩ ምጥዋ ወደብ ላይ
በተራገፈበት ሰዓት የጦሩ አዛዥ ፤ "ምጥዋ የገባነው በእንግሊዝ ፤ በቱ
ርክና በሐበሻ መንግሥታት ፈቃድ ነው ፤ አመጣጣችንም በወዳጅነት
ንግድን ለማስፋፋት እንጂ መሬት አንፈልግም" የሚል የይፋ ማስታ
ወቂያ መበተኑ ነበር ።

ነገር ግን ፤ የኢጣልያ መንግሥት መሪዎች በዚያን ጊዜ ያጭበረ
ብሩ የነበሩት የኢትዮጵያን መንግሥት ብቻ ሳይሆን የራሳቸውንም
ሕዝብ ጭምር ነበር ። በኢጣልያ አገር በድብቅ የቆየው የምጥዋ
ወደብ መያዝ በይፋ እንደ ተሰማ በምክር ቤት ግቢም በውጭም ብዙ
ክርክር ፈጥሮ ነበረ ። በመጨረሻ የወታደሩን አላላክ በምስጢር ያዘጋ
ጁት ባለሥልጣኖች በምክር ቤት አባሎች ተከሰው ፤ "ወደ ምጥዋ

ጦር የላከነው ለቅኝ አገር ፍለጋ ነው” ብለው በግልጽ በመናገር ፋንታ አንድ ጊዜ “ለንግድ ነው” ሌላ ጊዜ ፣ “አረመኔውን ሕዝብ ለማሠልጠን ነው” በሚል አነጋገር ትክክለኛ ዓላማቸውን ለመግለጽ እየደበቁ ብዙ ግርግር ከተፈጠረ በኋላ ፣ በመጨረሻ ጉዳዩን ያውጠነጠነው ማንቺኒ ተሽሮ በርሱ እግር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነቱን ካርሎ ፌሊቼ ደሮቢላ የሚባለው ተሾመ ። እሱም እንደ ተሾመ የቅኝ ፈላጊዎቹ ቁጥር ከመበርከቱ የተነሣ ማንቺኒ በሥራው አመራር ተነቅፎ ተሻረ እንጂ እርሱ ምጥዋን በመያዝ የወጠነው የቅኝ ፍላጐት ዓላማ አልከሸፈም ። ሮቢላም በወዲህ በራስ አሉላ በኩል ያለውን ተቃውሞ አዲስ ከተሾመው ከጄኔራል ካርሎ ጄኔ በሚደርሰው ራፖር እየተማመነ ፣ “አረመኔውን የአሉላን ጦር ለማቆም ከ600 እስከ 700 የሆነ ወታደራችን በቂ ነውና የቀረው መመለስ አለበት ። እዚያ የሚቀሩት ወታደሮቻችን ከኢጣልያ ባንዲራ ጋር በመድፎቻቸው በትር የሐበሻን ወታደሮች ከደጋው ወደ ቆላው እንዳይነቃነቁ ያደርጉዋቸዋል” እያለ ምክር ቤቱን ያጽናና ነበር ።

እውነትም ከመማክርቱ አንዱ ደረንሲስ ፍራንቸስኮ የሚባለው “ምጥዋ ያሉት ወታደሮቻችን በራስ አሉላ እንዳይጠቁ ሁኔታውን በየጊዜው እኛ አማካሪዎቹ መረዳት ስላለብን ፣ ሁልጊዜ ራፖር ይቅረብልን” የሚል ጥያቄ ቢያቀርብ ፣ ለዚህ መልስ በጄኔ አባባል የተታለለው ሚኒስትሩ ደ ሮቢላ የጄኔራል ጄኔን ጉብዝና አድንቆ ፣ “ሌላ ብዙ የምንወያይበት ዓለም አቀፍ ቁም ነገር ጉዳይ እያለን ስለነዚህ በእግራችን ድኳ ሥር ስላሉት አራት ሽፍቶች ጉዳይ ምክር ቤቱ ማስብና መነጋገር ያለበት አይመስለኝም” የሚል የንቀት መልስ በመስጠት የምክር ቤት አባሎቹን የሥጋት መንፈስ ሊአረጋጋ ሞከረ ።[1] “አራት ሽፍቶች” የተባሉት የራስ አሉላ ሰዎች ናቸው ።

ምጥዋ እንደ ተያዘ ከኢጣልያኖቹም ከእንግሊዞቹም ፣ ብዙ የማጭበርበር ሁኔታ ሲታይ ከፈረንሳይ ቆንሲሎች በኩል ግን ፣ እውነተኛው ሁኔታ ላፄ ዮሐንስ ተገልጾአል ። ለጊዜው ንጉሠ ነገሥቱም ሆኑ የምድር ባሕረ ገዥ (ኤርትራ) ራስ አሉላም ለጠብ አልቸኮሉም ። ሁለቱም አጋማሽ አሳባቸውንና የጦር ኃይላቸውን በሔዊት ውል መሠረት ስሜን ምዕራባዊውን ክፍል ለማግኘት የጦርነት ፊታቸውን ወደ ከሰላና ወደ መተማ አዙረዋል ። በዚያም ራስ አሉላ በቅርቡ ግብጾቹንም ለማውጣት

1 F. Martini, Cose Africane, p 2; A. Del Boca, Gli Italiani in Africa Orientael' p. 220.



ከሰላንም በመፋለም ከደርቡሾች ጋር ሲዋጉ ቆስለው ተመልሰዋል ። ከዚህም ጋር በሚያሳዝን አኳኋን ቀድሞ ራስ ወልደ ሚካኤል ከግብጾች ጋር ሆነው ዐፄ ዮሐንስን ያውኩ እንደነበረ ሁሉ ፣ አሁን ደግሞ ያፄ ዮሐንስ የእኅታቸው የትልቁ ራስ አርአያ ልጅ ደጃች ደብብ አርአያና ሌሎችም የክርስቲያንና የእስላም ሹማምንት በሹመትና በገንዘብ እየተደለሉ ለኢጣልያኖቹ ገብተው መሣሪያ ሆነዋል ።

በሌላው የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር እንደሚደርሰው ፣ በሰሜን ኢትዮጵያም ከመረብ ምላሽ ባሉት አውራጃዎች በአጋሜ የደጃች ሰባጋዲስ ወገኖች ለእንደርታዎቹ ለራስ ወልደ ሥላሴ ወገኖች መታዘዝን እንደማይወዱ ከመረብ ወዲያ ያሉትም በሐማሴን የተስፋ ጽዮን ወገኖች ፣ በደምበላን የደጃች እድጎ አምበሳ ወገኖች ፣ በካርኒሽም ደጃች ስብሐቱ ከነቤተሰባቸው ፣ ከአከለጉዛይ ደጃች ባሕታ ሐጐስ ፣ በሠራዬ የነባላምባራስ ተስፋ ማርያምና የፌታውራሪ ተስፋ ሚካኤል ወገኖች እርስ በርሳቸው ባላንጣ ከመሆናቸውም በላይ ፣ ዐፄ ዮሐንስ ባባታቸው ከመረብ ወዲህ የሹም ተምቤን ምርጫና በእናታቸው የእንደርታው የራስ ወልደ ሥላሴ ወንድም የደጃች ደብብ ልጅ የወይዘሮ ሥላስ ልጅ በመሆናቸው ፣ እንዲሁም የታወቁት የጦር አለቃቸው ራስ አሉላም ከመረብ ምላሽ ከተምቤን ስለሚወለዱ ፣ ከመረብ ወዲያ ያሉት እላይ የጠቀስናቸው ባላባቶች ለነዚህ መታዘዙን ፣ የጦር ኃይል ካላስገደዳቸው ወይም የሹመት ዕድገት ማርኮ ካልያዛቸው በቀር ፣ ራሳቸውም ቤተሰባቸውም እንደ ውርደት ይቆጥሩታል ። ባንዱ በሐማሴን አውራጃ ውስጥ በሐጸጋው ተወላጅ በራስ ወልደ ሚካኤልና በጸሐዘጋው ባላባት በደጃች ኃይሉ መካከል የነበረውን ጠብና ፍልሚያ ባለፈው ተመልክተናል ።

በዚያው ባንዱ አውራጃ ውስጥ እና ባንድ ቤተሰብ ውስጥ የነበሩት ዘመዳሞች እንኳን በሥልጣንና በበላይነት ፍለጋ የእርስ በርስ ውጊያ ያደርጉ ነበር ። ከውጊያው በኋላ ዕርቁ ፣ ከዕርቁ ወዲህ ተመልሶ ውጊያው ዐልፎ ዐልፎ መታየቱ አልቀረም ። በዚህ ምክንያት ደጃች ደብብና ዐፄ ዮሐንስ የታናሽና የታላቅ ልጆች ሆነው ሳለ ፣ ደጃች ደብብ ከዶጋሊ በፊት ካፄ ዮሐንስ ሸፍተው ወደ ኢጣልያ እንደ ገቡና ከዶጋሊ ጦርነት በኋላ ፣ የዐፄ ዮሐንስና የኢጣልያ ጦሮች በስሐጢ ለጦርነት ሲሰላለፉ ከኢጣሊያኖቹ ከድተው ወዳፄ ዮሐንስ እንደመጡ ፣ ቀጥሎም ካፄ ዮሐንስ ሞት ወዲህ ለራስ መንገሻ ላለመታዘዝ ወደ ኢጣልያኖቹ ሲመለሱ ወደፊት ይነበባል ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት ፣ የኢጣልያ ጦር ምጥዋ ከገባበት ጊዜ ዠምሮ ምንም ያህል ጊዜ ሳይቆይ ከነሰዋቸው ገብተው ለኢጣልያ ታማኝ የሆኑ ቀኛዝማች (በኋላ ደጃዝማች) እድጉ አንበሳ የደምበሳን ባላባት ፣ ቀጥለው ደጃዝማች ተስፋ ማርያም የዓዲኳላው ፣ ደጃች

ኪዳነ ማርያም የደቂ ተስፋው መሆናቸውን የኢጣልያኖቹ ሰነድ ያረጋግጣል ። [1] እንደዚሁም የኢጣልያ ጦር አዛዥ ፣ ግራና ቀኝ በተስፋፋና ሥልጣኑን ባጠነከረ መጠን ፣ ከክርስቲያንም ከእስላምም ወገን ብዙዎቹ ገብተውለታል ። ከእስላሞቹ ወገን ሐመድ ሐሰን ከንቲባይ የሐባቡ ተወላጅና ሌሎች ጓደኞቹ በዚህ ጊዜ ከኢጣልያኖቹ ጋር በመደረብ እነራስ አሉላን ከማወክ ላይ ይገኙ ነበር ። የኢጣልያ ባለሥልጣኖችም 'አለያይተህ ግዛ' በሚለው የገዥዎች ዘዴ በመጠቀም ባንድ ወገን ገንዘብና ሹመት ከማዕርግ ስም ጋር እያደሉ ፣ ለክርስቲያኑ ወገን "መጣንልህ እንዳንተው እኛም ክርስቲያን ነን" ሲሉ ፣ ለእስላሙ ወገን ደግሞ ክርስቲያኖቹ እንዳያጠቁህ ጠባቂህና ተከላካይህ እኛ ነን" እያሉ በመሰበክና በውል በመተሳሰር ያታልሉታል ።

ይህ የውስጥ የመለያየት ሁኔታዎች ስለ ጠቀመው ፣ እላይ እንደ ተባለው የምጥዋው አዛዥ በጠቅላላው በኢትዮጵያ አንድነት ድርጅትና ትጥቅ ፣ በተለይም በራስ አሉላ የጦር ኃይልና ብርታት ቅንጣት ያህል ሥጋት ሳያድርበት ለመከላከያ ሚኒስትሩ ለሪኮቲና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለሮቤላ የዚህኑ መንፈስ በማሳደሩ ሚኒስትሮቹ የንቀቱ ተካፋይ በመሆን ፣ "በየቀኑ የምጥዋ ሁኔታ ይገለጽልን" ብለው ለጠየቁት አማካሪዎች ፣ "በጫማችን ድኳ ሥር ላሉት አራት ሽፍቶች ጉዳይ ምክር ቤቱ በምንም ዐይነት ማሰብ የለበትም" እስከ ማለት ደርሷል ። ጄኔራል ጄኔ አሁንም በኢትዮጵያ ጦር ላይ የነበረውን ንቀትና በራሱ ኃይል የመተማመኑን ስሜት ለመግለጽ ሲል ጥር 21 ቀን 1879 ዓ.ም. ለካርሎ ሮቢላ በጻፈው ሰፊ ራፖር ውስጥ ፡—

> "...ከአሉላ በቀር ወታደሩ እኛን መውጋት አይፈልግም። ራስ አሉላ እኛን ለመውጋት በበቅሎ ሲመጣ የጊንዳው ሹም ባላምባራስ ወርቁ ደንጊያ ተሸክሞ አይሆንም ብሎ እንደ ለመነው ሰምቻለሁ። ንጉሠ ነገሥቱም አትዋጋ ብሎታል ነገር ግን ፣ አሉላ ሁለት ዐይነት ስሜት አለው ። ወደፊት ለመግፋት ፍርሃት ፣ ወደኋላ ለመመለስ ዕፍረት... ስለ ዚህ አሉላ ቢወጋኝ ተስፋ እንደማደርገው አሸንፈዋለሁ። ...ከዚያም አልፈን ለወደፊቱ ጸጥታ ሊሰጠን የሚችለውን ቀበሌና ለበጋ ወራት ለወታደሮቻችን ተስማሚ

1 L'Italia in Africa — Serie Storico — Militare Vol. 1, Cap. VII - pp. 130-123. Abyssinia ed Erytrea - M.Pate Seconda - pp. 141-291.



> የሚሆነውን (ደጋውን አሥመራን) ሥፍራ መያዝ ነው" የሚሉ ቃላት ይገኙበታል ። [1]

በዚህ ዐይነት አጻጻፍ ፣ የራስ አሉላን ደካማነት በመግለጽ ጄኔራሉ ተታሎ በሮማ የነበሩትን የሩቅ አለቆቹንም አታሏል ። በቅርብ የገቡለት ያገር ተወላጅ ሰላዮች ደግሞ ፣ ጄኔን ደስ በሚለው መንገድ፣ ረብ ለማግኘት ሲሉ ብቻ የሆነ ያልሆነውን እየፈጣጠሩ በማቅረብ ያታለሉት ይመስላል ። እርሱ በነዚህ ሲታለል እርሱ አለቆቹን ፣ አለቆቹ ደግሞ ከርሱ የሚደርሳቸውን በማመን የምክር ቤቱን አባሎችና በጠቅላላው የኢጣልያን ሕዝብ አሰቱን እውነት እያደረጉ በማቅረብ አታለውታል ። የዚህ ሁሉ እንደ ሰንሰለት የተያያዘው ውሸትና ማታለል ፣ ሊበጣጠስ የቻለው እንደተራ ሽፍታ የተናቁት ራስ አሉላ በዶጋሊ ጦርነት ማሸነፋቸው በኢጣልያ አገር በቴሌግራም ሲሰማ ብቻ ነበር ።

ይኸን የመሳሰለው ሁኔታ በሚታይበት ጊዜ ፣ በኢጣልያኖቹ ዘንድ በትጋት የተያዘው በኢትዮጵያ ላይ ሰላዮችን አሠራጭቶ ውስጣዊ ሁኔታን የማሰለሉና ማስረጃዎችን የመሰብሰቡ ጉዳይ ነበር ። በዚህ ሥራ ላይ እንዳሉ እነጉስታቮ ቢያንኪ ፣ እነጃን ፒዬትሮ ፖሮ በአዳል አገርና በሐርጌሳ አካባቢ ከዚህ በፊት መሞታቸው ይታወሳል ።

ለሰላ ወደ ኢትዮጵያ የሚላኩት ፣ አብዛኛውን ጊዜ ለአገባብ እንዲመች የእጅ ባለሙያዎች አናጢዎች ሐኪሞችና መሐንዲሶች ነበሩ ። ከዚህ የተነሣ አውጉስቶ ሳሊም ቤኒ የሚባለው መሐንዲስ አባይ ላይ ድልድይ እሠራለሁ የሚል ተስፋ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በመስጠት ከርሱም ጋር በሕክምና አገለግላለሁ በሚል ሰበብ ዶክተር ቾዛሬ ኔራሲኒ የሚባል ሐኪም ውስጡን ለሰላ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተመድበው ተልከዋል ። እንደዚሁም ከነዚህ ጋር ሻለቃ ፌዴሪኮ ፒያኖና ቴኔንቲ ታንግረዲ ሳቧሩ የሚባሉት የጦር መኰንኖች ከጦር ሚኒስቴር ውስጡን ለዚሁ ለስለላ ክፍል ተመርጠው ላዩን መሐንዲሶች ተብለው, የሲቪል ልብስ ለብሰው በምጥዋ በኩል መጥተው ወደ አሥመራ ደርሰው ከራስ አሉላ ጋር ንግግር ጀምረው ነበር ። ለማስመሰል ሲሉ ሁለት የገምቢ መሣሪያ የያዙ ተራ ሠራተኞችና እንደዚሁም ሻለቃ ፒያኖ ንጹሕ የቤተሰብ አባት

1 L'Italia in Africa - Serie Storico - Vol. 1, Documenti (1887—1888 -) G. Giglio - pp. 1-50.

ለመምሰል አማኑኤል የሚባለውን የ11 ዓመት ወጣት ልጁን አስከ ትሎ ነበር ።

እነዚህም በፈቃድ በታኅሣሥ ወር 1879 ዓ ም. አሥመራ ገብተው ሳለ ፤ በዚሀ ጊዜ ራስ አሉላ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በእንደርታ ነበሩና የርሳቸውን ወደ አሥመራ መመለስ ሲጠባበቁ ራስ አሉላ ወደ አሥመራ ተመልሰው ሁሉንም በደስታ ተቀብለው እርዳታ ማድረግና ማስተናገድ እንደ ጀመሩ በዚሁ ጊዜ ፤ "በሰላዮቻቸው አማካይነት ኢጣልያኖቹ ከምጥዋ ወደብ እየወጡ ዙላንና ዊአን በወረራ ይዘው መሽገው ተቀምጠዋል ። ለኑሮ የሚያገለግላቸውን የምንጭ ጉድጓድ ሁሉ እያበጁ እያያዛቸውን ያጠነክራሉ ። ወደ አሥመራም የመጡት ጣልያኖቹ ሰላዮች ናቸው እንጂ በፍጹም መሐንዲሶች አይደሉም" የሚል ወሬ ከደንበኛ ምንጭ ደረሳቸው ።

በዚህ ጊዜ አሉላ ፈረንጆቹን በፊታቸው አስቀርበው የዊአን በኢጣልያ ጦር መያዝ እንደሰሙ ገለጹላቸው ። ዋንየው ሳሊምቤኒ እርሱና ጓደኞቹ ንጹሐን መሐንዲሶችና የሥራ ሰዎች እንጂ ፤ የዚህን የጦርነትና የፖለቲካ ነገር እንደማያውቁ ተናገረ ። ራስ አሉላ ግን ፤ በርሱ አነጋገር ለመታለል ስለ አልቻሉ ፤ "ብል እንግዲያው ጀኔራል ካርሎ ጄኒ ያንተው ወገን ስለሆነ ፤ ደብዳቤ ጽፈህ ዊአን እንዲለቅና በምጥዋ ወደቡ ዐርፎ እንዲቀመጥ አድርግ ብለውት እሺ ብሎ ለግብር ይውጣጽፎ ነበር ። ነገር ግን የኢጣልያ ጦር ከወደቡ እየወጣ የመስፋፋቱ ጉዳይ ወደ ደጋው ወደ አሥመራም ፤ ወደ ከረንም የመዝመቱ ነገር በካርሎ ጄኒና በጓደኞቹ አሳሳቢነት በሮማ በከፍተኛ ባለሥልጣኖች የተወሰነ ጉዳይ ስለሆነ ፤ ጄኔራል ጄኒ የዙላንም የዊአንም ምሽግ ከማጠባበቅ አዳዲስ ወታደርም ከመመልመል ጋር የመጣበትን ወረራ ለማቆም አልቻለም ።

በዚህም ምክንያት ፤ ራስ አሉላ በመሐንዲስነትና በሕክምና ስም ለስለላ የመጡትን ሁሉንም ጠርተው ፤ "መሐንዲስ ነን ብላችሁ በሐሰት ያወራችሁት እኛን ለማሞኘት ነው እንጂ ፤ ሰላዮችና የጦር አለቆች መሆናችሁን ስለ ደረስሁበት ፤ ወደ ጐጃም ለመሔድ አትችሉምና ሁላችሁም በእስር ቤት ቆዩ" ብለው እርሳቸው ከአሥመራ ወደ ጊንዳ ወርደው በቀጥታ ከጄኔራል ካርሎ ጄኒ ጋር ይጻጻፉ ጀመር ። [1] "የመሸግኸውን ካለቀቅህ እነዚህን የታሰሩትን እገድላለሁ" ብለው እስከ ማስፈራራት ደርሰው ነበር ። ወደፊት ባለው ምዕራፍ እንደምናነበው ፤

1 A. Del Boca, Gli Italiani in Africa, pp. 218—219.



ራስ አሉላ በሰሐጢና በዶጋሊ ተዋግተው ምንም ቢያሸንፉ ፤ ብዙ ሰው በተለይ በሰሐጢው የክቢ ጦርነት ላይ ስለ ተጐዳባቸው ፤ እውነትም እነዚህን ሰላዮች ለመግደል አስበው ሳለ በአክራይ የነበሩት ፈረንሳዩ አባጄን ባቲስት ኩልቦ በምክር ገላግለው አዳኗቸው ይባላል ። *

በኢጣልያኖቹ አጥቂነት በእንግሊዞቹ ተባባሪነት ግንባር ፤ ፈረንሳዮቹ ከቀድሞ ከነሳርዚክ ፤ ከነጋስቶን ለሚይ ዠምሮ ያፄ ዮሐንስ ረዳቶች ስለሆኑ ፤ አሁንም በምጥዋ የሚቀመጠው ፍራንሷ ሱማኝ የራስ አሉላ ረዳት ስለሆነ ፤ ምንም እንኳን በካቶሊክ ስ ባኪነታቸው ካፄ ዮሐንስ ጋር ባይስማሙ በፈረንሳይ ዜግነታቸው ምክንያት ራስ አሉላ የአባ ኩልቦን ምክር በጥሞና ተቀብለዋል ።

ባለፈው የምጥዋ አያያዝ ፤ የኢጣልያንና የእንግሊዝን መመሳጠር እንደ ገለጡላቸው አሁንም ላፄ ዮሐንስም ፤ ለራስ አሉላም የኢጣልያን ትክክለኛውን አያያዝ ምናልባትም የነአውግስጦስ ሳሊምቤኒን የነሻለቃ ፒያኖን ሰላይነት በትክክል የገለጸላቸው ይኸው ቆንሲሉ ሱማኝ ይሆናል ። ራስ አሉላ ከሱማኝ ጋር በዶጋሊ ጦርነት ዋዜማ ከሚጻጻፏቸው ደብዳቤዎች ውስጥ ፤ "መልእክት ዘራስ አሉላ. . . ይድረስ ከቆንስል ፈረንሳዊ ሱማኝ. . . በክቡር ቃል የሰደድህልኝ ደብዳቤ ደረሰኝ የፍቅራችንም ነገር በቀደም እንደጻፍሁልህ ነው. . . ጣልያን የሚያደርገውን ነገር የምታየውና የምትሰማው ነው. . ." የሚሉ ቃላት ይገኙባቸዋል ። ደብዳቤው ምስጢራዊ ስለሆነ ባይገልጹትም ፤ ከቆንሲሉ የመጣላቸው መልእክት የኢጣልያኖቹን የአጥቂነት ዓላማ የሚያመለክት መሆኑ አይጠረጠርም ። የፈረንሳይ እርዳታ የተገኘውም ፈረንሳዮች ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ካላቸው የቅኝ አገዛዝ ፉክክር የተነሣ መሆኑን አንባቢ አይዘነጋውም ።

* ማርከስ በገጽ 86 ሰላዮቹ የተለቀቁት ከዶጋሊ ጦርነት በፊት እንደሆነ ይገልጻል ።

# ምዕራፍ ሠላሳ ስድስት

## የዶጋሊ ጦርነትና የራስ አሉላ አሸናፊነት

ጥር 28 ቀን 1878 ዓ.ም. ጣልያኖቹ የምጥዋን ወደብ ይዘው ከወዲህ የነራስ አሉላን ተቃውሞ በሐሰተኛ ወሬ ለማዘናጋት በሚጣጣሩበት ጊዜ ፣ ከመጋቢት ወር ዠምሮ አዳዲስ ጦር እየተከታተለ ወደ ምጥዋ በመግባት ምሽጉን ከማጠባበቁም በላይ ፣ ከወደቡም እየተሳበ አገር በመያዝ የ1878 ዓ.ም. ዘመንን አሳለፈ ። በዚሁ ዓመት በታኅሣሥ ወር የኢጣልያ መንግሥት ለዚህ የወረራ ጉዳይ ክብደት ለመስጠት ኮሎኔል ሳሌታን አስነሥቶ በርሱ እግር ዤኔራል ካፎሎ ዤኒን ሾመ ። ግብጾችንም በሰላምም በማስገደድም ምጥዋን ለቀው ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ካደረጉ በኋላ ፣ ጣልያኖቹ በምጥዋና በአካባቢው ብቻቸውን ጌቶች ሆኑ ። በዚሁ ጊዜ ካፄ ዮሐንስም ፣ ከነራስ አሉላም እየተቀያየሙ ወደነርሱ የተጠጉትንም ፣ ያልተጠጉትንም ያገር ተወላጆች እያባበሉ በማቅረብ ከዚህ በፊት እንደልነው ፣ ለክርስቲያኑ ለብቻው "መጣንልህ" እስላም ነክ የሆነውን "ክርስቲያን እንዳያጠቃህ ጠባቂህ እኛ ነን" እያሉ ላስተዳደርም ለውጊያም ያደራጁት ዠመር ።

በሳሌታ ጊዜ ከወደቡ አጠገብ ያሉት ምንኩሎና ዊዓ ከተያዙ ወዲህ አሁን ካርሎ ዤኒ ወረራውን እየቀጠለ ከወደቡ 19 ኪ.ሎ ሜትር ዐልፎ ዶጋሊን እስከ 26 ኪ.ሎ ሜትር* ዘልቆ ሰሐጢን ይዞ ይመሽግ ዠመር ። ለጊዜው በትኩሱ ተከላካይም አልገጠመውም ። የዚህን ሁኔታ ሁሉ ዐፄ ዮሐንስም ፣ ራስ አሉላም ሲመለከቱት እስከዚህ ጊዜ ድረስ ይተማመኑበት የነበረው የሒዊት ውል አታላይ መሆኑን እያደር ተገነዘቡት ። በተለይ ደግሞ ፣ 'ምጥዋ የገባነው ባፄ ዮሐንስ ፈቃድ ነው' ብለዋል የሚባለውን ወሬ በሰሙ ጊዜ ፣ በኢጣልያኖች በኩል እንዴት ያለ ቅጥፈት እንደሚነገር ታዝበው ባጠገባቸው ከብዙ ዘመን ዠምሮ በአገልግሎት የኖረውንና ይወዱት የነበረውን ናሬቲን "ኢጣልያኖች ለካ ውሸታሞች ናቸው" በሚል ስሜት እርሱንም ፊት ነሥተው ቆይቶ በመጨረሻም ስላለፈው አገልግሎቱ 5.000 ብር ስጥተው

* ሩቤንሰን በገጽ 380 ዶጋሊን እስከ 30 ኪሎ ሜትር መዝለቁን ገልጿል ።

አስናበቡት ።* ለመዘጋጀትም ይሁን ወይም ዐቅም በማጣት ከወ
መዠመሪያው ላይ አሉላ ቸኩለው ጦርነት አያንሡ እንጂ ፣ በኢጣል
ኖቹ ምጥዋ መግባትና መስፋፋት ገና ግብጾቹ ሳሉ በነገሩ ተከራክ
ውበታል ። ስለዚህ ገና ሳሌታም ግብጾቹም በኅብረት በምጥዋ በሚ
ሩበት ጊዜ ዋናው በግብጽ ስም ያስተዳድር የነበረው ኮሎኔል ቺር
ሳይድና ምክትሉ ከተመለሱ ወዲህ ፣ ምጥዋን ለመጨረሻ ጊዜ ከ
ጣልያኖቹ ጎን ሆኖ ያስተዳድር ለነበረው ለማርኮፖሎ ቤይ ራስ አሉ
ከዚህ የሚከተለውን ደብዳቤ ጽፈውለታል ።

> የተላከ ከራስ አሉላ ዘውእቱ ቱርክ ፓሻ ። ይድረስ ለክቡር ማርኮፖሎ ቤይ ። ኢጣልያኖች መጥተው ምጥዋ ሲገቡ ለምን ዝም አላችኋቸው ። ይኸም አመጣጣቸው በምስር ከደዊ (ከዲቭ) ፈቃድ እንዳልሆነ በኢትዮጵያና በምጥዋ መካከል ያለውን መንገድ እኔ እዘጋዋለሁ ። እናንተስ ለምን ፈቃድ ሰጣችኋቸው ይህቺም ስፍራ የኢትዮጵያ ግዛት መሆኗን ኢጣልያኖችም እንዲቀመጡበት አለመፍቀዱን በስመ ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ አስታውቃችኋለሁና ወደ አገራቸው ይመለሱ ። ሐምሌ 3 ቀን 1878 ዓ.ም.

ኢጣልያኖቹ ምጥዋ የገቡት በጥር 28 ቀን ሲሆን ፣ ደብዳቤው
የጻፉለት በመንፈቁ በሐምሌ ወር ነው ። ይኸውም ማለት በዚሁ ዘመ
በሚያዝያ ፣ በግንቦትና በሰኔ ከወደቡ እያለፉ የምንኩሎን የዊዓን አ
ባቢ ከያዙ በኋላ መሆኑ ነው ። የሆነ ሆኖ ፣ ማርኮፖሎ ራስ አሉላ ለ
ፉለት ደብዳቤ የሰጣቸው መልስ እንዳለ ለመመልከት ባፈላል
አላገኘሁትም ። ሰውዬው በዚህ ጊዜ ከኢጣልያኖቹ ዘንድ ተለጥ
የሚያገለግል ሲሆን ፣ የምጥዋም አያያዝ በከፍተኛ ደረጃ በሮማና በ
ንዶን ባለሥልጣኖች ውስጣዊ ስምምነት ያለቀ ስለሆነ ፣ በቂ ምክንያ
አግኝቶ መልስ የሰጣቸው አይመስለኝም ።

ራስ አሉላ ፣ ይኸን ደብዳቤ ለማርኮፖሎ የጻፉት የኢጣልያ ጦ
በገባበት ዓመት በ1878 ዓ ም. ቢሆንም ፣ ቀጥሎ ባለው በ1879 ዓ.ም
ባንድ ወገን የኢጣልያኖቹ "በወዳጅነት ንግድ ለማስፋፋት ነው የ
ጣነው" የሚለው ማጭበርበር ፣ በሌላ ወገን የእንግሊዝ መንግሥ
በነካፒቴን ሐሪስን ስሚዝ አማካይነት ፣ "የኢጣልያን ምጥዋን መያ

* ሩቤንሰን በገጽ 380 ዶጋሊን እስከ 30 ኪሎ ሜትር መዝለቁን ገልጿል ።

1 A. Del Boca, Gli Italiani in Africa, p. 217.



ተቀበሉ" የሚለው ተጽዕኖ ፣ በሦስተኛ በኩል በሒዊት ውል መሠረት ለሜናዊ ምዕራብ ኢትዮጵያን ከግብጾች ለመረከብ በከሰላ በኩል ከደርቡሾች ጋር የሚደረገው ጦርነት ጊዜ ስላልሰጠ ፣ በትኩሱ የኢጣልያን ጦር ለመቃወም እንዳልተቻለ ሁኔታው ያስረዳል ።

ስለዚህ ፣ ራስ አሉላ ወደ ከሰላ ከመዝመታቸው በፊት ለማርኮፖሎ ጽፈው ከዚያም ወደ ከሰላ ዘመቱ ። በኮፊት ከደርቡሾች ጋር ተዋግተው ቢያሸንፉም የከሰላን ከተማ እጅ ለማድረግ አልቻሉም ። በኮፊቱም ጦርነት ብዙ ሰው አልቆባቸዋል ። ራሳቸውም እንደ ቆሰሉ ተመልክቷል ። ስለዚህ በዚያ በኩል ያለውን ለጊዜው እንዳለ ትተው በ1879 ዓ.ም. ወደ አሥመራ ሲመለሱ ፣ የኢጣልያ ጦር ከወደቡ ዐልፎ ስሐጢ ፣ ዊዓና ዙላ ገብቶ መመሸጉን ሰሙ ።[1] ጄኔራል ጄኒ ይኸንን ወረራውን እንዲቀበሉት የአርኪቆውን (ደሆኖ) ባላባት መሐመድ ቤይ ወይም ናይብ መሐመድ የሚባለውን እየላከ የወዳጅነት ደብዳቤ እያስመሰለ በመጻፍ ያባብላቸው ነበር ።

ራስ አሉላም ፣ የኢጣልያኖች የወረራ አያያዝ ወሰን እንደሌለው ፣ የሚናገሩትም ፣ የሚጽፉትም ሁሉ ሐሰት የሞላበት መሆኑን በመረዳት የጦርነት ዝግጅታቸውን ሳይተዉ ከአሥመራ ወደ ጊንዳ በሚጓዙበት ጊዜ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ጻፉለት ።

> የተላከ ከራስ አሉላ ይድረስ ከጄኔራል ካርሎ ጄኒ... ሰላምታ... በናይብ መሐመድ የላኩብኝ ቃል መልካም ነው። እንግዲህ ወዳጅ ከሆንን ጦር ሠራዊትዎን ከዊዓ ያስነሡ ነጋዴውም በአድገዴ (ሐባብ) በኩል መሆኑ ቀርቶ ለመሸጥም ለመግዛትም ከጊንዳ በኩል ይመላለስ ዊዓ ያለው ጦርዎ እስከ ጥር 13 ቀን ድረስ ይልቀቅ ። ዙላ ያለው ወታደርዎ ከአንድ ወር በኋላ ይውጣ ። ወዳጅነት ከፈለጉ ይኸ መፈጸም አለበት ። ያለዚያ ግን ወዳጅነት መቅረቱን ይወቁት ጥር 5 ቀን 1879 ዓ.ም.

> ለዚህ ደብዳቤያቸው ጄኔራሉ እንደዚህ ሲል ይመልሳል ። በ5 ጥር የተጻፈውን ደብዳቤዎን ናይብ መሐመድ ሰጥቶኝ አነበብሁት ። ወዳጅነት እንደምፈልግ ዘወትር ነግሬዎታለሁ። ዊዓ ያሉት ወታደሮች ይኸን ወዳጅነት አይቃወሙም ። እኔ መቼም ቃሌን አልለውጥም ። ወታደሮቹ ዊዓ የሚቀመጡት

1 A. Del Boca, Gli Italiani in Africa, pp. 277—297.

ላገሩ ጸጥታ ሲባል ነው ። እንዲያውም ከማናቸውም ወገን ውጊያ ቢገጥማቸው እንዲቋቋሙ ከቀድሞው የበለጠ አጠንክሬያቸዋለሁ ይኸንንም የምልዎት የኢጣልያ መንግሥት ሌሎችን ሲያከብር ራሱም መከበር እንደሚፈልግ እንዲያውቁት ብዬ ነው ። የኛ ወዳጅ እስከሆኑ ድረስ እኔም ወዳጅዎ ነኝ ። ምጥዋ ጥር 15 ቀን 1887 ዓ.ም.

በዚህ ጊዜ የኢጣልያ ወታደር ምጥዋ ከገባ ሁለት ዓመት ሆኖታል ። በምጥዋ ሲገቡ ኢጣልያኖቹ ዙላንና ዊዓን በቅድሚያ ቀጥለው ሰሐጢን ሲይዙ የሚሰጡት ሰበብ አንደኛው "ይኸን ክፍል ግብጾች ያስተዳድሩት ስለነበርና እኛ በነርሱ እግር ከገባን መያዝ አለብን" ሁለተኛው "የምጥዋን ወደብ ለማስተዳደር ፣ ንግድን ለማስፋፋት ፣ ያካባቢውን ጸጥታ መጠበቅ ስለሚገባ ይዘነዋል ።" ሦስተኛው "በዚህ አካባቢ ያሉት እስላም ነክ የሆኑት ጎሣዎች በኛ የጥበቃ ሥር መሆንን ስለመረጡ ፣ ከላይ የራስ አሉላ ሹማምንት የነሻለቃ አርአያ የነባላምባራስ ተሰማ ሰዎች ከጊንዳና ከአይለት እየመጡ ስላጉላሉዋቸው እነርሱን የመጠበቅና የመከላከል ግዴታ አለብን" የሚል ነው ። ለነዚህ ሁሉ ራስ አሉላ የሚሰጡት መልስ ፣ ከምጥዋ ወደብ ዠምሮ ያለው ወረዳ የእስላምም ፣ የክርስቲያንም ሕዝብ የሰፈረበት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግዛት ነው ማለታቸውን ከየደብዳቤያቸው ተገንዝበነዋል ። በእርግጥ በሔዊት ውል ውስጥ የግብጾች መልቀቅ የኢጣልያኖች በግብጾች መተካት በምስጢር ስለተያዘ ፣ በሁለተኛው አንቀጽ የቦጎስ ይዞታ ያፄ ዮሐንስ የግዛት ክፍል እንደሚሆን ሲጠቅስ ፣ የምጥዋ ወደብና ቅርብ የወደቡ አካባቢ የሆኑት እነአርኪቆ ፣ እነአራፋሊ ፣ እነዶጋሊ ፣ * እነሰሐጢ ፣ እነአይለት ወደማን እንደሚሆኑ አልተጠቀሰም ።

የሆነ ሆኖ ፣ የኢጣልያ ጦር አዛዥ በየጊዜው እነዚህን አካባቢዎች ወታደር እየላከ ሲያስይዝ ራስ አሉላ በትኩሱ በወታደር ኃይል ሊቃወሙት ያልቻሉበት ምክንያት ካፄ ዮሐንስ ፈቃድ ማግኘቱ ብቻ ሳይሆን ራሳቸውም ፣ ጭፍሮቻቸውም ለዘወትሩ ነዋሪነታቸው ከጊንዳ በላይ በአሥመራ ከተማና በደጋማው ሥፍራ ስለነበረ ፣ ከጊንዳ በታች በበረሃውና በቆላው እስላማዊ ሕዝብ በበረከተበት መካከል ነዋሪ ወታደር የማስቀመጡ ጉዳይ በውሃም ፣ በስንቅም ፣ በአየርም ፣ በኅብረትም ረገድ ችግሩ የበረከተ በመሆኑ ነው ። በእውነትም በቱርክና

* በእግርኛ አጠራር ዶጋሊ የሚባለው በትግርኛ ተደአሊ ይሉታል ።



በግብጽ የበላይነት ሥር በየባላባቱ ሲተዳደር ለብዙ ዘመናት የኖረው የእስላም ሃይማኖት ያቀፈው የሐባብ ፣ የሰናሂት ፣ የሰመሀርና የሾሆ ሕዝብ ከራስ አሉላና ከክርስቲያናዊ ጭፍራቸው ጋር የነበረው ኅብረት የጠነከረ ነው ማለት አይቻልም ።

ስለዚህ ፣ ራስ አሉላ ከከሰላ ጦርነት እንደ ተመለሱ የዊዓንና የዙላን ሠፈሮች ኢጣልያኖች መያዛቸውን ፣ ሰሐጢንም መመሸጋቸውን እንደተረዱት ለዤኔራል ካርሎ ዤኔም ባለፈው ያነበብነውን ደብዳቤ ጽፈውለት የእምቢታና የማስፈራሪያ ቃል ከመለሰላቸው በኋላ ፣ 5 000 የሚደርስ የጦር ወታደራቸውን እንዳስከተሉ በጥር ወር አጋማሽ ላይ 1879 ዓ.ም. ከጊንዳ ቍልቁል ወደ ሰሐጢ መጥተው ወደ ምሽጉ ለመድረስ አምስት ኪሎ ሜትር ሲቀራቸው ሠፈር አደረጉ ። በዚህ ጊዜ በሰሐጢ የ2 ኮምፖኚ የነጭ ፣ 300 ያገር ተወላጅ ወታደር ይዞ መሽጎ የተቀመጠው ማዦር ቦረቲ ከምሽጉ ወጣ ብሎ ጦርነት እንደገጠመ ሁኔታው አደገኛ መሆኑን ሲረዳው ፣ ከነጦሩ ወደ ምሽጉ ተመልሶ ራስ አሉላም ተጠግተው በተደረገው ውጊያ ከኢጣልያኖቹ ወገን ፌደሪኮኩዎም የሚባለው የመቶ አለቃ ከሁለት የኢጣልያና ከሦስት ያገር ተወላጅ ወታደሮች ጋር ሞተ ። ይሁን እንጂ ፣ በምሽጉ ውስጥ ተገን ይዘው የሚዋጉት የኢጣልያ ወታደሮች በውጭ ያለምንም ተገን በሚዋጉት በኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ ብዙ ጉዳት ማድረሳቸውን ራስ አሉላ ሲመለከቱ ፣ የሰሐጢን ምሽግ ትተው ወደታች ወደ ዶጋሊ ወርደው ሠፈሩ ። *

በዚህ ጊዜ ፣ ማዦር ቦረቲ መከበቡን ገልጦ የጦር እርዳታም ፣ ስንቅም ባስቸኳይ እንዲላክለት ያንለቱን ከሰዓት በላይ ወደ ዤኔራል ዤኔ በግሥጋሤ ልኮ ነበረ ። ዤኔራሉም ምንኩሉ ለሠፈረው ለሦስተኛው ባታዬ የእግረኛ ጦር አዛዥ ለኮሎኔል ቶማስ ዴክሪስቶፎሪስ ወታደርም ፣ የጦር መሣሪያም በበቅሎና በግመልም ጭኖ በቶሎ ወደ ተከበበው ወደ ሰሐጢ ምሽግ እንዲዘምት አዘዘው ።

ከዶጋሊ ምንኩሎ ርቀቱ 11 ኪሎ ሜትር ነው ። ከምጥዋ ዶጋሊ 19 ኪሎ ሜትር ሲሆን ፣ ምንኩሎ ከምጥዋ የሚርቀው 8 ኪሎ ሜትር ነው ። በሰሐጢና በዶጋሊ መካከል ያለው ርቀትም 7 ኪሎ ሜትር ስለሆነ

* በሰሐጢ ምሽግ ከበባ 200 የራስ አሉላ ሰዎች ሞተዋል ። ግርክስ በገጽ 86 የሞቱት ቁጥር 100 ይሆናል ይላል ። ከኢጣሊያኖቹም 5 መሞታቸውን ጠቅሷል ።

ከሰሐጢ ምጥዋ 26 ኪሎ ሜትር ይሆናል ። ስለዚህ ኮሎኔል ክሪስቶፎሪስ ትእዛዙ ከሰዓት በላይ እንደ ደረሰው ሌሊቱን ጭምር ሲዘጋጅ አድሮ ሲነጋ 540 የነጭ ፣ ሃምሳ ያገር ተወላጅ ወታደር [1] ሁሉም በደንብ የታጠቁ 10 የሚሆኑ መድፎች ፣ ሁለት መትረየሶች እንደያዘ ከሌሊቱ በ11 ሰዓት በሐያ ደቂቃ ከምንኩሎ ተነሥተው ከጥዋቱ በሁለት ሰዓት ተኩል ዶጋሊ አጠገብ ሲደርሱ ፣ ራስ አሉላ ወታደሮቻቸውን ግራና ቀኝ ሥፍራ ሥፍራ አስይዘው ይጠባበቁ ነበር ። ጣሊያኖቹ ግን ፣ ሁልጊዜ የኢትዮጵያን ጦር በመናቅ መንገድ ለመንገድ ሲመጡ ፣ "ራስ አሉላ እነርሱን በሩቅ አይተው ወደ ጊንዳ እንደሚሸሹ የጦር መኰንኖቹ እምነው ይኸንኑ በጉዞ ላይ ይጨዋወቱ ነበር" ይባላል ። ይሁን እንጂ ፣ የራስ አሉላን አመጣጥና የጦራቸውን ብዛት የሰሙ አንዳንድ በጣልያኖቹ ውስጥ የተቀጠሩ ፓሽ ባዙቆች ከጉዞ ላይ ሰረቅ እያሉ ወደ ጫካ በመግባት የጠፉ ቢኖሩም ፣ በቅርብ የመጣውም ቀደም ብሎ የነበረውም የነጭ ወታደር ወደፊት ሲገሠግሥ ሳለ ሳያስበው ከራስ አሉላ ጦር የእሮምታ ተኩስ ላይ ወደቀ ።

ኮሎኔል ክሪስቶፎሪስ ወታደሩ በቶሎ የመከላከያ ሥፍራ እየፈለገ በመያዝ እንዲመከት ለየሹማምንቱ ትእዛዝ ወዲያው ሰጥቶ ወታደር ከወታደር እየተታኰሰ ውጊያው በተጋጋለበት ሰዓት እርዳታ እንዲደርስለት ወደ ካርሎ ዤኒ በጥድፊያ መላከተኛ ላከ ። ዳሩ ግን ፣ ተኩሱ በሚጋጋልበት ሰዓት ኢትዮጵያውያኑ እያደር ዙሪያውን እንደ ቀለበት ከበው ጠላቶቻቸውን መውጫ መግቢያ አሳጧቸው ። ጣልያኖቹም በያለበት መከበባቸውን ሲያውቁት ጠንክረው ይዋጉ ዠመር ። ነገር ግን ፣ ከያዙት የጦር መሣሪያ ግማሹ በተለይ መድፉና መትረየሱ ከግብጾች በውርስ ይሁን በግዥ ያገኙት አሮጌ መሣሪያ ስለነበረ በመካከሉ አልሠራ እያለ አስቸገረ ። ጥይቱም አለቀባቸው ። ወደ ዤኒ የተላከው መልክተኛ ኢጣልያኖቹ አደገኛ ሁኔታ ላይ መገኘታቸውን አስረድቶ በአራትና በአምስት ሰዓት መካከል ደርሶ እርዳታው ተዘጋጅቶ ከመላኩ በፊት ራስ አሉላና ወታደሮቻቸው ከወዲህ የድል አድራጊነት ሥራቸውን አከናውነው ጨረሱ ። ውጊያውም ያለቀው በመጨረሻ ላይ በጩበጣ ጦርነት ነበር ።

በውጊያው ላይ ዋናው አዝማች ኮሎኔል ቶማሶ ደ ክሪስቶፎሪስ ከ22 የጦር መኰንኖቹ ጋር በጦሩ ሜዳ ላይ እየተዋጋ ወደቀ ። ከመሞቱም በፊት ሻምላውን በቀኝ እጁ ይዞ ፣ "ኢጣልያ ሕያው ትሁን

1 ዘውዴ በገጽ 223 ፣ ሩቢንሰን በገጽ 381 የወታደሮቹ ቁጥር 500 ብቻ መሆኑን ሲገልጽ ፣ ማርከስ ደግሞ በገድ 86 ብዛታቸው 550 ነበረ ይላል ።



ኢጣልያ ሕያው ትሁን! ወደፊት ቅደም! በለው!" እያለ በመጮህ የዠግንነት ሞያ ለማሳየት ሞክሮ እንደነበረ በቁስለኞቹ አንደበት የተነገረው ፣ በኋለኛው ጊዜ በወገኖቹ በኢጣልያኖቹ ዘንድ የመደነቅ ታሪክ አግኝቷል ። ያልተናገረውንም በመጨማመር ቆስሎ ከመውደቁና ሕይወቱ ከመጥፋቱ በፊት በሕይወት ላሉት 12 ወታደሮች በውጊያ ወድቀው ለተረፈረፉት ወታደሮች "የብረት ሰላምታ ስጡ" የሚል ቃል ወርውሯል እየተባለ በየጊዜው ሲጻፍና ሲታመን የቆየውን የዛሬው ተመራማሪ ጸሐፊ አንጀሎ ደልቦካ የፈጠራ ወሬ አድርጎታል ።

በውጊያው ላይ ራሱ ኮሎኔል ክርስቶፎሪስ ከ22 የጦር መኰንኖች ጋር ሲወድቅ 418 ወታደሮች ሞተዋል ። * ከነዚህም ውስጥ ቆስለው ወደ ምጥዋ እንደርሳለን ብለው በሌሊት ጉዞ እያቃሰቱ በመንገድ የሞቱ ምጥዋ ደርሰው ነፍሳቸውን ያተረፉም ይገኛሉ ። አንዳንዶቹም ምጥዋ ሆስፒታል እንደተኙ ለየዘመዶቻቸው በጻፉት ላይ ፣ "ሹማምንቶቻችን ያለምንም ጥናትና ድርጅት ከጦርነት ላይ አጋፍጠውን 'ኢጣልያ ሕያው ትሁን ወደፊት ግፋ' ብለው በመጨረሻ እኛን ጥለውን እነሱ ሸሹ" የሚል ሮሮ ያቀረቡ ነበሩ ። ከተረፉት የጦር መኰንኖች መካከል ካፒቴን ሚሸሊኒ የሚባለው የመድፈኛ የጦር መኰንን እንደ ቆሰለ ወድቆ ሳይሞት የሞተ በመምሰል ከሬሳ ጋር ድምፁን አጥፍቶ ውሎ ሲጨልምና ጸጥ ሲል ከጥቂት ጓደኞቹ ጋር በሌሊት የችግር ጉዞ ተጉዞ ምጥዋ ከገባ በኋላ ፣ እንደ ቀሩት ቁስለኞች በራስ ሙዱር ሆስፒታል ታክሞ ከዳነ በኋላ ወደ አገሩ በሕይወት ለመመለስ ችሎአል ። [1]

በአገራችን የጦርነት ዝክረ ነገር በመዝገብ ይዞ ለትውልድ ማቆየት እምብዛም ስላልተለመደ ፣ በዶጋሊ ጦርነት ከኢትዮጵያ ወገን የሞቱትንም ፣ የቆሰሉትንም የሹማምንቱንም ፣ የወታደሩንም ቁጥር በትክክል አናውቅም ። ደልቦካ በመጽሐፉ ከራስ አሉላ ወገን የሞተውም የቆሰለውም እስከ 1 ሺ መድረሱን ያመለክታል ። [2]

ምንም እንኳን ፣ በዶጋሊ ጦርነት በኢጣልያና በኢትዮጵያ ፣ እንደዚሁም በእንግሊዝ መካከል ብዙ የፖለቲካና የጦርነት ውዝግብ በመፈጠሩ ባፄ ዮሐንስ ዘንድ ቅሬታ ቷፈጥሮ ራስ አሉላ ከጦር ጠቅላይ

* ማርከስ በገጽ 302 የሞቱት 430 ሲሆኑ ፣ የቆሰሉት 82 መሆናቸውን ገልጿል ።

1 L'Italia in Africa — Serie Storico - Ethiopia - Mar Rosso - Tomo VI Documenti (1878—88) - G. Giglio, PP. 27—32. Ang. Del Boca, Gli Italiani io Africa Orientale, pp. 240—243.

2 Ibid.

መሪነቱ ቢገለሉም፣ በዶጋሊው ጦርነት የራስ አሉላ የጉብዝና ዝና በመላው ኢትዮጵያ ተሠራጭቷል ። በኢጣልያኖቹም በኩል ከማናቸውም የዐፄ ዮሐንስ መኰንን የበለጡ የታወቁና በየመጽሐፉ የሚታወሱ ናቸው ። ከዶጋሊ ጦርነት ወዲህ በየጊዜው እንደዚህ እየተባለ ተገጥሞላቸዋል ።[1]

1. መብቱን ዮሐንስ ላሉላ ቢሰጠው
   እንደ ቀትር እሳት ቱርክን ገላመጠው
   ጣልያንም ወደቀ እያንቀጠቀጠው
   አጭዶና ከምሮ እንደ ገብስ አሰጣው

2. አባ ነጋ አሉላ ካሥመራ ቢነሣ
   እንዳንበሳ ሆኖ እሳት እያገሣ
   የችግር ምስጋና ባይወሳ
   ቢቸግረው ጣልያን አለ ፎርሳ ፎርሳ

3. ጣልያን በሀገርህ አልሰማህም ወሬ
   የበዝብዝ አሽከሮች እነሞት አይፈሬ
   ዘለው ጉብ ይላሉ እንደ ጐፈር ዐውሬ

4. አባ ነጋ አሉላ የዶጋ ላይ ኮሶ
   በጥላው ያደክማል እንኳንስ ተቀምሶ

5. ጣልያን ሰሐጢ ላይ እግሩን ቢዘረጋ
   በብረት ምጣዱ በሰሐጢ አዶጋ
   አንገርግቦ ቆላው አሉላ አባ ነጋ

6. ተው ተመከር ጣልያን ይሻላል ምክር
   ሰሐጢ ላይ ሆነህ መሬት ብትቆፍር
   ኋላ ይሆንልሃል ላንተው መቃብር
   ይቺ አገር ኢትዮጵያ የበዝብዝ አገር
   ምንም አትቃጣ እንዳራስ ነብር

ይሁን እንጂ፣ በዶጋሊ የራስ አሉላ አሸናፊነት ያሰፈቃዴ ተዋጋህ በማለት በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ቅሬታ ሲያሳድር፣ በሌላ በኩል በንጉሠ ነገሥቱ ዙሪያ የነበሩ መሳፍንትና የንጉሠ ነገሥቱ ቤተሰቦች ሳይቀሩ ባንድ ወገን አሉላ ከተራ ቤተሰብ የተወለዱ መሆናቸውን በመጥቀስ

---

1 ተ.ጸ.መ.፣ የኢት. ታሪክ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀ.ኃ.ሥ.፣ ገጽ 69



በሌላ በኩል ጠላትን በማሸነፍ ዝናቸው እየገነነ በሔደ መጠን፣ ለወደፊት አስፈሪ ሊሆኑ ይችላሉ በማለት በንጉሡ ዘንድ ጥላቻና ጥርጣሬ እንዲያድር ያደርጉ ነበር ይባላል ።

ከዶጋሊ ጦርነት ቀደም ብሎ በነበረው ጊዜ የወሎ፣ የዋጅራት፣ የየጁ፣ የራያና የአዘቦ ሕዝብ እስላሙ ሁሉ ክርስትና እንዲነሣ ዐፄ ዮሐንስ ባወጁት ምክንያት እነሸኮ ጣህላ የቀሰቀሱት የተቃውሞ ጦርነት አልበረደም ነበር ። ስለዚህም ብዙ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ከመቀሌም ከዐድዋም ወደነዚሁ ወረዳዎች እየዘመቱ ለመደምሰስ የተደጋገመ ሙከራ አድርገዋል ። አሁንም ራስ አሉላ በዶጋሊ የኢጣልያን ጦር ማሸነፋቸው ወሬው የመጣላቸው ደብረ ታቦር (በጌምድር) ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር ባሉበት ሰዓት ነበር ።

በሸዋ ደግሞ፣ በዚሁ ራስ አሉላ ከአሥመራ ወደ ጊንዳ ከጊንዳ ወደ ሰሐጢ ወርደው በዶጋሊ ከኢጣልያኖቹ በሚዋጉበት ሰዓት ራስ ዳርጌ አሩሲን ለማስገበር የሚታገሉበት፣ ንጉሥ ምኒልክ ለከተማቸው ለእንጦጦ ከእቴጌ ጣይቱ ጋር ዋና አልጋ ጠባቂ ራስ ጐበናን ትተው እርሳቸው ወደ ሐረርጌ አሚር አብዱላሂን ለማስገበር የሔዱበት ጊዜ ነበር ። ምኒልክ አሚር አብዱላሂን በታኅሣሥ 29 ቀን 1879 ዓ.ም. አሸንፈው በጥር 3 ቀን ሐረር ከተማ በገቡ በ5ኛው ቀን ራስ አሉላ በዶጋሊ ጦርነት ቀናቸው ማለት ነው ።

ራስ አሉላ በሰሐጢ የነበሩትን የምሽግ ተከላካዮች ለመርዳት የመጣውን ቁጥሩ ከ500 በላይ የሆነውን ጦር እንዳሸነፉ ወደ ምጥዋና ወደ ምንኩሎ ሔደው ወደቡን ለመያዝ ሳያምራቸው አልቀረም ። በዚያን ሰዓት በወደቡ የነበረው የኢጣልያ ጦር ቁጥር 2000 ወታደር ቢሆንም፣ ይኸው ጦር በያለበት ተበታትኖ በምጥዋ ወደብ የነበሩት በመቶ የሚቆጠሩ ፈቃደኞች ግሪኮችና ዐረቦች፣ እንደዚሁም ጥርቅም ባንዳ ብቻ ስለነበሩ፣ በጄኔራል ካርሎ ጄኒና አጠገቡ ባሉት ሹማምንቶች ዘንድ የዶጋሊ ጦርነትና ውጤቱ እንደ ተሰማ ታላቅ ፍርሃትና ሥጋት ነበር ። ስለዚህም ጄኔራሉ በፊተኛው ጊዜ በያለበት የበታተነውን ጦሩን በቶሎ እንዲሰበሰብ አደረገው ።

ስለዚህ ጉዳይ፣ ኤሚሊዮ ዴላቬታ የሚባለው የኢጣልያ የጦር መኰንን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ሐተታ ይሰጣል ።

> “. . . እንደ አላጌውና እንደ ዐድዋው፣ ከዚህ ከዶጋሊው ድል አድራጊነቱ በኋላ ጠላት በፍጹም ወታደር አልባ የሆነውን ምጥዋን ገሥግሦ በመውረር የድል አድራጊነቱን ፍሬ መልቀምን አላወቀበትም ። የዚህም ምክንያት ሐበሾች በጠባያቸው ድል ለማድረግ እርግጠኛ የሚሆኑ

በትን ነገር ካልጨበጡ አይዋጉም ። አወላዋይነት ያለበትን ነገር (ጦርነት) ለመግጠም ጥንቃቄ ማድረግ ይወዳሉ. . .” ፤

ጸሐፊው መኰንን የሚለው በአጋማሽ እውነት ሊሆን ይችላል ። የራሱ የጦርነቱ ዝርዝር ታሪክ እንደሌለን ሁሉ ፣ የራስ አሉላን ወደ ምጥዋ አለመዝመት በኛ በኩል ሰበቡንና ችግሩን የሚናገር ጽሑፍ ባይኖረንም ከአሁኑ ዘመናችን ላይ ሆነን የመላ ግምት ስንሰጥ አንደኛ ፣ የስለላ አቅማችው ደካማ ስለነበረ ፣ በምጥዋ ወደብ መሽጎ የተቀመጠውን የጦር ኃይል በትክክል አይረዱትም ይሆናል ። ሁለተኛ ጦሩ ትንሽም ቢሆን ፣ በደንብ መሽጎ የሚከላከል ጦር ከውጭ የመጣበትን ጠላት እንደ ምንም እንደሚያጠቃው በዚያው ሳምንት በሰሐጢ በተደረገው ውጊያ የደረሰባቸውን ሊገመግሙት ይችላሉ ። ሦስተኛ ከሁሉ የበለጠ ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስ በዙፋን ባላንጣቸው በምኒልክ አንጻር በእስላማዊው ሕዝብ አሸፋፈት ፣ በሰሜናዊ ምዕራብ ኢትዮጵያ በደርቡሾች አነሣሥና አጥቂነት ፊት ፣ ካንድ በእንግሊዝ መንግሥት በተደገፈ ኃያል አውሮፓዊ መንግሥት ጋር ሰረኸም ዘመን ጦርነት መግጠሙን እንደማይፈልጉት አይስቱትምና ከንጉሠ ነገሥቱ ባልተቀበሉት ግልጽ ትእዛዝ ምጥዋን ለመውረር መሞከሩ አደገኛ መሆኑ ሳይሰማቸው አይቀርም ። በዚህም ላይ በሔዊት ውል ውስጥ የግብጽ መሪና ንጉሠ ነገሥቱ ሲዋዋሉ የምጥዋ የወደብ ባለቤትነት ለግብጽ ስለረጋ ፣ ከግብጽም ለኢጣልያ የተላለፈው በእንግሊዝ መንግሥት ፈቃድ መሆኑን አሉላ በግልጽ ስለሚያውቁ ፣ በዚህ ሁሉ ምክንያት መዘዙ ወደበዛው ወደ ምጥዋ ወደብ በማምራት ፈንታ ከዶጋሊ ወደ ጊንዳ ፣ ከጊንዳ ወደ አሥመራ ተመልሰው መዠመሪያ በመልእክት ቀጥለው ራሳቸው በመገናኘት ሁኔታውን ለጌታቸው ለማብራራት ተወሰኑ ።

ስለዚህ ፣ ዤኔራል ካርሎ ዤኒ የራስ አሉላን ከነጦራቸው ወደ አሥመራ መመለሳቸውን ከሰላዮቹ ካረጋገጠ በኋላ ፣ ድንጋጤው በርዶ ወደ ዶጋሊ ሰው ልኮ የሞቱትን የወገኖቹን ሬሳ በሰላምና በጸጥታ ያስለቅም ዠመር ። ፌሪኒ ኦታቪዮ የሚባለው የሃምሳ አለቃ ወደ ኢጣልያ አገር ለወንድሙ ለሉዊጂ ከምጥዋ በጻፈው ደብዳቤ ላይ ፦

ውድ ወንድሜ ከጦርነቱ ወዲህ በሦስተኛው ቀን ባለቆቼ ትእዛዝ ጦርነቱ ወደ ተደረገበት ቦታ የዤግናውን

1 E. Bellavita, Adua, p. 59—67.



ያገራችንን ተወላጅ የሌተና ኮሎኔል ቶማሶ ደ ክሪስቶፎሪስንና ከርሱ ጋር የወደቁትን ሬሳ ለማምጣት ሔድን. . . እንዴት ያለ አስቀያሚ ትርዒት አለው ። ሦስት ጉብታዎች ራቁታቸውን በሆኑና ገና በሚደሙ ሬሳዎች ተሸፍነዋል ። የነዚህም ሰውነታቸው ከብዙ ቦታ ተቆራርጧል ። አንዳንዶቹም የተሰለቡ አሉ ። ጅብና አሞራ ምንም ያህል አልጐዳቸውም ። ውሎ በማደር ሬሳዎቹ ጠቋቁረዋል . . .ከጥቂት ፍለጋ በኋላ የኮሎኔል ክሪስቶፎሪስን ሬሳ አገኘንና በድንኳን ጨርቅ ጠቅልለን በግመል አጉዘን ወደ ምንኩሎ ስንደርስ የክብር አቀባበል ተደርጎለት በካቶሊኮቹ መቃብር ተቀበረ . . . ሲል ያረጋግጣል ።[1]

ነፍሱ የወጣውን ሬሳና አንዳንዱንም ገና የሚያጣጥረውን ሬሳ የምጥዋ ባለሥልጣኖች ከማግሥቱ ጊዜ ዠምሮ እያስለቀሙ የሞተውን በመቅበር ፣ የቆሰለውን በማሳከምና የዳነውን ወደ ኢጣልያ አገር በመርከብ ያግዙ ዠመር ።

1 M. A. Frassinesi, Saati E Dogali, pp. 34—36.

# ምዕራፍ ሠላሳ ሰባት

## ያፄ ዮሐንስ የስሞታ ደብዳቤ ለእንግሊዝ መንግሥት—በገርራር ፖርታል አማካይነት የመጣው አሳዛኝ ደብዳቤ

የዶጋሊ ጦርነትና ፍጻሜው ለኢጣልያ ወዳጅ በሆኑት በእንግሊዝና በጀርመን አገር ሲሰማ 'አብ ሲነካ ወልድ ይነካ' እንደሚባለው፤የነጭ ደም በጥቁር በመደፈሩ ንዴት አሳድሯል። ከጀርመን የበለጠ እንግሊዝ በመካከለኛው ምሥራቅ፤ በተለይ በግብጽና በሱዳን ለወጠነው የመስፋፋት ዓላማው ኢጣልያ፤ ለመሣሪያነት ተመድቦ ሳለ እንደዚህ ያለ ውድቀት ሲያገኘው ንዴቱ የርሱ ሞቅ ያለ ነበር። የፈረንሳይ መንግሥት ግን፤በምጥዋ የኢጣልያ አገባብ ሰበቡን ሁሉ ደህና አድርጎ ስለሚያውቀው ላፄ ዮሐንስ የሞራል ድጋፍ ከመስጠት በቀር በነገሩ አላዘነበትም። በዘርና በቋንቋ እንኳን ለላቲኑ ለኢጣልያ ከአንግሎ ሳክሶኑ ከእንግሊዝ ፈረንሳይ በላቲንነት በጣም ይቀርባል። ዳሩ ግን፤ የፖለቲካ ጥቅም ከዝምድና የበለጠ ስለሆነ ለኢትዮጵያ የፈረንሳይ ድጋፍ እስከ መጨረሻው እስከ ዐድዋ ጦርነት ድረስ ሲዘልቅ የእንግሊዝም ወዳጅነት ለኢጣልያ አልተለየም ነበር።

ቢሆንም፤ ዐፄ ዮሐንስ የዶጋሊን ጦርነት ዝርዝር ሁኔታ ከራስ አሉላ ከሰሙ በኋላ የእንግሊዝን መንግሥት በዚያን ሰዓት የነበረውን አቅዋምና የእርሳቸውንም የቆየ ወዳጅነት ለጥቅሙ ሲል ለኢጣልያ እንደ ለወጠው በትክክል ቢረዱትም፤በመሠረቱ የእንግሊዝ መንግሥት መልክተኛውን ሬር አድሚራል ሔዊትን ልኮ ከግብጽ መንግሥት ጋር ከአዋዋላቸው ወዲህ፤እርሳቸው በውለታቸው ጸንተው ወታደራቸውን በመሠዋት ደርቡሾች የከበቧቸውን ቱርኮችና ግብጾች አድነው በውሉ መሠረት በግብጽ ይዞታ ሥር የነበረውን ሁሉ ለመረከብ በሚዘጋጁበትና አብዛኛውን በተረከቡበት ሰዓት፤ ምስጢሩ ከርሳቸው ተደብቆ በግብጽ እግር የኢጣልያ ጦር አንደኛ ምጥዋ መግባቱ፤ ሁለተኛ ከወደቡ እያለፈ በግብጾች ይዞታ ሥር የቆየውን የአራፋሌን፤ የዊአን፤የዙላንና የስሐጢን አካባቢ መውረሩ፤ሦስተኛ ንጉሠ ነገሥቱ በምጥዋ ወደብ እንደ ልባቸው የሚያስፈልጋቸውን መሣሪያና ሸቀጥ ያለቀረጥ ለማስመጣት እንደሚችሉ በግልጽ ከውሉ ላይ ሠፍሮ የነበረው

ዓመት ሳይሞላው በኢጣልያ ባለሥልጣኖች መሻሩ ስላሳዘናቸው፣ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ለእንግሊዝ ንግሥት ለመጻፍ ተገደዱ።

> በስመ እግዚእነ ኢየሱስ...መልእክት ዘሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ይድረስ ኀበ ክብርት ወልዕልት ቪክቶርያ... ከጻፍኩልዎ ወዲህ* እጅጉን እንዴት ነዎ እኔ ከሠራዊቴ ጋር በእግዚአብሔር ቸርነት በእምነ ጽዮን አማላጅነት አምላከ ቅዱሳን ይክበር ይመስገን ደህና ነኝ ምህረቱ ለዘለዓለም ነውና። የውሉን ነገር መፍረሱን አምና በጾሙ ጽፌልዎ ነበር ምላሹ ግን አልመጣልኝም። በመጀመሪያ ከቱርኮች ጋር ስታስታርቁኝ ስታዋውሉን በሐበሻ መሬት የነበረ የቱርክ ጦር አገሬን ለቆ ወደ አገሩ ሊመለስ፣ እኔም ልሰደው ሲሄድም በስንሃት በእመዴብ ያለውን የጦር መሣሪያ ሁሉ መድፍ ነፍጥ ባሩድ ከዚያው ጥሎልኝ ሊሄድ ደግሞ ከዳተኛ ወስላታ ከኔ ተነስቶ ቅጣት ፈርቶ ወደነዚያ ቢሄድ አስረው ሊሰዱልኝ ከነዚያ ተነስቶ ከዳተኛ ወስላታ ቅጣት ፈርቶ ወደኔ ቢመጣ አስሬ ልሰድላቸው የኔ አገር የሀበሻ ነጋዴ ምጥዋ ገበያ አድርጎ ሲመጣ ላይቀረጥ በዚህ ውል ተዋደን እላንተም እኔም ጽፈን በየማኅተማችን አትመን ባፈረሰውም ምስክር ሊሆን የላንተ ማኅተም ከኔ የኔ ማኅተም ከላንተ ተቀምጧል። አሁንም ጥቂት ሳይቆዩ ውሉን አፍርሰው ደብብ የሚባል ከኔ ከድቶ ወደነዚያ ሄዶ አስረው እንዳይሰዱልኝ ብዙ ነፍጥ ሰጥተው ሸኝተው ቱርኮች ወደ በረሀ ሰደዱት። ነጋዴውንም ዓመት ሳይሞላው ዠምሮ እስከዛሬ ይቀርጣል። እኔ ግን ባዋዋላችሁኝ በውሀ ሙላት ሠራዊቴን አስፈጅቼ ብዙ ጦር ሰድጄ ተከቦ ተጨንቆ የነበረውን ጦራቸውን አውጥቼ ሰደድሁ። ሁለተኛም ደግሞ ኢጣልያ ወዳጅ መስሎ የፍቅር ወረቀት እየጻፈ ገጸ በረከት እየያዘ እየመጣ አገሬን እየሰለለ ነበር። አሁን በመጨረሻው ቱርክ የነበረበትን አገር እንይዛለን አለ። እኔ ግን በአገሬ ምን አለህ ብለው ተጋፍቶ ከሁለት ላይ ክር ቆርጦ ተቀመጠ። ራስ አሉላ ከሰው አገር ምን አመጣህ ሊለው ቢወርድ ተሰልፎ ከርሱ ጋር ተዋጋ ይህን ግን ወደ ላንተ መጻፌ በደሌን ትሰሙልኝ ብዬ ነው። ምን አድርጌ ነው ከኔ የደረሰ ቃል ኪዳኑ የፈረሰብኝ። አሁንም በላንተ ፈቃድ እንደሆነ ላኩብኝ። እርሱ ግን ጠግቦ ተጋፍቶ መጥቶብኝ እንደሆነ እግዚአብሔር ለተበደለ ይበል። ተጽሀፈ አመ 30 ለየካቲት በመቀሌ ከተማ በ1879 ዓ ም

የእንግሊዝና የኢጣልያ መንግሥታት ባፄ ዮሐንስና በኢትዮጵያ ዠርባ ላይ ሽርክነታቸው የታወቀ ስለሆነ፣ ከዚህ በላይ ካፄ ዮሐንስ ለንግሥቲቱ የተጻፈላቸውን ደብዳቤ ጠቅላይ ሚኒስትሩና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከተነጋገሩበት በኋላ፣ የኢጣልያ መንግሥት ጉዳዩን ዐውቆት መልስ ለመስጠት እንዲመቸው ትክክለኛ ግልባጩን ሎንዶን በሚቀመጠው በኢጣልያ ጉዳይ ፈጻሚ በሲኞር ካታላኒ አማካይነት እንዲተላለፍለት አደረጉ። እንደ እውነቱ ንጉሠ ነገሥቱ እንደ ዳኛ ሆኖ ይፈርድልኛል በማለትና በወዳጅነት መልክ እንደ ስሞታ የላኩት ደብዳቤ እንደ ምስጢር ተቆጥሮ መያዝ ነበረበት እንጂ ለባላጋራ መስጠት አልነበረበትም። ወይም የርሳቸውን ለኢጣልያ ባለሥልጣኖች እንደ ሰጡ የጣሊያኖቹንም ትክክለኛ የመልስ ሰነድ ላፄ ዮሐንስ መላክ ነበረባቸው። ነገር ግን፣ ይኸን ትክክለኛ የዳኝነት አቀዋም እንግሊዞቹ ስለ አልወሰዱ፣ ያፄ ዮሐንስ አቀዋምና ስሜት ለኢጣልያኖቹ ግልጽ ሲሆን፣ የኢጣልያንና የእንግሊዝ ትክክለኛ ዓላማ ላፄ ዮሐንስ ድፍንም ሳይሆን የተጭበረበረ ነበር ለማለት ይቻላል።

አሁንም ሲኞር ካታላኒ ከውጭ ጉዳዩና ከተጠባባቂው ጠቅላይ ሚኒስትር ከፍራንቸስኮ ክሪስፒ የተላከለትን መመሪያ መሠረት በማድረግ ያፄ ዮሐንስን ደብዳቤ ግልባጭ ስለሰጡት፣ ምስጋናውን አቅርቦ አሁንም በንግሥት ቪክቶርያ ስም ከእንግሊዝ መንግሥት ላፄ ዮሐንስ የሚሰጠው መልስ ዐፄ ዮሐንስን የልብ ልብ ሰጥቶ የሚያኮራ እንዳይሆን ለማሳሰብ ጉዳይ ፈጻሚው ለእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትርና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በጻፈው ደብዳቤ ላይ፡—

> ወደ ንግሥት ቪክቶርያ ንጉሡ ዮሐንስ በጻፈው ደብዳቤ ላይ እንደሚታየው፣ በእኛና በእንግሊዝ መንግሥት መካከል ያለው የጋራ ግንኙነት እንደዚሁም ምጥዋንና አካባቢውን ለመያዝ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር በመስማማታችን እንዳልገባው ይታያል... ስለዚህ በሚጻፍለት የመልስ ደብዳቤ ላይ የሁለቱ መንግሥታት ስምምነትና ወዳጅነት እንዲገለጽለት ያስፈልጋል የሚል ቃል ይገኝበታል። ይኸውም ማለት ከሁለቱ ጥብቅ ወዳጅነት የተነሣ በዚህ ወዳጅነት ተኩራርቶ የልብ ልብ የበቃው ክሪስፒ ዐፄ ዮሐንስ በእንግሊዝ ወዳጅነት ተስፋ እንዲቆርጡ በሌላው መንግሥት

* በካፒቴን ሐሪሰን ስሚዝ እጅ የላኩትን ማውሳታቸው ነው።

ጉዳይ ገብቶ የደብዳቤ አጻጻፍ እስከ ማስተማር ደርሷል ማለት ነው ።

በዚህ ምክንያት ፣ የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ለኢጣልያ መንግሥት ወደ ምጥዋ አገባብ እንደሚስማማ ሆኖ ላፄ ዮሐንስ ያዘጋጁትን የደብዳቤ ግልባጭ ራሱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሎርድ ሳሊስበሪ በጉዳይ ፈጻሚው በካታላኒ አማካይነት ለክሪስፒ ከላከ በኋላ ፣ ዋናውን ደብዳቤ ወዳፄ ዮሐንስ የሚያደርስ ሲፈልግ ፣ ምርጫው በካይሮ ከሚቀመጠው በባሪንግ ሥር የዲፕሎማሲውን ሥራ ከሚያካሒደው ከሚስተር ዤራል ፖርታል ላይ ወደቀ ። በዚህ መካከል ፣ የኢጣልያ መንግሥት የዶጋሊን እልቂት ለመበቀል ስለፃተ ፣ ለዚህም የሚያስፈልገውን የጦር ዝግጅት ከማድረግ ላይ ስለሚገኝ ፣ በጥቅምት 1880 ዓ ም የእንግሊዝ መንግሥት ሁለቱ መንግሥታት ወደ ትልቅ ጦርነት ከመግባታቸው በፊት ፖርታል በንግሥቲቱ ስም ሔዶ ሁለቱን ወገኖች ለመገላገል የሚያስችል የዕርቅ አሳብ እንዲያቀርብ ወሰነ ። እስከዚያም ድረስ ኢጣልያኖች የበቀሉን ጦርነት በትዕግሥት እንዲያቆዩ ስምምነት ተደረገ ።

ስለዚህ ፖርታል የንግሥቲቱን ደብዳቤ ይዞ ከርሱም ጋር ምስተር ቤች በግብጽ ጦር ውስጥ የሚያገለግለውን እንግሊዛዊና እንደዚሁም አህመድ ፋህሚ የሚባለውን ግብጻዊ የአማርኛ ቋንቋ ከነጽሕፈቱ ዐውቃለሁ የሚለውን ላስተርጓሚነት አስከትሎ ከካይሮ ወደ ምጥዋ ለመጓዝ ተዘጋጀ ። የጉዞው ዓላማ በምስጢር እንዲያዝ ስላስፈለገ ፣ ማናቸውንም ጥንቃቄ ለማድረግ ሲባል ፖርታል ከስዊዝ ወደ ምጥዋ ሲጓዝ በመርከብ ላይ ሥፍራ የተያዘለት በአገልጋዩ እንግሊዛዊ በሁትሺስንና በሦስት ጓደኞቹ ስም ነበር ።

በዚህ ዐይነት ፣ ፖርታል ከነጓደኞቹ በጥቅምት 1880 ዓ ም ከካይሮ ወደ እስክንድርያ ሔዶ ከሎንዶን በንግሥቲቱና በሎርድ ሳሊስበሪ ስም ላፄ ዮሐንስ የተጻፈውን ደብዳቤና ገጸ በረከት ተረከበ ። ላፄ ዮሐንስ ፣ ለልጃቸው ለራስ አርአያና ለራስ አሉላም በስጦታ መልክ የሚቀርብ የጦር መሣሪያ አብሮ ተዘጋጅቷል ። ፖርታል ከነጓዙ ከእስክንድርያ ካይሮ ተመልሶ ከዚያ ናርጊለህ በሚባለው የግብጽ መርከብ ተሳፍሮ በጀዳና በሱአኪን ዐልፎ በጥቅምት 29 ቀን ምጥዋ ገባ ። በዚያም በጄኔራል ጄኒ አግር የተሾመው ዋናው አዛዥ ጄኔራል ሳሌታና የኢጣልያ ባለሥልጣኖች ካመት በፊት ለካፒቴን ሐሪሰን ካደረጉት የበለጠ አቀባበልና መስተንግዶ ለሰር ፖርታል አድርገው ከምጥዋ ወደ ጉራዕ እስቲጓዝ ድረስ በግብዣ ሲያንከባክቡት ውለው አደሩ ። ከዚያም ወደ አሥመራ እርሱም ጓዙም የሚጫኑበት በቅሎም ፣ ፈረስም ፣ ግመልም አቅርበው በማናቸውም ነገር አስደሰቱት ።



ፖርታል ሁለቱን ወገኖች ለማስታረቅ የሚያስችለውን ከኢጣሊያ በኩል ከዶጋሊ ጦርነት በኋላ ፣ የበቀል ጦርነቱን ሊያስቀር ይችላል ተብሎ በኢጣልያን ባለሥልጣኖች የቀረበውን የጥያቄ ረቂቅ እንደያዘ ራስ አሉላ አሉ ወደ ተባሉበት ወደ ጉራዕ ለመሔድ ተዘጋጀ ። በጄኔራል ሳሌታም አሳሳቢነት ላስተርጓሚነት ብሩ ወርቄ ፣ እንደዚሁም ለመንገድ መሪነትና ለጭነት የሚያግዙ ያገር ተወላጆች ተጨማምረው ሰር ፖርታል ከምጥዋ ወደ ምንኩሎ ሔደ ። ከዚያም በኮሎኔል አቮጋድሮ አዘጋጅነትና ሸኝነት በኅዳር መዠመሪያ ላይ በአይለትና በጊንዳ በኩል ዐልፎ ወደ አሥመራ ጉዞውን ቀጠለ ። አሥመራም ደርሶ ወደ ጉራዕ ለመጓዝ ሲዘጋጅ ፣ “ወደዚያው መጣሁ ጠብቁኝ” የሚል መልእክት ከራስ አሉላ ደረሰው ። ከዚያም ራስ አሉላ ኅዳር 11 ቀን አሥመራ እንደገቡ ከሰር ፖርታል ጋር ተገናኙ ። ዐይናቸው የነብር ዐይን የሚመስለው አሉላ ቁጭ እንዳሉ ተቀብለው እጁን እንደ ጨበጡት ለርሳቸው የመጣውን የማንቸስተር ጠበንጃ ከ800 ጥይት ጋር አቀረበ ። ቀጥሎ ላፄ ዮሐንስ የሚሰጥ የንግሥት ቪክቶርያ ደብዳቤና ገጸ በረከት ስላለ ንጉሡ ወዳሉበት ወደ ደብረ ታቦር ለመሔድ ቢጠይቃቸው ፣ “ጉዳዩን ንገረኝ” ብለው እንዳስቸገሩትና አልነግርም በማለቱ ፣ “የኢጣልያን ሰላዮች ናችሁ” በማለት መጉላላት እንደ ደረሰበት ወደ ንጉሡም እነርሱን ለመላክ አሉላ የፈሩት ፣ ንጉሠ ነገሥቱ የዶጋሊን ጦርነት ሁኔታ ከነርሱ በዝርዝር ሲሰሙት እንዳይቆጧቸው ወይም ከሐማሴን ሽረው ወደሌላ እንዳያዛውሯቸው መሆኑን በአሳቡ የመሰለውንና ከየሰዉ የሰማውን በራሪ ወሬ በመጽሐፉ አስፍሮታል ።[1]

ይሁን እንጂ ፣ ራስ አሉላ የፖርታልን አሥመራ መድረስ ለዐፄ ዮሐንስ አስታውቀው ፣ ወደ ደብረ ታቦር ለመላክ ፈቃድ ሲጠባበቁ በመጨረሻ ንጉሠ ነገሥቱ ከደብረ ታቦር መጥተው አሸንጌ ላይ ለመገናኘት ማሰባቸውን ስለሰሙ ፣ ይኸንኑ ለፖርታል ገለጹለት ። ወዲያውም የዐድዋው ገዥ ቢቶደድ ገብረ መስቀል መጥተው መስተንግዶም አቅርበው ፖርታልን ወደ አሸንጌ ከሰደዱት በኋላ ፣ በአሸንጌ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ተገናኝቶ ከንግሥቲቱ የተላከውን ደብዳቤና የሰይፍ ገጸ በረከት አቀረበ ።

ከእንግሊዝ ንግሥትና ከሎርድ ሳሊስበሪ ላፄ ዮሐንስ የመጡት ደብዳቤዎች ሁለቱም በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል ስላለው ክርክር

1 G.H. Portal, My Missioo to Abyssinia, pp. 57—84.

ጉዳይ ለግልግል በካይሮ ሌጋሲዮን የዲፕሎማቲክ አባል በሆነው ሚስተር ፖርታል እጅ መላኩን ፣ እርሱም የታመነና ችሎታ ያለው ሰው ስለሆነ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከርሱ ጋር በእምነትና በግልጽ ተነጋግረው የዕርቁን ነገር እንዲጨርሱ የሚል የማስተዋወቂያ ደብዳቤ ነበር ። ሁለተኛው ደብዳቤ ፍሬውን ጉዳይ የያዘው ነበር ። ከዚህ በፊት እንዳልነው ፣ በሎርድ ሳሊስበሪ ተረቆ የኢጣልያ ተጠባባቂ ጠቅላይ ሚኒስትር ተመልክቶ የተቀበለውን የንግሥቲቱንና የራሱን የሎርድ ሳሊስበሪን ደብዳቤዎች አቀረበ ። የንግሥቲቱ ደብዳቤ በተለመደው አርዕስትና ሰላምታ ይዠምራል. . .

. . .ኃያላን ከሆኑትና መልካም ስሜት ካላቸው ኢጣልያኖች ጋር በመጣላታችሁ አዝነናል ። በሔዊት አማካይነት በተደረገው ውል መሠረት የንግድን ነጻነት በደንብ ለማከናወን ምጥዋን ሔደው በያዙ ጊዜ የውሉን ጉዳይ በጥንቃቄ ፈጽመዋል ። እርስዎ ውሉ በትክክል አልተፈጸመም ብለው ሐዘንዎን በገለጹ ጊዜ ፣ ነገሩን ለመመርመርና ጠቡ የተነሣበትን ሁኔታ ለማወቅ ምስተር ሐሪስን ስሚዝን ስለ ላክነው፣ ከዚያ ወዲህ በሁለታችሁ መካከል ያለው ጠብ ተወግዶ በሰላም የወዳጅነት ግንኙነት ታደርጋላችሁ ብለን ተስፋ አድርገን ነበር ።

የንግድን ነጻነት ለመጠበቅም አንድ ወኪል ለመላክ አስበናል ። ነገር ግን ፣ የርስዎ ዤኔራል ራስ አሉላ ኢጣልያኖቹ ኢትዮጵያን ለመውረር አሳብ ሳይኖራቸው ተጓዢ ነጋዴ በደንብ እንዲተላለፍ ሲሉ በመልካም ስሜት ሰሐጢንና ዊዓን መያዛቸው ነገሩ ስለ አልገባው ተሳስቷል ። ያለአገባብ በመውጋቱ በመካከላቸው ጦርነቱ ተፈጠረ ።

አሁንም ኢጣልያኖቹ በደረሰባቸው የጦርነት አደጋ ካሣ ካላገኘን እንደሰትም ጦርነቱን እንቀጥላለን ብለው በቁርጥ ተናግረዋል ። እነሱም በጣም ኃያላን ናቸው። ነገር ግን እርስዎ ሰላም ክፈለጉ በምን ሁኔታ ለመስማማት እንደሚፈልጉ ጠይቀን ወደ ስምምነቱ እንድትደርሱ ወደፊት እንረዳዎታለን ። ነሐሴ 1887 ዓ.ም.*

በዚህ ደብዳቤ ላይ ፣ የእንግሊዝ መንግሥት የቃል ኪዳን ጓደኛው እንደመሆኑ መጠን ፣ የኢጣልያ መንግሥትን ወራሪነት በደንብና

* ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ነው ።



በግልጽ ሲደግፍ ይታያል ። በንግድና በጸጥታ አጠባበቅ እያመካኙ የሰሐጢንና የዊዓን ወረዳ የወረሩትን ኢጣልያኖች የእናት አገራቸውን ግዛት ለመከላከል ራስ አሉላ ያደረጉት ጦርነት በእንግሊዞች ዘንድ እንደ ወንጀል ተቆጥሮባቸዋል ። አጻጻፉ ያው ከሪስፐ እንደ ተመኘው ዐፄ ዮሐንስን ተስፋ የሚያስቆርጥና የኢጣልያን የወራሪነት ዓላማ በግልጽ የሚደግፍ ነው ።

ስለዚህ ሰሞኑን መላክተኛው ፖርታል የራስ አሉላን አጥቂነት በመደጋገም ስለ ጠቀሰ ፣ ንጉሠ ነገሥቱም አሉላን ለመከላከል ሲሉ ፣ "እናንተስ እንግሊዞቹ ያገራችሁን ወሰን አበሾች መጥተው ጥሰው ቢገቡ ዝም ትሉዋቸዋላችሁ ወይ?" በሚል ጥያቄ ሲመልሱ ፣ እርሱም "በአውሮፖችና በሠለጠኑት አገሮች ዘንድ ይኸን የዶጋሊን አልቂት የመሰለ ሁኔታ አይፈጸምም" እያለ ለኢጣልያኖቹ ሲከራከር ሰነበተ። በአነጋገሩም ኢጣልያኖች በሰሐጢ መሽገው እንዳልተዋጉ ኮሎኔል ክርስቶፎሪስ የጦር ወታደር ይዞ እነዚያን በውጊያ ሊረዳ እንዳልመጣና እንዳልተዋጋ በሰላም ስንቅ ለማቀበል ጣልያኖቹ ሲመጡ ብቻ ራስ አሉላ በመንገድ አድብተው ያላገባብ እንደ ፈጅዋቸው እያስመሰለ ፣ በንግግሩ ውጊያ በማለት ፋንታ ደጋግሞ የሚጠቀምበት ቋንቋ 'ማላክር' "ፍጅት" ነው ።

የሆነ ሆኖ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከአሸንጌ ወደ መቀሌ ከመጡ በኋላ በክርክሩ መካከል ሚስተር ፖርታል ከኢጣልያኖቹ ጋር ስምምነት አድርጎ ከነርሱ የተቀበለውን የዕርቅ አሳብ ለንጉሠ ነገሥቱ አቀረበላቸው ። ከኢጣልያኖቹ ተዘጋጅቶ በሚስተር ፖርታል እጅ የቀረበው የስምምነት ረቂቅ ከዚህ እንደሚከተለው በአምስት አንቀጽ ላይ የተከፈለ ነው ።

1ኛ/ በአሳሆርታና በሐባብ የዐረብ (እስላሞች) ነገዶችና እነርሱ በሠፈሩበት ወረዳ ሁሉ የኢጣልያ የበላይ ጠባቂነቱ እንዲታወቅ ፣

2ኛ/ ሰሐጢና ዊዓ በዙሪያቸው እስከ አንድ ቀን መንገድ ያለው ወረዳ ጭምር የኢጣሊያ መንግሥት መሬት ይሆናል ።

3ኛ/ ሁለተኛ የወሰን ክርክር ተነሥቶ ጠብ እንዳይፈጠር ሁለቱ ወገኖች የሐበሻን ጥቅም ከሚጠብቀው ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር በመስማማት በወሰን ላይ ዐምዶች (ምልክቶች) ተክለው ይወስናሉ ። የጊንዳ ከተማው የሐበሻ ሆኖ እንደ ወሰን ይቆጠራል ።

4ኛ/ ሰናሂት የኢጣልያ ግዛት ይሆናል ።

## 5ኛ/ የሰላምና የወዳጅነት ፡ የንግድም ውል በኢጣልያና በሐበሻ መካከል ይፈረማል ።

ከዚህም በቀር ፡ ከኢጣልያኖቹ በኩል በአንደኛ አንቀጽ፡ "ባለፈው በጥር ወር በዶጋሊ በተደረገው አግባብ በሌለው ውጊያ ንጉሠ ሐዘናቸውን በይፋ እንዲገልጹ" የሚል ለፖርታል አቅርበውለት የነበረውን ሐሳብ ፡ ፖርታል ንጉሠ ነገሥቱ እንደማይቀበሉት በማመን ይኸን ወደጐን አድርጎ ከዚህ በላይ በአምስት አንቀጽ ያለውን ብቻ አቀረበላቸው ።[1]

ከዚህም ጋር አያይዞ ፡ ንጉሠ ነገሥቱ ይኸን የውል አሳብ ተቀብለው ከኢጣልያ ጋር መስማማታቸውን በመልከተኛው አማካይነት ለእንግሊዝ ንግሥት ቢገልጡ ፡ በሰላምና በንግድ መስፋፋት አገራቸውን ለማሳደግና ለማስፋፋት እንደሚችሉ ያለውን ተስፋ ከመግለጥ ጋር ፡ በበኩሉም የኢጣልያ መንግሥት ይኸን ውል በመቀበል ንግዱን በሰላምና በወዳጅነት እያስፋፋ ከንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ጋር በሰላም እንደሚኖር ከማረጋገጥ ጋር የውሉን አሳብ እንዲቀበሉ ገፋፋቸው ።

ንጉሠ ነገሥቱ ፡ የንግሥቲቱንም የሳሊስበሪንም ደብዳቤ አላይ የተዘረዘረውንም ድርድር በነብሩ ወልቃኢቴ አማካይነት ወደ አማርኛ የተተረጐመው በንባብ ተሰምቶ ጉዳዩን በየመልኩ ከተረዱት በኋላ ፡ በፍጹም እንደማይቀበሉት ገልጸው በበኩላቸው በንግሥቲቱ አማካይነት ለእንግሊዝ መንግሥት የሚላከውን ደብዳቤ አዘጋጅተው፡ ለራሱም ለመንግሥት መላከተኛ እንደሚያደርጉት ከግምጃ ቤታቸው አስገብተው ላንድ የኢትዮጵያ የደጃዝማችነት ማዕረግ ላለው የሚገባውን ቀሚስና ድርብ ኩታ ከባለ ጐፈር ለምድ ጋር አልብሰው በብር የተለበደ ጋሻና ጦር ሸልመው ወደ አገሩ መለሱት ።

ንጉሠ ነገሥቱ ለእንግሊዝ ንግሥት የመለሱት ደብዳቤ ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።


> በስመ እግዚአብሔር . . . ከሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ለወዳጃችን ለትልቂቱና ለደገኛዪቱ ንግሥት ቪክቶርያ. . . ከጻፍሁልዎ ወዲህ እንደምን ነዎ. . . በጥቅምት 12 ቀንና ደግሞ ከኢጣልያኖች ጋራ ታረቁ የሚል በኅዳር 16 የተጻፉ ደብዳቤዎች ደርሰውኛል በእርስዎም ላይ በቱርኮችም ላይ (ምስሮች) ምንም አለማድረጌንና ክፉ ሥራ አለመሥራቴን በእውነት ገልጬ እነግርዎታለሁ በእኔና በእንግሊዝ በምስርም መካከል የተደረገው ውል እኔ ሳልፈቅድ አንድ እንኳ መሣሪያ በምጥዋ በኩል እንዳይወጣ ነበር ። እነሱ ግን ውሉን አፍርሰው መሣሪያ አምጥተው ለሼሆ ጎሳ ሸጠዋል ። ሼሆም ጎሳ ባገሬ ላይ ትልቅ ሁከት አስነሥቷል ።
>
> ኢጣልያኖች ተበድለናል ስለ ማለታቸው ግን ፡ ጥፋቱ የነሱ ነው እንጂ የእኛ አይደለም ። የኢትዮጵያን ነጋዴዎች በመከልከላቸውና ስሐጢንና ዊዓን በመያዛቸው ጠብ የጀመሩ እነሱ ናቸው ። ንግዱን ስለምን ከለከሉ ፡ ወደአገሬ ስለምን ገቡ እኔም በንግሥት ቪክቶርያ ፈቃድ መጥታችሁ እንደሆነ ማኅተም አሳዩኝ ፡ አለዚያ አገሬን ልቀቁ ብዬ ጻፍኩላቸው ። እነሱ ግን፡ እምቢ ስለአሉ በዚህ ምክንያት ከራስ አሉላ ጋር ጦርነት ገጥመው ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰዎች ሞቱ ። እርስዎስ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠኝን አገር እንደ ምን ለኢጣልያኖች ልቀቅ ይሉኛል ፡ ልቀቅ እንኳ ቢሉኝ ያልተገባ ነገር ነው ።
>
> የእርስዎ አሳብ በመካከላችን እርቅ ለማድረግ እንደሆነ ይህ እርቅ የሚሆነው እነርሱም ባገራቸው እኔም በአገሬ ሆነን ነው ። አሁን ግን በሁለታችንም ወገን ፈረስ ተጭኗል ጐራዴም ተመዟል ቁጥሩም እንደ አሸዋ የሆነ ወታደሬ ለጦርነት ተዘጋጅቷል ። ኢጣልያኖች ጦርነት ማድረግ ፈልገዋል ።
>
> ቢሆንም ኃይል የኢየሱስ ክርስቶስ ነውና የፈቀዳቸውን ያድርጉ እኔ ግን በሕይወተ ሥጋ እስካለሁ ድረስ እነሱን ፈርቼ በጉድጓድ ውስጥ ተደብቄ ለመኖር አልችልም ። በኅዳር 24 ቀን 1880 ዓ.ም. በአሸንጌ ከተማ ተጻፈ ።

እንደዚሁም ከንግሥት ቪክቶርያ በምስተር ፖርታል እጅ ስለ ተላከላቸው አንድ በወርቅ ያጌጠ ጐራዴና አንድ በሩቅ የሚያሳይ መነጽር መድረሱን ገልጸው ፡ ለልጃቸው ለራስ አርአያም ለተላከው ማለፊያ ጐራዴ ለብቻም የምስጋና ደብዳቤዎች ጽፈው ከሰጡት በኋላ ከመቀሌ ቤተ መንግሥታቸው አሰናብተውት ወዳገሩ ሔደ ። ከዚህ ጊዜ በኋላ በኢትዮጵያም ፡ በኢጣልያኖቹም በኩል የጦርነቱ ዝግጅት በግልጽ ይካሔድ ጀመር ።

---


1 G. Portal, My Mission to Abyssina, pp. 167—169. F. Crispi, La Prima Guerra d'Africa, pp. 34—35.





ዐፄ ዮሐንስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት

(ፐብሊክ ሬኮርድ ኦፊስ ፡ ለንደን)



ዐፄ ዮሐንስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት

(ፐብሊክ ሪከርድ ኦፊስ ፣ ለንደን)

መልእክት፡ዘራስ፡አሉላ፡ዘውእቱ፡
ቱርክ፡ባሻ፡ይድረስ፡ከግሮልድ፡ሄር
ቃሐ፡የእንግሊዝ፡ንግሥት፡መልእክ
ተኛ።እንዴት፡ሰነበትህ፡እኔ፡እግዚአ
ብሔር፡ይመስገን፡ደኅና፡ነኝ፡የቀደ
ሞም፡አርቃችንን፡ታውቀዋለህ፡ከናን
ተም፡ወዲ፡ኢትዮጵያ፡አለፈቃዳችሁ፡
ለዋቻሁ፡ሊመጣ፡እንደሬን፡ሰንሰኛ።እና
ንተም፡ከኛ፡አለፈቃዳችን፡ከኢትዮጵ
ያ፡ወደናንተ፡ሰዋችን፡ሊመጣ፡አከሬ
ቻሁ፡ሐትለዱልን፡ይህ፡ነው፡እርቃችን፡
አሁንም፡በሁለታችን፡ቤት፡፲፰፻፹፩፡
መንግሥት፡መካከል፡ጠብ፡የለንም፡ጠ
ብ፡የሚያጣላን፡ይለ፡ነገሬ፡ተከሕክሎ፡
ይሉ፡በዚህ፡ይበብ፡በሚባል፡ሺፍታ፡ነው፡
እንጂ፡በሁለታችን፡ጠብ፡የለንም።አሁን
ም፡ይበብ፡ምጥዋ፡ውስጥ፡ነው፡ይለና፡
እንደ፡ርቃች፡እንድፍቅሎችን፡ይበብን፡
እንድ፡ትዝ፡ይሁን፡ከኢጣልያን፡ጋራም፡
ይጣላን፡ይበብ፡ነው፡ይህን፡ማለቴ፡ከሁ
ለት፡ቤት፡መንግሥት፡መካከል፡ይለ፡
አመጠኛ፡ቤጠት፡፲ቤት፡መንግሥት፡
ፍቅር፡ይጠናል፡ነጋዴም፡እንዲወትሮ
ው፡ይነግድ፡ብሎ፡ነው፡ግን፡ይህን፡
ማለቴ፡የፍቅራችንን፡እይቻ፡ነው፡እንጂ፡
የትእዛዝ፡አይደለም፡፲፪ተጽሕፈ፡አመ
፳ወ፳ለጥቅምት።



ራስ አሉላ ለሰ ርጀራልድ ኸርበርት ፖርታል የጻፉት

(ፐብሊክ ሪኮርድ ኦፊስ ፡ ሎንደን)

# ምዕራፍ ሠላሳ ስምንት

## የምኒልክ ኃይል እየተጠናከረ መሔድ በምጥዋ መያዝና በዶጋሊ ጦርነት ንጉሡ የነበራቸው አቅዋም

በዚህ ዘመን በነበረው የንጉሡ ነገሥታዊ ሥልጣን ደካማነትና እንዲሁም በኃይለኛና በደንበኛ ማዕከላዊ መንግሥት እጦት የተነሣ ባፄ ተክለ ጊዮርጊስ ዘመነ መንግሥት ዮሐንስና ምኒልክ ፥ ራሳቸውም ተክለ ጊዮርጊስ ጭምር በየፊናቸው ከውጭ መንግሥታት ጋር የወዳጅነት ግንኙነት ያደርጉ እንደ ነበረው ፥ እሁንም ቢሆን ንጉሥ ምኒልክ የዐፄ ዮሐንስን የበላይነት ዐውቀው ፥ የንጉሡ ነገሥትነትንም ሥያሜ በይፋ ከለቀቁላቸው በኋላ ፥ እንደ አንድ የነጻ መንግሥት መሪ ከውጭ መንግሥት ጋር የነበራቸውን ግንኙነት አላቋረጡም ።

በ1870 ዓ ም ዐፄ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ ለላሴ ተገናኝተው ስምምነት ባደረጉበት ጊዜ ፥ በዚያው ምዕራፍ ላይ የተመለከትነውን ግዴታ ሲያስገቡ ፥ ምኒልክ ከውጭ መንግሥታት መሪዎች ጋር በጽሑፍም ፥ በመላክተኛም አማካይነት ግንኙነት እንዳያደርጉ ንጉሠ ነገሥቱ ግዴታ አላስገቧቸውም ። ጉዳዩ እንደዚሁ በዝንጋታና ባለማወቅ ይታለፍ ወይም ተጠይቀው ምኒልክ እምቢ ይበሉ በትክክል አናውቅም ። የሚመስለው ግን ፥ ሳይታወቅ እንደዚሁ መታለፉ ይመስላል ። ራሱ መገበራቸው እንደ ትልቅ ውጤት ስለ ተቆጠረ ፥ ይኸኛውን ችላ ማለት ግዴታ የሆነ ይመስላል ።

ይሁን እንጂ ፥ ከ1870 ዓ ም እስከ 1880 ዓ ም ድረስ ባለው የ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ዮሐንስና ምኒልክ የበላይና የበታች ሆነው ይነስ ይብዛ በስምምነት ኖረዋል ። በመካከሉ ጠብ የሚያስነሣ ነገር ሲገጥም ሁለቱም ሲያበርዱት ታይቷል ። በዚህም ጊዜ ውስጥ ንጉሥ ምኒልክ ያፄ ዮሐንስን የበላይነት ዐውቀው በመገበር ተስማምተው ፥ በዚህ በኩል የነበረውን ችግር ካስወገዱ በኋላ ፥ እንደ ልባቸው ግዛታቸውን በደቡብ ፥ በምዕራብና በምሥራቅ ኢትዮጵያ በኩል ማስፋፋት ፥ ከቀድሞውም የሸዋ ግዛት በቀር በቅርብ ካቀኗቸው አውራጃዎች በጦር

አለቆቻቸው አማካይነት ወታደር እያስመለመሉ ኃይላቸውን ማጠና
ክር ፡ ከውጭ መንግሥታት በተለይም ከኢጣልያኖችና ከፈረንሳዮች
ጋር እየተላላኩ በስጦታም ፡ በግዥም በሚያገኙት ዘመናዊ የጦር መሣ
ሪያ ወታደራቸውን ማስታጠቅና ማደራጀትን ሥራዬ ብለው ይዘ
ውት ነበር ።

በ1874 ዓ ም ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር በእምባቦ ተዋግ
ተው ካሸነፉ ወዲህ ፡ በ1879 ዓ ም ከአሚር አብዱላሂ ጋር በጨ
ለንቆ ተዋግተው ሐረርጌን ከያዙ በኋላ ፡ በማናቸውም ረገድ ኃይላ
ቸው ከቀን ወደቀን እየጠነከረ ሔዶ ንጉሠ ነገሥቱን እስከ ማሥ
ጋት ማድረሱ ግልጽ ነበር ።

በዚህ ዐይነት ፡ በውስጥ አስተዳደርና በወታደር አያያዝ አቅዋማ
ቸውን እያጠነከሩ ፡ በዲፕሎማቲክ በኩል ደግሞ ከውጭ መንግሥ
ታት ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ገና በዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ዘመነ መን
ግሥት የዠመሩትን ባሁኑ ጊዜ የበለጠ እያስፋፉት ሔደዋል ። ከኢጣ
ሊያ ጋር ግንኙነት የዠመሩት ከ1864 ዠምሮ መሆኑን የግንኙነቱ
አማካይ ሞንሲኜር ፡ ጕሊዮልሞ ማሳያ የሚባሉት የካቶሊክ ሚስዮን መሪ
መሆናቸውን አባ ሚካኤል የሚባሉ ኢትዮጵያዊ በዚሁ ዘመን ከምኒ
ልክ ተልከው ወደ ኢጣልያ ሔደው ለኢጣሊያ ንጉሥ ለቪክቶር አማ
ኑኤል ካልዓይ ደብዳቤ አቅርበው ፡ የመዠመሪያውን የኢጣሊያንና
የሸዋን ግንኙነት እንደ ከፈቱ በታሪክ ተመዝግቦ የሚገኘውን ከዚህ
በፊት አውስተናል ።

ከዚያ ወዲህ ግንኙነቱ በመጻጻፍ ደረጃ ከዘለቀ በኋላ ፡ በመጨ
ረሻ በ1869 ዓ ም ማርኬዝ ኦራሲዖ አንቲኖሪ የሚባለው ከኢጣልያ
አገር በተለይ ከዢዎግራፊ ማኅበር ተልኮ መጥቶ ከንጉሥ ምኒልክ
ጋር ተገናኝቶ አንኮበር አጠገብ ልጥ ማረፊያ የሚባለው ሥፍራ ለማ
ረፊያ ተሰጥቶት እንደ ነዋሪ መልእክተኛ ሆኖ ተቀመጠ ። በዚያም
ሲኖር አቶ ነከሬ የሚባሉ ኢትዮጵያዊ ባልደረባ ተሰጥተውት የፖለቲካ
ውንም ፡ ያገር ምርመራውንም ሥራ ሲያካሒድ ፡ በመካከሉ በ1874
ዓ ም ዓውሬ አደን ሲሔድ ጠበንጃ ባርቆ ገደለውና እዚያው ልጥ
ማረፊያ ተቀበረ ።

ከአንቲኖሪ በኋላ ደግሞ ፡ ኮንት ፒዮትሮ አንቶኔሊ ወደ አንኮ
በር መጥቶ ደንበኛ ነዋሪና የኢጣሊያ ጉዳይ ፈጻሚ ሆኖ ተቀመጠ ።
በርሱም አማካይነት የኢጣልያ ንጉሥ ኡምቤርቶና የሸዋ ንጉሥ ምኒ
ልክ የጠበቀና የተቀራረበ ግንኙነት አድርገው ደብዳቤና ገጸ በረከት
በየጊዜው እየተለዋወጡ ወዳጅነታቸውን አጠበቁ ። ቀድሞ ዐፄ ዮሐ
ንስ "ኢጣልያ ወዳጅ መስሎ የፍቅር ወረቀት እየጻፈ ገጸ በረከት እየያዘ



እየመጣ አገሬን እየሰለለ ነበረ" ብለው ለንግሥት ቪክቶርያ
በጻፉት ደብዳቤ ላይ ከገለጹ በኋላ በመጨረሻ ግን ፡ የኢጣልያን የወ
ረራ ምኞት በግብርም በአሳብም ተረድተው እንደጻፉት ንጉሥ ምኒ
ልክም የኢጣልያ መልክተኞች ወደ ሸዋ ሲመላለሱ ከመልክተኞቹ አን
ደበት ዘወትር የሚሰሙት ፡ ፈረንጆቹ በሃይማኖት ክርስቲያኖች ፡
ከእስላሞቹ መንግሥት አደጋ ክርስቲያኖቹን የሚጠብቁ ፡ ባገር ላይ
ሥልጣኔን የሚያስገቡ ፡ የባሪያን ንግድ ለማስቀረትና ንግድን ብቻ
ለማስፋፋት የሚጣጣሩ ይመስሏቸው ነበር ። እንዳዬ ዮሐንስ እርሳቸ
ቸውም በዚያን ሰዓት ይወነጅሉና ይወቅሱ የነበረው በቀይ ባሕር
ዳር ያለውን የኢትዮጵያን ግዛትና በር የያዙትን ቱርኮችንና ግብጾችን
ነበር ። ሁለቱንም ነገሥታት የባሕር በር የማጣቱ ጉዳይ ያብከነክና
ቸው ነበር ።

ስለዚህም ፡ ንጉሥ ምኒልክ በ1872 ዓ ም ለሦስተኛው የፈረንሳዊ
ሬፐብሊክ ፕሬዚዳንት ለሙሴ ዤል ግሬቪ በጻፉት ረዥም ደብዳቤ
ውስጥ ፡—

"...ብዙ ጊዜ ወዳንተ መንግሥት ጽፈን ነበር ። አንድ እንኳ
መልስ አላገኘንም . . . ምነው የለመንነውን አትመልሱልንምን
የምንለምነውም ብርሃን (ሥልጣኔ) ነው እንጂ ሌላ አይደለም . . .
...ይህም ብርሃን ለምሥራቅ ሁሉ የተረፈው ምነው ከኛ ድረስ
አለመምጣቱ . . .የአውሮፓ ሥርዓት ሁሉ ምልክት ወደ መንግ
ሥታችን ተሰምቷል ። የባርያ ንግድ ጠፋ ዕለት ዕለት የወንበዴ
መቅሠፍት እናጠፋለን . . . ግብጻውያን ግን በኢትዮጵያ ሰዎች
ጥሩ ክርስቲያን በሆነ ሕዝብ የሚቀኑ በመልካም ሥርዓት ከቆሙ
ከአውሮፓ ሕዝብ ጋራ እንዳንስማማ መሰናከያውን ሁሉ ያመ
ጡብናል ። የኢትዮጵያ በር ሁሉ በእጃቸው ነው ለኛ የሚጠቅ
መውን ፡ መልካም ነገር የሚስበውን ምክንያት ሁሉ ይከለክሉ
ናል . . ."የሚል የሮሮና የወቀሳ ቃል ይገኝበታል ።

ከዚህም እያይዘው ፈረንሳይ የያዘውን የአቦክ (ጅቡቲ) በር
ለሸዋ መንግሥት በቸርነትና በፈቃዱ የሚሰጥ መስሏቸው ፡
"የፈረንሲስ መንግሥት ግን ለተጨነቁ ሰዎች የምታስብ ለተከበቡም
የምትረዳ ናት . .ምነው አቦክ (ጅቡቲ) የፈረንሳውያን በር የሚ . . .
ሆን ለወትሮው የሸዋ በር አይሆንም ? ወንድማችነን የምንለም
ነው ይህ ነበር ነገሩን በጣም መርምሮ ሲያበቃ . . ." የሚል ቃል
ጨምረዋል ።

እንደዚሁም ፡ ቀደም ብለው በደብዳቤና በመልክተኛ አማካይነት
የተዋወቁትን የኢጣልያ ንጉሥ ሲጠቅሱ ፡ "የሮማ የጊዎግራፊያ ማኅበር

ከወዳጃችንና ከወንድማችን የኢጣሊያ ንጉሥ ፣ አገር የሚያዩ መልክተኞች ሰደው ነበር” የሚል ቃል ይገኛል ። ይህ አሁን ወንድምና ወዳጅ የሚሉት የኢጣሊያ ንጉሥ ኡምቤርቶ ወደፊት እንደምን ጠላታቸው እንደሚሆን ይገነዘቡታል ።

አሁን ግን ፣ ንጉሥ ምኒልክ በዚህ ዘመን ከምጥዋ ወረራ በፊት በፈረንጆቹ የመንግሥታት መሪያዎች ላይ ያላቸውን አለኝታና ተስፋ በትክክል ይገልጻል ። በአውሮፓ የፈረንጆቹን አሳብ ሁሉ እየተከታተለ የሚጽፍላቸው ወኪል ስለሌላቸው ፣ የፈረንጆቹን የወራሪነት መንፈስ አፍሪካም እንዳትሠለጥን የሚያደርጉትን ተንኮል እምብዛም አያውቁትም ። ቢያውቁት ኖሮ ፣ የኢጣሊያ መንግሥት እንዳደረገው የፈረንሳይ መንግሥት ከባላባቶቹ ገዝቶ በውል የያዘውን የጅቡቲን ወደብ በልመናና በፈቃድ ይሰጠኛል ብለው ተስፋ በማድረግ በደብዳቤ እስከ መጠየቅ አይደርሱም ነበር ።

በዚህ ዘመን ባለው የአውሮፓ ሥልጡንነትና ኃያልነት በአፍሪካ አለመሠልጠንና ደካማነት የተነሣ ፣ የአውሮፓውያንን የወረራ ተንኮል ማናቸውንም የዚህን ዘመን የአውሮፓ የአጥቂነት በትር ቢሰሙም ቅሉ ፣ ከመቻል በቀር ምንም የሚያደርጉት ነገር አልነበረም ። በኋለኛው ዘመን እንደ ተፈጠረው ያለ አቤቱታ እንኳ የሚቀርብበት ዓለም አቀፍ ማኅበር አልነበረም ። የኢጣሊያ መንግሥት በግብጾች እግር ገብቶ ምጥዋንና አካባቢውን ሲወር ፣ ዐፄ ዮሐንስ በጥቅሻ አንዲይዝ ለጋበዘውና ለሚያበረታታው ለእንግሊዝ መንግሥት አቤቱታና ስሞታ ማቅረብ ግዴታቸው ሆኖ ሳለ ፣ የቅኝ አገዛዙ አንጋፋው መንግሥት ምንም ሊያደርግላቸው አልቻለም ። ቢችልም የሩቁን ጥቁር ‘ያልሠለጠነ’ አፍሪካዊ መንግሥት ከመርዳት ይልቅ ነጩን አውሮፓዊ በጦርነትና በፖለቲካ ሊረዳው የሚችለውን በዘርና በጉርብትና የሚቀርበውን ኢጣልያን መርዳቱ ይቀለዋል ።

የሆነ ሆኖ ፣ ንጉሥ ምኒልክ በማናቸውም ረገድ ከፈረንሳዊ መንግሥት ጋር በሙሴ አርኑ ፣በሙሴ ሽፍኔ ፣በሙሴ ብሬሞ ፣ በሙሴ ሳቩሬ . . . አማካይነት ፤ ከኢጣልያ መንግሥት ጋር በአባ ማስያስ ከዚያም ወዲህ በማርኬዝ አንቲኖሪ ፣ በኮንት አንቶኖሊ ፣ በትራቬርሲ ፣ በሳሊምቤኒና በሌሎችም አማካይነት ከሁለቱም መንግሥታት ጋር ግንኙነታቸውን በሚቀጥሉበት ጊዜ ፣ ወደ ንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣን ያወጣኛል ብለው ያመኑበትን የጦር መሣሪያ እንደልብ ይሰበስቡ ነበር ። ለዚህም ጉዳይ አማካይ የነበሩት የአውሳው ባላባት ሙሐመድ አንፋሪ ፣ የዘይላው ባላባት አቡበከር ፣ የሙሐመድ አንፋሪን ልጅ ያገባው አብዱራህማን ፣ የትግራይ ተወላጆች ዮሴፍና ንጉሤ የሐራምባው አቶ



አጥሜና ያንኮበሩ አቶ ነከሬ ናቸው ። ዮሴፍ በኋላ ግራዝማች ተብለው የውጫሌን ውል የተረጐሙ ናቸው ። በዘይላ በኩል ለሚመጣው የጦር መሣሪያና ሸቀጥ አቡበከር ተቀብሎ ለሐረሩ ገዥ ለደጃች መኰንን ሲያስተላልፍ ፣ በአሰብ በኩል ደግሞ የሚመጣውን መሐመድ አንፋሪ ተቀብሎ ለአንኮበሩ ገዥ ለአዛዥ ወልደ ጻድቅ ያስተላልፋል ። ሁለቱም እየተቀበሉ ገጸ በረከቱንም ይሁን ወይም የጦር መሣሪያውን ፣ አዲስ አበባ ለንጉሥ ምኒልክ ይልካሉ ወይም ራሳቸው ያስረክባሉ ። ከፈረንሳይ የበለጠ ንጉሥ ምኒልክ የወዳጅነትና የጥቅም ፣ የንግድ ግንኙነታቸውን ከኢጣልያ መንግሥት ጋር አጠንክረው ነበር ። በመጨረሻም በግንቦት 10 ቀን 1875 ዓ ም በ18 አንቀጾች የተከፈለ የወዳጅነትና የንግድ ውል የኢጣልያ ንጉሥ ወኪል አንቶኔሊና ንጉሥ ምኒልክ አንኮበር ላይ ተዋዋሉ ።

ስለዚህ ከዐፄ ቴዎድሮስ ሞት ወዲህ ኢትዮጵያ የሦስት ነገሥታት (ተክለ ጊዮርጊስ ፣ ዮሐንስ ፣ ምኒልክ) አገር ትመስል እንደ ነበር አሁንም የምኒልክ ሁኔታ ሲታይ ፣ አንድ መንግሥት በሌላ መንግሥት ውስጥ ወይም ኢትዮጵያ አሁንም የሁለት ነገሥታት አገር እንደሆነች የሚያስቆጥር ነበር ። በውጭ አገር መንግሥታትም ዘንድ የሚገመተው በዚሁ ዐይነት ነበር ። የሁለቱም ነገሥታት አቅዋም በየጐብኝዎቹ አስተያየት እየተገመገመ ዮሐንስ “ሃይማኖት አጥባቂ የሥልጣኔ ተቃዋሚ” እየተባሉ ሲዘለፉ ፣ ምኒልክ “ሥልጣኔ ወዳድ ፣ እንግዳ ተቀባይ ፣ ስለ ሃይማኖት እምብዛም ግድ የሌላቸው” እየተባሉ በመሞገስ መጽሐፉም ፣ ጋዜጣውም በውጭ አገር የሚጻፈው በዚሁ ዐይነት ነበር ።

የሆነ ሆኖ ፣ ምኒልክ የኢጣልያኖችን ምጥዋ መራገፍ አስቀድሞ በተባራሪ ወሬውን እንደ ሰሙት ፣ ቀጥሎም በሐረር አሚር አብዱላሂን አሸንፈው እንደ ተመለሱ ኢጣሊያኖች ከምጥዋ ወደብ እያለፉ መስፋፋታቸውን ፣ በመጨረሻም የዶጋሊውን ጦርነትና የራስ አሉላን አሸናፊነት የሰሙት ካፄ ዮሐንስ ደብዳቤ መሆኑንና በሰሙም ጊዜ በኢጣልያ የወረራ ሁኔታ መገረማቸውንና መሥጋታቸውን ፣ በሸዋም የኢጣልያ መልካሙ አቅዋም እንደ ተበላሸ ባጠገባቸው የኢጣሊያ መንግሥት ወኪል ሆኖ የተቀመጠው ኮንት አንቶኔሊ ያረጋግጣል ። የኢጣልያው ነዋሪ መልክተኛ የኢጣልያ ጦር ምጥዋ ስለ መግባቱ ምኒልክ ከንጉሠ ነገሥቱ ደብዳቤ በደረሳቸው ጊዜ መልክቱ የደረሳቸው ካፄ ዮሐንስ መሆኑን ሳይገልጹ ካንድ ተመላላሽ ነጋዴ እንደሰሙ መስለው እንደ ጠየቁትና እርሱ ስለዚህ ስለምጥዋ መያዝ የሚያውቀው ነገር አለመኖሩን እንደ ገለጸላቸው ያስረዳል ።

በእርግጥም የሮማ ባለሥልጣኖች ባለፈው እንዳመለከትነው ፣ ወደ ምጥዋ ጦር የላኩት ምክር ቤቱም ሳይጠየቅ ፣ ሕዝቡም ሳይሰማ በድብቅ ስለነበር በዘመኑ የመገናኛ ችግር እርሱ አንኮበር ወይም እንጦጦ ተቀማጭ ሆኖ በእርግጥም ላይሰማው ይችላል ። የዚሁኑ ጉዳይ ይኸው አንቶኔሊ እንጦጦ ሆኖ ለኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በግንቦት 1878 ዓ.ም. በጻፈው ሪፖርት ላይ እንደዚህ ይላል ።

> . . . አንድ በትግሬ የሚኖር ነጋዴ ፣ኢጣልያ በወታደር ኃይል ምጥዋን ይዞታል በየቀኑም የጦር መሣሪያ ያገባል 30 የሚሆኑ የጦር መርከቦች በምጥዋ ወደብ ቆመዋል ብሎ ከጠረፍ ስለጻፈልኝ ፣ ይህ ነገር ሐሰት ነው ወይስ እውነት ብለው ንጉሡ (ምኒልክ) ሲጠይቁኝ ከኢጣልያም ከአሰብም ምንም ስለዚህ ጉዳይ የደረሰኝ ወሬ የለም ብዬ መለስሁ ። በዚያን ጊዜ የኢጣልያ የጦር አዛዥ ለምጥዋ ሕዝብ ያደረገውን አዋጅና ነጋዴው የጻፈውን በዝርዝር አነበቡልኝ ። በዚያን ጊዜ ምንም እንኳን ገና እርግጡን ባልገነዘበው ነጋዴ የተባለው የበላዩ አለቃ (ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስ) መሆናቸው ገባኝ ። እኔም ከአሰብና ከኢጣልያ አገር ትክክለኛውን ወሬ እስካገኝ ድረስ ስለዚህ ጉዳይ ምንም የማስረዳው ነገር የለኝም ብዬ አስታወቅሁ...ከዚህ ቀን ዠምሮ ያለን ግንኙነትና በዚህ አገር (በሸዋ) ያለው ሁኔታችን የሚያወላውል አደገኛና እንግዳ ነገር ሆነ ። ኢጣልያ በርሳቸው ላይ ጦርነት እንደማታደርግ ቢገነዘቡም ፣ በነገሩ መገረምና ሥጋት በፊታቸው ላይ ይታይ ነበር . . .[1]

በእርግጥ እስከዚህ ጊዜ ድረስ እላይ እንዳልነው ፣ በዮሐንስም በምኒልክም ዘንድ እንግሊዞችም ፣ ፈረንሳዮችም ፣ ኢጣልያኖቹም በመጨረሻ እውነተኛው መልካቸው በተግባር እስኪገለጽ ድረስ እንደ ወዳጅ እንደ ጠባቂ ይታዩ ነበር ። ምኒልክና የኢጣልያ ንጉሥ ኡምቤርቶ በሚጻጻፉት የወዳጅነት ደብዳቤ ላይ ከየመልክተኞቹ እንደበት በሚሰማው ፣ "ኢጣልያ ከንግድ ማስፋፋትና ከወዳጅነት በቀር መሬት አይፈልግም" እየተባለ ነበርና አሁን ምኒልክን ከሥጋትና ከመገረም ላይ የጣላቸው ፣ እብለት ከሌለበት ከንጉሠ ነገሥቱ ደብዳቤ ላይ እንደ ወዳጅ ይመለከቷቸው የነበረው የኢጣሊያኖችን አገር ወራሪነት መስማታቸው ነው ።

አንቶኔሊ ብዙ ጊዜ በአንኮበርም ፣ በአንጐለላም ፣ በእንጦጦም ሲቀመጥ ከምኒልክም ፣ ከመኳንንቱም ፣ በተለይ ከአንኮበሩ ገዥ ከአዛዥ

1 F. Crispi, La Prima Guerra d'Africa, pp. 76—78; C. Rossetti, Storia Diplomatica, p. 27.



ወልደ ጻድቅ ጋር ቅርብ ግንኙነት ስለ ነበረው ፣ በኢጣልያኖቹ ምጥዋ መግባት የምኒልክ መሥጋትና መገረም እርሱን ትንሽ ሳይገርመው አልቀረም ። ሁልጊዜ አፍሪካዊን የመናቅና የማቅለል ስሜት ስለአለ በአንቶኔሊ አጻጻፍ በንጉሥ ምኒልክ ዘንድ የነበረውን የንጉሠ ነገሥትነት ምኞት ስለሚያውቅ ፣ ላፄ ዮሐንስ መገበራቸውም ያለውድ በግዴታ መሆኑን በመገንዘብ ፣ ከኢጣልያ መንግሥትም ጋር በነበራቸው ጥብቅ ወዳጅነት "መልካም ነው በርቱ እናንተ ከምጥዋ በኩል ስትዋጉ ፣ እኔ ደግሞ ዐፄ ዮሐንስን እወጋለሁ" የሚል መልስ ሲጠብቅ ሳለ ፣ አሁን የምኒልክ መገረምና የመሥጋት ሁኔታቸው እንደ ገረመው በሌላው አጻጻፉ ይታያል ። እንደዚሁም ምጥዋ በተያዘ በሁለተኛው ዓመት ስለ ደረሰው ስለዶጋሊ ጦርነት ሌላው ሌዎፖልዶ ትራቬርሲ የሚባለው የአንቶኔሊ ጓደኛ ኢጣልያ አገር ለሚገኘው ለፕሮፌሰር ዳላቬዶቫ በጻፈው ደብዳቤ ላይ፡—

> "የዶጋሊ የጦርነት ውጤት በቅድሚያ ከራስ አሉላ ቀጥሎ ከንጉሠ ነገሥቱ ተጽፎ ወሬው በዚህ አገር (በሸዋ) የተሰማ ጊዜ የሐበሾቹ (የሸዋዎቹ ጭምር) ደስታ እስከ ማላበድ ደርሶ ነበር ። ነገሩ የእኔን ራስ መብረቅ እንደ መታው ቆጥሬዋለሁ ፤ ብዙ ገንዘብ የወጣበት ብዙ ድካም የተደረገበት አሳብ(በንግድ የመስፋፋቱ ጉዳይ ?) እንደ ጭስ በኖ ጠፋ ። እንግዲህ አገራችን ብዙ በሚሊዮን የሚቆጠር ሰውና ገንዘብ ወደሚስያጠፋ ጦርነት መግባቷ ነው . . . ንጉሡ ብቻ ከሌሎቹ ብልህነት ስለአለው የነገሩን አደገኛነት በመገንዘብ በሥጋት የተዋጠ ይመስለኛል . . . "ሲል ጽፏል ።[1]

በዚህ ዐይነት ፣ በአንኮበርና በልጥ ማረፊያ ብዙ ዘመን በመቀመጥ የንጉሡንም ባለሟልነት እስከ ማግኘት የደረሰው ይኸው ሌዎፖልድ ትራቬርሲ አሳቡና ምኞቱ ኢጣልያ ወደ ኢትዮጵያ በሰላምና በወዳጅነት ገብታ ሁለቱ አገሮች በንግድና በልማት አብረው እየሠሩ ለመጠቀም እንደ ነበረ በአጻጻፉ ይታወቃል ። የዚህንም አሳብ የሚደግፉ በኢጣልያ አገር ብዙዎች እንዳሉ ከዚህ በፊት አውስተናል ። ነገር ግን ፣ እዚህ እዶጋሊ ጦርነት የተደረሰውና ወደፊትም እስከ አላጌውና እስከ ዐድዋ ኃይለኛ ጦርነት የሚራዘመው በዚህ የቅኝ አገዛዝ ምኞት በተጋነነበት ሰዓት የደጐቹ አሳብ እየመነመነ የከፉዎች ምኞት እያሸነፈ በመሔዱ ነው ።

1 A. Del Boca, Gli Italiani in Africa, p. 271.

# ምዕራፍ ሠላሳ ዘጠኝ

## በኢጣልያና ባፄ ዮሐንስ መካከል የምኒልክ ያስታራቂነት አሳብ አለመሳካት ፡ ለፈረንሳይ ፕሬዚዳንት የተላኩት የስሞታ ደብዳቤዎች ፍሬቢስነት

በዚህ ዘመን ፡ ኢትዮጵያን የሁለት መሪዎች አገር ከሚያስመስ ላት አንዱ ፡ ኢጣልያኖች ምጥዋ ገብተው በተስፋፉበት ሰዓት የምኒ ልክ የአስታራቂነት አቀዋምና ከመዠመሪያው ላይ ያፄ ዮሐንስም አሳቡን መቀበል ነበር ። በሁለቱም ቤተ መንግሥት ፈረንሳዮችና ኢጣሊያኖች ስለ የግል አገራቸው ከመሥራት ላይ ይገኙ ነበር ። በሸዋ ቤተ መንግሥት በዚያን ጊዜ አንቶኔሊ የኢጣልያን ምጥዋ መግባት ከመንግሥቱ መሪዎች በተለይ ከቀጥታ አለቆቹ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖች በዝርዝር ከተጻፈለት ወዲህ በተቻ ለው መጠን የሚሯሯጠው ለምኒልክና ለየመኳንንቱ የጦር መሣሪያና የሸቀጣ ሸቀጥ ገጸ በረከት በማቅረብና በማባበል ወዳፄ ዮሐንስ እን ዳይደረቡ ለማድረግ ነበር ።

ባንድ ወገን ደግሞ ፡ በሰሜን ባፄ ዮሐንስ ዘንድ ፖርታል ከእን ግሊዝ መንግሥት ተልኮ የዕርቅ አሳብ አቅርቦ ሁለቱን ጠበኞች ለማ ስማማት በሚሞክርበት ጊዜ ፡ ለሜይ የሚባለው በምጥዋ የፈረንሳይ ቆን ሲል የእንግሊዝና የኢጣሊያን መመሳጠር ለንጉሠ ነገሥቱ በጣማ ለጽ ዕርቁ እንዳይቃና ጥረት አድርጓል ። በሸዋም ካፒቴን ሎንግቢ የሚባለው የፈንረሳይ ተወላጅ ከእንግሊዝም ፡ ከኢጣልያም ለኢትዮጵያ የሚሻለው ፈረንሳይ መሆኑን ገልጾ ፡ "የኢጣልያ መንግሥት የጦርም ሆነ የገንዘብ ኃይሉ ደካማ ሆኖ ብድር በብድር ነው" እያለ በምኒ ልክ ዘንድ ለማስናቅና ለማጥላላት ቢሞክርም ፡ ለጊዜው በሸዋ ቤተ መንግሥት ቀደም ብሎ ከዐሥር ዓመት ዠምሮ የተመሠረተውን የኢ ጣልያኖቹን ወዳጅነት ሊፈነቅለው አልቻለም ።

በሌላ ወገን ደግሞ ፡ ምኒልክ ካፄ ቴዎድሮስ ሞት ወዲህ የንጉሠ ነገሥትን ሥያሜ በራሳቸው ለራሳቸው ከተቀዳጁ በኋላ ፡ በዕርቅ ይኸን ሥያሜ ለዮሐንስ መልቀቃቸው ፡ የወሎ ግዛት ከእጃቸው መውጣቱ ፡

ንጉሠ ነገሥቱ "ምኒልክ ያመጠብኝ እንደሆነ በሸዋ አነግሠዋለሁ" በሚሉ ዓላማ መሸሻ ሳይፉን ማቅረባቸውና ማከበራቸው በምኒልክ ዘንድ ግልጽ ቢሆንም ፤ ሁለቱ ውስጡን እየተጐነታተሉ ላዩን በጋብቻ ተሳስረው የስምምነት መልክ እያሳዩ ተቻችለው በነበሩበት ሰዓት በምጥዋ በኩል በኢጣሊያና ባዬ ዮሐንስ መካከል ጠብ ስለተፈጠረ ፤ በምኒልክና በመኳንንቶቻቸው ዘንድ ተመክሮና ተዘክሮ የተወሰነው ምኒልክ ሁለቱን ጠበኞች እንዲያስታርቁ የሚል ነበር ። በዚህ ምክንያት የኢጣሊያኑ ወኪል አንቶኔሊ መኳንንቱ ባሉበት ተጠርቶ ከምኒልክ የተነገረው ቃል እንደዚህ የሚል መሆኑን በኢጣልያንኛ ቋንቋ ራሱ ባሠፈረውና ለመንግሥቱ ባስተላለፈው ማስታወሻ ውስጥ ይገኛል ።

"የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና የኢጣሊያ ንጉሥ ለውጊያ መሰለፋቸውን ሰማሁ ።

እኔ እንደ አንድ ኢጣልያዊ ኢጣልያን እወዳለሁ ። ሔጄም ይቺን የተወደደች አገር ለመጐብኘት ምኞቴ ነው ማን ያውቃል አንድ ቀን አምላክ ይኸን ምኞቴን ይፈጽምልኝ ይሆናል ።"

ባንድ ወገን ደግሞ ፤ እዚህ ላይ ዝርዝሩን መግለጽ አስፈላጊ ባይሆንም ፤ "ከጃንሆይ (ዮሐንስ) ጋር በእምነትና በወዳጅነት በመሐላ ተሳስሬያለሁ ። አሁን እኔን የቸገረኝ ሊዋጉ በተሰለፉ ሁለት ወዳጆች መካከል መገኘቴ ነው . . . እኔ መቼም አንድ ንጉሣዊ አማራ ነኝ አገሬንም እወዳለሁ ስለዚህም የምፈልገው የሁለታችሁን ዕርቅ ነው ።

በዚህ ምክንያት ፤ ጃንሆይንና የኢጣልያን ንጉሥ የምጠይቀው ሽማግሌ ሆኜ እንዳስታርቃቸው ፈቃዳቸው እንዲሆን ነው ። አሳቤን ሁለቱም ወገኖች የተቀበሉ እንደሆነ ወደ ኢጣልያ አገር መልክተኛዬን እልካለሁ በዚህም የተነሳ (ዕርቅ የሆነልኝ እንደሆነ) ባገሬ ታሪክ ውስጥ ስሜ ይገኛል ። ከሁለቱ ወገኖች አንዱ ዕርቁን እምቢ ያለ እንደሆነ የማደርገውን እኔ አውቀዋለሁ ፤ ጦርነት ለፈለገው ወገን የኔን ድጋፍ አልሰጠውም ።"[1]

በዚሁ መንፈስ ለኢጣሊያ ንጉሥ ኡምቤርቶ የጻፉትን ደብዳቤ በልጥ ማረፊያ ተቀማጭ የሆነው የአንቶኔሊ ጓደኛ ዶክተር ራጋሲ

1 Carlo Rosseti, Storia Deplomatica dell Etiopia Durante il Regno di Menelik II, pp. 31—32.



ቪንቸንሶ ይዞ ወደ ሮማ እንዲሔድ ሲደረግ ፤ ስለዚሁ ጉዳይ ደብዳቤና ገጸ በረከት ይዘው ወዳጄ ዮሐንስ የተላኩት ደጃዝማች መሸሻ ወርቄ* እና ቢቶደድ አጥናፌ ፤ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ ነበሩ ። ጳጳሱ የተላኩት ለጉዳዩ ክብደት ለመስጠት ነበር ። የተጻፈው ደብዳቤ በትክክል ምን እንደሚል ለመረዳት ራሱንም ወይም ቅጅውን ለማግኘት አልቻልንም ። ዶክተር ራጋሲ የምኒልክን ያስታራቂነት ደብዳቤ ይዞ በሚሔድበት ጊዜ አንቶኔሊም በዚሁ አጋጣሚ ጊዜ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለክሪስፒ በጻፈው ደብዳቤ ላይ ፤ "አደራችሁን የምኒልክን አስታራቂነት በንቀት ተመልክታችሁ ችላ እንዳትሉት" የሚል ቃል ጨምሮ ልኳል ። ይኸንንም ለማሳሰብ የተገደደበት ምክንያት ፤ ባንድ ወገን በከፍተኛ ደረጃ የእንግሊዝ መንግሥት ሰር ጄራልድ ፖርታልን ልኮ ሁለቱን ጠበኞች ለማስታረቅ መዠመሩን ፤ በሌላ ወገን ደግሞ ፤ በእንጦጦ ቤተ መንግሥት እኔ አስታርቄ መልካም ዝና ላትርፍበት የሚል የጋለ ምኞት በምኒልክ ዘንድ ማደሩን ስለተገነዘበውና የኢጣሊያ መንግሥት ለእንግሊዞቹ አስታራቂነት ዋጋ በመስጠት የምኒልክን በመናቅ ፤ ምኒልክ ደግሞ በዚሁ ተናደው ኅብረታቸውን በእልህ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር እንዳያጸኑ ነበር ።

በቅርብ ጊዜ የኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በብዙ ቅጾች ከፋፍሎ ባሳተመው የሰነድ ጽሑፍ እንደሚነበበው አንደኛ ምኒልክ ወደ ዘመቻ መጠራታቸው ፤ ሁለተኛ ምኒልክ ጦሬ በየዳር አገሩ በሐረር በአሩሲ ፤ በከፋ . . . ስለ ተበታተነ ፤ እስኪሰበሰብልኝ ድረስ ጃንሆይንና ጣልያንን ላስታርቅ ማለታቸው ፤ ሦስተኛ ከዮሐንስ ለምኒልክ ቀደም ብሎ ከዶጋሊው ጦርነት በፊት በመጣው የመልስ ደብዳቤ ውስጥ "ለኛ ንጉሥ ከሌለውና ከአልጋው ከፈረንሳይ መንግሥት** የኢጣልያ መንግሥት ይሻለናል" የሚል ቃል እንደነበረበት ፤[1] አሁን ደግሞ ከዶጋሊ ጦርነት ወዲህ በኅዳር 12 ቀን 1880 ዓ ም ለምኒልክ በተላከው ደብዳቤ ውስጥ፡-

"ከኢጣሊያ ንጉሥ ጋር ያለኝ ወዳጅነት ታላቅ ነበር ። ገጸ በረከትም እንለዋወጥ ነበር ። ቆንሲላቸው ብራንኪ ሲመጣ በቤተ መንግሥቴ በክብር አስቀምጨ እስተናግደው ነበር ። በኋላ የእንግሊዝ መንግሥት መልክተኞች መጥተው ከግብጾች ጋር እናዋዋውላችሁ አሉኝና እሺ ብዬ ተዋዋልሁ . . በምን ምክንያት

* ያዬ ቴዎድሮስ አፈ ንጉሥ የነበሩት የወርቄ ልጅ ናቸው ።
** ፈረንሳይ ያለ ንጉሥ በሬፐብሊክ ስለምትተዳደር
1 Etiopia Mar Rosso, Tome 1 (1857—1885)., p. 410.

እንደሆነ ሳላውቅ ለኔም ሳይገልጹልኝ እንግሊዞች የምጥዋን
ወደብ ለኢጣልያ ሰጡ እነርሱም በምጥዋና በአካባቢው ምሽ
ጋቸውን እያጠነካከሩ የጦር መሣሪያም እኔ ሳልፈለግሁት (በኔ
ላይ ለሸፈቱት)) ያድላሉ በውላችን ውስጥ ያለውን በማፍረስ
የኔን ሰዎች እየቀረጡ ለኔ በተሰጠው መሬት ላይ ምሽጋቸውን
ይሠራሉ ስለዚህም በራስ አሉላና በነሱ መካከል የነበረው ሰላም
ሊደፈርስ ቻለ ። ነገር ግን ራስ አሉላ የፈጸመውን (የዶጋሊ ጦር
ነት) እንዲያደርግ ከኔ በኩል አላዘዝሁትም ። አሁን የሁለታችን
ጦር ለውጊያ በተሰለፈበት ሰዓት ከተቻለ ስምምነት ለማድረግ
ፈቃደኛ ነኝ ። ኢጣልያኖች ግን ማናቸውንም ስምምነት እንደ
ማይፈልጉ በምስክር ተረድቸዋለሁ ። ለቅዳሴ እንኳን የሚያስ
ፈልገው የወይን ጠጅ (ዘቢብ) ወደኛ እንዳያልፍ ከልክለዋል ።
የሆነ ሆኖ መሬቴን ከለቀቀ የኛን ሸቀጥ በነጻ የሚለቅ ከሆነ
ከኢጣሊያ መንግሥት ጋር ስምምነት ለማድረግና ለመታረቅ
ዝግጁ ነኝ ።" የሚል እንደሆነ ፣ የንጉሠ ነገሥቱም ይኸው
ደብዳቤ በንጉሥ ምኒልክ ትእዛዝ አለቃ ዮሴፍ ካነበቡለት
በኋላ ፣ ተርጉመው እንደ ሰጡት አንቶኔሊ ላለቃው ለፍራንቸ
ስኮ ክሪስፒ በጻፈው ውስጥ ያረጋግጣል ። [1]

ከዚህኛው ሰነድ በቀር በአጠገባቸው ሆኖ የሁለቱን ጠብ ለማ
ሟሟቅ የሚጣጣረው ይኸው ኮንት አንቶኔሊ ከእንጦጦ ወደ አደን
ሔዶ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለክሪስፒ በነሐሴ 1880 ዓ.ም. በምስ
ጢር ቃል ባስተላለፈው ቴሌግራም ውስጥ ፣ "ንጉሡ ዮሐንስ ጐንደ
ርን ለማዳን (ምኒልክ) እንዲዘምቱ ፣ ቀጥሎ ም ራሳቸው ኢጣሊያኖችን
ለማስወጣት ወደ ሰሐጢ እንደሚዘምቱ (ለምኒልክ) ጻፈላቸው ። በማ
ናቸውም ረገድ ምኒልክ ሁሉንም ያውቁት ዘንድ እምነትና ወዳጅነት
የተሞላ ደብዳቤ ይጽፍላቸው ነበር" ካለ በኋላ ፣ አከታትሎ ላለቆቹ
በላከው ራፖርር ውስጥ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስ በደጃች መሸሻ
ወርቄ እጅ ለንጉሥ ምኒልክ በላኩት መልእክት ውስጥ ይኸን ሁሉ
ችግር የፈጠሩባቸው እንግሊዞች መሆናቸውን እነሱም የማይ
ሆን የውል ዐይነት እያቀረቡ እንደልጅ አድርገው እንደ ተጫወቱ
ባቸው . . በነርሱ ፋንታ የመስኮቦቹን ወይም የፈረንሳዮችን አስ
ታራቂነት እንደሚቀበሉ ፣ ነገር ግን ከመስኮብ ጋር ወዳጅነት ስለ
ሌላቸው ፈረንሳዮች ደግሞ ንጉሥ የሌላቸው ስለሆኑ የማይሆኑ

1 Etiopia Mar Rosso, Tome 1, p. 410—415.



መሆናቸውን አሁንም የእንግሊዞች አስታራቂነት ካልሆነ በንጉሥ (ምኒ
ልክ) በኩል ይሞከር ፤ አለዚያ ያው ጦርነት መሆኑ ነው ከጦርነት
ግን ምንም ረብ እንደማይገኝ አውቀዋለሁ ፤ ኢጣሊያም ኢትዮጵ
ያን መግዛት አይሆንላትም ። እኔም ባሸንፍ ኢጣሊያን ባሕር ተሻ
ግሬ ለመግዛት አንድ እንኳ ታንኳ የለኝም ። የኢጣልያ ንጉሥ ክርስ
ቲያን ስለሆነ ወዳጅነቱን በወንጌል ምሎ ከገለጸልኝ እቀበለዋለሁ . .
ራስ አሉላ እኔ ሳላዘው በመዋጋቱ አጥፍቷል . . . አሁን አግዤው
በራስ ሐጐስ እጅ እንዲቆይ አድርጌዋለሁ . . . እኔ ቃሌ አንድ ሲሆን
አውሮፓውያን ቃላቸውን እንደ ፈለጋቸው ይለዋውጡታል ። ትንሽ
ቦታ ሲለቀቅላቸው ይዘው ትልቅ ከተማ ያደርጉታል ። ከዚያ ደግሞ
ትንሽ ምክንያት እየፈጠሩ ወደፊት ይገፋሉ ብለው መላካቸውንና
መሸሻ ይኸንኑ ለንጉሥ ምኒልክ ከነገሩ በኋላ ለኔ በዝርዝር አጫ
ወቱኝ በማለት ጽፏል ። [1]

ሁልጊዜ እንደምንለው ፣ በአገራችን ሰነድ ማስቀመጥ ወይም
የቃሉን መልእክት በደንብ መመዝገብ ስለ አልተለመደ ከዚህ በላይ
የተነገረውን በትክክል ተመልክተን ሐተታ እንደልብ ለማድረግ ይቸ
ግረናል ። አንቶኔሊም በኢጣልያንኛ መዝግቦት የቆየው ይህ ሰነድ ሐሰት
ነው ማለት አይቻልም ። በእርግጥም ንጉሠ ነገሥቱ እንዳሉት ቀድሞ
ወዳጅ የነበሩት የእንግሊዞቹም ክዳትና ተንኮል ፣ የኢጣሊያኖቹም
ውሸትና ማጭበርበር ፣ ለንግድ ማስፋፊያ ወደብ ብቻ የሚይዙ መስ
ለው እየተሳቡ ፣ አገር መውረራቸውና ቃላቸውንም አለመጠበቃቸው
ግልጽ ነው ። ራስ አሉላ በዶጋሊ ጦርነት ያገኙት ድል የሚያኮራ ቢሆ
ንም ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ከእንግሊዞቹ ጋር ግንኙነታቸው እየተበላሸ
የሔደው ፣ እንግሊዞቹም ወቀሳ ያበዙባቸው ከዶጋሊው ጦርነት ወዲህ
ስለሆነ ፣ አሉላን በግማሽ አግዘው የጦር አለቅነቱን ለታላቅ ወንድ
ማቸው ልጅ ለራስ ኃይለማርያም ሰጥተው ፤ ወደ መተማም የተዘመ
ተው በዚሁ ሁኔታ እንዳሉ ነበር ።

ምኒልክ ላዔ ዮሐንስ ያስታራቂነቱን ጉዳይ በሚመለከት ጽፈ
ውላቸው ከላይ የተነበቡት ደብዳቤዎች እንደ መጡላቸው ሁሉ ፣ ለኢ
ጣልያ ንጉሥ ለኡምቤርቶ ቀዳማዊ ስለዚሁ ስለዕርቅ ጉዳይ ጽፈው
በአንቶኔሊ እጅ ለሁለተኛ ጊዜ ከምኒልክ የተላከው እንደዚህ
የሚል ነው ።

" . . . ባለፈው ወር በጥቅምት በርስዎ መንግሥትና በጃንሆይ
መንግሥት መኻል የተነሣውን በከንቱ የክርስቲያን ደም

1 R. Battalia, La Guerra d'Africa, pp. 293—294.

እንዳይፈስ ጠብ ለማብረድ ለርስዎም ፣ ለጃንሆይም አስታራቂ ሽማግሌ ልሁን ብዬ ልኬባችሁ ነበር ። አሁን የጃንሆይ ምላሽ ቢመጣልኝ አገርዎን የሚያስማማ እጅግ መልካም ቃል ስለሆነ ደስ ቢለኝ አስታውቅዎታለሁ ። ይኸም ምላሽ ከዚህ የከፋ ነገር እንዳይመጣ ጠቡን የሚያበርድ እንዲሆን ተስፋ አድርጌያለሁ። አሁን ንጉሥን የምለምነው ይህ ነገር በኔና በመንግሥቴ ፊት ትልቅ ቁም ነገር ስለሆነ ፣ የላክሁብዎትን ጉዳይ ምላሹን ይላኩብኝ ብዬ ነው እኔ የምወደው ቅኑን ልቡናዬን ለርስዎና ለጃንሆይ አሳይቼ ከእግዚአብሔር ኃይል ጋር በሁለት ክርስቲያን ነገሥታት ወዳጆች የመጣውን ጦርነት ለማስቀረት ብበቃ እጅግ ደስ ይለኛል ። ትጽሕፈ በእንጦጦ ከተማ ኅዳር 22 ቀን 1880 ዓ.ም"

ይህ ደብዳቤ ፣ ለኢጣሊያኖች እንደ ደረሰ የጣሊያን ባለሥልጣኖች በጉዳዩ ሲመካከሩበትም ፣ በዚሁ ጊዜ በዤራልድ ፖርታል አማካይነት የእንግሊዝ መንግሥት ኢትዮጵያንና ጣሊያንን ለማስታረቅ የሚሞክርበት ጊዜ ስለነበረ ፣ በድጋሚ የንጉሥ ምኒልክን አስታራቂነት አልፈለጉትም ። ይህንንም ለእንግሊዝ መንግሥት መግለጽ አይፈልጉም ። በሌላው ወገን ደግሞ ፣ አንቶኔሊ አጥብቆ እንዳሳሰበው የምኒልክን አስታራቂነት በይፋ እምቢ ብለው የምኒልክን ወዳጅነት ማጣት አልፈለጉም ። በዚህ ምክንያት ምኒልክ አስታራቂነታቸው ቀርቶ ከእንግሊዝ በኩል የቀረበውን የዕርቅ ሐሳብ ዮሐንስ እንዲቀበሉ ምኒልክ እንዲመክሩዋቸውና ዕርቁ ወደ ፍጻሜ እንዲደርስ ማድረጉ ይሻላል ተብሎ ተወሰነ ። ይህንኑም ደበስበስ ባለ አነጋገር ንጉሡ ኡምቤርቶ የምስጋና ቃል ጨምሮ ደብዳቤ ለምኒልክ እንዲጽፍ ተወሰነ ።

ይህ በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ ፣ የዕርቁም ጉዳይ በእንግሊዝና በምኒልክ እንደዚሁም በጀርመን ጠቅላይ ሚኒስትር በቢስማርክ አማካይነት በሚሞከርበት ሰዓት ዮሐንስም ፣ ምኒልክም በየበኩላቸው ሁኔታውን ለፈረንሳይ ሬፑብሊክ ፕሬዚዳንት በጽሑፍ በለሞታ መልከ ማቅረቡ የተሻለ መስሎ ታይቷቸዋል ። ስለዚህ ዐፄ ዮሐንስ ከኢጣሊያና በተለይ ወዳጅ መስሎ ጠላት ሆኖ ከጐዳቸው ከእንግሊዝ በኩል የደረሰባቸውን በደል ለመግለጽ ለፈረንሳዊ መንግሥት ፕሬዚዳን ለሙሴ ዡል ግሬቪ የጻፉት ደብዳቤ እንደዚህ የሚል ነው ።

"በስመ እግዚእነ . . . . ይድረስ ኃበ ክቡር ወህፉር ለባዊ ወማዕምር ዩልዮስ ግረቢ ሊቀ ማኅበር ዘፈረንሳዊ . . . አሁንም እንግሊዞች የሚበድሉኝን በደል ግፌን ትሰሙት ብዬ ነው . . . እንግሊዞች ዘመድ መስለው እናስታርቃችሁ ብለው ላኩብኝ . . .



በበደለኛው ፈርዳችሁ አስታርቁኝ ብዬ ብልክ ተበደልሁ እንጂ የበደልሁ ይመስል ክርስቶስ በቸርነቱ የሰጠኝን አገሬን ቦጎስን ሐባብን ፣ ሰሐጢን ፣ ዊዓትን ፣ አሳውርታን ይስጧቸውና ታረቁ የሚል ቃል ላኩብኝ ። በውስጡ ለጣሊያን ረዳት ሆነው ይኸን ሁሉ የሚያደርጉኝ እንግሊዞች ናቸው ። ምነው ስሞት የክርስቲያን ደም በከንቱ ሲፈስ ዝም ብላችሁ ታዩኛላችሁ . . . ይህንንም የጻፍሁላችሁ በደሌን ትሰሙልኝ ብዬ ነው እንጂ ቀብቶ ያነገሠኝ አምላክ ለነዚህ በግፍ ለተነሱብኝ ሰዎች አቅም ይነሣኛል ብዬ አይደለም ። ነገር ግን ይኸን የጻፍሁላችሁን ደብዳቤ ለወዳጆቻችሁ ሁሉ ለነገሥታቱ እየጻፋችሁ አሳዩልኝ ። ተጽሕፈ በሐሸንጌ ከተማ አመ 20 ወ 9 ለኅዳር በ1880 ዓ. ም. ።" ከዚሁ አከታትለው ንጉሥ ምኒልክ በበኩላቸው ለዚሁ ለዡል ግሬቪ እንደዚህ ሲሉ ጽፈዋል ።

"የተላከ ከንጉሥ ምኒልክ . . . ይድረስ ኃበ ክቡር ወልዑል ዩልዮስ ግረቢ ሊቀ ማኅበር ዘፈረንሳዊ ቤተ መንግሥት . . . በኢጣልያ ሹማምንትና በጃንሆይ ሹማምንት መካከል የተነሳውን ጠብ ለማብረድና ለማስታረቅ ወደ ኢጣልያ ቤተ መንግሥት ደብዳቤ ልኬያለሁ ። ደግሞም እናንተ የፈረንሳዊ ቤተ መንግሥት ከኤውሮፓ ነገሥታት ከወንድሞቻችሁ መክራችሁ በደለኛውን መርምራችሁ አናስታርቅምን ። ምንም አገራችን ቢራራቅ ሁላችን ያንድ የክርስቶስ ልጆች ነን በከንቱ የክርስቲያን ደም ለምን ይፈሳል ። እኛስ ወንድሞቻችሁ አይደለንምን ። አሁንም ወደ ፈረንሳዊ ቤተ መንግሥት ጃንሆይ ደብዳቤ ልከዋልና ምላሹ ቶሎ እንዲመጣልን ያለ ትዕግሥት እንጠብቃለን ። ጤና ይስጥዎ በታኅሣሥ በ12 ቀን 1880 ዓ. ም በእንጦጦ ከተማ ተጻፈ ።"[1]

በዚህ ደብዳቤ ላይ ፣ "ወደ ፈረንሳዊ ቤተ መንግሥት ጃንሆይ ደብዳቤ ልከዋል" የሚል ስለ አለበት ፡ በጉዳዩ ካፄ ዮሐንስ ጋር የተስማሙበት ይመስላል።ዐፄ ዮሐንስ ፣ "ይኸን የጻፍሁላችሁ በደሌን ትሰሙልኝ ብዬ ነው። ለወዳጆቻችሁ ሁሉ ለነገሥታቱ እየጻፋችሁ አሳዩልኝ" ብለው ሲጽፉ ፣ ንጉሥ ምኒልክም "ከአውሮፓ ነገሥታት ከወንድሞቻችሁ መክራችሁ በደለኛውን መርምራችሁ አናስታርቅምን" ሲሉ ፣ ነገሩን ሁሉ ሁለቱም የሚመለከቱት ባገራቸው በኢትዮጵያ ልማድና ባህል ነው ። ሁለቱም

1 L'Italia in Africa. . . Tome VI - Documenti, Paris, (1887—1888)- G. Giglio, pp. 275—291.

የፈረንጅ አገር መሪዎች ሁሉ ክርስቲያን ስለሆኑ ፣ በስምምነትና በወንድማማችነት የሚኖሩ ይመስላቸዋል ። የእንግሊዝና የፈረንሳዊን ፉክክርና ባላንጣነት ፣ የጀርመንንና የፈረንሳዊን የቆየ ጠብ ፣ የጀርመንና የእንግሊዝን ከኢጣሊያ ጋር የመመሳጠር ውዝግብ በትክክል የሚያውቁ አይመስልም ። ሰምተውትም ቢሆን እንኳ ደህና አድርገው አላጤኑትም ማለት ነው ።


የሆነ ሆኖ ፣ ንጉሥ ምኒልክ አሳባቸውንም ፣ ኃይላቸውንም ከንጉሠ ነገሥቱ ካፄ ዮሐንስ ጋር አጣምረው የመጣውን ጠላት በመመከት ፈንታ እንደ ባዕድ ወይም እንደ ጐረቤት መሪ ላስታርቅ ማለታቸው በዛሬው ዘመን አስተሳሰባችን ግራ የሚገባ ነው ። ነገር ግን ፣ ካፄ ቴዎድሮስ ሞት ወዲህ ስለነበረው ሁኔታችን ባለፈው ያሠፈርነው የጽሑፍና የሰነድ መስተዋት ፣ ባፄ ተክለ ጊርጊስ ጊዜ የሦስት ሰዎች (ተክለ ጊዮርጊስ ፣ ዮሐንስ ፣ ምኒልክ) መንግሥት እንደነበረ ሁሉ ፣ አሁንም ምንም እንኳን ዮሐንስና ምኒልክ የበላይና የበታች ሆነው ለመተዳደር ቢስማሙም ፣ በዚህ ጊዜ የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት ለሁለት የተከፈለ መንግሥት መሆኑን በትክክል ያሳየናል ። ሁለቱ ለየብቻ በቀጥታ የሚያስተዳድሯቸው አውራጃዎች ሲኖሩአቸው የሁለቱ የጦር ሠራዊት የተለያዩ ነበሩ ። ዛሬ በ14 ከተከፈሉት ክፍለ ሀገራት ውስጥ ሸዋ ወሎ ፣ ሐረርጌ ፣ አሩሲ ፣ ሲዳሞ ፣ ባሌ ፣ ወለጋ ፣ ኢሉባቦር ስምንቱ ይነስ ይብዛ በንጉሥ ምኒልክ የቀጥታ ቁጥጥር ውስጥ ነበሩ ። ወሎ አንዳንድ ጊዜ ከምኒልክ ወደራስ አርአያ ፣ ከራስ አርአያ ወደ ባላባቱ ወደ ራስ ሚካኤል ቢዘዋወርም ፣ የቀሩት ሰባቱ ክ/ሀገሮች እንኳን ዐፄ ዮሐንስ በቀጥታ ከሚቆጣጠሩዋቸው ከምድረ ባሕሪ ፣ ከትግራይ ፣ ከቤጌምድር በስፋትም በሕዝብ ብዛትም ይበልጣሉ ። ስለዚህም በምጥዋና በአካባቢው መወረር ጉዳይ ከሁለቱ አቅዋም ያንደኛው ሞቅ ያለ ሲሆን የሁለተኛው ቀዝቀዝ ያለ ነበር ።

በዚህ ምክንያት ፣ የዶጋሊ ጦርነት በተካሔደበት ዓመት የንጉሥ ምኒልክ አሳብ ያተኮረው በሰሙና በስፋፊው የሐረርጌ ፣ የባሌ ፣ የአሩሲ ፣ የወላይታ ዘመቻ ጉዳይ ስለነበረ ፣ ከርሳቸው ከሺ ኪሎ ሜትር በላይ ለሚርቀው ለበረሃማው ለሰሐጢ ፣ ለዶጋሊ ፣ ለዊዓና ለዙላ መያዝ እንዳፄ ዮሐንስና እንደ ራስ አሉላ ማሰባቸው ባይቀርም በነገሩ የተጨነቁበት አይመስልም ። የዶጋሊንም ጦርነት ከግለሰቦችና ካፄ ዮሐንስም የሰሙት ከሐረርጌ ጦርነት መልስና አሩሲዎች ደግሞ ለራስ ዳርጌ አንገዛም ብለው ባወኩበት ሰዓት ስለነበር ፣ ምኒልክ የሰሜኑን ጉዳይ የሚመለከቱት በሁለተኛ ደረጃ ነው ማለት ይቻላል ።

የሆነ ሆኖ ፣ ዐፄ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ ለመዠመሪያ ጊዜ ተገናኝተው በውል ከተስማሙበት ከ1870 ዓመተ ምሕረት ዠምሮ



እስከ 1880 ዓ. ም. ድረስ ልጅ ከልጅ አጋብተው ፣ በተቻለ መጠን በሰላም የበላይና የበታች ሆነው የዐሥር ዓመት ጊዜያቸውን ካሳለፉ በኋላ ፣ አሁንም ከዶጋሊ ጦርነት ወዲህ ዐፄ ዮሐንስ ወደ ሰሐጢ እስከ ዘመቱበት እስከ ግንቦት ወር ድረስ ምንም ሁለቱን የሚያጣላ ነገር ሳይገጥም ወይም ቢገጥምም ሁለቱም ተቻችለው ኖሩ ። ንጉሠ ነገሥቱ ከሰሐጢ የጦር ግንባር ወደ ዐድዋ ከተመለሱ በኋላ ግን ፣ ባንድ ወገን በሁለቱ ነገሥታት መካከል በጋብቻ ቀለበት ወዳጅነትን ፈጥረው የነበሩት ራስ አርአያ ስለሞቱና በተለይ ደግሞ በዚያን ጊዜ ያፄ ዮሐንስ መኳንንትም ከሰሐጢው መልስ ፣ “ኢጣሊያኖችን ተላልከው ያመጡብን ንጉሥ ምኒልክ ናቸው” የሚለውን ወሬ እያጋነኑ ስላወሩትና ዮሐንስም ይኸንኑ ወደማመን ስለቀረቡ ፣ ከዚህ ጊዜ ዠምሮ በሁለቱ ነገሥታት መካከል የነበረው የወዳጅነትና የስምምነት መንፈስ ወደ ጠብና ወደ መወቃቀስ ሲለወጥ እናያለን ። ከዚያ ወዲህ ግን ፣ በሰሐጢ ግንባር ጣልያኖች ፣ በሰሜናዊ ምዕራብ በኩል የደርቡሾቹ ወረራ ስለ አፋጠጠ ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ወደ መተማ ዘምተው ተሸንፈው መመለሳቸው ስለ ተሰማ ፣ ዮሐንስ በምኒልክ ላይ የነበራቸውን ቂም በልባቸው እንደያዙ ምኒልክ ከነሠራዊታቸው ወደ ጐንደር ብቅ ብለው እንዲከላከሉ የትእዛዝ ጥሪ አደረጉላቸው ።



ዐፄ ዮሐንስ እንግሊዞችን እየነቀፉ ለፈረንሣይ ፕሬዚዳንት ለዡል ግሬቪ የጻፉት ደብዳቤ

(ሚኒስቴር ዳፌር ኤትራንዠር ሜምዋ ኤ ዶክዮሞ አፍሪክ ፣ ፓሪ)

ደሓማይ፡ ምኒልክ ንጉሠ፡ ሸዋ ወከፋ ወሐረር ወኵሉ አጥደማ
ሄ፡ ለብሔረ፡ ጋላ። ይድረስ ወዳጄ፡ ከበረ፡ ወዲ፡ ዘረረ፡ ዱኑ፡ ወዲጂቱ
ኝ፡ ንጉሥ፡ ኡምበርቶ፡ በለም፡ ወዘመርዩ፡ ንጉሠ፡ ኢጣሊያ፡ ለሰ
ም፡ ለርስዎ፡ ይሁን።

ንጉሥ፡ ሆይ፡

ባለፈው፡ ወር፡ በጥቅምት በርስዎ፡ መንግሥት፡ና፡ በጃንሆይ፡ መንግሥት፡ መካከል፡ የተነሳውን በክንቱ፡ የክርስቲያን ደም እንዳይፈስ፡ ጠብ፡ ለማብረድ፡ ለርስዎም፡ ለጃንሆይም፡ እስታራቂ፡ ሽማግሌ፡ ልሁን፡ ብዬ፡ ልኬባቸው ነበር። አሁን፡ የጃንሆይ፡ ምላሽ፡ ቢመጣልኝ። እንግዲህ፡ የሚያስማማ፡ እቃ፡ ጠሐነ ም፡ ቃል፡ ስለሆነ፡ ዲስ፡ ቢስኝ፡ እስታውቀዎታለሁ። ሀዘም ምላሽ፡ ከዚህ፡ የከፋ፡ ነገር፡ እንዳይመጣ፡ ጠብ፡ የሚያበርዱ፡ እንዲሆኑ፡ ተስፋ፡ አድርጌ አለሁ። እውነቱ፡ ንጉሥን፡ እምለምነውም፡ ይህ፡ ነገር፡ በኔና፡ በመንግሥቴ፡ ላይ፡ ትልቅ፡ ቂም፡ ነገር፡ ስለሆነ፡ የስክውብምን፡ ንዲይ፡ ምላሹን፡ ይላኩልኝ፡ ብዬ፡ ነው። እኔ፡ ከእግዚአብሔር፡ ኃይል፡ ጋራ በሁለቱ፡ ክርስቲያን፡ ነገሥታት፡ ወዳጆቼ፡ የመጣውን፡ መርነት፡ ለማስቀረት፡ ብርቱ፡ እጅጋ ይሰ፡ ይስኛል። ተጽፈ፡ በእንጦጦ፡ ከተማ፡ ከመ፡ ፯ ወደ ለኅ ዲር፡ በ፲ወ፰ ፻፹ ዓመተ፡ ምሕረት።

## ዐፄ ምኒልክ ፣ ዐፄ ዮሐንስና የኢጣሊያን መንግሥት ለማስታረቅ ያላቸውን አቋም ለኢጣሊያኑ ንጉሥ ለኡምቤርቶ ያስታወቁበት ደብዳቤ

(ኦርኪቪዮ ስቶሪኮ ዴ ስፒሬሶ ሚኒስቴሮ ዴልአፍሪካ ኢታሊዮና ፣ ሮማ)

# ምዕራፍ ዐርባ

## የደርቡሾች አጥቂነት—የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በደርቡሾች መሸነፍ ፣ የጐንደር ዘረፋና ቃጠሎ

በሰሜን ምሥራቅ በኩል ፣ ባፄ ዮሐንስና በኢጣልያኖች መካከል የነበረው የጦርነት ሁኔታ በዚህ ዐይነት እንዳለ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በኩል የደርቡሾች አጥቂነት እየባሰ ከመሔድ ላይ ይገኝ ነበር ። ዋናው የንቅናቄው መሥራች ማህዲ ሙሀመድ ከሞተ ወዲህ ተከታዩ ከሊፋ አብዱላሂ የማህዲን የግዛትና የእስልምናን ሃይማኖት የማስፋፋት ዓላማ በመከተል ፣ ግብጾችንና ቱርኮችን አስጨንቆ ካስወጣ ወዲህ የነበረው የጦርነት መፋጠጥ ከኢትዮጵያ ጋር ሆነ ። የመፋጠጡንም ሁኔታ ካባባሱት ምክንያቶች ዋነኞቹ ከዚህ ባፊት ደጋግመን እንዳወሳነው ፣ በሔዊት ውል መሠረት እነ ራስ አሉላ የቱርኮቹንና የግብጾቹን ሕይወት ለማትረፍ ሲሉ ከደርቡሾቹ ጋር የመዋጋታቸው ሰበብ ነው ።

በ1878-79 ዓ.ም ላይ ብዙ ጊዜ ዐፄ ዮሐንስ ከሞቁ ፣ ከደመቁ አብያተ መንግሥቶቻቸው ከመቀሌም ፣ ከዐድዋም እየመጡ ደብረ ታቦር በመቀመጥ በመተማና በጋላባት የደርቡሾቹን ንቅናቄ በሩቁ ይቆጣጠሩ ነበር ። እንደዚሁም የዋጅራትን ፣ የራያና የአዘቦዎችን ሸፍትነት ለመደምሰስ በአሸንጌ በሚገኙበት ጊዜ በተለይ የደርቡሾቹ ወረራ በጋላባት በሚገፋበት ወቅት ከአሸንጌ እየተመለሱ ብዙ ጊዜያቸውን በደብረ ታቦር ያሳልፉ ነበር ። በርሳቸውም ሥር በዚያ አካባቢ የነበሩትን አውራጃዎች ቤጌምድርን ልጃቸው ራስ አርአያ ፣ ጸለምትንና ሽሬን ራስ ሐጎስ ፣ ደምቢያን ሹም ደህና ፋንታ ያስተዳድሩ ነበር ። የቀረውም በደቡብ በኩል በዳሞት ፣ በአገው ምድርና በጭልጋ የነበረው ግዛት የጐጃሙ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የግዛት ክፍል ነበር።

በደርቡሾች በኩል ደግሞ ፣ በግብጾች ጊዜ ሳሊን ኢድሪስ የሚባለው የጋላባትን ወረዳ ሲያስተዳድር ቆይቶ ነበር ። የግብጾች ሥልጣን ከዚያ አካባቢ ሲነቀል መሐመድ ዋድ አርባብ የሚባለው የሳሊን ኢድሪስ ዘመድ ከደርቡሾች ይኸውም ማለት ከከሊፋ አብዱላሂ ተሹሞ ያስተዳድር ጀመር ።

በመተማ የደርቡሾቹ መግፋት በተሰማ ጊዜ ፣ የወሎ እስላሞች ሽፍትነት እንደገና ስለ ተቀሰቀሰ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከደብረ ታቦር ተንቃንቀው ወደዚያ ሲያመሩ በጋላባትና በመተማ የነበሩት ደርቡ ሾች ምቹ ጊዜ ስለ አጋጠማቸው ፣ ከወሰን ዐልፈው ደምቢያንና ጭል ጋን ወረሩ ። የደምቢያውም አስተዳዳሪ ሹም ደህና ፋንታ ከደርቡሾቹ ጋር በመዋጋት ሕይወታቸው ዐለፈ ። * ዐፄ ቴዎድሮስ የተማሩ በት ስመ ጥሩው ገዳም ማኅበረ ሥላሴ በዚህ ጊዜ ተቃጠለ ። ብዙም ሰው አለቀ ።

በዚህ ጊዜ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ወሎ ውስጥ እንደነበሩ የጐጃሙን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ጦራቸውን ይዘው ሔደው ከደርቡሾች ጋር እንዲዋጉ አዘዙዋቸው ። በሌላውም በኩል ራስ አርአያ (ልጃቸው) አምባ ጫራ ሆነው እንዲጠባበቁ ቀጥሎም ራስ ሐጎስ ፣ ዋግሹም ገብሩ፣ ደጃች በረሄና ደጃች ሥዩም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን እንዲረዱ አድ ርገው እርሳቸው ከወሎ ወደ መቀሌ ሔዱ ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በልዩ ልዩ ምክንያት የነራስ ሐጎስ እርዳታ ሳይጨመርላቸው እስከ 100 ሺ የሚደርሰውን የገዛ ** ጦራቸውን ይዘው በአገው ምድር አድርገው ወደ ደምቢያ ተጓዙ ። ከዚያም አልፈው በጥር ወር በታበረከ አላሀ በኤል ኑር ዋድ ትጋራ የሚመሩትን አንሳሮችን አሸነፉ ። *** ከዚያም ዐልፈው መተማ ደርሰው በመሐመድ ዋድ አራብ የሚመ ሩትን ደርቡሾች አሸንፈው በደስታ ወደኋላቸው መለስ ብለው በደ ብረ ሲና ሠፈሩ ።

የዚህን ሁሉ ወሬ ዋናው የደርቡሾች ጠቅላይ መሪ ከሊፋ አብ ዱላሂ ሲሰማ ፣ በበኩሉ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን የሚወጋ ጦር አዘ ጋጅቶ የበላይ መሪ ሐምዳን አቡ አንጋ የሚባለውን ሾመ ። በርሱም ውስጥ አህመድ ዐሊ አብዱላሂ ኢብራሂም ፣ አልዜኪ ቱማል ፣ አራቢ ዳፋ አላህ የሚባሉት የጦር አለቆች የየክፍል ጦራቸውን ይዘው ይገኙ ነበር ። እነዚህ ሁሉ በደንብ ከተዘጋጁ በኋላ ፣ በአቡ አንጋ እየተመሩ ከጋላባት ወደ ደምቢያ መጥተው ሣር ወሃ ከሚባለው ቀበሌ ሠፈሩ። በዚህም ጊዜ ጥር 10 ቀን 1880 ዓ.ም በንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ

---

* ሹም ደህና ፈንታ ባፄ ዮሐንስ ትእዛዝ በሰናሂት በከሰላ ከደርቡሾቹ ተዋግተው የተከበቡትን ቱርኮችና ግብጾች ያዳኑ መሆናቸው ይታወሳል ።

** ከነዚህ ውስጥ 2000ባለ ጠበንጃ መሆኑን ስላጢንና ውንጌት ያረጋግጣሉ ።

*** አንሳር የደርቡሽ አንድ የነገድ ክፍል ነው ። ደብረ ሲና የሚገኘው ከጐንደር ሰሜን ምዕራብ ሆኖ ርቀቱ ከጐንደር 38 ማይልስ ግድም ነው ።



ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ገሥግሠው መጥተው ደርቡሾቹን ሲገ ጥሙ ፣ እነዚያ ቀደም ብለው ምቹ ሥፍራ ይዘው ይጠባበቁ ነበርና የመ ዠመሪያውን ግንባር ቀደም የኢትዮጵያ ጦር በቀላሉ አሸንፈው ደጀ ኑንም በድንጉላ ፈረስ እያባረሩ ይወጉ ዠመር ። ከዚያ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጦር ፈራርሶ የማረኩትን ማርከው ጐንደርን ካጠፉ በኋላ ፣ ሐምዳን አቡ አንጋ ወደ አገሩ ተመልሶ እንደ ደምቡ ከማረከው ውስጥ ከአምስት አንዱን እጅ ለራሱ አስቀርቶ የቀረውን ምርኮ ከነሰዉ ለከሊፋ አብዱላሂ አስረከበ ። የምርኮኛው ቁጥር በደጃች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ ጽሑፍ ገጽ (446) 3445 ሲደርስ በማርከስ ሐሮልድ ገጽ 101 እስከ 8ሺ ተባዝቷል ። ከ44 የጐንደር አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ዐርባዎቹ መቃጠላቸው በየመጽሐፉ ተጠቅሷል ።

ስለዚህ ጦርነት ወደ ብዙ ሐተታ ሳይገቡ አለቃ ተክለ ሥላሴ የሚባሉት በራሳቸው በዘመኑ የጐጃምኛ አነጋገር ከሌሎቹ ያገራችን ጸሐፊዎች የበለጠ ከዚህ እንደሚከተለው ዝርዝር ይሰጣሉ ።

> “የጐጃም ሰው ያን ጊዜ ወደ ጦርነቱ ሲሔድ አዘን ትቶ ጠግቦ እንደ እንባቦው ምካ (የትምክህት ቃል) እየተናገረ ሔደ ።
>
> “አይታሰስም ምጣድ በግምጃ
> ዘንድሮ ደርቡሽ መትረፉን እንጃ”
>
> እያለ ያቅራራ ነበር ። “ያንን ሻግያ (ሻንቅላ) እንደ ፊተኛው እንደ ዱባ እየወጋን ጌጥ (ጊጤ) መጫወቻ እናደርገዋለን” እያለ ይዘባበት ነበር ። ይሸሻል እንጂ አይገጥመንም ተብሎ ሰላይ በፊታውራሪ ተሰፋዬ እግር አምስት መቶ ፈረሰኛ ወረደ. . . ወዲያው ጦር ሳይከት ማልዶ ድንገት ደረሰ ። በዚህ ጊዜ ጀግናው ሁሉ ፈረ ሱን አቡቀዳዲ እያለበሰ ድንፋታና ፉከራ አደረገ. . . ”

በማለት የጦርነቱን አጀማመር ፣ የተዋጊውን በራስ የመተማመንና የመመካት መንፈስ ጸሐፊው ከገለጹልን በኋላ ፣ ስለ ጦርነቱ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን አሥፍረዋል ።

> “በሊቀ መኳስ የተመኙ በንጉሥ አሳሳቹ እግር ጀግናው ሁሉ ወረደ ። መጀመሪያ ነጋሪት ሲያገሣ ፣ ቀንደ መለከት ሲያከላላ መድፍ ሲተኰስ ፣ ስናድር (ጠመንጃ) ሲከተል፣ ደርቡሽ ሞኙ መስሎ አምስት ቁርጥ ሆኖ ተሰልፎ የአረር (ጥይት) በረዶ የአንድ ጊዜ ወላፈን ዝም ብሎ ተቀበለ ። ከዚህ በኋላ እረባዳው መሬት ላይ ሆኖ አሻቅቦ አንድ ጊዜ ቢተኵስ ፣ ጐጃሜን እንደ ምርት አመረተው

"የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሠራዊትም እኩሉ ጀግና አይገጥመ ንም እያለ ገና በጕዳና ያላግጥ ነበረ ። በዚህ ጊዜ በኋላ የቀረው ሠራዊት ተሰልፎ አንድ ጥይት ሳይተኩስ መጀመሪያ የወረደው ጦር ተፈታና ሽሽት ሆነ ። ደርቡሽም በድንጉላው (በጠገበ ፈረስ) እየተጋባ ሰይፉን መልጦ (መዞ) ተለቀቀው ፣ (አባረረው)መሔጃ መድረሻ አሳጣው. . . ያን ጊዜ ንጉሡና ጳጳሱ ከገዳሙ ሆነው ጳጳሱ ሽሽተኛውን (የሚሸሸውን) እየገዘቱ ንጉሡ እየተኮሱ የአረር በረዶ ሲወርድ ፣ ፈሪ ሜዳ ሲጠበው ምድርና ሰማይ የዞረ ሲመስል ፣ መምህር ካሣ የንጉሡን ጥላ ገትሮ እንደያዘ አረር በእጁ ላይ አረፈና በታተነና ጨረሰው ። ከዚህ በኋላ በለው አባ ዳንዴ ንጉሡንና ጳጳሱን ተቆጣ ። ሠራዊታችን ሲሸሽ እኛ ምን እናያለን አለ ። ያን ጊዜ ንጉሡ ጉሉ በሚባል ፈረስ ጳጳሱ አቡነ ሉቃስ በስጋጃ (ሲጋር) በቅሎ ወጥተው አመለጡ ። ራስ በዛብ ህና ራስ ደረሶ ፣ በለው አባዳንዴ ፣ ብሩ አባጉሉ ፣ ይመር ፋንታ ልጅ ቢረሳው እየዞሩ ከደርቡሽ ጋር እየተዋጉ ንጉሡንና ጳጳሱን በዳንገር በር * ይዘው ወጡ ። . . . ሕዝቡ በፈረስም በበቅሎም ፣ በእግርም ሲሸሽ እግረኛውን ቃታ እያስጨነቀው ሳን ባው በጉሮሮው እየተወተፈ በየመንገዱ እየወደቀ ደርቡሽ ተሜ ወተበት ። "

እያሉ የጦርነቱን ሁኔታ በዚህ ዐይነት ከዘረዘሩ በኋላ ፣ በዚህ ቀን ጦርነት ፣ በለው ተክለ ሃይማኖት የሚባሉት የንጉሡ ልጅ ፣ ዳሰው በሚባል ፈረሳቸው ሆነው ከደርቡሽ መካከል ገብተው ብዙ ገድለው እምስት የሰናድር ጠበንጃ ማርከው ወደ ሠፈር ሲመለሱ ፣ ንጉሡም ጳጳሱም ሁሉም ሸሽተው ስላገኙዋቸው ፣ "እኔን እንመለስ ሳይሉ ለሞት ዳርገው ራስ በዛብህን ይዘው ጥለውኝ ሔዱ" በማለት ብዙ ቀን ከአባታቸው (ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት) ጋር ተኳርፈው መሰን በታቸውን ፣ በተደረገው ጦርነት ደጃች ካሣ ፣ ደጃች ይማም ካሣ ፣ ፊታውራሪ እሸቴ ፣ ፊታውራሪ ንጉሤ ፣ ፊታውራሪ ረታ ፣ ፊታውራሪ ይልማ ፣ ጸሐፌ ትእዛዝ አለቃ እሸቴ ፣ ቀኛዝማች ለማ ፣ ባላምባራስ ጋርጠው በጀግንነት እየተዋጉ ከጦሩ ሜዳ ወድቀው መሞታቸውን ተክለሥላሴ አብራርተው ገልጸውታል ። [1] ከሱዳኖቹ ወገን 519 ሲሞቱ ፣ 563 መቁሰላቸውን አቡ አንጋ ለአሚር አብዱላሂ በጻፈው ራፖር አመልክቷል ።

* ዳንገል በር በጣና ባሕር በስተደቡብ በደብረ ማይ ምሥራቅ ይገኛል ።
1 የእጅ ጽሑፍ ገጽ 131-132



ጸሐፊው ከዚሁ እያይዘው ጽሑፋቸውን በማራዘም ፣ ድል አድ ራጊው አቡ አንጋ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መኳንንት ውስጥ የ12 ሰው ጭንቅላት ቆርጦ ለሱዳኑ መሪ ለአሚር አብዱላሂ ሰለባ ላከ ። የቀረውን ምርኮ እየነዳ ጉንደር ገብቶ ቤተ ክርስቲያን ማቃጠሉን፣ ብዙ ክርስቲያን ማረዱን ፣ የተረፈውን ምርኮኛ እየነዳ ወስዶ በምርኮ ካገኘው ከ30,000 ብር ጋር ወስዶ እምዱርማን ለነበረው አለቃው ለአብዱላሂ ማስረከቡን ፣ ከሊፋ አብዱላሂም አቡ አንጋን አመስ ግኖ ከተማረኩት ሴት ወይዛዝርት ውስጥ ቆንጆዎቹን ለራሱ በዕቁባ ትነት አስቀርቶ ፣ የቀሩትን ጉንጫቸውን እያስተለተለ ባሪያ ሆነው መሸ ጣቸውን ከተማረኩት ሴት ወይዛዝርት ውስጥ የራሳቸው የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ልጅ ምንትዋብ አዳል የምትባለው ባለቤቷ ደጃች ጀምበሬ ሲሞቱ ፣ እሷ ተማርካ ሳለ በእስላም እጅ አልበላም ብላ (አል ሰልምም ብላ) በችጋር እንደ ሞተችና ከመሞቷም በፊት ፣

"ጕጃም የምትሔዱ እንደኔ እማትቀሩ
እርኩስ አርማ ሞተች ብላችሁ ንገሩ" [1]

ብላ እንደ ገጠመች ዘርዝረዋል ።

ሌሎች የገጠሙት ደግሞ ፣

"ማር ወኻ ከሜዳው የተዘራ አዝመራ
አሜጃ ደርቡሽ ነው ሰብሳቢው አሞራ

አትከለክልዋይ (ተክለ ሃይማኖት) ይዘህ አለንጋህን
አሞራ (ደርቡሽ) ሲበላው የገዛ ገላህን (ምንትዋብን)" የሚል ነው ።

የሆነ ሆኖ ሐቁን ስንመለከተው ፣ ባለፈው ጊዜ በኢትዮጵያ በተ ለይ በወሎና በአካባቢው የነበሩት እስላሞች በ1870-75 ዓ.ም. ላይ በግዱታ ክርስትና እንዲነሡ ተብሎ በታወጀው መሠረት የፈራው ክርስትና በመነሣት ሕይወቱን ሲያተርፍ እምቢ ባለው የእስላም ተወላጅ ላይ እስራት ፣ መቆረጥ ፣ ግድያ ፣ ስደት እንደ ደረሰበት አሁን ደግሞ የዚያ በቀል በደርቡሾች መነሣት ፣ በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መሸነፍ ፣ በክ ርስቲያኖች ላይ የሞትና የስደት መከራ ደርሶባቸዋል ማለት ነው ።

ስለ ጦርነቱ አዠማመርና አፈጻጸም ግን ፣ ተክለ ሥላሴ እንዳሉት ጦሩ ከመሸነፍ የደረሰው ፣ እናሸንፋለን ብለው ጕጃሞቹ ትምክህት

1 በሌላ ጽሑፍ "የምትሔዱ ሰዎች የምትቸገሩ ፣ ድመት በልታ ሞተች ብላችሁ ንገሩ ።"ይላል ። ተ.ጸ.መ.፣ የኢት. ታሪክ ካ፤ ቴዎድሮስ እስከ ተ.ኃ.ሥ ፣ ገጽ 81

በማብዛታቸው ብቻ ሊሆን አይችልም ። ማንም ጦር ወደ ዘመቻ ሲሔድ አሸንፋለሁ ብሎ ማመንና መፎከርም መሸለልም ባህል ነው ። ነገር ግን በተለይ የአየር ኃይል በሌለበት ዘመን ፣ ብዙ ጊዜ ጠላቱን ላጥቃ ልበቀል ብሎ ወደፊት በሚገሠግሥ ጦር ላይ ምሽግ መሽጎ ወይም በተፈጥሮ እንደ ዲብ ወይም እንደ ቋጥኝ ያለውን ምቹ ሥፍራ በቅድሚያ ይዞ በልቡ ተኝቶ ጣቱን እጠበንጃው ምላጭ ላይ አድርጎ በተከላካይነት የሚዋጋ ጦር ብዙ ጊዜ አሸናፊ ሆኖ ይገኛል ። ዐፄ ዮሐንስ በመተማ የተሸነፉት ፣ ዐፄ ምኒልክም ኢጣልያኖችን በዐድዋ ያሸነፉት በዚህ ዕቅድ ነው ። ጦሩን ፈልጎ ከሚሔደው ብዙ ጊዜ የሚቀበለው አሸንፎ ይገኛል።

በተረፈ ስለዚሁ ጦርነት የነጋድራስ አፈወርቅ አጻጻፍ ከአለቃ ተክለ ሥላሴ አጻጻፍ ለየትና አጠር ብሎ እንደዚህ ይላል ።

> "... የዚህን ጊዜ ዐፄ ዮሐንስ ሰሐጢ ላይ ከኢጣልያ ጋር ተሰላልፈው ነበረ * ደርቡሽ ዐፄ ዮሐንስ መያዛቸውን (መጠመዳቸውን) አይቶ ወደ ጐንደር ገፋ አጤ ዮሐንስ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ውረድና ከደርቡሽ ተዋጋ ብለው ላኩ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ግን የደርቡሽን ብርታት አይተው ዛሬ የመጣው ደርቡሽ ለኔ የሚቻል አይደለም ብለው ላኩ ። እንዲህ ማለትህ ፈርተህ ነው ውረድና ተዋጋ ብለው ላኩባቸው ። ምንም ነገሩን (መሸነፋቸውን) ቢያውቁት በኔ ምንም ፍርሐት የለብኝ እስትሞት እዋጋለሁ ብለው ተዋጉ ድል ሆኑ ሰውም አለቀ እርሳቸውም ሸሽተው አመለጡ ።"

ከዚህም አያይዘው የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ድል ሆነው መሸሻቸውን ዐፄ ዮሐንስ በሰሙ ጊዜ ፣ "እንኳን እግዚአብሔር ከሞት አዳነህ" በማለት ፋንታ ፣ "ፈክረህ ወርደህ ተሸንፈህ ሰውን አስፈጀህ" ብለው እንደ ተቆጧቸውና በዚሁም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መቀየማቸውን ፣ ከዚህ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ እባክህ ደርቡሽ መጥቶ ቤተ ክርስቲያን ሲያቃጥል ታቦት ሲያረክስ ዝም አትበል ፤ ለኔ አልልም ስለ ሃይማኖትህ ስላገርህ ብለህ ተዋጋ ብለው ለምኒልክ መላካቸውን ምኒልክ ከወሎ ገሥግሠው ወደ ጐንደር በሔዱ ጊዜ ደርቡሽ ጐንደርን አቃጥሎ ወዳገሩ መመለሱን ያረጋግጣሉ ። [1]


---

* ገና እጉዞ ላይ ነበሩ እንጂ በዚህ ጊዜ ሰሐጢ አልደረሱም ።

1 አፈወርቅ ገብረ የሱስ ፤ ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ፣ ገጽ 48-49







ኢጣሊያኖች ለማስፈራሪያነት ባየር የተሞላ ኳስ ወደ ሰማይ ሲለቁ

# ምዕራፍ ዐርባ አንድ

## በዮሐንስና በምኒልክ መካከል የተዳፈነው ጠብ—የንጉሥ ምኒልክ ጉዞ ወደ ወሎና ወደ ቤጌምድር—ታላቅ ሰልፍ በአዘዞ

የእንግሊዝ መንግሥት ፣ ለራሱ ጥቅም ሲል ለወገኑ ለኢጣሊያ መንግሥት አድላዊ በመሆኑ በእንግሊዝ መንግሥት መላክተኛ በሰር ዤራልድ ፖርታል አማካይነት የተጀመረው የግልግል ሁኔታ ሊሳካ አልቻለም ። በዚሁ ጊዜ በተደራቢ የምኒልክን አስታራቂነት ዐፄ ዮሐንስም ፣ የኢጣልያ መንግሥትም በይሉኝታ ምክንያት ከመዠመሪያው ላይ ባይገፉትም ሁለቱም ዋጋ እንዳልሰጡት ይታወቃል ። ለፈረንሳይ መንግሥት ፕሬዚዳን ለዡል ግሬቪ ዮሐንስም ምኒልክም የላኩት የስሞታ ደብዳቤ ፈረንሳይና እንግሊዝ ባላቸው የቅኝ አገር የአያያዝ ቅራኔ ምንም ዋጋ ሊያስገኝ አልቻለም ። የጀርመኑ ጠቅላይ ሚኒስትር እቶን ቢስማርክ የእንግሊዝን አስታራቂነት ለመገፋፋት በክሪስፒ በኩል ያደረገው ጥረት ዋጋ አላገኘም ።

ስለዚህ ፣ ከዚያ ወዲህ ያለው ዝግጅት ለጦርነት ብቻ ሆነ ። የጦሩም ግምባር በሰሜን ምዕራብ ከደርቡሽ ፣ በሰሜን ምሥራቅ ከኢጣልያኖች ጋር ስለሆነ ፣ ወደ ሰሜን ምሥራቅ ለመዝመት ንጉሠ ነገሥቱ ሲዘጋጁ ለምኒልክ ባለፈው ጥሪ ባደረጉ ጊዜ ንጉሡ ፣ "በየዳር አገር የተበተነው ጦሬ እስኪሰበሰብ ድረስ የዕርቁን ጉዳይ ልሞክር" ብለው ለዚሁ አቡነ ማቴዎስን ፣ ደጃች መሸሻን ፣ ቢቶደድ አጥናፌን መላካቸው ይታወሳል ። ስለነዚህ መልእክት ያገራችን ጸሐፊዎች ብላቴን ጌታ ኅሩይና አቶ አጥሜ እንዳሠፈሩት ፣ ንጉሠ ነገሥቱ አቡነ ማቴዎስን ብቻ ተቀብለው ሲያነጋግሩ፥ ሁለቱን እንደ ሰላይ አድርገው ፊትነሥተው ሳያነጋግሩዋቸው እንደቀሩ ፣ በመጨረሻም ሁለቱን መኳንንት ወዳገራቸው ሲመልሱ አቡኑን ይዘው ወደ ሰሐጢ እንደ ተጓዙ ሲገልጡ ፣ በውጭ አገር ጸሐፊዎች በተለይም በኢጣልያኖቹ ሰነድ ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ምንም እንኳን አቡኑን በሁለተኛው የጉዞ ጊዜ ማስቀረታቸው የተረጋገጠ ቢሆን ፣ ሁለቱን መኳንንት በደንብ እነጋግረው በአቡኑና በደጃች መሸሻ እጅ ስለ ዕርቁ ጉዳይ ለምኒልክ የላኩትን ባለፈው ምዕራፍ አንብበናል ። ምናልባት የመልእክቱ መመላለስ

ሁለት ጊዜ ሆኖ የመጀመሪያው ጊዜ መልእክት በደህና ተከናውኖ
በሁለተኛው ጊዜ ለምኒልክ አስታራቂነት ልዩ ልዩ ትርጉም እየተ
ሰጠው ይኸውም ማለት ፤ "ጣልያኖችን ሰበው ያመጡ ምኒልክ
ናቸው ፤ አሁንም ለጦርነት ቢጠሩ ጦሬ አልተሰበሰበልኝም ያሉት
ለምክንያት ነው" እየተባለ ፤ ባፄ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት የሚነፍ
ሰው ወሬ ስለገነነ ፤ በመጨረሻው ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ማመን
ደርሰው ለምኒልክ እንደ መጀመሪያው ጥሪ ሳያደርጉ ከሸዋ ሁለተኛ
ጊዜ ወደ ትግራይ የተመለሱትን አቡኑን እንደያዙ ወደ ሰሐጢ ጉዟ
ቸውን ጀምረዋል ማለት ነው ።

ብዙ የውጭ አገር ጸሐፊዎች በተለይ ኢጣሊያኖቹ በንጉሥ
ምኒልክ ቤተ መንግሥት የኢጣሊያን የወራሪነት አቅዋም አበክረው
የሚቃወሙና ዐፄ ዮሐንስን በስሜት የሚደግፉ እንደነበሩ ጽፈዋል።
እነዚህም የንጉሡ ባለቤት ወይዘሮ ጣይቱ ፤ ወንድማቸው ደጃች ወሌ፣
የአገው ምድሩ ተወላጅ ደጃች መንገሻ አቲከም፣ ደጃች መሸሻ ሰይፉ፣
የደጃች ገርማሜ ልጅ ደጃች መኩሪያና ብዙ የቤተ ክህነት አለቆች
ነበሩ ። የመኳንንቶቹ ዮሐንስን ደጋፊነት በግልጽ አይታይም እንጂ
የሊቃውንቱ ዐፄ ዮሐንስን መውደድ ዕውቅ ነበር ። የእነዚህም አደ
ጋገፍ ከፖለቲካው ይዞታ ይልቅ በሃይማኖት በኩል ዮሐንስን ስለተ
ዋሕዶ ሃይማኖት የነበራቸውን መንፈሳዊ ቅንዓትና ምኒልክ በዚህ
ረገድ ያሳዩ የነበሩትን ቸልታና ገለልተኛነት እያነጻጸሩ በመ
ገምገም የአንኮበር አለቆች ሳይቀሩ ፤ "ሐቀኛ የተዋሕዶ ክርስቲያን
ንጉሥ ማለት ዐፄ ዮሐንስ ናቸው ። የእኚህ (የምኒልክ) ይዞታቸው
አይታወቅ ፤ ሁሉ እንደ ሃይማኖቱ ይኑር ባይና የካቶሊክ ሃይማኖት
ያለውን ፈረንጅ የሚያቀራርቡ ናቸው" እያሉ ውስጥ ውስጡን ያሙ
ነበር ። በፊተኛው ጊዜ ከደጃች መሸሻ ሰይፉና ከወይዘሮ ባፈና ጋር
እያደሙ ወዳፄ ዮሐንስም ይላላኩ እንደ ነበር የታወቀ ነው ። ምናልባት
ከነርሱም ጋር በአሳብ የተደረቡ መኳንንት ይኖሩ ይሆናል ። እንዲያ
ውም አልፈው ተርፈው እነዚሁ የአንኮበር ታላላቅ የእድባራት ሊቃ
ውንት በፊታቸው ተሰብስበው ፤ "ሃይማኖትዎ ተዋሕዶ መሆኑን እላ
ወቅነውምና ይገዙቱልን" የሚል ጥያቄ አቅርበውላቸው "እኔ ከናንተ
ካባቶቼ ከተዋሕዶ ሃይማኖት የተለየ የለኝም" ብለው ተገዘቱ (ማሉ)
ይባላል ።

በእነዚህ መኳን ንትና ሊቃውንት አንጻር አብዛኞቹ መሳፍንትና
መኳንንት ምኒልክን ከልብ የሚወዱ ፤ እስከ መጨረሻ ለንጉሣቸው፣
ታማኝ የሆኑ ፤ የምኒልክ ለዮሐንስ መገበር ቅር የሚላቸውና ውኒዖ
የሚያምራቸው እንደ ራስ ጐበና ፤ እንደ ደጃች መኰንን ፤ እንደ ደጃች
ወልደ ጊዮርጊስ፣ እንደ ደጃች ወልዴና ሌሎችም ተሰማ ናደው፣ በሻህ



አቦዬ ፤ አጥናፌ ገበየሁ ይገኙ ነበር ። ከዚህ በፊት ስማቸውን የጠቀስ
ነው የጐጃሙ ጸሐፊና ሠዓሊ አለቃ ተክለ ሥላሴ የዚህን ጉዳይ ሲያ
ወሱ እንደዚህ ብለዋል ።"...የሸዋ ሰው ጉልበት እየተሰማው እን
ዋጋ የሰጠ (ሰሰጠ) ይስጠው ለትግሬ አንገብር እያለ ንጉሥ ምኒል
ክን ያውክ ነበር። ንጉሥ ምኒልክ ግን የመነሻውን ጊዜ ዐውቆ ዝም
ብሎ እስተጊዜው ሲገብር ኖረ ።"[1]

ዮሐንስና ምኒልክ በ1870 ዓ.ም የበላይና የበታችነታቸውን በዕ
ርቅ ጨርሰው ከዚያም ወዲህ ልጅና ልጅ አጋብተው በስምምነት
በነበሩበት ሰዓት ምኒልክ እየተጠሩም ሆነ በራሳቸው ፈቃድ ወደ ደብረ
ታቦርና (ቤገምድር) ወደ ቦሩ ሜዳ (ወሎ) ብዙ ገጸ በረከት ይዘ
ውና ብዙ ሠንጋ እያስነዱ ከንጉሠ ነገሥቱ በሚገናኙበት ጊዜ ፤ ዐፄ
ዮሐንስን የተከተሉት የትግራይ መኳንንቶችና ወታደሮች ፤ "ይኸን
ሁሉ ከኛ የበለጠ ወታደር ይዘው እንዴት አይዋጉም ? ለምን ይገ
ብራሉ" እያሉ ምኒልክን ማማታቸውን ሌላው ጸሐፊ አቶ ዐፅመ
ጊዮርጊስ (አጥሜ) ጠቅሰውት የነበረው ይታወሳል ።[2]

ነገር ግን አፈወርቅ "የሸዋ ሰው እንዋጋ ...ሲል ዐጤ ምኒልክ
ጊዜዎን እየጠበቁ ዝም ብለው በጆሮአቸው ይሸኙት ነበር" እንዳ
ሉት ፤ በጠባያቸው ደመ በራድ ታጋሽና አመዛዛኝ የነበሩት ምኒልክ
የግራ ቀኙን አባባል እያዳመጡ ፤ "አንተም ተው ያንተም እውነት ነው፣
ነገር ግን .." እያሉ በፖለቲካ አነጋገር ከበሰሉት የሽማግሌ አባቶች
ከነራስ ዳርጌ ፤ ከነፊታውራሪ ሀብተ ማርያም (የዝቋላው) ከነአዛዥ
ወልደ ጻድቅ (ያንኮበሩ) ከፈረንጁም ሳይቀር እየተመካከሩ ፤ ባንድ
ወገን ኃይላቸውን እያጠነከሩ ፤ በሌላ ወገን ካፄ ዮሐንስ ጋር የነበራ
ቸው ግንኙነት ፈጽሞ እንዳይበላሽ "እንዋጋ ይዋጣልን" እያሉ የሚ
ወተውቱትን በትዕግሥት እያበረዱ ጊዜያቸውን በመጠበቅ ቆዩ ።
የኢጣልያ ጦር ምጥዋ የመውረዱ ወሬ ሳይሰማ ሐረርጌን ለመያዝ
በሚዘጋጁበት ወቅት በ1878 ለኢጣልያ ንጉሥ በጻፉት ደብዳቤ
ላይ ፤ "ካባቴ ከወዳጄ ካፄ ዮሐንስ ታረቅን አንድ አካል አንድ አም
ሳል ሆንን" ብለዋል ። ከዚያ ወዲህ ነገሩ እየተለዋወጠ ሔደ ።

አሁን ወደ ወሎ ለመዝመት በሚዘጋጁበት ጊዜ ፤ በየዳር አገር
ያሰው ጦር ተሰብስቦ ሳያልቅ በሚካከሉ የፈንጣጣ በሽታ ተነሥቶ
ብዙ ሰው ፈጀ ። ከነዚህም መካከል ብዙ ጊዜ ባፄ ዮሐንስ ደጋፊነት

---

1 የእጅ ጽሑፍ ገጽ 133
2 አቶ አጥሜ ፤ የጋላ ታሪክ ፤ ገጽ 155

የዙፋን ባላንጣቸው ሆነው የቆዩት ደጃች መሸሻ ሰይፉ በመጨረሻ በራስ ዳርጌ አማካይነት ታርቀው ከገቡ በኋላ ፣ በዚሁ በፈንጣጣ በሽታ ታመው በታኅሣሥ 7 ቀን 1880 ዓ.ም. ሞተው አዲስ አምሮ ተሠርቶ በተመረቀው በእንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ ። ይኸውም ምኒልክ ለዘመቻ ከመነሣታቸው ከ11 ቀን በፊት ማለት ነው ።ከዚህም ትንሽ ቀደም ብሎ እቴጌ ጣይቱ ታመው የንጉሡ አክስትና የራስ መኰንን እናት ወይዘሮ ተናኘ ወርቅ በነሐሴ ወር መጨረሻ 1879 ሞተው በቤተ መንግሥቱ ሐዘን ነበር ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ፣ በየዳር አገር የነበረው ጦር በክተት ዐዋጅ ይነስ ይብዛ ከተሰበሰበ ወዲህ በታኅሣሥ 18 ቀን 1880 ዓ ም. ለከተማና ላገር ጥበቃ በዚህ ጊዜ ጤንነታቸውን መልሰው ያገኙትን ባለቤታቸውን እቴጌ ጣይቱንና ራስ ጐበናን ትተው ከ120.000 እስከ 130.000 የሚደርሰውን ጦራቸውን ይዘው ከእንጦጦ ተነሥተው ምስርምድር ሠፍረው ሳሉ ፣ ከርቀት የተነሣ ወደኋላ ዘግየት ብለው የነበሩት ደጃች መኰንን ከሐረርጌ አሚር አብዱላሂን ይዘው ስለ መጡ ታላቅ ደስታ ሆነ ። ከዚያ አልፈው በታኅሣሥ 23 ቀን ደብረ ብርሃን ከተማ ደርሰው የሁለት ቀን ዕረፍት ካደረጉ በኋላ ፣ በጥር 22 ቀን ተሁለደሬ (ወሎ) ገቡ ።[1]

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ቁጥር ሳይጠቅሱ የሠራዊቱን ብዛት ለማመልከት በደፈናው ፣ “የተከተላቸው ሠራዊት እጅግ ብዙ ነበርና ሠፈሩ ከአርዲቦ ባሕር እስከ ሐይቅ ባሕር ደረሰ” ሲሉ ፣ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በበኩላቸው ፣ “የሠፈሩ ብዛት ከአርዲቦ ባሕር እስከ ቀይ ባሕር ነበር” ያሉት ። በቃለ አጋኖ ወይም የሥፍራውን ርዝመት ባለማወቅ ስለሚመስል የሚታመነው የብላቴን ጌታ ኅሩይ አባባል ነው ።*

በእርግጥም ንጉሥ ምኒልክ በዚያን ጊዜ ያስከተሉት ጦር በቁጥር ብዛት ብቻ ሳይሆን በጥራትም ጭምር ዝግጅቱ የላቀ ነበር ። በወታደር ፣ ባለቆቹና በንጉሡ መካከል የነበረው የግንኙነት ሥነ ሥርዓት ከመቸውም የጠነከረ ነበር ። ወደኋላ አሳባችንን መለስ አድርገን ሁኔታውን ስንመለከተው ፣ መቸም ምኒልክ ከመቅደላ አምልጠው

---

1 ጸ.ት. ገ/ሥላሴ ፣ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 148-150 ብ.ጌ.ኅሩይ ፣ ከንግሥት ሳባ እስከ ዐድዋ ጦርነት ፣ የእጅ ጽሑፍ ገጽ 138 ፤ አፈወርቅ ፣ ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ ገጽ 50 ።

* የአርዲቦ ሐይቅ ፣ ከሐይቅ እስጢፋኖስ ርቀቱ እስከ 10 ኪሎ ሜትር ይደርስ ይሆናል ።



ሸዋ ከገቡበት ጊዜ ከ1857 ዠምሮ እስከዚህ እስከ 1880 ዓ.ም. ድረስ በ23 ዓመታት ውስጥ ከአቶ በዛብህ ጋር ባጋዲሎ ፣ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር በእምባቦ ፣ ከአሚር አብዱላሂ ጋር በጨለንቆ ሐረርጌ ባደረጉዋቸው ጦርነቶች ሁልጊዜ ድልን ስለ ተቀዳጁ፣ ይህ ሁኔታ ግዛታቸውን ከማስፋትና የሠራዊታቸውን አቅዋም ከማጠንከር በቀር አላዳከመውም ። የደቡቡንም ክፍል በባሰው ራሳቸው እየዘመቱ ፣በቀሪውም የጦር አለቆቻቸውን እየላኩ ፣ የግራኝ አህመድ መነሣትና የጐንደር መንግሥት ከሥፍራው መራቅ አግዞአቸው ከኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት ቁጥጥር የወጡትን ነገዶች ከነአውራጃቸው ወደ እናት አገር ሲመልሱ ፣ ያገር ተወላጆቹ የያዙት የጦር መሣሪያ አንካሴና ጦር ፣ ጐራዴና ጩቤ ስለነበረ ፣ በጠበንጃና በጥይት ከሚያሳምናቸው የደረጀ ጦር ጋር ምንም ያህል የመቋቋም ኃይል ስለአልነበራቸው የምኒልክን የጦር ቁጥር ሊቀንሱ አልቻሉም ።

በዚህ ፈንታ እነዚህ አዳዲስ አውራጃዎች ከገበሩ በኋላ ፣ንጉሥ ምኒልክ አለቃና ጭፍራ ከመካከላቸው እየመለመሉ በሹመት ፣ በማዕረግ ስምና በሽልማት እያሳደጉ ከውጭ አገር በግዥም በስጦታም በሚያገኙት የጦር መሣሪያ እያስታጠቁ የጦር ሠራዊታቸውን ቁጥር ከቀን ወደ ቀን ለማበርከት ችለዋል ። ከነዚህ አውራጃዎች በሚገኝ በቡና ሀብት ፣ በወርቅ ፣ በዝሆን ጥርስ ሽያጭ ፣ በቀንድና በጋማ ከብት ረገድ ሀብታም ሆነዋል ።በዚህ ሀብትና በተወዳጅነት የጐጃምን ፣ የቤገምድርን ፣ የወሎንና የትግራይን ተወላጅ ሳይቀር እየሳቡ በውስጣቸው በማሳደር ሁኔታው ንጉሠ ነገሥቱን እስከ ማሥጋት ደርሷል ።

ከላይ በተመለከተው ዐይነት ተዘጋጅተው ከነሠራዊታቸው ቦሩ ሜዳ ላይ እንዳሉ፣ “እርስዎን ለመርዳት ጣልያንን ለመውጋት ልምጣ” ብለው ወዳጄ ዮሐንስ ላኩ ። ከንጉሠ ነገሥቱ “ለኢጣልያን ጦር አንሰንፍም ። ይልቅስ ደርቡሽ በመተማ አለና ጐንደርን እንዳያቃጥለው ዐይንህን ወደዚያ አድርግ ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትንም በቤገምድር ተቀምጠህ ጠብቅ ብዬዋለሁ”የሚል መልስ እንደ መጣላቸው አቶ ዐጥሜ ገልጸዋል ። ቀጥለውም ንጉሠ ነገሥቱ ምኒልክን ወደኔ አትምጣ ያሉዋቸው ምናልባት ከኢጣልያ ጋር ዱለት (መመሳጠር) እንዳላቸው ብለው ሠግተው ስለነበረ መሆኑን ፣ በዚሁ ጊዜ ደርቡሽ ከመተማ ወደ ደምቢያ (ጣር ውኃ) መጥቶ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር ተዋግቶ ማሸነፉን ፣ ጐንደርን ማቃጠሉንና ሰውንም መፍጀቱን አቶ ዐጥሜ ጽፈዋል ። ምኒልክ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን መሸነፍ ሲሰሙ ፣ ከቦሩ ሜዳ ወደ ቤገምድር መገሥገሣቸውን ከዚያም ወደ ጐንደር ወርደው በአዘዞ ሠፍረው ከሠራዊታቸው ብዛት የተነሣ ሠራዊታቸውን ባንድ ጊዜ ማሰለፍ ስለ አልቻሉ ፣ ሁለት ጊዜ አሰልፈው

ያገደኛውን ስልፍ ሁኔታ በአቅራቢያው የነበሩት ደርቡሾች በስላዮቻቸው በኩል ተገንዝበው ግድነታቸውን ዘርዝረዋል ።[1]

በጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ መጽሐፍ ከወሎ ሳይነሡ "ከጨለለቅላቃ በመሰስ ሚያጥ ወንዝ ድረስ ያለህ ሰው ፣ ሠራዊት ቢራብብኝ እህል ለምገኘለሁና ግዝህን ፥ከብትህን ይዘህ ተነሣልኝ ፣ ወታደር እህል ፈቅጀልሃለሁ ፣ ልብስና ከብት አትንካ" የሚል ዐዋጅ አድርገው ወደ ቤገምድር መጓዛቸውን ፤ በዚሁ ጊዜ የንጉሥ ተከለ ሃይማኖትን በደርቡሾች የመሸነፍ ወሬ ሲሰሙ በየካቲት 6 ቀን ወርጣየ ፣ በ18 ቀን ዋር መስፈራቸውን ፣ ከዋሮ 12 ቀን ተጉዘው በመጋቢት 1 ቀን ደብረ ታቦር መግባታቸውን፣ በደብረ ታቦር 19 ቀን ቆይተው በሚያዝያ 11 ቀን አዘዞ ደርሰው ከሠፈሩ በኋላ ከሜዳ ላይ ወጥተው ሠልፍ ሲያሳዩ መዋላቸውን ፣ ከሠልፉ ላይ መኳንንቱም ወታደሩም እየፎከረ ግባት ቢተኩስ ድምጡ (የጥይቱ) ሳያቋርጥ አንድ ሰዓት መቆየቱን ፤ በዚህ ጊዜ ደርቡሽ ከሜዳ ላይ ወጥቶ መዋጋቱን ፈርቶ ከዚያም ካለበት (መተማ) ቦታ ምሽጉን ብቻ ማጠናከሩን ገልጠዋል ።[2]

መቸም ያገራችን ጸሐፊዎች የሚጽፉት ሁሉ ፣ በመሠረቱ ሲስማማ ባንዳንድ ዝርዝር ሁኔታ ይለያያል ። አንዱ የተወውን ሌላው ፣ ሌላው የተወውን አንዱ ይጽፈዋል ። ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ የዚህን ጉዳይ ሲያወሱ እንደዚህ ብለዋል ። "ዐጤ ምኒልክ ከወሎ ገሥግሠው ወደ ጐንደር በሔዱ ጊዜ ደርቡሽ ጐንደርን እቃጥሎ አገሩን (ወደ አገሩ) ገባ ።ደርቡሽና ዐጤ ምኒልክ ግን ፤ ነገር ለነገር ተዋውቀው ነበር አስቀድመው ። ለሁሉም ነገር ዐጤ ምኒልክ አዘዞ ላይ ሠራዊትዎን (ሠራዊታቸውን) ሁሉ አሰልፈው አዩ ። ሰልፉ አምሮ ሠራዊቱ በዝቶ እንኳን ደርቡሽ ይቆምለት ላጤ ዮሐንስም ሠራዊት ቢሆን በግርማው ብቻ አለመድፍና አለነፍጥ የሚያንቀጠቅጥ ነበር ። ዐጤ ምኒልክ ያን ሁሉ ሰልፍ በፈረስ ሆነው ዳር እስከ ዳር እየቃኙ አዩ አዩና ከልብዎ በደረሰ ጊዜ ቀኝና ግራውን በዘንግ እያሳዩ በዚህም ቢመጣ (በመታማ) በኩል ደርቡሽ በዚህም ቢመጣ በትግሬም በኩል ዐፄ ዮሐንስ (ውሎህ እንዲህ ነው በዚህ በኩል ትዋጋለህ) አሉና ለሠራዊቱ ተናገሩ. . ነገሩን አውጥተው ባይናገሩም ትግሬ ቢመጣ እንዲህ ሁነህ ተሰልፈህ ትዋጋለህ. . ማለታቸው ነው" ብለው

1 አቶ ዐጥሜ ፣ የጋላ ታሪክ ፣ ገጽ 163-165 ።

2 ጸ.ት.ገ/ሥላሴ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ምዕ.37 ፣ ገጽ 48-150 ።



ራሳቸው ተርጉመው ያመለከቱና ፣ ሠራዊቱም ነገሩ እንደ ገባው ዐፄ ዮሐንስን መከዳታቸው በዚሁ ስለ ታወቀ ከዚያው ላይ አቅራሪ ተነሥቶ፣

— አይሆንም እንጂ ተሆነማ
— ተመጋዞ ይሻላል ጉልማ *

ብሎ እንዳቅራራ ጽፈዋል[1]

ንጉሥ ምኒልክ ከአዲስ አበባ በታኅሣሥ 18 ቀን ተነሥተው በሚያዝያ 11 ቀን አዘዞ መድረሳቸውን ለጉዞ የአራት ወር ጊዜ መፍጀታቸውን ፤ ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴም ማርክስ ሀሮልድም በየመጽሐፋቸው የልግም ጉዞ አድርገው ቆጥረውባቸዋል ።[2] እንደ ዛሬ የአባይ ድልድይ ሳይሠራና በጐጃምና በባሕር ዳር ያለው መስመር ሳይከፈት ከእንጦጦ በደብረ ብርሃን ፣ በመንዝና በግድም ፣ በኤፍርሃታ ፤ በወረይሉ ፣ በቦሩ ሜዳ በደብረ ታቦር ዞሮ አዘዞ ለመድረስ ርቀቱ ወደ 800 ኪሎ ሜትር ድረስ የሚጠጋ ይመስለኛል ። ያስከተሉት ጦር እስከ 130.000 ሊደርስ ይችላል ሲባል ፣ የነዚህ ተከታይ በእግሩ የሚጓዘው ሽከም የማይለየው አሽከሩ ፥ገረዱ ፣ ስንቅና ዕቃ የጫነው አህያ፣ አጋሰስና በቅሎ ይኸን ሁሉ ጓዝ አግተልትሎ በግሥጋሤ መሔድ ችግር ነው ። በዚህ ላይ ደግሞ ለዘመቻ የታዘዘው ጦር ሁሉ ምንም የንጉሥ ትእዛዝ ቢሆንበት ፣ በቅርብ ቀን ያቀናውን ዳር አገር ሁሉ ባንድ ጊዜ ለቆ የመምጣቱ ነገር የሚታሰብበት ነው ። የራስ ጐበና ከዚህ ዘመቻ ተለይቶ አዲስ አበባ ለጥበቃ መቅረት ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነበር ። ራስ መኰንን ጦራቸውን አስከትለው ከሐረርጌ በንጉሡ ሠፈር ምስር ምድር (ለንዳፋ አካባቢ) የደረሱባቸው በመንገድ ጉዞ ላይ ሳሉ መሆኑ ባለፈው ተጠቅሷል ። እንደዚሁም ከዋነኞቹ የጦር አለቆች አንዱ የኤፍራሃታና የአንጾኪያው ገዥ ደጃች ወልዴ አሻግር በዚሁ ወቅት ታመው ስለ ነበረ ፣ ጦራቸውን ያዘው የደረሱባቸው የጥር ወር ካለቀ በኋላ ቦሩ ሜዳ ሳሉ ነው ። ስለዚህ ከዚህ ሁሉ ጋር በምኒልክ ጠባይና የጦር ስልት ዐዋቂነት በግሥጋሤ ሔደው እጦርነት ላይ ወድቀው ራሳቸውንም ፣ ሠራዊታቸውንም ከመሸነፍ አደጋ ላይ ከመጣል ወታደርንም ከብትንም አጠዋሮ በሩጫ ሳያዳክሙ ከኋላ የቀረውን

* መጋዞ ጭሰኝነት ጉልማ ቁራጭ የርስት መሬት ነው ። ባጭሩ ያዬ ዮሐንስ ጭሰኛ ገባር ከመሆን ነጻ መሆን ይሻላል ማለቱ ነው ።

1 አፈወርቅ ፣ ገ/የሱስ ፣ ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ፣ ገጽ 50-51 ።

2 ዘውዴ ገ/ሥላሴ በገጽ 240-241 የጉዞ ርቀት 350-400 ኪ.ሜ. እንደሚሆን ገልጸዋል ። P. Rosenfeld, Chronology of Menilik 11, p. 128.

እየጠበቁ ሰብስበው ከፊት የቀደመውን በማርጋት ባንድነት አጠራቅ
መው ለመዋጋት ነው ። በአዘዞ ከፈረስ ላይ ሆነው ያሳዩት ታላቅ
ሰልፍ ደርቡሾንም ሊያስበረግግ የቻለው ከጥናት ጋር በዚህ ዐይነት
የተዘጋጀ በመሆኑ ነው ማለት ይቻላል ።

ሌላው በዚህ ምዕራፍ ሊጠቀስ የሚገባው ፣ የእርሳቸውና የደር
ቡሾች ግንኙነት ነው ።በጥር ወር መዠመሪያ ላይ ንጉሥ ተክለ ሃይ
ማኖትን ደብረ ሲና አጠገብ ሣር ውሃ ከሚባለው ቀበሌ (ደምቢያ
ውስጥ) ደርቡሾች ካሸነፉ ወዲህ ፣ ንጉሠ ነገሥቱም ወደ ሰሐጢ ግን
ባር ስለ ዘለቁ ንጉሥ ምኒልከም በወሎና በሸዋ መካከል ገና ከጉዞ
ላይ ስለነበሩ ፣ ሁኔታው ለድል አድራጊዎቹ ደርቡሾች ምቹ ጊዜ ስለ
አስገኘ ፣ የደምቢያን ወረዳ የጐንደርን ከተማ እስከ መተማ ድረስ ያለ
ውን ከቁጥጥራቸው ውስጥ አውለውታል ።

በዚህም ጊዜ ፣ በመሸነፍ ወደ አገራቸው የተመለሱት ንጉሥ
ተክለ ሃይማኖት ስለ ተማረኩት ልጃቸው ስለ ወይዘሮ ምንትዋብና
ልጅ መኰንን ስለሚባለው የቅርብ ዘመዳቸው ሁኔታ ከሐምዳን አቡ
አንጋ ጋር እየተጻጻፉ ፣ የደርቡሹ መሪ የምንትዋብን ሞት በደብዳቤ አስ
ረድቶ በርስዎ እጅ ያሉትን የኔን ምርኮኞች ቢልኩልኝ እኔም በኔ
እጅ ያሉትን የርስዎን ሰዎች እነልጅ መኰንንን በሰላም እልካለሁ
በማለት በመተማና በአካባቢው የደርቡሽ ገዥ በመሐመድ ሳላህ
አማካይነት በሰላማዊ መንገድ ከመጻጻፍ ላይ ይገኙ ነበር ።


አሁን ደግሞ ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወደ ጐጃም ቢመለሱም
ንጉሠ ነገሥቱም ከነሠራዊታቸው ወደ ሰሐጢ ቢርቁም ፣ ምኒልክ
ከሸዋ አዲስ ያልተነካ ጦር ይዘው አዘዞ መድረሳቸውና ታላቅ ሰልፍ
በማሳየታቸው ሱዳኖች ባገኙት የሣር ውሃ ድል እንደ ልብ ተዝና
ንተው በያዙት ወረዳና በጐንደር ከተማ ሊቆዩ አልቻሉም ። በዚህ
ምክንያት የደርቡሾቹ ባለሥልጣኖች በሰላዮቻቸው በኩል እንደ ተገ
ነዘቡት ፣ የምኒልከ የጦር ኃይል የማይገፋ መሆኑን ሲረዱት ወደኋላ
መለስ ብለው ደግሞም ፣ "ዐፄ ዮሐንስ በሰሐጢ ግንባር ከኢጣልያኖች
ጋር ሲዋጉ ሞተዋል" የሚል ሐሰተኛ ወሬ ስለ ተሰማ ፣ አልጋውን
የሚወርሱት ምኒልከ መሆናቸው አይቀርም በማለት ነጋሽ መሐመድ
የሚባለውን የቃል መልእክት አሲይዘው ወደ ምኒልከ ልከዋል ።ይኸ
ንንም ሲያደርጉ ከሣር ውሃ ጦርነት በኋላ ፣ የያዙትን የደምቢያን
ምድርና የጐንደርን ከተማ የምኒልከ ጦር ስለ አሠጋቸው ከለቀቁ
በኋላ ነበር ። የመላክተኞቹም ዓላማ በሰላም ንግግር አማካኝተው
የምኒልክን ጦር ዝግጅት ለመሰለል ጭምር መሆኑ አይጠረጠርም ።



የምኒልከም አሳብ ሁኔታው እንደሚያስረዳው ፣ 'አትንኩኝ አልነ
ካችሁም' የሚል ስሜት ስለ ነበረበት ፣ ደርቡሾቹ ደምቢያንና ጐንደርን
የማይለቁ እንደሆነ ለመዋጋት ፣ ከለቀቁ የጦራቸውን ሕይወት ጠብ
ቀው በሰላም ለመመለስና ለኢጣሊያኑ ግንባር ካፄ ዮሐንስ ጋር
ለመላላክ ነበር ። ከደርቡሾቹ ለቀረበላቸው ሰላማዊ አሳብ እርሳቸ
ውም ሐጅ አህመድ በሚባለው በኩል ስለ ሰላሙ ጉዳይ ተላል
ከዋል ። በዚያውም በነጋሽ መሐመድ አማካይነት በዡማዳ አል ሐኪር
የካቲት 1880 የዮሐንስ በሕይወት መኖር ሲሰማ ፣ "ከንጉሠ ነገሥቱ
ያስማሙን" የሚለውንም የደርቡሾች አሳብ በእሺታ ተቀብለው [1]
ጉዳዩ በዚሁ እንዳደረ ንጉሠ ነገሥቱ ከሰሐጢ የጦር ግንባር ወደ
መቀሌ ከዚያም ወደ ቤጌምድር ሲመለሱ ነገሩ ሁሉ ሌላ መልክ ያዘ።
እካሁን ተቻችለው በኖሩት በዮሐንስና በምኒልከ መካከል በይሉ
ኝታና በጋብቻ ተደፋፍኖ የቆየው ጠብ ወደ መገለጥ ደረሰ ።

1 Zewde G.S. The Process of Re-unification of the Ethiopian Empire, Vol. II, pp. 525—530.

ንጉሠ ምኒልክ ከእንጦጦ ወደ አምባጫራ ያደረጉት የጉዞ መስመር



# ምዕራፍ ዐርባ ሁለት

## ባፄ ዮሐንስ ውስጥ ያሉ መሳፍንትና መኳንንት—ንጉሠ ነገሥቱ በከተት ዐዋጅ ወደ ሰሐጢ ያደረጉት ጉዞ፣ የጎንደርን መቃጠል ስለ መስማታቸው

እንደዚያው እንዳፄ ቴዎድሮስ ዘመን፣ ባፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት በየአውራጃው የነበሩት መሳፍንት በቅርብ ከነበሩት የራሳቸው መኳንንት ጋር ልዩነት ነበራቸው። በየአውራጃው የነበሩት በሸዋ እንደ ንጉሥ ምኒልክ፣ በጐጃም እንደ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት፣ በወሎ እንደ ራስ ሚካኤል፣ በቤጌምድር እንደ ራስ ወሬኛ (ወልደ ሥላሴ) በላስታና በሰቆጣ እንደ ዋግሹም ብሩ ያሉት ትክለኛ ባላባቶች ስለ ሆኑ፣ ፊት ለፊት ካልሸፈቱ በቀር እምብዛም እንደ ልብ የማይሻሩና የማይሾሙ፣ በትክለኛ ባላባትነታቸው የሚኮሩ ጉልተኞች ስለሆኑ፣ በንጉሠ ነገሥቱ አጠገብ ከነበሩት እንደነራስ አሉላ ከመሳሰሉት የቅርብ ረዳቶችና እንደ ራስ አርአያ ካሉት ቤተሰቦች ጋር የተለየ አቅዋም ነበራቸው። የእነዚያ ሹመትና ዕድገት በጉልተኛ ባላባትነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ የእነዚህ በአገልግሎት ወይም የንጉሠ ነገሥቱ ተወላጅ በመሆን ነው።

አብዛኞቹም፣ በባላባትነትና ከንጉሠ ነገሥቱ ተወላጅነታቸው በላይ ንጉሠ ነገሥቱ አገልግሎታቸውንና ታማኝነታቸውን እያመዛዘኑ ያሳደጉዋቸው፣ በማዕረግ ስም በሹመት በሽልማት ያከበሩዋቸው ስለሆኑ ከነዚያ የበለጠ ታማኝነታቸው የጠበቀ ነበር። እነዚያ የሩቅ፣ እነዚህ የቅርብ ረዳቶች ነበሩ። የነዚህም የዋነኞቹ ስማቸው ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

1. ትልቁ ራስ አርአያ ድምፁ አጎታቸው፣
2. ትንሹ ራስ አርአያ ዮሐንስ ልጃቸው፣
3. ራስ ቢቶደድ ኃይለ ማርያም ጉግሣ የታላቅ ወንድማቸው ልጅ
4. ደጃዝማች መንገሻ ዮሐንስ *

---

*- ደጃች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ ያፄ ዮሐንስ ልጅ አድርገዋቸዋል። ሌሎቹ የታላቅ ወንድማቸው የደጃች ጉግሣ ልጅ ናቸው ይላሉ። እውነትም ዐፄ ዮሐንስ ከመሞታቸው በፊት ጽሑፉ ሁሉ መንገሻ ጉግሣ ይላቸው ነበር።

5. ራስ ቢቶደድ ገብረ ኪዳን የእህታቸው የእቴጌ ድንቅነሽ ባለቤት (በዚህ ጊዜ ሞተዋል)
6. ራስ አሉላ አባ ነጋ ተምቤናዊ (ዙቅሊ)
7. ደጃች ባርያ ጋብር (የደጃች ገብረ ሥላሴ አባት)
8. ራስ ሐጐስ ተምቤናዊ
9. ቢቶደድ ገብረ መስቀል ገብረ ጻድቅ (እንደርታ)
10. ዋግሹም ገብሩ
11. ደጃች ተሰማ ገብረ ሚካኤል
12. ደጃች መሸሻ
13 በጅሮንድ ሰውጤ
14. ደጃች ተድላ ባሕራይ
15. ሊቀ መኳስ ይልማ ደስታ . . . . .

ስጊዜው ስማቸውን ያገኘነውን ከየመጽሐፉ ለቅመን ዘረዘርነው እንጂ፣ ብዙ መኳንንት በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያልተጻፉ እንደሚኖሩ የታወቀ ነው ። ከዶጋሊው ጦርነት ወዲህ የጦር ጠቅላይ አዛዥነቱን ንጉሠ ነገሥቱ ከራስ አሉላ አንሥተው ለታላቅ ወንድማቸው ልጅ ለራስ ኃይለ ማርያም ሰጥተው፣ አሉላን በሐማሴን ግዛት ስለወሰኗቸው ቅሬታ ነበራቸው ይባላል ። በዚህም ላይ ያፄ ዮሐንስ የእህታቸው የእቴጌ ድንቅነሽ ባለቤት ራስ ቢቶደድ ገብረ ኪዳን ስለሞቱ የራስ ቢቶደድነቱን ሥልጣን ከነማዕረጉ ለኝሁ ለራስ ኃይለ ማርያም ሰጥተው አክብረዋቸዋል ።

በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳሉ፣ በመስከረም ወር 1880 ዓ ም. ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ወደ መተማ የጦር ግንባር ከደርቡሾች እንዲዋጉ ልከው ሳለ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በዛር ወሃ ከተሸነፉና ጐንደር በደርቡሾች ከተበዘበዘ ወዲህ፣ ካህናቱ "እግዚኦ ቦኡ አሕዛብ ውስተ ርስትከ፣ ወአርኰሱ ጽርሐ መቅደስከ፣ ወረሰይዎ ለጐንደር ከመ ልገተ ዓቃቤ ቀምሕ" የሚል ከዳዊት መዝሙር ጠቅሰው ወዳፄ ዮሐንስ ላኩ። ዐፄ ዮሐንስም ንጉሥ ምኒልክን ወደ ጐንደር ብቅ ብለው እንዲጠብቁ አዘው እርሳቸው ደብረ ታቦር እንዳሉ፣ በእንግሊዝ አማካይነት የተሞከረው የዕርቅ ድርድር ከሳተ ወዲህና በጄኔራል ሳን መርሳኖ መሪነት 20,000 ወታደር መጥቶ ሰሐጢ ላይ በመመሸግ የዶጋሊን በቀል ለመመለስ መምጣቱን በየጊዜው ሰምተው ስለነበረ፣ ወደዚያ ለመዝመት በሚዘጋጁበት ጊዜ መኳንንቶቻቸው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ገብተው፣ "ጃንሆይ ሁላችንም እስከ ምጥዋ ወርደን ኢጣልያኖችን ከእናታችን ከኢትዮጵያ ምድር እንድናስወጣቸው ይፍቀዱልን" አሏቸው ። እርሳቸውም በመኳንንቱ አነጋገር ተደስተው ቀጥሎ ያለውን መለሱ ።



"መኳንንቶቼ፣ ልጆቼና ሕዝቦቼ ሆይ! እኔም ስለ እናቴ ስለ ኢትዮጵያ ሕይወቴን ልሠዋላት ሙሉ ፈቃድ አለኝ ። ደግሞ በኔ ልብ ያለው በናንተ ልብ ስለመታሰቡ በጣም ደስ ብሎኛል እንግዲህ አሳባችን አንድ አሳብ ከሆነ፣ ጠንክሩ እንጂ አትፍሩ ። ለዘመቻውም አሁን አዋጅ እነግራለሁና አይዟችሁ በርቱ" ብለው በቅድሚያ አዝማች መኳንንቶቻቸውን በንግግር ካበረቱ በኋላ፣ ለጠቅላላው ወታደር ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የክተት ዐዋጅ አስነገሩ ። "ሀገሬ ሆይ ስማ ፤ መኳንንቶቼ፣ ወታደሮቼ፣ ሕዝቦቼ ስሙ ። በመጋቢት 25 ቀን በምጥዋ መንገድ አቅንተህ ለጦርነት እንድትገሠግሥ የኢትዮጵያ መንግሥት በጽኑ ያዝሃል ። ወደፊት ገሥግሥ እንጂ ወደኋላ አትቅር ።

"የኢትዮጵያ ልጅ ሆይ፣ ልብ አድርገህ ተመልከት ኢትዮጵያ የተባለችው አንደኛ እናትህ ናት፣ ሁለተኛ ዘውድህ ናት ፤ ሶስተኛም ሚስትህ ናት፣ አራተኛም ልጅህ ናት፣ አምስተኛም መቃብርህ ናት፣ እንግዲህ የእናት ፍቅር የዘውድ ክብር የሚስት ደግነት የልጅ ደስታ፣ የመቃብር ካባቲነት (ታቃፊነት) እንደዚህ መሆኑን አውቀህ ተነሣ ።" [1]

ይኸን ዐዋጅ ባናገሩ ጊዜ፣ ሁሉም በየአለቃው ስንቁንና መሣሪያውን እየያዘ አብሮ ተነሣ ። በዚህም ጊዜ ጌታቸውን ከድተው ከጠላት ጋር ተባብረው የነበሩት ያጐታቸው የራስ አርአያ ልጅ ደጃች ደብብ በአባታቸው በራስ አርአያ ምክር ከኢጣሊያኖቹ ከድተው ወዳፄ ዮሐንስ ስለመጡ፣ በኢጣልያኖች ዘንድ ጸጸት ሲያሳድር በዚህ በኩል ደስታ ሆነ ። በተለይ የራሳቸው መመለስ የኢጣልያኖቹን ይዞታና የጦር ልክ ይዘው ስለ መጡ፣ ጉዳቱ ለኢጣልያኖች ሲሆን ላፄ ዮሐንስ ጠቀሜታ ሆኗል ። (በዚህ ጊዜ ግን፣ አልጋ ወራሻቸውና ልጃቸው ራስ አርአያ ታመው መቀሌ ቀርተዋል ።)

ከዚህ በኋላ፣ በመጋቢት 25 ቀን 1880 ዓ ም የመረብን ወንዝ አልፈው በጉራዕ በኩል ወደ ሰሐጢ ጉዞው ተዠመረ ። የተከተላቸውን የጦር ሠራዊት ቁጥር ዠራልድ ፖርታል ከእንግሊዝ መንግሥት ተልኮ ካፄ ዮሐንስ ሠፈር በሰነበተበት ጊዜ ያጠራቀመውንና ለመንግሥቱ ያቀረበውን መሠረት በማድረግ፣ ዛሬ ብዙ ጸሐፊዎች ጠቅሰውት ይገኛል ። በፖርታል ጽሑፍ ውስጥ ያፄ ዮሐንስ ጠቅላላ ጦር

1 አቶ ዐጥሜ፣ የጋላ ታሪክ (የእጅ ጽሑፍ) ገጽ 163-164 ። ብላቴን ጌታ ኅሩይ (የእጅ ጽሑፍ) ገጽ 139 ።

ከ70 እስከ 80 ሺ የሚደርስ መሆኑን ይገልጽና ዝርዝሩን ሲያወጣ የራስ አሉላ 16.000 ፤የራስ ሐጐስ 20.000 ፤የንጉሥ ነገሥቱ ዘበኛ 5000 የራስ ሚካኤል 25.000 ፤የደጃች መሸሻ 5000 ፤ የራስ ኃይለ ማርያም ከራስ አሉላ እኩል 16.000 መሆኑን ይገልጻል ። ከነዚህም በቀር የራስ አርአያን ፤ የነዋግሹም ብሩን ፤ የነንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ሳይደባልቅ ነው ።[1]

ነገር ግን ፤ ከነዚህ ውስጥ ደንበኛ ጠበንጃ ሁሉም ወታደር የያዘው የራስ አሉላና የንጉሥ ነገሥቱ አምስቱ ሺ መሆኑን፣ ጠቅላላውም የንጉሠ ነገሥቱ ጦር እስከ መቶ ሺ መድረሱን ፤ ከዚያ ወዲህ የተመራመሩ ጸሐፊዎች ሲያመለክቱ ፣ [2] ሌሎች ጸሐፊዎች መጠኑንና ሠፈሩን በመጥቀስ ከዚህ ከፍ አድርገው አሥመራ የሠፈረው የራስ አሉላ ጦር 16.000 የራስ ሐጐስ በከረን 20.000 የራስ ሚካኤል ጦር በአጐላ (ወሎ) 25000 ፤ የራስ መንገሻ ጉግሣ 5000 ፤ የራስ ኃይለ ማርያም ጉግሣ ጦር በዋድላ 16.000 ፤የራስ አርአያ ዮሐንስ ጦር በዐድዋ የሠፈረው 40.000 ፤ የደጃች ተሰማ 32.000 ፤ የንጉሠ ነገሥቱ የግል ጦር ወይም ዘበኛ 5000 ድምር 159.000 መድረሱን ያረጋግጣሉ ።[3]

ስለዚህ ያፄ ዮሐንስ ጦር ሰሐጢ አቅራቢያ አይለት ላይ ከደረሰ በኋላ፣ የሰሐጢን ምሽግ በጥንካሬ መመሸጉን ንጉሠ ነገሥቱ ተመልክተው ምሽጉን መውጋት በከንቱ ሕዝብ ማስጨረስ መሆኑን ተመለከቱ ። በበኩሉ የኢጣልያም ጦር ጠቅላይ አዛዥ ከምሽግ ወጥቶ ቁጥሩ የበረከተውን የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ለመውጋት አልደፈረም ። በዚሁ መካከል ከእንግሊዝ አገር በጥናት አሠርተው የኢትዮጵያን ሠራዊት ሊያስበረግግ ይችላል ብለው ተማምነው ፤ ወደ ምጥዋ ያመጡትን በአየር ላይ እየተወረወረ የሚጮህ የኤሌክትሪክ መብራትና እንደ ትልቅ ኳስ በሰማይ ላይ የሚያንዣብብ በእነርሱ አጠራር ፖሎኒ አኢሮስታቲኮ ወደ ሰማይ ከመወርወር ጋር ባቡሮችንም በማስጮህ ለማስደንበር ከፍ ያለ ሙከራ አደረጉ ። እውነትም ወታደሩ በዚያን ጊዜ የኤሌክትሪክ መብረቅ አይቶ ስለማያውቅ ፤ መብረቅ ከሰማይ ወርዶ የሚመታው መስሎት ሽሽት ዠምሮ ነበር ይባላል ።

1 G.H. Portal, My Mission to Abyssinia, pp. 143—146, 256—261 Zewde G.S., The Process of Reunification. . ., pp. 517—518.

2 Battaglia, La Guerra d'Africa, pp. 298—300.

3 Rosenfeld, Chronology of Menelik II, p. 127.



ዐፄ ዮሐንስና መሪዎቻቸው የድንጋጤ መልክ ሳያሳዩ ወታደሩን በማረጋጋት ለጦርነት ቢዘጋጁም ፤ ጣሊያኖች ከምሽጋቸው ወጥተው ጦርነት የማይዠምሩ ሆነ ። ስለዚህ አንድ ወር ጠብቀው ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አሥመራ ከዚያም ወደ መቀሌ ከመመለሳቸው በፊት ከኢጣሊያ ጦር ሠራዊት አዛዥ ከጀኔራል ሳን ማርሳኖ ጋር የሰላም ድርድር ይሞከሩ ዠመር ። ዳሩ ግን ፤ ከሁለቱም መንግሥታት የተራራቀ ሐሳብ የተነሣ ሙከራው ምንም ውጤት አለማግኘቱን በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመልከት ።

# ምዕራፍ ዐርባ ሦስት

## ዐፄ ዮሐንስ ስለ ዕርቅ ጉዳይ ከጄኔራል ሳን ማርሳኖ ጋር የተለዋወጡዋቸው ደብዳቤዎች

ዐፄ ዮሐንስ በከተት ዐዋጅ ከደብረ ታቦር እስከ አይለት ድረስ ባይን ግምት 800 ኪሎ ሜትር የተጓዙበት የጦርነት ጉዳይ በወታደርነት መስከ ሊከናወን አልቻለም ። ጦርነቱንም ያገደው የኢጣልያ ጦር ከምሽጉ ወጥቶ የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ለመግጠም ባለመድፈሩ ሲሆን ፣ ንጉሠ ነገሥቱም በእልህ ምሽጉን ለመውረርና ለመደምሰስ የምሽጉ ጽናት ስለ አላስቻላቸው ነው ። እንደ እውነቱ የኢጣልያ ጦር ከሮማ በመርከብ ተሳፍሮ ሲመጣ ከመዠመሪያው ላይ አሳቡ ጥቁሩ ራስ አሉላ በዶጋሊ ነጮቹን 500 የኢጣልያን ወታደሮች በኃይል በመደምሰስ ስለ ደፈሩ ፣ በተለይ ለርሳቸው በጠቅላላው ለኢትዮጵያ ጦር ትምህርት የሚሆን የበቀል ውጊያ ለማድረግና በዚያውም ሰሜን ኢትዮጵያን በሙሉ ለመውረር ነበር ።

በኋላ ደግሞ ፣ ዐፄ ዮሐንስ ካሥር ዓመት በፊት በጉንደርና በጉራዕ ያገኙትን የሁለት ጊዜ ድልና "የኢትዮጵያን ጦር አደራችሁን እንዳትንቁት" የሚለው የሎርድ ሳሊስበሪ ምክርን የኢጣሊያ ሹማምንት ማመዛዘን ላይ ሳሉ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ቁጥሩ የበረከተ ሠራዊት ይዘው የመጓዛቸው ወሬ ሲሰማ ሁሉም ፉከራ ቀረና "በሰሐጢ ምሽግ ብቻ ራሳችሁን ደብቃችሁ ተከላከሉ" የሚለው መመሪያ ከመንግሥቱ መሪዎች ለጄኔራል ሳን ማርሳኖ እንዲሰጥ ግዴታ ሆነ ። ስለዚህ ንጉሠ ነገሥቱ አይለትና ሰበርጉማ * 10 ኪሎ ሜትር ግድም ከሰሐጢ ራቅ ብለው በሠፈሩበት ሰዓት ጣሊያኖች ከምሽጉ ወጥተው ይገጥሙኛል በሚል ተስፋ አንድ ወር ጠብቀው ኢጣልያኖቹ የማይነቃነቁ ሆኑ ።

---

* አይለት ከምጥዋ ዐርባ ኪሎ ሜትር ፣ ሰበርጉማ ዐርባ ስድስት ኪሎ ሜትር ይርቃል ።

ስለዚህ ፡ በክተት ዐዋጅ ጦር ሰብስበው ያን ያህል ተጉዘው ያለ
ምንም ውጤት መመለሱ ቅሬታ ስለ አሳደረባቸው ፡ የዕርቅ ነገር ስመፈ
ተን ከዋናው አዝማች ጋር መላላክ ዠመሩ ። መልክተኞቹ ካፄ ዮሐ
ንስ ወገን ልጅ ወሰን የዓይባ * ሹም ፡ ብላታ ገብረ ሕይወት የእል
ፍኝ አስከልካይ ፡ባሻ ሃይማኖትና ልጅ ዜና (የከንቲባ አማን ወን
ድም) ሲሆኑ ከኢጣልያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ በኩል ሸክ መሐመድ
ዑስማን የአርኪቆ (ደሆኖ) ባላባት ፡ ከንቲባ አማን ፡ ባላምባራስ ከፌል
(ከፍሌ?) ና ልጅ ተሰፋ (ሁለቱም የራስ ወልደ ሚካኤል ጋብቾች)
ከንቲባ ሰብሐትና አድጐ እንበሳ መሆናቸውን ** ዤኔራል ሳን ማር
ሳኖ ላለቆቹ ለጦር ሚኒስትሩ ለቤርቶሊ ቪያሌና ለጠቅላይ ሚኒስትሩ
ለፍራንቼስኮ ክሪስፒ ባስተላለፈው ሰነድ ላይ ይገኛል ።

በቅድሚያ ሸክ መሐመድ ዑስማን ከጉራዕ ወደ አርኪቆ ሲመጣ
ዐፄ ዮሐንስ ዘንድ ካለው ከባሻ ሃይማኖት የተጻፈ አንድ ደብዳቤ
ለከንቲባ አማን እንደ አመጣለት ደብዳቤው ፡ "የሐበሾች ፍላጎት ከኢ
ጣሊያኖች ጋር ሰላም ማድረግ ነው" የሚል መሆኑን ይገልጽና ይኸው
ቃል ሲቀርብለት ዤኔራሉ "ሰላም ከፈለጉ ንጉሡ በቀጥታ ለኔ መጻፍ
አለባቸው" ብሎ ለአማን እንደ ገለጸለት ፡ አማንም ይኸንኑ አሳብ
ለባሻ ሃይማኖት ከላከ በኋላ ፡ በመጋቢት 1880 ዓ ም. ከማታው በአንድ
ሰዓት ወደ አይለት በሚወስደው መንገድ ላይ ልጅ ወሰንና ልጅ ዜና
(ዘይኑ) ባሽከሮቻቸው ታጅበው የንጉሡን ደብዳቤ ይዘው መምጣታ
ቸውን በማመልከት ፡ ደብዳቤውን ወደ ኢጣልያንኛ አስተርጉሞ ያነ
በበው ቃል ዋና ዋናው ፍሬ ነገር ከዚህ እንደሚከተለው መሆኑን
ይገልጻል ።

1ኛ. ንጉሡ ነገሥቱ ከንጉሡ ኡምቤርቶ ቀዳማዊ ጋር በደብዳቤ
ልውውጥ የወዳጅነት ግንኙነት ፈጥረው እንደነበረ ፡ በቅርብ ከማ
ገኘው ከአሰቡ አስተዳዳሪ ከጂዎቫኒ ብራንኪ ጋር ቁም ነገር ያለው
ብዙ የወዳጅነት አሳብ እየተለዋወጡ ብራንኪም ከርሳቸው ጋ
የከረምቱን ወራት ያሳልፍ እንደ ነበረና በዚሁ ጊዜ በአሰብ በኩ
ከትግራይና ከሸዋም ነጋዴዎች እየተመላለሱ ከኢጣልያ ነጋዴዎች ጋ
እንደ ልባቸው የንግድ ልውውጥ የሚያደርጉበትን ሁሉ ተነጋግረ
እንደ ነበረ ፡ ከዚህም በቀር ኢትዮጵያውያንና ኢጣሊያኖቹ እን

---

* አይባ የሚገኘው አምባ አላጌ አጠገብ ነው ።

** እነዚህ ሁሉ የራስ ወልደ ሚካኤል ጋብቾች ወይም ተወላጆች ናቸው ። ራ
ወልደ ሚካኤል ከቀድሞ ዠምሮ ባላቸው ቅራኔ ባፄ ዮሐንስ ትእዛዝ ከስር
ይገኛሉ ።



አንድ አካል ሆነው ዐረመኔዎቹን (እስላሞችን) በመውጋት ግዛታቸ
ውን በኅብረት ለመግዛት የነበራቸውን ምኞት ገልጸውለት በመጨ
ረሻ እንደ ወዳጃቸው ቆጥረው እንከባከበው ካስተናገዱት በኋላ ሲለ
ያዩ ኒሻን ሸልመው እንዳሰናበቱት ፤

2ኛ. ከርሱ በኋላ ቢያንኪ (ጉስታቮ) የመጣ ጊዜ ይኸንኑ ጉዳይ
ተነጋግረው ለኢጣሊያ ንጉሥ የወዳጅነት ደብዳቤ መላክ ብቻ ሳይ
ሆን ፡ በዚሁ በተከበረው የኢጣልያ ንጉሥ ውስጥ ላሉት መኳንንት የኒ
ሻን ሽልማት መላካቸውንና ከርሱም ቀጥሎ እምባጫራ ሳሉ አንድ
ሰው (ፒሴግሪኖ ማቲዎች) ከኢጣልያ ንጉሥ ዘንድ ገጸ በረከት ይዞ
ላቸው ቢመጣ ፡ እሱንም በሽልማት አስደስተው ከኢጣሊያኖች ጋር
ሊወዳጁ የሚችሉበትን ደብዳቤ ሰጥተው እንዳሰናበቱት ፡

3ኛ. ይኸን በመሰለ የወዳጅነት ግንኙነት እያሉ ሳለ ፡ በእንግሊ
ዞች አማካይነት ከግብጾች ጋር ያደረጉትን ውል ኢጣልያኖች ሽረው
የኢትዮጵያን ነጋዴ በምጥዋ ሲያልፍ አለአግባብ ቀረጥ ማስከፈላቸ
ውን ፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ከግብጾች የተረከባቸውን ሥፍራዎች መያ
ዛቸውን ጠቅሰው አሁን ግን ፡ እንግሊዞች ከግብጾች ጋር ያዋዋሉዋ
ቸውን ውል ኢጣሊያኖቹ እንዲያከብሩና ከእግዚአብሔር የተሰጣቸ
ውን የኢትዮጵያን ግዛት ለቀው በራሳቸው ግዛት (በኢጣሊያ ግዛ
ታቸው) እንዲረጉ ፡

4ኛ. እግዚአብሔር ኃይሉን ቢሰጣቸው እርሳቸው ካንድ ወገን
ኢጣሊያኖቹ ከሌላ ወገን ሆነው ፡ በሕብረት አረመኔዎቹን ደርቡሾችን
አጥፍተው ግዛት ማስፋፋቱ ለሁለቱም ወገኖች ጠቃሚ መሆኑንና
እርሳቸው እንደ ኢጣሊያኖች ክርስቲያን በመሆናቸው ወንድማማች
ሆነው ሳለ ፡ የሁለቱ ጠብና ውጊያ ለሌሎች (ለጠላቶች) መሣለቂያ
መሆኑን ፡

5ኛ. ራስ አሉላ ሳይጽፉላቸው ስላደረጉት ነገር (የዶጋሊው ጦር
ነት) ከነርሱም (ከኢጣሊያኖቹ) ምንም እንዳልደረሳቸው ፡ ይኸም
የደረሰው ጦርነት የሰይጣን ሥራ መሆኑን ከሁለቱም ወገን የሞቱት
እግዚአብሔር ቢፈርድ መሆኑን ኡምቤርቶም ፡ እሳቸውም ነገሥታት
ስለሆኑ ከሁለቱ የበላይ ዳኛ ቢኖር ኀቤቱታ ለማቅረብ መብት እንደ
ነበራቸው ከአመለከቱ በኋላ ፡ አሁን ለውጊያ ወደ ሰሐጢ የመጡት
ያገራቸውን መወረር ስለሰሙ ድንበራቸውን ለመጠበቅ መሆኑን ገል
ጸው አሁን ግን ፡ "እያንዳንዳችን በየሥፍራችን እንርጋ የምጥዋም ወደብ
እንደ ቀድሞው ክፍት ሆኖ በሁለቱም ወገን ያለው ነጋዴ እንደልቡ
እየነገደ እንጀራውን (ትዳሩን) ያቃና መልሱም በቶሎ ይምጣልኝ"
ሲሉ መደምደማቸውን ሸክ መሐመድ አሊ ያመለከታል ።

ዠኔራል ሳን ማርሳኖ ፣ ይህ ደብዳቤ ሲደርሰው አሳቡን ከአለቆቹ ጋር በቴሌግራም ከተመካከረ በኋላ ፣ መልሱን ከዚህ እንደሚከተለው ለንጉሠ ነገሥቱ ጻፈላቸው ።

“. . . የኔም የኃያሉ ንጉሤ የኡምቤርቶ ቀዳማዊ አሳብ ከኢትዮጵያና ከንጉሧ ጋር በሰላምና በወዳጅነት ለመኖር ነው ። ስለዚህም የጦርነቱን ሁኔታ አቁሞ በሰላም ለመደራደርና በዕርቅ ለመፈጸም ዝግጁ ነው ። ይኸም የሚሆነው አንደኛ በሐባብ ዐረቦችና በአሳሁርታ ነገዶች ላይ የኢጣሊያ የበላይ ጠባቂነት በኢትዮጵያ ዘንድ ሲታወቅ ። ሁለተኛ የሰሐጢ የዊአ የአይለት እስከ ቀይ ባሕር ድረስ ያሉት ወረዳዎች የኢጣሊያ ግዛት እንዲሆኑ የኢትዮጵያ ወሰን ጊንዳ እንዲሆንና ወሰኑ ወደፊት በስምምነት እንዲከለል ።

“ይኸን ውል የተቀበሉ እንደሆነ ገዥው ንጉሤ ከግርማዊነትዎ ጋር ለሁለቱም ወገን ጥቅም የሚሰጥ የንግድና የወዳጅነት ውል ለማድረግ ዝግጁ ናቸው ። ስለዚህ ይኸን የውል አሳብ ግርማዊነትዎ የሚቀበለው እንደሆነ የሚያምኑትን ሁነኛ ሹምዎን ወደ ሰሐጢ መቀመጫዬ እንዲልኩልኝና ከርሱ ጋር ስምምነቱን እንድንፈጽም እለምንዎታለሁ ። ሰሐጢ መጋቢት 30 ቀን 1888 ዓ.ም”

ይህ ደብዳቤ ከደረሳቸው በኋላ ፣ ከመኳንንቶቻቸው ጋር መከረው ዘከረው ፣ ዐፄ ዮሐንስ የመለሱት ደብዳቤ ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

“ከእንግሊዞችና ከግብጾች ጋር እንደ ተደረገው ያለ ስምምነት ከናንተም ጋር ታርቀን የምንስማማ መስሎኝ ነበር ። ባለፈው የጸፍሁት የወዳጅነት ደብዳቤ ከልብ ያፋቅረናል ብዬ አስቤ ነበር ። በምን ምክንያት ነው የቀድሞው ውል (የሒዊት) የሚፈርሰው። እሱስ ከፈረሰ ምን የሚያስማማን ነገር ይኖራል ? አምላክ የናንተን ከባሕር ወዲያ እስከ ሮማ የኔን መንግሥት (ኢትዮጵያን) ከባሕር ወዲህ አድርጎ ስለሰጠን የሚያጣላን ነገር ሊኖር አይገባም ነበር ። አባቶቼ ነገሥታቱ ያወረሱኝን ክርስቶስ የሰጠኝን መሬት እንደምን ጽፌ አትሜ ተዋውዬ እለቃለሁ? እናንተ ከወዲያ እኔ ከወዲህ ሆነን የሚያገናኘንና የክርስቲያን ደም በከንቱ የሚያፋስሰን ነገር አልነበረም ። ከእንግዲህ ወዲያ ግን የኔም መላክተኛ ወደናንተ አይመጣም የናንተም ወደኔ አይመጣም ። ”[1]

1 R. Battaglia, La Guerra d'Africa, pp. 319.
ያማርኛው ደብዳቤ ስለ አልተገኘ ከዚህ በላይ የሠፈረው ከኢጣልያንኛው ትርጉም ወደ አማርኛ የመለስሁት ነው ።



ይህ በዚህ እንዳለ ፣ ይኸን ያፄ ዮሐንስን ቁርጠኛ ደብዳቤ ያመጣው ሰው (ልጅ ወሰን) በቃል ንጉሠ ነገሥቱ በራስ አሉላ አድራጎት ማዘናቸውን ወደፊት ለጣልያኖቹ የሚመች ሹም ለመሾም ዕቅድ እንዳላቸው አሁን ግን ፣ በመኳንንቶቻቸው ፊት ለመፈጸም የሚቸገሩበትንና (የሚያፍሩበትን) የመሬት ጥያቄ ኢጣልያኖቹ በጽሑፍ እንዲያረጋግጡ አይጠይቁዋቸው እንጂ ፣ የያዙትን መሬት (ሰሐጢንና ዊዓን) ለኢጣሊያኖቹ ለመልቀቅ ፈቃደኛ መሆናቸውን ፣ ይኸንንም የሚፈጽሙት ከደርቡሾች ጋር የሚያደርጉት ጦርነት ከተፈጸመ በኋላ መሆኑን ለዠኔራሉ እንደ ተናገረ በጽሑፍ አስፍረውት ይገኛል ።

የሆነ ሆኖ ፣ ዤኔራል ሳን ማርሳኖ ላፄ ዮሐንስ የላከው የዕርቅ ድርድር አንባቢ እንደሚያስታውሰው ፣ ከዚህ በፊት ኢጣሊያኖች በእንግሊዝ መንግሥት መላክተኛ በጄራልድ ፖርታል አማካይነት አቅርበው ሳይቀበሉ የቀረው ነው ። አሁንም የቃል መልእክት የተባለው እውነትም ይሁን ሐሰት ዋጋ የሌለው ሲሆን ፣ ከዚህ በላይ የጻፉት ደብዳቤ እንደሚያስረዳው ግን ፣ ምንም ዐይነት መሬት ቆርጠው ለመስጠት አለመፍቀዳቸውን በትክክል ገልጸዋል ።

የዕርቁ ነገር በዚህ በመጨረሻው ቁርጠኛ ንጉሣዊ ደብዳቤ ከተዘጋ ወዲህ ባንድ ወገን ኢጣልያኖቹ ፣ “እንግዲህ በምሽጉ ላይ የንጉሠ ነገሥቱ ሠራዊት ጦርነት ይከፍታል” የሚሉ ሥጋት ስለ ነበራቸው ፣ ሁሉም በተጠንቀቅ ላይ ነበሩ ። በሌላ ወገን ደግሞ ፣ በምሽጋቸውና “በዘመናዊ መሣሪያቸው በመተማመን አበሾቹ ከውጭ ሲወጉን እንደ ልባችን ከውስጥ በብዛት በሚተኮስ የመድፍ ፣ የመትረየስና ጠመንጃ ጥይት እንፈጃቸዋለን” በሚሉ ዓላማ ፍርሃት በተደባለቀበት ሁኔታ ሲጠባበቁ በማግሥቱ መጋቢት 23 ቀን ያንድ ክፍል ጦር ከምሽጉ ብቅ ብሎ ሲሰልል ብዙ የኢትዮጵያ ጦር በዲግዲግታ በኩል ግርግር ይል ነበር ። በመጨረሻ ይኸውም ማለት በማግሥቱ ከሚያዝያ 2 ቀን እስከ 4 ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ የሐበሻ ጦር የጊንዳን መንገድ ይዞ ወደ አሥመራ እየተዥጐደጐደ ሲሔድ ታየ ።[1] ይኸም ለኢጣሊያ የጦር ሠራዊት ታላቅ የዕፎይታ መንገድ ፈጠረለት ።

በዤኔራል ሳን ማርሳኖ ግምት ንጉሠ ነገሥቱ ሳይዋዋሉም ፣ ሳይዋጉም ወደኋላ የመመለሳቸውን ምክንያት በምሽጉ ጽናት ፣ በአየር

1 L'Italia in Africa — Vol. Primo - Tomo VI - Documenti (1887—88) - G. Giglio' pp. 336—341. R. Battaglia, La Guerra d'Africa, p. 298.

ላይ ሲውለበለብ የታየው ትልቅ የኤሌክትሪክ ኳስ የጣለው ሥጋት በስንቅ ማለቅና ክረምቱ ገብቶ መንገዱንና ጉዞውን ሳያበላሸው ከቆላው ወደ ደጋው ለመመለስ አስበው መሆኑን አመልክቷል ። ይኸም በአጋማሽ እውነት ሊሆን ይችላል ። በተጨማሪ ግን ፣ እንዲመለሱ ያደረጋቸው የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በሣር ውሃ መሸነፍና የጐንደር መዘረፍ ፣ የአብያተ ክርስቲያናቱ መቃጠል ነበር ። የንጉሥ ምኒልክም አያያዝ እሥጋት ላይ ጥሏቸው ነበር ይባላል ።

የዚህን ሁሉ ሁኔታ ዤኔራል ሳን ማርሳኖ በየቀኑ በትጋት ላለቆቹ በቴሌግራም ያስተላልፍ ስለነበር ፣ የጦር ሚኒስትሩ "አንድ ዕውቅ የሆነ የማጥቃት ሥራ በኢትዮጵያ ጦር ላይ የመፈጸምህ ወሬ በንጉሡ በኡምቤርቶ የልደት በዓል ላይ ተነግሮ እኔም እኮራበታለሁና አስብበት" ብሎ ጽፎለት እንደ ነበረው ፣ አሁንም የኢትዮጵያ ጦር በሚመለስበት ጊዜ በጊንዳ በኩል የማጥቃት ዘዴ ለመሞከር ይቻል እንደሆነ ተጠይቆ ዤኔራሉ "የማይሆን ነው" ብሎ ስለ መለሰ ፣ "እንግዲያው ለወደቡና ለአካባቢው የሚበቃ ጦር ትተህ አንተ ብዙውን ጦር እንደ ያዝህ ወደ ሮማ ተመለስ" የሚል ትእዛዝ ስለ ደረሰው ፣ ዤኔራል አንቶኒዮ ባልዲሠራ የሚባለውን የታወቀ ዤኔራል ከ6000 ምርጥ ወታደሮች ጋር ትቶ እርሱ ወደ አገሩ በሰላም ተመለሰ ።[1] ከርሱም ቀደም ብሎ በመርከብ የተመለሰው የበላይ የጦር መኰንን ቁጥር 500 የተራው ወታደርና የበታች ሹማምንት ቁጥር 11.000 የጭነት ከብት (ፈረስና በቅሎ) ቁጥር 1400 ነበር ።

ዤኔራል ሳን ማርሳኖ ፣ ይኸ ሁሉ ድካም ተደርጎ ለዚህ ጉዳይ ከመንግሥቱ ሐያ ሚሊዮን የሊሬ * ገንዘብ ወጭ ሆኖ አንዲት አነስተኛ የማጥቃት ሥራ በኢትዮጵያ ጦር ላይ ሳይፈጽም እንደዚሁ በምሽጉ ተደብቆ በመመለሱ ፣ ብዙ መማክርትና ጋዜጠኞች ወቅሰውት ለርሱም ለወታደሩም የተደረገለት አቀባበል የቀዘቀዘ ነበር ። የሆነ ሆኖ ፣ የኢጣሊያ ጦር በወታደርነት መስከ ያጣውን አሁን ዐፄ ዮሐንስ ስይዋጉም ፣ ሳይታረቁም ተመልሰው ወደ ትግራይ ስለ አመሩ ፣ ከዚያም ወደ ጐጃምና ይልቁንም ወደ መተማ ጦርነት ስለ ሔዱ ፣ ለኢጣልያ ወረራ በጊንዳ በኩል ወደ አሥመራ ፣ በአይለት በኩል ወደ ከረን ለመዝለቅ መንገዱ ሁሉ ክፍት ሆነለት ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ፣ አሁን ካለንበት ዘመን እንደምንመኘው በኢኮኖሚ የደረጀ አንድነቱ የጸና ፣ ከዘመናዊ ሥልጣኔ ያልራቀ

1 A. Del Boca, Gli Italiani in Africa, p. 296.

* አንድ ማሪያ ቴሬዛ ብር በዚያን ዘመን 5 ሊሬ ይመነዘራል ።



ቢሆን ኖሮ ጣሊያኖች ለማስፈራሪያ ብቻ ከእንግሊዝ አገር በቅርብ አምጥተው ባመጡት የኤሌክትሪክ ኳስ ጦሩ ሳይሸበር ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከመቀሌ ቤተ መንግሥት ወይም ከአሥመራ ከተማ ሳይነቃነቁ የነራስ አሉላ ፣ የነራስ ኃይለማርያም ጦር ከአይለት የሰሐጢን ምሽግ ወደ ግራ ትቶ በዶጋሊና በምንኩሎ በኩል በቀኝ በዊዓና በአርኪቆ በኩል ወደ ግራ ተጠምዞ በሩቁ በመከበብ ስንቅና መሣሪያ የሚገኝበትን የምጥዋን ወደብ ከሰሐጢ የሚያገናኘውን መንገድና ሐዲድ ቢያፈራርሰው ኖሮ በሰሐጢ የመሸገው ጦር በቀን ብዛት አንድም እጁን ለመስጠት ፣ አለዚያም ከምሽግ ወጥቶ ለመዋጋት መገደዱ አይቀርም ነበር ። ከምሽግ ወጥቶ ከተዋጋም በጦር ሠራዊት ብዛት የኢትዮጵያ ጦር ከሰባት እጅ በላይ ስለ ነበረ ፣ ባለፈው ዓመት በራስ አሉላ መሪነት ዶጋሊ ላይ የተጀመረው የድል ምዕራፍ በዚህም ጊዜ መደገሙ የማይቀር ነበር ።

ዳሩ ግን ፣ እንደ ኢትዮጵያ ያለ በማናቸውም መስክ ኋላ ቀር የሆነ መንግሥት በዚያ በቆላ በረሃ 150.000 ጦር ይዞ እንኳን ለረጅም ጊዜ ለአጭርም ቀን ቢሆን ለሠራዊቱ የሚሆን ምግብና መጠጥ ለእንስሳው (በቅሎ ፣ አህያና ፈረስ) ወሃና ሣር የማግኘቱ ጉዳይ ከፍ ያለ ችግር ነበር ። ስለዚህ ወደኋላ ከተመለሱባቸው ምክንያቶች አንዱ ይኸው መሆን አለበት ። ከዚህም ጋር ኗሪው ሕዝብ በስንቅ አቀራረብና በወሬ አነጋገር የወገኑን ዘማች ሠራዊት ካልደገፈ ተጨማሪ ችግር ነው ። የአይለትና የአካባቢው ይኸውም ማለት የሐባብና የቦጎስ ፣ የመንሳና የአሳውርታ ነገድ እስላማዊ ሕዝብ ስለሆነ ፣ በዚያን ጊዜ የኢጣሊያኖቹ ባለሥልጣኖች ከየአንዳንዱ ባላባት ጋር በቀጥታ የጠባቂነት ውል እየተዋዋሉና ለየአንዳንዱ የጎሳ ባላባት የወር ቀለብ እየሰጡ አቀራርበዋቸው ነበር ። ለምሳሌ ለሐባቡ ባላባት ለከንቲባ ሐመድ (እህመድ) ቀለብ 500 የማሪያ ቴሬዛ ብር በወር እየከፈሉ ከሐባብ ወደ ምጥዋ ከባለሥልጣኖቹ ለመገናኘት ሲመጣ በሰልፍና በሙዚቃ እየተቀበሉ አከባብረውታል ።[1]

በተጨማሪም ካፄ ዮሐንስም ፣ ከራስ አሉላም ጋር በሹመትና በግልቂም እየተጣሉ ወደነርሱ የሚጠጉትን የክርስቲያን መኳንንትና ሹማምንት ጣሊያኖቹ ሹመትና ማዕረግ እየሰጡ የወር ቀለብ እየወሰኑ መሣሪያ አድርገዋቸዋል ። በዚህ ሁሉ ምክንያት ያፄ ዮሐንስ ዕርቅ ፈላጊነትም ሊሳካ ባለመቻሉ ፣ ሳይዋጉ አንዳንድ ታማኝ ያልሆኑ ዜጋዎች ከነበሩበት አካባቢ ተነሥተው ወደ መጡበት መመለስ ምርጫ የሌለው ውሳኔ እንደሆነ በግልጽ ይታያል ።

1 Angelo Del Boca, Gli Italiani in Africa Orientale, pp. 265—266.

# ምዕራፍ ዐርባ አራት

## ዐፄ ዮሐንስ ከሰሐጢ ወደ መቀሌ መመለስ — የመንግሥታቸው መዳከም — ከደርቡሾች ጋር የሞከሩት መቀራረብ አለመሳካት

ዐፄ ዮሐንስ ፣ ከደብረ ታቦር በየካቲት ወር 1880 ዓ.ም. ተጉዘው በመጋቢት ወር ላይ ሰሐጢን ከበው ከሰነበቱና ውጊያውም ፣ የዕርቁም ስምምነት ሳይሳካ ስለቀረ በመጋቢት ወር መጨረሻ ላይ ወደ አሥመራ ተጉዘው ፣ ከዚያም በሚያዝያ ወር ዐድዋ ገብተው ከነራስ ሚካኤል ፣ ከነራስ ሐጎስ ፣ ከነደጃች ደብብ ጋር ስለ ወደፊት ሁኔታ ሲመካከሩ ሰነበቱ ። በዚህ ጊዜም በቤጌምድርና በጐጃም ፣ በወሎና በሸዋ ስለ ነበረው ሁኔታ ሲጠያየቁ ፣ ወደ ሰሐጢ ጉዞ በዠመሩበት ወቅት በጥር 10 ቀን የተፈጸመውን የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን በማር ወሃ መሸነፍና ፣ ስለ ተማረኩት ልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ደኅንነት ከሱዳኖች ጋር መጻጻፋቸውን ሰሙ ። እንደዚሁም ወደ ቤጌምድር ብቅ ብለው ደርቡሾቹን እንዲጠባበቁ የታዘዙት ንጉሥ ምኒልክ በአዘዞ ጠላታቸውን ለማስፈራትና ወዳጃቸውን ለማስመካት የሚያስችለውን ወታደራቸውን ከግባት ተኩስ ጋር ከአሰለፉ ወዲህ ፣ ወደ እምባሜራ መዝለቃቸውንና ከሠራዊታቸውም አጋማሹን ወደ መተማ ጠረፍ ከአስማሩ በኋላ ምኒልክ የመተማን ወሰን አልፈው ደርቦሾቹን በማጥቃት ፈንታ በምስጢር ተነጋግረው መለያየታቸውንና ፣ "ጣልያንንም ያስመጡ እርሳቸው ናቸው ፣ አሁንም በወሎና በቤጌምድር ባለፉበት ጊዜ ሁሉንም በስጦታና በሽልማት እየሸነገሉ ወደ ራሳቸው ወሰዱት ፣ አሁንም ወደዚህ ወደ ትግራይ ቢጠሩ ፣ ሁሉም ግልብጥ ብሎ ወደሳቸው ይሔዳል" የሚለውን ወሬ በዝርዝር ሳያዳምጡት አልቀሩም ።

ሆኖም ሁሉንም በትዕግሥት እየሰሙ ከመኳንንቶቻቸው ተማከረው በመጨረሻ ምኒልክን ወደ ዐድዋ ወይም ወደ መቀሌ ቤተ መንግሥታቸው ጠርተው ፣ የወሬውን ሐሰትና እውነት በጥያቄ በምርምር በመረዳት ፈንታ በሚያዝያ ወር ላይ በደፈናው ፣ "በመጣችሁበት መንገድ ወደ አገራችሁ ወደ ሸዋ ተመለሱ" የሚል የደብዳቤ መልእክት ወደ ምኒልክ ላኩ ። 'ወደ ዐድዋ ወይም ወደ መቀሌ ጠርተው እንገናኝና ሁሉንም እንመካከር በማለት ፈንታ ሠራዊቴን አድክሜ እዚህ

ከደረስሁ በኋላ እንደ ምን ተመለስ አሉኝ? ይኸማ የጠብ መሆኑ ነው’ የሚል ሥጋት በምኒልክ ላይ አደረባቸው ። በመጣችሁበት መንገድ ተመለሱ ማለት በደብረ ታቦርና በወሎ የመንገድ መስመር ማለት ነው። ያገራችን ጸሐፊዎች እነአቶ ዐጥሜ ይኸኛውን መስመር ስወስድ ከጀርባ በግሥጋሤ ደርሰው ሊወጉኝ ይችላሉ በሚሉ ሥጋት በጐጃም እንድሔድ ይፍቀዱልኝ ብለው ንጉሠ ነገሥቱን ጠየቁ ለማለት እንደዚህ ቢሉ አቅርበውታል ።

. . . . . ንጉሥ ምኒልክ ግን ፡ የተላከባቸውን ደብዳቤ አይተው ዐፄ ዮሐንስ ለጠብ እንደ ፈለጓቸው ተረዱትና በብርቱ ካሰቡበት በኋላ ፡ በመጣሁበት መንገድ ስመለስ ገሥግሠው መጥተው ቢቆዩኝስ ዳግመኛ እጅ ልነሣ ያውም ለወቀሳ ለከሰሳ ይኸስ የማይሆን ነገር ነው ብለው “እባክዎ ጃንሆይ በጐጃም አድርጌ ወደ ሸዋ እንድመለስ ይፍቀዱልኝ” የሚል ደብዳቤ ጽፈው በግሥጋሤ ላኩ ። ዐፄ ዮሐንስም ከመኳንንቶቻቸው ጋር መክረው ንጉሥ ምኒልክ በጐጃም አድርገው ወደ ሸዋ ለመመለስ ቁርጥ አሳብ አድርገው እንደሆነ በመጡበት ይመለሱ ብንላቸውም አይመለሱም ። ብንገሠግሥም አንደርስባቸውም ሠራዊታችንም በሰሐጢ (ጉዞ) ተጎድቷልና (ብንዋጋም) አንችላቸውም ። ስለዚህ በጐጃም እንዲሔዱ ቢፈቀድላቸው ይሻላል ተባለና በጐጃም ይሒዱ የሚል ፈቃድ መጣላቸው ወደ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ለንጉሥ ምኒልክ መንገድ አትከልክል ስንቅም ስጥ የሚል ትእዛዝ አለፈላቸው ። [1]

ንጉሥ ምኒልክ ሸዋም ፡ ወሎም ፡ አዘዞና አምባጫራም ሳሉ ብዙ ነገር ቢወራባቸውም ፡ በመሠረቱ ከኢጣልያ ጋር ዕርቁ ከሳተ ወዲህ “ወደርስዎ መጥቼ ጦርነቱን ልካፈል” ብለው ላፄ ዮሐንስ እንደጻፉ የሚያስረዱ ብዙ ሰነዶች አሉ ። በእርግጥም መጻፋቸውን ንጉሠ ነገሥቱ በራስ ዳርጌ አማካይነት ከምኒልክ ጋር ወደፊት እንደምናነበው በሚወቃቀሱበት ጊዜ በጽሑፍ አረጋግጠዋል ። ስለዚህ ምኒልክ ከሸዋ ወደ ቤጌምድር የዘመቱት በንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ መሆኑ ግልጽ ሲሆን ፡ “ጦርነቱን መጥቼ ልካፈል” ብለው ከጻፉላቸውና ከሔዱ በኋላ እርሳቸው “በጉዞ ተቸገርሁ ሠራዊቴ ተራበብኝ ፡ በሽታም ጥር ላይ ተነሥቷል ። ወዳገሬ ወደ ሸዋ ልመለስ ይፍቀዱልኝ” ብለው ሳያስቸግሩ ፡ ዮሐንስ ምኒልክን “ለምን በመጣህበት መንገድ ተመለስ

1 አቶ ዐጥሜ ፡ የጋላ ታሪክ ፡ ገጽ 165 ። ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወ.ሥላሴ ፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐድዋ ጦርነት ፡ ገጽ 141 ።



አሉዋቸው? በመጀመሪያ ወደ ሰሐጢ ለጦርነት ሲጓዙ ወደፊትም ወደ መተማ ሲዘምቱ ምኒልክን አጠገባቸው ግንባር ቀደም አድርገው ለምን አላዋጉዋቸውም? የእምቢታ ወይም የልግም መልክ ቢያሳዩ እዚያው በትግራይ አካባቢ ባሉበት ሰዓት ለምን እጃቸውን አላስያዟቸውም? ከኢጣልያኖች ወይም ከደርቡሾቹ ጋር የተመሳጠሩበት ሰነድ እንዳለ በዐድዋ ወይም በመቀሌ ቤተ መንግሥት አደባባይ አቅርበው አስከሰሰው ለምን አላስፈረዱባቸውም? ሰነድስ ቢጠፋ ለምን የሰው ምስክር አላስቀጠሩባቸውም?” የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል ።

ከዚህ አሁን ካለንበት 20ኛው መቶ ዓመት ዘመን ላይ ሆነን ጉዳዩን ስንመለከተው ፡ የአንድነቱ መሠረት በጸና የማዕከላዊው መንግሥት ፡ ጣራና ግድግዳው በደንብ በተዋቀረና በሠለጠነ መንግሥት ውስጥ አንዱ መስፍን ወይም ጄኔራል ከጠላት ጋር ሲመሳጠርና ይኸውም መመሳጠሩ በሰነድ ወይም በቃል ምስክር ሲረጋገጥ ተይዞ በከሐዲነት ከፍ ያለ ቅጣት ይፈጸምበታል ። ጥርጣሬው በማስረጃ ያልተደገፈ እንደሆነ ባይሆን ከሥልጣኑ ታግዶ ይቆያል ። ነገር ግን ፡ ባለፉት ምዕራፎች እንደ ተረዳነው ፡ ኢትዮጵያ በተለይ በዚህ በ19ነኛው መቶ ዓመት ዘመን የዚህን ዐይነት የመንግሥት አቅዋም ለማግኘት ዕድል አላገኘችም ። የዚህ የ19ነኛው መቶ ዓመት አንድነቷ በመካከለኛው ዘመን ከነበራት አንድነት የባሰ የላላ ነበር ማለት ይቻላል ። በዚያን ዘመን ሁልጊዜ ዐልፎ ዐልፎ የሚሸፍት ባይጠፋም ፡ ሁሉም ባንድ ንጉሠ ነገሥታዊ ዘር ተጠቃሎ ይገዛል ። የቀሩት መሳፍንት እንዳያስቸግሩ በአምባ ግሽን ተራራ ወይም በወህኒ ይጠበቃሉ ።

በዘመነ መሳፍንትና የዘመነ መሳፍንት ሥልጣን ባፄ ቴዎድሮስ አገዛዝ ካከተመ ወዲህ ፡ ባለው ቅርብ ጊዜ ውስጥ ሥልጣንን የሚያረጋግጠው የጦር ኃይል ብዛትና የመሪው ዘዴ ብቻ ነው ። በዚህ ጊዜ አንዱ በራሱ ንጉሠ ነገሥታዊ መሪነት ኢትዮጵያን ለመገንባት ሲነሣ ወይም የራሱን ሥልጣን ሲያጠብቅ ፡ ሌላው ወደዚህ ሥልጣን ለመውጣት ያተኮረው ባላንጣ ያፈርሰዋል ። በሁለት የዙፋን ባላንጣ መካከል የተደረገው መሐላም ሆነ ጋብቻ በምንም ዐይነት አያስቀረውም። ዐፄ ዮሐንስ ደጃዝማች ካሣ ሲባሉ ዠምሮ በቴዎድሮስና በተክለ ጊዮርጊስ ላይ የፈጸሙት አሁን ምኒልክ በርሳቸው ላይ ሲፈጽሙት የሚታየው ነው ። እንዲያውም ካሳ (ዮሐንስ) በተክለ ጊዮርጊስና በቴዎድሮስ ጊዜ ከፈጸሙት ግልጽ ሽፍትነት በ1870 ዓ.ም. ከተስማሙ ወዲህ ፡ አሁን ምኒልክ በዮሐንስ ላይ የሚያሳዩት ግፈንጥቅ ለዘብና ለስለስ ያለ ፡ በአብዛኛው የሐሳብ ፡ የፖለቲካና የዘዴ ትቃውሞ ነው ። ቀድሞ በእቴጌ ድንቅነሽ በኩል በዮሐንስና በተክለ ጊዮርጊስ መካከል የተደረገው የጋብቻ ዝምድና ውጤት እንዳልሰጠ

አሁንም የወይዘሮ ዘውዲቱና የራስ አርአያ ጋብቻ የሁለቱን ነጋሥያን ባላንጣነት አላስቀረውም ።

ቢሆንም ፣ በሁለቱ መሪዎች መቻቻልና ትዕግሥት በመካከላቸው የይፋ ጦርነት ሳይደረግ ሁለቱም እየተጠባበቁ ፣ እየተሰላለሉ የባላንጣቸውን ኃይል ከማዳከም ጋር የየግል ጦራቸውን በማጠባበቅ እዚህ ጊዜ ላይ ደርሰዋል ። እላይ በጥያቄ መልክ ዮሐንስ ምኒልክን ወደ መቀሌ ጠርተው ይኸን አድርገሃልና ተፋረድ ፣ ተቀጣ ፣ ታሰር ፣ ተፈታ ለማለት ነገሩ ወደ ውጊያ ያመራል እንጂ በዚህ ጊዜ የሁለቱ የኃይል ተመጣጣኝነት አቅዋም አያስችልም ነበር ። ሁለቱማ በዚህ የተነሣ ቢዋጉ ኖሮ ለደርቡሾችና ለኢጣልያኖች ምን ያህል ባስደሰቱ ! ለሁለቱም በሰሜን ምዕራብና በሰሜን ምሥራቅ ለመግባት እንደምን በተመቻቸው! ይኸን አደገኛ ሁኔታ ሁለቱም በኃላፊነት አመዛዝነው ሁለቱ ለመጠቃቃት ሲሉ ለውጭ አገር ጠላት መሣሪያ መሆንን በተለይ በዚህ ጊዜ አይፈልጉትም ። አንዱም ሌላውን ለማሸነፍ ያለው ዋስትና የመነመነ መሆኑን ይረዳዋል ።

አሳባችንን ወደኋላ መለስ አድርገን ሁኔታውን ስናመዛዝነው ፣ ዐፄ ዮሐንስ በ1863 ዓ ም ከዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ጋር በ1866 እና 68 ከግብጾች ጋር ተዋግተው ከድል ወደ ድል በተራመዱ ጊዜ ራሳቸውም ባለግርማ ፣ ሠራዊታቸውም የሚያስፈራ ነበር ። በ1870 ዓ ም ወደ ሸዋ ምኒልክን ለማስገበር የመጡ ጊዜም የድል አድራጊነት ግርማቸው ገና የሚያስፈራበት ሰዓት በመሆኑ እንደነጎበና ዳጬና እንደ ነበሻህ አቦዬ ያለ ዠግና የሞላበት የሸዋ አገር ሊቋቋማቸው አልደፈረም ። ውጊያ ከመዠመር በፊት ጥንቃቄን የሚያበዙት ምኒልክም፣ ውስጡን እየነደዳቸው/ያትሙበት የነበረውን የንጉሠ ነገሥትነት ማኅተም አስጨፍልቀው ፣ የቀመሱትንና የጣማቸውን የንጉሠ ነገሥትነት ሥያሜ ለቀው ፣ በንጉሥነት እንዲረጉና ለወደፊቱ እንዲገብሩ ሲጠየቁና ሲቀበሉ በግዴታ እንጂ ፣ በልባዊ ፈቃድ እንዳልነበረ ግልጽ ነው ።

ከ1879 ዓ ም ዠምሮ በተለይ በ1880 ዓ ም ላይ ደግሞ ፣ አጻፋውን ያፄ ዮሐንስ የኃይለኝነት አቋም ቀስ እያለ ወደ ምኒልክ በመዞር ፣ ባፄ ዮሐንስ ዘንድ ከመቆየት የተነሣ መዳከም ቀስ እያለ ሥሩን ሲሰድ ይገኛል ። ወደ ስሐጢ የጦር ግምባር ሠራዊታቸውን በከተት ዐዋጅ አስከትተው ከሔዱ በኋላ ሳይዋጉም ፣ ሳይዋዋሉም እንደዚሁ መመለሳቸው ቅርታን እንዳሳደረባቸውና የደርቡሽ መነሣትና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መሸነፍ እንዳናደዳቸው አይጠረጠርም ። እንደዚሁም ወደ ስሐጢ ሲዘምቱ ታመው የነበሩት የሚወዷቸው ልጃቸውና አልጋ



ወራሻቸው ራስ አርአያ አሁን ከስሐጢ መልስ ወዲህ በሰኔ ወር መዠመሪያ ላይ ሞተው ተረዱ ። ከዚህም ጋር ከጠላት ጋር ሆኜ አገሬን አልወጋም ብለው ወደ ርሳቸው መጥተው ባለሟልና አማካሪ ሆነው የነበሩት ደጃች ደብብ አርአያ እኔን ወደጎን እየተዉ ደጃች መንገሻ ጉግሳን አክብረው የራስነት ማዕረግ ሰጧቸው በሚል ቂም ተመልሰው ወደ ነበሩበት ወደ ኢጣልያ ሠፈር ተጠግተዋል ። በነርሱም አማካይነት አደን ከሚቀመጠው ከእንግሊዙ አገረ ገዥ ከጀኔራል ሆግ እየተጻጻፉ ዮሐንስን ለንጉሠ ነገሥትነት እንዳቢቃችሁ እኔንም አግዙኝ እያሉ ከመጻጻፍ ላይ ይገኛሉ ።[1] በሚቀጥለው ጊዜ ደጃች ሥዩም ገብረ ኪዳንና የስቆጣው ባላባት ዳንጉል እየከዱ ወደ ምኒልክ ገቡ ። ባለሟሎችና ታማኞች ከነበሩት ውስጥ ደጃች ተድላ ከምኒልክ ጋር ፣ በጅሮንድ ለው ጤ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር በመላላክና ምስጢር በማውጣት እየተጠረጠሩ ታሰሩ ። ራስ ሐጎስ ቤገምድርን ከተሾሙ በኋላ የምኒልክ ወዳጅ ነው ተብለው ተሻሩ ። ባገርም ላይ ረኃብና በሽታ ተነሥቶ ብዙ ሰው አለቀ ። ከሁሉም የበለጠ ያሳዘናቸው ወደፊት የምናነበው የንጉሥ ምኒልክና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የከዳት ስምምነት ነው ። ስለዚህ ባሁኑ ጊዜ በኃይለኛውና በባለ ግርማው ንጉሠ ነገሥት ላይ ከዕድሜ መግፋት* ጋራ ጸጸት ፣ ንዴት ፣ ሐዘን ፣ ሥጋትና ጥርጣሬ በተቀራረበ ጊዜ ውስጥ ተደራርቦ ደርሶባቸዋል ማለት ነው ።

ቢሆንም ፣ ይኸን ሁሉ የደረሰባቸውን በሃይማኖታዊ መንፈስ በትዕግሥት ተሸክመው መንግሥታዊ ሥራቸውን አላቋረጡም ። አንድ ጊዜ ወደምነና ለመሔድ አስበው ባለሟሎቻቸው መክረው አስቀሩዋቸው ተብሏል ። ስለዚህ ዐድዋ ሳሉ መኳንንቱ ከነሠራዊቱ ወደየአውራጃው ተመልሶ የክረምቱን ወራት እንዲያሳልፍ ባሰናበቱበት ሰዓት የክርስትና ልጃቸውን ራስ ሚካኤልን ከራስ አሉላ ላይ የተገፈፈውን 500 ጠበንጃ ጨማምረው በጥቢው ለመገናኘት ተቃጥረው ወደ አገራቸው ወደ ወሎ አሰናበቷቸው ። በዚሁ ዐይነት ሌሎቹም ሲሰናበቱ ራስ ሐጎስም ወደ ሺሬ ተመለሱ ።

ራሳቸውም በዐድዋና በመቀሌ ከሚያዝያ እስከ ሰኔ በቤተ መንግሥታቸው ከቆዩ በኋላ ፣ በሰኔ ወር መጨረሻ ላይ ከመቀሌ ወደ ደብረ ታቦር መጡ ። በዚህ ጊዜ ነው እስካሁን በኢጋማሽ ግዞት ራስ አሉላን

1 L'Italia in Africa — Etiopia Mar Rosso — Documenti, Paris, (1888—1889) pp. 159, 160, 177.

* በ1880 ዓ.ም. ላይ የንጉሠ ነገሥቱ ዕድሜ 55 ዓመት ገብቷል ።

ካጠገባቸው ሳይለዩ አቆይተው የርሳቸውን የጦር ጠቅላይ አዛዥ ነት ከራስ ቢቶደድነት ማዕረግ ጋር ለታላቅ ወንድማቸው ልጅ ለራስ ኃይለ ማርያም የሰጧቸው ። ደጃች መንገሻ ጉግሣም የራስነት ማዕ ረግ ያገኙት ።[1]

በዚህ መካከል ፡ ንጉሠ ነገሥቱ በሰሐጢ በነበሩበት ሰዓት ለኢጣሊያኑ ጠቅላይ አዛዥ ለሳን ማርሳኖ ፡ "እኛና እናንተ ክርስቲያ ኖች ወንድማማቾች ነን ፡ የኛ መዋጋት ለጠላቶቻችን ለእስላሞቹ መጣ ለቂያ እንዳንሆን በሕብረት ተስማምተን ደርቡሾቹን ብንዋጋ ይሻ ላል" የሚል አሳብ አቅርበው እንደነበረ እናስታውሳለን ። ነገር ግን የኢጣልያ ባለሥልጣኖች በዚህ ጊዜ የሚከተሉት መሠረታዊ መመ ሪያ እስላሞቹን በሹመትና በገንዘብ እያባበሉ በማቅረብ ፡ በውል እያ ሰሩ 'የክርስቲያኖች ጦር እንዳያጠቃችሁ በውለታችን ተጋፍጠን የም ንጠብቃችሁ እኛ ነን' በማለት የነራስ አሉላን ጠበኞች ክርስቲያኖቹን ሳይቀር እያባበሉ ፡ ወደነርሱ በመሳብ የንጉሠ ነገሥቱ ጦር እንዲ ዳከም ሆነ ብለው የሚጥሩበት ጊዜ ስለነበረ ፡ ከኢጣሊያኖቹ ለመተ ባበር የሞከሩት ያፄ ዮሐንስ ምኞት የወሃ ላይ ኩበት ሆኖ እንደቀረ ባለፈው ተመልከተናል ።

ስለዚህም ፡ ከሰሐጢ ግንባር መልስ ምኒልክንም ፡ እነራስ ሚካኤ ልንም በየግዛታቸው እንዲመለሱ ከአደረጉ በኋላ ፡ ከደርቡሾቹ መሪ ከአብዱላሂ ጋር በደርቡሽ ሹማምንት በነ ሐምዳን አቡአንጋ አማካ ይነት ፡ "እኛና እናንተ አፍሪካውያን ሁላችንም የካም ልጆች ወን ድማማች ነን ። በዚህም ላይ ወሰነተኞችና ጐረቤቶች ስለሆንን ባንድ ነት ሆነን ነጮቹን እንቃወም" የሚል ደብዳቤ በመጻፍ በዚህም በኩል አዲስ የፖለቲካ መስሞር ከፍተው ነበር ። አብዱላሂ ግን ፡ ባንድ ወገን ዮሐንስ ባለፈው ዘመን ከማህዲስት ጠላቶች ጋር መተባበራቸውን በመገንዘብ ምኒልክ ስለ ሃይማኖት ጉዳይ ያላቸውን ትዕግሥት ወይም ግዴለሽነት በማመዛዘን ፡ "ምኒልክ ያስማሙን" የሚል መልእክት ከላከ ወዲህ በመጨረሻ ይግረምዎት ብሎ መደምደሚያውን ፡ "እኛና እናንተ ሕብረት የምናገኘው የክርስትና ሃይማኖትዎን ለውጠው የኔን ሃይማ ኖት እስልምናን ሲቀበሉ ብቻ ነው" የሚል የመጨረሻ መልስ ስለሰጠ ፡ በዚህም በኩል የመስማማቱ ነገር እንደዚሁ ውድቅ ሆነና ሁለቱም ለሚለየው ጦርነት ይዘጋጁ ጀመር ።[2]

---


1 C.P. Rosenfeld, Chronology of Menelik II, pp. 125—130.

2 Zewde G.S., The Process of the Reunification of the Ethiopian Empire, p. 525—533.

ጎሩይ ወልደ ሥላሴ ኢትዮጵያና መተማ ያፄ ዮሐንስ ታሪክ ባጭሩ ገጽ 11 ።







ዐፄ ዮሐንስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት

(ፐብሊክ ሪኮርድ ኦፊስ ፡ ለንደን)

# ምዕራፍ ዐርባ አምስት

### የንጉሥ ምኒልክ ጉዞ ወደ ጐጃም — የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና የንጉሥ ምኒልክ ዐፄ ዮሐንስን መከዳት — የደጃች ሥዩም ወደ ሸዋ መምጣት

ባለፉት ምዕራፎች እንደ ተረዳነው ፥ ምኒልክ በሚያዝያ 11 ቀን ጐንደር አጠገብ በአዘዞ ላይ ታላቅ ሰልፍ ከአሳዩ በኋላ ፥ በሚያዝያ 17 ቀን ወደ አምባጫራ መለስ ብለው ሠፈሩ ። በዚያም 22 ቀን ያህል ባንድ ወገን ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር እየተጻጻፉ ፥ በሌላ ወገን የሱዳንን ሁኔታ እያሰለሉ ፥ ወደ እንጦጦም ስለ አውሮፓ ወሬ ከነአንቶኔሊም ከእ ቴጌ ጣይቱም ጋር ይላላኩ ነበር ። በዚሁ ጊዜ አብረዋቸው የነበሩት ጸሐፊያቸው አለቃ ዮሴፍ ቀደም አድርገው እንጦጦም ፥ አንኮበርም ተዋ ውቀው ወዳጅነት ከወጠኑት ከኢጣልያኑ ወኪል ከአንቶኔሊ ጋር ይጻጻፉ ነበር ። በዮሴፍ ደብዳቤ ውስጥ አንዳንድ አዲስ ነገር ተጠቅሶ ይገኛል ።

በዚሁ በግንቦት ወር ከአምባጫራ ዮሴፍ ለአንቶኔሊ በጻፉለት ደብዳቤ ላይ ፥

አንደኛ— ዐፄ ዮሐንስም ፥ ራስ አሉላም ከሰሐጢ ወደ ዐድዋ መመለሳቸው እርግጥ መሆኑን ፥ ሰሐጢም ንጉሠ ነገሥቱ ለመ ዝመት ከተነሣሡባቸው ምክንያቶች አንዱ ባገር ላይ ድርቅ ተነሥቶ በረኃብ ሠራዊቱ ስለ ተቸገረ ፥ "እዚህ በችጋር ከምናልቅ ሔደን ከጠ ላት ጋር እየተዋጋን ብንሞት ይሻላል" ብሎ አቤት ስለአለ መሆኑን፥

ሁለተኛ— የንጉሠ ነገሥቱ ጦር ሰሐጢ ደርሶ ራቅ ብሎ በሠ ፈረበት ሰዓት የኢጣሊያ ጄኔራል የኤሌክትሪክ ኳስ በሰማይ ላይ እያ ውለበለበ ልክ እንደ ፀሐይ አድርጎ ቁልቁል የኢትዮጵያን ጦር ወለል አድርጎ በማሳየቱ ስለ አስደነገጠ ፥ ወታደሩ በድንጋጤ የሚያደርገውን አጥቶ እንደ ተቸገረና ፥ "ከሰው የጦር ሠራዊት ጋር እንዋጋለን እንጂ ከሰማይ ከወረደ ከእግዚአብሔር ጦር ጋር እንዴት እንዋጋለን" ብሎ መሸሹን ፥ የወሎና የቤጌምድርም ጦር ከሰሐጢ ወደ አገሩ ተመልሶ ጉብቶ ይኸንኑ በማውራቱ የሸዋንም ጦር ከፍርሃት ላይ መጣሉን ፥ የኢጣልያ ወታደሮች አንድም ጥይት ሳይተኩሱ የኢትዮ ጵያ ጦር ሲሸሽ በሩቅ እያዩ ዝም ብለው ይሥቁ እንደ ነበረ ፥

ሦስተኛ— ዐፄ ዮሐንስ በእርግጥ ጣልያኖቹን ወደ ምጥዋ ያስመጡ ምኒልክ መሆናቸውን ለማወቅ ፈልገው መኳንንቶቻቸውን ቢጠይቁ ደጃች ደብብ፤ "እንደ እውነቱ ምኒልክ እንደዚህ ያለ ስሜት የላቸውም" ብለው መመለሳቸውን፤ በዚህ ጊዜ የራስ አሉላ ባለሟልነት ወድቆ በርሳቸው ፈንታ ደጃች ደብብ ለንጉሠ ነገሥቱ ከባለሟሎቹ እንደ አንዱ መቆጠራቸውን፤* ጸሐፊው ያመለክታሉ ። [1] መቸም ዮሴፍ ይኸን ሁሉ የጻፉት ከያለበት በወሬ የሰሙትን እንጂ በሥፍራው ተገኝተው ባይናቸው ያዩት ፣ በጆሮአቸው የሰሙት ነገር አይደለም ። ዐፄ ዮሐንስም ወደ ሰሐጢ የዘመቱት የኢጣልያ ጦር የኢትዮጵያን ድንበር ዐልፎ ሰሐጢ ስለገባ፤ ያገራቱን የነጻነት ህልውና ለማስጠበቅ እንጂ ጸሐፊው እንዳሉት በረኃብ የተነሣ አለመሆኑ ግልጽ ነው ። ነገር ግን የረኃቡ እነሣሥ ተጨማሪ ሆኖ ወታደሩ ሔደን እንሙት ብሎም ይሆናል ።

ምኒልክም በበኩላቸው፤ ለዚሁ ለአንቶኔሊ በሚያዝያ 15 ቀን 1880 ዓ ም በጻፉለት ደብዳቤ ውስጥ በየካቲትና በመጋቢት ወራት ከኢጣሊያ አገር የመጣላቸውን ደብዳቤ ትርጉሙ በአማርኛ እንደደረሳቸው ገልጸው ስለ ዘመቻው ፤"ደርቡሾች ከመተማ መውጣት ፈርተዋል ፤ እኔም ወደ መተማ ለመዝመት እስቤ ሳለ ሰው ሁሉ በሚያዝያ ወር ላይ ኃይለኛ የወባ በሽታ መተማ አካባቢ መኖሩን ስለ ገሰጸልኝ ወታደሮቼ እንዳያልቁ ብዬ ቀረሁ" የሚል ይገኝበታል ።

ቀጥሎም ዐፄ ዮሐንስ ከርሳቸው ጋር የዘመቱትን የሸዋውን ጳጳስ አቡነ ማቴዎስን ራስ ሚካኤል ከትግራይ እየመሩ ወስደው፤ በወሎ አሳልፈው ወደ ሸዋ ደንበር እንዲያደርሱ አዘዙ ። ምኒልክንም ቤጌምድርን ለቀው በጐጃም እንዲያልፉ ከፈቀዱ በኋላ፤ ለቤጌምድር አጎታቸውን ራስ አርአያን ሾሙ ። እንደ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ አባባል ንጉሥ ምኒልክ በግንቦት 11 ቀን አምባጫራን ** ለቀው ወደ ጐጃም ጉዞ ዠምረው በደብረ ሚካኤል በጉማር በኩል አድርገው በግንቦት 24 ቀን ደብረ መዊዕ ሠፈሩ ። ደብረ መዊዕ የባለቤታቸው የወይዘሮ ጣይቱ እናት የወይዘሮ የውብዳር አገር ስለነበር፤ ወይዘሮይቱ ጡል ከሚባለው ወንዝ ላይ ሰፊ ዳስ አሠርተው ብዙ ድግስ ደግሰው ንጉሡን ከነሠራዊታቸው አስተናገዱ ። በዚያም ሳሉ፤ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት

* ለዳግመኛ ከመከዳታቸው በፊት ማለት ነው ።
1 L'Italia in Africa — Vol. Primo — Tomo VII — Documenti, Paris, (1888—1889) C. Giglio, - pp. 51—52.
** አምባጫራ የሚገኘው በጐንደርና በበለሳ መካከል ነው ።



መጥተው ስለነበረ፤ የምኒልክ ሠራዊት ተሰልፎ በታላቅ ክብር ተቀበላቸው ። ምኒልክ የጐጃምን መሬት እስኪለቁ ድረስ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እጅግ ያማረና የተደነቀ መስተንግዶ ሲያደርጉላቸው መሰንበታቸውንና አባይ አፋፍ ላይ ተሰነባብተው መለያየታቸውን ገብረ ሥላሴ ሲገልጹ፤ ሁለቱ ነገሥታት በዐፄ ዮሐንስ ላይ ያደረጉትን አድማ ዐውቀው ይሁን ሳያውቁ በዝምታ ዘለውታል ። [1] የሚመስለው ግን፤ የዚያን ዘመን ጸሐፌ ትእዛዝ የሰማውንና የሚያውቀውን ሁሉ ለመጻፍ ነጻነት ስላልነበረው፤ ወደ መዘዝ ላለመግባት ዐውቀው የተዉት ይመስላል ።

የሁለቱን ግንኙነትና ባፄ ዮሐንስ ላይ ማደማቸውን በቅድሚያ አቶ ዐጥሜ፤ ቀጥሎም ብላቴን ጌታ ኅሩይ ሰፋ አድርገው ዘርዝረውታል ። በነርሱም አባባል ንጉሥ ምኒልክ ጐጃም ሲደርሱ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንደ መጠርጠር ብለው መሸሸ ዠምረው እንደ ነበረ፤ በኋላ የፍቅር (የወዳጅነት) መልእክት ስለ ተላከባቸው፤ ተመልሰው መጥተው በደስታና በፍቅር እንደ ተቀበሏቸው ሁለቱም ሲገናኙ እንደ ወንድም በእኩልነት ደረጃ እንጂ፤ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አደግድገው ምኒልክን እጅ አለመንሣታቸውን፤ ሁለቱም ተቀምጠው በሚነጋገሩበት ጊዜ ሦስት ዙፋን እየተዘረጋ አንደኛው ለንጉሥ ምኒልክ፤ ሁለተኛው ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት፤ በመካከለኛው የነበረው አምሮ ተነጥፎ የንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ዙፋን ይባል እንደ ነበርና ንጉሥ ምኒልክ በዚያው ሰሞን በጐጃም በሚዘዋወሩበት ጊዜ ካህናቱ በወረብ ንጉሥ ምኒልክ ዐፄ የሚባሉበት ጊዜ ደረሰ ለማለት "ናሁ በጽሐ ጊዜሁ ለሣህለ ማርያም" * እያሉ ሲያሸበሽቡ ሴቶችም በዘፈን ያሞጋግሱዋቸው እንደነበረ ጠቅሰውታል ።

የሆነ ሆኖ፤ ሁለቱ ተገናኝተው በሚወያዩበት ጊዜ የልብ ምስጢራቸውን ተገላልጠው፤ ሁለቱም በንጉሠ ነገሥቱ ባፄ ዮሐንስ ተበዳዮች መሆናቸውን ተማመኑ ። ንጉሥ ምኒልክ "የኢጣልያን ጦርነት ለመከፈል ከሸዋ ሠራዊቴን አድክሜ በወሎና በቤጌምድር ዐልፌ አምባጫራ ሆኜ ደርቡሽን ስጠባበቅ፤ ጣልያንን ስቦ ያመጣ ምኒልክ ነው የሚላቸውን ነገረኛና ሰብቀኛ በመስማት ተገናኝተን እንመካከር ሳይሉኝ

1 ጸ.ት.ገ.ሥላሴ ታሪክ ዘመን ዘዳግ.ምኒልክ ። ገጽ 150 ።
* ሣህለ ማርያም የምኒልክ የክርስትና ስም ነው ። የምኒልክ የመንገሥ ይኸውም ማለት ንጉሠ ነገሥት የመባያው ጊዜ ደረሰ ለማለት ነው ።
2 ብ.ጌታ ኅሩይ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐድዋ ገጽ 142 ። አቶ ዐጥሜ የጋላ ታሪክ ገጽ 165-166 ። አፈወርቅ ገ/የሱስ ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ ፤ ገጽ 50-51 ።

ወደ መጣህበት ተመለስ ብለው ላኩብኝ” ሲሉ ፤ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ደግሞ ፤ “የደርቡሽን ጦር ብዛቱንና ብርታቱን እያወቁት አብረን ለመመከት የሺሬውና የጸለምቱ ገዥ ራስ ሐጎስ ከኔ ጋር ከተሰለፈ በኋላ ፤ እርሱን ከነጦሩ አስነሥተው በመውሰድና ብቻዬን ከደርቡሾች ፊት አጋፍጠው እንድሸነፍ አደረጉኝ ። ከተሸነፍሁ በኋላም እንኳን እግዚአብሔር ከሞት አተረፈህ ሳይሉኝ እኔን እንደ ጥፋተኛ በመቁጠር በከንቱ ሰው አስጨረስህ ብለው ወቀሱኝ” እየተባባሉ ሲነጋገሩ ፤ ውለው አድረው በመጨረሻው በተስነባበቱበት ቀን ከመስ ያየታቸው በፊት የሁለቱን ዙፋን ብቻ አድርገው በመካከል የነበረውን የንጉሠ ነገሥቱን ዙፋን ትተውት ጎን ለጎን ተቀምጠው ያያቸው የሸዋና የጎጃም ሰው ዐፄ ዮሐንስን መክዳታቸውን ተረዳው ይባላል ። ሲለያዩ ዐፄ ዮሐንስ ወደ ጎጃም የዘመቱ እንደሆነ ምኒልክ በቤጌምድር ብቅ ብለው ተክለ ሃይማኖትን ሊረዱ ፤ ወደ ሸዋ የመጡ እንደሆነ ተክለ ሃይማኖት በቤጌምድር ብቅ ብለው ለምኒልክ ለመርዳት ተስማምተው ነበር ይባላል ። በሰነድ መልክ በጽሑፍ የሠፈረ ነገር ስለሌለ ፤ ሁኔታውን በትክክል ለመረዳት አልተቻለም ።

ከዚህ ስምምነት በኋላ ፤ ምኒልክ ለተክለ ሃይማኖት ሁለት መድፍና 250 ጠመንጃ በደርቡሽ ጦርነት ስለ ጠፋባቸው የጦር መሣሪያ እርጥባን ሰጥተው ሁለቱም በጠበቀ ወዳጅነት ከተሳሰሩ በኋላ ፤ ተክለ ሃይማኖት ምኒልክን እስከ አባይ ወንዝ ድረስ (ደጀን) ሸኝተው ሲመለሱ ምኒልክም አባይን ተሻግረው በግንቦት ወር መጨረሻ ላይ በሰላሌ በኩል አድርገው እንጦጦ ከተማቸው ገቡ ። ከርሳቸውም ጋር ደጃች ሥዩም ገብረ ኪዳን የፈረስ ስማቸው አባ ጎበዝ ከጎጃም አብረው መጥተዋል ።

ደጃዝማች ሥዩም ፤ እናታቸው እቴጌ ድንቅነሽ ያፄ ዮሐንስ እህት የዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ባለቤት ሲሆኑ ፤ አባታቸው ያፄ ዮሐንስ እንደራሴ ራስ ቢቶደድ ገብረ ኪዳን ናቸው ። ከዕለታት አንድ ቀን ከንጉሠ ነገሥቱ ልጅ ከራስ አርአያ ጋር ሲጫወቱ በትንሽ ግጭት ተጣልተውና * ታስረው ምሕረት ካገኙ በኋላ ፤ “እንደገና ያስሩኛል ” ብለው ፈርተው ወደ ጎጃም ከመጡና ከታሰሩ ወዲህ አሁን ደግሞ ጎጃም ላፄ ዮሐንስ ቀረብ ስለሚል ፤ ምኒልክና ተክለ ሃይማኖት በተወዳጁበት

* የጠቡ ሰበብ ከዕለታት አንድ ቀን ሥዩም ገብረ ኪዳንና አርአያ ዮሐንስ ቆጥ ብለው ሲጫዋወቱ አርአያ ‘የእቴጌ ድንቅነሽ ጡት ትልቅ ትራስ ያህላል’ ቢል፥ ሥዩም መልሶ ‘ምነው ይኸ የጥልጣል ልጅ እንዴት ይናገራል’ ብሎ ስለ ሰደበው፥ አርአያ ላባቱ ይኸንኑ ነገር ስለ አስገረፈው ነው ይባላል ።



ሰዓት በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፈቃድ ነጻነታቸውን አግኝተው ወደ ሸዋ መጥተው ለንጉሥ ምኒልክ እጅ ነሥተው ገቡ ።

በዚሁ ዐይነት ፤ ደጃች በሰው ተክለ ሃይማኖትም “ብሳር ወሃ ጦርነት ትተውኝ ሸሹ” በማለት ካባታቸው ጋር ተኳርፈው ወደ ጉድሩ መጥተው ቆይተው ሳለ ፤ አሁን ዐፄ ዮሐንስ ወደ ጎጃም ሊዘምቱ በተቃረቡበት ሰዓት ደጃች በለው ወደ እንጦጦ መጥተው ለምኒልክ ገቡ ። ዶክተር ትራቬርሲ የሚባለው የአንቶኔሊ ጓደኛ ወደ ሮማ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በጥቅምት 1880 ዓ. ም. በላከው ራፖሩ ውስጥ የሥዩምንና የበለውን ወደ ሸዋ መምጣት ካወሳ በኋላ ፤ “ባሁኑ ጊዜ ሸዋ የስደተኞችና የሐዘንተኞች መጠጊያ ሆኗል” ሲል ጠቅሷል ።[1] ይሁን እንጂ ፤ ከሸዋ ሸሽቶ ወደ ትግራይ ፤ ከትግራይ አምልጦ ወደ ሸዋ እየመጣ ሰውነቱን ከቅጣት ቢያድንም ፤ እነዚህን ስደተኞች ነገሥታቱ በበኩላቸው ባላንጣቸውን ለማጥቂያ ወይም ለመታረቂያ መሣሪያ ያደርጉዋቸዋል ።

በዓለም ታሪክ ውስጥ ፤ ነገሥታትና ሌሎች የመንግሥታት መሪዎች ያንጊዜም እንደዛሬ ባላጋራቸውን ለማጥቃት ከሚያደርጉዋቸው ዘዴዎች አንዱ ፤ የመረጃ ምስጢር ከመሰብሰብ ጋር ዘመዱን በዘመዱ ማስጠቃት ነው ። ይኸም ሁኔታ ከጥንት ሲያያዝ እንደ መጣው ባሁኑ ጊዜም ባፄ ዮሐንስና በንጉሥ ምኒልክ ግንኙነት ላይ ጎልቶ ይታያል ። ዐፄ ዮሐንስ የምኒልክ ባላንጣነት ከበድ እያላቸው በሔደበት ጊዜ የምኒልክን ያጎት ልጅ ደጃች መሸሻ ሰይፉን አቀራርበዋቸው እንደ ነበረ ፤ በኋላም ምኒልክ በአማራ ሳይንት (በታሞ) ሰይፉን ቢያስሩ ዮሐንስ ከዚያ አስፈትተው ለሸዋ ንጉሥነት ተጠባባቂ እጩ ለማድረግ ሞክረው እንደነበረ የሚታወስ ነው ።

አሁንም ንጉሥ ምኒልክ ከጎጃም እንደ ተመለሱ ፤ በጎጃም ባፄ ዮሐንስ ትእዛዝ በግዞት የነበሩት ደጃች ሥዩም ገብረ ኪዳን (ያፄ ዮሐንስ የእህት ልጅ) በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ውስጠ ትብብርነት ከጎጃም ወደ ሸዋ ከገቡ በኋላ ፤ ምኒልክ ካፄ ዮሐንስ ጋር ያላቸው የተዳፈነው ጠብ እስኪገለጥ ድረስ ሥዩምን ባፄ ዮሐንስ ላይ መሣሪያ ለማድረግ እንከባክበው ይዘዋቸዋል ። በምኒልክ ዘንድ ግን ፤ ማናቸውንም ነገር በጥንቃቄ ማድረግ ፤ ነገ የሚሆነውንም ዛሬ አስቦ መፍትሔ መፈለግ ልማድ ስለሆነ ፤ ሥዩምን በእጃቸው አስቀምጠው “ሥዩምን ስጠኝ አልሰጥም” የሚል ውዝግብ ወደፊት ካፄ ዮሐንስ በኩል

1 L'Italia in Africa . . . Documenti, Paris, (1888—1889), p. 154.

ምናልባት ይፈጠር ይሆናል ብለው በማሰብ በዶክተር ትራቬርሲ ምክር መስፍኑን ተያዥና ዋስ ሆነው ወደ ምጥዋ ለመላክ ተዘጋጁ ።

ወዲያውኑ ስንቅም ተከታይም ሰጥተው ለመላክ ሲሉ ወደ ኢጣሊ[ያ] ጠቅላይ ሚኒስትርና ተጠባባቂ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ይዘው እን[ዲሄዱ] ሐዱ የተጻፈው ያደራ ደብዳቤ እንደዚህ ይላል ።

> ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ሸዋ ወከፋ ወሐረር . . . ይድረስ ከም[ኒ]ኒስቴር የውጭ ነገር ሁሉ የሚያደርግ ። ሰላም ላንተ ይሁን ። ደጅ አዝማች ሥዩም የጃንሆይ (ዐፄ ዮሐንስ) የእህታቸው ልጅ ተስዶ ወደኔ መጣ አሁን ጃንሆይ በርሱ ተናደው እሥረሀ ላክልኝ ብለው ቢልኩብኝ በእንደዚህ ያለ ጊዜ እንደርሱ ያሉ ሰዎች ለኔም ለናንተም የሚፈለጉ ስለሆኑ አልሰድም ብዬ አስ[ቀ]ቀረሁት ። አሁን የሚሸኘው ጦር ሰጥቼ በዙብል መንገድ ወደ ትግሬ መሬት ከእናንተ ደጃዝማች ዘንድ (ዤኔራል ባልዲ[ሰ]ሰራ) ድረስ ሰድጃለሁና ደህና አድርጋችሁ ተቀበሉልኝ ። አደራ ሰጥቻችኋለሁ ዋሱ እኔ ነኝ ። የቀረውን ከሐኪም ትራቬርሲ ደብዳቤ ታገኙታላችሁ በጥቅምት 20 ቀን 1881 በእንጦጦ ከተማ ተጻፈ ።[1]

ንጉሥ ምኒልክ በደብዳቤያቸው ላይ የጠቀሱት ትራቬርሲ ሙሉ ስሙ ሌዎፖልዶ ትራቬርሲ ለስሙ በሐኪምነት ሙያ ተሠማርቷል። ዋናው ተግባሩ ግን ፣ ብዙ ጊዜ 10 ኪሎ ሜትር ከአንኮበር ራቅ ብሎ ለኢጣልያኖች ማረፊያ ለተሰጠው ለልጥ ማረፊያ ሠፈር ኃላፊ ሆኖ ለኢጣልያ መንግሥት ያገር ወሬ እየለቀመ በቀጥታ ወይም በአንቶኔሊ በኩል ማስተላለፍ ነበር ። አሁንም አንቶኔሊ ከምኒልክ ተልኮ ወደ ሮማ በሔደ ጊዜ እንጦጦ የአንቶኔሊ ወኪል ሆኖ ይሠራ ነበር ።

እርሱም ስለዚሁ ስለደጃች ሥዩም አላላክና ስለሌላውም ስለ ኢትዮጵያ የጊዜው ሁኔታ ከእንጦጦ አንደኛ ጥቅምት 1880 ዓ. ም ለክሪስፒ በጻፈው የራፖር ማስታወሻ ሥዩምና እርእያ ዮሐንስ በተ[ጣ]ጣሉበት ነገር ሥዩም ታስረው ሳለ ፣ በኋላ እርእያ ስለሞቱ ሥዩም ቢፈቱ "እንደገና እታሰራለሁ" ብለው በመፍራት ወደ ጎጃም መሸሻቸውን ከዚያም ወደ ቀድሞ ወዳጃቸው ወደ ሸዋ ንጉሥ ወደ ምኒልክ*

1 Archivio Storico del Sopresso Minisrero Africa Italiana Fondo, Archivistico A.S. Mai 36-5—50.

* ሥዩም ከምኒልክ ጋር ቀደም ያለ ዕውቂያና ወዳጅነት ነበራቸው ማለት ነው ።



መሔዳቸውን ፣ በዚህም ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ዮሐንስ "በሰንሰለት አስረሀ ላክልኝ" ብለው ለምኒልክ ቢልኩባቸው "ከኔ ዘንድ ሸሽቶ ሔዷል" ብለው መመለሳቸውን ፣ ከዚያ በራሱ አሳባቢነት ወደ ጠቅ ላይ ሚኒስትሩ (ክሪስፒ) በምኒልክ ዋስትና አደራ ተብሎ እንዲላክ ማድረጉን አመልክቷል ።ቀጥሎ ቢታኅሣሥ 16 ቀን በዚሁ ዓመት በላከው የድጋሚ ራፖር ላይ ፣ "የሥዩም ጠባይ ስለማይታወቅ አንድ የማይሆን ነገር የሠራ እንደሆነ ኃላፊውና ዋሱ እርስዎ ነዎት" ብሎ ለንጉሥ ምኒልክ ቢያስጠነቅቅ ፣ ምኒልክ ሥዩምን አንከባክበው አስንብተው ፣ በመጨረሻም ብዙ ፈረስና በቅሎ አራት መቶ ባለጠበንጃ ወታደር ሰጥተው ወደ ዞቡል ከላኩዋቸው በኋላ ፣እንደገና ጥር ጣሬ ገብቷቸው በሐዱ በ15ኛው ቀን ሥዩምን ለመመለስ ፈረሰኛ መላካቸውን ከገለጸ በኋላ ፣ ከዚሁ አስከታትሎ በማናቸውም ረገድ ሥዩም ምጥዋ ሲደርሱ የኢጣልያ ባለሥልጣኖች በሰውዬው ላይ የጥንቃቄ አያያዝ እንዲያደርጉ አሳሰቦአል ። ቀጥሎ በማግሥቱ በታኅሣሥ 17 ቀን በጻፈው ሦስተኛ ማስታወሻ ላይ ደጃች ሥዩም ከጉዞአቸው ወደ እንጦጦ ተመልሰው እንዳያመልጡ በጥንቃቄ መጠበቃቸውን ያመለክታል ።[1] በበኩሉ አንቶኔሊ በጻፈው ማስታወሻ ሥዩም ወደ ሸዋ ከተመለሱ በኋላ ፣ ንጉሥ ምኒልክ በአቡነ ማቴዎስ አማካይነት ከዐፄ ዮሐንስ ምሕረት ጠይቀው እንዳስማሩዋቸውና በዚያው በሸዋ እንደቆዩ ይጠቅሳል ።[2]

ምኒልክ ሥዩምን ከደብዳቤ ጋር ወደ ኢጣልያ ባለሥልጣኖች ዘንድ ከላኩ በኋላ ፣ ፈረሰኛ ልከው ወደ እንጦጦ የማስመለሳቸው ምክንያት በሁለት ላይ የሚመደብ ይመስላል ።አንደኛው ሥዩም አባ ጉበዝ በጀግንነት ስመ ጥር የነበሩና ለሥልጣን ምኞታቸውም ወሰን ያልነበራቸው በመሆናቸው "ለኔም አይገዛም" የሚል ጥርጣሬ ስለ አሳደረ ፣ ሁለተኛው ደግሞ በዚህ ጊዜ ምኒልክና ዮሐንስ ውስጡን ቢጣሉም ገና በግልጽ ከውጊያ ስለ አልደረሱ ፣ "ሥዩምን አስረሀ ላክልኝ" ካሉዋቸው ወዲህ ጭፍራና ስንቅ ሰጥተው ወደ ጣልያን ባለሥልጣኖች መላካቸው የተሰማ እንደሆነ ካፄ ዮሐንስ ጋር ጠቡን እንዳያባብሰው ይሆናል ። ቀጥሎም ደጃች ሥዩም ወደ ሸዋ ከተመለሱ በኋላ ፣ አቡነ ማቴዎስ ምኒልክንና ዮሐንስን ለማስታረቅ በሚሞክሩበት ጊዜ ፣ "እኔ ዘንድ ነውና ያለው ምሕረት ያድርጉለትና

1 L'Italia in Africa . . . Documenti (1888—1889) pp. 154, 186—188, No. 183—194.
2 Ibid.

ወደርስዎ መመለስን ስለፈራ እኔ ዘንድ እንዲቆይ” ብለው በአቡነ አማካይነት ጊዜያዊ ፈቃድ አግኝተው ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ፣ ሥዩም አባ ጉበዝ ዐፄ ዮሐንስ ካረፉ በኋላ ወደ ትግራይ ሔደው ባንድ ወገን ከደጃች ደብብ አርአያ ፣ በሌላ ወገን ካፄ ዮሐንስ አልጋወራሽ ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ ጋር ያደረጉትን የፖለቲካና የጦርነት ወዝግብ ፣ በመጨረሻም ላገር ሰላምና ጸጥታ ሲሉ አጼ ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ለራስ መንገሻ ትግራይን ሰጥተው ሥዩምን የቁም እስር አድርገው ወደ ሸዋ ሲመለሱ ዝርዝሩን ወደፊት እናነባለን ።





ኮንት ፒዬትሮ አንቶኔሊ

(ከክርለዊ ኢ ምኒልክ)

# ምዕራፍ ዐርባ ስድስት

## ዐፄ ዮሐንስ ጐጃምን ስለ መውረራቸው ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንደገና ታምነው በዕርቅ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ስለ መግባታቸው

ምኒልክና ተክለ ሃይማኖት ፣ ባለፈው ያነበብነውን የከዳት ስምምነት አድርገው መለያየታቸውን ዐፄ ዮሐንስ እንደሰሙ ፣ ወዲያው ወደ ጐጃም ወይም ወደ ሸዋ አልዘመቱም ። ነገር ግን ፣ የንጉሥ ምኒልክን ከአምባጫራ ወደ ሸዋ መመለስ የሰሙት ፣ "ደርቡሾች እንደገና ወሰን እያለፉ መጥተው ሠፈራቸውን በተንኮል ሜዳ አድርገው ቤተ ክርስቲያን አቃጠሉ ፣ አገርም ዘረፉ" የሚባል ወሬ ስለ ደረሰቸው ፣ በሰኔ ወር መዠመሪያ ላይ የሞቱትን የልጃቸውን የራስ አርአያን የሐዘን ጊዜ ከፈጸሙ በኋላ ፣ ከደብረ ታቦር ተነሥተው በሰኔ ወር አጋማሽ ላይ ወደ ቤገምድር ዘልቀው አሞራ ገደል ሠፈሩ ። በዚያም ላይ ምክር ሲደረግ ፣ "ደርቡሽ ወደ ጐንደር ለመግባት ማቀዱ ቢታወቅም ፣ በመዠመሪያ ወደ ጐጃም ሔደን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን እንዋጋለን ፤ ደርቡሽ ጊዜ የሚሰጠን የሆነ እንደሆነ ንጉሥ ምኒልክን ለመውጋት ወደ ሸዋ እንዘምታለን ፤ ጊዜ የ ማይሰጠን እነደሆነ ግን ከጐጃም ወደ መተማ ሔደን ደርቡሽን እንዋጋለን" በማለት ተመክሮ በዚሁ ስለተወሰነ ፣ በሐምሌ ወር ላይ ከቤገምድር ወደ ጐጃም ተጓዙ ።[1]

ይኸ ሁሉ ሲሆን ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ምኒልክን ሸኝተው ከተመለሱ ወዲህ ዐፄ ዮሐንስ እንደሚዘምቱባቸው በቅድሚያ በመገንዘብ በሜዳ ላይ እንደ እኩያ ጦርነት ለመግጠም ያላቸው ኃይል እንደማይፈቅድላቸው በመረዳት ፣ ቀደም ብለው ወደ ጅበላና ወደ ሙተራ ተራራ ለመሸሸግ ስንቅም ፣ መሣሪያም እያስጋዙ በደንብ አስመሽገውታል ። ቀጥሎም የንጉሠ ነገሥቱ ጦር ያለምንም ተከላካይ ወደ ጐጃም ዘልቆ ጉዛምን ላይ ሲሠፍር እርሳቸው ሙተራ አምባ ላይ ቀደም ብለው ወጥተው ተቀምጠዋል ። አቡነ ሉቃስ ግን

---

1 ብ.ጌ. ኅሩይ ፣ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐድዋ ጦርነት ፣ ገጽ 142 143 ።

እስታርቃለሁ ብለው ወደ ተራራው አልወጡም ፤ ቀጥለውም ወደ ዐፄ ዮሐንስ ሠፈር ሔደው ተቀመጡ ።

ካቶ ዐጥሜም ከብላቴን ጌታ ኅሩይም የበለጠ ስላፄ ዮሐንስ የጐጃም ወረራ በቂ ዝርዝር የሚሰጡን አለቃ ተክለ ሥላሴ ዋቅጅራ እንደ ልማዳቸው አንቱታ ሳይጨምሩ እንደዚህ ብለው በጽሑፍ አስፍረውት ይገኛል ።

...ዐፄ ዮሐንስ ጉዛምን ላይ ሠፍሮ እምባውን (ሙተራን) ሊሰብር በጭምትና በማይ አፋፍ መድፍ ጠመደ ። ግን አልሆንለትም ኃይለኛው መድፍ ጀብላን እያለፈ ከአባይ በረሀ ወደቀ ቀላሉም መድፍ የእምባውን ገደል እየመታ ቀረ ። ያን ጊዜ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የመድፍ የዘበኛ አለቃ ባሻ አስናቀ የሚባል ነበረ ። ጅብላ ሆኖ ጭምት ላይ ከተጠመደው(የተጠመደውን) መድፍ ተመልከቶ ቢተኩስ የመድፉ አረር (ጥይት) በመድፉ አፍ ገብቶ ከነመንኰራኩሩ የኋሊት ገልብጦ ጥሎ ተኳሹን ጨምሮ ገደለው ። ባላንባራስ ጊዮርጊስ የሚባል ዝግና የግሪክ ሰው ነበረ ።* እርሱ ደግሞ ብዙ ትግሬ ገደለ ። ከዚህ በኋላ ዐፄ ዮሐንስ ጭምት አፋፍ መቀመጡን ተወ" ካሉ በኋላ ፣ ጸሐፊው ያፄ ዮሐንስ ወታደር በጉዛምንና በማቻከል የተገኘውን የቤተ ክርስቲያኑን ሳንቃ እየነቀለ እያወጣ በጭምት አፋፍ የጥይት ማብረጃ ለማድረግ ተራውን (ተርታውን) አቁሞ ፣ ማገሩን እየፈለጠ ማንደዱ ፣ ታቦቱንም ከመንበሩ እያወጣ በየሜዳው በጣለው ጊዜ በንዴት ጳጳሱ አቡነ ሉቃስ ፣ "ደርቡሽን አጠፋለሁ ብዬ መጣሁ ያልከው ለጐጃም አንተ ደርቡሽ ሆንክ" ብለው ዐፄ ዮሐንስን መቆጣታቸውን ፣ ወደ አምባው ሌሊት ሰብረው እንዲገቡ በጨረቃ የተላኩት ያፄ ዮሐንስ ወታደሮች አሳባቸውን ተከላካዮቹ በጠቋሚ ደርሰውበት ከላይ ናዳ እየሰደዱ ብዙ የትግሬ ወታደር እንደፈጁ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ በዚሁ ተናደው ብዙ ጭፍራ ሰደው ጐጃምን ከፉኛ ማዘረፋቸውን ፣ በዚህ ጊዜ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጀግኖች አንዱ እምባ (ሙተራ) ውስጥ ያልገቡት ደጃዝማች ወዳጄ መርጡለ ማርያምን እንዳትበዘበዝ ተከላክለው እንዳዳኑ ከተረኩ በኋላ ፣ በዚሁ በጦርነቱ ሰዓት ልብሷ የተገፈፈባትና ከብቶቿ የታረዱባት አንዲት የጐጃም አልቃሽ ፣

"በላይኛው ጌታ በባልንጀራዎ ፣
በቅዱስ ሚካኤል ቢጋሻ ዣግሬዎ
በጽላተ ሙሴ በነጭ አበዛዎ *
ጐጃምን ይማሩት ፈሪም አንልዎ"

ብላ መግጠሟን ጽፈውታል ።[1]

በበኩላቸው ብላቴን ጌታ ኅሩይም፡-

"ዐፄ ዮሐንስ ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የተደበቁበትን አምባ (ተራራ)በመድፍ ማፈራረስ ሲያቅታቸው ተናደው አገሩን ጐጃምን ያጠፉት ዠመር ። በሌላው ሥፍራ ይቅርና ጐጃሜው ከመከራ የሚድን እየመሰለው ገንዘቡን እየያዘ በየቤተ ክርስቲያኑ እየተማጠነ ቢገባ ፣ የትግሬው ወታደር በኃይል እየገባ ገንዘቡን እየቀማ እምቢ ያለውንም እየገደለው ይወጣ ነበር ።"

ሲሉ አመልክተዋል ።[2]

መቼም በሥልጣኔ ኋላ ቀር በሆኑ አገሮች ፣ (በተለይ በባለ ጉልተኞች ዘመን ጉልተኛ መስፍን ባጠፋ ጊዜ ይኸውም ማለት በሸፈተ ቁጥር የርሱን ጥፋት በቀጥታ ከፋዩ በጉልት አገሩ ውስጥ የሚገኘው ሕዝብ ነበር ። በፈረንጆችም "መስፍኑ ሲያጠፋ ኩርኩም የሚቀምሰው የልፍኝ አሽከሩ ነው" እየተባለ ይተረታል ። አሁንም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከምኒልክ ጋር አድመው በከዱ ፣ እርሳቸው በሙተራ ተራራ ተሸሽገው ሕይወታቸውን ከማናቸውም አደጋ ሲያድኑ ፣ ነዋሪው ሕዝብ ሴቱ ሳይቀር በሚያሳዝን አኳኋን ባልገባበትና በማያውቀው ነገር የዘረፋውንና የግድያውን ሥቃይ ተቀበለ ። የጌታውን ከዳት ሳያውቅና ሳይሰማ ፣ ከነገሩ ሳይገባ ዝም ብሎ የተቀመጠ በተግባርና በአሳብ እንደ ተባበረ ተቆጥሮ ይኸን የመሰለ ግፍና ሥቃይ ደርሶበታል ። የጌታውን ሽፍትነት እምቢ አልደግፍም ብሎ ጌታውን የተቃወመ ወታደር ፣ ባላገርና ነጋዴ ቢኖር ደግሞ በዚህ የተነሣ የሚደርስበት መዘዝ ከዚህ የባሰ ነበር ። በጌታው ትእዛዝ የዘመተ ወታደር ጌትዮው ሲሸነፍ ፣ የምርኮኛነት ዕጻውን እንደ ማራኪው የመንፈስ ሁኔታ በሞት በእስራት የቀረው ቢቀር በግዞት ይከፍላል ። ጌታውን ያልተከተለ ወታደር ደግሞ ፣ ከኃዲ ዐመጸኛ ተብሎ ዕድሉ ከምርኮኝነት የባሰ ነበር ። ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ኋላ ቀር በሆኑ ወይም የዲክታተር አገዛዝ ባለበት አገር ሁሉ ሲደረግ የኖረ ነበር ፤ ወደፊትም ይኖር ይሆናል ።

* ጊዮርጊስ የነወይዘሮ አበቻ አባት ናቸው ። ባፄ ቴዎድሮስ ዘመን መጥተው ባፄ ዮሐንስም በንጉሥ ምኒልክም ዘንድ የታወቁ ነበሩ ።

* ነጭ እንጀራ ጋጋሪዎ ለማለት ነው ።

1 ያለቃ ተክለ ሥላሴ የእጅ ጽሑፍ ገጽ 133—135 ።

2 ብ.ጌ. ኅሩይ ፣ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐድዋ ጦርነት ፣ ገጽ 143 ።

ያለዚያ ግን ፣ ሐቁን መንገድ ያሰቡን እንደሆን ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይ
ማኖት የንጉሠ ነገሥቱን የጦር ኃይል ለመመለስ እንደማይችሉ እያ
ወቁት ለምን ከዱ ? ከክዱና ኃይላቸውን ከተማመኑ ንጉሠ ነገሥቱ ለው
ጊያ ሲመጡባቸው የሚችሉትን ያህል ተቋቁመው አልሆን ሲል ወደ
ሸዋ በመሸሽ የሕዝባቸውን ሥቃይ ለማቅለል በቻሉ ነበር ።
ባፄ ዮሐንስም በኩል በከዳተኝነት የበደሉት ሁለቱ ነገሥታት ሲሆኑ
በተቻለ እነሱን በማናቸውም ረገድ ይዞም ፣ ሳይዞም መቅጣት ሲገባ
በነገሩ የሌለበትን ባላገር ወታደር ማዘረፍና ማስገደል እንደማይገባ
ግልጽ ሲሆን ፣ ደግሞ ባሁኑ ጠላት በሰሜን ምዕራብና በሰሜን ምሥ
ራቅ አገሪቱን በሚያዋክብበት ሰዓት ምንም ዐይነት በደል ቢደርስ
የሁለቱ ነገሥታት መክዳት ኃላፊነቱ የከበደ መሆኑን እንገነዘባለን ።

ምኒልክ ፣ ከጐጃም ዘመቻ ቀጥሎ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ሸዋ መዝ
መታቸውን በማመን ፣ በግዛታቸው ጦራቸውን በመሰብሰብና በማደራ
ጀት ላይ ይገኙ ነበር ። ለርዳታ ወደ ጐጃም ያልዘለቁበት ምክንያት
በነሐሴ ወር ላይ አባይ ወንዝ ሞልቶ ስለማያሻግር ነው የሚሉ
ሰበብ አግኝተዋል ። አባይ ባይሞላም ከአምባጫራ መልስ በኋላ
የበተኑትን ጦር ሰብስበው እርሳቸው በቅድሚያ ሳይመክቱ ሙተራ
ተራራ የተቀመጡትን ወዳጃቸውን ይታደጋሉ ማለት ዘበት ነው ።
ነገር ግን ፣ ምንም ወደ ጐጃም ባይዘልቁ ራስ ሚካኤል ከንጉሠ ነገሥቱ
ጋር ጐጃምን ለመውጋት መሔዳቸውን ፣ በዚያም ጐጃምን መሾማቸ
ውን ሲሰሙ ፣ ምኒልክ ደግሞ በበኩላቸው ወደ ወሎ ደጃች መንገሻ
አቲከምን ፣ ደጃች ወሌ ብጡልን ፣ ደጃች ወልዴ አሻግሬን ልከው በዚያ
ያሉትን የራስ ሚካኤልን ሰዎች በማስጠቃት ላይ ነበሩ ። እነርሱንም
ሲያይ ቦርኒ አባ ጐዳ የሚባለው የቦረና ባላባት በነዳጃች መንገሻ
አቲከም ድጋፍ ራስ ሚካኤል ብዙ ሀብታቸውን በመቅደላ አፋፍ አስ
ቀምጠው ለጥበቃ ትተውት የሔዱትን ልጃቸውን በውጊያ ከመቅደላ
ላይ ሊያባርረው ችሏል ።

ከውጊያውና ከዘረፋው በኋላ ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንዲ
ገቡ በንጉሠ ነገሥቱ ተጠይቀው እምቢ ስለአሉ የጎጃምን ግዛት
ለራስ ሚካኤል ለማስተላለፍና የንጉሥነቱንም ማዕረግ ከተክለ ሃይ
ማኖት ገፈው ለኚሁ ለራስ ሚካኤል ለመስጠት አስበው ነበር ይባ
ላል ። ነገር ግን ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ባንድ ወገን ንጉሥ ምኒልክ
ለእርዳታ አለመምጣታቸውን በሌላ ወገን የሕዝባቸውን መዘረፍና መገ
ደል በርሳቸው ሸፍትነት ምክንያት መሆኑን ስለ ተረዱት ፣ በመጨ
ረሻ በአቡነ ሉቃስ አማካይነት ተላልከው ላያስሩአቸው ቃል አስገ
ብተው ወደ ዐፄ ዮሐንስ ገብተው እጃቸውን ሰጡ ።[1]

1 ብ.ጌ. ኅሩይ፣ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐድዋ፣ ገጽ 133—144 ።





ጆርጅ ለእንግሊዝ ሲላክ
(ከሰቴር ቶ ሞንድ መጽሐፍ)

# ምዕራፍ ዐርባ ሰባት

## የንጉሥ ምኒልክና የኢጣሊያ መንግሥት ወዳጅነት እየጠበቀ መሔድ

ንጉሥ ምኒልክ ፥ "በመጣችሁበት መንገድ ተመለሱ" የሚለው የንጉሥ ነገሥቱ ደብዳቤ ከደረሳቸው ወዲህ ጠቡ እየከረረ መሔዱን በመገንዘብ ፥ ቀደም ብሎ የኢጣሊያ መንግሥት ደንበኛ ወኪል ለሆነው ለአንቶኔሊ እዚያው አምባጫራ እንዳሉ በግንቦት 9 ቀን 1880 ዓ.ም. "ወደ እንጦጦ እንደ ደረስሁ ወደ ኢጣልያ አገር የምልክህ ብርቱ ጉዳይ አለኝና እንጦጦ ሆነህ ተዘጋጅተህ ጠብቀኝ" የሚል ደብዳቤ ጻፉለት ። እርሱም ከኢጣልያ ንጉሥ ተወክሎ ከመጣ ዠምሮ ምኒልክንና ዮሐንስን ለማጣላት ሁሉንም ነገር እየሰለለ ፥ ታጥቆ ይጠብቅ ነበርና ይኸ ደብዳቤ ሲደርሰው በሁሉም ተዘጋጅቶ ሲጠብቃቸው በሰኔ 22 ቀን እንጦጦ ገቡ ።

አንቶኔሊ እንደሚለው ፥ በደረሱ በሦስተኛው ቀን አስጠርተው አስተርጓሚው አለቃ ዮሴፍ ባሉበት ቄስና ወንጌል አስመጥተው ፥ "የምነግርህ ነገር አለና ምስጢሩን ለሰው እንዳታወጣ ማልልኝ" ብለው እንደ ኢትዮጵያ ደንብ በወንጌል እንዳስማሉትና እሱም እሺ ብሎ መሐላውን እንደ ፈጸመ ፥ አስማዩ ቄስ ከወጣ በኋላ ዐፄ ዮሐንስ የጐጃም ጦር በደርቡሾች ከተሸነፈ በኋላ እርሳቸውን ወደ ጐንደር ጠርተዋቸው ሔደው እስከዚያ ጊዜ ድረስ የእምነትና የወዳጅነት ግንኙነት ከንጉሡ ነገሥቱ ጋር እንደ ነበራቸው ከስሐጢ መልስ ግን ፥ በእርሳቸው ላይ ያላቸው እምነት ተለውጦ እንደ ተጣሏቸውና ቀድሞ የተስማሙበትንም የመተማመን መሐላ አፍርሰው እንደ በደሏቸው ፥ ስለዚህም አሁን ከዐፄ ዮሐንስ ጋር ጠቡ ግልጽ ስለሆነ ፥ የኢጣልያ መንግሥት ዐሥር ሺ የሬሚንግተን ጠመንጃና አራት መቶ ሺ የወተርሊ ጥይት በቶሎ በአሰብ በኩል እንዲልክላቸው ፥ ይህም የጦር መሣሪያ ሲደርሳቸው በዚህ መሣሪያ ኢጣልያኖችን ይጐዱበታል ተብለው እንዳይጠረጥሩ ይልቅስ በዚህ ፈንታ እንዲያውም በዶጋሊ የሞቱትን የኢጣሊያኖች ደም እንደሚበቀሉ በቃል አረጋግጠው ወዲያውም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ለራሱ ለአንቶኔሊ ሰኔ 8 ቀን 1880 ዓ.ም. የጻፉለትን ደብዳቤ እንዳስረከቡት ይገልጻል ። የደብዳቤው ቃል ቀጥሎ ያለው ነው።

“ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ያለኝን ዝምድና የምታውቀው ነው። ኮንቴ ሳሊምቤኒ በሲኞር ቢያንኪ ጊዜ ተጀምሮ የነበረውን ወዳጅነት ወደ ፍጻሜ ለማድረስ በመሞከሩ እስራትና ውርስ ደርሶበታል ።* አሁን ግን ፣ የኔን ሐሳብ ሁሉ ከንጉሥ ምኒልክ ትሰማዋለህ ይህን ማህተሜን የላኩልህ በንጉሥ ምኒልክ በኩል የላኩልህን መልእክት እንደምታምንና ጥርጣሬ እንዳይገባህ ነው ።”

እንግዲህ የራሳቸውንና የንጉሥ ተከለ ሃይማኖትን በሕብረት መከዳት ለወኪሉ ለአንቶኔሊ እንደ ገለጹለትና እርሱም በቶሎ ወደ አገሩ ሔዶ እላይ የተጠቀሰውን የጦር መሣሪያ በቶሎ ይዞ እንዲመጣ አደራ ብለውታል ። ወደ ኢጣልያ አገርም ሲሔድ ስለዚሁ ጉዳይ ለኢጣልያ ንጉሥ ለኡምቤርቶ ቀዳማዊ ሰኔ 30 ቀን 1880 ዓ. ም. የተጻፈ ደብዳቤ ሰጥተውታል ።

በደብዳቤው ውስጥ የሠፈረው ታሪካዊነት ያለው ስለሆነ ፣ ከአድራሻና ከሰላምታው በቀር በሙሉ እንደሚከተለው አስፍረነዋል ።

“በ12 ጥር በተጻፈ ደብዳቤዎ የርስዎን ቃል ለማስታወቅ ኮንት አንቶኔሊ ከኔ ዘንድ እንዲኖር ስለ አስታወቁኝ እጅግ ደስ አለኝ ። ንጉሥ ሲልኩብኝ ኮንት አንቶኔሊ የታመነውን ሉሌዎን ለርስዎና ለኔ ነፍስ የሚበጀውን ብናስይዘው የታመነ ነውና አይጠርጥሩት ብለው ላኩብኝ ።[1]

“አሁን ግን ይህ የታመነ ሰው እኔ ቃል ለቃል ልነግርዎ የሚገባኝን ነገር ሁሉ እንዲነግርዎ ወደርስዎ ልኬዋለሁ ። ነገሩም ይህ ነው። ያልታሰበ ነገር ተነስቶ መንግሥቴን የሚያውከብኝ ሆነ ። በሰዎች ልቡና ውስጥ ያለውን የሚመረምር እግዚአብሔር ብቻ ነው ። በርስዎና በጃን ሆይ መሀል የክርስቲያን ነገሥታት ሐሳብ ከቀሩት ይበልጥ ደስ ይለው ዘንድ በሚገባው ሰው (ዮሐንስ ) ፊት ክፉ ነገር ሆኖ ታዬ ። አሁን ዛሬ ባየው ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ተስማምቶ በምጥዋ በኩል ጦር አስወጥቶ (አስመጥቶ) ሊያስወጋኝ የመከረ ንጉሥ ምኒልክ ነውና ብለው አገሬን መጥተው ለመውጋት ያስፈራሩኝ ጀመር ። እኔም ከእንግዲህ ወዲህ ባገሬ እመክታለሁ ብዬ ሆዴ

* ተከለ ሃይማኖት ይኸን የጠቀሱት በዶጋሊ ጦርነት ዋዜማ ሳሊምቤኒ ከነኮሎኔል ፒያኖ ጋር ወደ እሥመራ ዘልቆ ሳለ መሐንዲስ ነኝ ብሎ ሲያታልል በራስ አሉላ ትዕዛዝ ታስሮ የነበረውን ነው ።ከዚያ በፊት ይኸው ሳሊምቤኒ የአባይን ድልድይ እሠራለሁ ብሎ ተስፋ ሰጥቶ ነበር ።

1 L'Italia in Africa... (1888—89) No. 95, p. 101.



ቆርጧል ። ነገር ግን ንጉሥ ይገዙኝ (ያግዙኝ) ባለፈው ዓመት በጥቅምት ከኮንት አንቶኔሊ ጋራ ከኢጣልያ መንግሥት ፍቅሬን አላፈርስም ብዬ ተዋውዬ ደብዳቤ አትሜ ሰጥቼው ነበር ። ኮንት አንቶኔሊም ደግሞ የኢጣሊያ መንግሥት 5000 ሬሚንግቶን ይሰድልዎታል ብሎኝ ነበር ። ንጉሥም በደብዳቤዎ ኮንት አንቶኔሊ ያደረገውን መቀበልዎን ላኩብኝ እንዲህ ከሆነ አገሬን መክቼ ያዳንሁ እንደሆን የፈሰሰውን በዶጋሊ የዜጎችዎን ደም ለመመለስ ያገለግልዎታል ሐረርጌ ላይ የዜጐችዎ ደም* በፈሰሰበት አገር እንደረዳኝ ዛሬም ይረዳኛል ብዬ ተስፋ አለኝ ። ዛሬ ብቻ የንጉሥ ረዳትነት ይፍጠንልኝ አሁን ፈጥኖ ነፍጥ ይምጣልኝ ፣ ነፍጡም ቢያንስ ቢያንስ ከዐሥር ሺህ ሰናድር ያነሰ አይሁንብኝ ። ይህም ነፍጥ አገሬን ስለማዳን ለመመከት ነው እንጂ ኢጣልኖችን ለመውጋት ይሆናል ብለው እንዳይጠረጥሩኝ ምዬልዎታለሁ ። በደብዳቤ ብናደርገው ይበዛል ብዬ ኮንት አንቶኔሊ ቃል በቃል እንዲነግርዎ ብዙ ነገር አጫውቼዋለሁ ። ይህን ሁሉ መናገሬ እንደ ወንድም ነው ። ለኮንት አንቶኔሊ ስነግረው በቅዱስ ወንጌል በቅዱስ መስቀል አምዬ ነውና እርሱ የሚነግርዎን የኔን ነገር ሁሉ ይመኑልኝ ። ቃሉንም ሰምተው ለመስከረም ሸዋ እንዲገባልኝ ያድርጉልኝ ። ይህንንም ነፍጥ ይምጣልኝ ስላልሁ ለኮንት አንቶኔሊ ስለዛሬ ጭንቅ የኢጣልያ መንግሥት ገዝቶ ያበድረኝና መንግሥት የሰጠውን (ያቀረበውን) ዋጋ ኋላ አሰብ ድረስ እከፍላለሁ ማለቴ ነው እንጂ የኢጣልያ መንግሥት እንዲያው ይስጠኝ ማለቴ አይደለም ብዬ ነግሬዋለሁ ። እግዚአብሔር በረዳትነቱ ዕድሜያችን ልክ ፍቅራችን እንዲጠና ለልጅ ልጃችንም ርስት እንዲሆን ያድርገው ። በሰኔ 30 ቀን 1880 ዓ.ም በእንጦጦ ከተማ”[1]

በዚህ ዐይነት ፣ ንጉሥ ምኒልክ እስካሁን ከዐፄ ዮሐንስ ጋር የጋብቻ ዝምድና የተበረዘበትን የድብብቆሽ ጠብ አሁን በገሃድ ገልጸው ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ረገብ አድርገው ይዘውት የነበረውን የወዳጅነትና የፖለቲካ ግንኙነት አሁን እንደ ኢትዮጵያ ልማድ በወንጌልና በመስቀል መሐላ ባዲስ ኃይል ቀስቅሰው ለማጥበቅ ፈልገዋል። እንደዚህ ረገብ አድርገው ይዘውት የቆዩትን ዝምድና አሁን የፈለጉትና መሣሪያውንም በጥድፊያ እንዲደርሳቸው ለመለመን ያስገደዳቸው

* ኮንቴ ፖር የሚባለውን የኢጣልያ አገር መርማሪ የአሚር አብዱላሂ ሰዎች ገድለውት ስለነበረ ፣ እርሳቸው አብዱላሂን አሸንፈው ሐረርን በያዙ ጊዜ እንደ መበቀል ቆጥረውታል ። እንደ መበቀል የቈጠሩት ግን አሁን ነው ።

1 C. Rosseti, Documenti Amharici - Guidi Storia Diplomatica ... p. 305.

ከጐጃም ወረራና ብዝበዛ በኋላ ፣ ቀጥሎ ከብዶ ሊመጣ የተዘጋጀው የንጉሠ ነገሥቱ የጦርነት ዳመና በራሳቸውና በመደበኛ ግዛታቸው በሸዋ ላይ ስለ እንዣበበ ነው ። ከዐሥር ዓመት በፊት ያለውዴታ በግዴታ እንዳደረጉት ሁሉ ፣ አሁን ሁለተኛ ወዳፄ ዮሐንስ ቀርበው እጅ ነሥተው ላለመገበር በአሳባቸው ሲወስኑ ፣ አስፈሪውንና ድል አድራጊውን የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ለመመለስ የሚችሉት በጦር መሣሪያ ብዛት መሆኑን ስለተረዱትና ባሁኑም ጊዜ ከእንግሊዝም ከፈረንሳይም ይልቅ ለጥቅሙ ሲል የጦር መሣሪያ ሊያቀብላቸው የሚችለው የኢጣልያ መንግሥት ብቻ መሆኑ ስለ ገባቸው ነው ።

መቼም ንጉሥ ምኒልክ ከምጥዋ መያዝ በፊት ካለው ጊዜ ጀምሮ ከፈረንሳይና ከእንግሊዝ የበለጠ ከኢጣልያ መሪዎች ጋር የሚያደርጉት የደብዳቤና የገጸ በረከት ልውውጥ በርከት ያለ መሆኑ አይጠረጠርም ። ነገር ግን ፣ ባፄ ዮሐንስ ዘንድ እንደታሙት በኢጣልያ ወደ ምጥዋ አገባብ ላይ ግን በፍጹም እንደሌሉበት የታወቀ ነው ። ይኸንኑም የኢጣልያኖቹ ጸሐፊዎች ሳይቀሩ በየመጽሐፋቸው አረጋግጠዋል ።[1] የኢጣልያን ወታደር ምጥዋ መግባት ወሬውን በደብዳቤ የተረዱት ሐረርጌን ድል አድርገው ወደ እንጦጦ ሲመለሱ ከንጉሠ ነገሥቱ ደብዳቤ መሆኑን በዚህም ምክንያት “ምንድነው ነገሩ” ብለው አንቶኔሊን ቢጠይቁት ፣ እሱም የሚያውቀው ነገር አለመኖሩን ገልጾ ወደ መንግሥቱ መሪዎች ለጥያቄ መጻፉን ከዚህ በፊት አመልክተናል ።

አሁን ባላደረጉት ነገር ፣ “ጣልያንን ያስመጡ ንጉሥ ምኒልክ ናቸው” የሚለው ወሬ ባፄ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት ገኖ መውራቱን ከየወዳጆቻቸው እንደ ሰሙት በዚያው አቅራቢያ በመቀሌ ይልቁንም ወደ ደብረ ታቦር ጠርተው ለጤናም ይሁን ለወቀሳ ሳያነጋግሩአቸው እንዲሁ በደፈናው ፣ “በመጣህበት ተመለስ” ማለታቸው ግልጽ ጠብ መሆኑ ስለ ተሰማቸው ፣ በልባቸው ቂማቸውን ይዘው በጎጃም ዐልፈው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን አስከድተው ወደ ሸዋም ሲገቡ ይኸንኑ ለመኳንንቶቻቸው ለነራስ ዳርጌም ፣ ለነእቴጌ ጣይቱም አዋይተው “ወደፊት ላፄ ዮሐንስ አልገብርም” ብለው ለወሰኑት ውሳኔ እንዲተባበሩ አድርገዋል ።

ኮንት አንቶኔሊ እንደሚለው ፣ ቀደም ባለው ጊዜ ውስጥ እቴጌ ጣይቱና አንዳንድ መኳንንቶች ከኢጣልያ ጋር ስላገር ነጻነት የተሰለፉትን ዐፄ ዮሐንስን መርዳት አለብን የሚሉት ሁሉ ፣ አሁን ምኒልክ

1 A. Del Boca, Gli Italiani in Africa Orientale, p. 305.



ከቤጌምድርና ከጐጃም ከተመለሱ ወዲህ ዮሐንስን በመጥላት ሁሉም በምኒልክ ዙሪያ ተባብረዋል ። በእርግጥም ቀድሞውንም ባይቀርም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ምኒልክና ኡምቤርቶ ደብዳቤና ገጸ በረከት እየተለዋወጡ የበለጠ ሲወዳጁ ፣ ጣይቱና የኢጣልያ ንጉሥ የኡምቤርቶ ባለቤት ማርጌትም የወዳጅነት ደብዳቤ በመለዋወጥ ላይ ነበሩ ። እንኳን እነሱ መኳንንቱ እነራስ ጐበና ፣ እነራስ መኰንን ፣ እነ አዛዥ ወልደ ጻድቅ በአንቶኔሊ አማካይነት ከነክሪስፒ ጋር የወዳጅነት ደብዳቤ መጻጻፍ ዠምረው ነበር ። ሰነዚህም ሁሉ ወደፊት እንደምናነበው በልዩ ልዩ መልክ ገጸ በረከቱ ሲላክ ከዚህም ወደነኛ ይሔዳል ።

የዮሐንስና የምኒልክ መተባበር ፣ ለኢጣሊያ የቅኝ አገር አገባብ እንቅፋት በሆነው መጠን የሁለቱ መጣላት ከዚያም ዐልፎ ሁለቱ እርስ በርሳቸው ተዋግተው መዳከማቸው ሰፊ የመግቢያ በር እንደሚያስገኝ በማሰብ ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩንና የውጭ ጉዳይንም ሚኒስቴር በተጠባባቂነት የሚመራው ክሪስፒ ከጦር ሚኒስትሩ ከቤርቶሌ ቪያሌ ጋር በመተባበር በምኒልክ ቤተ መንግሥት ስለነበረው ሁኔታ በአዲስ አበባ አንቶኔሊና ትራቬርሲ ፣ በሐረር በደጃዝማች መኰንን ዘንድ የተቀመጠው ቺዛሬ ኔራሲኒ ፣ በምጥዋ ግንባር ያለው የጦሩ ጠቅላይ አዛዥ ዤኔራል ባልዲሴራ ፣ በሐማሴን ፣ በሠራዬ ፣ በአከለጉዛይ ፣ በቦጐስ ፣ በሐባብ ፣ በመንሳና በቤኒአሚር ስለሚሆነው ፣ ከዚያም ዐልፎ በቤጌምድር ፣ በጐጃምና በወሎ በንጉሠ ነገሥቱ አካባቢ ስለአለው ሁኔታ ከየሰላዮቻቸው ወሬ እያጠናቀሩ በትጋት ወደ ሮማ በራፖር ወይም በቴሌግራም እንዲያስተላልፉ ታዘው ነበር ።

ለነዚህ ሁሉ በተለይ ለምጥዋው አስተዳዳሪ የተሰጠው መመሪያ በተቻለ መጠን እስላሙንና ክርስቲያኑን ማጋጨት ፣ ከንጉሠ ነገሥቱም ከነራስ አሉላም እየተጣሉ ወደነርሱ የሚጠጉትን ሁሉ ሹመትና የጦር መሣሪያ ከጥሬ ገንዘብ ጋር እየሰጡ ማበረታታትና ያፄ ዮሐንስን መንግሥት ማዳከም ፣ ከእስላሙም ከክርስቲያኑም መካከል ወታደር እየመለመሉ ቀለብ እየሰጡ ልብስ እያለበሱ ለውጊያ ማደራጀት ነበር ።

ስለዚህም ፣ ባለፈው ካፄ ዮሐንስ ከድተው ወደነርሱ የመጡት ደጃች ደብብ አርአያ በስሐጢው ዘመቻ ጊዜ ባባታቸው ምክር ከጣላት ጋር ሆኜ አገሬን አልወጋም ብለው ላፄ ዮሐንስ መጥተው ከተደረቡ ወዲህ ፣ አሁን ደግሞ ተመልሰው ለኢጣልያኖቹ ሲገቡ ባለፈው ሥራቸው ተቀይመው አንቀበልህም አላሉዋቸውም ። ‘እንኳን ደህና መጣህ’ በማለት እንደገና የጦር መሣሪያና ጥይት እየመጠኑ በመስጠት የነጋሢነት ዓላማቸውን የሚደግፉ እየመሰሉ ፣ በነርሱም

እማካይነት ለመንግሥት አብቁኝ እያሉ በአደኑ ገዥ በኩል ከእን
ግሊዝ መንግሥት ጋር እንዲጻጻፉ አድርገዋቸዋል ። የእንግሊዝ መን
ግሥት ግን ለደብብ ምኞት ምንም ዐይነት ዋጋ ባለመስጠት ለጥያ
ቄያቸው መልስ እንኳን አላገኙም ። እዚያው ከኢጣልያ ባገኙት መሣ
ሪያ ግን ፣ ደብብ በየካቲት ወር መጀመሪያ (1881 ዓ.ም.) የራስ አሉላን
እማች ደጃች ኃይለ ሥላሴን በአዲባሮ ላይ ተዋግተው መግደላ
ቸውንና ወደፊትም ዐፄ ዮሐንስ ከነጠራቸው ቤጌምድርና ጐጃም ባሉ
በት ሰዓት በኢጣልያኖቹ እርዳታ ከሐማሴን ዐልፈው እከሱምንና
ዐድዋን ለመያዝ መዘጋጀታቸውን ጣልያኖቹም እሥመራን እንዲይዙ
መጋበዛቸውን ጄኔራል ባልዲሠራ ለጦር ሚኒስትሩ የካቲት 1881
ዓ.ም. ባስተላለፈው የቴሌግራም ቃል ገልጾታል ።[1]

እንደዚሁም ፣ የንጉሠ ነገሥቱ የክርስትና ልጅ የወሎው ባላባት
ራስ ሚካኤል በበኩላቸው ፣ "ምናልባት ፈረንጅ ጥበበኛ ነው ፣ ኃይለኛ
ነው ፣ ዐፄ ዮሐንስን አሸንፎ ኢትዮጵያን የወረረ እንደሆነ እንዳልጠቃ
በሚል ሥጋት ለአንቶኔሊ ፣ "እኔም ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ተባባሪ
ነኝ" የሚል የቃል መልእክት በዳዊ ሰዎች እጅ ለባልዲሠራ በላኩበት
ጊዜ አሳባቸውን በጽሑፍ አድርገው በመሐመድ አንፋሪ እማች በአ
ብዱልራህማን እጅ ይላኩብኝ ካላቸው ወዲህ በጽሕፈት ማድረጉን
አልደፈሩም ። ይኸውም ምናልባት የጽሑፉ ደብዳቤ መንገድ ላይ
ወድቆ ባፄ ዮሐንስ ሰዎች እጅ የተገኘ እንደሆነ አደጋ እንዳያመጣ
ባቸው ለመጠንቀቅ ይሆናል ።

ቢሆንም ፣ አንቶኔሊ በጥብቅ የሚከታተለው ከሌሎቹ ሁሉ የበ
ለጠ ምኒልክን ከዮሐንስ ጋር የማጣላቱንና የማዋጋቱን ጉዳይ ነበር።
ከምኒልክ በምስጢር ተነጋግሮ ለኡምቤርቶ የተጻፈውን የጦር መሣ
ሪያ በሚያስችኩል የሚጠይቀውን የምኒልክን ደብዳቤ ተቀብሎ ከመ
ላኩም በፊት ፣ በላከበትም ጊዜና ከላከም በኋላ በትጋት የኢጣልያን
ባለሥልጣኖችን አጥብቆ በመወትወት የሚያሳስበው፡-

1ኛ/ ያሁኑ የምኒልክና የዮሐንስ የከረረ ጠብ ለኢጣልያ በሰሜን
በኩል ስለሚያስበው የመስፋፋት ዓላማ ምቹ ሁኔታን ስለፈ
ጠረ ፣

2ኛ/ በሁለቱ ነጋሢያን መካከል ተሞክሮ የነበረው የወይዘሮ ዘው
ዲቱና የራስ አርአያ የጋብቻ ዝምድና አሁን በአርአያ መሞት
ስለ ተቋረጠ ፣

3ኛ/ ባሁኑ ጊዜ ዐፄ ዮሐንስ ከጐጃም በኋላ ወደ ሸዋ ለመዝመት
ስለአሰቡ ፣ ምኒልክም ለመመከት ከልብ ስለቆረጡ ፣ የጠየቁት
የጦር መሣሪያ በአስብ በኩል ሳይዘገይ ይላክላቸው የሚል
ነበር ። ለጠቅላይ ሚኒስትሩ መሣሪያው ለምኒልክ እንዲደርስ
በላከው ደብዳቤ ላይ አሳቡን ሲደመድም፡-

"... ምኒልክ ለመዋጋት የሰጡትን ቃል በሙሉ እንደሚፈጽሙ
ከልቤ ባልረዳው ኖሮ እንደዚህ አድርጌ አጥብቄ በመጻፍ መሣሪያው
እንዲላክ አልጎተጉትም ነበር ። ኢጣልያ ከሁለቱ ነገሥታት ውጊያ
የምታገኘው ጥቅም በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። ምኒልክ የኛ የታ
መነ የቃል ኪዳን ጓደኛ ሆኗል ። እሱም በቀላሉ ዮሐንስን ሊያዳክምልን
ችሎታ አለው ። የሸዋይቱ ንግሥት ጣይቱ ራሷ ቀደም ብላ ለዮሐንስ
ታደላ የነበረችው ፣ አሁን ዋና ጠላት መሆኗን ራሷ ገልጣልኛለች ።
ዛሬ የሸዋ ሰው ሁሉ ተስፋው በኢጣልያ መሆኑን አረጋግጣለሁ ።"[1]

ቀጥሎ በሐምሌ ወር ወደ ሮማ ደርሶ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ባቀ
ረበው ራፖር ውስጥ የሸዋን ብቻ ሳይሆን የሐረርን ፣ የኦሮሞን አገር፣
የጐጃምንና የቤጌምድርን ሁሉ ሁኔታ በደንብ ማጥናቱን ፣ ኢትዮጵያን
ለቆ ወደ ሮማ ሲመጣ የነበረው ሁኔታ የክረምቱ ጊዜ በጥቅምትና
በኅዳር ሲያልቅ ዮሐንስ ወደ ሸዋ ሔደው ምኒልክን ለመውጋት መቁ
ረጣቸውን ፣ ምኒልክም ከኛ ዐሥሩን ሺህ ጠበንጃ ፣ አራት መቶውን
ሺህ ጥይት ካገኙ ለመመከት መቁረጣቸውን ካወሳ በኋላ ፣ ከዚህ ከሁ
ለቱ ጦርነት ኢጣልያ የምታገኘውን ጥቅም እንደዚህ ሲል በግልጽ
አብራርቶት ይገኛል ።

1ኛ. ምኒልክ ከዮሐንስ ሲዋጉ በዶጋሊና በሰሐጢ የሞቱትን
የወገኖቻችንን ደም ይበቀሉልናል ፣ በዚህ ጊዜ የመሣሪያ ኃይላችን
እንደሚፈቅድልን ከሁለቱ ውጊያ ወዲህ ለቅኝ ግዛታችን ልማትና
ጸጥታ የሚሰጠውን መሬት ለማግኘት እንችላለን ።

2ኛ. ዮሐንስ በሙሉ ጦራቸውን ይዘው ወደ ሸዋ ሲዘምቱ የን
ጉሠ ነገሥቱ ግዛት የሆነው ሁሉ ያለወታደር ባዶውን (ያለተከ
ላካይ) ስለሚሆን ፣ በዚያን ጊዜ የኛ ወታደር ወደ ጤናማውና ወደ
ነፋሻው አገር (ሐማሴን ፣ አከለ ጉዛይ ፣ ሠራዬ) በቀላሉ ለመዝለቅ
ይመቸዋል ።

3ኛ. የተጠየቀውን መሣሪያ ለምኒልክ እምቢ ያልን እንደሆነ
ግን፣ እንዲሸፍቱ እኛው ከገፋፋን በኋላ መልሰን እንደ ካድን ይቆጠራል።

1 L' Italia in Africa ... Documenti (1888-1889) pp. 176-177, 196-197.



1 L' Italia in Africa Documenti ... (1888-189) pp.69-72.

በዚህ ዐይነት አልጋ ወራሹ ራስ አርአያ ከሞቱ ወዲህ ከዮሐንስ ቀጥሎ ንጉሠ ነገሥት የሚሆኑት ምኒልክ መሆናቸው የማያጠራጥር ስለሆነ ፣ በዚያን ሰዓት ከእንደዚህ ያለው መሪ ጋር ተጣልቶ ተቀያይሞ መገኘቱ ለኢጣልያ ጠቃሚ አይደለም . . . እኛም የከለከልናቸውን የጦር መሣሪያ ፈረንሳይና እንግሊዝ ሊሰጧቸው ይችላሉ ።

ኮንት ፒዬትሮ አንቶኔሊ በዚህ ዐይነት መንግሥቱን አጥብቆ ቢማጠንም ፣ ምኒልክም "በምትሰጡን መሣሪያ እናንተን መልሼ አልወጋበትም" ብለው ቢምሉም ፣ ቢገዘቱም 10.000 ጠበንጃ ሰጥተን በኋላ ከዮሐንስ ታርቀው መልሰው እኛን ቢወጉንስ የሚል ሥጋት በሮማ ባለሥልጣኖች ዘንድ ስለአደረ ፣ "ምኒልክ በቅድሚያ መሬት ቈርጠው ለመስጠት ቃል ይግቡ ፣ አንድ የቤተ መንግሥት ተወላጅ እንደማያዣ ሆኖ ሮማ ይቀመጥ" የሚል አሳብ ቀርቦ ንግግር ከተደረገ በኋላ ፣ በመጨረሻ ይኸን ሁሉ ለማድረግ ጊዜው ስላጠረ በምክር አሁን አጋማሹ ይላክ ፤ የቀረው ወደፊት የሁለቱን ነገሥታት ውጊያ አዝማሚያው እየታየ ይላካል ተብሎ ተወሰነና 5.000 ጠበንጃና 200 000 ጥይት ከኢጣልያ እስከ አሰብ ወደብ በመርከብ ተላከ ። ከአሰብ በግመልና በሰው ሸክም አንኮበር ደረሰ ። ለዚህም ክንውን በኢጣልያ አግባቢነት ጭምር የአውሳው ሡልጣን መሐመድ አንፋሪና የአንኮበሩ አዛዥ ወልደ ጻድቅ በሕብረት ይሠሩ ነበር ።

አንቶኔሊ ፣ የዚህን ጉዳይ አከናውኖ ከሮማ ተመልሶ በየካቲት 1881 አዲስ አበባ ሲደርስ ፣ ከመቼውም የበለጠ ከጠበቀው በላይ ከዚህ በፊት ተደርጎለት የማያውቀው አቀባበል እንደ ገጠመው ከሐርቱማ* ዠምሮ እቤተ መንግሥቱ እስኪደርስ ድረስ 4.000 ወታደር ያስከተሉ በልዩ ልዩ ቀለም ያሸበረቀ ልብስ የለበሱ ሹማምንቶች እንደ አጀቡትና ወደ ቤተ መንግሥቱ ገብቶ በደስታ ከንጉሥ ምኒልክ ጋር መገናኘቱን ፣ ከተገናኘና ሰው ሁሉ ከተገለለ በኋላ ፣ ዐፄ ዮሐንስ ወደ ሸዋ ለመዝመት ወደ ግንደ በረት ማዝገማቸውን ፣ ለጊዜው በእጃቸው የገባውም 4.700 ጠበንጃና 200.000 ጥይት በቂ አይደለም ብለው ምኒልክ እንደ ገለጹለት ያመለክታል ።[1]

---

* ሐርቱማ ወይም አርጡማ የሚገኘው በአውሳና በይፋት መገናኛ ላይ ነው ። ወደ አርጐባ ይጠጋል ።

1 L' Italia in Africa . . . Documetni (1888-1889) pp. 207-208; A. Del Bǫca, Gli Itaiani in Africa Orientale, pp. 306-309.



# ምዕራፍ ዐርባ ስምንት

## በሸዋ የተጠንቀቅ ዐዋጅ—ያፄ ዮሐንስና የንጉሥ ምኒልክ በደብዳቤ መወቃቀስ

ንጉሥ ምኒልክ ፣ ዠሮአቸውን ወደ ጐጃም አድርገው ከውጭም ባገኙት የጦር መሣሪያ ወታደራቸውን እያስታጠቁ የሚመጣውን በመጠባበቅ ላይ እንዳሉ ፣ በመጨረሻ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ላፄ ዮሐንስ መግባትና ከዚያም ቀጥሎ ንጉሠ ነገሥቱ ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን እንደያዙ ከጐጃም ወደ ሸዋ ለመዝመት መዘጋጀታቸውን ሰሙት ።

ስለዚህ ለመመከት ሁለተኛም ላፄ ዮሐንስ ላለመግባት ልባቸው ስለቆረጠ ፣ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የክተት ዐዋጅ አደረጉ ።

"ስማ የሸዋ ሰው ስማ ! ያገሬ ሰው እስካሁን ስላገሬ ስለድሃዬ የለፋሁትን የደከምሁትን ታውቀዋለህ ። አንተም እስካሁን ባልሁህ እደኸየሁህ አሁን እኔ ሳልሞት አላስነካህም ልጄም ወንድሜም አገሬ ነውና ስላገሬ እሞታለሁ እገላለሁ ። አሁንም ከጋላ አገር የመጣውን ሰው ጓዝ ፣ እርጉዙን ፣ በሽተኛውንና ለመዝመት የማይችለውን ያዝልኝ ። ከኔም ጋር ለሚዘምተው ለጋሻውም ለጓዙም ያንድ ወር ቀለብ ስጥልኝ ። በጐጃም የሆነውን ነገር ሰምተኸዋልና በእጅህ የሰጠኸው አይጎዳህም በእህል መስፈር አትመረር ። እንግዲህማ ማረፊያህ ደርሷል ። ለጥቂት ቀን ነው እንጂ እስከ ሁሉም አነሣልሃለሁ ። ወታደርም የወር ቀለብህን ተቀብለህ በኅዳር መድኃኔ ዓለም ክተት እርጉዝና በሽተኛ የማይችለውን ጓዝህን ተው እንጂ ጠንካራ ጓዝህን አትተው ። ካንድ ሹም ወዳንድ ሹም ካንድ አለቃ ወዳንድ አለቃ የሔድህ ሰው አይሆንም ሐያጅም ተቀባዩም ጠላቴ ነው ። ባገሬ ያለህ ወንድ ልጅ የምትዘምተው . . . ለቤትህ ፣ ለሚስትህ ፣ ለልጅህ ነውና ለእርዳታ ጦር የበቃህ ወንድ ልጅ አትቅር ፤ የቤትህን የሚስትህን ፤ የልጅህን ጥፋት ከማየት ጠንክረህ ወጥተህ ከድንበርህ ላይ መሞት መጋደል ይሻልሃል ። ለጦር የበቃ ሰው ዛሬ ሳይወጣ የቀረ ሴት ነው እንጂ ፣ ወንድ አይባልም በሚስቱ ስም ይጠራ ። ገንዘቡንም ከሚስቱ አይካፈል ። ከርሱ ሚስቱ ትሻላለችና ገንዘቡንም

ለሚስቱ መርቄላታለሁ ። በኅዳር በ15 ቀን 1881 ዓ.ም ይኸም የከተት ዐዋጅ በገበያው ሁሉ በየአደባባዩም ተነገረ ።

ንጉሡ ይኸን የመሰለ የማስጠንቀቂያ ዐዋጅ ሲያደርጉ አንድ ጊዜም ያፄ ዮሐንስን ስም አልጠቀሱም ። ነገር ግን የከተቱ ዐዋጅ ባፄ ዮሐንስ ላይ መሆኑን የሚያረጋግጠው ፤ "በጐጃም የሆነውን ነገር ሰምተኸዋል" የሚለው ዐረፍተ ነገር ነው ። በዚህ ዐይነት ሠራዊታቸውን ይዘው በ1880 ዓ.ም. ከኅዳር ወደ አምባጫራ ዘምተው በሰኔ ወር በዚሁ ዓመት ወደ እንጦጦ ከተመለሱ በኋላ ፤ በ6ኛው ወር በኅዳር በ1881 ዓ. ም በዚህ ዐዋጅ ጦር ሠራዊታቸውን እንደገና ወደ አባይ ዳር ማዝመታቸው ነው ። ስለዚህ "አንተም እስካሁን ባልሁህ አደኸየሁህ" ያሉት በተቀራረበ ጊዜ ውስጥ ከሐረርጌ ዘመቻ (1879 ዓ.ም) ወደ አምባጫራ (በ1880 ዓ. ም) ከአምባጫራ ከተመለሱ በኋላ ፤ አሁን ደግሞ በ1881 ዓ. ም. ባሁኑ ዘመቻ ወታደሩን መቀስቀሳቸው ለወታደሩ ባላገሩን ስንቅ ስፈር የማለቱ ጉዳይ ስለ ጸጸታቸው ነው ። የሆነ ሆኖ ፤ ንጉሥ ምኒልክ ከወለጋ ጫፍ ጀምሮ እስከ ደራ ግዛት በደጃች መኰንን የሚታዘዘውን የሐረርጌን ጦር ፤ በሰላሌና በደራ ግንባር የራስ ዳርጌን ጦር ፤ በአባይ ወንዝ በምሥራቅ በኩል ዳር ዳሩን አሰለፉት ። ቀደም ባለው ጊዜ በወለጋ በኩልም ብዙ የጦር መሣሪያ (ነፍጥ) የያዘ ደርቡሽ ተነሥቶ ለዚሁ ራስ ጎበና ዘምተው ስለ ነበረ ፤ ግማሹን ደግሞ በዚያ ግንባር ማሰለፍ ግዴታ ሆኖባቸው ነበር። እንደ እውነቱ የራስ ጐበና በደርቡሽ የተነሣ ወደ ወለጋ ተባለ እንጂ ዋናው ጉዳይ ያፄ ዮሐንስ አመጣጥ በጉድሩ በኩል ነው ተብሎ ገነን ብሎ ስለ ተወራ በዚያ ግንባር ያለውን ለማጠንከር ፤ ሸፍቷል ወይም ሊሸፍት ነው የተባለውን የጅማውን አባ ጅፋርን ጭምር ለመጠባበቅ ነው ። ከዋናው የጦር ጠቅላይ አዛዡ ከራስ ጐበናም ጋር የንጉሡ የእኅስት ልጅ ደጃች በሻህ አቦዬ ወደ ጉድሩ ተልከዋል ።[1] ምኒልክ በዚህ ዐይነት የመከላከያ ኃይላቸውን እያጠነከሩ በሌላው በኩል ሁለቱን አስታርቃለሁ ብለው ለሚደክሙት ለአቡነ ማቴዎስ በደላቸውንና የሚታረቁበትን መንገድ ከማስጠናት አልቦዘኑም ።

በኩላቸው ዐፄ ዮሐንስ ፤ ከጉዛምን ወደ አባይ ዳር ደርሰው በአባይ ወንዝ በወዲህኛው ማዶ ዳር ዳሩን የሠፈረውን የሸዋ ጦር ብዛቱን በመነጽር አይተው ንጉሥ ምኒልክ በሠራዊታቸው መካከል ያሉ መስሏቸው "ምነው የንጉሡ ቀይ ግምጃ ድንኳን አይታይ"

1 L'Italia in Africa....P. 187.



ብለው ቢጠይቁ ፤ "ይህ የሚታየው የሐረሩ ጌታ የደጃዝማች መኰንን ጦር ብቻ ነው ፤ ንጉሡ እንዲያውም ከአዲስ አበባ አልተነሡም" ብለው ውስጥ ዐዋቂዎች ነገሩአቸው ይባላል ።

ከዚህ በኋላ ፤ ዐፄ ዮሐንስ ምኒልክ ለውጊያ መቁረጣቸውን ብቻ ሳይሆን ፤ በጐጃም እንዳደረጉት ወደ ሸዋ ለመዝመት በቀላሉ የማይመች መሆኑን በሕሊናቸው ስለ ተረዱት ፤ ወደ ዳሞት መለስ ብለው በሠፈሩበት ሰዓት በቀጥታ ለባለጉዳዩ ለምኒልክ መጻፉንም ስለ ጠሉት ፤ በንጉሡ እኅት በራስ ዳርጌ ሣህለ ሥላሴ አማካይነት ትንሽ ማስፈራራት የተጨመረበት የወቀሳና የስሞታ ደብዳቤ ይጻጻፉ ጀመር ።

በኅዳር 18 ቀን 1881 ዓ.ም ከንጉሠ ነገሥቱ ካፄ ዮሐንስ ለራስ ዳርጌ የመጣው የደብዳቤ ቃል እንደዚህ የሚል ነው ።

"....11 ዓመት ሙሉ በፍቅር ተጠምደን በምግባርና በሃይማኖት አንድ ሆነን ሳለ.... አሁን ዲያብሎስ ፀላኤ ሠናያት ነውና የአሕዛብ መሣለቂያ ሊያደርገን ከሁለታችን ወንድማማች መካከል እንዲህ ያለ ነቅ አገባብን .... ዝምድናችን እንዲጸና... ምንም እግዚአብሔር ቢያሳፍረን ልጅ ከልጅ አጋባሁ... አሁንስ በትውልድ አባት ነዎ በዕድሜ ሽማግሌ ነዎ ሰይጣን በሆኑ ሰዎች አድሮ ነገር ሲያበላሽ እያዩ ምነው ዝም ይላሉ... አህጉረ ኢትዮጵያን ሁሉ ከፍዬ ሰጥቼ ትግራይንና ቤጌምድርን ይገዢ ብቀመጥ በቤጌምድር ሹም ሽር ተደረገበት በትግራይም የንጉሥ ደብዳቤ አልመጣ እንደሆነ ነው እንጂ የመኳንንቱ ደብዳቤ በሀገሩም በሰፈሩም ያልመጣበት በመልክት ያልተባባለ ፤ ወርቅ ያልተቀበለ ሰው አይገኝም .... አሁንም አምባጫራ ወርዳችሁ ሳለ ፤ በደምቢያም በቤጌምድርም ያለ ሁሉ ዝግናውም ደብተራውም ፈላሻውም ሴቱም የቀረ የለም ። እየተባበለ ከናንተ ጋር ባንድ ሄደ ። ሳይጠሩኝ ይኸን ሁሉ እየሰማሁ ዝም ብል በመጨረሻም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን አባብላችሁ አስከዳችሁት... ይኸን ሁሉ እያደረገ እናንተንና እኔን ሰይጣን ሆኖ የሚያፋጀን ቤገምድሬ መሸሻ ወርቄ የሚባል መካር አበጅታችሁ የተንኮሉ ሁሉ ምንጭ እርሱ ነው እንጂ ከንጉሥም ከናንተም ይኸን ያህል ተንኮል ፤ እንደሌለ አውቃለሁ ። አሁንም እኔ ግድ የለም አስተውላችሁ ብትመክሩበት ይሻላል ። ደብዳቤውንም እርስዎ አይተው ወደ ልጅዎ ወደ ንጉሥ ይስደዱት ።"

ራስ ዳርጌ ይህ ደብዳቤ ሲደርሳቸው ፤ በጉዳዩ ደንግጠው በቶሎ ወደ ንጉሥ ምኒልክ ላኩት ። ምኒልክም ደብዳቤውን ካዩ በኋላ ከዚህ የሚከተለውን መልስ በታኅሣሥ 15 ቀን 1881 ዓ.ም ጻፉ ።

“. . . ሰይጣናት በሰው አድረው በእኔና በጃንሆይ መካከል ነቅዕ ስለ አገቡብን ደብዳቤውን አይቼ እጅግ አዘንሁ ። እኔም ከመስጋቴ በቀር ከያዝሁት መንግሥት ሌላ መንግሥት ፈልጌ እንደሆነ ጃንሆይንም ጠልቼ የጃንሆይ መንግሥት እንዲናወጥ አድርጌ እንደሆነ እግዚአብሔር ምስክሬ ነው ። ደግሞም እስካሁን በጃንሆይ ትእግስት በጃንሆይ ልብ ጥሩነት ነው እንጂ ሠራዊቱማ የሚያወራብኝ ብዙ ነው ። ፊት ደርቡሽን አመጡ ተብዬ ነበር ። ኋላም ኢጣልያ ቢመጣ ይኸንኑ አለኝ ። እኔ ግን ይህን ሁሉ ቢያወራ ግድ የለም ከጦርነቱና ከሞቱ የተለየሁ እንደሆነ ያን ጊዜ ሁሉም ይታወቃል ብዬ ሠራዊቴን እስ ከትቼ ብመጣ ጃንሆይ ወደ ደርቡሽ አዘዙኝ ።

“እኔም ደስ ብሎኝ እግዚአብሔር ኃይል ቢሰጠኝ የክርስቲያን ደም እመልሳለሁ ብሞትም ሰማዕትነት እቀበላለሁ ብዬ ሄድሁ በእግዚአብሔር ቸርነት በጃንሆይ ሃብት ጠላታችን ሸሽቶ ቢሄድ ታርቀው ሄዱ እያለ ያወራል አሉ ። ዳግመኛ ጃንሆይ ባዘዙልኝ ቃል ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መልካም አድርጎ ቢቀበለኝ ደስ ብሎኝ ክርስቲያን ለክርስቲያን ወንድም ለወንድሙ መርጠብ ይገባል መስሎኝ 2 መድፍ 250 ጠመንጃ ረጥቤው መጣሁ ። ይህ ነውር ሆኖብኝ ንጉሥ ተክለ ይማኖትን አባብላችሁ አስከዳችሁት ይላል . . . አሁንም የፈራሁብትን ነገር ከምህረትዎ ጋር ላባታችን ላቡነ ማቴዎስ ነግሬያለሁ ። ለራስ ዳርጌም ጽፌአለሁ ።”

በበኩላቸው የሁለቱም ሽማግሌ ራስ ዳርጌ የንጉሡ ነገሥቱንና የንጉሡን ደብዳቤ ለሁለቱም ከላኩ በኋላ ፣ በሁለቱም ዘንድ ዕርቅና ሰላም እንዲወርድ ሲሉ ላፄ ዮሐንስ በታኅሣሥ 15 ቀን 1881 ዓ ም በላኩላቸው ደብዳቤ ውስጥ እንደዚህ ብለዋል ።

“. . .ወደኔ የተላከው የጃንሆይ ደብዳቤ ደረሰልኝ እኔን ሽማግሌ አድርገው ስለላኩብኝ እግዚአብሔር በምሕረት ልቡናው ያስብዎ ደብዳቤውንም ዓይቼ ወደ ንጉሥ ምኒልክ ሰደድሁት . . .ከንጉሥ ምኒልክም የመጣልኝን ማህተም (ደብዳቤ) ነገሩ የተንኮል የክፉት እንዳልሆነ ባየው ከንጉሥ ሳላስፈቅድ ጃንሆይ እንዲያዩት ብዬ ይኸው ሰድጀዋለሁ ። አሁንም ጃንሆይ ምሕረት ልማድዎ ነውና ከልብዎ ይማሩት ። መግባቱን ግን ሥጋት ከሆነበት ጃንሆይ የሰይጣናትን ክንፍ ይሰበሩት ። ኋላም ነገሩ እየተመረመረ እንደዚህ ቀደሙ ፍቅርዎ ሰቦት ቶሎ እንዲገባ አውቃለሁ ። እግዚአብሔር ምክሩን ጥበቡን ይግለጥልዎ ።”

ዐፄ ዮሐንስ ይኸና ከንጉሥ ምኒልክ የተጻፈው ደብዳቤ ከደረሳቸው ወዲህ ፣ አንድ ጊዜ ልባቸው ስለ ተቀየመ ፣ ለምኒልክ መጻፉን ትተው ከምኒልክ ለተላከው ደብዳቤ መልስ ለራስ ዳርጌ ብቻ እንደዚህ ሲሉ መልሰዋል ።



“. . .ኢጣልያ የመምጣቱ ወሬ የመጣልኝ በሐረርጌ በደጃዝማች መኰንን በኩል ነው ።* ኢጣልያን ንጉሥ ምኒልክ አመጡት እያለ በደጅ ይጫወት እንደሆነ ነው እንጂ በፊቴ ደፍሮ እንዲህ ያለ ነገር የሚናገር የለም ። ከዚያ በኋላም መምጣቱ ከታወቀ ወዲያ ጃንሆይ የጦሩ ለት እንዳልለይ ያድርጉልኝ የሚል የንጉሥ ቃል በአቡነ ማቴዎስ እጅ መጣልኝ ። እሺ ብዬ ወደ ንጉሥ ላከሁኝ ። ከዚያ ወዲያ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ድል ሆኖ (በሣር ወሀ) ነበርና ዳግመኛ ሕዝበ ክርስቲያኑን ደርቡሽ መጥቶ ይፈጀዋል ብዬ ቢያሳዝነኝ በእግዚአብሔር ፈቃድ ለኢጣልያው እኛ እንበቃዋለን አምባጫራ ላይ ሆኖ እርሱን (ደርቡሽን) መጠበቅ ይሻላል ብዬ ወደ ንጉሥ ላከሁኝ ይህም ሆነ አልቀረም በምጥዋም በመተማም ያለውን ጠላታችንን እግዚአብሔር አሳፈረው ።

“ንጉሥ ምኒልክ ከደርቡሽ ጋር ተላልከዋል ብለው የደምቢያና የቤገምድር ሰዎች ይጫወቱ እንደሆነ ነው እንጂ ፣ ከኔ መኳንንቶች አፍ እንዲህ ያለ ነገር አልወጣም ። እኔም መቅደላ እከርማለሁ ብዬ ሳለሁ ደርቡሽ ወጣ (መጣ) ቢሉኝ ክርስቲያኑን ይፈጀዋል ብዬ ወደ ቤገምድር ወርጄ አሞራ ገደል ሠፍሬ ሳለሁ ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አሲረው ከድተዋል ተማምለዋል ወደ ኢጣልያም እኛና እናንተ አንድ ነን ብለው ጽፈው አትመው ሰደዋል ። ጃንሆይንም ነገሥታቱ ከድተዋቸዋል ። በወዲያም (በመተማ) ደርቡሽ መጥቶባቸዋል እንግዲህ ምን ኃይል አላቸው እያሉ ኢጣልያኖች ይሳለቁብዋል ። (ይሳለቁብዎታል) የሚሉ ወሬ ሰማሁኝ በዚህ ምክንያት ጕጃም ተሻገርሁ ። በእኔም በደህው ኃጢአት እንደሆነ አይታወቅም አገሩን ሳጠፋው ከረምሁ ። ኋላም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ታርቆ ገባ ። ከገባ ወዲያ ይኸንኑ ቃል እውነት ጽፋችሁ ልካችኋል (ወደ ኢጣልያ) ወይ ብዬ ብጠይቀው አወን ልከናል አለኝ መከዳቱንስ እውነት ተማምላችሁ ከድታችሁኛል ወይ ብለው ከጃንሆይ ጋር ውጊያ አልዋጋም ብያለሁ እንጂ መሐላውን እሺ ብዬ ምያለሁ ብሎ ነገረኝ ። ክዚያ ወዲያ ግን ወደርስዎ ደብዳቤ የጻፍሁ ከዚህ የተነሣ ነው ።

የመተማመኑ ነገር ግን ፣ እኔ አልከዳሁ መሐላ አላፈረስሁ አፍርሼ እንደሆንሁ ክርስቲያን አልባልም ። ዳግመኛ የምንተማመነው የፊቱን ማን አፍርሶት ነው ። በእኔም በንጉሥም ፈርሶ እንሆነ ከእዚህ ከኔ ጋራ ብዙ መኳንንት በወዲያም (በሸዋ) ብዙ

* መኰንንና ምኒልክን ለማጣላት ይሆን? ወይስ በርግጥ መኰንን ጣልያን ወደ ሰሐጢ መጣ ብለው ጽፈው ይሆን ?

መኳንንት አሉና በያሉበት ሆነው መርምረው እንዴ ከድቷል እንዴ መሐላውን አፍርሷል ይበሉን ። ከዚያ ወዲያ ወደ ቁም ነገራችን እንሄዳለን ። ታኅሣሥ 16 ቀን 1881 ዓ.ም.”

እንደ ተለመደው ራስ ዳርጌ ይኸ ደብዳቤ ሁለተኛ ሲደርሳቸው ወደ ንጉሥ ምኒልክ ከላኩት በኋላ ከምኒልክ እንደዚህ የሚል መልስ ለዮሐንስ የተሰጠውን ላኩ።

“ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን እውነት ልትከዱኝ ተማምላችሁ ኖሯልን ወደ ኢጣልያንስ ልካችሁ ኑሯልን ብዬ ብጠይቀው ከጃንሆይ ጋራ አልዋጋም ብያለሁ እንጂ መሐላውንስ ተማምያለሁ አለኝ የሚል አገኘሁ ። መከዳቱን ከድቻለሁ መዋጋት ግን አልዋጋም ማለት ይህ ስንፍና የማይመስል ነው እንጂ መቼ ትሕትና (ሐቅ) ነው ። ነገሩም ሐሰት መሆኑ በዚህ ይታወቃል ። መሐላ ተማምለን ነበር ወደ ኢጣልያም ተላልከን ነበር ያለውን ግን አሁን እኔ ብናገር እውነት አይመስልም ። ነገር ግን አልቦ ክዱን ዘኢያስተርኢ ወእልቦ ኅቡዕ ዘኢይትከሠት* እንዲል እግዚአብሔር ይግለጠው ። እኔ ግን የማልሁት መሐላ እንደዚህ ብዬ ነው ።

“ከአምባጫራ ተነሥቼ ፎገራ ስደርስ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት 3 መነኮሳት ላከብኝ ። የመጣችሁበት ነገሩ ምንድነው ብዬ ብጠይቃቸው ባገሬ ላይ ሊመጡብኝ ነውና ንጉሥን አስታምኑልኝ (እኔን ላይጎዱ ይማሉልኝ) ብለዋል ብለው ቢነግሩኝ ቀድሞ ጃንሆይ አማምለው አገዛዝተው አስታርቀውናል አሁን ደግሞ ከጠረጠረኝ መጥቶ አይገናኘኝ እንጂ ቢሻው አምባው (ሙተራ) ይግባ አለዚያም ከፈቀደው ቦታ ይቀመጥ ። እኔ ጃንሆይ ባዘዙኝ መንገዴን እሄዳለሁ ብዬ ለጊዜው ተቆጣሁ በኋላ ግን ነገሩ ይህ አይደለም የምንጫውትም ብርቱ ምስጢር አለኝ ይኸን ለሰው እንዳያወጡብኝ አስታምኑልኝ (አስምሉልኝ) ያሉት ስለዚህ ነው ቢሉኝ ለዚህማ ምን ከፋኝ ብዬ ታመንሁ(ማልሁ)። ወዲያው ጐጃም ገባሁ ። ከርሱ ከተገናኘን በኋላ ምን ጠርጥረኸኝ ነው ማል ተገዘት ብለህ መነኮሳት የላክህብኝ ብዬ ጠየቅሁት ።ራስ አርአያ ሥላሴ (ያጼ ዮሐንስ ልጅ) ደጃች ሥዩምን (የራስ ገብረ ኪዳንን ልጅ) ይዞ እንደሰጠ እኔንም ጃንሆይ ይያዙት ብለዎ እንደሆነ ብዬ ነው የሠጋሁት አለኝ ።

‘በምን ምክንያት ምን አጠፋህና እንደዚህ ያለ ነገር ይደረጋል ይህስ እውነት አይመስለኝም’ አልሁት ። ‘እርስዎም ኢጣልያን አመጡ ተብሎ ታምተዋል ። እኔንም የኢጣልያን መንግሥትና የጐጃም መንግሥት አንድ ነው ብለህ ጽፈሃል ብለው ጠልተውኛል ። ከገባንም ሁላችንም አይተውንም ይይዙናል’ አለኝ ። ‘ይህ በምን ይታወቃል’ ብለው‘አሁን መጥተው ጐጃም ይከርማሉ ። እኔም ከዚያ ከደንጊያዬ (የሙተራ ቋጥኝ) ገብቼ እሞታለሁ እንጂ አልገባም’ አለኝ ። ‘ሰይጣናት በፍቅር ይቀናሉ የኛን አንድነት ለመለየት ነው እንጂ ጃንሆይስ እንዲህ ያለ ነገር አያደርጉም ። አሁንም ወደ ጐጃም የመጡ እንደ ሆነ ነገሩ ተገልጦ እንዲምሩህ እንድትታረቅ ወደ ጃንሆይ ደብዳቤ እልክልሃለሁ’ ብዬው መጣሁ ። ወዲያው ደግሞ‘ንጉሥ ምኒልክ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መድፍና ብዙ ነፍጥ ሰጥተው ተማምለው መጡ ተብሎ ይህን ጃንሆይ ሰምተው ራስ አሉላ በሰሜን በኩል ተጓዙ ጃንሆይ መምጣታቸው ነውና ይጠንቀቁ’ ብሎ እዚያው ያለ ወዳጁ ላከብኝ ። ወዲያው ደግሞ ‘ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከዳኝ ወደ ጐጃም ተሻገርሁ’ የሚል የጃንሆይ ደብዳቤ መጣልኝ ። እኔም ፊት እንደ ላክሁት ‘ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ለእኔ ነግሮኛል ጃንሆይ ተናደው አገርዎን እንዳያጠፉት’ ብዬ ወደ ጃንሆይ ላክሁ ።

“የዚህም ምላሽ ‘ይልቅስ በእኛ በሁለታችን ሰይጣን አይግባብነ እግዚአብሔር እንደ ሞቱትና እንዳሉት አድርጎ አይለያየን ባገሩም ጥፋት እግዚአብሔር በፈረደው ይፍረድ’ የሚል ደብዳቤ መጣልኝ እንዲህ መታረቁ ላይቀር ሰይጣን አበርዳለሁ አስታርቃለሁ ብዬ ብልክ የኔ ቃል ሳይሰላልኝ ቀረ ። ከዚያ ወዲያ ግን የሆነ ያልሆነውን ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጻፍሁለት ። ታኅሣሥ 20 ቀን 1881 ዓ.ም.”

መቼም በሦስቱም አጻጻፍ ውስጥ ግማሽ እውነት ፣ ግማሽ እስት ያለ ሦስቱም ጠባቸውን እየደበቁ የሰላምን የዕርቅን ፣ ላገርና ለወገን የማሰብን መልክ እያሳዩ ጥፋትን ከራሳቸው እያራቁ በሌላው ለመላከክ የሚጣጣሩ ይመስላል ። በተለይ በምኒልክና በዮሐንስ የደብዳቤ ልውውጥ ውስጥ ውስጡን ተጣልተው ተቀያይመው ሳለ ፣ ላይ ላዩን በዲፕሎማሲ መንገድ ባነጋግር ይሸፍኑታል ። ውስጡን ለጦርነት እየተዘጋጁ ባንደበት ዕርቅና ሰላም ፈላጊዎች መስለው ይታያሉ ።

ዐፄ ዮሐንስ ፣ “ኢጣልያኖችን ያመጡ ንጉሥ ምኒልክ ናቸው ከደርቡሽም ተራርቀው ሳይዋጉ ተለያዩ” ተብሎ የቀረበላቸውን ወሬ አምነው ፣ ጠርተውም ሳይጠይቁ “በመጣችሁበት መንገድ ወዳገራችሁ ተመለሱ” ያሉትን ወደጐን አድርገው

* ሳይታይ ተሸሽጎ ፣ ሳይገለጽ ተደብቆ የሚቀር የለም ። የማቴዎስ ወንጌል 10—26 ።

አሁን ከደብዳቤ ልውውጡ ላይ ፣ 'ጣልያንን ንጉሥ ምኒልክ አመጡት' እያለ በደጅ ይጫወት እንደሆነ ነው እንጂ በፊቴ እንዲህ ያለውን ነገር ደፍሮ የሚናገር የለም ። "ከደርቡሽም ጋር ተላልከዋል ብለው የደምቢያና የቤገምድር ሰዎች ይጫወቱ እንደሆነ ነው እንጂ ፣ ከኔ መኳንንቶች አፍ እንዲህ ያለ ነገር አልወጣም' ብለው በንጉሥ ምኒልክ ላይ በዚሁ ረገድ ምንም ቂም አለመያዛቸውን ሽፋፍነው የምኒልክ ጥፋት በቤጌ ምድርና በሌላውም በኩል ሲያልፉ ያለፉበትን አገር መኳንን ትና ሹማምንት በሹመትና በገንዘብ እያባበሉ ከርሳቸው ጋር መውሰዳቸው ብቻ ሆኖ ይታያል ።

በበኩላቸው ምኒልክም የዐድማውን ወጣኝነት በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ላይ ከማመካኘት ጋር ለአንቶኔሊም የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ደብዳቤ ማምጣታቸው የዶጋሊን ደም እበቀልላ ችኋለሁና መሣሪያ በፍጥነት ላኩልኝ ማለታቸው እየታወቀ ለን ጉሡ ነገሥቱ እምነታቸውን እንዳላጐደሉ በንጉሥ ተክለ ሃይማኖ ትና በንጉሠ ነገሥቱ መካከልም የአስታራቂነት አቅዋም ለመው ሰድ የሚሞክሩት ሁሉ ከሐቅ መንገድ የራቀ የዲፕሎማሲ አነ ጋገር ሆኖ ይታየናል ። የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም የዐድማውን ምስጢር ቀደም አድርገው በማውጣት "መሐላውን ተማምለ ናል ጃንሆይን ግን አልወጋም ብያለሁ" ያሉት ፣ እውነት ብለው እንደሆነ ከሸፈቱትና አገራቸው ከተበዘበዘ እንዳይመከቱም መደበኛው የጦር ኃይላቸው በሣር ወሃ ጦርነት ከፈራረሰና አሁን ባዔ ዮሐንስ መዳፍ ውስጥ ከገቡ በኋላ ፣ ራሳቸውን ከቅጣት ለማዳን ያላሉትንም ብያለሁ ቢሉ ሊፈረድ አይቻልም ። ውላቸው በጽ ሑፍ ስለ አልሠፈረ ፣ ያስካደውንና የካደውን ለይተን ልናው ቀው አንችልም ።

ዐፄ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክም የሚጻጻፉት ፣ አሳባቸውንና አባባላቸውን እየተለካኩ መሆኑ በጽሑፉ ላይ ይታያል ።በራስ ዳርጌ በኩል ዐፄ ዮሐንስ በታኅሣሥ 16 ቀን የላኩት መልዕክ ክት ከፍ ያለ ወቀሳ ያዘለ መሆኑን ምኒልክ ሲመለከቱ ፣ በፊተ ኛው ደብዳቤያቸው ጊዜ ሊገልጹ ያልፈለጉትን ነገር ግን ፣ በል ባቸው አምቀው ያኖሩትን የተጠራቀመውን በደላቸውንና ቂማ ቸውን አሁን እንደዚህ ሲሉ ዘርዝረውታል ።

"ይድረስ ከሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። 'ዳግመኛ የምንተማመን የፊቱን ማግን አፍርሶት በኔም በንጉሥም ፈርሶ እንደሆነ ከዚህም ከኔ ጋራ ብዙ መኳንንት ከወዲያም ከሸዋ ብዙ መኳንንት አሉ ።



በያሉበት ሆነው መርምረው እገሌ ከድቷል እገሌ አፍርሷል ይበሉን' የሚል ቃል አገኘሁ ። ነገር ግን ፣ መጀመሪያ የተማመን ጊዜ * ካልተገናኘን (ካልገባህልኝ) ወሎን እወስዳለሁ የተገና ኘን እንደሆነ ግን ለሌላ ሰው አልሰጥም አሉኝ ። እኔም ከጃን ሆይ የምገባ ነኝ ብዬ ለሰዎቼ ባማከራቸው ግባ ቢሉኝ ለእጂ ብቻ ይታመኑልኝ ** እንጂ ከገባሁስ ዐፄ ቴዎድሮስ ሳይ ሞቱ ዠምሮ ያቀናሁትን አገሬን ወሎን ይነሡኛል ብዬ አል ጠረጥርም አላምልም ብዬ ገባሁ ።

ጃንሆይም በተናገሩት ቃል ከበሽሎ ወዲህ ስጥቼሃለሁ ብለው አዋጅ ነግረውልኝ ደስ ብሎኝ ተቀምጬ ሳለሁ ወዲ ያው ደግሞ ራስ ሚካኤል ከፋኝ አለ ወረሂመኑን ልቀቅልኝ አለኝ ለቀቅሁ ። ደግሞ የምኖርበት ሥፍራ ሳላጣ ጃንሆይን በማ መኔ ደጃች መሸሻን *** ሳይንት ላይ ባስር ፈትተው ወሰዱብኝ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አገሬ ላይ (እምባቦ) መጥቶ ቢወጋኝ እግዚአብሔር ረድቶኝ እርሱንም መኳንንቱንም ይዤ ብገባ (ወደርስዎ ብመጣ) ነፍጡን (የጦር መሣሪያውን) መልስለት አሉኝ እሺ ብዬ መለስሁ ። ደግሞ ወዲያው ወሎን ለኔ አደርገ ዋለሁ ሐዋርያ እሆንበታለሁና ልቀቅልኝ ቢሉኝ ለራስ ሚካ ኤል የሰጡብኝ እንደሆነ ይከፋኛል እንጂ ለጃንሆይማ ከሆነ እሺ ብዬ ለቀቅሁ ። ኋላ ግን ፣ ለራስ አርአያ ቢሰጡት ጥጃ ጠባ ከሆድ ገባ እንዲሉ **** ለልጂ ከሆነ ብዬ ደስ አለኝ ። ወዲያው አይስጥብኝ ሳልሁት ለራስ ሚካኤል መልሰው ቢሰጡት እየኖረ ፍቅር እየተጨመረ ይሄዳል እንጂ ይጐድላልን ብዬ በዚህ ከፋኝ ።

"እምነትና ፍቅር ፈረሰብኝ አልሁ እንጂ መሐላና ግዝትስ ፈረሰብኝ አላልሁም ። ባገሬም እኔ ባልገባ ተማምዬበት አልቆ ነበር ። ኋላ ግን ፣ ቢቀርብኝ (ቢወሰድብኝ) በቀድሞው ውሌ አለሁ ማለቴ ስለዚህ ነው ። እኔስ ለጃንሆይ ሽማግሌ ምን

* በ1870 ዓ.ም. በመዠመሪያ የገቡላቸው ጊዜ የሰጡዋቸውን ተስፋ ነው የሚጠቅ ሱት ።

** ስገባላቸው እንዳያስሩኝ ብቻ

*** መሸሻ ስይፉ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ ስለሆን ፣ ለምኒልክ ባላንጣ እንዲሆን ዮሐንስ መሞከራቸውን ባለፈው አመልክተናል ።

**** ከርስዎ ወጥቶ ለልጅዎ ክሰጡት ለኔም ለልጂ ባል ላማቹ ያው ነው ለማለት የቀረበ የቆየ ተረት ነው ።

እስፈልጐኝ ። ይኸን ደብዳቤ በብሩህ ልቡናዎ ተመልከተው ይህ ያስከፋዋል ። ይህ አያስከፋውም ብለው ጃንሆይ ይፍረዱት ። ደግሞ ይህንን ሁሉ መጻፌ የመድፈሬ (ለመድፈር) አይደለም ። ጃንሆይ ከፈቀዱልኝ ብዬ ነው ።ጥር 10 ቀን 1881 ዓ.ም. እን ጦጦ ከተማ ።”

ከዚህ ከመጨረሻው የምኒልክ ደብዳቤ በኋላ ዮሐንስ የመለሱት ደብዳቤ የለም ። በደላቸውን ከዘረዘሩ በኋላ ፣ ‘እኔ ሽማግሌ ቆጥሬ ከጃንሆይ ጋር አልከራከርም በብሩህ ልቦናዎ ተመልከተው ፣ ይህ ያስከፋዋል ይኸኛው አያስከፋውም ብለው ራስዎ ጃንሆይ ይፍረዱት’ ብለው የደመደሙት በንጉሠ ነገሥቱ ሕሊና ውስጥ ሥፍራ ያገኘ ይመስላል ።

በዚህም ላይ ምኒልክ ከመኳንንቶቻቸው ጋር መክረው ዘክረው በአቡነ ማቴዎስ እጅ በራስ ዳርጌ አማካይነት የላኩት እኔን እንደ ቀድሞው ግባ አይበሉኝ እርሳቸውም በዚያው ባገራቸው በትግራይና በቤገምድር ይቀመጡ ፤ እኔም ባገሬ በሸዋ ልርጋ እንደ ደንቡ ያመት ግብሬን ልላክ ። ያለዚያ ግን እጅህን ካልሰጠህ አይሆንም ብለው ወሰኔን አልፈው ከመጡ ለመዋጋት ቆርጫለሁ የሚል ነው ። [1] ስለዚህም ነው ሽማግሌው ራስ ዳርጌ ላፄ ዮሐንስ በጻፉት ደብዳቤ ላይ“ . . መግባቱን ግን ሥጋት ከሆነበት ጃንሆይ የሰይጣናትን ክንፍ ይሰበሩት ። ኋላም ነገሩ እየተመረመረ እንደዚህ ቀደሙ ፍቅርዎ ሰቦት ቶሎ እንዲገባ ዐውቃለሁ. . . .” እስከ ማለት የደረሱት ።

ስለዚህ ዐፄ ዮሐንስ ባንድ ወገን የምኒልክን ኃይል በመገመት ፣ ሁለተኛም ወዲያና ወዲህ እየተመላለሱ ለማስታረቅ የሚደከሙት ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ ሁለቱ የክርስቲያን ነገሥታት እንዳይዋጉ እየለመኑም ፣ እያወገዙም ስለተማጠኑ በእርግጥም የሁለቱ ውጊያ ለኢጣልያም ፣ ለደርቡሾቹም መግቢያ ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ባገርና በወገን ስሜት አመዛዝነው ወይም ምኒልክን የማሳመኑ ጉዳይ በኋላ ያደርሰኛል በማለት ፊታቸውን ወደ መተማ አዙረዋል ማለት ነው ።

1 L'Italia in Africa . . . (1888-1889), PP. 187-189.





ራስ ዳርጌ ሣህለ ሥላሴ

(ከሳሙኤል ቤከር መጽሐፍ)

# ምዕራፍ ዐርባ ዘጠኝ

## የወይዘሮ ዘውዲቱ ወደባታቸው መመለስ
## በዐፄ ዮሐንስና በሐምዳን አቡ እንጋ መካከል የተደረገ
## የደብዳቤ ልውውጥ

ወይዘሮ ዘውዲቱ ምኒልክ ፥ ባላቸው ራስ አርአያ ዮሐንስ ከሞቱ ወዲህ በዚያው በዐፄ ዮሐንስ ሠፈር ነበሩና የዐፄ ዮሐንስና ያባታቸውን ጠብ እየሰሙ ያዝኑ ስለነበረ ፥ "ባለቤቴ ራስ አርአያ ባይሞቱ ኖሮ ጃንሆይና አባቴ ሳይታረቁ አይቀሩም ነበር" የሚል ቃል ወረወሩ ። ይኸንኑ ዐፄ ዮሐንስ ስለሰሙ ከመኳንንቶቻቸው ጋር ተሰብስበው ታላቅ ለቅሶ ማድረጋቸውንና ከዚያም በኋላ በማዕረግና በክብር አድርገው የሚሸኙ መኳንንቶች ጨምረው በሰላሌ በኩል ላባታቸው ለንጉሥ ምኒልክ መላካቸውን ፥ የሸዋ መኳንንትም ዐፄ ዮሐንስ ወይዘሮ ዘውዲቱን ለንጉሥ ምኒልክ መያዣና ማስፈራሪያ አድርገው የሚያስቀሩዋቸው መስሏቸው ነበርና አሁን ወይዘሮይቱ ሲደርሱ ፥ ሁሉም ዐፄ ዮሐንስን ማመስገናቸውን ብላቴን ጌታ ኅሩይ መዝግበውት ይገኛል ።[1]

ዐፄ ዮሐንስ ፥ ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ባለፈው ምዕራፍ የተመለከትነውን የደብዳቤ ልውውጥ ካደረጉ በኋላ ፥ አባይን ተሻግረው በሸዋ ምኒልክን የማሳመኑን ጉዳይ እንዳለ ትተው ፊታቸውን ወደ መተማ አዙረው ከደርቡሽ ጋር ለመዋጋት ወደ ደምቢያ ሔዱ ። ደምቢያ ደርሰው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና ደርቡሾች ከተዋጉበት ሣር ወሃ ከሚባለው ሥፍራ ደርሰው ፥ በጦርነቱ ውስጥ የሞቱትን የሕዝበ ክርስቲያኑን አጥንት አይተው በጣም አዘኑ ይባላል ። እርሳቸውም ወደ ደምቢያ ሲጓዙ አንዲት ልብሷ በዮሐንስ ወታደር የተዘረፈባት የጐጃም ሴት ፥

"ዘንድሮ ንጉሡ ደህና ቢመለሱ
ምንኛ ጐልድፏል ጐጃሜ መላሱ"

ብላ በመግጠም ፥ ንጉሥ ነገሥቱ ከመተማው ጦርነት በጤና ለመመለስ እንደማይችሉ ገምታ መተንበይዋን ተክለ ሥላሴ ያወሳሉ ።[2]

---

1 ብ.ጌ.ኅሩይ ፥ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐድዋ ጦርነት ፥ ገጽ 151 ።
2 የአለቃ ተክለ ሥላሴ የእጅ ጽሑፍ ገጽ 135 ።

ሌላው ደግሞ ከወሎዮዎች የተገጠመው

“የዮሐንስ በቅሎ ብረኪ ፥ ብረኪ
በመተማ በኩል መጣልሽ ማራኪ” የሚል ነበር ።

የሆነው ሆኖ ፥ ዐፄ ዮሐንስ ወደ መተማ ለመዝመት ከመሔዳቸው በፊት ቀደም ብሎ በሣር ወሃ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ላሸነፈው ለአሚር አቡ አንጋ ደብዳቤ መጻፋቸውን ከዚህ በፊት ጠቅሰናል ። ሊጽፉለትም ከአማርኛው ደብዳቤ ጐን የዐረብኛ ትርጉም አድርገው እንደ ዐረቦች ልማድ ለአሚር ሐምዳን አቡ አንጋ በማለት ፈንታ እንደ አገራቸው ልማድ ለደጃዝማች አቡ አንጋ ብለውታል ። በደብዳቤው ውስጥ ከዐሥር ዓመት በፊት ቱርኮች እስከ መተማ ያለውን የሱዳን ግዛት ያስተዳድሩ እንደ ነበረ ፥ ከዚያም እነዚሁ ቱርኮች (ግብጾች) በምጥዋ በኩል መጥተው ሐማሴንን ስለወረሩ ሁለት ጊዜ ተዋግተው ማሸነፋቸውን ፥ ቀጥሎ ሳማራ በነበሩበት ጊዜ ማህዲ (ሞሐመድ አህመድ ኢብን ሰይድ አብደላ) እስልምናን ተቀበል ብሎ በጻፈላቸው ጊዜ ተናደው ወደ መተማ ጦር ልከው በመዋጋት ብዙ ሰው መሞቱን ፥ ከዚያ በኋላ አቡ አንጋ ወደ ደምቢያ መጥቶ በሣር ወሃ ባደረገው ጦርነት አሁንም እንደገና ብዙ ሰው ማለቁን ጠቅሰው አሁን ደግሞ መደምደሚያውን፤

“እኔ አንተ አገር መጥቼ ብዋጋ አንተ እኔ አገር መጥተህ ብትዋጋ በከንቱ ሕዝብ ከማስጨረስ በቀር ጥቅም ስለሌለው ፥ በየወሰናችን ረግተን በዚህ ፈንታ አንድነታችንን አጠንክረን የጋራ ጠላቶቻችንን አውሮፓውያንን እንመክት ። አንተም አገር መጥተው አሸንፈው ቢገዙህ እኔን አይተውኝም ። እኔም ዘንድ ቢመጡ አንተን አይተውህም ። ስለዚህ የሚጠቅመን አንድነታችንን አጠንክረን ንግድ መለዋወጡ ነው ። የሁለታችን ሕዝብ ከላይ ዘሩ አንድ (የካም ልጅ) ስለሆነ ምን የሚያዋጋን ነገር አለ?

“ስለዚህ ሁለታችን አንድነታችንን አጠንክረን በፍቅር ተሳስረን አገራችንን ለመግዛት የአውሮፓ ባህር ተሻግረው የመጡትን ፈረንጆችና ቱርኮች እንቃወም ። የአንተ ጠላቶች የኔ ጠላቶች ናቸው. . . . ከኔ በኩል የምሰጥህ ምክር ይሄው ነው” ብለው ጽፈውለታል ።

ደብዳቤውን የጻፉለት ታኅሣሥ 17 ቀን 1881 ዓ. ም በዳሞት (ጐጃም) ሆነው በዚያው ከንጉሥ ምኒልክ ጋር በራስ ዳርጌ አማካይነት በሚጻጻፉበት ወቅት ነበር ማለት ነው ። ለዋናው የሱዳን መሪና ለእኩያቸው ለከሊፋ አብዱላሂ አል ታሺ ኢብን መሐመድ በመጻፍ ፈንታ ራሳቸውን



ዝቅ አድርገው ፥ ለሱዳን ምሥራቃዊ ክፍል (ገዳሪፍ) አስተዳዳሪ መጻፋቸው በትክክል አይገባንም ።

ዐፄ ዮሐንስ ፥ በስሐጢ የጦር ግንባር ከኢጣልያኖች ጋር በውጊያ በተሰላለፉበት ወቅት የጣልያኖች ምሽግ የማይደፈር መሆኑን ከተገነዘቡና ሰዋቸውም ኢጣልያኖች ወደ ሰማይ እየወረወሩ በሚያውለበልቡት የኤሌክትሪክ ኳስ ከተደናገጠ ወዲህ ፥ “እኛና እናንተ በክርስቲያንነት የተሳሰርን ወንድማማች ነንና እርስ በርሳችን ከምንዋጋ አንድነት ሆነን የቱርክ ፥ የግብጽና የሱዳን እስላሞችን እንውጋ” የሚል አሳብ አቅርበውለት ሳይሳካላቸው መቅረቱን እናስታውሳለን ። ዳሩ ግን ፥ የኢጣልያ መንግሥት መሠረታዊ አሳብ ክርስቲያኖችን ከእስላሞች እንደዚሁም ክርስቲያኑን ከክርስቲያን ጋር አዋግቶ በነዚህ መዳከም የአገር ወረራውን ዓላማ ከፍጻሜ ለማድረስ ስለሆነ ፥ ለሃይማኖቱና ላፄ ዮሐንስ አባባል ምንም ዋጋ ሳይሰጥ ሊቀበሉት የማይችሉትን ውለታ እንደ ጠየቃቸውና የዕርቁ ጉዳይ እንደሳተ ባለፈው አንብበናል ።

አሁንም ፥ ሐምዳን አቡ አንጋ የማዕረግ ስሙ አሚር አል ቱማር (ዋነኛው አሚር) ባለፈው ጊዜ የሁሉ የበላይ አለቃና መሪ የነበረው ሙሐመድ አህመድ ኢብን ሰይድ አብደላ (ማህዲ) በሱዳን የእስልምናን ሃይማኖት ባዲስ ኃይል ቀስቅሶና አዲስ የአስተዳደር ሥርዓት መሥርቶ በተነሣበት ጊዜ በሱዳን ላይ ተመሥርተው በገዥነት ተቀምጠው የነበሩትን ግብጾችንና ቱርኮችን አባሮ ፈረንጆቹን ሳይቀር አንቀጥቅጦ ፥ በእንግሊዝ መንግሥት ፈቃድ ከግብጹ መሪ ከተውፈቅ ፓሻ ለሱዳን ጠቅላይ ገዥነት ተሾሞ የመጣውን ጐርዶን ፓሻን (ጄኔራል ቻርልስ ጆርጅ ጐርዶንን) አሸንፎ ጭንቅላቱን እስከ መቁረጥ በደረሰበት ሰዓት አሁን አንጋ ከዋናዎቹ መሪዎች (አሚሮች) እንደ አንዱ ሆኖ በሁሉም የጦር ግንባር ተካፍሏል ። ደግሞ በቅርቡ በደምቢያ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ማሸነፉ በልቡ ትዕቢት አሳድሮበታል ። ያለፈውን የነጐርዶን ፓሻን አሟሟት በመገምገም ፥ አሁንም የማህዲን ትምህርት ተከታዩን የከሊፋ አብዱላሂን አመራርና ዓላማ ሁሉ የሚቃወም እንደሚጠፋና ቢዋጋም እንደሚሸነፍ ከልቡ ያመነ ይመስላል ።

ስለዚህ ያሁኑ ያፄ ዮሐንስ ፥ “የሱዳንና የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘሩ አንድ ነውና እኛ ተስማምተንና ተፋቅረን ፈረንጆቹን እንቃወም” ብለው ያቀረቡለትን የዝምድና አሳብ ከፍርሃት የመነጨ አድርጎ ቆጥሮታል ። በዚህም ላይ በደብዳቤያቸው አናት ላይና በማኅተማቸው ዙሪያ “ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ዘኢትዮጵያ” በሚለው ፋን በግዕዝና በዐረብኛ ቋንቋ “መስቀል ሞዓ ነገደ እስማኤል”

ይኸውም ማለት "ክርስትና እስልምናን አሸነፈው" የሚለው ዐረፍተ ነገር እንደ አቡ አንጋ ለመሰለ ሃይማኖቱን አጥባቂ የሚያንገፈግፈው ቃል እንጂ ወደ ሰላም አይጋብዘውም ። ደግሞም ከኢትዮጵያ በተለይ ከወሎና ከዋጅራት የተሰደዱት እነ ሸከ ጦልሃ ቤን ጃፋር በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል በነበረው የጦርነት እሳት ላይ ዘይት ከመጨመርና ከማባባስ በቀር ፣ ሁለቱ ወገኖች የሚስማሙበትን መንገድ አይፈልጉትም። እነሱ የሚጠብቁት በ1870—75 ዓ. ም. ክርስቲያን ሁኑ ተብለው የደረሰባቸውን ያለፈውን ጥቃታቸውን በመመለስ ደርቡሾቹ ከዐፄ ዮሐንስ ተዋግተው እንዲበቀሉላቸው ብቻ ነበር ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስ ለጻፉለት የዕርቅና የሰላም ደብዳቤ ፣ አቡ አንጋ ከአለቃው ከአሚር አብዱላሂ ጋር ተመካክሮ የመለሰላቸው ቀጥሎ የምንመለከተው ደብዳቤ ኩራት የተመላበት የትዕቢትና የዕብሪት መልስ ነው ።

"ከእግዚአብሔር ባሪያ የማያምኑትን ለማጥፋት ከተመደበው ከእስላም ጦር መሪ ከሀምዳን አቡ አንጋ ለሐበሻው ዮሐንስ" ብሎ ይዠምርና ባረብኛና በውጭ አገር ቋንቋ * የተጻፈው ደብዳቤ እንደ ደረሰውና እሳቸው በደብዳቤያቸው መዠመሪያ ላይ ያሉትን ከጠቃቀሰ በኋላ ፣ ማህዲ እስላም እንዲሆኑ ጽፎላቸው ለነበረው መቆጣታቸው ያላግባብ መሆኑን ፣ በዚህም ምክንያት ወደ መተማ የዘመቱት (ሐበሾች) መከራ እንደ ደረሰባቸውና ያም ለሳቸው ትምህርት ሊሆን እንደሚገባ ካመለከተ በኋላ እንደዚህ ሲል ይደመድማል ።

> "ተዋጊዎቹ አንበሶች (ደርቡሾች) የእስልምናን ሃይማኖት የሚቃወመውን ሁሉ በመቃወም ፣ ለመሞት በእግዚአብሔርና በነቢዩ (መሐመድ) በማህዲውና በከሊፋው ስም ምለዋል ። እነኝህንም ባለፈው አላወቅሃቸው እንደሆነ ነገ ታውቃቸዋለህ ። እነሱም የሚመጡት አንተንና ኢአማኒዎቹን (ክርስቲያኖች) ለማጥፋት እንጂ ክብርና ገንዘብ ለመፈለግ አይደለም ። ስለዚህ ንቃ ከእግዚአብሔር ቁጣ የማያድንህ ሰይጣን እያሳሰትህ ። ለመማር ለሚፈልጉ ሁሉ ያለፈው ትምህርት ነው ። በደብዳቤ ላይ ደጃች አቡ አንጋ ብለኸኛል ደጃዝማች አለመሆኔን ልታውቅ ይገባሃል ። ደጃዝማች እንደ አንተ በእግዚአብሔር የማያምኑ ስያሜ ነው ። በከሃዲነትህ እያለህ ሰላም እናድርግ ያልከው ሁለት የማይጣጣም ነገር እንዴት ይገናኛል ብለህ ታስባለህ? ይህም የአእምሮህን ዝቅተኛነት ያሳያል ። . . . በእርግጥ ሰላም ትፈልግ እንደሆነ ከልብህ ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም መሐመድም ነቢዩ ነው ብለህ ማመን አለብህ ። ያለዚያ አምላክ በመጽሐፉ እንደ ሰጠው ተስፋ አንተንም እንወጋሃለን ፤ አገርህንም እናጠፋለን ፤ ሕዝብህንም እንገላለን ፤ ሀብትህንም እንወስዳለን . . . በአላህ ካላመንክ እኛ የምንለውን ካልተከተልህ በቀር አንተንና እኛን ፣ የሚደግፉህንም ጣልያኖችንና አውሮፓውያንን የሚለየን ሰይፍ ብቻ ነው ። . . . እኛን ለመውጋት ኃይልና ድፍረት ካገኘህ ግጠመን እስከ አሁንም ያቆየህ ፍርሐትህ ነው እንጂ ቢቻልህ እኛን ለመውጋት አታመነታም ነበር ። ነገር ግን አንተ ባትወጋንም እዚያው እርጋ እኛ አለህበት ድረስ መጥተን በማይሸነፈው ጦር ሠራዊታችን እናጠፋሃለን ። ስለዚህ ጊዜው ሳያመልጥህ ወደ አምላክ ተመለስና (ስለምና)፤ሕይወትህን አድንደህንነትህም እስላም በመሆን ጥፋትህም ባለመሆን ነው . . . የምሰጥህ ምክር ይኸው ነው . . . "[1]

አቡ አንጋ ከንቀቱ የተነሣ ሲጽፍላቸው ለመሊክ (ለንጉሥ) ዮሐንስ ለማለት እንኳን ሳይፈልግ ንጉሠ ነገሥቱን እንደ ተራ ሰው "ለሐበሻው ለዮሐንስ" ነው ያላቸው ። በሌላውም እነጋገሩ ጽሑፉ ራሱ እንደሚያመለክተው ፣ "በየወሰናችን ረግተን በመዛመድ ፈረንጆችን እንቃወም" በማለት የዘረጉለትን የሰላም እጅ ሊጨብጥ አልፈለገም ። ምናልባት ይኸን ዐይነቱን አባባል ላለመቀበል ያስገደደው ንጉሠ ነገሥቱ ከአምስት ዓመት በፊት በእንግሊዝ አዋዋይነት መሠረት የገዛ ጦራቸውን ልከው በከሰላ ከደርቡሾቹ ጋር በማዋጋት የተከበቡትን ቱርኮችና ግብጾች አድነው ባገራቸው አስተናግደው ማሳለፋቸውን ቂሙ አልተዘነጋም ይሆናል ። ምናልባትም ከሰሐጢ የጦር ግንባር የተመለሱት ፣ "ከኢጣሊያኖች ጋር እስላሞችን አንድ ሆነን እናጥቃ ተባብለው ተስማምተው ዕርቅ አድርገው ነው" ተብሎ የተወራውን አምኖ ይሆናል ። በዚህ ዐይነት ለንጉሠ ነገሥቱ ከእንግዲህ ወዲያ የቀራቸው መዋጋት ብቻ ነው እንጂ ፥ እንደ በሐጢው ግንባር ጠልጠል ያለ ሰነፍ ዕርቅ እንኳን ለማድረግ አልቻሉም ማለት ነው ።

ሐምዳን አቡ አንጋ ይኸን የፉከራ ፣ የትንቢትና የትዕቢት ደብዳቤ ጥር 3 ቀን እንደ ጻፈላቸው ፣ ምንም ያህል ጊዜ ሳይቆይ በጻፈበት

---

* የውጭ አገር ቋንቋ የሚለው ያማርኛውን መሆኑን ቀደም አድርገው ደጃች ዘውዴ ገ/ሥ አስገንዝበዋል ።

1 Zewde G.S.,) The Process of Re-Unification of the Ethiopian Empire (1868-1889), Vol. II,PP.645-651.

ወር በጥር 29 ቀን 1881 ዓ. ም. ሞተ ። [1] ነገር ግን በትንቢት ይሁን በጥንቆላ ፥ በግምት ይሁን በመላ በደብዳቤው ላይ የተመኘው ያ፪ ዮሐንስ ውድቀት እርሱ ከሞተ በኋላ ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መተማ ላይ ተፈጸመ ። እርሱም ሲሞት በእርሱ እግር በከሊፋ አብዱላሂ ፈቃድ ዛኪ ቱማል (ታማል) ተሾመ ። ይህ አዲሱ ሹም ወደፊት በመጋቢት 1 ቀን 1881 ዓ.ም. በመተማ ከዐ፪ ዮሐንስ ጋር ተዋግቶ ሲያሸንፋቸውና እርሳቸውም ከደርቡሾቹ በተተኮሰች ጥይት ሲሞቱ ዝርዝሩን ወደፊት እናነባለን ። የአቡ አንጋ የደብዳቤው አባባልም ይነስ ይብዛ ተፈጸመ ማለት ነው ።

1 A.B Theeobald, The Mahidya, PP.154-155.



# ምዕራፍ ሃምሳ

## ያ፪ ዮሐንስ ጉዞ ወደ መተማ — የጦር ድርጅታቸው

ዐ፪ ዮሐንስ ፥ ሸዋን ሳይወጉና ምኒልክን ሳያሳምኑ ጉዞአቸውን ወደ መተማ ያዞሩበት ምክንያት ፥ ሰበቡ አንድ ሆኖ ሳለ ጸሐፊ ዎቅጅራ፡- ሁሉ እንደ መሰሰው ልዩ ልዩ ትርጉም ሰጥቶታል። አለቃ ተክለ ሥላሴ

"ዐ፪ ዮሐንስ ንጉሥ ምኒልክን ሊወጋ ሸቀ ሊሔድ ተነሣ ። የዚህን ጊዜ ንጉሥ ምኒልክ በሰላሌ ራስ ዳርጌን ፥ በግንደ በረት ደጃች መኰንንን ፥ በወሎ ደጃች ወሌን ጠባቂ አኑሮ ነበረ። ያንጊዜ ዐ፪ ዮሐንስ አስቀድሞ ግጥም ላከ (እንዲህ ሲል)

"እርሳሱ ብዙ የሐምሌ ቴግብ (ተግብ)
ደንጊያ መንከስ ነው ካሴን ማሰብ" *

"ይኸን ግጥም ንጉሥ ምኒልክ በሰማ ጊዜ ደነገጠ ። 'አገሬን አላዘርፍም' ሲል ከደብረ ሊባኖስና ከዝቋላ ደረቋ ላይ አማላጅ መነኮሳት ላከ ግብሩን [1] ሰጥቶ ታረቀ ። ከዚህ በኋላ ዐ፪ ዮሐንስ ወደ መተማ ተመለሰ. . ." ብሰዋል ።

ከአቡነ ማቴዎስ ጋር መነኮሳት ሁለቱን ሊገላግሉ ሊማልዱ መሔዳቸው እርግጥ ነው ። ደንበኛ እርቅ ግን ፥ ለመደረጉ ምንም የማስረጃ ምልክት የለም ። ግጥሙንም አንድ በንጉሠ ነገሥቱ ሠራዊት ውስጥ ያለ ወታደር ወይም መኰንን በቀረርቱ ጊዜ ገጥሞት ይሆናል እንጂ በዚህ ጊዜ ይኸን የመሰለ ተራ የድንፋታ ግጥም ንጉሠ ነገሥቱ ገጥመው የሚልኩ አይመስልም ።

በበኩላቸው ነጋድራስ አፈ ወርቅ፡-

"... በዚያ በኩል (በዐባይ ዳር) መሄዳቸው ጥንቱንም ለማንገራገር ነበር እንጂ ዐባይን መሻገር ሆኖላቸው ቢሆን እውነት

* ዐ፪ ዮሐንስን ልውጋ ብሎ መከጀል ከንቱ ነው ፥ ካሴ የካሳ (የቀድሞ ስማቸው) ቁልምጫ ነው ።

1 ያለቃ ተክለ ሥላሴ የእጅ ጽሑፍ ገጽ 135 ።

የዚያን ጊዜ ጉሮሮ የሚውጠውን እጅ ይመጥነዋል * ነውና ካባ
ዳኛው (ከምኒልክ) ጋራ ተዋግተው እንዳይወጡት ያቁው
ነበረ... ወግድ ምኒልክስ መቸም እምልጠ አያመልጠንምና
አሁንስ ቤተ ክርስቲያናችንን ያቃጠለውን ታቦታችንን ያረከስ
ውን ደርቡሽን እንውጋ ደማችንን እንመልስ ብለው ወደ መተማ
ወረዱ..." ሲሉ አመልክተዋል ።[1]

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ደግሞ ፥

"...ዐፄ ዮሐንስ ፊታቸውን ወደ መተማ ስለ ማዞራቸው
አንዳንድ ሰዎች ፥ "ዐፄ ዮሐንስ ወደ ሸዋ መጥተው ከንጉሥ
ምኒልክ ጋራ ለመዋጋት ሸዋንም እንደ ጐጃም ለማጥፋት ካሰቡ
በኋላ ፥ የንጉሥ ምኒልክን ሠራዊት ብዛት ቢሰሙ ፈርተው ተመ
ለሱ" እያሉ ይናገራሉ ። አንዳንዱ ደግሞ ፥ ዐፄ ዮሐንስ ወደ ሸዋ
ለመምጣት ሲነሡ በምስጢር ከንጉሥ ምኒልክ የተላኩ መነኮሳት
መጥተው (ሂደው?) "ወደ ሸዋ የሄድህ እንደሆነ ንጉሥ ምኒልክን
ድል ታደርጋለህ በነፍስህ ግን ትጎዳለህ ። ወደ መተማ የሄድህ
እንደሆነ ግን በሰማዕትነት ትሞታለህ ፥ በነፍስህ ትጠቀማለህ
ቢኋቸው በሥጋዬ ተጠቅሜ በነፍሴ ከምጎዳ ሞት ይሻለኛል ብለው
ወደ መተማ ሄዱ" እያሉ ይናገራሉ ። ሌሎች ደግሞ "ደርቡሽ
ለጦርነት መሰናዳቱን ሰምተው ነበርና ወደ ሸዋ የሄድሁ እን
ደሆነ የቤጌምድርን አገር ያጠፉዋል ፥ ሕዝበ ክርስቲያኑን ያርደ
ዋል... እግዚአብሔር ቢረዳኝ በፊት ደርቡሽን ወግቸ ድል ካደረ
ግሁ በኋላ ወደ ሸዋ እዘምታለሁ ብለው ወደ መተማ ተጓዙ
ብለው ይናገራሉ... በእውነተኛ ልብ ስንመረምረው ይህ በሦ
ስተኛው የተነገረው ቃል እውነት ይመስላል..." ብለዋል ።[2]

እውነትም በዚህ ጉዳይ ብላቴን ጌታ የሰጡት ግምት ትክክል
ይመስላል ።

የሆነ ሆኖ ፥ የሁሉም አባባል መላም እውነትም የተደበላለቀበት
መሠረት ያለው አባባል ነው ። የሁሉም አባባል ይኸውም ማለት

---

* ጉሮሮ የሚውጠውን የመብል ጉርሻ ፥ መጠኑ በእጅ ይለካል ለማለት ነው ። ትርጉ
ሙም በዚህ ላይ ዮሐንስ ጦራቸው የምኒልክን ጦር እንደማያሸንፍ ራሳቸው ይገ
ምቱታል ለማለት ነው ።

1 አፈወርቅ ገ/የሱስ ፥ ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ ፥ ገጽ 53—54

2 ብ.ጌ.ኅሩይ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐድዋ ጦርነት ፥ የእጅ ጽሑፍ ፥ ገጽ 152 ።



ፍርሃቱም ፥ ሥጋቱም ፥ ጥንቃቄውም ባፄ ዮሐንስና በንጉሥ ምኒልክ
አእምሮ ውስጥ የሚመላለስ ነው ። ቢሆንም ሁለቱም በደላቸውን በራስ
ዳርጌ አማካይነት የተገላለጹት በታሪካዊ ጽሑፍ ላይ የሠፈረ ደንበኛ
ሰነድ ስለሆነ ፥ የደብዳቤዎች ልውውጥ ለአእምሮአችን እውነተኛ
ውን መንገድ ለማስጨበጥ የሚረዳ ይመስለኛል ። በእርግጥ በምኒልክ
በኩል ባንድ ወገን ፥ "ላፄ ዮሐንስ እንደዚህ ቀደሙ ገብሬ ከም
ዋረድ መዋጋቱ ይሻለኛል" ሲሉ ፥ በሌላ ወገን ፥ "በኔ እምቢታ ምክ
ንያት አገሬ እንደ ጐጃም ከሚዘረፍ ሕዝቤ ከሚበዘበዝ እኔን ግባ እጅ
ንሣ አይበሉኝ እንጂ ፥ ያመት ግብሬን እገብራለሁ የቀረው እንደ
ሁኔታው እየታየ ወደፊት ይፈጸማል" ብለው ሲወስኑ ፥ ባፄ ዮሐንስ
በኩል ደግሞ "ጐጃምን ያጠቃሁት አንሶ አሁንም በምኒልክ እምቢታ
ሸዋን አላጠቃም ፥ ምናልባትም አጠቃለሁ ስል ተሸንፌ በገዛሁትና
በአስገበርሁት በምኒልክ እጅ ወድቄ ከምዋረድ አንደኛውን ወዳገሬ
ወደ ሕዝቤና ወደ ሃይማኖቴ ጠላት ብዘምት ይሻላል ። በዚያም የጦር
ግንባር ከቀናኝ ምኒልክ ዐውቆ ይገባል ፥ እምቢ ቢልም በደርቡሽ
ድል ሞራሉ ከፍ ባለው ሠራዊቴ መትቼ አስገብረዋለሁ" ብለው
ይሆናል ።

ስለዚህ አስተዋዩ ንጉሠ ነገሥት ፥ ይኸንን ሁሉ በልቦናቸው ካመ
ዛዘኑ በኋላ ከነበሩበት ከዳሞት በየካቲት ወር ተነሥተው በአገው
ምድር አልፈው ወደ መተማ ጉዞ ዠመሩ ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት
ግን ባለፈው የሣር ውሃ ጦርነት ሠራዊታቸው ስለ ተጎዳ፥ በንጉሠ ነገሥቱ
ፈቃድ አንጅባራ ላይ ተሰናብተው ቀሩ ። የጐጃሙ ጳጳስ አቡነ ሉቃስ
ብቻ 'ከንጉሠ ነገሥቱ አልለይም' ብለው አብረው ተጓዙ ። አብሮ
የዘመተውን የጦር ሠራዊት ቁጥር ብላቴን ጌታ ኅሩይ 150,000 ከዚ
ሁም 20,000 ፈረሰኛ ሲያደርጉት ፤ አለቃ ተክሌ 100,000 እግረ
ኛና 20,000 ፈረሰኛ ላይ መድበውታል ። የኢጣሊያኖቹ ሰነድ በዚሁ
አካባቢ ያደርግና አንዳንዱ እስከ 80,000 ያወርደዋል ። የተከተሉዋቸው
ዋና ዋና የጦርና ያስተዳደር መኳንንት ዕድሜያቸው ወደ ሰማንያ
ዓመት የተጠጋው አጐታቸው ትልቁ ራስ አርአያ ድምፁ ፥ የጦር ጠቅ
ላይ አዛዥነቱን ከራስ አሉላ የተረከቡት የታላቅ ወንድማቸው የደጃች
ጉግሣ ልጅ ራስ ቢትወደድ ኃይለ ማርያም ጉግሣ ፥ ራስ አሉላ እንግዳ
(ቁቢ) ፥ የወሎው ባላባትና የክርስትና ልጃቸው ራስ ሚካኤል አሊ ፥
ራስ መንገሻ ጉግሣ የራስ ኃይለ ማርያም ታናሽ ወንድም ፥ ራስ
ሐጐስ... የሺሬና የጸለምት ገዥ ፥ ዋግ ሹም ገብሩ ፥ ቤትወደድ ገብረ
መስቀል ገብረ ጻድቅ ፥ ደጃች ቦጋለ አርአያ (የራስ አርአያ ልጅ)
ደጃች መሸሻ የወንድማቸው የደጃች ማሩ ልጅ የቀረውም ደጃዝማ
ቹና ፊታውራሪው ፥ ቀኛዝማቹና ግራዝማቹ ብዙ መሆኑ አይጠረጠ
ርም ። ከቤተ ክህነትም ወገን ከአቡነ ሉቃስ በቀር ጳጳሳቱ እነአቡነ

ጴዋሮስ ፣ እጨጌው አባ ቴዎፍሎስ ፣ ታቦት አጅበው የሔዱ ብዙ ካህና
ትና ቀሳውስት ይገኛሉ ። አገው ምድርን አልፈው ደምቢያ ገብተው
በግር ውሃ ሲያልፉ ባለፈው ዓመት ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና ሐም
ዳን አቡ አንጋ ከተዋጉበት ቦታ ደርሰው የሞቱትን ሰዎች ዐፅም አይ
ተው በጣም አዘኑ ይባላል ። "የጐጃም ጦር ሳይዋጋ ሸሸ ብላችሁ
በከንቱ ያሳማችሁኝ" ብለው ራስ አሉላን ተቆጡ ሲሉ ተክለ ሥላሴ
አመልክተዋል ።[1]

በደርቡሾቹ በኩል ባለፈው እንዳልነው ፣ ዋናው የደርቡሾቹ
መሪ ከሊፋ አብዱላሂ በዋናው ከተማ በኡምዱርማን እንደ ተቀመጠ
አገሪቱንም ጦሩንም በትእዛዝ ይመራል ። ከኩራቱም የተነሣ የንጉሡ
ንጉሥቱን መዝመት እያወቀ ራሱ መሪ ሆኖ ለመመከት ወደ መተማ
አልመጣም ። ነገር ግን ፣ ለምሥራቅ ሱዳን ገዥ ለአቡ አንጋ ተከታይ
ለዘኪ ቱማል ማናቸውንም ወታደርና የጦር መሣሪያ ሰጥቶ መሪ ትእ
ዛዝ ብቻ እየላከ እርሱ በከተማው ተቀምጦ ወሬውን ይከታተል
ነበር ። በመተማ በዘኪ ቱማል ሥር የዘመተው የወታደር ቁጥር ከ70—
80 ሺ መካከል እንደሆነ ተገምቷል ። ከደርቡሽ ጦር በቀር ከወሎና
ከወሎ አካባቢ ፣ ከዋጅራት ፣ ከራያና አዘቦ እየሸሸ የሔደው በሼክ
ጦልሃ ቤን ጃፋር መሪነት የቀረውም ከወዲህ ከኢትዮጵያ ሰሜንና
ሰሜን ምዕራብ ከቦጎስና ከቤኒ አሚር በነአህመድኤል ጅር ፣ በነዲግላል
መሐመድ እየተመራ ግማሹ ወደ ኢጣልያ ሲጠጋ የቀረው ወደ
ደርቡሾቹ ተደባልቆ ኃይላቸውን አጠንክሮላቸዋል ።[2]

ከማህዲ እነሣሥ ወዲህ ደርቡሾች የእስልምናን ሃይማኖት ለማስ
ፋፋት ፣ የቱርክንና የግብጽን ግዛት ፣ የፈረንጆችን በተለይ የእንግሊ
ዞችን የበላይ ተቆጣጣሪነት ደምስሰው እስልምናን በያለበት ለማስ
ፋፋት የተነሡበት ፣ እንደ ነቢዩ መሐመድ ተከታይ የቆጠሩት ማህዲ
አህመድ የተናገረው ሁሉ የሚፈጸም ፣ የርሱንም እምነት ተከትሎ
በተነሣው ተዋጊ ጦር ላይ የማንም ኃይል ተነሥቶ እንደማይመልሰው
መረዳታቸውን አቡ አንጋ ላዔ ዮሐንስ በጻፈው ደብዳቤ ላይ ተረድ
ተነዋል ። ይህ እምነት አንድነታቸውን አጠንክሮ ለሞራላቸውም ከፍ
ያለ ድጋፍ ሆኗል ።

በዚያ አንጻር ላዔ ዮሐንስ ስለ ክርስትና ሃይማኖት ፣ ከዚያውም
በተለይ ስለ ኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መቋቋምና መስፋፋት
ያላቸው ምኞት ከፍ ያለ ስለነበረ ፣ ምኒልክን በ1870 ዓ.ም. ከስገበሩበት

1 የአለቃ ተክለ ሥላሴ የእጅ ጽሑፍ ገጽ 135 ።
2 L'Italia in Africa . . . . PP.239-240



ጊዜ ዠምሮ ፣ "የእስልምና ሃይማኖት የያዘ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ክርስትና
እንዲነሣ ብለው ባወጁት መሠረት ፣ እስላሙ ሁሉ በክርስቲያን ሹማም
ንትና መኳንንት እየተነዳ ወደየቤተ ክርስቲያን በመሔድ እንዲጠመቅና
እንዲቆርብ የተደረገበት ዋናው ንጉሠ ነገሥታዊ ዓላማቸው ኢትዮጵያዊ
ሁሉ ባንድ ሃይማኖት ላንድ ዓላማ እንዲቆም ነበር። በዚያን ጊዜ ኢትዮጵ
ያውያንና ሱዳኖች ያደረጉት ጦርነት ፣ ከፖለቲካና ከመሬት ፍሊጋው
የበለጠ በሃይማኖት ሽፋን የተደረገ ጦርነት መሆኑ ይታወቃል ።

በዚህ መካከል የሚያሳዝነው ፣ እንግሊዞች ወደ መቅደላ ዐፄ
ቴዎድሮስን ለመውጋት የመጡ ጊዜ ካዔ ዮሐንስ (ያን ጊዜ ደጃች
ካሳ) የተደረገላቸውን አቀባበልና መስተንግዶ ንጉሠ ነገሥቱም ከል
ባቸው ንግሥት ቪክቶርያን እንደ እናት ፣ ጄኔራል ናፒየርን እንደ
አባት ቆጥረው ሲመኩባቸው የነበረው ሁሉ ቀርቶ ፣ ያሁኑም ያዔ
ዮሐንስና የደርቡሾች ጦርነት ዋና ሰበቡ የእንግሊዝ መንግሥት በአ
ድሚራል ሔዊት አማካይነት ግብጽንና ኢትዮጵያን አዋውሎ ውሉን
ለማክበር ሲሉ ንጉሠ ነገሥቱ ለግብጾቹ ረድተው ከሱዳኖቹ ጋር በተ
ዋጉበት ምክንያት መሆኑን እያወቀው ፣ ባሁኑ ጊዜ በሰሜን ምሥ
ራቅ በኩል ጣልያንን ጋብዞ ማስጠቃቱ ሳያንሰው በርሱ ሰበብ በተ
ነሣው የደርቡሾች ጦርነትና የርሱንም ጄኔራሎች እነጐርዶን ከፈጅዋ
ቸው ደርቡሾች ጋር ለመዋጋት ወደ መተማ ሲጓዙ አንዳች እርዳታ
ሊያደርግላቸው አልፈለገም ። ወታደርና የጦር መሣሪያ ባያቀብል እን
ኳን ፣ "በዚህ ዐይነት መከቱ ፣ እንደዚህ አድርጋችሁ ብታጠቁ ታሸን
ፋላችሁ" ብሎ የሚመክር አንድ የጦርነት ልማድ ያለው እንደ ማር
ከሃም ያለ እንግሊዛዊ መኰንን ሊለግሣቸው አልቻለም ። ካፒቴን
ሐሪሰንና ምስተር ጄራልድ ፖርታልን ልኮ ፣ "ለኢጣልያ መሬት ቆር
ጠው ይስጡ" የተባለውን አባባል ንጉሠ ነገሥቱ ሳይቀበሉ ከቀሩ
ወዲህ ፣ ይኸው የእንግሊዝ መንግሥት አንድነቱንና ዝምድናውን ከኢ
ጣልያ ጋር አጥብቆ እርሳቸውን ገሸሽ አድርጎ ትቷቸዋል ።

በመንግሥታት መካከል ጥቅምን መከተል እንጂ ፣ የሞራል ግዴታ
ቢምንም ዐይነት ስለሌለ ሁኔታው ያሳዝናል እንጂ አያስገርምም ።
ስለዚህ የመንግሥት መሪ ሁሉ በሌላው መሪ መታመንን ትቶ ራሱ
በራሱ ለራሱ የሚወጣበትን መንገድ ጠንክሮ ከማበጀት በቀር ሌላ
መድኅን እንደሌለ ይህ ያሁኑ የእንግሊዞች አቅዋም ደህና መማሪያ
የሆነ የፊደል ሰሌዳ ነው ። ማናቸውም ውል ወይም የቃል ኪዳን
ወዳጅነት ቢደረግም ፣ ውሉ የሚሠምረው በመዠመሪያ ራስን አደር
ጅቶ መሆን እለበት ። ያለዚያ ውሉ የጌታና ያገልጋይ መልክ ፈጥሮ
ጸጸት ሊያስከትል ይችላል ። ያዔ ዮሐንስና የእንግሊዞች ውል ከዚህ
ሁኔታ ላይ እንደ ወደቀ ይታያል ።

# ምዕራፍ ሃምሳ አንድ

## የመተማ ጦርነት — ያፄ ዮሐንስ አሳዛኝ ሞት

ዐፄ ዮሐንስ ሠራዊታቸውን እንዳስከተሉ በመኳንንቶቻቸው ታጅበው ሲሔዱ፣ ከጦሩ ብዛት የተነሣ የምድሩ ትቢያ እንደ ደመና ሆኖ ፀሐይን እንደ ከለላት፣ ንጉሠ ነገሥቱም የየካቲቱ ወር ሲያልቅ ወደ መተማ አካባቢ በደረሱ ጊዜ፣

"መጣሁ ታጠቅ እንደ ሌባ በድንገቴ መጣብኝ እንዳትለኝ መምጣቴም የክርስቲያንን ደም ለመበቀል ነው" ብለው

ለዘኪ መላካቸውን፣ ብዙ ጊዜ ስማቸውን የጠቀስናቸው ያገራችን ደራሲዎች አመልክተዋል ።

ከዚሁ አያይዘው ይህ መልእክት ለዘኪ ቱማል ሲደርሰው፣በርግጥም ያፄ ዮሐንስ ከነጦራቸው መምጣት በመተማና በአምዱርማን በተሰማ ጊዜ በደርቡሾች ዘንድ ሽብርና ድብልቅልቅ መፈጠሩን፣ አዝማቹ ዘኪ ቱማልም የወታደር አለቆቹን ሰብስቦ፣ "ጠላቶቻችንን እንዴት ሆነን እንቋቋማቸው? በውጭ ወይስ በቅጥር ውስጥ?" ብሎ ምክር ቢጠይቅ አህመድ አሊ የሚባለው የእስላሞች ቃዲ "በሜዳ ተሰልፈን የቆየናቸው እንደሆነ አበሾች ፈረሰኞች ናቸውና በፈረስ አጐዳ ይጥሉናል ። ስለዚህ እዚሁ አጥራችን (ከግምብ ምሽጋችን) ውስጥ ተሰልፈን ብንቆያቸው ይሻለናል" ብሎ እንደ መከረ፣ ዘኪም ሠራዊቱን ቢያስቆጥረው 85ሺ መድረሱን፣ ይህን ጦር ባጥር (በምሽግ) ውስጥ አሰልፎ በተረፈ (በተጨማሪ) በየገበያውና በየመንደሩ ዐዋጅ ነጋሪ እየሰደደ ነጋዴውን ከንግዱ ላይ፣ ገበሬውን ከእርሻው ላይ እያስነሣና የጦር መሣሪያ እያስያዘ ማስለፉን፣ ወደ አምዱርማን ለከሊፋ አብዱላሂ መልእክት ልኮ "ወዳጃ * አስይዘህ ጸልይልኝ ። ረዳትም ላክልኝ ወደ ሐበሾች ሰላይ ልኬ ነበርና ብዛታቸው እንደ

---

* ወዳጃ ማለት አንድ ክፉ ነገር እንዳይደርስ ወይም ምኞት እንዲፈጸም ቃዲዎች ሸኮች ባሉበት ዕጣን እየተጨሰ፣ ቡና እየተጠጣ፣ ቁራን እየተጠቀሰ በዜማ በዝማሬ አምላክ የሚለመንበት ልዩ የጸሎት ወቅት ነው ።

ሰማይ ኮከብ ፡ እንደ ባሕር አሸዋ ነው” ብሎ መላኩን ጽፈዋል።[1] በኢትዮጵያውያን በኩል የጦር አሰላለፍ ከሦስት ላይ ተከፍሎ ራስ መንገሻ በቀኝ ፡ ራስ ኃይለ ማርያም ጉግሣ በግራ ሆነው በመካከል ራሳቸው ንጉሠ ነገሥቱ ነበሩ ይባላል ። በዚህ አኳኋን በመጋቢት 1 ቀን 1881 ዓ.ም. ቅዳሜ ለት ጧት በሦስት ሰዓት ላይ ጦርነቱ ተጀመረ ። ካገራችን ጸሐፊዎች ውስጥ በመጠኑ ዘርዘር አድርገው የታሪክ ማስታወሻ የተዉልን ብላቴን ጌታ ኅሩይ የመተማውን የጦርነት አጀማመሩንና ፍጻሜውን እንደዚህ ሲሉ አስፍረውታል ።

“በመጋቢት 1 ቀን ቅዳሚት ጦርነት ተጋጠሙ ከሠራዊቱም ብዛት የተነሣ ትቢያው እንደ ደመና እየሆነ ሰውና ሰው በጣም አይተያይም ነበር ። በአንድ አፍታ የከተማውን ቅጥር (ግንብ) ጥሰውት ገቡ (ኢትዮጵያውያኑ) በዚያን ጊዜ በከተማው ውስጥ ያሉት የሴቶች ፡ የሕፃናቱ ፡ የሽማግሌው ፡ የባልቴቱ ጩኸትና ለቅሶ ዠግናው ሲፎክርና ሲያቅራራ ድምጡ እየተደበላለቀ የክረምት ነጐድጓድ ይመስል ነበር ይባላል ። በብርቱ ጦርነት ከተዋጉ በኋላ ግን የከተማውን ቅጥር ባንድ ወገን ጥሰውት ገቡ ። በከተማው ውስጥ ያለ ሰው ሁሉ እየወጣ እንዲሸሽ ቤቱንና ቅጥሩን አቃጠሉት ። ባንድ ወገንም ዘልቀው ግምጃ ቤቱን ያዙት ያቡ አንጋንም አጽም ለማቃጠል ቤቱን ሁሉ ይቀሰቅሱ ነበር ። ይኸንንም ያሰቡበት ምክንያት አቡ አንጋ ጐንደርን አጥፍቶ ሊቃውንቱን ሁሉ በእሳት አቃጥሏቸው ነበርና የዚያን ብድር ለመመለስ ነበር ። ነገር ግን ዐፄ ዮሐንስ ምንም ጠንክረው ቢዋጉ ድል ማድረግ ያለ እግዚአብሔር ፍቃድ አይሆንምና ድል ለማድረግ ጥቂት ሲቀራቸው በጠመንጃ ቆሰሉና ወሬው ያንጊዜውኑ በየሰልፉ ውስጥ ተሰማ ።መኳንንቱም ወታደሩም ከቅጥሩ ውስጥ እየወጡ መሸሽ ዠመሩ ።”

ከ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ሆነን ስንመለከተው ፡ ምንም እንኳን በሠለጠኑት አገሮች ጦርነት ሲደረግ አስቀድሞ ለጠላት ማስታወቅ ፡ “ኡልቲማቱም” የተለመደና የሚገባ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም ፡ ባንድ ወገን በጠላት ላይ ድልን ለማግኘት ከሚያስችሉት ዘዴዎች አንዱ ጠላት ሳይጠነቀቅ በድንገት ደርሶ ሳያስበው አደጋ ጥሎ መውጋት ነው ። ዐፄ ዮሐንስ ፡ “መጣሁ ጠብቀኝ ፡ እንደ ሌባ አዘንግቶ ወጋኝ እንዳትል” የሚል መልእክት ለዘኪ ቱማል ሲልኩ አሳቡ ከወንድነትና

1 ብ.ጌ. ኅሩይ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐድዋ ጦርነት ፡ ገጽ 153 ።
አለቃ ተክለ ሥላሴ የእጅ ጽሑፍ ፡ ገጽ 136 ።



ከጀግንነት መንፈስ የመነጨ መሆኑ ነው ። በሌላ ወገን ደግሞ ፡ ከላኩበት ዠምሮ ወታደሩን ለማደራጀት ምሽጉን ለማጠንከር እንዳገዛት የታወቀ ነው ።

ትልቁ እስክንድር ፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ333 ዓመት በግራኒክ ዐርባ ሺ ወታደር ይዞ አንድ ሚሊዮን ያስከተለውን የፋርሱን ንጉሠ ነገሥት ዳርዮስን አሸንፏል ። ናፖሊዎን ቀዳማዊም የሞስኮብንና የኦስትሪያን ጥምር መንግሥት 120,000ሺ የሚደርስ የጦር ሠራዊት ከነርሱ አጋማሽ በሆነ ጦር ለማሸነፍ የቻለው ባመራር ዘዴ ነበር ።ስለዚህ ምን ጊዜም በማናቸውም ጦርነት ድል የሚገኘው ፡ በዘዴና ምቹ ሥፍራ ይዞ ጠላትን አዘንግቶና አሳስቶ አደጋ በመጣል ወይም ምሽግ ይዞ ተጠንቅቆ በመጠበቅ እንጂ በጦር ሠራዊት ብዛት አይደለም ። ራሳቸው ዐፄ ዮሐንስ ደጃዝማች ካሳ ሲባሉ በ1863 ዓ.ም. ዐድዋ አጠገብ ከ12,000 የማይበልጥ ወታደር ይዘው 60,000ሺ ጦር ያዘመቱባቸውን ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስን ያሸነፏቸው ምሽግ ወይም በጠባዩ ምቹ የሆነውን ሥፍራ በመቆጣጠርና በጥሩ መሣሪያ በመዋጋት መሆኑ ሊዘነጋቸው አይችልም ነበር ። ባገራችን “ኪታዳጊ ጌታ ስገዳዳ ቦታ” ይባላል ይኸውም ማለት ለጦርነት እርዳታ ከሚደርስ ጌታ የውጊያ ሥፍራ ይበልጣል ለማለት ነው ።

ከሱዳኖቹ የተሻለ የጦር መሣሪያ በተለይ በመድፍ በኩል ኢትዮጵያውያኑ ይዘው እንደነበረ በብዙ ጸሐፊዎች ዘንድ ተረጋግጧል ። ደግሞም በቅርቡ ከሰሐጢም ግንባር የተመለሱት ፡ የኢጣልያኖች ምሽግ የማይበገር መሆኑን ከተገነዘቡ በኋላ ነበር ። ደርቡሾቹም በደንብ መሽገው መጠባበቃቸውን ሲሰሙ ሌላ የውጊያ ዘዴ መፈለግ ነበረባቸው ።

ከዚህም በቀር የደርቡሹ መሪ ከሊፋ አብዱላሂ ፡ በጦሩ ግንባር አለመኖሩን እያወቁ ራሳቸው በመዝመት ፈንታ ራስ አሉላም ቢቀሩ ፡ በራስ ቢቶደድ ኃይለ ማርያም ወይም በትልቁ ራስ አርአያ መሪነት በቂ ጦር ልከው እርሳቸው ደብረ ታቦር ወይም ጐንደር ላይ ሆነው ለማዋጋት ቢችሉ ፡ የተላከው ጦር እንኳን ቢሸነፍ እርሳቸው አዲስ ያልተዋጋ ጦር ይዘው እንደገና ለመሔድ በቻሉ ነበር ። አለዚያ ደግሞ የርሳቸው መሔድ ግዴታ ከሆነ የእርሳቸው ሕይወት ከመሪነታቸው የተነሣ የተከበረና በዚያን ጊዜ የድልም ፡ የጸጥታም መድን መሆኑ የታወቀ ነበርና እርሳቸው ጥይት ወደማይደርስበት ወደ ኋላ ሆነው በርሳቸው አምሳያ በኢትዮጵያ እንደ ተለመደ አሳሳች ሊቀ መኳስ ወይም መሰል አዋጊ አስቀድመው ደጀን ሆነው ተዋጊውን በንግግር በማበረታታት ፡ ጦር ባነሰበትና በላላበት በኩል አዳዲስ ጦር እየላኩ የታወቁትን የጦር አለቆች ግንባር ቀደም አድርገው ቢያዋጉ ኖሮ በተባራሪ ጥይት ከመቁሰልና ከመሞት ፡ በርሳቸውም ሕያውነት ጦራቸውን ከመሸነፍ አደጋ ያድኑት እንደ ነበረ አይጠረጠርም ።

ወይም እጃቸውን ለመወጣት ወደፊት ቀድመው መዋጋትና ማዋጋት አስፈላጊ መስሎ ከታያቸው ወደ ጦርነት የሔዱ ሁሉ ሕይወቱ አሥጊ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ የታወቀ ስለሆነ ፡ የቅርብ ታላላቆቹን የጦር አለቆች በግል ሰብስበው በጦርነት ላይ እኔን የመቁሰል ወይም የመሞት አደጋ ቢገጥመኝ 'እገሌ አልጋ ወራሼ ነውና እርሱን ይዛችሁ እርሱም የኔ ዕድል ቢገጥመው እገሌን መሪ አድርጋችሁ ጦርነቱን ቀጥሉ' ብለው አስቀድመው አስጠንቅቀው ቢሆንኖሮ ፡ ከድል አፋፍ ላይ የተቃረበውን ተዋጊ ጦራቸውን ጨርሶ ከመፍረስና ከመሸነፍ ያድኑት ነበር ። ይኸ ሁሉ ጥንቃቄ አስቀድሞ ታስቦ ባይፈጸም በመቅረቱ እርሳቸው እንደ ተራ ወታደር በእግራቸው ሆነው ጠመንጃ ይዘው እየተኰሱ በመጋፈጣቸው ከደርቡሾቹ በተተኰሰች ጥይት ቆስለው ፡ ሊገኝ ጥቂት የቀረው ድል አድራጊነት ከርሳቸው እጅ ወጥቶ ከጠላቶቻቸው እጅ ሆኖ የርሳቸውና የጦራቸው ዕድል ከመጥፎ ሁኔታ ላይ መውደቁ ያሳዝናል ፤ ከማሳዘንም ዐልፎ ያስቆጫል ። ምናልባት የራስ አሉላም በዚህ ጊዜ ከጦር ጠቅላይ አዛዥነት መገለል ድል መሆንን ካስከተሉት ምክንያቶች አንዱ እንደሆነ አይታወቅምና እርሳቸውን ሽረው የወንድማቸውን ልጅ ራስ ኃ/ማርያም ጉግሣን መሾሙ ቢቆይ የተሻለ ሳይሆን አይቀርም ነበር ያሰኛል ።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ፡ የጦርነቱን አጀማመርና የንጉሠ ነገሥቱን መቁሰል ፡ የሠራዊቱንና የመኳንንቱን የሽሽት አጀማመር እላይ በጠቀስነው ዐይነት ከተረኩ በኋላ ፡ ፍጻሜውን እንደዚህ ሲሉ ያስከትላሉ ።

“ዐፄ ዮሐንስ ከመቁሰላቸው የተነሣ ሰውነታቸው መድከሙን ስለ ተረዱት ፡ የወንድማቸውን የደጃች ጉግሣን ልጅ ራስ ኃይለ ማርያምን (ጠቅላይ የጦር አዝማቹን) አልጋ ወራሽ ለማድረግ አስበው ጳጳሱንና እጨጌውን ለጊዜው ባጠገባቸው የተገኙትን ትልልቆች መኳንንት ሰብስበው ራስ ኃይለ ማርያምን ጥሩት ቢሉ በጦርነት ስለ ቆሰሉ ለመምጣት አይችሉም አሏቸው ። እርሳቸው ግን አይችልም ያሉኝ ቢሞት ነው ብለው በጣም አዘኑ ቀጥለው ወንድሙን ራስ መንገሻን ጥሩልኝ ብለው እኔ የሞትሁ እንደሆነ አልጋ ወራሼ ልጄ ራስ መንገሻ ነውና ለርሱ ተገዙ ብለው የኑዛዜ ቃል ተናገሩና በማግሥቱ ዐረፉ ።”

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ፡ ከዚሁ አያይዘው መኳንንቱ የንጉሠ ነገሥቱን ሬሳ በሳጥን ውስጥ አግብተው ወደ አትባራ ወንዝ ፊታቸውን አዙረው መሸሻቸውን ፡ ደርቡሾቹ በጦርነቱ ውስጥ በዠግንነት እየተሞቱ የሞቱትን የኢትዮጵያን መኳንንት ሁሉ ራሳቸውን እየቆረጡ እምዱርማን ድረስ ለከሊፋ አብዱላሂ መላካቸውን ፡ ቢሆንም ሐበሾች



በማግሥቱ እሑድ እንደገና ተመልሰው አደጋ ይጥሉብናል እያሉ ሲፈሩ ማደራቸውን ፤ ነገር ግን ሰላይ ልከው ስለነበረ ሰላዩ ተመልሶ አበሾች ፊታቸውን ወደ አትባራ ወንዝ አዙረው ይሸሻሉ እንጂ ፡ አንድም መኰንን ተዳፍሮ ፊቱን ወደኛ ያዞረ የለም ብሎ ስለ ተናገረ ፡ የጦር አበጋዙ ዘኪ ቱማል ሠራዊቱን እንደገና ባዲስ ኃይል ሰብስቦ በድንጉላ ፈረስና በግመል ጠያር አድርጎ ፡ እግር በእግር ተከታትሎ በመጋቢት ፫ ቀን (ሰኞ) ያፄ ዮሐንስን ሬሳ ይዘው የሚጓዙትን መኳንንት በአትባራ ወንዝ ዳር ሠፍረው ደርሶ አደጋ ጥሎ እንደ ተዋጋቸው ፡ ያፄ ዮሐንስ አሽከሮችና መኳንንቱ በድንኳኑ ዙሪያ ተሰልፈው እርስ በርሳቸው እየተፏከሩ ጠንክረው መዋጋታቸውን ፡ 'የጌታችንን ሬሳ አናስማርክም' በማለት በድንኳኑ በር ላይ ትልቁ ሹም አርእያ (አጐታቸው) ፡ ቢቶደድ ገብረ መስቀል ገብረ ጻድቅ ፡ የዘበኞች አለቃ ደጃች ተድላ ፡ ብላታ ገብረ ማርያም ፡ አዛዥ ወንድም ሁነኝ ፡ አዛዥ ላዕከ ፡ ጽራግ ማሠሬ ዘሚካኤል ፡ መምሕር ወልደ አረጋይ ፡ መምሕር ክንፈ ኪሩብ ፡ ቄስ ገበዝ ሰላማ መሞታቸውን ዘርዝረውታል [1]

ቴዎባልድ የሚባለው የውጭ አገር ጸሐፊ በበኩሉ ፡ “ዘማሕዲያ” ፀሚባለው መጽሐፉ የዚህን የመተማን ጦርነት ሁኔታ ባተተበት ምዕራፍ ላይ ፡

“ዘኪ ቱማል የአበሾቹ የጦር ኃይል በጣም ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ ያተኰረው ከመከላከል ላይ ብቻ ነበር . . .ስለ ዚህም ጥልቀት ያለው ጉድጓድና ዘሪባ የሚባለውን ምሽግ ከፊትና ከኋላ (በሁለት ረድፍ) እንዲሠራ አድርጎ በዚህ ሁኔታ ጥቃት እንኳ ቢደርስ ተከላካዩ ኃይል በዚያው ረግቶ እንዲከላከል አድርጎ ካንደኛው ወደ ሁለተኛው ዘሪባ (ምሽግ) ም ለመዛወር እንደሚችል አስቦ በደንብ አሠርቶት ነበር ። በመጋቢት 9 ቀን 1889 ቁጥር ስፍር የሌላቸው አበሾች እየገሠገሡ ለማጥቃት ይጐርፉ ዠመር ። በንጉሣቸው ፊት ከፍተኛ መሥዋዕትነት በመክፈል አምስት ሰዓት ያህል እንደ ተዋጉ የመዠመሪያውን ዘሪባ ሰብረው በመግባት የጥይት መዓት በጠላቶቻቸው ላይ በማውረድ ያለአንዳች ችግር ያገኙትን ሁሉ መፍጀት ዠመሩ ። ከዚህ በኋላ ቁጥራቸው ያነሰውና የተረፉት ማህዲስቶች ወደ ሁለተኛው ምሽግ (ወደኋለኛው) ተመልሰው ሕይወታቸውን

---

1 ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐድዋ ጦርነት ፡ ገጽ 154 156 ።

ለማትረፍ በሚከላከሉበት ጊዜ አበሾችም ለድል አድራጊነት በቀረቡበት ሰዓት ፥ አንዲት የተተኮሰች ጥይት (የባዘነች) ንጉሡን መትታ ጣለቻቸው የዚህም ወሬ በአበሾቹ ተዋጊዎች ዘንድ ሲደርስ ልባቸውና መንፈሳቸው ተሸብሮ የቻሉትን ምርኮ እንደያዙ ሸሽት ዠመሩ ።

ይኸን ሁኔታ የተመለከቱት ማህዲስቶች (ደርቡሾች) ምናልባት በሚቀጥለው ቀን ተመልሰው ሐበሾች ይወጉናል የሚል ሥጋት አድሮባቸው ሳለ ፥ የንጉሡ መሞት በምሽት እንደ ተሰማና ጦሩም መበታተኑን ሲመለከቱ ወደፊት ገሥግሠው በመድረስ ከንጉሡ የቅርብ ወታደሮች ጋር አትባራ ወንዝ ዳር ከተዋጉ በኋላ ብዙ ዕቃና የንጉሡን ሬሳ ማርከው ፥ ራሳቸውን ቆርጠው ፥ ለድል አድራጊነታቸው ማብሰሪያ ወደ አምዱርማን ላኩት ። አሥጊውና በጣም ኃይለኛ የነበረው የአበሾች ጦርነት በዚህ ዐይነት አከትሞ ከዚያ ሰዓት ቀጥሎ አጨቃጫቂው የዘፋን የወራሽነቱ ውዝግብ በአበሾች መካከል ቀጠለ ሲል ደምድሟል ።[1]

የቲዎባልድ አጻጻፍ ፥ ከብላቴን ጌታ ኅሩይ አባባል ጋር ስለሚገጥም ፥ ታሪኩን ለሚያነብ ሁሉ ሙሉ እምነት ይሰጣል ። ንጉሠ ነገሥቱ ከምናቸው ላይ እንደ ተመቱ ሁለቱም አልገለጹትም ። በሸዋ የሚቀመጠው ኮንት አንቶኔሊ ከትግሬዎቹ የጦር ሠፈር ከሞት ተርፎ አምልጦ የመጣ አንድ ወታደር እንዳጫወተው ፥ ንጉሠ ነገሥቱ በጠበንጃ ጥይት የተመቱት በቀኝ በኩል ዠሮ ግንዳቸውን መሆኑን ይገልጻል ። ከዚያም አከታትሎ ጦርነቱ በተዠመረበትና በድብልቅልቁ ሰዓት እንዳጋጣሚ በአበሾቹ ሠፈር ላይ ድንገተኛ ጉም ስለጣለ ፥ ሳይተያዩ በመታኮስ ብዙ አበሾች እርስ በርስ በጥይት መሞታቸውን ውጊያውም የተዠመረው እ.ኤ.አ. መጋቢት 10 ቀን መሆኑን ያወሳል ። ከጦርነቱ ቦታ ሸሽተው ያመለጡት እጨጌ ቴዎፍሎስ ንጉሠ ነገሥቱ ጦርነቱ እንደ ተዠመረ በጦሩ መካከል ሆነው የደርቡሾቹ ምሽግ በመድፍ ጥይት ከተከፈተ በኋላ ፥ ጠበንጃቸውን እንደያዙ ተዋጊው ወታደር አለበት ቆሞ ሲዋጋ እርሳቸው እስከ 400 ሜትር ቀደም ብለው ሲተኩሱ ቀኝ እጃቸውን መመታታቸውን ፥ የተመቱትን ምንም አይደለም ብለው በጨርቅ አስረው አሁንም እየቀደሙ ሲታኰሱ ከደርቡሾቹ የተተኮሰች ጥይት ግራ እጃቸውን መትታ ወደ ደረታቸው መግባቷንና ከዚያ ሰዎቻቸው ይዘው ወደ ድንኳናቸው እንደ

1 A.B. Theobald, The Mahdiya, PP. 154- 157.



ወሰዷቸው አጫወቱኝ ሲል ኮንቲ ሮሲኒ የሚባለው የኢጣልያ ዕውቅ ጸሐፊ ያመለክታል ።[1] ሌላው ጸሐፊ ደግሞ ፥ ንጉሠ ነገሥቱ በሐርና በወርቅ ያጌጠ ልብሳቸውን እንደ ለበሱ ሲዋጉ ድርቡሾቹ ባለባበሳቸው ለይተው አነጣጥረው እንደ መቷቸው ያወሳል ።[2]

በሌሎቹም ጸሐፊዎች ዘንድ ንጉሠ ነገሥቱ እንደ ተራ ወታደር በእግራቸው ሆነው በጠበንጃ ሲታኰሱ በጥይት የተመቱት ክንዳቸውንና ሆዳቸውን መሆኑ ፥ ውጊያው የተዠመረው መጋቢት መጀመሪያ ላይ መሆኑ ተገልጿል ። ነገር ግን ፥ በመተማ የተዋጉበት ጊዜ በትክክል በኢትዮጵያ አቆጣጠር መጋቢት 1 ቀን በፈረንጆች ቁጥር መጋቢት 8 ቀን እንጂ እንደ አንቶኔሊም ፥ እንደ ሌሎቹም አባባል መጋቢት 10 ቀን ወይም 9 ቀን አይደለም ። መጋቢት 10 ቀን ሰኞ አትባራ ወንዝ ላይ የተዋጉበትና እነራስ አርአያ ሞተው የንጉሠ ነገሥቱ ሬሳ የተማረከበት ነው ።

ስለዚህ መደምደሚያውን እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ንጉሠ ነገሥቱ መጋቢት 1 ቀን ቅዳሜ በመተማ ተዋግተው ከቆሰሉ በኋላ በሽሽት ጉዞ ላይ እሑድ መጋቢት 2 ቀን በተወለዱ በ54 በነገሡ በ18 ዓመት በ1881 ዓ.ም ዐርፈዋል ። ከዚያ በመጋቢት 3 ቀን ሰኞ አትባራ ወንዝ ዳር ደርቡሾቹ ደርሰው ጭንቅላታቸውን ቆርጠው ፥ ውጊያው በሱዳኖቹ አሸናፊነት ተፈጽሟል ። ደርቡሾች በመተማው ጦርነት ድሉንም ያገኙት በቅድሚያ የሐበሻን ጦር እንደምን ለመመከት እንደሚችሉ ተመካክረው በሁለት ረድፍ በጥናት ባሠሩት የመከላከያ ምሽግ መሆኑ ፥ የኛዎቹም የተሸነፉት በያዙት የጦር መሣሪያና በሠራዊታቸው ብዛት በመተማመን በእልህ ተጋፍጠው በነዚያ ምሽግ ላይ በመውደቃቸውና ይልቁንም ወደፊት ቀድመው እንደተራ ወታደር በመዋጋት ላይ የነበሩት የንጉሠ ነገሥቱ በድንገተኛ ጥይት ተመትተው መቁሰላቸው ነው ።[3]


1 Co Conti Rossini, P. 461 Italia ed Etiopia del Trattato d'Ucciali alla Battaglia d'Adua-
እርግጥ ንጉሠ ነገሥቱ ከ300 እስከ 400 ሜትር ከሠራዊታቸው ርቀው ሲዋጉ ካዩዋቸው የተከበሩት እጨጌ ለምን ተቆጥተው እምቢ ቢሉም ገዝተው አላስቀሩቸውም ? እንደሚመስለው በዚህ አፍላ ጦርነት እጨጌው ወሬ ስሙ እንጂ ያሉበት አይመስልም ። እርሳቸው ቀደም ብለው ሸሽተዋል ።
2 A. Anestrini I Prigionieri del Mahdi, P. 72.
3 A. Del Boca,, Gil Italiaoi in Africa Orientale, PP.323-324.

ስለ ዐፄ ዮሐንስ አሟሟት በኋለኛው ጊዜ እንደዚህ ተብሎ ተገጥሞላቸዋል ።

ዐፄ ዮሐንስ ሞኝ ናቸው
እኛም ሁላችን ናቅናቸው
ንጉሥ ቢኋቸው በማኸሉ
ወሰን ጠባቂ ልሁን አሉ
በጐንደር መቱኮስ ፡ በደንቢያ መታረድ አዝኖ ዮሐንስ
ደሙን አፈሰሰ እንደ ክርስቶስ
እንዳያምረው ብሎ ድሃ ወዳጁን
መተማ አፈሰሰው ዮሐንስ ጠጁን
የጐንደር ሃይማኖት ቆማ ስታለቅስ
አንገቱን ሰጠላት ዳግማይ ዮሐንስ
እጅግ ደስ ይለኛል ያንተ ስም ሲነሣ
የቁና አፈር ንፉግ አንተ ነህ ወይ ካሳ?[1]

1 ኀሩይ ወ. ሥላሴ ኢትዮጵያና መተማ የዐፄ ዮሐንስ ታሪክ ፣ ገጽ 17 ።
ተ.ጸ.መ. ፣ የኢት. ታሪክ ካፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀ. ኃ.ሥ. ፣ ገጽ 84 ።





ዐፄ ዮሐንስ

(ከምስተር ስማትስ ሐሪሰን መጽሐፍ)

አፄ ዮሐንስ ከደርቡሾች ጋር የተዋጉበት የመተማ ሥፍራ



# ምዕራፍ ሃምሳ ሁለት

## የደርቡሾች አሸናፊነትና የዘኪ ቱማል ድንፋታና ውድቀት-የከሊፋ አብዱላሂ አል ታሺ ፍጻሜ

ያፄ ዮሐንስ ታማኝ መኳንንትና የቤተ መንግሥት ዘበኞች የጌታቸው ሬሳ በተቀመጠበት ድንኳን በራፍ ላይ ቢቻል ሕይወታቸውን አለያም ሬሳቸውን ከምርኮ ለማዳን በፍጹም ጀግንነት እየተዋጉ ቢሞቱም ፍጻሜውን ከመሸነፍ አልዳኑም። አሸናፊዎቹ ሱዳኖች ከድል በኋላ ግማሹ ሲማርክ ግማሹ የጓዝ ዕቃ ሲዘርፍ፣ ዋንኞቹ ወደ ድንኳኑ ውስጥ ገብተው በሰም የተመረገውን ሳጥን ገንዘብ ያለበት መስሏቸው ቢከፍቱ የሰው ሬሳ ሆኖ አገኙት። ከምርኮኞቹ አንዱን አቅርበው "የማን ሬሳ ነው" ብለው ቢጠይቁት "ያፄ ዮሐንስ ነው" ብሎ አረጋገጠላቸው። በሳጥኑም አጠገብ ከሬሳው ጋር ዘውዳቸው፣ በብራና የተጻፈና ገበታው በባሕር ዐረብና በወርቅ የተለበጠ አርባዕቱ ወንጌል፣ የዕለት የሳምንት የወር ያመት ቊጥር የሚቆጥር የወርቅ ሰዓት፣ በነስሚት ሐሪሰንና በነፖርታል አማካይነት ከንግሥት ቪክቶሪያ በተለይ በወዳጅነት ዘመን በየጊዜው የመጣላቸው ትልቅ በሩቅ የሚያሳይ መነጥር፣ ባለፈርጥ መስቀልና ሌላም ብዙ ዕቃ ተገኘ።

ደርቡሾቹ በዘኪ ቱማል ትእዛዝ የንጉሠ ነገሥቱን ጭንቅላት ቆርጠው ከነራስ አርአያና ከጓደኞቻቸው የተቆረጠ ራስ ጋር ወደ አምዱርማን ለከሊፋ አብዱላሂ ላኩለት። ከሊፋ አብዱላሂ የጦርነቱን ውጤት ወዳጀ ከማስያዝ ጋር አቆብቁቦ ይጠብቅ ነበርና የድል አድራጊነቱን ዜና ከንጉሡ ጭንቅላት ጋር ሲደርሰው፣ በደስታ ተውጦ ነጋሪት እንዲመታና መለከት እንዲነፋ አዞ የከተማው ሰው ሁሉ ብዙ ሸኮችና ቃዲዎች በተሰበሰቡበት ታላቅ የድል በዓል ተደረገ። ከሦስት ቀን በኋላም ያፄ ዮሐንስን የተቆረጠ ጭንቅላት በዕንጨት ላይ ሰክቶ በግመል ጀርባ ላይ አስደርጎ ገበያ ለገበያ፣ መንደር ለመንደር እየዞረ በመታየት እስላማዊው የሱዳን ሕዝብ እንዲደሰትበት አደረገ።[1]

---

1 ብ.ጌ. ኅሩይ፣ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐድዋ ጦርነት፣ ገጽ 155።

ይኸ ሁሉ ሲሆን ፥ ድል አድራጊው የምሥራቅ ሱዳን (የገዳሪፍ) አገረ ገዥ አሚር ዘኪ ቱማል መጋቢት 1 ቀን ያገኘውን ድል በአስቸኳይ ወደ እምዱርማን ለጌታው ለከሊፋ አብዱላሂ ከላከ ወዲህ ፥ እዚሁ ገዳሪፍ ተቀምጦ ያዬ ዮሐንስን ሬሳ ይዘው ወደ አትባራ ወንዝ የሸሹትን ኢትዮጵያውያን ተከታትሎ ከመደምሰስ በቀር እምዱርማን ራሱ ሔዶ ደስታ አልተካፈለም ።

አሁን ደግሞ ፥ አትባራ ወንዝ ዳር እንደ ሰፈሩ በኢትዮጵያውያኑ ላይ በድንገት ደርሶ የተዋጋበትንና ያገኘት ቀረጣውን ሁኔታ እንደዚህ ሲል በጽሑፍ ለከሊፋው አብራርቶታል ።

"በይቅር ባዩና በመሐሪው እምላክ ስም ምስጋናና ጸሎት ለነቢዩና ለቤተሰቡ ።

ከእግዚአብሔር ምስኪን ደሃ ከዘኪ በእግዚአብሔር ዘንድ ድጋፍ ላለው ለመህዲ ተከታይ ለከሊፋ አብዱላሂ ቤን መሐመድ. . .

ጌታ ሆይ ።

ቀዳሚ 6 ራጀብ 1306 * ከእግዚአብሔር ጠላቶች ከሐበሾቹ ከተዋጋን ወዲህ ከዚህ በፊት ሥፍራውን ለጌትነትዎ እንደ ገለጽሁት ሁሉ ፥ ዱካቸውን እየተከታተልን ስንሔድ ቆይተን በእኩለ ሌሊት ከሠፈራቸው ተጠግተን የሚያነዱትን እሳት እያየን እስኪነጋ ድረስ እየጠበቅናቸው አደርን ። እነሱም ጠርጥረው ኖሮ ያንድ ክፍል ጦር ጠባቂ ቃፊርና ሰላዮች ልከው ሲሰልሉ አግኝተን ወግተን ወዲያው ደመሰስናቸው ። ከዚህ በኋላ ሲነጋ በእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ፊት ተጓዝን ። እንደ አሸዋ የበረከቱት ጠላቶቻችን ከአትባራ ወንዝ ማዶ ሠፍረው ሳለ በመሬት ላይ ዝናም ባንድ ጊዜ ዤቅ ብሎ እንደሚወርድ በላያቸው ላይ ደርሰን ጦርነት ገጠምናቸው ። የኛዎቹ በሃይማኖታቸው ጸንተው ጥይትን ሳይፈሩ ኢአማናውያኑን ** ሳይፈሩ ጠንክረው በመዋጋት አሸነፉ ። እስከ ቀኑ ሁለት ሰዓት ድረስ ከተዋጋናቸው በኋላ ከሐዲዎቹ ከእስላሞቹ በፊት ስለሸሹ ሠፈሩ ባዶ ሆኖ ቀረ ። ንጉስ አቧራን እንደሚጠርግ እነሱም እንደዚያ ተጠረጉ ። የጦርነቱ ቦታ በአበሾች ሬሳና ቁስለኛ ተሞልቶ ነበር ። በሽሽታቸው ጊዜ ወንድም ወንድሙን ሊረዳው አባትም ስለ ቆሰለው ልጁ ለማሰብ አልቻለም ። ሠፈሩ በብዙ ድንኳን ከሺ በሚበልጡ በፈረሶች ፥

በበቅሎና በአህዮች ተሞልቶ ነበር ። በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉንም ወርሰን በነርሱ እጅ በመሐመድ አርባብ መሪነት ተዋግተው በምርኮ የነበሩትን እስላሞች ተበጀናቸው ። *

እዚያ ላይ የእግዜር ጠላት የሆነው ዮሐንስ ቅዳሜለት በተደረገው ጦርነት ሞቶ ኖሮ ሬሳው በሳጥን እንደሆነ በጃችን ገባ ። አለቆቹ ግን ይኸን ደብቀው ለወታደሩ መቁሰሉን ብቻ አውርተው ሌላ የጦር አለቃ ሾመው ነበር እኛም የንጉሡን የዮሐንስንና በሁሉ ቦታ እየተከተለ የሃይማኖቱን ጉዳይ የሚፈርደውን (ፍትሐ ነገሥት አውጪ ወይም ንስሐ አባት?) ትልቁን ካህን እንደዚሁም የደጃች በርሄንና የብዙ አለቆች ጭንቅላት ቆረጥን ። ለእግዚአብሔር ለነቢዩ ለመሐመድና ለተከታዮቹ ተስፋ በመስጠት የተሞቱትን ሁሉ እምላክ ይሸልማቸው በሚመጣው ዓለም (በሰማይ) የሚገኘውን ደስታ ተስፋ በማድረግ ድሉን ለማግኘት ስንል ሞትን እየተሽቀዳደምን እንዋጋ ነበር። ይህ ያሁኑ ጦርነት ፥ መሰል የሌለው ታላቅ ጦርነት ነው ። ስለዚህም እግዚአብሔር ስለረዳን እናመሰግነው ። ለወደፊቱም ስለ ሃይማኖታቸው እነዚህ የሚዋጉት ኃይላቸውም ፥ ሞራላቸውም ከፍ ያለ ስለሆነ ኢአማናውያንን ለመዋጋት የተዘጋጁ ናቸው ። የተረገመው ዮሐንስ የመሸነፉን ምልክት ከመተው በቀር ተከታዮች ስላላደረገ ያሁኑ ድል አድራጊነታችን አበሻን እንደሚያስገዛን ተስፋ እናደርጋለን ።

ባሁኑ ጊዜ ከባሕር ዳር ሰፍረው የኛዎቹ ታማኞች በራሪዎቹን ከማሳደድ ላይ ይገኛሉ ። ብዙ ወንዶች ከነሚስቶቻቸው ከነቤተሰቦቻቸው ማርከዋል ። ከብዛቱ የተነሣ የምርኮውን ዕቃ ሦስት ቀን ሙሉ እግዘው ለመጨረስ አልቻሉም ። ስለ ቸርነቱ እምላክን እናመሰግናለን ። ለርስዎም ከኛ ወገን ከድል ወሬ በቀር ሌላ (ክፉ ወሬ) እንዳይደርስዎት እንመኛለን ። ሁሉም ነገር ከተጠናቀቀ በኋላ ለጌትነትዎ ዝርዝሩን ወደፊት እልካለሁ ። በድል አድራጊነታችን ወዳጆቻችን ይተማመኑባቸው ዘንድ ልዩ ልዩ የተማረኩትን የዮሐንስን ዕቃዎች ይኸን ደብዳቤ በሚያቀርብልዎት ሰው እጅ ልኬያለሁ ። የሐበሾቹም መድፎች ከነጥይቶቻቸው በእጃችን ገብተዋል ። በጸሎትዎ እንዲረዱን ጌትነትዎን እንለምናለን ። **

* በዐረብኛ አቆጣጠር በኢትዮጵያ መጋቢት 1 ቀን 1881 ዓ.ም.

** ኢአማናውያን (ከሐዲዎች) የሚሉት በእስላሞች ዘንድ ከእስልምና ሃይማኖት ውጭ ሆኖ በቁራን የማያምነው ሁሉ የማያምን ከሐዲ ይባላል ።

* በ1879 ዓ.ም. ራስ አሉላ የተዋጉ ጊዜ የተማረኩ መሆን አለባቸው ።

** የደብዳቤው ትክክለኛ ትርጉም ከዐረብኛ ዱግስ በሚባል ተተርጉሞ በኢጣልያንኛ ያገኘሁትና በፎቶ ኮፒ የወሰድሁት ከቀድሞው የኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ታሪካዊ መዝገብ ቤት ውስጥ (3- 6) ነው ። ወደ አማርኛም የመለስኩት ከኢጣልያንኛው ትርጉም ላይ መሆኑን ለአንባቢ አስገነዝባለሁ ።

ዘኪ ቱማል በዚህ ደብዳቤ ውስጥ "አቧራን ነፋስ እንደሚጠርግ ፣ እኛም አበሾቹን ጠረግናቸው . . . አበሾች በሸሹበት ሰዓት ወንድም ወንድሙን ፣ አባት የቆሰለውን ልጁን አልረዳም . . . " ከማለት ጋር የራሱንና የወገኖቹን ጉብዝና ከማድነቅ በቀር ፣ በዋናው በመተማው የቅዳሜው ጦርነት ለት አበሾቹ አንደኛውን ምሽግ አስለቅቀው ከሁለተኛው ምሽግ ውስጥ ተጋብተው በሚዋጉበት ሰዓት ጸሐፊው ሁሉ ያወሳውን በደርቡሾቹ ላይ የነበረውን ፍርሃትና ሽብር ሊያነሣው አልፈለገም ። እንደዚሁም ከመተማው ጦርነት ወዲህ ሰኞ ለት አትባራ ወንዝ የጌታቸውን ሬሳ ላለማስማረክ በድንኳኑ በራፍ ላይ እየተፏከሩ የተላለቁትን የነራስ አርአያን የነቢተደድ ገብረ መስቀልን ዝብዱ ምልክቱንም ስለ አልጠቀሰ ፣ አድላዊ መሪና ጸሐፊ ነው ማለት ነው ። በርሱ አንጻር ከ350 ዓመት በፊት የግራኝን ታሪክ የጻፈው ሺሃብ ኤዲን አህመድ ቤን አብድል ቃድር የጠላቶቹን የነአዝማች አዳሉን ፣ የነራስ ወሰን ሰገድን ጀግንነት ሳይደብቅ የጻፈውን ስናስታውስ ፣ በሁለቱ መካከል ያለውን የሐቅና የመንፈስ ልዩነት እንገነዘባለን ።

የሆነ ሆኖ ፣ በመተማውና በአትባራ ወንዝ ያፄ ዮሐንስ መሸነፍ ለከሊፋ አብዱላሂ ሥልጣኑን በጣም ከፍ አድርጎ በአካባቢው ፣ ባገር ውስጥም ትልቅ ያሸናፊነትን ዝና አተረፈለት ። በርሱ ላይ ባገር ውስጥ የሚነሡት አሚሮች ሁሉ አነሣሣቸው እየከሸፈ ሲያዙ ወይም ሲማረኩ በካርቱምና በኦምዱርማን ባደባባይ ግማሾቹ በስቅላት ፣ ግማሾቹ አንገታቸው በሰይፍ እየተቀረጠ መፈጀቱን ቲዎባልድ የተባለው እንግሊዛዊ በመጽሐፉ ገልጾታል ።[1]

እንደዚሁም ፀፄ ዮሐንስን በማሸነፉና የመኳንንቱን አንገት በሰይፍ በማስቀረጡ የተመካው ዘኪ ቱማል ሦስት ዓመት ያህል በባለሟልነትና በባለሥልጣንነት ከቆየ በኋላ ፣ ከ1885 ዓ.ም ላይ ባለሟልነቱ መቀዝቀዝ ጀመረ ። ቀጥሎም አንዳንድ ባለሥልጣኖች እየተያዙ የሞት ቅጣትና እስራት ሲደርስባቸው ፣ አሚር ዘኪ ቱማልም በተራው በቀናተኛው በያኩቡ (ያዕቆብ) ጠቋሚነት በከዳት ወንጀል ተከሶ ከግዛቱ ከገዳሪፍ በዚሁ ዓመት ተጠርቶ ኦምዱርማን ሲገባ ወዲያው እጁ ተይዞ በወህኒ ቤት ገብቶ በከባድ እግረ ሙቅ ታሰረ ። በኋላም ከሰው በፍጹም ወደማይገናኝበት ወደ አንዲት ትንሽ ጎጆ ተዛውሮ ብቻውን ሐያ ቀን ያህል እንደቆየ በረኃብና በውሃ ጥም ተሠቃይቶ ሞተ ። በርሱም እግር አህመድ ዋድ ዐሊ ተሾመ ።[2]

1 A. B. Theobald, The Mahdiya, PP.156- 157.

2 Slatin and Wingate, Fire and Sword in the Sudan, PP. 300-301 .



ይኸን ሁሉ ካደረገ በኋላ ፣ ታላቁ ኃይለኛውና ጨካኙ አሚር አብዱላሂም በሱዳን ተፈርቶና አንቀጥቅጦ ሲገዛ ከቆየ በኋላ ፣ ዘኪ ቱማል በሞተ በአራተኛው ዓመት ከ1889 ዓ ም ላይ በእንግሊዝ መንግሥት ትእዛዝ ፣ በማህዲስቶች እጅ የተገደሉትን የጀኔራል ጐርዶንን ፣ የነጀኔራል ሂክስን ደም ለመበቀል ጀኔራል ኪችነር 28ሺ የሚደርስ የእንግሊዝና የግብጽ ድብልቅ ጦር ይዞ መጥቶ 40ሺ ጦር ይዞ ከጠበቀው ከከሊፋ አብዱላሂ ጋር በ1890 ዓ ም በሚያዝያ ወር ላይ እዚያው ያፄ ዮሐንስ አንገት ከተቀረጠበት ከአትባራ ወንዝ አጠገብ ጦርነት ተጋጥመው ደርቡሾቹ በአሮጌ ጠመንጃ በመታኮስና አንገት መቁረጥ ያስለመዱትን ሰይፋቸውን እያወዛወዙ ለመመከት ሲዋጉ እንግሊዞቹ ማክሲም በሚባለው መድፍና ዘመናዊ በሆነ ጠመንጃ እንደልብ አጨዱዋቸው ። ከዚያም አብዱላሂ የተረፉትን ወታደሮቹን ይዞ ወደ ዋናው ከተማ ወደ ኦምዱርማን ቢሸሽ የእንግሊዙ ጀኔራል እዚያው ድረስ ተከታትሎ ሔዶ ወጋው ። ከዚያም ወደ ጐርዶፋን ቢሸሽ የኪችነር ተከታይ ሰር ረጂናልድ ዊንጌት በበረሃ የብዙ ቀን ክቢ አድርጎ ከማረከው በኋላ ከግብረ አበሮቹ ጋር በ1891 ዓ.ም. በፍርድ ገደለው ።[1]

ከዚህም በኋላ ያፄ ዮሐንስ ኢትዮጵያ ከጠላት ጋር እየተዋጋች ድሏን እየተጐናጸፈች በነጻነት ስትኖር ፣ የኃያሉ የከሊፋ አብዱላሂ ሱዳን ግን ፣ ከእንግሊዝና ከግብጽ ጥምር አገዛዝ ውስጥ ገብታ ሱዳን አንግሎ ኤጂፕሺያን ኮንዶሚኔሽን የሚባል ሥያሜ ተሰጥቷት የአፍሪካውያን የነጻነት ጊዜ እስኪመጣ ድረስ ቆየች ።

1 E. Anghieri, Storia Della Politica Inglese Nel Sudan, PP. 120-127.

# ምዕራፍ ሃምሳ ሦስት

## ዐፄ ዮሐንስ ሞት ያስከተለው የዙፋን ባላንጣነት — በባላንጣነቱ ፊት የተጠቀሙት ወገኖች

ምንም እንኳን በ10—13ኛው መቶ ዓመት መካከል የዛጉዌ ነገሥታት ጣልቃ ቢገቡ ከዚያም በፊትና ከዚያም በኋላ ፣ በኢትዮጵያ ዙፋን ተቀምጦ ዘውድ ደፍቶ የሚገዛው ነጋሢ ከሰሎሞን ዘር የተወለደ መሆኑን ያገራችን ታሪክ ነገሥት በብዙ ቦታ ይነግረናል ። አንዱ ነጋሢ በኃይሉ ወይም ባባቱ ኑዛዜ ነግሦ እዙፋን ከወጣ በኋላ ፣ የቀሩት ወንድሞቹና የደረሱ ልጆቹ የመንግሥ ፍላጎት አድሮባቸው በዚህ ምክንያት ባገር ላይ ሁከት እንዳይደርስ ሁሉም ተይዘው ባንድ ተራራ ወይም ባንድ ደሴት ሥፍራ ተለይቶ ፣ ጠባቂ ተደርጎ በተራቸው የመንገሥ ዕድል እስኪገጥማቸው ድረስ በግዞት ይኖሩ ነበር ። ለዚህ የግዞት ሥፍራ ከሁሉም በጣም የታወቀው በወሎ ክፍለ ሀገር በአምባሰል አውራጃ የሚገኘው ግሸን አምባ ነው ። እርሱም የነጋሥያን የማጋገሪ ሥፍራ ከመሆኑ የተነሣ ፣ ብዙ ጊዜ የግዕዙ መጽሐፍ አምባ ነገሥት ይለዋል ።[1]

በጐንደር ዘመነ መንግሥት ደግሞ ፣ እዚያው ጐንደር አቅራቢያ ወሀኒ እየተባለ የሚጠራ አለ ። በጐንደር የነገሠው በሞተ ቁጥር የትኛውን ነጋሢ አውጥቶ ለማንገሥ በነበረው ፍጅት የጦር አለቆችና አስተዳዳሪዎች ወገን ለይተው እርስ በርሳቸው ሲዋጉ ከሁለቱም ወገን የሚያልቀው ሕዝብ መጠኑ ከፍ ያለ ነበር ። ጠቡ ገና ንጉሡ ከታመመበት ጊዜ ይዠመርና አለቆች የተስማሙበት ነግሦ በዙፋኑ እስኪረጋጋ ድረስ ፍጅቱና ትርምሱ በታሪክ ውስጥ ተመዝግቦ የሚገኘው ብዙ ነው ።[2]

---

1 ተ.ጸ.መ. ፣ የግራኝ አህመድ ወረራ ምዕ 100 ፣ ገጽ 570—576.

2 ተ.ጸ.መ. ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ካ፮ ልብነ ድንግል እስከ ፀ፪ ቴዎድሮስ ፣ ገጽ 83—85 ፣116—123 ፣ 216—318 ፣ 221—222 ።

ብለው ተናዘዋል የሚል ያዋጅ ቃል ተነገረና ከደጃች ቦጋለና ከደጃች መሸሻ በቀር ሁሉም አሜን ብሎ ተቀበለ ። ደጃች ቦጋለና ደጃች መሸሻ ግን ለጃንሆይ ልጅ የላቸውም ። በወንድም ልጅነት የሆነ እንደሆነ ግን ሁላችንም እኩል ነንና አገራችን ከገባን በኋላ እግዚአብሔር ለሚሰጠው ይሰጠዋል እያሉ ልብሳቸውን (ኩታቸውን) በአፍንጫቸው ላይ እያደረጉና እያጉረመረሙ ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ ይባላል ።”[1]

ስለራስ መንገሻ ያፄ ዮሐንስ ልጅነት ብዙ የሚወራ ነገር አለ። አንዳንዱ ዐፄ ዮሐንስ በምስጢር ከመነኮሱ በኋላ የወለዷቸው ናቸው ሲል ፣ ሌላው ደግሞ ወንድማቸው ጉግሣ ከሞቱ ብዙ ዘመናቸው ስለ ሆነ በድብቅ ከወንድማቸው ሚስት ወለዷቸው ይላሉ ። የቀሩት ደግሞ ብዙዎቹ እንደ ብላቴን ጌታ ኅሩይ የወንድማቸው የደጃች ጉግሣ ልጅነታቸውን በማረጋገጥ ያፄ ዮሐንስ ልጅ የተባሉት አልጋቸውን ስለ አወረሷቸው ብቻ ነው ይላሉ ። በእርግጥም የሚመስለው ይኸው ነው ። መንገሻ የባሕርይ ልጃቸው ቢሆኑ ኖሮ በቆሰሉበት ሰዓት መዠመሪያውኑ ለልጄ ለመንገሻ አልጋዩን አውርሻለሁ ባሉ ነበር ። ነገር ግን የመንገሻ አልጋ ወራሽነት የመጣው የታላቅ ወንድማቸው ልጅ የራስ ኃይለማርያም ጉግሣ ሞት ከታወቀ በኋላ ነው ።

የሆነ ሆኖ ፣ እነራስ መንገሻ ከመተማ ወደ መቀሌና ወደ ዐድዋ ከተመለሱ በኋላ ፣ ከቦጋለና ከመሸሻ በቀር ሌሎች የዙፋኑ ባላንጣዎች ባንድ ጊዜ ይገጥማሉ ። እነዚህም አንደኛ ካፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ዠምሮ ዙፋኑን ካፄ ዮሐንስ ጋር ሲከራከሩ የቆዩት ደጃች ደብብ ናቸው ። እርሳቸውም የትልቁ ራስ አርአያ ከፍተኛው ልጅ ስለሆኑ ፣ በተለይ ባሁኑ ዐፄ ዮሐንስ ባረፉበት ጊዜ ዙፋኑን አገኛለሁ በማለት የኢጣልያንንና የእንግሊዝን እርዳታ ደጅ የሚጠኑበት ሰዓት ነበር ። ሁለተኛ የራስ ገብረ ኪዳንና የእቴጌ ድንቅነሽ ልጅ ደጃች ሥዩም አባ ጎበዝ የሚባሉት ናቸው ። እርሳቸውም የዙፋን ፍላጐታቸውን ደበቅ አድርገው በምኒልክ ደጋፊነት ከደጃች ደብብም ፣ ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላም ጋር እየተዋጉ የቀረው ቢቀር የትግራይን ግዛት ለመያዝ የሚጣጣሩ ነበሩ ።

ስለዚህ ፣ በሰሜን ምሥራቅ የኢጣሊያኖች ወረራና መስፋፋት በሰሜን ምዕራብ በኩል ለተነሡት ደርቡሾች እንዳገዘ በሰሜን ምዕራብም በኩል በደርቡሾች መነሣትና በመተማው ጦርነት ባፄ ዮሐንስ መሞት ፣ በዙፋን ባላንጣዎቹ መብዛት በጣም የተጠቀመው

1 ብ. ጌ. ኅሩይ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐድዋ ጦርነት ፣ ገጽ 155—156 ።



የኢጣልያ መንግሥት ነበር ። በዚህ ምክንያት ፣ አንቶኔሊ ከሸዋ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ለክሪስፒ በላከው አስቸኳይ ራፖር ውስጥ መደምደሚያውን “የትግሬ ተዋጊዎች ከመተማ ተመልሰው ቁስላቸው ሳይድን ኃይላቸው በደከመበት ፣ ሞራላቸው በወደቀበት ሰዓት ወደ አሥመራ መገሥገሥ ነው” የሚል ቃል ይገኝበታል ። ይኸንኑ እንዲፈጽም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቼስኮ ክሪስፒ ምጥዋ ለሚገኘው ለጀኔራል ባልዲሠራ ቢያስተላልፍ ከጀኔራሉ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የተሰጠው ፣ “እኔ ከምጥዋ ወደ አሥመራ ከመጓዜ በፊት ባላንጣዎቹ በቅድሚያ እርስ በርሳቸው ቢተላለቁ ይጠቅማል” የሚል መልስ ነበር ። በትክክል ቃሉ፦

“. . . ደብብ ኃይሉን ለማጠንከር ከዐድዋ (እየከዱ ከነራስ መንገሻ) የሚመጡትን ወታደሮች እየጠበቀ ነው ፤ ወደ ዐድዋ መሔድም ይፈልጋል ። እኛንም በቶሎ ወደ አሥመራ እንድንዘልቅ ጠይቆናል ። ከያለበት የተጠራቀሙ 20ሺ የትግሬ ወታደሮች የበለጠ ለሚከፍላቸው ለመዋጋት ተዘጋጅተዋል ። ነገር ግን እኛ ሳንሔድ የነርሱ (የመንገሻና ደብብ) መተላለቅ ቢቀድም ይጠቅማል” የሚል ነው ።[1]

በነዚህ ሁሉ መካከል ቀደም ብለው በመታወቅና በማናቸውም መስክ በመደርጀት ፣ በትግሬዎቹም መሳፍንት የርስ በርስ ውጊያ በመጠቀም ራስ መንገሻም ፣ ደጃች ደብብና ደጃች ሥዩምም በኢጣሊያኖቹ የጦር መሣሪያ እንዳይታጠቁ ፣ የኢጣልያን መንግሥት ወዳጅነት ቀደም አድርገው በመያዝና በማጠንከር የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ በዚህ ጊዜ አቅማቸውን በማኸል አገርና በደቡብ በኩል አጠንክረው ይገኙ ነበር ። ከመተማ ጦርነት የተመለሱት እነራስ ሚካኤል ጳጳሳቱም እየመጡ ስለ ገቡላቸው ፣ የቤጌምድርም መሪዎች የጐጃሙም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አሉበት ድረስ መጥተው በመገናኘት ስለ ታመኑላቸው ካፄ ቴዎድሮስ ዘመን ዠምሮ ይመኙትና ይጠብቁት የነበረው ንጉሠ ነገሥታዊ ዙፋን ያለጦርነት በእጃቸው ገባ ። የምኒልክ መንግሥትም እያደር የመጠንከር ፣ ነገዶችን በውስጡ የመሰብሰብና የመደርጀት መልክ ስለአሳየ ፣ ዘኪ ቱማል እንደ ተመኘው ከዘረፋ በቀር ከሊፋ አብዱላሂ ኢትዮጵያን ለመግዛት የነበረው ፍላጐት በሰሜን በኩል የተንጠለጠለውም የርስ በርስ ጦርኒት ቆመ ። በፊት ወዳጅ መስሎ በኋላ ጠላት ሆኖ ከተገኘው ከኢጣልያ ጋር የተደረገው ሰፋ ያለው የፖለቲካና የጦርነት ውዝግብ ግን ፣ በሚቀጥለው መጽሐፍ ለብቻው ይተነተናል ።

1 L'Italia in Africa . . . Documenti . . (1888-1899) PP.219-226.

## ያፄ ዮሐንስ መሳፍንት ፣ መኳንንትና ሹማምንት ዝርዝር

### 1ኛ ራስ አርአያ ሥላሴ ዮሐንስ

ራስ አርአያ አባታቸው ዐፄ ዮሐንስ ሲሆኑ ፣ እናታቸው ደግሞ የደንከል ተወላጅ ፣ ክርስትና ተነሥተው ጥበበ ሥላሴ የተባሉ ሴት ናቸው ። የተወለዱት በ1860 ዓ. ም. ነው ። በ1875 ዓ. ም. የስምንት ዓመቷን ወጣት ዘውዲቱ ምኒልክን አግብተው ነበር ።በዘመናቸው የቤጌምድር ግዛት ተሰጥቷቸው ሲኖሩ ፣ በተወለዱ በሐያ ዓመታቸው በ1880 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ። (እርሳቸውም ከሌላ ሴት ራስ ጉግሣ አርአያን ወልደዋል ።

### 2ኛ ራስ አርአያ ድምፁ

ያፄ ዮሐንስ እናት የወይዘሮ ሥላስ ወንድም ናቸው ። ዘራቸው ከዚህ እንደሚከተለው ይነበባል ። ተስፋ ኢየሱስ ከወይዘሮ ወለተ ጽዮን ራስ ወልደ ሥላሴንና ደጃዝማች ደብብን ፣ ደብብ ደጃዝማች ድምፁን ፣ ድምፁ ከወይዘሮ ታቦቱ ራስ አርአያንና ወይዘሮ ሥላስን ፣ ሥላስ ዐፄ ዮሐንስን ፣ ራስ አርአያ ፣ ደጃዝማች ደብብን ፣ ደጃች ቦጋለን ፣ ደጃዝማች አብርሃን ፣ ደጃዝማች ተድላ አባ ጉበንን ፣ ወይዘሮ አምለሱን ይወልዳሉ ። አምለሱ የራስ አሉላ ባለቤት ናቸው ።

አርአያ በመዠመሪያው ወቅት ላፄ ቴዎድሮስ እንደ ባለሟል ሆነው በዓልጋዳ አርአያ እየተባሉ እንደርታን ያስተዳድሩ ነበር ። ዠግንነታቸውንም ዐፄ ቴዎድሮስ መስክረውላቸዋል ። በመጨረሻው ጊዜ እንደ ሌሎቹ መሳፍንት በመቅደላ ታስረው መቅደላ ሲሰበርና ዐፄ ቴዎድሮስ ሲሸነፉ ፣ ነጻነታቸውን አግኝተው የእንግሊዝ ጦር ሲመለስ አብረው ሔደው በዚያን ጊዜ በትግራይ ሥልጣን ከጨበጡት ከእኅታቸው ከወይዘሮ ሥላስ ልጅ ከደጃዝማች ካሳ ጋር በስናእፌ ተገናኙ ። ካሳ ዐፄ ዮሐንስ ተብለው ከነገሡበት ከ1864 ዓ. ም. ዠምሮ በመተማ በ1881 ዓ.ም. እስኪሞቱ ድረስ ለንጉሠ ነገሥቱ ጭፍራም አባትም ሆነው በስምምነትና በፍቅር ኖሩ ።

## 3ኛ ራስ ኃይለ ማርያም ጉግሣ

ራስ ኃይለ ማርያም ያፄ ፡ ዮሐንስ ታላቅ ወንድም የደጃዝማች ጉግሣ ልጅ ናቸው ። ቀደም ብሎ በደጃዝማችነት ማዕረግ ዋድላን ያስተዳድሩ ነበር ። በኋላም የራስነት ማዕረግ ተጨምሮላቸው ራስ አሉላ ይዘውት የነበረውን የጦር ጠቅላይ አዛዥነት ተሾመው በዚሁ ሥልጣን እንዳሉ ፡ የመተማ ዘመቻ ጊዜ ሕይወታቸው በጦርነቱ ላይ ዐለፈ ። ንጉሠ ነገሥቱ በቆሰሉበት ሰዓት ዙፋናቸውን ለማውረስ ሲያስጠሩዋቸው መሞታቸው ስለ ተነገራቸው ፡ እንግዲያውስ ወንድሙን መንገሻን ጥሩ ብለው ዙፋናቸውን ለራስ መንገሻ አወረሱ ።

## 4ኛ ራስ መንገሻ ዮሐንስ

ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ ፡ በመጽሐፋቸው ራስ መንገሻን ያፄ ዮሐንስ ልጅ አድርገዋቸዋል ። ብዙ የሰሜን ክፍለ ሀገር ሰዎች እንደ ራስ ኃይለ ማርያም የደጃዝማች ጉግሣ ልጅ ያደርጓቸዋል ። በእውነትም ልጃቸው ቢሆኑ ኖሮ ዐፄ ዮሐንስ በመተማ በቆሰሉ ጊዜ ዘውዳቸውን ለማውረስ ኃይለ ማርያምን ጥሩልኝ በማለት ፈንታ መንገሻን ጥሩልኝ ባሉ ነበር ለማለት ይቻላል ። የሆነ ሆኖ ፡ ንጉሠ ነገሥቱ የራስ ኃይለ ማርያምን ሞት ከሰሙ በኋላ ፡ አልጋዬን ለመንገሻ አውርሻለሁ ስላሉ ልክ እንደ ልጅ አድርገዋቸዋል ለማለት ነው ። በዚህም ምክንያት ራስ መንገሻ በማኅተማቸውም ፡ በጽሑፍም 'ራስ መንገሻ ወልዱ ላፄ ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ' ይሉ እንደ ነበር ግልጽ ነው ።

ነገር ግን ከመተማ ጦርነት ወዲህ የንጉሠ ነገሥቱን ሥልጣን የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ስለያዙ ፡ ምኒልክም የቀሩትን ባላንጦች እነ ደጃዝማች ሥዩም አባ ጉበዝን ወደ ጐን ትተው ፡ የትግሬን ግዛት በሙሉ ሰጥተዋቸው የበለጠም ለማቅረብ የእቴጌ ጣይቱን ወንድም የራስ ወሌን ልጅ ወይዘሮ ከፋይን ድረውላቸው ከሁለቱ ጋብቻ ወይዘሮ አስቴር ተወልደው ነበር ። የዐድዋንም ጦርነት መካፈላቸው ይታወሳል ። ዳሩ ግን ባንድ ወገን ያፄ ዮሐንስ ዙፋን ከእርሳቸው እጅ በመውጣቱ ቅር እያላቸው ፡ ደጋግመው የከዳት መልክ ስለአሳዩ በመጨረሻ ተይዘው አንኮበር በአዛዥ ወልደ ጻድቅ ጠባቂነት በግዞት እንዳሉ በ1898 ዓ.ም. ዐረፉ ።



## 5ኛ ራስ ቢቶደድ ገብረ ኪዳን

ራስ ቢቶደድ ገብረ ኪዳን ፡ ከወጣትነት ዠምሮ ብላታ ገብረ ኪዳን እየተባሉ ዐፄ ዮሐንስን ስላገለገሉ ፡ በመጨረሻም የእንደራሴነት ሥልጣን ይዘው ኖሩ ። ካፄ ተክለ ጊዮርጊስ ሞት በኋላም የንጉሠ ነገሥቱን ያፄ ዮሐንስን እኅት እቴጌ ድንቅነሽን አግብተው ደጃች ሥዩም አባ ጉበዝን ወልደዋል ። ዐፄ ዮሐንስ ወይዘሮት ዘውዲቱን ለልጃቸው ለራስ አርአያ ሚስትነት ለማጨት ሲወስኑ ፡ ወደ ንጉሥ ምኒልክ ዋና አማላጅ ሆነው የተላኩት ራስ ገብረ ኪዳን ናቸው ። በዚህም ምክንያት ከንጉሥ ምኒልክ ባለ ብር መጣብር ፈረስ ፡ ባለመርገፍ በቅሎ ፡ 8 ሌጣ ፈረስ ፡ የወርቅ ጋሻና ጥንድ ጦር ተሸልመዋል ። (ጸ. ት. ገ. ሥላሴ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ምዕ. 33)

## 6ኛ ራስ አሉላ አባ ነጋ ወደ ቁቢ

አሉላ የተምቤን ተወላጅ ናቸው ። በወጣትነታቸው ዘመን ፡ በዓልጋዳ አርአያ የተምቤንን አውራጃ በሚያስተዳድሩበት ጊዜ ፡ ለርሳቸው አድረው ልጃቸውን እምለሱን አግብተው ይኖሩ ነበር ። ቀጥሎ በበዓልጋዳ አርአያ ፈቃድ ወደ ደጃዝማች ካሳ (ዐፄ ዮሐንስ) ተዛውረው በአጋፋሪነት አገልግለዋል ። ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ካሳን አስገብራለሁ ብለው ወደ ዐድዋ ዘምተው በተዋጉበት ጊዜም ንጉሠ ነገሥቱን የማረኩ እርሳቸው ናቸው ይባላል ።

ከዚህ በኋላ ፡ ካሳ ዐፄ ዮሐንስ ተብለው በ1864 ዓ.ም. ከነገሡ ወዲህ ሊጋባ ተባሉ ። ቀጥሎም ራስ ተብለው የንጉሠ ነገሥቱ ጠቅላይ ጦር አዛዥ ፡ የሐማሴንና የዙሪያዋ ገዥ በነበሩበት ሰዓት ከግብጾችና ከሱዳኖች ፡ እንደዚሁም ከኢጣልያኖች ጋር ያደረጉት ጦርነትና ያገኙት ድል በየመጽሐፉ ተጽፏል ።

ከዶጋሊ ድል ወዲህ የእንግሊዞች ወቀሳና የኢጣልያኖች በጦርነት ማስፈራራት እየበዛ ፡ የራስ አሉላም ዝነኝነት እያየለ በሔደበት ሰዓት እርሳቸውን በከፋት የሚመለከቷቸው የመሳፍንቱ ጥላቻ ተጨማምሮ በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ የጦር ጠቅላይ አዛዥነቱ ሥልጣን ለራስ ኃይለ ማርያም ሐጐስ ተሰጠ ።

የመተማው ጦርነትም በንጉሠ ነገሥቱ የበላይነትና በራስ ኃይለ ማርያም አዝማችነት በተካሔደበት ጊዜ የኢትዮጵያ ጦር በደርቡሾች

አሸናፊነት ተፈጽሞ ንጉሠ ነገሥቱም ራስ ኃይለ ማርያም ስለሞቱ ያፄ ዮሐንስን እልጋ ከወረሱት ከራስ መንገሻ ጋር ጥቂት ጊዜ አን ገራግረው እንደቆዩ ፥ በ1882 ዓ.ም. ከራስ መንገሻ ፥ ከራስ ወልደሚካ ኤልና ከራስ ሐጐስ ጋር ወደ አዲስ አበባ መጥተው እነራስ መንገሻ ሲመለሱ አሉላ እዚሁ አዲስ አበባ መቆየት ይሻለኛል ብለው ቀሩ ። በኋላም የዓድዋ ጦርነት በተነሣ ጊዜ የአላጌንም ፥ የመቀሌንም የዐድ ዋንም ጦርነት ተካፍለዋል ። ከዚህ በኋላ የዐድዋን ግዛት ባፄ ምኒልክ ፈቃድ በራስ መንገሻ ስምምነት ተሹመው እንዳሉ በሽሬ ግዛት ከራስ ሐጎስ ጋር በ1889 ዓ.ም. በየካቲት ወር ተጣልተው ሲዋጉ ሁለቱ ታላላቅ መኳንንት በሚያሳዝን አኳኋን ሞቱ ።

በጠቅላላው በኢትዮጵያ ፥ በኢጣሊያኖች ፥ በግብጾችና እንደዚሁም በሱዳኖች ዘንድ እንደራስ አሉላ ስመጥር የሆነ የለም ። በኢትዮጵያም በትግሬ አሉላ ፥ በሸዋ ጐበና ፥ በጐጃም ደረሶ እየተባለ በቃለ አጋኖ ስማቸው ይጠራል ።

## 7ኛ ራስ ባርያው ጳውሎስ

በትግሬ ካፄ ቴዎድሮስ ዘመን ዠምሮ ታማኝና ስመ ጥር አገረ ገዥ ነበሩ ። ከታማኝነታቸውም የተነሣ ዐፄ ቴዎድሮስ በፊት ለደጃዝማች ምኒልክ ድረዋቸው የነበሩትን ልጃቸውን አልጣሽን ድረውላቸው ከዚህ ጋብቻ ደጃዝማች ገብረ መድኅን ተወልደዋል ። በሕይወት ያሉት ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ የራስ ባርያው የልጅ ልጅ ፥ የደጃዝማች ገብረ መድኅን ልጅ ናቸው ።

## 8ኛ ራስ ባርያው ገብረ ጻድቅ

ሌላው ያፄ ዮሐንስ ታማኝ ባለሟል ናቸው ። በታማኝነታቸ ውም ደብረ ሲና ላይ በዚያን ወቅት የደጃዝማችነት ማዕረግ ከነ በራቸው ከካሳ ጋር ተዋግተው በመሸነፍ ተማርከዋል ። ካሳ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ በኋላም በውጊያ ፥ "እንዴን ዐይኔን ለቴዎድሮስ መን ግሥት ገብሬያለሁ ፥ የተረፈውን ደግሞ ለርስዎ መንግሥት እሰጣ ለሁ" ብለዋል እየተባለ ይነገራል ። ከዚህም የተነሣ ባፄ ዮሐንስ ፈቃድ የራስነት ማዕረግ ይዘው ሐማሴንን ሲያስተዳድሩ ከግብጾች ጋር በተደረገው ጦርነት ብዙ ሞያ እንደ ሠሩ ይነገራል ። በመጨረሻ ከራስ ወልደ ሚካኤል ጋር ሲዋጉ ሞቱ ።



## 9ኛ ራስ ሐጎስ

ከዐፄ ዮሐንስ ታላላቅ መኳንንት አንዱ ራስ ሐጐስ ናቸው ። ቀደም ብለው በደጃዝማችነት ማዕረግ ተምቤንን ሲያስተዳድሩ ቆይተው በመጨረሻ ራስ ተብለው ሽሬን ሲገዙ በዚሁ ማዕረግ እንዳሉ ፥ በ1881 ዓ.ም. በንጉሠ ነገሥቱ ባፄ ዮሐንስ የተመራውን የመተማን ጦርነት ፥ ቀጥሎም በ1887 የተደረገውን የዐድዋን ጦርነት ተካፍለ ዋል ።

ራስ መንገሻ በ1887 አ.አበባ የመጡ ጊዜ አብረው መጥተው እንደ ሌሎቹ ተሸልመዋል ። በመጨረሻ በ1889 ዓ ም. በየካቲት ወር በግዛት ግጭት ከራስ አሉላ ጋር ሲዋጉ ሕይወታቸው ዐለፈ ።

## 10ኛ ራስ ገብረ መድኅን ኃይለ ማርያም

ኃይለ ማርያም የደጃዝማች ወብ ወንድም የሰሜን አገረ ገዥ ነበሩ ።

## 11ኛ ደጃጅ መሸሻ

## የዐፄ ዮሐንስ ወንድም የደጃች ማሩ ልጅ

## 12ኛ ቢትወደድ ገብረ መስቀል

ሌላው ባፄ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት ከነበሩት ታላላቅ መኳንንት አንዱ ቢትወደድ ገብረ መስቀል ናቸው ። የዐድዋ ገዥ ስለነበሩ ፥ ራስ አሉላ የሐማሴን ገዥ በነበሩበት ጊዜ እንግዶች በምጥዋ በኩል ሲመጡ እርሳቸው ከራስ አሉላ እየተቀበሉ ንጉሠ ነገሥቱ ወደሚገኙበት ወደ መቀሌ ወይም ወደ ደብረ ታቦር ይልኩ ነበር ። በመጨረሻም በዚሁ በታማኝነታቸው እንዳሉ በመተማ ተዋግተው ሞቱ ።

## 13ኛ ደጃዝማች ቦጋለ

የትልቁ ራስ አርአያ ልጅ የመተማን ጦርነት ተካፍለዋል ።

## 14ኛ ዋግሹም ገብሩ

የጎንደርታ ተወላጅ ቀደም ብሎ ሐማሴንና ሠራዬን ሲያስተዳድሩ ቆይተው በመጨረሻ ዋግሹም ተብለው ላስታን ተሾሙ ።

## 15ኛ በጅሮንድ ለውጤ

እንደ ሌሎችም ስለኝህ መኰንን ብዙ የምናውቀው ነገር የለም ። ንጉሥ ምኒልክ ዐፄ ዮሐንስ አልገብርም ብለው ባፈነገጡበት ሰዓት ሁለቱን ለማስማማት ከሸዋ እና ደጃች ናደው ሲመደቡ ፤ ከዔ ዮሐንስ በኩል ወደ ንጉሥ ምኒልክ ተልከው የመጡት በጅሮንድ ለውጤ እን ደነበሩ ሰነዱ ሁሉ ያመለክታል ። በጅሮንድ መላካቸው ምናልባት የገንዘብና የንብረት ኃላፊ ሆነው በማስተዳደራቸው ይሆናል ።

## 16ኛ ደጃዝማች ኃይሉ ወልደ ሚካኤል

ደጃዝማች ኃይሉ ወልደ ሚካኤል ፤ ደጃዝማችነታቸው ባዔ ቴዎድ ሮስ ነው ። በመቅደላም ታስረው ነበር ። ከዚያም በእንግሊዞች ነጻ ወጥተው ለዐፄ ዮሐንስ በመታመን ሐራማትን ተሾመዋል ።

## 17ኛ ሊቀ መኳስ ይልማ ደስታ

ይልማ ደስታ ፤ ያዔ ዮሐንስ የቅርብ ዘመድና ታማኝ መኰንን ናቸው ። እንደሚታወሰው ፤ የእንግሊዝ ጦር ዐፄ ቴዎድሮስን ለመ ውጋት በመጣበት ጊዜ ከደጃዝማች ካሳ (በኋላ ዐፄ ዮሐንስ) ተል ከው በሰናዓፌ እንግዶቹን ተቀብለው አስተናግደዋል ።

## 18ኛ ሳሙኤል ጊዮርጊስ ርዕሰ መማክርት

ሳሙኤል የሰናፌ ተወላጅ ፤ በፊት የዐፄ ቴዎድሮስ ታዛዥ ሆነው በእንግሊዞችና ባዔ ቴዎድሮስ ፤ እንደዚሁም በእስረኞችና በንጉሠ ነገሥቱ መካከል ሆነው በመላላክ ብዙ ሚና መጫወታቸው ፤ የእን ግሊዝኛ ቋንቋ ማወቃቸው ይታወሳል ።

አሁንም ላዔ ዮሐንስ አድረው የፈረንጅ አስተናጋጅ በመሆን ወደ እንግሊዝ ንግሥት ወደ ቪክቶሪያ በመላክ አገልግለዋቸዋል ። ዐፄ ዮሐንስ በሚልኩት ደብዳቤ ላይ ሳሙኤልን ርዕሰ መማክርት ብለዋቸዋል ። ምናልባትም ሳሙኤል ባዔ ቴዎድሮስ ዘመን በንጉሠ ነገሥቱና በእንግሊዞቹ መካከል የተነሣውን የጠብና የክርክር ውዝ ግብ ፤ በእስረኞቹ ምክንያትም የደረሰውን እልቂትና የንጉሠ ነገሥቱን ሞት ያይን ምስክር የሆኑበትን እያስረዱ ላዔ ዮሐንስ ዋና ተደማጭ አማካሪ ሆነው አገልግለው ይሆናል ።



## ዋቢ መጻሕፍት

(ከገር ውስጥ)


መንግሥቱ ለማ ፤
መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ። አዲስ አበባ ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ. ማ/ቤት ፤ 1959 ።

ተክለ ሥላሴ ዋቅጅራ (አለቃ)
(ያልታተመ)

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ፤
የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ። 4ኛ መጽሐፍ፤ አዲስ አበባ ፤ መርሐ ጥበብ ማ/ቤት 1938 ።

የኢትዮጵያ ታሪክ
ከዔ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ (5ኛ እትም) ። አዲስ አበባ ፤ ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት ፤ 1965 ።

ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል
3ኛ መጽሐፍ። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ. ማ/ቤት 1966 ።

የግራኝ መሐመድ ወረራ
አ.አ ፤ ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት ፤ 1966 ።

ኅሩይ ወልደሥላሴ (ብላቴን ጌታ)
ኢትዮጵያ መተማ—የዐፄ ዮሐንስ ታሪክ ። አዲስ አበባ ፤ ኢት ዮጵያ ማ/ቤት ፤ 1910 ።

የሕይወት ታሪክ
አዲስ አበባ ፤ ራስ ተፈሪ ማ/ቤት ፤ 1915 ። ዋዜማ ፤ ጎሐ ጽባሀ ማ/ቤት ፤1921 ።

የኢትዮጵያ ታሪክ
ከንግሥተ ሳባ እስከ ዓድዋ ጦርነት (ያልታተመ)

አድማሱ ጀንበሬ
(መልአ ከብርሃን)፥ መጽሐፈ ቅኔ። አዲስ አበባ፥ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት ፥1963 ።

አጥሜ
(አጽመ ጊዮርጊስ)፥ የጋላ ታሪክ (ያልታተመ)

አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ፥ (ነጋድራስ)
ዳግማዊ ምኒልክ ፥ ሮማ ፥1901 ።

እምሩ ኃይለሥላሴ (ልዑል ራስ)
(ያልታተመ)

ገብረ ሥላሴ ወ/አረጋይ (ጸሐፌ ትእዛዝ)
ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፥ አዲስ አበባ ፥ አርቲስቲክ ማ/ቤት ፥ 1959 ።



## ዋቢ መጻሕፍት (እንግሊዝኛ)

Anchieri, E., **Storia della Politica Inglese Nel Sudan (1882—1939)** Milano: Fratelli Bocca, 1939.

Bardi, P.M., **Pionieri E. Soldati**, Milano: Ulrico Hopli,1936.

Battaglia, R., **La guerra d'Africa.** Torino: Giulion Einaudi editore, 1958.

Bellarita, E., . . .**Adua I Precedenti**, Genova: "Rivista di Roma", editrice, 1931.

Canestrini, A.S., **I Prigionieri del Mahdi**, Roberato, La cassa Scolastico del R. Istituto, 1939.

Chaine, M., **Histoire du Regne de Yoahnnes IV Roi d, Ehtiopie**, Paris: Ernest Leroux, 1943.

Coppet, De M., **Chronique du Regne de Menelik II**, Paris: Maisonnevve, Freres, 1930.

Cortese, G., **Eritrea**, Roma: Cassa Editrice, 1934.

Coulbeaux, J.B., **Histoire Politique et Religiense d' Abyssinie**, Paris: Geuthner, 1929.

Coursac, De J., **Le Regne de Yohannes**, Rommans, Imprimerie Jeanne D'Arc. 1926.

Crispi, F., **Le Prima Guerra d'Africa**, Milano : Fratelli Trever, 1914.

Dei Sabelli, L., **Storia di Abyssinia**, Roma: Edizon Roma, 1938.

Del Boca, A., **Gli Italiani in Africa Orientale,** Roma: Bari, Giuslateria & Figlispa, 1979.

Douin,G., **Histoire du Regne Kedive Ismael, Tome III, 2e Partie, 1869-1873,** Caire: pour La Societe Royale De Geographie del, Egypte, 1939.

Guidi,I., **Annales Rogum Iyasu II et Iyoas,** Louvain: Secritariat Du Corpusco, 1962.

Marcus.H,G., **The Life and Times of Menelik II,**Oxford : Clarendon press, 1975.

Markham, **A History of the Abysinian Expedition,** London: Macmillan and Co, 1869.

Matteucci,P., **In Abyssinia,** Milano: Fratelli Trever, Editori, 1880.

Mazzucconi,R., **Storia dela Conquista deila Africa,V-II,** Milano: Instituto per gli studi di politic Internationale,1929.

Pacha,J.C., **Coup d' Oeil sur la Chronologie de la Nation Egyqtienne, Paris: Plon, 1931.**

Petrides, S.P., **Le Livre d'Or de la Dynastie Salomonienne d,Ethiopie,** France: Plon, 1964.

Portal,G.H., **My Mission to Abyssinie,** New York: Negro Universities Press ,1969.

Raffray,A,. **Afrique Orientale Abyssinie,** Paris:1876.

Rassam.H., **Narrative of the British Mission to Theodore King of Abyssinia,**Vol. II,London: Johon Murray, 1869.



Rosenfeld,C.P., **A Chronology of Menelik II of Ethiopia** (1844-1913), U.S.A., Michigan State University,1976.

Rossetti,C., **Storia Diplomatica** dell, **Etiopia Durante il Regno di Menelik II,** Torino.: Societa Topografico editrice nazionale, 1910.

Rossini,C., **La Cronaca Reale Abyssina,** Roma:Rediconti della Accadamia dei Lencei, 1916.

**Italia ed Etiopia-Alla Battaglia di Adua,** Italia Istituto per l'Ori iente ,1935.

Rosso,M., **L'Italia in Africa Serie Storica,** Vo.I, Roma: Istituto Poligrafico dello Stato P.V., 1958.

Rubenson,S., **The Survival of Ethioplan Independence,** Great Britain, Richard Clay (The Chaucer Press Ltd,) 1976.

Salimbeni,A., **Crispi e, Meneliek nel Dlario,** Torino: Industria Libraria topografico editrice, 1956.

Sapeto,G., **Viaggio ai Mensa, ai Bogos e, Agli Habat,** Milano, Istitato per gli Studi di Politica Internazionale, 1941:

Smith, F. H., **Through Abyssinia,**New York: A.C. Armstrong & Son, 1980

Bairu Tafla, **A Chronicle of Emperor Yohannes IV** (1872-89), Wiessoden: Franzsteiner Verlag GMBH, 1977.

Wylde,A.B., **Modern Abyssinia,** London: Methurn x Co., 1901.

## SOURCES FOR UNPUBLISHED MATERIALS

1. Archives Nationales - Ministere d' Outre mer Francaise - Paris.

2. Archivio Storico del Sopprosse Ministero Africa Italiania - Roma.

3. Biblioteca Nazionale - Roma.

4. Biblioteca Vaticana - Roma.

5. Indian Office - London.

6. Instituto Italiano per l'Africa - Roma.

7. Ministero degli Affari Esteri, Comitato per la Documentazione dell' Attivita Italiana in Africa - Roma

   «L,Italia in Africa ...Vol primo Ethiopia Mare Rosso, Tomo VI, Documentsi (1887-1888) e VII Doumeenti (1888-18889) -cura di Carlo Giglio.

8. Ministere des Affaires Etrangeres - Memoires et Documents Afrique (M.D.) - Paris.

9 «The Process of the Reunification of the Ethiopian Empire» (Thesis)- Zewde Gebre Selassie.

10. Public Record Office - London.